አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የትምህርትና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ

አማርኛ ቋንቋ ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# ባህልና ልማት በዋግኽምራ ብሔረሰብ

በ

አያሌው አስፋው መሸሻ

2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ባህልና ልማት በዋግኽምራ ብሔረሰብ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የትምህርትና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ

አማርኛ ቋንቋ ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በፎክሎር ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

አያሌው አስፋው መሸሻ

አማካሪዎች

የወንድወሰን አውላቸው (ዶክተር)

መሀመድ አሊ (ዶክተር)



2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማረጋገጫ (Declaration)

**ባህልና ልማት በዋግኽምራ ብሔረሰብ** በሚል ርዕስ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የትምህርትና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል በፎክሎር ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሠራ የራሴ ወጥ ሥራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ዋቢ መረጃዎችም በትክክል ዋቢ የሆኑ ናቸው፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡ አያሌው አስፋው መሸሻ

ፊርማ:_____________

ቀን:_______________

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የትምህርትና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ

## አማርኛ ቋንቋ ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

**ባህልና ልማት በዋግኽምራ ብሔረሰብ** በሚል ርዕስ በፎክሎር ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ በአያሌው አስፋው መሸሻ በመጋቢት 2018 ዓ.ም የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርስቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

### የፈታኝ ቦርድ አባላት

አማካሪ -1፡- <u>የወንድወሰን አውላቸው (ዶክተር)</u> ፊርማ: ___________________

አማካሪ -2፡- <u>መሀመድ አሊ (ዶክተር)</u> ፊርማ: ___________________

የውጭ ፈታኝ፡- <u>ጄይላን ወሊይ (ፕሮፌሰር)</u> ፊርማ: ___________________

የውስጥ ፈታኝ፡- <u>ፍሌ ጃለታ (ተ/ፕሮፌሰር)</u> ፊርማ: ___________________

# ምስጋና

በድካሜ ኃይል እየሆነ ለረዳኝና እዚህ ላደረሰኝ አምላኬ እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ ክብርና ምስጋና ይገባዋል፡፡

ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ጥናቱን በተደጋጋሚ በማረምና በማስተካከል ልዩ ልዩ ጠቃሚ መረጃዎችንና መጻሕፍት በማዋስ ተግቼ እንድሰራ ያልተቆጠበ ምክርና እገዛቸው ላልተለየኝ አማካሪዎቼ ዶክተር የወንድወሰን አውላቸው እና ዶክተር መሀመድ አሊ ከታላቅ አክብሮት ጋር ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

ትምህርቱን እከታተል ዘንድ ለፈቀደልኝና ጥናቱን ለማድረግ ለአበረታታኝ የወልዲያ ዩኒቨርስቲ ምስጋና ይገባዋል፡፡

የዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ጥናቱ በተገቢው ሁኔታ እንዲሰራ ላሳደረው ፍላጎትና ሥራዬን ካለ ችግር እንድወጣ ከፍተኛ አቅም ፈጥሮልኛልና ከልብ አመሰግናሁ፡፡ በተለይ የብሔረሰቡ የባህልና ቱሪዝም ባለሙያ ባየ አስመሮም የጥናቱን ጠቀሜታ በመረዳትና እንደራሳቸው ሥራ በመቁጠር ላደረጉልኝ ቅንነት የተሞላበት እርዳታ ፣ ድጋፍና ማበረታታት ሳመሰግናቸው ከልብ ነው፡፡

የብሔረሰቡ መስተዳድር የጤና ፣ የግብርና ፣ የባህልና ቱሪዝም መምሪያዎች ለሰቆጣ ከተማ መስተዳድር ፣ ለሰቆጣ ዙሪያ ወረዳ ፣ ለአበርጌሌ ወረዳ ፣ ለደሃና ወረዳ ፣ ለዝቋላ ወረዳ ፣ ለስሃላ ሰለምት ወረዳ እና ለጋዝጊብላ ወረዳ አስተዳደሮች መረጃ በምሰበስብበት ጊዜ ላደረጉልኝ ትብብር ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

መምህርት ወርቃፈራሁ ቸኮል የጥናቱ መረጃ ስብሰባ ከተጀመረ ጀምሮ ከጎኔ ሳትለይ ከቦታ ቦታ በመዘዋወር መረጃ ሰጪዎችን ፈልጎ በማግኘት ፣ መረጃ በመስጠት ፣ ግልፅ ያልሆኑ የአካባቢውን ባህላዊ አገላለጽ በመተርጎም ፣ የሚበላና የሚጠጣ በማዘጋጀትና የመጠለያ ቤት በመስጠትና በማኖር ፣ ለስራዬ ስኬት ምክርና አስተያየትሽን በመለገስ ላደረግሽልኝ ድጋፍ ከልብ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረስሽ፡፡

አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ወ/ሮ ሙቀት ወንዴ ፣ አባ አሸብር አለሜ ፣ አቶ ደሳለኝ ታደለ ፣ ወ/ሮ ማንጠግቦሽ አየለ ፣ አርሶ አደር እሸቱ አበራ በየነ የሚያስፈልገኝን ሁሉ

በማሟላት ፣ አብራችሁኝ በመንከራተት መንገድ በመምራትና ከሰው ጋር በማስተዋወቅ ለሰጣችሁኝ በዋጋ የማይተመን ፍቅር እና እንክብካቤ ምስጋናዬ ያንስባቸዋል፡፡

በአካባቢያችሁ ተገኝቼ ሥራዬን እንድሠራ አምናችሁኝ እንደራሳችሁ አድርጋችሁ ከልብ ተቀብላችሁኝ የምፈልገውን መረጃ ካለስስትና ጥርጣሬ የሰጣችሁኝ በአባሪነት ስማችሁን ያያያዝኩት መረጃ ሰጪዎችና ሌሎች የብሔረሰቡ አባሎች በሙሉ ደግነታችሁ ወሰን የለውምና ምስጋናዬን ተቀበሉ፡፡ በናንተው ጣፋጭ አባባል "ማርያምን!" ስማችሁን ልዘርዝር ብል ሰው መለየት ይሆንብኛል ፣ ሁላችሁም ውስጤ ናችሁ ፤ ገራገርነታችሁን ፣ ሰው አማኝነታችሁንና መልካምነታችሁን አውግቼ አልጠግብም፡፡ ውድ ባለቤቴ አሰገደች ንጉሤ ለኔ ከዚህ ደረጃ መድረስ የከፈልሽው መስዋዕትነት አቅም ሁነሽኛልና ድካምሽ ፍሬ አፍርቶ ለውጤት ስላበቃሽን እነሆ ገፀበረከትሽ፡፡ የአንቺ እገዛ ፣ አይዞህ በርታ የሚሉት የማጠናከሪያ ድምጾሽ አቅም ባይሆነኝ ኖሮ ለዚህ አልበቃም ነበር ፤ ምስጋናየ ጥልቅ ነው ፤ እግዚአብሔር ጤንነቱን ይስጥሽ በማለት ከልብ እመኛለሁ፡፡ ውድ የአብራኮቼ ክፋይ ልጆቼ ሳባ ፣ ኤደን ፣ ዳንኤልና ፅንሰወርቅ አያሌው በሁኔታዎች ሁሉ እየተረዳችሁኝና እየተገነዘባችሁኝ ፍላጎታችሁን ሁሉ ወደ ጎን ብላችሁ የኔን ክፍተት ሞልታችሁ አባታችሁ እንድበረታ አግዛችሁኛልና ልዑል እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡፡

ጥናቱ ይህንን ቅርፅ ይዞ እንዲወጣ ሙሉ ጊዜዉን ሰጥቶ ይዘቱን በማስተካከል ፣ የኮምፒዉተር ስራዉን በጥንቃቄ በማረም ፣ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ከፍተኛ እገዛና በንቃት እና በትጋት አይዞህ እያለ ያለመሰልቸት የአገባብ እና የፊደል ስህተቶችን ሳይቀር የሰራልኝን ጥንቁቁ ልጄ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የአካዉንቲንግና ፋይናንስ ትምህርት ክፍል መምህር የሆነዉ ዶ/ር ሀይምሮ ልንገርህ እጅግ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን ከልብ አቀርባለሁ ፤ ያለእሱ እርዳታ ይህ ጥናት በዚህ መልኩ ሊቀርብ አይችልም ነበርና ፈጣሪ በሁሉም ሁኔታ ለትልቅ ደረጃ ያብቃህ እያልኩ በድጋሚ ምስጋናዬን ከልብ እገልፃለሁ፡፡

**ማውጫ**


ማረጋገጫ (Declaration) ........ iii

ምስጋና ........ v

የኢትዮጵያ ካርታ ........ xiii

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስተዳደር ካርታ...Error! Bookmark not defined.

የዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ካርታ ........ xv

አጠቃሎ /Abstract/ ........ xvii

**ምዕራፍ አንድ ........ 1**

**1. መግቢያ ........ 1**

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 3

1.2. የጥናቱ አካባቢ እና የብሔረሰቡ የዘር ሐረግ ታሪካዊ ዳራ ........ 8

1.2.1.የዋግኽምራ ብሔረሰብ አጠቃላይ ገፅታ ........ 8

1.2.2. የብሔረሰቡ ታሪካዊ ዳራ ........ 12

1.3. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 19

1.4.1 የጥናቱ ዋነኛ አላማ ........ 22

1.4.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 22

1.5. የጥናቱ ጥያቄዎች ........ 22

1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 23

1.7. የጥናት አካባቢው መረጣና የጥናቱ ገደብ ........ 24

1.8.የመስክ ገጠመኝ ........ 25

1.8.1.ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎች ........ 26

1.8.2. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........ 27

1.9. የጥናቱ ስነ-ምግባር ........ 30

**ምዕራፍ ሁለት ........ 32**

**2. ክለሳ ድርሳን ........ 32**

2.1. የተዛማች ጥናቶች ቅኝት ........ 32

2.2. የፅንስ ሃሳብ ማዕቀፎች ........ 36

2.2.1. የባህል ፅንሰ ሀሳብ ........ 36

2.2.2. የልማት ፅንሰ ሀሳብ ........ 41

2.2.3. የባህልና የልማት ትስስር ....................................................................................... 45
2.2.4. ግብርና ኤክስቴንሽን........................................................................................... 50
2.2.5. ጤና ኤክስቴንሽን ............................................................................................. 51
2.3. ንድፈ ሃሳባዊ መሠረቶች ....................................................................................... 53
**ምዕራፍ ሶስት ................................................................................. 68**
**3.የጥናቱ የአሰራር ዘዴ ......................................................................... 68**
3.1. የጥናቱ ንድፍ ...................................................................................................... 68
3.2. የጥናቱ አቀራረብ................................................................................................... 68
3.3. ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች የተሰበሰቡበት አውድ ........................................... 69
3.3.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች............................................................................. 71
3.3.1.1 ምልከታ.............................................................................................................. 71
3.3.1.2. ቃለ መጠይቅ ...................................................................................................... 73
3.3.1.3. ቡድን ተኮር ውይይት .......................................................................................... 74
3.3.2. የመቅረጫ መሣሪያዎች አጠቃቀም ........................................................................ 75
3.4 የመስክ ጉዞ............................................................................................................. 76
3.5 የጥናቱ አካሄድና አተናተን ዘዴዎች … … . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ..59
**ምዕራፍ አራት ..........................................................................79**
**4.የዋግኽምራ ብሔረሰብ ዋና ዋና ባህላዊ ገፅታዎች ................................ 79**
4.1. ቁሳዊ ባህል.............................................................................................................. 79
4.1.1. አለባበስና አጊያጊያጥ ............................................................................................. 79
4.1.2. የምግብ አሠራርና አመጋገብ..................................................................................... 84
4.1.3 የእደ ጥበብ ዕውቀቶች ........................................................................................... 87
4.1.4. የቤት አሠራር ....................................................................................................... 105
4.2 ሀገረ ሰባዊ ልማዶች ................................................................................................ 109
4.2.1. ደቦ /ወበራ/ ............................................................................................................ 109
4.2.2. በቁም የመረዳዳት ባህል/እርጥባን ........................................................................... 110
4.2.3 የጋብቻ ጥያቄ እና የማጨት ሂደት ........................................................................... 111
4.2.3.1. እርግዝናና ልደት................................................................................................ 138
4.2.3.2 አራስን መጠየቅ ፣ ግርዛት እና የስም አወጣጥ ....................................................... 142

4.2.4 ሞትና የሀዘን ስርዓት ........................................................................ 146
4.2.4.1. ብሔረሰቡ ስለሞት ያለው እይታ ........................................................ 146
4.2.4.2. የቀብርና የሀዘን ሥርዓት ............................................................ 147
4.2.5 ክብረ በዓላት ............................................................................ 158
4.2.5.1 ሻደይ ............................................................................ 158
4.2.5.2 ዋርዳ ሆዬ ........................................................................ 163
4.2.5.3 በዓላዊ ዘፈኖችና ውዝዋዜዎች ........................................................ 166
4.2.5.4. የሥራ ላይ ዘፈኖች ................................................................ 173
4.3. ሀገረሰባዊ እምነቶችና መድሀኒቶች ................................................... 180
4.4. ሥነ-ቃላዊ መገለጫዎች ............................................................ 183
4.4.1. ቃል ግጥም ........................................................................ 184
4.4.2 ምሳሌያዊ አነጋገሮች ................................................................ 187
4.4.3. እንቆቅልሽ ጨዋታ ................................................................ 188
4.4.4 በትረካ መልኩ የሚቀርቡ ............................................................ 191
4.4.5 ምርቃትና እርግማን ................................................................ 193
4.5. ሀገረ ሰባዊ የዕውቀት ትግበራ ....................................................... 197
4.5.2 የእርሻ ዕውቀት .................................................................... 199
4.5.3 የሙዚቃ መሳሪያዎች ስራ ........................................................... 203
4.5.4 የብረታብረት ስራ ................................................................ 206
**ምዕራፍ አምስት** ............................................................................ 211
5. የብሔረሰቡን ልማት ለማፋጠን ያለው አዎንታዊ ባህላዊ/ፎክሎራዊ ገፅታዎች ............................................................................ 211
5.1. የዋግኽምራ ብሔረሰብ ሁለንተናዊ የጋራ ሕይወትና አኗኗር ................... 211
5.2 ግጭቶችን በጋራ መፍታት ........................................................... 215
5.3. ሀቀኝነት ፣ ግልፀኝነትና ያልተገባ ጥቅምን አለመፈለግ ............................ 219
5.4 የዘመዳሞችና ጎረቤታሞች የጋራ ትብብሮች ........................................ 227
5.4.1. የደቦ ስራ (ወበራ) ................................................................ 228
5.4.2 የሰርግ መዋጮ .................................................................... 230
5.4.3 እርጥባን ........................................................................ 230
5.5. በመንደር ተሰባስበው መኖራቸው ያበረከተው በጎ ገፅታ ................................ 233

**ምዕራፍ ስድስት ............................................................................ 238**

**6. የአካባቢውን ልማት የሚያስተጓጉሉ አሉታዊ ባህላዊ ጉዳዮች ........... 238**

6.1. የግብርና ልማት እና የዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህላዊ ተግዳሮቶች ...................... 238

6.1.1. ምርትና ምርታማነትን አለማሳደግ ...................................................... 238

6.1.2. ሰፊ ጊዜውን በእርሻ ስራ ላይ አለመገኘት እና ለትርፋማነት አለመጨነቅ ............... 243

6.1.3. የስንፍና ችግር ወይስ ባህሉን አለመገንዘብ ................................................ 245

6.2. የጤና ኤክስቴንሽንና የዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህል/ልማዶች ............................. 255

6.2.1. ባህላዊ/ልማዳዊ ህክምና ............................................................... 255

**ምዕራፍ ሰባት ............................................................................ 277**

**7. ማጠቃለያና ይሁንታ ...................................................................... 277**

7.1 ማጠቃለያ ........................................................................................ 277

7.2. ይሁንታ /Recommendation/ ................................................................ 281

ዋቢ ሰነዶች ....................................................................................... 286

# የምስሎች ዝርዝር



| ምስል | ገፅ |
|---|---|
| 1፡- ፀጉራቸውን ቁንጮ የተላጨና ኪታ የለበሱ ልጆች / ኳርቶ የለበሰ ወጣት | 61 |
| 2፡- ጋሜና ቁንጮ/ሁለት ዙር ጋሜና ቁንጮ | 62 |
| 3፡-ቃንጃ መትር የለበሰች የብሔረሰቡ ሴት | 64 |
| 4፡- የብሔረሰቡ ሴቶች ባህላዊ አለባበስ | 64 |
| 5፡- የብሔረሰቡ ባህላዊ የምግብ አቀራረብ | 66 |
| 6፡- የብራና መጽሐፍ ባለሙያው በስራ ላይ | 70 |
| 7፡- አንቀልባ | 72 |
| 8፡- የጌጣጌጥ ባለሙያው እና የጌጣጌጥ አይነቶች | 74 |
| 9፡- የብሄረሰቡ የክሸላ ድስት ዓይነት | 77 |
| 10፡- በውበት ያጌጠ የቅል ስራ (ለወተት እና ለቅቤ ማስቀመጫነት የሚውል) | 80 |
| 11፡- የስፌት ስራ ዓይነቶች | 81 |
| 12፡- ህድሞ /ጽራ/ ቤት | 82 |
| 13፡- የስሬን ቀበሌ ከፊል ገፅታ | 84 |
| 14፡- የድንጋይ ግንብ (ናስ ቤት) | 84 |
| 15፡- ማርዳ የለበሰች የታጨች ልጅ (ፎቶ የፀመራ ልጅ) | 95 |
| 16፡- የአውራጅ ምግብ አቀራረብ | 102 |
| 17፡- አዋጅ ነጋሪ ገንዘብ ሲሰብስብ (ፎቶ ዋግኽምራ ዞን ባቱ) | 104 |
| 18፡- ወጥ ከተሰራባቸው የሸክላ ድስቶች በከፊል/ወንዶች ወጥ ሲሰሩ | 105 |
| 19፡- ዳስ ውስጥ የወንዶች አቀማመጥ በፎሌ/በሽክና ኮረፌ እየጠጡ | 106 |
| 20፡- ሴቶች ሲመገቡ በከፊል | 107 |
| 21፡-ለሽማግሌዎች የቀረበ ዝልዝል ፍሪምባ | 108 |
| 22፡- ልጆች ሲመገቡ በከፊል | 108 |
| 23፡- የማርገጃ ቦታ ለቅሶ ሲካሄድ | 118 |
| 24፡- ስንብትን በከፊል የሚያሳይ | 121 |
| 25፡- ለአኅበር የመጣው እንጀራ ከርክክብ በፊት | 122 |
| 26፡- የአኅበር እንጀራ ርክክብ | 123 |

| ምስል | ገፅ |
|---|---|
| 27፡- ወንዶች ሲመገቡ በከፊል/ሴቶች ሲመገቡ በከፊል | 124 |
| 28፡- የዐዋቂዎች የሻደይ ጭፈራ/የወጣቶች የሻደይ ጭፈራ | 127 |
| 30፡-የጨዋታዉ አጀማመር ሂደት | 130 |
| 31፡- ባህላዊ ውዝዋዜ | 137 |
| 32፡- ለፎረፎር መድሃኒትነት የሚያገለግለው ግሸ ዛፍ | 145 |
| 33፡- የግብርና መሳሪያዎች | 162 |
| 34፡- ዋሽንቶች እና ማሲንቆ | 164 |
| 35፡- ቀልጦ ብረት የሚሆነው አጭነ ድንጋይ/የብረታብረት ባለሙያዎች በስራ ላይ | 165 |


# የኢትዮጵያ ካርታ




## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስተዳደር ካርታ


N.Gondar
Wag Hemra
N.Wello
S.Gondar
W.Gojam
Agew Awi
East Gojam
S.Wello
N.Shewa
Oromia
Lake Tana
Metema
Quara
Alefa
Chilga
Dembia
Debark
Sekota
Zikuala
Dehana
Kobo
Meket
Habru
Bati
Kalu
Fogera
Farta
Dera
Este
Simada
Achefer
Merawi
Adet
Kuant
Dangela
Banja
Guangua
Ankesha
Bure Wemberma
Guzamn
Awabel
Dejen
Baso Liben
Debresina
Legambo
Sayint
Mekdela
Kutaber
Tenta
Ambasel
Kelala
Jama
Wegde
Kewot
0 35 70 140 210 280 Km

# የዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ካርታ




ምንጭ፦ ኅግል ማፕ 2018 ዓ.ም

# የቃላት መፍቻ

| የአካባቢው ቃል | ፍች |
|---|---|
| ህድሞ | ክብ ፎቅ ቤት |
| ላስታ ቅቤ | የፀጉር ቅቤ |
| መወቀር | መነቀስ |
| ማርገጃ ቦታ | የለቅሶ ሥርዓት የሚከናወንበት ሜዳ |
| ማዘያ | አንቀልባ |
| ቁርንጮ | ከቆዳ የተሰራ፣ ለመቀመጫነት ለመመገቢያነት የሚያለግል |
| ቃንጃ መትር መቀነት | ዋጋው ውድ የሆነ የተለያየ ቀለም ባላቸው ክር የተዋበ በሰፊ ጥለት ያለው መቀነት |
| ቆለምሸሸ | ከሣር የተስፋች የቆሎ ማቅረቢያ |
| የላይትላይ | የመንፈስ ስቃይ፣ ህመም፣ የሚያስጎራ፣ የሚያጠራራ |
| አስጨንግፍ | የማያሳድግ በሽጋ/ሾተላይ/ |
| መሸከክ | መጠየፍ፣ በቅሬታ ወይም በጥላቻ መመልከት/ የስሜት መለዋወጥ |
| አይጠረቃ | አይወፍር፣ አያምር፣ ሰውነት አለማስገባት |
| ምጥቻ | የሦሶ ዶሮ፣ የተመረጠ ዶሮ/በግ፣ ፍየል ወዘተ/ በሰውነት ላይ አዞሮ መጣል፡፡ ከዚያም በቤት ውስጥ እንደጠባቂ አምላክ ተቆጥሮ ይቀመጣል፡፧ አይታረድም ተቀማጭ ነው፡፡ |
| ጨንገር | በባህላዊ አምልኮው መስፈርት የተመረጠ የፍየል ወጠጠየ ተቀማጭ |
| መከተሪያ | የልብስ ቁልፍ |
| መጎጫሜ | ደረጃ |
| ፎሌ | ከቅል የሚሰራ ለዉሃና ለጠላ መጠጫነት የሚያገለግል ቁስ |

# አጠቃሎ /Abstract/

*የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ስር ከሚገኙት ብሔረሰቦች መካከል የዋግኽምራን ብሔረሰብ ባህል/ፎክሎር በማጥናት በሀገር አቀፍ ደረጃ በመንግሥት ታቅደው እንዲተገበሩ የሚሰራጩ የልማት ዕቅዶችን ለመተግበር የብሔረሰቡ ባህል/ፎክሎር ለአካባቢው ልማትም ሆነ "በልማት ወደኋላ መቅረት" ያደረገው አስተዋጽኦ ወይም ተግዳሮት ይኖር እንደሆነ መመርመርና ባህላዊ ገፅታዎችን የልማት መሣሪያ በማድረግ የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን የሚቻልበትን መንገድ ተንትኖ ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ (Qualitative) የአጠናን ዘዴን ተከትሎ የተደረገ ሆኖ ተንታኝ (Interpretative) የአጠናን ስልትን የሚከተል ነው፡፡ በጥናቱ የዋግኽምራ ብሔረሰብ በሚኖርበት ሰባት ወረዳዎች በቃለ መጠይቅ ፣ በተሳትፏዊ ምልከታና በተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡ በመስክ ቆይታው እንዲጋጠመው ምቹ ሁኔታም በየወረዳዎቹ በሚገኙ የተለያዩ ቀበሌዎች የተለያየ ቁጥር ያላቸው 31 ሴቶችና 56 ወንዶች በጠቅላላው 87 ሰዎች መረጃ በመስጠት ተሳትፈዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ 16 ሴቶችና 29 ወንዶች በድምሩ 45 ሰዎች በቃለ መጠይቅ የተሳተፉ ሲሆን ባህሉን በሚገባ የሚያውቁ ስድስት ወንዶችና አራት ሴቶችን ያጠቃልላል፡፡ በጥናቱ የዋግኽምራ ብሔረሰብ የማንነቱ መገለጫዎችና የራሱ የሆኑ የጋብቻ ፣ የልደት እና የሞት ሥርዓቶች ፣ ሀገረሰባዊ ልማዶች ፣ ክብረ በዓላት ፣ የአምልኮ ሥርዓቶችና ባህላዊ መድኃኒቶችም እንዳሉት ተረጋግጧል፡፡ በብሔረሰቡ ባህል ቢያሳድጓቸውና ቢያጎለብቷቸው ጠቃሚ የልማት መሣሪያ የሚሆኑ የጋራ ትብብሮችና የአኗኗር ልማዶች ፣ መልካም አስተዳደርን ፣ ከብልሹና ከአድሏዊ አሠራር የፀዳ ማህበረሰብን መገንባት የሚያስችሉ ሃቀኝነትና ዕውነተኛነት መሠረታቸው የሆነና ሌብነትና ቅጥፈትን የሚጠየፍ ባህላዊ መልኮች እንዳሉ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ብሔረሰቡ በባህሉ በጋራ ተረዳድቶና ያለውን ተካፍሎ የሚኖርና ለነገ ሳይጨነቅ ኑሮዬ ይበቃኛል ብሎ የሚያድር በመሆኑ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ፣ ጥሪት መቋጠር ፣ ምጣኔ ሃብታዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ምርቶች ማምረት ፣ ምርጥ ዘር ማዳበሪያና የመሳሰሉትን የግብርና ግብዓቶች በብድር ወስዶ መጠቀም የሚሉት የመንግሥት ተልዕኮዎች ተግዳሮት እንደገጠማቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽኑንም አስመልክቶ ብሔረሰቡ የራሱንና የአካባቢውን ንጽህና መጠበቅ በባህሉ የተለመደ ጉዳይ በመሆኑ ይህን አስመልክቶ ለታቀደው የጤና የኤክስቴንሽን አፈጻጸም አዎንታዊ ባህላዊ አስተዋጽኦ ሲኖረው በሌላ መልኩ ደግሞ በባህሉ ተጽዕኖ ምክንያት የቤተሰብ ምጣኔ ፣ በጤና ተቋማት መጠቀምና በጤና ጣቢያ መውለድና የመሳሰሉት ጉዳዮች ተፈጻሚነታቸው ተግዳሮት እንደገጠመው ተረጋግጧል፡፡ በአካባቢው ልማት ላይ የባህላዊ/የፎክሎር ዘውጎች አሉታዊውም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ የማሳደራቸው ሃይል የሚገለጸው ደግሞ እርስ በእርስ እየተጋመዱና እየተሳሰሩ የራሳቸውን መህን ዘርግተው በተደጋጋሚ መከሰታቸውና ብሔረሰቡ ውስጥ ሰርፀው መኖራቸው መሆኑ በጥናቱ*

*በተለያዩ ምሳሌዎች ተተንትኖ ተረጋግጧል፡፡ ከጥናቱ በመነሳትም የተለያዩ ይሁንታዎች ለሚመለከታቸው ክፍሎች ተሰጥተዋል፡፡*

***ቁልፍ ቃላትና ሐረጎች፡-*** *ልማት ፣ ባህል ፣ አሉታዊ ባህላዊ ተጽእኖ ፣ አዎንታዊ ባህላዊ ተጽዕኖ ፣ ዋግኽምራ*

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ይህ ጥናት የተካሄደው “ባህልና ልማት በዋግኽምራ ብሔረሰብ” በሚል ርዕስ ላይ ነው፡፡ ባህል የኅብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ ፣ ወግ ፣ ልማድ ፣ እምነት (ኢ.ቋ.ባ.አ.፣ 2006 ፣ 235) በማለት ይተረጉመዋል፡፡ ልማት የሚባለውን ደግሞ የኅብረተሰብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ፣ ብልፅግና ፣ ግንባታ (ኢ.ቋ.ባ.አ.፣ 2006 ፣ 15) ብሎ ይተረጉመዋል፡፡ ከእነዚህ ሁለት ትርጓሜዎች በመነሳት የጥናቱን ስያሜ ባህልና ልማት በዋግኽምራ ብሔረሰብ የሚለውን እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ ባህል የኅብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ ፣ ወግ ፣ ልማድ ፣ እምነት ከሆነ ልማት ደግሞ የኅብረተሰብ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ እድገት ፣ ብልፅግና ፣ ግንባታ ከሆነ የአንድ ብሔረሰብ የአኗኗር ዘዴ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገቱ የሚለያዩ አይደሉም ለማለት ይቻላል፡፡

በመሆኑም የአንድን ብሔረሰብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ወይም እድገት ለማምጣት የአኗኗር ዘዴውን ፣ ልማዱን ፣ ወዘተ መመርመርና ማጥናት ማህበረሰቡ ይበለፅግ ዘንድ ፣ ባህሉ ለልማቱ ፥ ልማቱ ለባህሉ የሚኖራቸውን አዎንታዊ አስተዋፅኦና ተግዳሮቶች መለየት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

ጥናቱ በፎክሎር ስር የሚጠቀሱትን ዘውጎች አጠቃሎ (ሥነ ቃል ፣ ቁሳዊ ባህል ፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት እና ሀገረሰባዊ ልማድን) ይይዛል፡፡ እነዚህ ዘውጎች የየራሳቸው የሆነ የመከሰቻ መልኮች አሏቸው፡፡ በመሆኑም የባህል/ፎክሎር[1] ዘውጎች በዝርዝር በማጥናት ለብሔረሰቡ የሚኖራቸውን የልማት አበርክቶ አንጥሮ በማውጣት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ይህም የተደረገበት ዋናው ምክንያት ባህል የሰውን ልጅ ባህሪን የሚያደራጅና የሚተክሉ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሁኔታዎችን የሚይዝና በአመለካከትና በንግግር ፣ በአስተሳሰብና

---

[1] በዚህ ጥናት “ባህል” እና “ፎክሎር” የተሰኙት ቃላት የሚሰጡት ትርጉም ተመሳሳይ ነው፡፡ “ባህል” ሲባል ፎክሎር “ፎክሎር” ሲባል ባህል መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

በድርጊት የሚገለፅ ማህበራዊ ንብረት ነው፡፡ ይህንን አስመልክተው ኃይለ ገብርኤል ዳኜ ባህልና ትምህርት በኢትዮጵያ በሚል ለህትመት ባበቁት ፅሁፍ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> ባህል የአካባቢውን ማህበረሰብ አባላት እርስ በርስ ያግባባል ፣ ያስተሳስራል፡፡ በጊዜ አንፃር ሲታይ ደግሞ ባህል ዘላቂና የማይለወጥ ንብረት መስሎ ፣ ከርሱ የተሻለ ሌላ እንደ ሌለ ሆኖ በአባላቱ ህሊና ይንፀባረቃል፡፡ የማህበረሰቡም አባላት በተግባር አማካኝነት ወደ አዲሱ ትውልድ ይተላለፋሉ፡፡ ባህል አንድ ክስተት ሆኖ ግዙፍና ረቂቅ ወይም ውጫዊና ውስጣዊ መልክ አለው (ኃይለ ገብርኤል ፣ 2007 ፣ 1)፡፡

ከዚህ ገለፃ የተለያዩ ዋና ዋና ሀሳቦችን መረዳት ይቻላል ይቻላል፡፡ ይኸውም አንድን ማህበረሰብ ወይም ግለሰብ ከባህሉ ውጪ ማሰብ የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ ባህል የአንድ ማህበረሰብ የአካባቢው አባላት እርስ በእርስ የሚያግባባና የሚያስተሳስር ሲሆን በጊዜ ሂደት ባህሉ ዘላቂና የማህበረሰቡ የማይለወጥ ንብረቱ /ገንዘቡ መስሎ እንደሚታየው ያመላክተናል፡፡ በተጨማሪም በአባላቱ አዕምሮ የሚንፀባረቅ  መሆኑንም ያስገነዝበናል ፡፡

ባህል የአንድ ማህበረሰብ ሁለንተና የሚከሰትበት በመሆኑም ግዙፍና ረቂቅ ገፅታ አለው፡ ፡ ስለ ማህበረሰቡ ሕልውና መረጋገጥ ፣ ስለ ማንነቱ ፣ እድገቱ ፣ ጤናው ፣ ትምህርቱ ፣ አስተዳደሩ ፣ ፓለቲካዊ ተራክቦው ፣ ልማታዊ ተሳትፎው/እንቅስቃሴው ወዘተ ስናነሳ ልናልፈው የማንችለው ጉዳይ ባህላዊ መሰረቱን ነው  ፤ ለባህሉ ተገዥ ይሆናል ፤ ለባህሉ ህግና ሥርዓት ያለምንም ማንገራገር ይገዛል፡፡ በባህሉ ተለምዶ ትክክል የሆነ እሳቤ ትክክል ፣ ነውር/ሀራም የሆነ ነገር ውጉዝ ሲሆን ይስተዋላል፡፡ ይህም በተግባር እየዋለ ፣ እየታየ ቀስ በቀስ ይለመዳል ፤ ብሎም ባህል ይሆናል፡፡ ተቀባይነት ለማግኘት በባህሉ ሚዛን ተፈትኖ ማለፍ እንደሚኖርበት ያመለክታል፡፡

የአንድን ማህበረሰብ ልማት ለማፋጠን የማህበረሰቡ ባህል የሚያሳድረው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖው ሁነኛ ድርሻ ይኖረዋል (የራስ ወርቅ ፣ 2004) ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚህ ሃሳብ መነሻነት ይህ ጥናት አንፃራዊ በሆነ መልኩ በልማት ወደ ኋላ ቀሩ ከሚባሉት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አንዱ ከሆነው ከዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህል አኳያ ለሚካሄዱ የልማት ስራዎች ስኬታማነት ያሉ ምቹ ሁኔታዎች እና ተግዳሮቶች ምን መልክ እንዳላቸው ለመመመርመር ነው፡፡

ጥናቱ ሰባት ምዕራፎች ይዟል። በመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ የጥናቱ ዳራ ፣ የጥናቱ አካባቢ ዳራ ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ፣ የጥናቱ ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች ፣ የጥናቱ ጥያቄዎች ፣ የጥናቱ ጠቀሜታዎች ፣ የጥናቱ አካባቢ መረጣና የጥናቱ ገደብ ፣ ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎች ፣ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች ይቀርባሉ። በምዕራፍ ሁለት የክለሳ ድርሳን ፣ በምዕራፍ ሶስት የጥናቱ አሰራር ዘዴዎች ይተነተናሉ። በምዕራፍ አራት የዋግኽምራ ብሔረሰብ ዋና ዋና ባህላዊ ገፅታዎች ይተነተናሉ። በምዕራፍ አምስት ደግሞ የብሔረሰቡን ልማት ለማፋጠን ያለው አወንታዊ ባህላዊ/ፎክሎራዊ ገፅታዎች ይቀርባሉ። ምዕራፍ ስድስት የአካባቢውን ልማት የሚያስተጓሉ አሉታዊ ባህላዊ ጉዳዮች ለማየት ተሞክሮአል። ምዕራፍ ሰባት የጥናቱ ውጤት ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦች የቀረቡበት ሲሆን በመጨረሻም ዋቢ መፅሀፍት ፣ ልዩ ልዩ መረጃዎችና ፎቶ ግራፎች በአባሪነት ቀርበዋል።

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ባህልና ልማት በሰው ልጅ የአኗኗር ስርዓት ውስጥ ከፍተኛ ትስስርና ቁርኝት አላቸው። ባህል በኢኮኖሚ ልማት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ሊኖር እንደሚችል የጀርመኑ የሶሾሎጂ ሊቅ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በፊት ቀድሞ ተገንዝቦ ነበር። የባህልና የልማትን ጥብቅ ቁርኝት በመገንዘቡ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች በቴክኖሎጂና በካፒታሊዝም ፈጥነው ሊጓዙ የቻሉት የፕሮቴስታንት መርህ (ኤቲክ) በመከተላቸው ነው እስከ ማለት ደርሶ ነበር (Weber, 1930)። ይህም አስተሳሰቡ ሰፊ ተቀባይነትን አግኝቶለት ነበር። Weber “Economy and society” በሚል በ1930 እ.ኤ.አ ባሳተመው መፅሀፍ ውስጥ “The protestant Ethic and spirit of Capitalism” በሚል ርዕስ ባቀረበው ፅሁፍ ዘመናዊ የኢኮኖሚ እድገት የመጣው በፕሮቴስታንት እምነት ባህላዊ እሴቶች ላይ የመጣ ቀዳሚ ለውጥ ነው። የእምነቱ አራማጆችና ተከታዮች በብዛት ማምረትና መሸጥን ፣ ቁጠባን ፣ ፍትሃዊ የሆነ የንግድ ልውውጥን እንደ እምነቱ ምሰሶዎች አድርገው በመፈፀማቸው ካፒታሊዝም ማቆጥቆጥ ጀመረ። በእምነቱ ታታሪ ሠራተኛ መሆን ፣ በቁጠባ መኖር ፣ ጊዜውን በሥራ ማሳለፍ ፣ ጥሪት መቋጠርና መቆጠብ ተገቢ የሥነ ምግባር ግዴታና ኃላፊነት እንደሆነ መውሰድ ሲጀመር ለካፒታሊዝም መሰረት ሆኗል ይላል (Weber , 1930) ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የምሥራቅ እሲያ አገሮች (መጀመሪያ ጃፓን ፣ ቀጥሎ ደግሞ ደቡብ ኮርያ ፣ ታይዋን ፣ ሆንግ ኮንግ እና ሲንጋፖር) ከእድገት ጋር ተያይዞ የመጣው አስተሳሰብ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ በተለይ የጃፓን ዕድገትን ከኮንፊዩሽየስ (Confucian) እምነት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ የኮፊሺያን እምነት ለጃፓን ምጣኔ ሃብታዊ ዕድገት መሰረት እንደሆነ የሚናገሩ ወገኖች አሉ፡፡ Kahn (1993) ለአብነት የጃፓን ዕድገት ሊመጣ የቻለው ለዓለም ዝግ ያደረጉትን በራሳቸው በመክፈት ከአሜሪካ ጋር በመርከብ ንግድ በመጀመራቸውና አንድን ነገር አስመስሎ የመስራት ተሰጥኦ ስላላቸው ነው የሚሉ አስተሳሰቦች ቢኖሩም በTokugawa ዘመን የነበረው ሃይማታዊ አስተምህሮ ነው ይላል፡፡ በ1929[2] ሺ.ጋጉ በሚል ንቅናቄ መርህ የሆነው ከተለያዩ እምነቶች መልካም መልካም ሃሳቦችን አንድ ላይ አድርጎ ያዘ መንፈሳዊ ሆኖ ዓለማዊ ገፅታ ያለው እንቅስቃሴ በመሪዎቹና በሃይማኖት አባቶች ተቀባይነት በማግኘቱ ለጃፓን ዕድገት መሰረት ሆነ ይላል (Kahn,1993) ፡፡

የኮንፊሺየስ እምነት ጠንካራ የቤተሰብ ትስስርን የማጎልበትና ለቤተሰብ ስምና ደህንነት ሲባልም ራስን እስከ መስዋት የሚያደርስ ፈቃደኝነትን የሚያሰርፅ ነው፡፡ ግለሰቦችም ታማኝነትን ፣ ዕውነተኝነትን ፣ መብታቸውን ለቡድን መብቶች ማስገዛትንና ለዓላማ መስራትን ፣ በቡድኖች መካከል ጠንካራ ግንኙነት መፍጠርን ፣ የስራ ትጋትንና የቁጠባ ባህልን የሚሰብክ ስለሆነ በእነዚህ የእምነቱ ስነ ምግባራት አማካኝነት ካፒታሊዝም ሊያድግ ቻለ ይላሉ (Kahn, 1993; 169 -172)፡፡

ጃፓኖች የመልካም ልምዳቸው መገለጫ በሆነው ስኬታማ አስተዳደራቸው ፣ በላቀ ደረጃ በመማራቸው ፣ በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባው ቤተሰባዊ ትስስራቸው ፣ በስራ ባህላቸውና ራስን የመግዛት ብቃታቸው ፣ በብሄራዊ ማንነታቸው ላይ ባላቸው ኩራትና ውስጣዊ የበላይነታቸው አማካኝነት ከጥንካሬዎቹ ፣ ከባህሪያቱና ከዘዴዎቹ ጋር ወደ ተሟላ ዘመናዊነት ገብተዋል ይላሉ (Landes, 2001:8)፡፡

በአፍሪካ ያለው ደግሞ ከዚህ በተለየ መልኩ ለኋላ ቀርነትና ለድህነት መንስኤው ዕምነቶችና ሃይማኖቶች እንደሆኑ ይነሳል፡፡ አፍሪካ ማደግ ከፈለገች ከባህላዊ ማነቆዎቿ ተላቃ የምዕራባውያንን አስተሳሰብ መቀበል አለባት ብለው የሚከራከሩ ወገኖች እንዳሉ

[2] የኢትዮጵያ አቆጣጠር የሆኑት ዓ.ም ሲገለጹ ከዚህ ውጭ የሆኑት በአውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው፡፡

የአፍሪካን የልማት ሁኔታ ያጠኑ ምሁራን ያስረዳሉ (Ojameruay, 2005, Gebre, 2005)፡፡

የልማት ሳይንሶች ላይ የነገሰው አስተሳሰብ ለባህል ስፍራ የማይሰጥ ፣ ልማት እንዲኖር ከተፈለገ ወሳኞቹ ሁነቶች የማዕድን መኖርና ወይም በሌላ መልክ ካፒታል ማግኘት ፣ በእነዚህም ላይ ተመስርቶ ትምህርትን ማስፋፋት ፣ ኢንቨስትመንትን ማሳደግ ፣ ወዘተ የመሳሰሉት ስለነበሩ ሊቃውንቱ ይህንኑ ሲያስተምሩ ቆይተዋል[3]፡፡ ይሁን እንጂ ከልማት የትምህርት መስኮች ውስጥ አንዱ የሆነው ኢኮኖሚክስን ብንወስድ ልማታዊ ኢኮኖሚክስ መልክ ይዞ ከተፈጠረበት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ በኋላ እስከ 1980ዎቹ (እ.አ.አ) ማብቂያ ድረስ ፣ ባህል በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ለሚኖረው ድርሻ እዚህ ግባ የሚባል ግምት አልተሠጠውም ነበር፡፡ ሁኔታዎች መቀየር የጀመሩት በ1980ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ነው በማለት ገልፀዋል (ባህልና ልማት በኢትዮጵያ ፣ 2004)፡፡

Gebre Yntiso "Culture and Development in Africa" በሚለው የምርምር ሥራቸው በባህልና ልማት መካከል ያለውን ግንኙነት በሁለት የተለያዩ መንገዶች ሲገለፅ የኖረ እንደሆነ ገልፀው እነዚህም ሁለት የክርክር ነጥቦች፡-

> አንደኛው የመከራከሪያ ነጥብና በአሁኑ ሰዓት ብዙም ተሰሚነት የሌለው ባህል በልማት ውስጥ ምንም ዓይነት አዎንታዊ ሚና የለውም እንደውም የታዳጊ ሀገሮች ባህል ለልማታቸው እንቅፋት ነው የሚለው ሲሆን አስተሳሰቡ ከዘመናዊነት ቲዎሪ ጋር የተዛመደ ሆኖ የታዳጊ ሀገሮች ባህል ላለመልማታቸው ምክንያቱ በባህላዊና ልማዳዊ ተፅዕኖዎቻቸው ሳቢያ ያለ ውስጣዊ ክፍተትና ችግር እንደሆነ የሚገልፅ ነው፡፡ የዘመናዊነት ቲዎሪ አቀንቃኞች የሚመክሩትም ደሀ ሀገራት ለማደግ ከፈለጉ አገሮች በሚዋሷቸው ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች መተካት አለባቸው ብለው እንደሚከራከሩ ያስረዳሉ፡፡ ሁለተኛው የመከራከሪያ ነጥብ ደግሞ ባህል ለልማት አስተዋፅኦ ሲኖረው ባህሉ ራሱ ከልማቱ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ባህልና ልማት እርስ በእርስ የሚደጋገፉ ናቸው፡፡ ስለልማት ስናነሳ ባህሉን ወደ ጎን ጥለን መሆን የለበትም ብለው የሚከራከሩ እንደሆነ

[3] ባህልና ልማት በኢትዮጵያ ፣ 2004 ዓ.ም ፕ/ር ሺፈራው በቀለ ከፃፉት መቅድም ላይ (Vi) ያሰፈሩት ሀሳብ ላይ የተወሰደ ነው፡፡

አሳይተው እሳቸውም ይህንን ሀሳብ ወስደው በጥናታቸው ለማሳየት እንደሞከሩ ገልፀዋል (Gebre, 2005;12-13)፡፡

Gebre በዚህ ስራቸው የአፍሪካን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የባህልንና የልማትን ግንኙነት ለማስረዳት ባህል ለልማት የሚኖረውን አዎንታዊ አስተዋፅኦ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ መነሻ ያደረጉትም የባህልን እና ልማድን መሰናክላዊነት ከማጉላት /ከማሳየት ይልቅ ሊኖረው የሚችለውን ጠቃሚ ክፍሎች ከመግለፅ ላይ ነው፡፡ እነዚህንም ጠቃሚ ገፅታዎች ትብብሮች ፣ ማለትም የጋራ የስራ ቡድኖች ፣ የጋራ የእርሻ የልማት ስራዎች ፣ የጎረቤታሞች የቁጠባና ብድር ማህበራት ፣ ባህላዊ መረዳጃዎች ፣ ከተማ ምስርት ባህላዊ ማህበራት ፣ ሁለተኛው ደግሞ ባህላዊ የተግባቦት ስራዎች ፣ በተለይም ደግሞ ኤች አይቪ ኤድስን ለመከላከል ከባህላዊ ትምህርት ቤቶች ጋር መስራት ፣ ካለእድሜ ጋብቻንና ብዙ ማግባትን ማስወገድ ፣ ባህላዊ መድሀኒት አዋቂዎች ጋር መስራት ፣ ባህላዊ የመረጃ ልውውጦችን ፣ ሶስተኛው ክፍል ያሉ የጾታ እኩልነትና የሴቶች ሚና ፣ የሴቶችን መብት የሚጠብቁ ባህላዊ ተቋማት ፣ የሴቶች የኢኮኖሚ አቅም ፣ የሴቶች በጎ ፍቃደኛ ማህበራት ፣ በአራተኛ ደረጃ ያስቀመጡት ደግሞ የህፃናት ጥበቃ አስተዳደግ እና የእናት ጡት ወተት ምገባ የተሰኙት ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ባህላዊ መሰረቶች ከሰላሳ ሀገሮች በላይ ጥናቱን በማካሄድ በባህልና ልማት መካከል ያለው ግንኑነት የጠበቀና እርስ በርሱ የሚደጋገፍ መሆኑን አንዱ ለአንዱ አስተዋፅኦ የሚያደርግና እርስ በርሱም ተመጋጋቢ እንደሆኑ ይህም ሰዎች ምጣኔ ሀብታዊ ፣ ዕውቀታዊ ፣ መንፈሳዊ ፣ ስነምግባራዊ/ሞራል እና ስሜታዊ ተጠቃሚነትን እንዲያገኙ የተመቻቸ ሁኔታን እንደሚፈጥርላቸው ያሰርፃሉ፡፡ አክለውም በባህልና ልማት መካከል ያለው ግንኙነት በልማት ስትራቴጂዎች ውስጥ ባህላዊ ጉዳዮች መካተት እንዳለባቸው የሚያመላክት ነው ይላሉ፡፡

በአፍሪካ ያለው ዋናው ተግዳሮት የባህልን ውጤታማ ጠቀሜታ እንዴት ለላቁ የልማት ግቦች እንጠቀምበት የሚለው እንደሆነ ገልፀው ጥናታቸው የአፍሪካን ባህል አዎታዊ ገፅታዎች በማሳየት ድህነትን ለማጥፋት ፣ ኤች አይቪ ኤድስን ለመዋጋት ፣ በፆታ እኩልነትና ሴቶችን ለማብቃት እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ያመለከተና የአፍሪካ ማህበረሰብ ሀገር በቀል እውቀት ለልማት አስተማማኝ ሀብትነት የሚያስገነዝብ ነው በማለት ያጠቃለሉ (Gebre, 2005 ፣ 35)

ሀገራችን ኢትዮጵያን አስመልክቶ በልማት ላለመግፋቷና ለኋላ  ቀርነቷ በውጭም ሆነ በሀገራችን ሊሂቃን የተለያዩ ምክንያቶች ሲዘረዘሩ እንደቆዩ ይታወቃል፡፡

> የምዕራቡ ስልጣኔ የኢንዱስትሪው አብዮትን በማካሄድ የተፋጠነ የኢኮኖሚና የሶሻል እርምጃዎችን ማስመዝገብ ከጀመረበትና በምዕራብያን አለምና በሀገራችን መካከል ያለው የእድገት ልዩነት እጅግ እየሰፋ መሄድ ከጀመረበት ከ18ኛው ምዕተ አለም ወዲህ ወደ ሀገራችን በብዛት ብቅ ማለት የጀመሩት አውሮፓውያን ሚሲዮናውያን አገር ጎብኚዎች ይኼን ጉዳይ በተመለከተ የየበኩላቸውን ብለዋል፡፡ የአብዛኛዎቹ አመለካከት በአንድ አቅጣጫ ያነጣጠረ ነበር፡፡ ይህም የአገሪቱን ኋላ ቀርነት ወግና ልምድ ላይ የሚያላክክ ነበር (የራስ ወርቅ ፣ 2004 ፣ 14)፡፡

የሀገሪቱን በእድገት ወደ ኋላ መቅረት ምክንያት በ19ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ የፕሮቴስታንትን እምነትን የያዘ ህዝብ ሀብትና ብልፅግና እንደሚያስገኝ እንግሊዝን በማስረጃነት በማቅረብ ወደ ኢትዮጵያ የተላኩት የዕምነት ተከታዮችና ሰባኪዎች ያስረዱ ነበር፡፡ የኢትዮጵያም ኋላ ቀርነት ከተዋህዶ ክርስትና ዕምነቷ የመነጨ እንደሆነና የእምነት መሻሻል ብታደርግ ወደ ብልፅግና ጎዳና እንደምታመራ ይገልጹ ነበር፡፡ ቀስ በቀስም የክርክራቸው አቅጣጫም ከሀይማኖታዊ ጉዳዮች ይልቅ ወደ ባህላዊ ጉዳዮች ማመዘኑን የተመለከተ ነበር (የራስ ወርቅ ፣ 2004 ፣ 14-15)፡፡

የአውሮፓውያንንና የጃፓንን ስልጣኔ የተመለከቱ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ (2007) እና ከበደ ሚካኤልም (1946) ሀገሪቱ በኋላ ቀርነት ተቀፍድዳ የታሰረችው በጊዜው የነበረውን ሥርዓት የመሬት ስሪት ፣ ኋላ ቀር የአስተዳደር ስርዓትን ፣ የትምህርትና የስልጣኔ አለመስፋፋትን ፣ ለገበሬው የነበረው ዝቅተኛ አመለካከት ፣ ወዘተ በግንባር ቀደምነት ቢጠቅሱም ባህላዊ ሁኔታዎችንም ሳያወሱ አላለፉም፡፡

ይሁንና ባህል በልማት ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ አስመልክቶ የተደረገና በተለይ ከኔ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚመሳሰል ጥናት አላገኘሁም፡፡ ይሁን እንጂ በዋነኛነት በዚህ ዙሪያ የሚነሳ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በሚል ርዕስ ከመጋቢት 2001 እስከ ጥር 2003 ዓ.ም ድረስ ባህልና ልማት በሚል ርዕስ ይዘጋጅ በነበረው የውይይት መድረክ ላይ በተጋበዙ ምሁራን በርዕሱ ዙሪያ የቀረቡ 12 ጥናታዊ ጽሑፎችን አንድ ላይ በማሰባሰብ በሺፈራው በቀለ አርታኢነት ባህልና ልማት በኢትዮጵያ በሚል ርዕስ በ2004

ዓ.ም ያሳተመው መጽሐፍ ይገኛል፡፡ በዚሁ ውስጥ የየራስ ወርቅ አድማሴ ባህልና ልማት ምንነታቸውና ትስስራቸው ፣ የዘውዴ አበጋዝ ባህል ከልማትና ከስርዓተ ፆታ ጋር ያላቸው ግንኙነት ፣ የአሉላ ፓንክረስትና የገብሬ ይንቲሶ አገራዊ እውቀትና ተዛማጅ ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ ፣ የፈቃደ አዘዘ ቁዘማ ፎክሎር (ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ የሚሉት ጥናቶች በሀገራዊነታቸውና በሚያነሱት ጉዳይ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያያዙ ጭብጦች ስላሏቸው የጥናት አቅራቢዎቹን እየጠቀስኩ በጥናቴ የምጠቀምባቸው ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ ሲታዩ ግን በተለይ ይህ ጥናት የሚያተኩርበትን የዋግኽምራን ብሔረሰብ የማይመለከቱ መሆናቸው ከዚህ ጥናት ጋር ይለያሉ፡፡

ይህ ጥናት ባህልና ልማት የሚኖራቸውን ቁርኝት ለማሳየት የሚቀርብ ስለሆነ በዚያው ይታያሉ፡፡

ይህ ጥናት ባህልና ልማት የሚኖራቸውን ቁርኝት ለማሳየት በዋግኽምራ ብሔረሰብ አውድ ላይ ተገኝቶ ተጨባጭ ማስረጃዎችን እያቀረበ የሚያሳይ በመሆኑ ከተጠቀሱት ጥናት አቅራቢዎች የተነሱ የባህልና የልማት ቁርኝትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ለማረጋገጥ የሚያስችል መረጃ ሊያስገኝ ይችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አካባቢ እና የብሔረሰቡ የዘር ሐረግ ታሪካዊ ዳራ

በዚህ ክፍል የብሔረሰቡ አጠቃላይ ገፅታና የጥናቱ ዋነኛ ትኩረት የሆነው የዋግኽምራ ብሔረሰብና አካባቢው ፣ ታሪካዊ ገፅታ ፣ አኗኗር ፣ ማህበራዊ ፣ መንፈሳዊ ገፅታና ልዩ ልዩ መገለጫዎቹ በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

### 1.2.1.የዋግኽምራ ብሔረሰብ አጠቃላይ ገፅታ

በአሁኑ ጊዜ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰባት የአስተዳደር ዞኖች ፣ አንድ ልዩ የከተማ አስተዳደር ዞንና ሶስት የብሔረሰብ ዞኖች የተዋቀረ ነው፡፡ ቀደም ሲል ከነበሩት አስራ ሁለት አውራጃዎች መካከል አንዱ የነበረው የዋግ አውራጃ ከሚያዚያ 1986 ዓ.ም ጀምሮ በዞን ደረጃ ተዋቅሮ የዋግኽምራ ብሔረሰብ ዞን ተብሎ በክልሉ ከሚገኙ ሶስቱ የብሔረሰብ ዞኖች መካከል አንዱ ሆኗል (አበባው ፣ 2001 ፣ 3)፡፡ የዞኑ ስያሜም

የተወሰደው “ዋግ” ከሚለው የቀድሞ የአውራጃ ስሙና “ኽምራ” ከሚል በዞኑ ኽምጥኛን በአፍ መፍቻ ቋንቋነት ከሚናገረው ብሔረሰብ ስም ጥምረት ነው። አሰያየሙን በሚመለከት (Vaughan, 2003; 242) በአሁኑ የዞኑ ስያሜ ላይ ታሪካዊ የሆነው ሥነ ምህዳራዊና ፓለቲካዊ ስያሜው “ዋግ” እና የማንነት መገለጫው “ኽምራ” በጥምረት ተካተውበታል በማለት አስፍረዋል።

የዋግኽምራ ዞን የሚገኘው በአማራ ክልል ሰሜናዊ ጫፍ ፣ በሰሜን ፣ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ከትግራይ ክልል ፣ በደቡብ ከሰሜን ወሎ፣ በምዕራብ ከሰሜን ና ከደቡብ ጎንደር በመዋሰን ነው። በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ (2003 ዓ.ም ፣ 24)መረጃ መሰረት የዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ስፋት 9,039.04 ካሬ ኪሎ ሜትር ነው ።

ዞኑ እስከ 1998 ዓ.ም ድረስ በሶስት ወረዳዎች (ደሃና ወረዳ ፣ ሰቆጣ ወረዳ እና ዝቋላ ወረዳ) የተከፈለ ነበር። አሁን ግን በስድስት ወረዳዎች እና በአንድ የከተማ አስተዳደር ተከፍሏል። እነዚህም ሰቆጣ ከተማ አስተዳደር ፣ ሰቆጣ ወረዳ ፣ ድሃና ወረዳ ፣ ሰሃላ ሰየምት ወረዳ ፣ አበርገሌ ወረዳ ፣ ጋዝ ጊብላ ወረዳ እና ዝቋላ ወረዳ ናቸው። በብሔረሰቡ ዞን ውስጥ 122 የገጠርና ሶስት የከተማ በድምሩ 125 ቀበሌዎች ይገኙበታል። እንደ 2007 ዓ.ም የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሰረት የዞኑ ህዝብ ብዛት 426,213 ነው። ከዚህ ውስጥ 213,845 (50.1%) ወንድ ፣ 212,368 (49.83%) ደግሞ ሴት ነው። ይህ ቁጥር በከተማ እና በገጠር ተከፋፍሎ ሲታይ ደግሞ በከተማ 29,951 (7.02%) ሲሆን በገጠር ደግሞ 396,262 (92.98%) ነው።

በዞኑ ዝቅተኛው ቦታ የተከዜ በረሀ ሲሆን ከባህር ጠለል በላይ 1,000 ሜትር ነው። ከፍተኛው ደግሞ ከባህር ወለል በላይ 3,715 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኘው የቤላ መስቀሎ ሰንሰለታማ ተራራ ነው። በዞኑ ከሚገኑት ወንዞች መካከል ትልቁ የጥራሪ ወንዝ ነው። ጥራሪ ወንዝ የሚገኘው በወጣገባና ተራራማ ቦታ መሃል ሲሆን ሞቃታማ ነው። የዞኑ የአየር ንብረት ደጋ ፣ ወይና ደጋና ቆላ ሲሆን በመቶኛ ሲሰላ በተከታታይ 8.3% ፣ 34.5% ፣ እና 57.2% ነው። ዓመታዊ የዝናብ መጠኑም ከፍተኛው 681 ሚሊ ሜትር ሲሆን ይህም በክረምት ብቻ የሚገኝ ነው። ዞኑ በበጋ ዝናብ አያገኝም። የዞኑ አርሶ አደር የሚያመርተውም በአመት አንድ ጊዜ በመኸር ብቻ ነው። ከተወሰኑ

የመስኖ ምርት አምራቾች አካባቢዎች በስተቀር በዞኑ የበልግ ምርት የሚባል አይታወቅም (ጌታቸው ፣ 2000 ፣ 160)።

በአማራ ክልል ድርቅ በተደጋጋሚ ከሚያጠቃቸው አካባቢዎች መካከል አንዱ ይህ ዞን ነው። በሽምራጎኸ (1993 ፣ 6) ሰፍሮ እንደሚገኘው በቅርቡ በኢትዮጵያ የድርቅና የረሀብ ወቅት ተብለው የሚጠቀሱት የ1966 ዓ.ም እና የ1977 ዓ.ም ድርቅ የዞኑን ህዝብና እንስሳት በጣም የጎዳና ህዝቡን ለእልቂትና ለስደት የዳረገ ነበር።

የዋግኽምራ ዞን ዋና ከተማ ሰቆጣ ነው። ሰቆጣ ከአዲስ አበባ 720 ኪሎ ሜትር ፣ ከክልሉ ዋና ከተማ ባህር ዳር 250 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል።

ይህ ከተማ ጥንታዊ ከሚባሉት ከተማዎች መካከል ይጠቀሳል። ይህንንም (Pankhurst,1982,125) ሲገልጹ ሰቆጣ የዋግ ዋና ከተማ ፣ በዘር ሀረግ እየተወራረሱ የሚገዙት የዋግ ሹሞች መቀመጫ ስትሆን በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢ ታዋቂ ከነበሩት ከተማዎች ውስጥ አንዷ ናት ብለዋል። የዋግ ሹሞች መቀመጫነቷንና ጥንታዊ ከተማቷን በሚመለከት ፣ ሰቆጣ ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በሰሜን ወሎ የታወቀች የከተማ ማዕከል የነበረች ከተማ ስትሆን ለረዥም ጊዜም የዋግ ሹሞች መቀመጫ ነበረች በማለት አስፍረውታል (Mc Can,1984,24)።

ሰቆጣ የታወቀች የገበያ ቦታም ነበረች። ይህንንም Mc Can (1984) ሲገልጹ የሰቆጣ እድገት እና መረጋጋት የተገኘው በአስተዳደራዊ ሚናዋ ብቻ አይደለም። በገበያ ቦታነት አገልግሎቷም እንጂ። ከቅርብ ፣ ከመካከልና ከሩቅ የሚመጡ በጥቅሉ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ከሰሜን ወደ ደቡብ ፣ ከደቡብ ወደ ሰሜን ለሚደረግ የንግድ እንቅስቃሴ ቁልፍ ቦታ ነበረች ብለዋል። Vaughan ( 2003) (Richard Pankhrst, 1968:520)ን ጠቅሰው የሰቆጣ የገበያ ቦታነት በሰሜን ኢትዮጵያ የነጋድራስነት ማዕረግ ያላቸው ሰዎች ይገኙባቸው ከነበሩት ስድስት ታዋዊ የገበያ ቦታዎች መካከል አንዷ ሰቆጣ ናት። ስለዚህ ሰቆጣ በቁጥር የተወሰኑ ከነበሩት የገበያ ከተሞች ተርታ የምትሰለፍ እንደነበረች እንረዳለን።

ላምረው (1986 ዓ.ም) በሰቆጣ ገበያ የሚገበያዩ የተለያዩ ማህበረሰቦች የባህል ልውውጥ የሚያድረጉባት እንደነበረች ጠቅሰው እንደሚከተለው አስፍረውታል።

የሰቆጣ ገበያ ለትግራይ ፣ ለሰሜን ፣ ለቤጌምድር ፣ ለጎጃም ፣ ለአማራና ለወሎ ገበያተኞች አማካይ ሆኖ የተለያዩ ሸቀጦች ይውሉበት ነበር፡፡ የአገው ፣ የአማራ ፣ የትግራይና የሌሎችም ማህበረቦች ወግና ባህሎች የሚገናኙበት ከተማ ሰቆጣ ከተማ ነበር ብሎ ለመናገር ያስችላል፡፡ ከ17ኛው እስከ 20ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ድረስ ሰቆጣ በዝናዋ የገነነች እንደነበረች በዘመኑ የተፃፉ መጻህፍትን በዋቢነት ማቅረብ ይቻላል፡፡

እኔም የአካባቢውን ታዋቂ አባቶች በመጠየቅ የሰቆጣን ታዋቂ የገበያ ቦታነት በሚመለከት በከተማዋ የተለያዩ ነገሮች ግብይት ይካሄድ እንደነበርና ለመገበያየት የሚመጡት ሰዎች ማረፊያም የተለያየ ቦታ እንደነበርም እንደሚከተለው ገልፀውልኛል፡፡

> በጥንት ጊዜ ወደ ሰቆጣ የማይመጣ አልነበረም ፤ ከኤርትራ ፣ ከጎጃም ፣ ከቤጌምድር ፣ ከወለጋ ፤ ጨርቁን ፣ በርበሬውን ፣ ጨውን ይዞ ይመጣል፡፡ ከዚህ ደግሞ ቅቤውን ፣ ማሩን ፣ ከብቱን ፣ ፍየሉን ፣ ቆዳውን ፣ ገዝቶ ይሄዳል፡፡ ለገበያ ከሚመጡት ውስጥ አማራዎች የሚያረፉት አሁንም “አማራ ተራ” ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ነው፡፡ ይህ ሰፈር ስያሜውን ያገኘው ሲያርፉ ከነበሩት ነጋዴዎች ማንነት ነው፡፡ የገበያው ቀንም ማክሰኞና ረቡዕ ነበር፡፡ ገበያተኛውና የሚገበያዩት ነገርም ብዙ ስለነበር ተራውም የሚገዛበትና የሚሸጥበት እንደ ዛሬው በአንድ ቦታ አልነበረም፡፡ አህያ ፣ ቅቤና ማር ፣ በርበሬ ፣ ቡና ፣ አቡጀዴ ፣ ጫማ ፣ ጨው ፣ ፍየል ፣ በተለያዩ ቦታዎች ነበር የሚገዙትና የሚሸጠው፡፡ እነዚህ ተራዎች አህያ ተራ ፣ እህል ተራ ፣ ቅቤና ማር ተራ ፣ ጨው ተራ ፣ ፍየል ተራ ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ እስከ አሁን የሰፈር ስም መጠሪያ ሆነው የቀጠሉት “አማራ ተራ” እና “አህያ ተራ” ብቻ ናቸው ፤ ሌሎቹ ተረስተው ቀርተዋል (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቃ.መ. 19/10/2009 ዓ.ም)፡፡

በማዕከላዊነት ያገለግል የነበረው የገበያ ቦታ በአሁኑ ጊዜ ግን አይታይም፡፡ የዛሬዋ የዋግኽምራ መስተዳደር ዞን ዋና ከተማ ሰቆጣ ከቀደምት የኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ አንዷ ስትሆን በዋግ ሹሞች መቀመጫነት እና በገበያ ቦታነቷ የምትታወቅ ነበረች፡፡

### 1.2.2. የብሔረሰቡ ታሪካዊ ዳራ

የአገዎች መኖሪያ ከሆኑት ውስጥ አንዱ የዋግኽምራ ብሔረሰብ መስተዳደር ዞን ነው። የአገው ህዝብ ደግሞ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ህዝብ መሆኑን የተለያዩ የታሪክ ምሁራን በጽሑፎቻቸው አስፍረውታል። ከነዚህም መካከል Taddesse (1988:6) ለአብነት ይህል በፅሁፋዊ ምንጮች ተገልፀው ከምናገኛቸው የኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል የአካባቢው ጥንታዊ ነዋሪዎች አገዎች ናቸው ሲሉ በሌላ ስራቸው (1972 ፡ 37) ደግሞ አገዎች ከጆማ ወንዝ በስተ ሰሜን በሚገኙ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ ቀደምት ነዋሪዎች ናቸው ብለዋል። Bahru (2005:5)ም ዋና ዋና ከሚባሉት ቀደምት የኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል አገዎች ተጠቃሽ እንደሆኑ ሲገልጹ የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆኑት ኢትዮጵያውያን ውስጥ በታሪክ ታዋቂዎቹና ዋና ዋናዎቹ አገውና ቤጃ ናቸው ብለዋል።

Bender እና ሌሎች (1976 ፡ 40) ደግሞ የአገውን ህዝብ ጥንታዊነትና በአሁኑ ጊዜ መኖሪያቸው የተለየ መሆኑን አስመልክተው ሲገልፁ የአገው ህዝቦች በአንድ ወቅት ብዙውን የኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታ ሸፍነው የነበሩ ናቸው ፤ በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው ለመገኘታቸው ምክንያቱ በሴም ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች ቦታቸውን እንዲለቁ በመገደዳቸው በመሆኑ ይታመናል ይላሉ።

አገዎች ከጥንታዊ የኢትዮጵያ ህዝብነታቸው ሌላ የተለያየ የጥራጥሬ ተክሎች ማምረትን በኢትዮጵያ ያስለመዱ እንደሆኑም ገልጸዋል (Levine, 2000, 29; Melkneh, 1990 : 20 እና Gamst,1968 :12; Murdock,1959) ። ሽቱ አያን እና ሌሎችም (1988 ፡ 6) በግብርና ስራ በዋናነት የሚጠቀሱ አንኳር የሆኑ የእህል ዓይነቶችን አበርክተዋል ብለዋል።

በአንድ ወቅት በአንድ አካባቢ ይኖሩ የነበሩት ጥንታዊዎቹ የአገው ህዝቦች በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው ይገኛሉ። ይህንንም Levine, (20003, 7) ሲገልጹ፦

> አገዎች ከአክሱም መነሳት በፊት በሰሜን ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች ከሌላው ልቀው ይኖሩ የነበሩ ህዝቦች ሲሆኑ ፣ እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ጠንካራ ኃይል ያላቸው ሆነው በአካባቢው ቀጥለው ነበር። በአሁኑ ጊዜ የአገው ቅሪቶች በኤርትራ ፣ በቤጌምድር ፣ በወሎና በጎጃም ኪስ ቦታዎች ይገኛሉ።

በሌላ መልኩ ደግሞ አገዎች በሶስት እንደሚከፈሉና የዋግ አገዎች (ኽምራዎች) ቀደምት ቦታዎችን ሳይለቁ በነበሩበት ቦታ እንደሚገኙ ታዬ (1964 ፣ 32) እንደሚከተለው አስፍረውታል:

> አገዎች በሶስት ተከፍለው ቋንቋቸውም ስሩ አንድ ሲሆን በየክፍላቸውና በየአገራቸው ጥቂት ጥቂት ልዩነት ያለው ነው። እነርሳቸውም በሶስት አገር ስም ይጠራል። የላስታ አገው ፣ የዳሞት አገው ፣ የሐልሐል በጎስ አገው ይባላሉ። የሁለቱም መሰረትና ምንጭ የላስታው አገው ነው ፤ የላስታ አገዎች በዋግ የሚኖሩ ዋኖቹ ናቸውና በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ የያዙትን አገር አልለቀቁም ፤ እስከ ዛሬም አልተነቃነቁም።

እነዚህ የአገው ዘሮች መቼና በምን ምክንያት ከዋግ ተነስተው ወደ ተለያዩ ቦታዎች እንደፈለሱ ወይም እንደሄዱ በአፈ ታሪክ በጽሁፋዊ ምንጮች በተለያዩ መንገድ ተገልፀዋል። ቢለኖች ከዋግ ላስታ የተንቀሳቀሱበት ምክንያት ተብሎ በፅሁፋዊ ምንጮች የተገኘው ሁለት ዓይነት ነው። ይኸውም በችግር ምክንያት ነው የሚል ሲሆን ሌላው ደግሞ ድንበር ለመጠበቅ ነው የሚል ነው።

ዩሐንስ (1940 ፣ 120) የሐልሐል በጎስ አገዎች በአንድ ዘመን በሀገሩ ረሀብ ስለሆነ ከላስታ አገው ተለይተው ሰባት ወንድማማቾች ከነሚስቶቻቸውና ከነልጆቻቸው ፣ አምስት እህቶቻቸውና ባሎቻቸው ተሰደው ሐልሐል በጎስ ገቡ። ከዚያም ዱሩን መንጥረው ፣ እባቡን ፈጅተው ፣ ቤት ሰርተው ፣ አገር አቅንተው ተቀመጡ ይባላል በማለት ለመሄዳቸው/መፈናቀላቸው ምክንያቱ ረሃብ እንደሆነ ሲገልጹ ፤ (Adhana,1988 :747) ደግሞ የዛጉዌ ነገስታት ቢለኖችን ወደ ሰሜን የላኩዋቸው በቤጃዎች የሚወሰደውን መሬት እንዲከላከሉና የንግድ መስመሩን ከሰዋኪን ወደ የተቀደሱ ቦታዎች የሚደረገው ጉዞ ነፃ እንዲያደርጉ ነው ብለዋል። Kiflmariam (1988:7) ደግሞ ይህንን ስደት የሚያመለክቱ የቦታ ስሞች መኖራቸውን እንዲህ በማለት ገልጸዋል። ስደቱ ከላስታ ላሊበላ እስከ ከረን በሚገኙ የአገውኛ የቦታ ስሞች ምልክቱን አስቀምጧል ፤ እነዚህም ዲቦራዋ ፣ በስራየ ፣ ቺንዱዋ ፣ ቲልኩስትዋ ፣ ጀገርታውና የመሳሰሉት የቦታ ስሞች በሃማሴን ይገኛሉ።

ቢለኖች ተንቀሳቀሱበት ተብሎ የሚነገርበት ዘመንም የተለያየ ሆኖ እንገኘዋለን፡፡ Lenvine (2000:71) ምን አልባት ወደ ሰሜን መጥተው የሰፈሩት ከ10ኛው ምእተ ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ ላይ ይሆናል ይላሉ፡፡ Kiflmariam (1988:6) ደግሞ Conti Rossiniን በመጥቀስ ስደቱ በሁለት ዙር የተካሄደ መሆኑን አስፍረዋል፡፡ Adhana (1988:7) ቢለኖች ወደ እዚህ አካባቢ የመጡት ከዛጉዌ ስርዎ መንግስት በኋላ በ11ኛው ክፍለ ዘመን ነው በማለት የሁለቱን ሀሳብ ተጋርተው አስፍረዋል፡፡

ሌላው የአገው ብሔረሰብ አዊ ነው፡፡ አዊዎች ከዋግ ላስታ ተነስተው መሄዳቸውን የተለያዩ ምንጮች ቢሰፍሩም ፤ የተንቀሳቀሱበት ምክንያትና ዘመን ግን የተለያየ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በመጀመሪያ የምናገኘው በዮሐንስ (1940 ፣ 120) የተገለጸውን ነው፡፡ እንደ እሳቸው አገላለፅ አዊዎች ከዋግ ላስታ ተነስተው የሄዱት ለአደን ነው፡፡ Melkneh (1990, 29)ም ለአደን እንደሄዱ አስፍረዋል፡፡

አዊዎች ወደ ጎጃም ሄዱ የሚባለው በአንድ ዙር ሳይሆን በሁለት ዙር ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሰባት ሆነው መሰደዳቸውንና የሄዱበትም አካባቢ በእነዚህ ሰባት ሰዎች ስም መጥራታቸውን Taddesse (1988:11) ዘርዘር አድርገው እንደሚከተለው አስፍረውታል፡፡

> የአገው ምድር እና የመተከል አገዎች "Laneta Awiya" ወይም ሰባት ቤት አገውን (Seven house Agew) ለመመስረት ከላስታ ሰቆጣ የመጡ ሰባት ወንድማማች እንደ አያቶቻቸው አይነት ባህል አላቸው ፤ ሰባት ቤት የተሰየመው ከሰባት ወንድማማቾች ባንጃ (Banja) ፣ አንካሻ (Ankasha)፣ ክዋክውራ (Kwakwra) ፣ ጫራ (Chara) ፣ መተከል (Metekkel) ፣ ዚገም (Zigem) እና አዘና (Azena) ናቸው፡፡ ሌሎቹ አነስተኛ የቡድን አባላት የሆኑት ቱምኀ (Tumha) ፣ ዳንጊዝህ ወይም ዳንግላ (Dangezh/Dangla) ፣ ቢል ወይም ባላይ (Bil /Belaya)እና ጓዋጉሳ (Gwa gwsa) ወይም ዘግየት ብለው የመጡ ካልሆነም የመጀመሪያዎቹ የሰባቱ ዝርያዎች (Descendants) ናቸው፡፡ እነዚህ ጥንታዊ አባቶች የሰፈሩባቸው ቦታዎች ስሞች የአውራጃ ፣ የወረዳ ወይም የንዑስ ወረዳ መጠሪያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡

Melakneh (1990:32-33)ም የጉዞው ምክንያት አደን መሆኑን ፣ ጉዞው ሁለት ዙር እንደ ነበርና የመጀመሪያና የሁለተኛ ዙር ሰፋሪዎች በተከታታይ ሰባትና አምስት መሆናቸውን በእነዚህ ሰዎች ስም የተሰየሙ የአውራጃ ፣ የወረዳና የንዑስ ወረዳ መጠሪያ እንደነበሩ የአዊዎች አጠራር (አሰያየም) ከአማርኛው የተለየ እንደሆነ በዝርዝር አስፍረዋል፡፡

የአገው ዘሮች በአንድ ላይ ይኖሩበት ከነበረው አካባቢ በተለያዩ ምክንያቶችና ዘመናት ከተለያዩ ቦታዎች መፍለሳቸውን በሚመለከት ከጽሑፋዊ ምንጮች ከተገለፀው ሌላ ከዋግ ላስታ ተነስተው በምን ምክንያት እንደሄዱ የዋግ ኽምራ አባቶች በአፈታሪክ የሚነገሩወን የተወሰነውን አንመልከት፡፡

> ቢለኖችን በሚመለከት በአፈ ታሪክ የሚተረከውን ተንተርሰው የሄዱት በዘመኑ (በሄዱበት ዘመን) የቀይ ባህርን ወደብ ዐርብ ፣ ጣሊያንና ቱርክ እንዳይሻገሩ ለመከላከል አስፈላጊ ስለነበር በአፄ ካሌብ ዘመነ መንግስት ወታደሮች በሰቆጣ አካባቢ ከሚገኘው ቤላ ተራራ ከሚባለው አካባቢ ተነስተው ለጥበቃ ሄዱ ፤ የአካባቢውም ለምለምነትና ተስማሚነት በማየት ከዚያው ለምደው ቀሩ፡፡ ቢለን የሚለውም ስየሜ የመነጨው ተነስተው ከሄዱበት ቦታ ቤላ ከሚባለው ተራራ ነው ይላሉ (አቶ አስራት ታደሰ ፣ ቃመ. 20/08/2011 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ ለመረዳች የሚቻለው የጉዞው ምክንያት ድንበር ለመጠበቅ ሲሆን የሄዱበት ዘመንም በፅሁፋዊ ምንጮች ከተገለፀው ዘመን ቀደም ብሎ በስድተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደሆነ ነው፡፡

አዊዎችን በሚለከት ደግሞ ከዋግ ተነስተው የሄዱበትን ቦታና ምክንያት አስመልክቶ በዋግ ኽምራ አባቶች የሚገለፀው የተለያየ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ሰቆጣ አካባቢ ከሚገኘው ብርብር ከተባለው ቦታ ተነስተው የሄዱት በችግር ምክንያት ነው፡፡ የሄዱበትም ቦት ጎጃም ለምለም ሆኖ ስላገኙት ቦታውን አቅንተው ከዚያው ቀሩ ሲል ፤ ሌሎች ደግሞ የሄዱት ከተለጅ ጉድያ እየሱስ ከተባለው ቦታ ነው፡፡ ሰባት ወንድማማቾች ለአደን ሄዱ ፣ የሄዱበትም ቦታ ለምና ማር የበዛበት በመሆኑ ወደ ዋግ ተመልሰው ወገኖቻቸውን ይዘው በመሄድ ሰባት ቤት አገውን አቀኑ፡፡ የተንቀሳቀሱበት ዘመን ደግሞ በዋግሹም ጅርወሰን ዘመን ነው (አቶ ደረበው ታረቀኝ ፣ ቃመ. 2011 ዓ.ም) ይባላል፡፡ ከዚህ

የምንረዳው በጽሁፋዊ ምንጮች የሰፈረው ለአዊዎች መንቀሳቀስ ምክንያት ነው የተባለው አደን አባቶች በአፈ-ታሪክ ከገለጹት ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት የሚመለከተው የዋግኽምራ ብሔረሰብ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ነዋሪ ከመሆኑም በላይ በቀደምት ጊዜ የሰፈረበትን ቦታ ያልለቀቀ መሆኑን እንረዳለን፡፡

አገዎች በአንድ ወቅት በኢትዮጵያ በከፍተኛ ስልጣን ላይ የነበሩ መሆናቸውን በታሪክ መዛግብት ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ስያሜ መንግስታቸውም የዛጉዌ ስርዎ መንግስት ሲሆን ዋና መድናቸውም ላሊበላ ነበር (Ullendorf, 1966 : 64; Wudu, 1995 : 7; Melakneh, 1990 ; 24)፡፡ የስርዎ መንግስቱን ስያሜ በሚመለከት የተለያዩ የታሪክ ፀሐፊዎች ሶስት የተለያየ ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ አንዳንዶቹ ከአገዎች ስያሜ ጋር የተያያዘ መሆኑን ሲገልፁ ፣ ሌሎች ደግሞ በትረ ስልጣኑን ጨብጠው ከነበሩት ሰዎችና ወደ ስልጣን ለመውጣት ካከናወኑት ድርጊት ጋር የተያያዘ ስያሜ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ከነእዚህ መካከል የተወሰኑትን እንመልከት፡፡ ተክለፃዲቅ (1966 ፣ 344) ስመ መንግስቱ ሁለት አይነት የስያሜ መነሻ እንዳለው ሲገልፁ ፣… ከዚህ በኃላ መራ ተክለ ሀይማኖት በኢትዮጵያ ነገሰና አዲስ ስርዎ መንግስት አቆመ፡፡ ስመ መንግስቱም ዛጉዌ ተባለ ፣ ዛጉዌ የተባለበትም ምክንያት እንደ ግማሾቹ ዘ አገው (የአገው ወገን) ማለት ነው፡፡ እንደ ግማሾቹ ደግሞ ድልናዖድን ስላባረረ ፣ ግዕዘኛውን ቃል ዘአጉየየ (ያባረረ) የሚለውን በመከተል ዛጉዌ ተባለ ይላሉ፡፡

የዛጉዌ ስርዎ መንግስት የስያሜ መነሻ ብቻ ሳይሆን ወደ ስልጣን የወጣበት ምክንያት ቢሆንም ጥርት ብሎ አለመቀመጡን የታሪክ ምሁራን በስራዎቻቸው አስፍረዋል (Gamst, 1968:12 and Bahru, 2002 : 8)፡፡ አያሌው (2007 ፣ 88) ደግሞ የአክሱም ዘመነ መንግስት ወደ ዛጉዌ ዘመነ መንግስት ሊሸጋገር የቻለበትን ምክንያት በሚመለከት በርካታ ምንጮችን እየጠቀሱ ከገለጹ በኂላ እሳቸው የሚስማሙበት ምክንያትነት ግን የተገለፀው የጋብቻ ጉዳይ የንጉሡ ልጅ መሶበ ወርቅ መራ ተክለ ሀይማኖትን አግብታ ከሚለው ይልቅ የአገዎች ሀይል እየበረታ መጥቶ በትረ ስልጣኑን በሽግግር መልክ ወይም በጦር ሀይል በመውሰድ መዲናቸውን በላስታ ዋግ አድርገው ከ300 ዓመታት የበለጠ ዙፋን ላይ ሊቀመጡ በቅተዋል የሚለው ተቀባይነት አለው፡፡

ተክለጻድቅ (1966 ፣ 331)ም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሀሳብ ገልፀዋል፡፡ ሌላው ደግሞ የዛጉዌ ስርዎ መንግስት ወደ ስልጣን የመጣበት ዘመን በትክክል በዚህ ዘመን ተብሎ በእርግጠኝነት አለመስፈሩን የታሪክ ምሁራን ገልፀዋል፡፡ ይህንን አስመልክተው (Sergew, 1972,40) የዛጉዌ ስርዎ መንግስት የተጀመረው በ1030 እና 1050 መካከል ሊሆን እንደሚች ማስላት እንችላለን ብለዋል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም ስልጣን ላይ የወጣው በተለያዩ ምክንያቶች ነው የተባለው የአገው ስርዎ መንግስት በተለያዩ የታሪክ ምሁራን የተገለፀው የተለያየ ነው፡፡ Taddesse (1972 :55) የዛጉዌ ስርዎ መንግስት የግዛት ዘመን በሚመለከት ሁለት የማይስማሙ አገላለፆች አሉ፡፡ የተለመደው ይኩኖ አምላክ በ1270 ስልጣኑን እስኪይዝ ድረስ ለ333 ዓመታት ቆይቷል የሚለው ሲሆን ፣ ሌላው ደግሞ 133 ዓመት ብቻ ነው የሚል ነው ሲሉ Lenvine (2000:71) ደግሞ የዛጉዌ ስርዎ መንግስት በ1135 ላስታ ላይ ተመሰረተና ለ135 ዓመታት ገዛ ይላሉ፡፡ Bahru, (2000 :71) ደግሞ በትረ ስልጣኑ ለ120 ዓመት የቆየ መሆኑን አስፍረዋል፡፡ Aymiro (1970 :5) ደግሞ በትረ ስልጣኑ የቆየባቸው ዓመታት 200 መሆናቸውን አስፍረዋል፡፡ ለዚህ ሳይሆን አይቀርም (Sergew, 1972,32) በማያያዝ የገለጹትም ስርዎ መንግስቱ የተጀመረበትንና ስልጣን ላይ የቆየበትን ዘመን ብቻ ሳይሆን በስርዎ መንግስቱ ወቅት የገዙት ንጉሦች መጠንም በትክክል አለመታወቁን ነው፡፡ ሶስት ዓይነት ዝርዝር አለ አጭር ፣ ረጅም እና በጣም ረጂም፡፡ "አጭሩ" አምስት ገዢዎች የያዘ ነው በማለት ዝርዝራቸውን አስፍረውታል፡፡ Melakneh (1990) ደግሞ ታዬን በመጥቀስ ከ920-1255 ለ333 ዓመታት 11 ነገስታት መግዛታቸውን ስም ዝርዝርራቸውንና እያንዳንዳቸውንም ስንት ዓመት ስልጣን ላይ እንደ ቆዩ በመግለፅ አስፍረውታል፡፡

በአጠቃላይ በአንድ ወቅት ከፍተኛ ስልጣን ላይ የወጣበት ምክንያትና የቆየበት ዘመን እንዲሁም የወረደበት በትክክል የማይታወቅ መሆኑን የታሪክ ምሁራን ሀሳባቸውን ቢሰነዝሩም አገዎች ታሪካዊ ህዝቦች መሆናቸውን ግን መገንዘብ እንችላለን፡፡

የድሮዋ ዋግ የአሁኗ ዋግኽምራ በጥንታዊ ህዝቦች መኖሪያነቷ ብቻ ሳይሆን በገዢዎቿም ትታወቃለች፡፡ የዋግ ገዢዎች ዋግ ሹሞች ይባሉ ነበር፡፡ ይህንንም Wudu (1995:14 እና 1998:228) በስራዎቻቸው አስፍረዋል፡፡ ዮሐንስ (1940 ፡ 223) ደግሞ

የተለያዩ አካባቢዎች ገዢዎች የሚገዙበት አካባቢ ገዢነታቸው እየተገለፀ ማዕረጉ ይሰጣቸው እንደነበር ፣ ዘላቂነት ያገኘው ግን የዋግ ሹሞች ብቻ እንደ ገዢዎች ዋግሹም ፣ ሽሬሹም ፣ ጉራጌሹም እየተባሉ ይጠሩበት ነበር። ነገር ግን የሌላዎቹ እየቀረ ሲሄድ የላስታው (የዋጉ) ዋግሹም እየተባለ ይኸው ከፍ ባለ ማዕረግ እስከ ጊዜያችን ደርሷል።

የዋግ ሹማምንትን አጀማመር በሚመለከት በጽሑፍ እና በአፈ ታሪክ የሚገለጸው የተለያየ ነው። የዋግኽምራ አባቶች ማዕረጉ የተጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደ ነበር መግለፃቸውን ነው አፀደ (1989፡21) ያሰፈራችው። እንደ አፈታሪኩ ከሆነ ዋግሹምነት የተጀመረው በዚህ ወቅት አካባቢውን ይመራ በነበረው በዋግሹም ሲራክ ነው።

ጽሁፋዊ ምንጮች ደግሞ የተለያየ ዘመን አስፍረዋል። የአንዳንዶቹ በ13ኛው ክፍለ ዘመን እና በ16ኛው ክፍለ ዘመን የሚል ሲሆን የሌላዎቹ ደግሞ 16ኛው ክፍለ ዘመን የሚል ነው። በ13ኛውና በ16ኛው ካሉት መካከል Wudu (1995,14 and 1998, 221) ይኸ ሹመት የተጀመረው በ1270 ዓ.ም የዛጉዌ ስርዎ መንግስት ተገርስሶ በሰለሞናውያን ሲተካ ነው የሚልና ሌላው ደግሞ በ16ኛው ክፍለ ዘመን የሚለው ከዋግሹም ዮናታን ጋር የተያያዘ መሆኑን የሚገልፀው ነው። ዋግሹም በግራኝ ጦርነት ላደረጉት ተጋድሎ የተሰጠ ማዕረግ ነው። ለክብሩም ሲባልም በአካባቢው፡-

ለክብረ መንግስቱ ቢዋጋ ዮናታን፣

ግምጃ ሱሪ ታጥቆ ታጠበ በዳታን።

የሚል ቃል ግጥም እንደተገጠመላቸው አስፍረዋል (Wudu 1995, 23)። ብርሃነ መስቀል (1951 ፣ 118-119)ም የዋግ ሹምነት ማዕረግ የላስታ ህዝቦች የግራኝ መሀመድን ወረራ ለመቋቋም ላደረጉት ግንባር ቀደም ተፋላሚነት ቃል ከተገባላቸው ውስጥ አንዱ በመሆኑ ነው ብለዋል።

ስለተጀመረበት ዘመን የሚገለፀው ቢለያይም እስከ 1966 የዘውድ አገዛዝ መውደቅ ድረስ አካባቢው ይተዳደር የነበረው በዋግሹሞች ነበር። ዋግ ሹምነት በወቅቱ ልዩ ክብር የሚሰጠው ማዕረግ ነበር። ይህንን አባቶች በአፈታሪክ ያገኙትን ጠቅሰው የገለጹትን አፀደ (1989 ፣ 24) እንደሚከተለው አስፍራዋለች፡-

የማዕከላዊ መንግስት ንግሥና በሚካሄድበት ወቅት ዋግሹሞች አንጋሽ ነበሩ። ለምሳሌ አፄ ኃይለሥላሴን ያነገሱት/ያለበሱት) ዋግሹም ከበደ ናቸው። ዋግሹሞች ስልጠናቸው የሚሻረውም ሆነ የሚፀናው በማዕከላዊ መንግስት ነው። ንጉሦች ግብር በሚያበሉበት ወቅት ወደ ግብር መግቢያው አዳራሽ በመጀመሪያ እንዲገቡ የሚጠሩት ዋግሹሞች ናቸው። በዋግሹሞችና በንጉሦች መካከል ጋብቻ ነበር። ይህም የዋግሹምነትን ትልቅነት ያሳያል።

Wudu (1995)ም ዋግሹሞች ከራሶች ይበልጥ በንጉሶች ዘንድ ልዩ ከበሬታ የሚሰጣቸው እንደነበሩ እንደሚከተለው ገልፀዋል።

ዋግሹሞች እስከ ቤተ መንግስቱ በር ድረስ የብር ነጋሪት ይጎስሙ ነበር። ዋግሹም ብሩም ወደ አፄ ሚኒሊክ ቤተ መንግስት ሲገቡ ለሌሎች የማይፈቀደውን ነጋሪታቸውን እስከ ቤተ መንግስት ቅጥር ግቢ ድረስ እየጎሰሙ ገብተዋል። ንጉሡ በሚታጠብበት የወርቅ ዳታን ይታጠቡ እንደነበርና በዚህም ዋግሹም ተፈሪ አፄ ዮሐንስ በታጠቡበት የወርቅ ዳታን መታጠባቸውን ፣ ግብር የማይገብሩ እንደነበር ፣ በብር ወንበርም ከንጉሡ ጎን እንደሚቀመጡ (Bekele, 1940)ን በመጥቀስም:-

ዋግሹም ለወንበር፣

ንጉሥ ለመንበር።

የሚል ቃል ግጥም እንደተገጠመ አስፍረዋል።

## 1.3. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ በአንፃራዊነት በልማት ወደ ኋላ የቀሩ የሚባሉ ሶስት ዞኖች ይገኛሉ። ለእነዚህ ዞኖች በልማት ወደኋላ መቅረት ምክንያት የሆኑ ብዙ ጉዳዮች ቢኖሩም አንዱና ዋነኛ የየዞኖቹ ማህበረሰቦች ባህል/ፎክሎር በወጉ ተጠንቶ የልማት ዕቅዱን ለማስተግበር የሚኖረው አስተዋፅኦ ግምት ውስጥ አለመግባቱ ይሆን የሚል አስተሳሰብ በውስጤ ካደረብኝ ቆይቷል። ይህ አስተሳሰብ እንዲያድርብኝና እንድገፋበትም ያደረጉኝ ምክንያቶች አንደኛው ስለ ባህልና ልማት ቁርኝት የሚያስረዱ

የተለያዩ ጽሑፎችን ማንበቤና ይልቁንም ደግሞ ዶ/ር ፊቃደ አዘዘ ይህንኑ ጉዳይ አስመልክተው በልዩ ልዩ ጽሑፎችና መድረኮች የሚሰነዝሯቸው ሃሳቦች ትኩረቴን ስለሳቡት ነው (ፊቃደ ፣ 1996 ፣ 2002 ፣ 2004[4] ፣ Sims & Stephens, 2005, Radcliffe, 2006; UNESCO, 2005, 2010)፡፡

ሁለተኛው በወልዲያ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ኃላፊ ሁኜ ስሰራ ለሥራ ጉዳይ ወደ ተለያዩ የሰሜን ወሎና ዋግኽምራ ዞኖች በምዘዋወርበት ጊዜ አንዳንድ አዳዲስ ቴክሎጂዎች ተቀባይነታቸውና ተግባራዊነታቸው እብዛም የሚሆነው ለማህበረሰቡ ባህልና አገር በቀል ዕውቀት እንግዳ ሲሆኑ መሆኑን በመታዘቤ ነው፡፡ ለአብነት ያህል በጋሽና እና አካባቢው ውጤታማ የሆነው የደጋ ፍራፍሬ አፕል ፣ ለቋሚ ተክሎች እንግዳ ለሆነው ለጋሽና እና መቄት አርሶ አደር ብዙም ትኩረት ሳይሰጠው “እኔ እምሞት ዛሬ ማታ ፤ ገብስ የሚደርስ በፍልሰታ” ዓይነት ጉዳይ አድርጎ እንደሚቆጥረው በማየቴ ነው፡፡

ሦስተኛው የዋግኽምራ ኅብረተሰብ የተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት ያልተሟሉለት ፣ ቋንቋውም ኽምጣኝ ከንግግር ቋንቋነት አልፎ በጽሑፍ ያልዋለና ያልዳበረ እንደነበር ይታወቃል፡፡ በዚህም ምክንያት በተለያዩ አጋጣሚዎች ወደ ቦታው ጉዞ ያደረጉ የውጭ ተመራማሪዎች ስለ ቋንቋውና ህዝቡ ጥንታዊነት በጨረፍታ ከመመልከታቸው በስተቀር ባህልና ወጉ አልተጠናም፡፡ ብሔረሰቡ ግን አሁንም ቢሆን የራሱን ባህልና ማንነት ጠብቆ የሚገኝ ነው፡፡ ይህንንም አያሌው (2007 ፣ 80) የዋግን መልካዓ ምድራዊ ምሽግነት ተገን በማድረግ የላስታ ዋግ አገዎች ነገዳዊና ቋንቋዊ ማንነታቸውን ኅብረተሰቡ ለረጅም አመታት ጠብቆ ያቆየው ወግና ባህል በወጉ በጥናት አልተገለፀም፡፡ የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት ባደረኩበት ወቅት ለመገንዘብ እንደቻልኩት በዋግኽምራዎች ፎክሎር/ባህል ላይ ጥናት የተደረገባቸው አራት የአንደኛ ዲግሪ እና አራት የሁለተኛ ዲግሪ እና አንድ የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያዎች ሲሆኑ ሶስቱ በስነ ቃል ይዘት ትንተና ላይ ያተኮሩ ከመሆናቸውም በላይ ፎክሎሩን/ባህሉን በጥልቀት ያዩ አይደለም ፤ በእርግጥም አይጠበቅባቸውም፡፡ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያዎች ቢሆኑም ከዞኑ የተወሰኑ አካባቢዎች

[4] ዶ/ር ፊቃደ ባህልና ልማት በሚል ርዕስ ሰኔ 18 ቀን 1996 ዓ.ም “የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር” ባዘጋጀው “የርዕይ 2020” መድረክና መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓ.ም “ፎረም ፎርሶሻል ስታዲስ” ባዘጋጁት መድረክና በ2004 ዓ.ም ባሳተመው መጽሐፍ ላይ ጉዳዩን በተደጋጋሚ አንስተዋል፡፡

በተወሰኑ የፎክሎር/ባህል ዘውጎች (በቃል ግጥም)፣ በክብረ በዓል ፣ እና በቁሳዊ ባህል ፣ በአለባበስና አጊያጊያጥ ላይ የተሰሩ ሲሆኑ የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያው እንዲሁ ከፎክሎር ዘውጎች በአንዱ በሆነው "የሽግግር ሥነ ሥርዓትና ደረጃዎች" በሚል የተሠራ ነው፡፡ በመሆኑም ብሔረሰቡን ለጥናት የመረጥኩበት የመጀመሪያው ምክንያት በፎክሎር መስክ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ደረጃ ያለው ጥናት ያልተካሄደበት አካባቢ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአሁኑ ጊዜ እየጎላ በመጣው ማህበረሰባዊ መስተጋብርና የዘመናዊነት እንቅስቃሴ የባህልና ልማት ቁርኝትና መስተጋብርን ለማህበረሰብ እድገት ያላቸውን አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ ለማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም ብሔረሰቡ ከትውልድ ትውልድ ሲወርድ የመጣውን ባህል ጠብቆና ማንነቱን በሚያንፀባርቅ መንገድ የሚተገብረውን ባህላዊ ሥራዎችን በዘመናዊነት ሰበብ እንዳይጠፉ በሚገኙበት ሁኔታ ጠቃሚነታቸውን ለማጎልበት አስፈላጊ መሆናቸውን ለማሳየት ነው፡፡ አራተኛው ምክንያት ደግሞ ማህበረሰቡ ሥራ ተግተው እንዳይሰሩ ተግዳሮት የሆኑ ልማዳዊ አባባሎችን ከዘመናዊነት አስተሳሰብ ጋር አስተሳስሮ የሥራ ባህሉን እንዲያጎለብት እና እነዚህ ልማዳዊ አባባሎች ላይ ያለውን የተዛነፈ እይታ መኖሩን በመገንዘብ ባህሉን የልማት መሳሪያ ማድረግ የሚቻልበት መንገድ ይኖር እንደሆነ ለመፈተሽና ለማረጋገጥ መፈለጌ ነው፡፡

ሌላው ከእነዚህ በተጨማሪ ለጥናት የመረጥኩበት ምክንያት በተለያዩ ምክንያቶች አንፃራዊ በሆነ መልኩ አካባቢውን ስለማውቀው ነው ፤ ምክንያቱም Wilson (1989 :228) እንደገለጹት አንድ የፎክሎር/ባህል ተመራማሪ መረጃውን በሚያውቀው ህዝብ አካባቢ ቢሰበስብ ጥናቱ ስኬታማ ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ ጥናት በሚከናወንበት ወቅት ጉልበትን ፣ አቅምንና ገንዘብን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡ ይኸውም ርዕሱን በሚመለከት በባህልና ልማት ውስጥ የሚካተቱ በርካታ ሁኔታዎች ቢኖሩም ይህ ጥናት የተመለከተው ግን ባህል የብሔረሰቡን የአኗኗር ዘይቤ ሊያሻሽል የሚችልበትን አዎንታዊ አበርክቶ ባህሉን በማሳደግ ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ (አዎንታዊ) ማሳየት እና በባህሉ ውስጥ ለእድገት እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉትንም እሴቶች ማሳየት ላይ ብቻ ነው፡፡

## 1.4 የጥናቱ አላማዎች

### 1.4.1 የጥናቱ ዋነኛ አላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሚገኙት ብሔረሰቦች መካከል የዋግኽምራ ብሔረሰብን ባህል/ፎክሎር በማጥናት የብሔረሰቡ ባህል/ፎክሎር በክልል አቀፍ ደረጃ በመንግስት ታቅደው እንዲተገበሩ የሚሰራጩ የልማት ዕቅዶችን ለመተግበር የብሔረሰቡ ባህል ለአካባቢው ልማትም ሆነ በልማት ወደኋላ መቅረት ያደረገው አስተዋፆ ወይም ተፅዕኖ ይኖር እንደሆነ መመርመርና ባህላዊ ጉዳዮችን የልማት መሳሪያ በማድረግ የአካባቢውን ልማት ለማሳደግ የሚቻልበትን መንገድ ለማሳየት ነው።

### 1.4.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

በዋነኛ ዓላማው ስርም የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ተነድፈዋል።

1. የዋግኽምራ ብሔረሰብ አጠቃላይ ፎክሎራዊ ዘውጎች ምን ምን እንደሆኑ ማጥናት፤
2. ፎክሎሩ ልማትን ለማፋጠን የሚያግዙ ምን ዓይነት ልማዶች እንዳሉት መመርመር፤
3. የመልማት ሂደቱን የሚገዳደሩ ወይም የሚያደናቅፉ ልማዳዊ ሁኔታዎ ካሉ መለየት፤
4. ያሉትን ምቹ ፎክሎራዊ ሁኔታዎችን እንደ ጥሩ መነሻ ቆጥሮ የሚታሰበውን ልማት ለማምጣት የሚቻልበትን መንገድ መግለፅ የሚሉት ናቸው።

## 1.5. የጥናቱ ጥያቄዎች

ከላይ በቀረበው ዋነኛ ዓላማ መሠረትም ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል።

1. የብሔረሰቡን ዋና ዋና ባህላዊ መገለጫዎች ምን ምን ናቸው?
2. ልማት በእነዚህ ባህላዊ ጉዳዮች ውስጥ እንዴት ይገለፃል ፣ ብሔረሰቡ ስለ ልማት ያለው አጠቃላይ እሳቤ ምን ይመስላል?

3. በዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህላዊ/ፎክሎራዊ መገለጫዎች ውስጥ ልማትን ለማፋጠን ያሉት አዎንታዊና አሉታዊ ነባር ልማዶች /Traditions/ የትኞቹ ናቸው?
4. ለብሔረሰቡ ልማት መፋጠን ነባር ልምዶችን በማልማት ምን አይነት መፍትሔ ማምጣት ይቻላል?

## 1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ ባህልና ልማት ያላቸውን የጠበቀ ቁርኝት አውጥቶ ለማሳየት የልማት እቅዶች ሲታቀዱና ለትግበራ ሲዘጋጁ ለብሔረሰቡ ባህል ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ጠቃሚ ማስረጃ በመሆን ያገለግላል፡፡ ለብሔረሰቡ መስተዳድር እንዲሁም ለክልሉ መንግስት ለብሔረሰቡ ትኩረት በመስጠት ባህሉ በወጉ ተጠንቶና ለልማት ያለው ጠቀሜታ ታውቆ ማህበረሰቡን ለልማት ለማነሳሳትና ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል መሳሪያ አድርጎ መጠቀም እንዲቻል የሚያሳይና የሚያነቃ መነሻ ማስረጃ የሚሰጥ ጥናት ይሆናል፡፡

በብሔረሰቡ በየደረጃው ላሉ መንግስታዊ ሆነ መንግስታዊ ላልሆኑ የልማት ድርጅቶች አስተባባሪዎቸና ባለሙያዎዎች እቅዳቸው ውጤታማ እንዲሆንና ተቀባይነት እንዲያገኝ በቅድሚያ የማህበረሰቡን ባህል ጠንቅቀው መረዳት ፣ ለባህሉ ዕውቅና መስጠትና ለማህበረሰቡ ባህላዊ ወይም ሀገር በቀል ዕውቀቶች /Indigenous knowledge/ ላይ ዕቅዳቸውን ለማስተግበር እንዲያስችል ጥናቱ መረጃ ይሰጣል፡፡

ፖሊሲ አውጭዎች ማንኛውም የልማት እቅድ ከማውጣታቸው በፊት በየአካባቢው ያሉ ባህላዊ ምቹ ሁኔታዎችንና ተግዳሮቶችን መረዳትና ትኩረት መስጠት እንደሚገባቸው ያስገነዝባል፡፡

የዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህል በአጠቃላይ እና አንዳንድ በመጥፋት ላይ ያሉ ልማዳዊ ድርጊቶች ጨርሰው ከመጥፋታቸው በፊት በቅርስነት ለማቆየት የራሱን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

ለተመራማሪዎችና በርዕሱ ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ ባለሙያዎች መነሻ መረጃዎችን ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 1.7. የጥናት አካባቢው መረጣና የጥናቱ ገደብ

ይህንን ጥናት ለማድረግ ከሚያስፈልገው ጊዜና ወጪ አኳያ በክልሉ ከሚገኙት ዞኖች ውስጥ በአንዱ ላይ አተኩሮ መሥራቱ የተሻለ ነዉ ብዬ ስላሰብኩ በክልሉ ከሚገኙት ዞኖች መካከል በዋግኽምራ ብሔረሰብ ላይ ብቻ አተኩሪያለሁ፡፡ ብሔረሰቡ የተመረጠበት ዋነኛ ምክንያት በክልሉ ከሚገኙ ብሔረሰቦች በአብዛኛዉ ባህሉን እና ልምዱን ጠብቁ በመያዙ የክልሉን ፎክሎራዊ/ባህላዊ ዘዉጎች ያሳያል ብዬ ስላመንኩ ነዉ፡፡ ይህንንም አያሌው (2007 ፤ 80)ሲገልፁ የዋግ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ በተከዜና በጥራሪ ወንዞች የተዘጋው ወይም የተከበበውን ፤ ለማድረስ የማይቻለውን የቦታውን የተፈጥሮ ምሽግነት ተገን በማድረግ የላስታ ዋግ አገዎች ነገዳዊና ቋንቋዊ ማንነታቸውን ሳያስበርዙ ሊያቆዩ እንደቻሉ ግልጽ ነው ብለዋል፡፡

የጥናቱን ወካይነት ለማጎልበትም የዋግኽምራ ብሔረሰብ ከሚኖርባቸዉ ሰባት ወረዳዎችና የሰቆጣ ከተማ አስተዳደርን ጨምሮ ነዉ፡፡ ይህም ስድስት የገጠር ወረዳዎችና አንድ የከተማ አስተዳደርን ጨምሮ ማለት ነ፡፡ ወረዳዎቹ የተምረጡበት ምክንያት ከጥናቱ አላማ ጋር በተያያዙ ከተማ ቀመሶቹ ወረዳዎች ለከተሜነትና ለዘመናዊነት አንፃራዊ በሆነ መልኩ ቅርብ ስለሆኑ የተለዬ ባህላዊ ሁኔታ ይታይባቸዉ ይሆናል ተብሎ ስለሚታሰብ ነዉ፡፡ ሰቆጣ ከተማ የተካተተበትም ምክንያት የዞኑ ዋና ከተማ ቢሆንም ለመንግስታዊ አስተዳደሩ ቅርብ የሆኑ ብዙ የገጠር ቀበሌዎች ያሉት በመሆኑ የተለዬ ባህላዊ ሁኔታ ይታይበት ይሆናል ተብሎ ስለታሰበ ነዉ፡፡ የገጠር ወረዳዎቹ አበረገሌ እና ሰሀላ ሰለምት በጣም ገጠራማ እና ለጎረቤት ክልል ትግራይ ቅርብ ቢሆኑም የብሔረሰቡ አካል በመሆናቸዉ ከዋናው ብሔረሰብ መኖሪያ ተዓማኒ መረጃ ለመሰብሰብ እንዲቻል ጠቃሚነታቸው ታምኖበት የተመረጡ ናቸዉ፡፡

ጥናቱ ስለ ባህልና ልማት ሲያነሳ የሚመለከተዉ የብሔረሰቡን መንፈሳዊም ሆነ ቁሳዊ ልማትን በመሆኑ በዚህ ረገድ በብሔረሰቡ ዘንድ ያሉ ባህላዊ ክንዋኔዎች ሁሉ ይዳሰሳሉ ፤ በተለይም ደግሞ የብሔረሰቡ የሥራ ፣ የቁጠባ ፣ ጥሪት የመቋጠር ፣ የመረዳዳት ፣ አብሮ የመኖር እና የማደግ ፣ የጤና አጠባበቅና የአኗኗር ዘይቤ ምን እንደሚመስል በተገኙት ባህላዊ ዘዉጎች መነሻነት የሚመረመር ይሆናል፡፡

ጥናቱ የሚያተኩረዉ በዋናነት በሀገር አቀፍ ደረጃ በመንግስት ታቅደው ወደ ክልሉ የሚሰራጩ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አተገባበሮች የገጠሟቸዉን ባህላዊ ምቹ ሁኔታዎችና ተግዳሮቶችን በመመርመር ላይ በመሆኑ በገጠር ልማት ላይ የሚያተኩረው የግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በጥናቱ የሚፈተሽ አንዱ ዋነኛ ጉዳይ ይሆናል፡፡

ኅብረተሰቡ አምራች ዜጋ እንዲሆንና እራሱንና አካባቢዉን እንዲያለማ ጤናዉ የተጠበቀ መሆን ስላለበት የጤናን ጉዳይ ከልማት ነጥሎ ማየት አይቻልም፡፡ ስለዚህም የኅብረተሰቡን ጤና አጠባበቅ የሚመለከተው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በጥናቱ የሚፈተሽ ሌላዉ ዋነኛ ጉዳይ ነው፡፡

ትምህርት ለአንድ ሀገር ልማት የሚኖረዉ ጠቀሜታ በቀላሉ የሚታይ ባለመሆኑ ስለልማት ሲነሳ የትምህርትን ጉዳይ መመልከት ተገቢና የማይታለፍ ጉዳይ እንደሆነ ይታወቃል ፤ ይሁንና ትምህርትን ከባህል ጋር አያይዞ ማጥናት እጅግ ሰፊና እራሱን ችሎ መጠናት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት በዚህ ጥናት ለማንሳት አልተሞከረም፡፡ ለዚህ ዋናው ምክንያትም ካለው የጊዜ ፣ የገንዘብና ጉልበት ውስንነት አኳያ ጥናቱ እንዳይሰፋ እና ተገቢዉን ጥልቀት ሳይዝ ላይ ላዩን እንዳይሄድ ከመስጋት የመነጨ እንጂ አስፈላጊ ሳይሆን ቀርቶ እና ካለመፈለግ እንዳልሆነ ከግምት ዉስጥ ገብቶ ይህም የጥናቱ ውስንነት እንደሆነ ተወስዷል፡፡

ጥናቱ ከግብርና ልማትና ከጤና ኤክስቴንሽን ዉጭ ያሉትን ሌሎች የልማት ፕሮግራሞችን አይመለከትም፡፡

## 1.8.የመስክ ገጠመኝ

ማንኛውም ተመራማሪ ለጥናቱ ግብአት የሚረዱትን መረጃዎች ወደ መስክ ወጥቶ በሚሰበሰብበት ወቅት ያልተገመቱ ምቹ ሁኔታዎችና ችግሮች ሊያጋጥሙት ይችላሉ፡፡ በዚህ ጥናትም ካጋጠሙት ዋና ዋናዎቹን ብቻ ማንሳት ወደፊት መስክ በመውጣት የባህል/ፎክሎር ጥናት ለሚያደርጉ ትምህርት/ልምድ ይሰጣል ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ ቀርቧል፡፡

### 1.8.1.ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎች

ይህን ጥናት ለማድረግ ወደ መስክ ስወጣ ብዙ ምቹ ሁኔታዎች አጋጥመውኛል፡፡ የመጀመሪያው የክልሉ መንግስት ሃላፊዎች ሆኑ የብሔረሰቡ አስተዳዳሪዎች የብሔረሰቡ ባህል እንዲጠና ያላቸው ከፍተኛ ፍላጎት ነው፡፡ ይህም ቀደም ሲል እንደገለፅሁት በ2009 ዓ.ም ለወረዳ ፎክሎር በተለይም ባህልና ልማት /Seminar on Folklore and Development /Folk 804) መረጃ ስብሰባ ወደ አካባቢው ስሄድ በቀናነት ተቀብለው የሄድኩበትን ዓላማ እንዲሳካ የክልሉ መንግስት ወደ ብሄረሰቡ መስተዳደር ደውለው የጥናቱን ዓላማ በመግለፅ አስተዋውቀው የምፈልጋቸውን ማንኛውንም ባህላዊ /ፎክሎራዊ/ መረጃ እንዲሰጡኝና እንዲተባበሩኝ አድርገዋል፡፡ የዞኑ አስተዳደሪም ከዞኑ ዋና ከተማ ሰቆጣ ስደርስ መኪና በመላክ ወደ ቢሯቸው አስመጥተውኝ በደስታ ተቀብለውኛል፡፡ በመቀጠልም የመጣሁበትን ዓላማ አዳምጠው አስፈላጊውን ቁልፍ ሰዎች ራሳቸው ስማቸውን ሰጥተውኝ በስልክም ጠርተው አስተዋውቀውኛል፡፡ በመሆኑም የዞኑ አስተዳዳሪ ከፍተኛ ርዳታ ያደርጉልኝ ዋነኛው ሰው ናቸው፡፡

አስተዳዳሪው ያስተዋወቁኝ ሰውም የዞኑ ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ የሆኑትን አቶ ባዬ አስምሮም ናቸው፡፡ ይህም ሰው ወዲያውኑ የብሔረሰቡን ባህል ፣ አኗኗር ዘይቤ የሚያውቁትን አቶ ደርበው ታረቀኝን ፣ አቶ አስራት ታደሰንና መምህርት ወርቃፈራሁ ቸኮልን ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች የብሔረሰቡ ተወላጅ ሲሆኑ ያኔም ሆነ በተደጋጋሚ ለመረጃ ስብሰባ በምወጣበት ሁሉ ያለአንዳች ማቅማማት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የግል ስራቸውንም ሳይቀር እየተው ከእኔ ጋር ሳይለዩ ከብሔረሰቡ ጋር ስቀላቀል ዓላማዬን በማስረዳት የምፈልገው መረጃ እንዲሰጡኝ በማድረግ መረጃ ሰጪዎችን አፈላልገው በማገናኘት ፣ ራሳቸውም መረጃ በመስጠት ፣ መንገድ በመምራት ፣ በኽምጣንኛ መረጃ የሚሰጡኝ ሲገጥሙኝ ራሳቸው በመተርጎም ፣ የማድርበትን ፣ የምመገበውን ፣ በግል የሚያስፈልገኝን ሁሉ በማመቻቸት አስቸጋሪ ሊሆኑብኝ የሚችሉ ሁሉ ምቹ እንዲሆ አድርገውልኛል፡፡

የአካባቢው ማህበረሰብም ደግ ፣ ገር ፣ እንግዳ ተቀባይና አክባሪ በመሆኑ ለግል ስራዬ እንደሄድኩ ሳይሆን እነሱን ለመጠየቅ እንደመጣሁ በመቁጠር ማወቅ የምፈልገውን ሁሉ እንድጠይቅ ፣ እንድመለከት ፣ እንድሳተፍ በድምፅም ሆነ በምስል እንድቀርፅ ያለምንም

መጠራጠር ፈቃደኛ ሁነውልኛል፡፡ ለሙከራና ለዋናው ጥናት ተመልሼ ናፍቀውኝ ልጠይቃቸው እንደመጣሁ በመቁጠር ስራዬን ሁሉ ምቹ አድርገውልኛል፡፡ በየምዘዋወርበት ቀበሌ ሁሉ በደስታ በመቀበል ወደ ቤታቸው ገብቼ እህል ውሃ እንድቀምስ የሚያደርጉት ጥያቄ በፍጹም ገርነት ፣ የዋህነትና ደግነት ነው፡፡

በመረጃ ስብሰባ ወቅት መረጃ ሰጪዎቼ ከተወሰኑ አንዳንድ ቦታዎች በስተቀር በአብዛኛው ለሚሰጡኝ መረጃ ገንዘብ አለመጠየቃቸው ዋነኛው ምቹ ሁኔታዎች ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡ አልፎ አልፎ ለሚደረጉ ባህላዊ ክዋኔዎች የሚያስፈልጉ አነስተኛ ነገሮች መግዢያ ካልሆነ ያን ያህል የጎላ የገንዘብ ጥያቄ አልቀረበልኝም፡፡

አንዳንዴ ከስራቸው ላይ አስነስቼ /የጌጣጌጥ ባለሙያዎች ፣ ብረት ቀጥቃጮች ፣ ወዘተ/ያመጣኋቸው ከሆነ በጣም በማፈርና በመሽቆጥቆጥ የስኳር መግዣ ወይም ለዕለት የቸገራቸው ነገር ካለ እንድሰጣቸው በግልፅ ጠይቀውኛል ፤ እኔም ይበቃል ያልኩትን ስሰጣቸው "እግዚያብሄር ጨምሮ ጨምሮ ይስጥህ ሀሳብህ ይሙላ" ብለው ከመመረቅ በቀር አነሰኝ ብለው የተከራከሩኝም ሆነ ፊታቸውን ያጠቆሩብኝ የሉም፡፡ የብሔረሰቡ አካባቢም ሆነ ነዋሪው ፍጹም ሰላማዊ በመሆኑ በምንቀሳቀስበት ቦታ ሁሉ ምንም አይነት የደህንነት ስጋት ሳይገጥመኝ በሰላም ስራዬን አጠናቅቁ ለመመለስ ረድቶኛል፡፡

## 1.8.2. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

ምንም እንኳ ቀደም ሲል የተገለጹት አዎንታዊ /ምቹ ገጠመኞች ቢኖሩም አሉታዊም ገጠመኞች አልጠፉም፡፡ ከእነዚህ አሉታዊ ገጠመኞች መካከል በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሰው ባህላዊ ሥነ ሥርዓቶች የሚከወንባቸው የገጠር ቀበሌዎች ወጣ ገባ ፣ በጣም ሞቃታማ ፣ ርቀት ያላቸውና የመኪና መስመር ያልገባባቸው መሆናቸው ነው፡፡ ይህንን መሳይ መንገድም በመስክ መኪና መጓዝ ስለማይቻል በእግር መጓዝ የግድ ነበር፡ ፡ መንገዱ ከርቀቱም በተጨማሪ ገደላማና ወጣ ገባ በመሆኑ ለኔም ብቻ ሳይሆን ለተከራየኋቸው የካሜራ ባለሙያዎችም በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ በዚህም በድካም ምክንያት በሚቀጥሉት ተከታታይ ቀናት ወደ መስክ ለመጓዝ አልችልም ነበር፡፡

ሁለተኛው ተግዳሮት ደግሞ አብዛኛዎቹ የዞኑም ሆነ የወረዳ አስተዳደር አካላት መኪና ለመተባበር ፍቃደኛ ቢሆኑም መረጃ ለመሰብሰብ ወደምሄድባቸው ቦታዎች የሚገቡ

መኪናዎች ዓይነት የተወሰኑ መሆናቸው ባህላዊ ክዋኔዎቹ በሚከወኑበትና በፈለግሁት ጊዜ ለማግኘት አልቻልኩም ፤ ሊተባበሩኝ እንደሚችሉ ከገለፁልኝ በኋላ ድንገተኛ መስክ የሚያስወጣ ስራ ማጋጠም ሌላው ተግዳሮት ነበር፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ቅድሚያ የሚሰጡት ለመንግስት ስራ ነውና ፤ ያንን በመተው ለኔ ሊሰጡኝ ስለማይቻላቸው የመስክ ጉዞ የተሰናከለበት ወቅት ነበር፡፡

ሶስተኛው ለመረጃ አሰባሰብ አስቸጋሪ የነበረው በገጠር ቀበሌዎች የመብራት አገልግሎት አለመኖር ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የሰርግ ሥነ ሥርዓት ሂደት ክዋኔዎች የሚካሄዱት በሙሽራዋ ዳስ ውስጥ የወንዱ ሙሽራ ወገን ከገባ በኋላ ነው፡፡ ይህም በአብዛኛው ከምሽቱ ከሶስትና ከአራት ሰዓት በኋላ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሰርግ ሥነ ሥርዓቶቹን ሂደት ሙሉ ለሙሉ ለመቅረፅ እንዲሁም ፎቶ ለማንሳት አልቻልኩም፡፡ በተለይም በሴት ዳስ ውስጥ የሚከናወነውን የጋብቻ ውል መረጃ የሰበሰብኩትና የስርዓቱን ሂደት ለመረዳትና ለመግለፅ የቻልኩት በምልከታና ማስታዎሻ በመያዝ ነው፡፡

አራተኛው አስቸጋሪ ገጠመኝ ከቀረፃ ጋር ተያይዞ የነበረው የማህበረሰቡ የግንዛቤ ችግር ነው፡፡ ለምልከታና ለቀረጻ በሄድኩባቸው ቦታዎች ስለቀረጻ አስፈላጊነት ግንዛቤ ያላቸው አንዳንድ ሰዎች ቢያጋጥሙኝም አብዛኛው ሰው ግን ጥሩ አመለካከት አልነበረውም፡፡ በዚህም ምክንያት በተለይ በሀዘን የቀብር እና የአኀበር ሂደትን ለመቅረፅ አስቸጋሪ ነበር፡፡ ለመቅረፅና ፎቶ ለማንሳት ፍቃደኝነተታቸውን ስጠይቅም አሉታዊ መልሳቸው "ደስታ እንጂ እንዴት ሀዘን ይቀረፃል" የሚል ነው፡፡ ፎቶ ለማንሳትና ለመቅረፅ ፍቃድ ያላገኘሁበትን በምልከታና ማስታወሻ በመያዝ መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ አንድ የለቅሶ ክዋኔ ግን የተማሪዬ ዘመድ በመሆኑ ሀዘንተኞቹን በማግባባታቸው የተወሰነ ቀረፃ ለማድረግ ችያለሁ፡፡

አምስተኛው አሉታዊ የመስክ ገጠመኝ የወሊድ ሥነ ሥርዓትን የሚመለከት ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ እናቶች በጤና ተቋማት መውለድ እንደሚገባቸው እየተነገረ ነው፡፡ ይሁን እንጂ መረጃ ለመሰበሰሰብ በሄድኩበት አካባቢዎች በቤት ውስጥ የሚከናወን የወሊድ ሥነ ሥርዓት ገጥሞኛል ነገር ግን ስርዓቱን እንድመለከት እንጂ እንድቀርፅም ሆነ ፎቶ እንዳነሳ አልተፈቀደልኝም ፤ ለዚህም ምክንያቱ የቀረፃውም ሆነ የፎቶ መረጃ በጤና ተቋም ያልወለዱትንና ቤተሰቦቻቸውን ችግር ላይ ይጥላል በሚል ስጋት ነው፡፡ እኔም

መረጃ አቀባዬች ችግር ያደርሱብናል ያሉትን መረጃ በማስገደድ መቀበል አግባብ ባለመሆኑ መረጃውን በምልከታና በቃለ መጠይቅ አሟልቼዋለሁ፡፡

ስድስተኛው ምቹ ያልሆነ ገጠመኝ ሙሽራዋ ከወንዱ ሙሽራ በሚላክላት አልባሳትና ጌጣጌጥ ከማጌጧ አስቀድሞ ሙሽራዋን ለመመልከት ፍቃድ አለማግኘቴ ነው፡፡ የዚህ ክልከላ ምክንያትም አንደኛው ያለ እድሜና ያለ ምርመራ የሚካሄድ ጋብቻን የምቆጣጠር መስሏቸው ሲሆን ሌላው ምክንያት ደግሞ ሙሽራዋ ጋር ወደ ዳስ ከመግባቷ በፊት ሌላ ሰው ሊያያት አይችልም በሚል ልማዳዊ አስተሳሰብ ምክንያት ነው፡፡ ይህም ክዋኔ የሚከናወነው ቀደም ሲል እንደተገለፀው በጨለማ በመሆኑ መረጃውን በምልከታና በቃለ ምልልስ ከማግኘት ውጪ ፎቶ ለማንሳትም ሆነ ለመቅረፅ አላስቻለኝም፡፡ በዚህ ምክንያት ከአንድ ሰርግ በስተቀር ሙሽራዋ በእናት ወገን ታዝላ ስትወጣ ለመቅረፅም ሆነ ፎቶ ለማንሳት አልቻልኩም፡፡ ይህንን ክፍተትም ከወረዳ ባህልና ቱሪዝም ፅህፈት ቤቶች ምስሎችን በመውሰድ አሟልቻለሁ፡፡

ሰባተኛው አሉታዊ ገጠመኝ ብዬ የያዝኩት መረጃ አቀባዬች ለአንዳንድ ድርጊቶች መከወን ምክንያቱን እንዲገልፅልኝ ስጠይቃቸው ትክክለኛውን በግልፅ ከመናገር ይልቅ የማቅማማት ሁኔታ ይታይባቸዋል፡፡ እውነቱን ለመናገር ይቸገራሉ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በወቅቱ ከሚሰጣቸው የስልጠና ይዘት ጋር የሚጋጭ መስሎ ከታያቸው ሲሆን ምክንያቱን ቢያውቁትም "ከአያት ቅድመ አያቶቻችን የወረስነው ባህል ስለሆነ ነው" የሚል ድፍን ያለ መልስ ሰጥተውኛል፡፡ ለአብነት ያህል ወደ ብረት ቀጥቃጭ ቤት ሲኬድ ለምን ምስር ይያዛል ፣ ሙሽሮቹ ወንዝ ሲሻገሩ ለምን ጫጩት ይታረዳል ፣ ሙሽራው ወደ ሙሽራዋ ዳስ ሲገባ ለምን በአመድ ይረጫል ፣ ወዘተ ለመሳሰሉት ጥያቄዎች የሰጡኝ መልስ "ከአባቶቻችን የወረስነው ባህል ነው" የሚል ነው፡፡ ለእነዚህ አይነት ጥያቄዎች መልሳቸውን ለማግኘት በቡድን ተኮር ውይይት ባደረኩበት ወቅት ተወያዬችን በአንክሮ በመከታተል በሚያካሂዱት ውይይት ወቅት ትክክል ነው የሚሉትን በክርክሩ ወቅት ለማግኘት ችያለሁ ፤ ለዚህም የተፈጠረውን የመረጃ ክፍተት ለመሙላት ችያለሁ፡፡

## 1.9. የጥናቱ ስነ-ምግባር

የአንድን ማህበረሰብ ባህል ወይም ፎክሎር የሚያጠና ተመራማሪ ጥናቱን በሚያካሂድበት ወቅት መረጃ የሚሰጡ ፣ የሚያስተረጉሙ ፣ የጥናቱን አካባቢ ምቹ የሚያደርጉ ፣ መንገድ የሚመሩ ፣ ወዘተ ሰዎች እገዛና ትብብር እጅጉን አስፈላጊ ነው፡፡ የእነዚህ ሰዎች ቀና ትብብር ሳይጨመርበት የተዋጣለት ምርምር ማድረግ አይቻልም፡፡ በመሆኑም መረጃዎችን ለመሰብሰብ ወደ መስክ በሚወጣበት ወቅት መረጃ የመሰብሰብ ሂደቱ ፣ ትንታኔውና የጥናቱ ውጤት ስኬታማ ይሆን ዘንድ በማህበረሰቡ መታመንና ወግና ባህላቸውን ጠብቆ መቆየት ተገቢውን ከበሬታ መስጠትና የጥናቱን አላማ በግልፅ ማሳወቅ ከተመራማሪው የሚጠበቁ ስነ ምግባሮች ናቸው (Dawson, 2002)፡፡

Goam (2008 : 365) በበኩላቸው የጥናትና ምርምር ስነ ምግባር ... የተመራማሪውን መልካም ምግባር መላበስና መረጃ የሚቀበሉባቸውን አካላት አደጋ ላይ እንዳይወድቁ መጠበቅን እንደሚገባ ይገልፃሉ፡፡ ስነ ምግባራዊ ጉዳቶች ከጥናቶቻችን መጀመሪያ ጀምሮ የጥናቱ ሪፓርት እስከሚፃፍ ድረስ ተግባር ላይ የሚውል ጉዳይ ነው፡፡ ይኸውም ስነ ምግባራው ጉዳዮች ከጥናታዊ ጥያቄዎችን ከማዘጋጀት ጀምሮ ናሙና ስናካሂድ ፣ መረጃ አቀባዮችን ስናገኝ ፣ መረጃ ስንሰበስብ ፣ ስንተነትን እና ስንፅፍ ሁሉ ጠቃሚነታቸው የጎላ ነው (Seale, 2005 : 116)፡፡ Jensen (1983 : 253) በበኩሉ ደግሞ የምርምር ስነ ምግባር የሚመለከተው መረጃ አቀባዩንና ተመራማሪውን ብቻ ሳይሆን ወደፊት ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ ፣ የጥናቱ ውጤት ተሳታፊዎችና የትምህርት መስኩ አካላትንም እንደሚጨምር ይገልፃሉ፡፡

በመሆኑም የጥናትና የምርምር ስነ ምግባር ተመራማሪው መረጃውን ከመሰብሰቡ በፊት ፣ በሂደትና በኋላ በሚተገበሩ የምርምር ደረጃዎችና ሂደቶች የሚቀጥሉ እንጂ ለአንድ አፍታ ስራ ላይ ውሎ የሚዘጋ አይደለም (Creswell, 2009; 92-93)፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ ተኣማኒነትን ለማግኘት አጥኚው ስለጥናቱ ዓላማ በግልፅ ማስረዳት ተገቢ ነው፡፡ ለዚህም የመጀመሪያ ስራ የሚሆነው የተጠኚዎቹን መረጃ የመስጠት ፈቃደኝነት ማረጋገጫ ለማግኘት በየደረጃው ላሉ የመንግስት አስፈፃሚ አካላት የጥናቱን ዓላማ በማስረዳት ፈቃድና ትብብራቸውን መጠየቅ ነው፡፡ ወደ ማህበረሰቡ ዘንድም ሲገባ እንዲሁ በግልፅ የምርምሩን ዓላማ ገልፆ እና መረጃ የመስጠት ፈቃዳቸውን አግኝቶ

መግባት ተገቢ በመሆኑ ለዚህ ጥናት መረጃ ስብሰባ ወደ አካባቢው በሄድኩ ቁጥር ከትምህርት ክፍሉ ደብዳቤ ለብሔረሰቡ መስተዳድር ዞን እያፃፍኩ ነበር፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው በመጀመሪያ ከዩኒቨርስቲው /ትምህርት ክፍሉ/ የተፃፈልኝን የትብብር ደብዳቤ ለዋግኽምራ አስተዳደር ዞንና ፣ ለሰባቱም ወረዳ አስተዳደር ፅህፈት ቤቶች እና መረጃ ለምሰበስብባቸው የተለያዩ ስፍራዎች የቀበሌ አመራሮች በማሳየትና የጥናቴን ዓላማ በማስረዳት እና ግልፅ በማድረግ የመረጃ አሰባሰብ ሂደቴ እንዲመቻች አድርጌያለሁ፡፡ ተጠኚዎቹም መረጃ ከመስጠታቸው በፊት የጥናቴን ዓላማ አሳውቄያቸዋለሁ፡፡

በመሆኑም መረጃ አቀባዮቼ የሚሰጡኝ መረጃ ለምን እንደሚውል በማስረዳት መረጃ ለማቀበል ፈቃደኝነታቸውን በቃል እንዲያረጋግጡልኝ አድርጌያለሁ፡፡ የመረጃ መሰብሰብ ሂደቱን በግልፅ እንዲያውቁት ለማድረግ መረጃ የምሰበስበው በመቅረፀ ምስልና ድምፅ ፣ እንዲሁም በፎቶ ካሜራ በመታገዝም እንደሆነ አሳውቄያቸዋለሁ ፤ የተቀበልኩት መረጃም በትክክል መረጃ አቀባዮቼ እንዲያደምጡት አድርጌያለሁ፡፡ መረጃ በምሰበስብበት ወቅት የአካባቢውን ወግና ባህል በመጠበቅ ፣ ማህበረሰቡ የሚያስደስተውን ተግብሬያለሁ ፣ ከሚያስከፋውም ተቆጥቤያለሁ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ መረጃ አቀባዮቼ ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ መረጃ ስላቀበሉኝ እና መንገድ በመምራትና በማሳየት የረዱኝን ለማበረታቻ እንዲሆን ለተወሰኑት የተወሰነ ገንዘብ ሰጥቻለሁ፡፡ ለአንዳንዶቹ ደግሞ በስጦታ መልክ ለሽማግሌዎች እና ለቄሶች ጋቢ ፣ ለሴቶች ያልተሰፋ ጨርቅ ፣ ወጣት ለሆኑት ደግሞ ቁምጣ ሱሪ ፣ ሸሚዝ ፣ ዓይነቶችን በመግዛት ሰጥቻለሁ፡፡ በዚህም አድራጎት ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር እጅጉን ለመግባባት ችያለሁ፡፡ የተደረገላቸውንም ትንሽየ ነገር በአክብሮት ተቀብለው እነሱ ያደረጉትን ትልቅ ተግባር ከምንም በመቁጠር ከኔ የተሰጠውን አግዝፈውና ትልቅ ውለታ እንደሆነባቸው ከልባቸው ታላቅ ምስጋና ያቀርቡልኝ ነበር፡፡ በተደረገላቸው ስጦታ በጣም ተደስተው ለመናገር ሁሉ እምባ ያንቃቸው ነበር፡፡ በዚህም እኔም ለእነሱና ለአካባቢው ማህበረሰብ ያለኝ አድናቆት በቃላት ከምገልፀው በላይ ሆነብኝ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# 2. ክለሳ ድርሳን

## 2.1. የተዛማች ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ምዕራፍ ዋና ትኩረት ከጥናቱ ጋር ቁርኝት ያላቸውንና ቁልፍ ሚና ለመጫወት በተደጋጋሚ የሚነሱትን ባህል ፣ ልማት ፣ የባህልና የልማት ትስስር ፣ ግብርና እና ጤና ኤክስቴንሽን የሚሉትን ፅንሰ ሃሳቦች ምንነት ማብራራት እና መተርጎም ይሆናል፡፡

በዚህ ምዕራፍ በጥናት ርዕሱና በዋግኽምራ ብሄረሰብ ባህል ዙሪያ የተሰሩ የቀደሙ ጥናቶች ይከለሳሉ ፤ ይህም በመሆኑ ጥናቱ ከሌሎቹ የሚለይበት እና ይዞት የተነሳውን አዲስ ጉዳይ ለማሳየት ይጥራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ የሚመራባቸው ንድፈ ሀሳባዊ መሰረቶችን ምን ምን እንደሆኑ ይቃኝበታል፡፡

በዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህል ወይም ፎክሎር ላይ በተለይም የጥናቱ ርዕስ በሆነው ባህልና ልማት ላይ የሚያተኩሩ ጥናቶች በጣም ውስን ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በብሄረሰቡ ፎክሎር ላይ የሚያተኩሩ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሁፍ ፣ በውጭ ቋንቋዎች (በ Applied sociology, በ Social antropology) ትምህርት ክፍሎች አራት የመጀመሪያ ዲግሪ ፣ ሶስት የሁለተኛ ዲግሪ እና አንድ የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፎች ተገኝተዋል እነዚህ ስራዎች ከዚህ ጥናት ርዕስ ጋር በቀጥታ የሚዛመዱ ባይሆኑም በፎክሎር /በባህል/ ዙሪያ በመሆናቸው እና ብሔረሰቡን የሚመለከቱ በመሆናቸው እዚህ ላይ መጠቀሳቸው ተገቢ ይሆናል፡፡ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የተሰሩ ሶስት ጥናቶችና በApplied sociology ትምህርት ክፍል የቀረበውን አንድ ጥናታዊ ፅሁፍ ስንመለከት መኮንን አለማየሁ በ1974 የዋግ አውራጃ አማርኛ ግጥሞች ፣ ማሞ ቢህለ በ1988 ዓ.ም በሰቆጣ ከተማና አካባቢዋ የረሀብ ግጥሞች ጥናት እና ታደሰ እሸቱ በ1997 ዓ.ም በሰቆጣ ከተማና አካባቢዋ የረሀብ ግጥሞች ይዘት ትንተና በሚሉ ርዕሶች የተሰሩና የHailemariyam Kebede 1983 “Cultural and Economical Life of the Agew People of Wag Awraja” በሚሉ ርዕሶች ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟይ ጥናታዊ ፅሁፍ ተገኝተዋል፡፡ እነዚህ ጥናቶች የብሔረሰቡን የቃል ግጥሞች ወይም የሻደይ እንዲሁም የቃል ግጥሞችን አይነትና ገፅታ

በመግለፅ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ከተዘረዘሩት ውስጥ የዚህ ጥናት ትኩረት በሆነው በዋግኽምራ ብሄረሰብ የባህልና የልማት አስተዋፅኦ (አወንታዊና አሉታዊ) የሚሉት ነገር የላቸውም፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስል ነገር የላቸውም፡፡ በዚህ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ጥናቶች ደግሞ የአፀደ ተፈራ “በሰቆጣ ከተማና አካባቢዋ የክብረ በዓላት አከባበርና ባህላዊ ጨዋታዎች” በ1996 ዓ.ም በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን ይህ ጥናት የሶስት ክብረ በዓላት የፍልሰታ በዓል አከባበርና የሻደይ ጨዋታ ፣ የመስቀል በዓል አከባበርና ባህላዊ ጨዋታዎች እና የጥምቀት በዓል አከባበርና ባህላዊ ጨዋታዎች በተፈጥሮአዊ መቼት በመቅረፀ ምስልና ድምፅ እና በፎቶግራፍ በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ አውዳዊ ክዋኔያቸው የተገለፀበት ጥናት ነው፡፡ በክብረ በዓል ወቅት የሚገጠሙ ከ460 በላይ የሆኑ የቃል ግጥሞች ተሰብስበው ዘጠናዎቹ ምደባ ተካሂዶባቸዋል ፤ ጭብጣዊ ትንታኔም ተደርጎባቸዋል፡፡ 278 የቃል ግጥሞች ደግሞ በአባሪነት ተይዘዋል፡፡ አጥኝዋ የሰቆጣ ነዋሪን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን ሲገልፁ የወሊድ ፣ የጋብቻንና የሞት ፣ ሥነ ሥርዓቶችንም በጥልቀትም ባይሆን በወፍ በረር ቃኝተዋል፡፡ የተመለከቱትም የሰቆጣ ከተማ ዙሪያ የሚገኙትን ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ነገር የለም፡፡ ቢኖር በመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ብቻ ነው፡፡ ያሬድ ተፈራ 2002 ዓ.ም በሰቆጣና በአበርገሌ ገጠራማ ወረዳዎች የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና የአጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች በሚል ርዕር በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍና ፎክሎር የቀረበ ጥናት ነው፡፡ አጥኚው መረጃቸውን የሰበሰቡት ወደ ጥናት ቦታው በመሄድ ፎቶ ፣ መቅረፀ ምስልና ድምፅ በመጠቀም ነው፡፡ ጥናታቸው ያተኮረውም በቁሳዊ ባህል አልባሳትና ማጋጌጫ ነገሮች ላይ ነው፡፡ የያሬድ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በመረጃ አሰባሰብ ዘዴው እና ከፎክሎር ዘውግ አንዱ የሆነውን ቁሳዊ ባህልን ማጥናታቸው ሲሆን ልዩነታቸው ደግሞ የኔ ጥናት የብሔረሰቡን አጠቃላይ ባህላዊ ወይም ፎክሎር ዘርፎችን በመሰብሰብ ባህል ለልማት ያለውን አወንታዊና አሉታዊ አበርክቶ ማሳየት ላይ ነው፡፡ በጥናት ቦታውም ላይ ቢሆን ልዩነት አለ፡፡ የኔ ጥናት በዞኑ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ወረዳ የሚዳስስ ሲሆን የሌሎቹ የተጠቀሱት ጥናቶች ሁሉ አንድን ወረዳ ብቻ የተመለከተ ነው፡፡ Alebachew Merka (2007) “Socio Economic and Political Issues in Wag Hemra Oral Poetry” በሚል ርዕስ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለውጭ ቋንቋዎች ትምህርት ክፍል የቀረበ ነው፡፡

ጥናቱ በወቅቱ በዋግኽምራ ዞን በነበሩት ሶስት ወረዳዎች ከሰላሳ ሰዎች ከእያንዳንዱ ወረዳ አስር አስር ሰዎችን በመረጃ አቀባይነት በመጠቀም በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ በተሰበሰበው መረጃዎች ላይ ተመስርቶ የተጠና ጥናት እንደሆነ አጥኚው ገልፀዋል፡፡ ይህ ጥናት በብሔረሰቡ ባህል በሆነው ቃል ግጥም ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በዚህም ቃል ግጥሞች ማህበረ ምጣኔ ሀብታዊ እና ፓለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ሁኔታ መመልከት ላይ ያተኮረ ሲሆን የኔ ጥናት ግን የፎክሎርን አራት የዘውግ አይነቶች በመተንነንና በመተርጎም ፎክሎር በልማት ላይ ያለውን አስተዋፅኦ ማሳየት ላይ ነው፡፡ በዚህም በሰፊው እንለያያለን፡፡

ሌላው Andenet Gizachew (2010) "Development Induiced Displaement and Impoverishment: the case of Tekeze Hydro Power Project and It's Impacts on the Affected Villages of Wag Hemra Zone, North East Ethiopia" በሚል ርዕስ በ Social Antropology ለሁለተኛው ዲግሪ ባጠኑት ጥናት የዋግኽምራ ዞን ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ዳራ የተመለከቱበት ንዑስ ክፍል በመጠኑም ቢሆን ከኔ ጥናት ጋር ይቀራረባል፡፡ በኔ ጥናት የብሔረሰቡን ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ዳራ ችግርን ከግብርና ኤክስቴንሽን ጋር ተያይዞ ከተጠናው ክፍል ጋር ይመሳሰላል፡፡ ነገር ግን በአሰራር ዘዴው ፣ በንድፈ ሀሳብና በጥናት አላማው ከፍተኛ ልዩነት አላቸው፡፡ በዚሁ ትምህርት ክፍል ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ደግሞ የአፀደ ተፈራ "የዋግኽምራ ዞን የወሊድ ፣ የጋብቻ እና የሞት ሥነ ሥርዓቶች ክዋኔዎች" በዘመናዊነትና በሉላዊነት ሰበብ ሙሉ በሙሉ ሳይለወጡና ሳይጠፉ አውዳቸውን መሰረት በማድረግ በመቅረፀ ምስልና ድምፅ በፎቶ ካሜራ መረጃ በመሰብሰብ እንዲቀረፅ በማድረግ ፣ ፋይዳቸውን መግለፅና ለውጥና ቀጣይነታቸውን መተንተን እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ይህ በመሆኑ የተጠቀሱት የወሊድ ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ ሥርዓቶች ሳይጠፋና ሙሉ በሙሉ ሳይለወጡ አውዳቸውን መሰረት አድርጎ መሰብሰብ ፣ መሰነድና መቅረፅ ላይ እንጂ ለብሔረሰቡ ከልማት ጋር ያላቸውን ግንኙነት አይመለከትም፡፡ ሥነ ሥርዓቶቹ (ወሊድ ፣ ጋብችና ሞት) እንዴት ፣ በማን ፣ መቼና የት እንደሚከናወኑ በመግለፅና በመተንተን እንዲታወቅ ማድረግ በዝርዝር ዓላማዎቹ ስር ሲገለፅ እነዚህ ፎክሎራዊ ዘውግ የሆኑት የባህል ዘርፎች ከልማት ጋር ሊኖራቸው የሚችለውን አዎንታዊና አሉታዊ አበርክቶ ስለማያመለክቱ ከዚህ ጥናት ጋር ከመረጃ አሰባሰብ ዘዴ እንዲሁም መሳሪያዎች አንፃር ብቻ ይመሳሰሉ

አንጂ ፍፁም የተለያዩ ናቸው፡፡ ይህ የአፀደ ጥናት በቅርብ ጊዜ የተሰራ በመሆኑ ስለብሔረሰቡ የሚነሳውን ታሪካዊ ዳራ በአብዛኛው ተመሳሳይ ያደርገዋል፡፡

በተጨማሪም የዋግኽምራ ባህላዊ የወሊድ ፣ የጋብቻና የሞት ሥነ ሥርዓቶች በዚህ ጥናት የሚዳሰስ በመሆኑ በመጠኑም ተዛምዶ ቢኖረውም አፀደ ባላየችው አቅጣጫ ከልማት ጋር አያይዞ የሚነሳ በመሆኑ ይሄ ጥናት ከአፀደ በጣሙን ይለያል፡፡ ጥናቱ በሚመለከተው ብሄረሰብ ላይ ባይሆንም በትምህርት ክፍሉ በስንቅነሽ አጠላ "ባህልና ልማት በበርታ ብሄረሰብ" በሚል ርዕስ በ2007 ዓ.ም የተሰራ የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ እናገኛለን፡፡ ስንቅነሽ የበርታን ብሔረሰብ ባህላዊ መገለጫዎችን በመሰብሰብ የይዘት ትንተና ወይም የፋይዳ ትንተና በማድረግ የበርታን ብሄረሰብ ማንነት ፣ የአኗኗር ብልሀት ፣ ስለዓለም ያላቸውን አተያይና ያልተጠኑ ወይም ያልተዳሰሱ የቆዩ ልማዳቸውንና እሴቶቻቸውን በማጥናት ባህሉ ለልማት ሊኖረው የሚችውን አወንታዊ አበርክቶ እና አሉታዊ ተፅዕኖ አሳይተዋል፡፡ ስንቅነሽ የጥናቱን ጥቅም ሲያስረዱ ጥናቱ ባህልና ልማት ያላቸውን የጠበቀ ቁርኝት አውጥቶ በማሳየት የልማት ዕቅዶች ሲታቀዱና ለትግበራ ሲዘጋጁ ለማህበረሰቡ ባህል ትኩረት መስጠት እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ማስረጃ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑ ለብሔረሰቡ ባህል ትኩረት በመስጠት ባህሉ ተጠንቶና ለልማት ያለው ጠቀሜታ ታውቆ ማህበረሰቡ ለልማት ለማነሳሳትና ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል መሳሪያ አድርጎ መጠቀም እንደሚቻል የሚያሳይና የሚያነቃቃ መነሻ ማስረጃ የሚሰጥ ጥናት እንደሆነ በየደረጃው ላሉ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች አስተግባሪዎችንና ባለሙያዎችን እቅዳቸው ውጤታማ እንዲሆንና ተቀባይነት እንዲያገኝ በቅድሚያ የማህበረሰቡን ባህል ጠንቅቀው መረዳት ፣ ለባህሉ እውቅና መስጠትና በማህበረሰቡ ባህል ወይም ሀገር በቀል እውቀት ላይ በመመስረት እቅዳቸውን ለማስተግበር እንደሚያስችል መረጃው የሚሰጥ መሆኑ ፤ ፖሊሲ አውጪዎች ማንኛውንም የልማት ዕቅድ ከማውጣታቸው በፊት በየአካባቢው ያሉ ባህላዊ ምቹ ሁኔታዎችና ተግዳሮቶች ምን እንደሆኑ ማጤንና ለእነሱም ትኩረት መስጠት እንደሚገባቸው ያስገነዝባሉ፡፡ የስንቅነሽ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ምንም እንኳ ተጠኚዎቹ ብሄረሰቦች በአካባቢ ቢለያዩም የልማት ጉዳይን በባህል ወይንም በፎክሎር ዘውጎች በሚሰበስቡ ስነ ቃሎች ፣ ቁሳዊ ባህሎች ፣ ልማዳዊ ሀገረሰባዊ ጥበባት እና ሀገረሰባዊ እምነቶች የይዘት ትንታኔ ውጤት ለማሳየት

እንደሚቻል አሳይተዋል፡፡ በመሆኑም የስንቅነሽ የአተናተን ዘዴና የመረጃ አሰባሰብ ስልት እንዲሁም ባህል ለልማት የሚኖረው አበርክቶ ያሳዩበት መንገድ ለዚህ ጥናት አሰራር ዘዴ ጥቅም የሰጠ በመሆኑ ለጥናቱ መነሻ እንዲሆን እረድቷል፡፡ በዚህ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሚያለያያቸው ሁለቱም የሚያጠኗቸው ብሄረሰቦች ባህልና የሚኖሩበት ቦታ እና የሚሰበሰቡት ጥሬ መረጃዎች ፍፁም የማይገናኙ መሆናቸው ነው፡፡

## 2.2. የፅንሰ ሃሳብ ማዕቀፎች

የዚህ ምዕራፍ ዋና ትኩረት ከጥናቱ ጋር ቁርኝት ያላቸውንና ቁልፍ ሚና በመጫወት በተደጋጋሚ የሚነሱትን ባህል ፣ ልማት ፣ የባህልና የልማት ትስስር ፣ ግብርና እና ጤና ኤክስቴንሽን የሚሉትን ፅንሰ ሃሳቦች ምንነት ማብራራት እና መተርጎም ይሆናል፡፡

### 2.2.1. የባህል ፅንሰ ሀሳብ

ባህል የሚፈጠረው አዲስ የሆነ ዕውቀትና ነገር በተግባር እየተለመደ ሲሄድ ነው፡፡ ያልተለመደ አዲስ ነገር ከባህል እንደሚለየው ሁሉ ፣ አንድ ነገር እየተለመደ ሲሄድ ባህል ይሆናል፡፡ ይህም በኅብረተሰቡ አባላት ዘንድ በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኛል ፤ ያስተሳስረዋል፡፡ ከቋንቋው ጋር ተያይዞ ባህል አንድን ማኅበረሰብ ከሌላው ለየት ያደርገዋል፡፡ የማህበረሰቡ ንብረትና መለያ ሆኖ የዚያን ማህበረሰብ ማንነትን ያመለክታል፡፡ ማህበረሰቡም በተግባር ወይም በትምህርት አማካኝነት ለአዲሱ ትውልድ ባህሉን እንደንብረቱ ያስተላልፋል፡፡ ኃይለ ገብርኤል (2007) ዳኜ ይህንን ሀሳብ ሲያረጋግጡ "አንድ ማህበረሰብ ባህሉ ሲነካበት ማንነቱ እንደተነካበት ሆኖ ሲያስቆጣው የምናየው ለዚህ ነው"ይላሉ፡፡ የራስ ወርቅ (2004)ም ባህል ኅብረተሰብ ወይም ዝቅ ሲል ማህበረሰብ ነው፡፡ ባህል በኅብረተሰብ ወይም በማህበረሰብ ውስጥ የታቀፉ ሰዎች የሚጋሩት እንጂ የግል ጉዳይ አይደለም ፤ ሊሆንም አይችልም ይላሉ፡፡ የራስ ወርቅ አክለውም "ሰዎች ባህልን ይማሩታል እንጂ በደም አይወርሱትም ከአንድ ትውልድ ወደ ሚቀጥለው በመማር እየተሸጋገረ ይቀጥላል፡፡ በውልደት ይሁን በማደጎ ወደ አንድ ኅብረተሰብ የገባ አዲስ አባል የኅብረተሰቡን ባህል በኅብረተሰባዊ የአስተዳደር ሂደት ውስጥ እንደ ቤተሰብ ፤ የአቻዎቹ ቡድን ትምህርት ቤትና የዕምነት ቤቶች በመሳሰሉት አማካይነት ይላበስዋል" (የራስ ወርቅ ፤ 2005 ፣ 5)፡፡

ከዚህ ለመረዳት የሚቻለው ባህል ከአካባቢያችንና ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት የምንለምደው እና በውስጣችን ተቀርፆ አስተሳሰባችንን የሚገራንና የሚመራን እንደሆነ ነው፡፡ ለዚህም ነው "ባህል የአንድ ህዝብ የአኗኗር ዘዴ ነው" (Ferraro, 2001; 22) ያለው፡፡ Ferraro ከላይ የተጠቀሰውን የባህልን ፅንስ ሀሳብ በሶስት ቁልፍ ቁምነገሮች ቀንብቦ ይተረጉመዋል፡፡

የባህልን ፅንሰ ሀሳብ "ሰዎች እንደ ኅብረተሰብ አባላት ያላቸው ፣ የሚያስቡት እና የሚያደርጉት ማንኛውም ነገር ሁሉ ነው" ብለን እንተረጉመዋለን (Ferraro, 2001; 22) ይላል፡፡ በመቀጠልም Ferraro እነዚህን ሦስት ቁምነገሮች የፍቺ ጠቃሚነት አላቸው፡፡ ምክንያቱም በውስጣቸው የያዟቸው ሦስቱ ዋና ዋና ግሶች ከሦስቱ ዋነኛ የባህል ይዘቶች ጋር ይጣጣማል፡፡ ይኸውም ማንኛውም ሰዎች ያሏቸው ነገር ሁሉ የሚለው ቁስ አካላዊ ንብረትን ያመለክታል ፣ ማንኛውም ሰዎች የሚያስቡትን ነገር ሁሉ የሚለው በጭንቅላታቸው ይዘው የሚዞሩትን እንደ ሀሳቦች ፣ ኅብረተሰባዊ ደንቦችንና ፣ አመለካከቶችን ፣ እንዲሁም መልክ የያዘ ባህሪን ያቅፋሉ ማለት ነው (Ferraro, 2001; 22) በማለት ያብራራል፡፡ ከላይ ከቀረበው Ferraro (2001) የባህል ፍቺን ለመረዳት የሚቻለው ባህልን በሁለት ዋና ዋና ገፅታዎች ከፍለን ልንገነዘበው እንደሚቻል ነው፡፡ ቁሳዊ የሆነ እና ከቁሳዊው ጀርባ መንፈሳዊ የሆነ የማይታዩ ግን ልዩ ልዩ መገለጫዎች ያላቸው ማህበራዊ አመለካካት ናቸው፡፡ ከግዙፉና ቁሳዊ ባህል "ጀርባ" አቅጣጫ ሰጪና የወል የሆነ በርካታ ማህበራዊ አመለካከትን የያዘ የባህል ስውር ገፅታ አለ ማለት ነው፡፡ ይህም አስተሳሰብ ነው፡፡ አስተሳሰቡም ማህበራዊ ሲሆን በአብዛኛው የማህበረሰቡ አባላት የሚያምኑትና የሚሰሩበት "ያልተፃፈ ህግ" ነው፡፡ ግለሰቡ ይህ አስተሳሰብ ከልጅነቱ ጀምሮ ከአስተዳደጉ በቤተሰቡና በባህል መሪዎች አማካኝነት ይዋሀደዋል፡፡ የተዋሀደው አስተሳሰብ የህይወቱን አቅጣጫ ይመራል /ምኞቱን ፣ ፍላጎቱን ፣ የደስታና የሀዘን ስሜቱን ይመራል/ ፣ የልፋት አቅጣጫውን ያሳየዋል ፣ ከሀይሉና ከእውቀቱ ምን ያህል ምን ላይ ማዋል እንዳለበት የሚገፋፋው ወይም የሚገታው ባህላዊ አስተሳሰብ ነው (Eric Fromm ,1971:79)፡፡ ይህንን ማህበራዊ ባህሪ ያለዋል፡፡ የአንድ ማህበረሰብ አባላት በአመዛኙ ተመሳሳይ ማህበራዊ ባህሪ አላቸው ይህም የወል ማህበራዊ ባህሪ ብለን ልንፈርጀው እንችላለን፡፡ ማህበራዊ ሥነሰብ የእውቀት ዘርፍ የባህል ፅንሰ ሀሳብ የሚረዳው ሰፊና መላ ህብረተሰባዊ ይዘቶችን/ክስተቶችን በሚያካትት መልኩ ነው፡፡

ይኸውም ባህል ማለት የአንድ የህብረተሰብ አባላት የሚረከቡአቸውን የተጠራቀሙ አውቀቶች ፣ እምነቶች ፣ ኪነ ጥበባት ፣ መመሪያዎች ፣ አርማዎች ፣ አመለካከቶች ፣ ሥነ ምግባራት ፣ ህግጋት ፣ ወጎች ፣ ተለምዶዎች እና ሰዎቹ የሚገለገሉባቸውን ቁስ አካላዊ ንብረቶችን ጭምር የሚያጠቃልል ውህድ ነው፡፡ ይህንን ሰፊ የባህል ግንዛቤ ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው ባህል አንድ ክስተት ሆኖ ግዙፍና ረቂቅ ወይም ውጫዊና ውስጣዊ መልክ ያለው ነው ለማለት ያስችለናል፡፡ ብዙውን ጊዜ የባህል ግዙፍ ወይም ቁሳዊ መልኩ ጎልቶ ይታያልና ይነገርለታል፡፡ ለምሳሌ አልባሳት ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች ፣ ባህላዊ የምግብ አሰራር ፣ ሥነ ህንጻዎች (የቤተክርስቲያን ፣ ቤተ መስጊድ ፣ የቤተ መንግስት ህንፃዎች ፣ ሐውልቶች) ፣ ወዘተ እንደ ባህልና ቅርስ ይታያሉ፡፡ ከእነዚህ ቁሳዊ ነገሮችና ቅሪቶች ጀርባ ረቂቅ ባህል አሉ፡፡ እነዚህም አስተሳሰብ ፣ እምነት ፣ እሴት ፣ ሃይማኖት ናቸው፡፡ እንደ እውቀት ፣ ጣዕም ፣ ውበት ፣ ብልህነት ፣ ክህሎት የመሳሰሉት አእምሮታዊ እሴቶች በግዙፉ ባህል ላይ ይንፀባረቃሉ፡፡ በቁሳዊ መልክ ይካብታሉ፡፡ አለባበስ ፣ አመጋገብ ፣ የአኗኗር ፈሊጥ ጣዕምን ፣ ብልህነትን ፣ ዕውቀትን ፣ ውበትን ብሎም ጥበብን ያንፀባርቃሉ፡፡ ስለዚህ ባህልን ስንተረጉምና ስንገነዘብ ከእነዚህ ከሁለቱ ግዙፋዊና ረቂቃዊ ተዋህዶት አንፃር መሆን ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ ይህንን ያቅፋል ብለን ስንነሳ በዚህ ጽሑፍ ለምንመለከተው የባህልና የልማት ቁርኝት ጉዳይ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

ባህል የማይነካካው የማህበረሰቡ ጉዳይ ስለሌለ በአብዛኛው የዘርዛሪነት ይዘት ያላቸው ብያኔዎች ሲሰጠው ይታያል፡፡ በተለይም የሥነ ሰብና የሥነ ማህበረሰብ ጠቢባን በልዩ ልዩ መንገዶች ይበይኑታል፡፡ “Calhoun”ን የተባለ ተመራማሪ ኤድዋርድ ቴለር እ.ኤ.አ በ1871 የፃፈውን ጠቅሶ “ባህል ፣ የሰው ልጅ የኅብረተሰብ አባል በመሆኑ የሚማራቸው/የሚለምዳቸው ዕውቀት ፣ እምነቶች ፣ ሥነ ጥበብ ፣ ሥነ ምግባር ፣ ህግ ፣ ደንብ/ወግ እና የመሳሰሉትን ችሎታዎችና ልማዶችን ሁሉ የሚያካትት የተወሳሰበ ሥርዓት ነው” ይላል (Calhoun, 2002;105)፡፡

የቴለር ብያኔ በአንዳንድ ጉዳዮች ቢተችም በተለይ ባህል በዝርያ የተበታተኑ ጉዳዮችና ክንውኖች ስብስብ ሳይሆን ሥርዓታዊ ፣ የተደራጁና ምሉዕ ነው የሚሉት ብያኔው ያካተታቸው ሃሳቦች እስካለንበት ዘመን ድረስ በሥነ ሰብ ተመራማሪዎች ዘንድ ተቀባይነት አላቸው፡፡ ቀረብ ባለ ጊዜ ደግሞ Ferraro “ባህል ከአካባቢያችንና ከሌሎች

ሰዎች ጋር ያሉንን ግንኙነቶች በተመለከተ የሚመራን የአእምሮ/የሕሊና ካርታ ነው" (Ferraro, 2001; 22) በማለት ገልጾታል፡፡

ባህል ሰዎችን ከበርካታ ሁኔታዎች ጋር የሚያስተሳስር ትርጉም አለው፡፡ ባህል በአንድ የማህበረሰብ አባላት የተሰሩ አካላዊ ቁሶችን/ነገሮችን ማካተት እንዳለበት ያስገነዘቡ የሥነ ማህበረሰብ ሊቃውንትም ነበሩ፡፡ ከነዚህም መካከል Merrill "ባህል እውቀትን ፣ እምነትን ፣ ሥነ ጥበብን ፣ ሞራልን ፣ ህግን ፣ ሀገረሰባዊ ልማድን ፣ የተለያዩ ችሎታዎችንና ተግባራትን የሚያጠቃልል ሥርዓት ነው፡፡ አንድ ሰው እንደ አንድ ኅብረተሰብ አባልነቱ የሚያውቀውና የሚፈፅመው የማህበራዊ ሕይወቱ ነፀብራቅ ሁሉ የባህል ክፍል ነው" በማለት ይገልፃል (Merrill, 1961; 36)፡፡

በጥቅሉ ባህልን አስመልክተው ከተሰጡ አተያዮች የምንረዳው ዋና ፍሬ ሀሳብ ባህል ኅብረተሰብ የእለት ከዕለት ሕይወቱን የሚመራባቸውን አስተሳሰቦች ፣ ድንጋጌዎች ፣ ወጎች ፣ እንዲሁም የእነዚህ መገለጫ የሆኑ ልዩ ልዩ የአሠራር ዘዴዎችን ፣ ሥነ ጥበባዊ ውጤቶችንና ነባር አገራዊ ተቋማትን የሚያካትት ሰፊ ፅንሰ ሃሳብ መሆኑን ነው፡፡ ባህል አንድ እንዲህ ነው ተብሎ የሚነገር ጉዳይ ሳይሆን የበርካታ ሃሳቦች ፣ ግብሮች ፣ ድርጊቶችና ነገሮች መማከያ ስርዓት ወይም ተቋም ነው፡፡ ስለዚህም ባህልን ለመገንዘብና ለመረዳት ተመራጩ የአቀራረብ ዘዴ ለሁሉም ማህበረሰቦችና ባህሎች አማካይነት ባላቸው ሁለት ዋና ዋና ገፅታዎቹ መድቦ መግለፅና ማብራራት እንደሆነ በምሁራን ዘንድ አጠቃላይ ስምምነት አለ፡፡ እነዚህም ሁለት ምድቦች መንፈሳዊ ባህል ቅርሶች እና ቁሳዊ የባህል ቅርሶች የሚባሉት ናቸው (Okpewho, 1992; 5, ፈቃደ ፣ 1991 ፣ 15-16)፡፡

ቁሳዊ ባህል አንድ ኅብረተሰብ በተፈጥሮኣዊ አካባቢው ላይ ለመሰልጠን ፣ ለአካላዊ ምቾቱና ደህንነቱ እንዲሁም ለመንፈሳዊ ፍላጎቱና እርካታው የሚያስፈልጉትን ምርቶችና ነገሮች ለማሟላት ይችል ዘንድ የፈለሰፋቸውን የማምረቻና ኪነ ህንፃዎችን የሚጠቀልል እሳቤ ነው፡፡ ይኼም የነፍስ ወከፍ የእጅ መሣሪያዎች ፣ የግብርና መሣሪያዎች ፣ የቤት ቁሳቁሶች ፣ የጦር መሣሪያዎች ፣ የወግና የግል ቤቶች ፣ መፃህፍትና ሰነዶች ፣ ሀውልቶች ፣ የግብይትና የልውውጥ መሣሪያዎች (ገንዘቦች) ፣ የልክ ዕቃዎችና መስፈሪያዎች ፣ የእምነት ማከናወኛ እቃዎችና መሣሪያዎች ፣

የሙዚቃ መሣሪያዎች ፣ የመጫወቻ ቁሳቁሶች ወዘተ፡፡ አንድ ኅብረተሰብ አኗኗርና አሰራሩን ለማቀላጠፍና ስረዓት ለማስያዝ የፈለሰፋቸው ከትውልድ ትውልድ ሲሸጋገሩ የኖሩ የቁሳዊ ባህል ገፅታዎች ናቸው (Mbarogu, 2004; Storey, 2009)፡፡

ረቂቅ ወይም መንፈሳዊ ባህልም በቋንቋና ተምሳሌታዊ (Symbolic) ክንውን የሚገለጡ ሃይማኖትን ፣ ፍልስፍናን ፣ ርዕዮተ ዓለምን ፣ ፓለቲካን ፣ ትምህርትን ፣ ዕውቀትን ፣ ሥነ ጥበብንና ሥነ ቃልን (ተረቶችን ፣ ቃል ግጥሞች ፣ ቃላዊ ትረካዎች)፣ በጥቅሉም የአንድን ማህበረሰብ አባላት ሃሳብና ስሜት የሚለዋወጡባቸውንና የሚግባቡባቸውን እንዲሁም ግለሰቦች አባት አደር ባህላቸው አድርገው የሚያስቧቸውን ልዩ ልዩ ግብሮች ፣ ምሳሌያዊ አባባሎች ፣ እውቀትና ክሂሎችን ያካትታል፡፡ መንፈሳዊ ባህላዊ ቅርስ ከሚገለፅባቸው ጉዳዮች ጥቂቶቹ ቃላዊ ባህሎችና አገላለፆች ፣ ማህበረሰባዊ ትውን ጥበባት ፣ ማህበረሰባዊ ክብረ በዓሎች ፣ ተፈጥሮንና ሁለንተናን የሚመለከቱ እውቀቶችና ግብሮች ባህላዊ እደ ጥበብ ናቸው፡፡ መንፈሳው ባህላዊ ቅርሶች ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋሉ፡፡ የእያንዳንዱም ትውልድ ማህበረሰብ አባላትና ቡድኖች ለየዘመናቸው አካባቢያዊ ፣ ተፈጥሮአዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች በሚጣጣም እና በሚያገለግል መልኩ ስለሚያሻሽሏቸውና መልሰው ስለሚፈጥሯቸው ለማህበረሰቡ የማንነት ፣ የነባርነትና የቀጣይነት ስሜት ያጎናጽፉታል (Ojameruaye, 2005; 5)፡፡

ባህል የማህበረሰቡ አባላት የሚጋሩት ፣ በዘር ወይም በደም የማይተላለፉ ከአንድ ትውልድ ወደ ቀጣዩ ትውልድ በታሪክና በልማድ የሚተላለፉ ፣ ከማህበራዊ አኗኗር ጋር ለማዛመድ በሚደረግ ተራክቦ የሚፈጠር በሁሉም ማህበረሰብ የሚገኝ የጋራ ባህሪ እና ተለዋዋጭ የሆነ እሳቤ ነው፡፡ በመሆኑም ባህል ሳንገነዘበው/ልብ ሳንለው ባህሪያችንን ፣ አተያያችንን ፣ እሴታችንን ፣ መዳረሻችንን እንዲሁም እኛነታችንን በመቅረፅ አኗኗራችንን የሚያስተካክል ነው፡፡ በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ሰው ከባህል ውጪ ምንም ነው፡፡ ማንኛውም ማህበረሰባዊ ልማዱ ውጪ እንደ ታላቅ ህዝብ ሊቆጠር አይችልም  በማለት የባህልን ሁለንተናዊ ገፅታውን በዝርዝር ይገልፃሉ (Mbakogu, 2004; 40)፡፡

ባህል የዚህን ያህል ላቅ ያለ ሚና የሚጫወት ከሆነ ሥነ ምግባራዊና መንፈሳዊ ህልውናን ለማጎልበት ፣ ድህነትን ለማስመገድና የምጣኔ ሃብት ልማት/እድገት

ለማምጣት ትልቅ ሚና አለው ማለት ይቻላል፡፡ የUNESCO (2005) ሰነድ ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ እሴት ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡን እና የግለሰቡን የሕይወት አቅጣጫ የሚመራ ፣ የአዳዲስ የፈጠራ ግኝቶች ምንነትና የሀገር በቀል ዕውቀቶች የመሰረት ድንጋይ ፣ የዕውቀት መገለጫና ማስተላለፊያ መንገድ ፣ የመጪውን ችግሮች ለመወጣትና የማህበረሰቡንም ልማድ ለመጠበቅ የሚያስችል መሆኑን ሰነዱ ላይ አስፍሯል፡፡ በዚሁ ሰነድ አክሎም ባህል ይህ ከሆነ በዛሬው ዓለምም ሥነ ምግባራዊና መንፈሳዊ ህልውናዎችን ለመቀዳጀት ወሳኝ ከመሆኑም በላይ "… while having often unrecognized potential interms of economic development and efforts to combat poverity (UNESCO, 2005; 1-2)" ለኢኮኖሚው እድገትና ድህነትን ለመዋጋትም ትልቅ አቅም እንዳለው ሰነዱ ላይ ተገልጿል፡፡

ከዚህ በላይ በዝርዝር ያየናቸው የባህል ትርጉሞች ሲጨመቁ ባህል የአንድ ማህበረሰብ የሕልውና መሠረት ፣ የማንነቱና የአመለካከቱ መለያና ማሳያ ፣ የዕውቀቱና የሥልጣኔው ማሸጋገሪያው እንዲሁም የአኗኗር አቅጣጫውን የሚወስን ነው፡፡ ስለዚህ ባህል በሰው ልጅ የአኗኗር ሕይወት ውስጥ የማይነካው አንዳች ጉዳይ የለም፡፡ በመሆኑም የልማትን ጉዳይ ስንመለከት ባህልን ወደ ጎን መተው አይቻልም፡፡ ይህም በመሆኑ በሁለቱ መካከል ከፍተኛ ቁርኝትና ትስስር ያላቸው መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡

### 2.2.2. የልማት ፅንሰ ሀሳብ

ልማት ብለን የምንጠራውን ፅንሰ ሃሳብ ብዙዎቻችን ምን ማለት እንደሆነ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዳለን አጠያያቂ አይደለም፡፡ በጥልቀትና ወደ ዝርዝሩ ስንገባ ግን ሁኔታው የሚመስለንን ያክል ቀላል አይደለም ፤ ሰፊና ውስብስብ ትርጉም ያለው ነው፡፡ በዘርፉ ምርምር የሚያደርጉ ምሁራን በየጊዜው የተለያየ ብያኔ ሲሰጡት ይታያል፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ በ2006 ዓ.ም ያሳተመው የአማርኛ መዝገበ ቃላት "ልማት" የሚለውን ቃል "ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ፣ ብልፅግናና ግንባታ" በማለት ይተረጉመዋል፡፡ ይህም ፍች "Development" ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ከሚሰጡት የተለያዩ ፍቺዎች ቢያንስ የጥቂቶቹን ይዘት የሚጋራ ነው፡፡ "Development" "እድገት"

የተባለውን የተፈጥሮ ክስተትን የሚያመለክትም ነው፡፡ ሕይወት ያለው ሁሉ ያድጋል ፤ ልጅ ያድጋል ፣ ዛፍ ያድጋል ፣ ወዘተ ሕይወት የሌለው ነገር አያድግም፡፡ ከዚሁ ተወርሶ እድገት ከልማት ጋር ተያይዞ በአሁኑ ዘመን ማህበራዊ ትርጉም ተሰጥቶታል፡፡ የሀገር ኢኮኖሚ ሲሻሻል እድገት ይባላል፡፡ የአንድ ማህበረሰብ ኑሮ ደረጃ ሲሻሻል እድገት ይባላል፡፡ ይህንን አስመልክተው ፕ/ር ሀብታሙ ወንድሙ[5] በአንድ ዐውደ ጥናት ለይ ባቀረቡት መጣጥፋቸው "እድገት/ልማት" ሲባል ከሆነ ሁኔታና ደረጃ ኀብረተሰብ ወደሚፈልገውና ሌሎች ሕዝቦች /አገሮች/ ወደ ደረሱበት ወደ ተሻለው ሁኔታና ደረጃ መድረስ ፣ መሸጋገር ይመስለኛል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ስለዚህ የአንድ ማህበረሰብ ኑሮ ደረጃ ሲሻሻል እድገት ይባላል፡፡ የእድገት ምልክቶችና መመዘኛዎች የምርት መጠን ከፍ ማለት ፣ እንዲሁም የገቢ መጠን ፣ የጤንነት ደረጃ ፣ የዕውቀት ደረጃ ፣ የፍጆታ ሁኔታ ከነበረበት ሲጨምር እድገት ይባላል፡፡ የእድገት ዋና ዓላማው የሰውን ሕይወት ኑሮ ማሻሻል ነው፡፡ በመሆኑም ልማት/እድገት አንድ አይነት ኀብረተሰባዊ ለውጥ ነው፡፡ ነገር ግን ማንኛውም ኀብረተሰባዊ ለውጥ ልማት/እድገት ነው ማለት አይደለም፡፡ ይህንን ሁኔታ አስመልክተው የራስወርቅ አድማሴ "ልማት አዎንታዊ ፣ በጎ ፣ ወይም ጠቃሚ ኀብረተሰባዊ ለውጥ ማለት ነው፡፡ ልማት ብለን የምንጠራው አጠቃላይ አርዕስት ስር የሚካተቱትን ኀብረተሰባዊ ለውጦች… በአብዛኛው ጠቃሚ የሆኑትን መሻሻሎች ነው" በማለት ይገልፃሉ (የራስወርቅ ፣ 2004 ፣ 6) ፡፡ በመሆኑም ከዚህ ላይ መረዳት የሚቻለው ልማት/እድገት ሲባል በመጠንና በዓይነት ኑሮንና ሕይወትን ማሻሻል ነው፡፡ ስለዚህም ከነበረው የተሻለ በቂ ምግብ ማምረትንና ማቅረብ የእድገት ወይም የልማት እመርታ ነው፡፡ ለኑሮ አመቺ የሆነ በቂ መኖሪያ ቤት መሥራት መቻል ፣ በቂ ልብስ ፣ ጫማ ፣ ወዘተ ማምረት የመሳሰሉት የልማት ምልክቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ልማት ሲባል በመጠንና በዓይነት ኑሮንና ሕይወትን ለማሻሻል የተሻለ ለማምረት ሀብት ለማፍራት የሚደረግ መሻሻልን ይመለከታል፡፡ በመሆኑም ልማት ከህብረተሰብ ለውጥ ጋር የተያያዘ ነው ለማለት

---

[5] ፕ/ር ሀብታሙ ወንድሙ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር የምዕተ ዓመቱ የኢትዮጵያ የሥነ ጽሁፍ እድገት ፣ የንባብ ባህል ይዞታን የመጪው ክፍለ ዘመን ፈር በሚል ርዕስ ለተዘጋጀው ዐውደ ጥናት ከግንቦት 27 እስከ 28 /1999ዓ.ም "ዘመናዊነት በኢትዮጵያ ህብረተሰብ አኗኗር ላይ ያመጣው ለውጥ" በሚል ካቀረቡት የተወሰደ፡፡

ይቻላል፡፡ ለውጥ ማለት ደግሞ በጎም መጥፎም ገፅታ ሊኖረው ይችላል ፤ ከልማት ጋር የተያያዘው ለውጥ ግን በአብዛኛው በጎ የሆነው እንደሆነ የራስ ወርቅ ያስረዳሉ፡፡

ልማት ማለት በማህበረሰቡ መንፈሳዊና ቁሳዊ ጉዳዮች ረገድ የተሻለ ሕይወት ማምጣት ከሆነ የልማት ፍቺ ከምጣኔ ሀብታዊ እድገት (Economic Growth) የሚለይ ነው፡፡ የምጣኔ ሀብታዊ እድገት የፍጆታ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ማምረት ፣ የሀገራዊ ምርት (GDP) መጨመርን እና አጠቃላይ የሀገራዊ ገቢ (GNI)እድገት ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የምጣኔ ሀብት እድገት የማህበረሰቡ ዋነኛ ጉዳይ የሆነው ድህነት ላይ ለውጥ ሳይመጣ እድገቱ በተወሰኑ ሰዎች ብቻ የመጣ ሲሆን ነው (Peet and Hartwick, 2009)፡፡

ባለፉት 30 ዓመታት በብዙ የምዕራባውያን ሀገሮች የታየው ዕድገት በዚህ መልኩ የተመዘገበ ነው፡፡ ይህ የጠቀመው ሀብታምና ጥቂት ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን እንጂ ብዙዎችን አይመለከትም፡፡ የምጣኔ ሀብት እድገት ሀብትን በተወሰኑ ሰዎች እጅ ማስገባት ከሆነ ለብዙሃኑ የተሻለ የኑሮ ህይወትን ስለማያስገኝ ልማት ሊሆን እንደማይችል ተመራማሪዎች ይስማማሉ (Peet and Hartwick, 2009)፡፡ በ1950ዎቹ እና 1960ዎቹ የአንድ ኅብረተሰብ ልማት ከኢኮኖሚ ዕድገቱ ጋር አንድ እንደሆነ ተደርጎ የመውሰድ አተያይ እንደነበርና ባሁኑ ወቅት ግን ተለውጦ ልማት ሲባል በሰፊው ትርጉሙ በመውሰድ የኢኮኖሚ ልማትና የህዝብን የፖለቲካና የሶሻል ደህንነት እንዲያቅፍ መደረጉን የራስ ወርቅ UNDPን ጠቅሰው ያስረዳሉ (የራስወርቅ ፣ 2004 ፣ 7)፡፡

የአውሮፓውያን የልማት ፖሊሲ ችግሮች ዋነኛ ምንጭ የሆነው ምዕራባዊነትን በሌላው ላይ የመጫን አዝማሚያ ነው የሚሉት (Bob Cumming, 1990)፡፡ ይህ የምዕራባውያን አስተሳሰብ ስልጣኔን ከምዕራባዊነት ጋር ብቻ የሚያያዝ ፣ ለባህል ልዩነት ቦታ የማይሰጥ ፣ ከግብርና ይልቅ በኢንዱስትሪ ዕድገት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ በልማት ዙሪያ የሚሠሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እታች ድረስ ወርደው ማህበረሰቡን በማግኘት እንደሚሰሩ ላይ ላዩን ቢያሳዩም የማህበረሰቡን ባህል ማወቅና የልማት ተልዕኳቸውን በዚያ ላይ መመስረት የማይፈልጉ መሆናቸው ትልቅ ችግር እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

የማህበረሰቡን ፍላጎት ፣ የለውጥ ተነሳሽነቱን እና አቅሙን መገንዘብ ለልማቱ ውጤታማነት ዋነኛ ጉዳይ ነው፡፡ ፍላጎቱንና ነባራዊ ሁኔታውን ከግምት ውስጥ ያላስገባ የልማት መርሀ ግብር ሊሳካ አይችልም፡፡ በማህበረሰቡ ላይም የጥገኝነት አስተሳሰብ እንደሚፈጥርም ያሳያሉ (Cumming, 1990)፡፡ Ojamer Vaye የተባሉ የምጣኔ ሀብት ተመራማሪ የምጣኔ ሀብት ልማትን /Economic Development/ፍቺ እንደ ሚከተለው ያብራሩታል፡፡

> ምጣኔ ሀብታዊ ልማት በጠንካራ ገፅታው ሲተረጎም የሰው ልጅ ሁለንተናዊ ኑሮ ጥራት ባለው ደረጃ ከአራት ጉዳዮች አንፃር ማደግ ነው፡፡ እነዚህም አንደኛ ከምጣኔ ሀብታዊ ልማት ጋር የሚታየው የዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ምርት መጨመር ፤ ሁለተኛው ከሰዎች የኑሮ ደረጃ ማደግ ጋር የተያያዘው የገቢያቸው መጨመር ፣ የምግብ ፣ የጤና ፣ የትምህርት ፣ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ፍላጎት መሟላት ነው ፤ ሶስተኛ ሰዎች በራስ መተማመን እንዲኖራቸው ሰብዓዊ ክብራቸውንና ተቀባይነታቸውን እንዲከበር የሚረዱ ተገቢ ማህበራዊ ፣ ፓለቲካዊ ፣ ምጣኔ ሀብታዊ ሥርዓት ተቋማትና ምቹ ሁኔታዎች መኖርና መጠበቅ ፤ አራተኛ የሰዎች መሠረታዊ ፍላጎቶችን የሚያሟሉ ምርቶችና አገልግሎቶችና ሌሎች ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች የሚቀርቡባቸው የተለያዩ አማራጮችን ለመምረጥ ያላቸው ነፃነት ማለት ነው (Ojamer Vaye,2005;2)፡፡

ከላይ በዝርዝር እንደተገለፀው ልማት የሰው ልጆች የተሻለ ህይወት እንዲኖሩ ለማስቻል የሚደረገውን ሁለንተናዊ ለውጥና መሻሻል ከሆነ የዚህ ጥናትም ትኩረት በዚሁ ሁለንተናዊ ትርጓሜ ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ ጥናቱ የምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት (Economic Growth) እና ከሥልጣኔ ጋር ብቻ የሚያያይዘው ጉዳይ አይመለከትም፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የሰው ልጅ ሁለንተናዊ መገለጫ የሆነውን ባህል በማልማትና ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶችን በጥምር አበርክቶ የተሻለ ኑሮ እንዲኖር ማድረግን የሚጠይቀውን የልማት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ልማት የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ከዚሁ ከማህበረሰቡ ቁሳዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች ልማት ጋር በማቆራኘት ከባህሉ ጋር ያለውን ትስስርና መስተጋብር የሚመለከት ጥናት ነው፡፡

### 2.2.3. የባህልና የልማት ትስስር

ባህልን ወደ ልማት ጉዳይ ስናመጣው የልማቱን ዓላማዎችና ከባህል ውስብስብ ፅንሰ ሃሳቦች ጋር ያለውን ትስስር በአንክሮ ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ የልማትንና የባህልን ሰፊና ውስብስብ ትርጓሜዎች በማሳየት ባህል ለልማት ቁልፍ ጉዳይ እንደሆነ የቀደምት አስተሳሰቦች የነበሯቸውን ችግሮች በማንሳት የሚያስረዱ አሉ፡፡ ይኸውም የቀደሙት የልማት አስተሳሰቦች ውድቀቶችን ፣ በሉላዊነት ሰበብ ዙሪያ ፣ ለባህላዊ ብዝሃነት የሚሰጠው አናሳ ግምት ፣ በማህበራዊ ልዩነቶች ዙሪያ /በሥርዓተ ጾታ ፣ በጎሳዊነት እና ዘረኝነት) ያለው አቀንቃኝነት ፣ የምስራቅ እስያ የልማት ስኬቶችና ድሎች እና የማህበራዊ ትስስር ፍላጎቶች የባህልንና የልማትን ቁርኝት ጎልቶ እንዲታይ አድርገውታል ይላሉ (Radcliffe, 2006: Cumming, 1990፡፡

ባህል በልማት ውስጥ ዋነኛ ጉዳይ እየሆነ መታየት የጀመረው ከ19ኛው ምዕተ ዓመት የመጨረሻዎቹ ዓመታት ወዲህ እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ Radcliffe (2006) ባህልና ልማት ያላቸውን ትስስር በዋነኛ ርዕስ ጉዳይ ይዘው የተነሱ ዩኔስኮን የመሰሉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከ1988-1997 አስርት ዓመታት ባህልን ለልማት ያለው አበርክቶ ትኩረት እንዲያገኝ አድርገዋል፡፡ በእነዚህ ዓመታት በሀገራት የልማት አጀንዳ ውስጥም ባህላዊ አሴቶች ፣ አስተሳሰቦች  እና መስተጋብሮች በሰፋት ግምት ውስጥ እየገቡና ትኩረት እያገኙ መጥተዋል፡፡ የባህል ልዩነቶችና ብዝኃነቶች በልማት መስተጋብር ውስጥ በተገቢ ሁኔታ ከተስተናገዱ ስኬታማ የልማት መሣሪያዎች እንደሆኑ እየተረጋገጠ እንደመጣ ያስረዳሉ (Radcliffe, 2006; 10)፡፡

Cumming (1990) እንደገለጹት ባህል ከልማት ንድፈ ሀሳብ ጋር የሚያያዝ ሰፊ እሳቤ ያለው በመሆኑ ለልማት ዕቅዶችና ስትራቴጅዎች መሳካት ለተለያዩ ባህሎች እውቅና እና ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በልማት ዙሪያ የሚሰሩ የተወሰኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለልማት ግባቸው መሣካት ለእነሱ ባህል ማለት ጥበብ ፣ ሙዚቃ ፣ ዳንስና ሥነ ጽሑፍ ብቻ እንደሆነ እንደሚያስቡ እያንዳንዱ ማህበረሰብ ለእነሱ እንግዳ የሆነና ለልማቱ ሥራ ላይ ሳይቀር ተፅዕኖ ሲያደርግ ሙያዊ ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ፖለቲካዊ ባህል እንዳለው እንደማይቀበሉ ያስረዳሉ፡፡

በመሆኑም በትምህርት ስም የማህበረሰቡን ቃላዊ ባህል እንደሚያጠፉ ፣ በግብርና ዘመናዊነት ስም የተሻለውን የመሬት አያያዝና አከፋፈል ፣ ሀብት ፣ ቁጥጥር የሌለበትን የሚመስለውን ኢኮኖሚያዊ ፣ ባህላቸውን ፣ ትብብራቸውንንና ጓዳዊነታቸውን እንደሚደመስሱ ፣ በዴሞክራሲ አስተሳሰብ ስም ሰላማዊ የሆኑ አስተዳደራቸውንና መሪዎቻቸቸውን ፣ በሰብዓዊ መብት ስም ሀገረሰባዊ ሥርዓታቸውን እንደሚያጠፉ ይተነትናሉ፡፡

Cumming (1990) በመቀጠልም የምዕራባውያን የልማት ንድፈ ሀሳብና ተግባር "ዘመናዊነትና" "ምዕራባዊነት"[6] በሌሎች ላይ መጫንን መሠረት አድርጎ ስለሚነሳ ነው፡፡ የሦስተኛው ድህነት ኢኮኖሚውን በማዘመን ብቻ ሊቀረፍ የሚችል የታሪካዊ ኃላቀርነት ውጤት አይደለም፡፡ ምዕራቡ "በደቡብ" ላይ የፈጠረው ስልታዊ የሴረኝነት የቅኝ ግዛት ውጤት እንደሆነና ለልማት ስትራቴጂዎችን ፕሮጀክቶችን አለመሳካት በዋና ምክንያትነት የሚነሱት ማህበረ-ምጣኔ ሀብታዊ ወይም ፖለቲካዊ ጉዳዮች ሳይሆኑ በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ውስጥ ያለው የባህል ልዩነትና ከዚህ አንፃር ማህበረሰቡ የሚኖረው ፍላጎት ነው በማለት ያሰርፃሉ፡፡

Schech and Haggis (2000) እንደሚገልጹት የዘመናዊነት አስተሳሰብ አቀንቃኞች ባላደጉ ሀገሮች ማህበረሰቦች ውስጥ የድህነትን ዑደት ለመስበርና ከገቡበት ማጥ ለማውጣት ኋላ ቀር አመለካከቶችን የሚንድ ሁለንተናዊ ለውጥ ያስፈልጋል ፤ እነዚህ ሀገራት ማደግ እንዲችሉም የምርት እድገትና ምጣኔ ሀብታዊ ለውጥ ብቻ ሳይሆን የትምህርት ሥርዓቱ ፣ የአስተሳሰብ ሂደቱና ዘዴው ፣ የአኗኗር ይትባህሉ ሁሉ ከኋላቀርነት ተላቆ መዘመን አለበት ባይ እንደሆኑ ያብራራሉ፡፡

የእነዚህ የዘመናዊነት አስተሳሰብ አቀንቃኞች የመከራከሪያ ነጥብ እንደማይሠራ ሊያሳዩም ከላይ ወደ ታች የሚዘረጋ የዘመናዊነት አስተሳሰብና የልማት አቅጣጫ

---

[6] "ዘመናዊነትና" "ምዕራባዊነት" የተሰኙት የእንግሊዝኛውን "Modernization" እና "Westernization" የተሰኙ ቃላት እንዲተኩ ታስቦ የተመረጡ/የተወሰዱ ናቸው፡፡ ይህም የዘመናዊነት አስተሳሰብ እና የምዕራባዊነት አስተሳሰብ /Thought/ ወይም አተያይ ፣ አመለካከት ፣ ፈለግ የሚሉትን የፍልስፍና ጠገግ እንዲገልጹ ታስቦ መርጬ ልጠቀምባቸው ወድጃለሁ፡፡

ውጤት አልባ መሆኑ የልማት ድርጅቶች ከድህነትና ከርሃብ ጋር የያዙትን ውጊያ መኮላሸትና ለውጥ አለማምጣት ጥሩ ማሳያ ነው፡፡ ለግብርና ሥራ ከፍተኛ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምና ግብርናውን በኢንዱስትሪ መተካት የዓለም ደሃ ህዝቦችን የኑሮ ደረጃ ውድቀት በተለይም የሴቶችንና የህፃናትን ድህነት አባብሷል በማለት የዘመናዊነት አስተሳሰብን ችግር ያመለክታሉ (Schech and Haggis, 2000 ፡ 9)፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረቡት አስተሳሰቦች የምንረዳው ባህላዊ ሁኔታዎችን መሠረት ያላደረገና በዘመናዊነት ላይ ብቻ የተንጠለጠለ የልማት አስተሳሰብና አተገባበር ውጤታማ መሆን እንደማይችል ነው፡፡ ለዚህም ሳይሆን አይቀርም በአሁኑ ወቅት ዓለም አቀፍ ተቋማት ሳይቀሩ የልማት ርዕሰ ጉዳዮችን ይዞ የሚነሳ አካል ገና ከመነሻው የባህል ጉዳዮችን አካቶ ማሰብ እንዳለበትና ሀገራትም በየልማት ፖሊሲዎቻቸው ውስጥ የባህልን ጉዳይ አብረው አካተው እንዲሰሩ የሚያሳስቡት፡፡

ባህል የልማት ዋነኛ ጉዳይ ሆኖ በልማት ክርክሮች ውስጥ ተጠቃሽ እየሆነ የመጣው ከ19ኛው ምዕተ ዓመት የመጨረሻዎቹ ዓመታት ወዲህ እንደሆነ ሰነዶች ይጠቁማሉ፡፡ እንደ ተባበሩት መንግስታት ያሉ ዓለም አቀፋዊ ተቋማት የልማት አስርት ዓመታት በሚባሉት ከ1988 -1997 ባሉት ዓመታት ባህልና ልማት ሳይነጣጠሉ እንዲታዩ አድርገዋል፡፡ የዓለም ባንክና ሌሎች ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ባህል በሰፊ ትርጉሙ በልማት ጉዳይ ውስጥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ እንደሆነ መናገር መጀመራቸውን ያስረዳሉ (Radcliffe, 2006;2)፡፡

የባህልንና የልማትን ጉዳይ አቢይ ዓላማው አድርጎ እየሠራ ያለው የተባበሩት መንግስታት የትምህርት ፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ)ፓሪስ ላይ በ2005 Convention on the protection and promotion of the diversity of cultura expressions በሚል ባወጣው ሰነድ ባህል ለዘላቂ ልማት ያለው ፋይዳ አስመልክቶ አንቀፅ 13 ላይ Integraton of culture in sustainable development በሚል ርዕስ ስር የሚከተለውን ደንግጓል፡፡ “Parties shall endeavor to integrate culture in the development policies at all levels for the creation of conditons conducive to sustainable development and with in this frame work, foster aspects relating to the protection and promotion of the diversity of cultural

expressions” በማለት አባል ሀገራት በሙሉ በልማት ፖሊሲ ሰነዳቸውን ሁሉ የባህልን ጉዳይ ትኩረት እንዲሰጡት ያስገነዝባል፡፡ ይኸው ድርጅት “The power of culture for development” በሚል ርዕስ በ2010 ባዘጋጀው ሌላ ሰነድ በሁለንተናዊ መልኩ ለዘላቂ ልማት መሠረታዊ ጉዳይ እንደሆነ በማስረገጥ ባህል በቁሳዊና መንፈሳዊ መልኮቹ (Tangable and Intangible) ፣ በፈጠራ ኢንዱስትሪና በተለያዩ በተለይም ጥበባዊ መገለጫዎች ፣ በምጣኔ ሀብታዊ ልማት ፣ ማህበራዊ መረጋጋት ለመፍጠርና ለአካባቢ ጥበቃ ዓይነተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ይገልፃልለ፡፡

በተጨማሪም ባህል ሰዎች በአካባቢያቸው እንዴት መኖር እንዳለባቸውና በሀገራዊም ሆነ በዓለማቀፋዊ መስፈርት እንዴት ግንኙነት እንደሚያደርጉ የሚበይን ዋነኛ ጉዳይ እንደሆነ ገልፆ ባህል የአዳዲስ ሃሳቦችና የፈጠራዎች ምንጭ ፣ የአንድ ማህበረሰብ ልዩ ልዩ ውስብስብ የሆኑ መንፈሳዊና ቁሳዊ ዕውቀቶችና ውስጣዊ ስሜቶች ተጋምዶዎች ዕውቀቶችና እሴቶች መገለጫ እንዲሁም ከዓለም ጋር የሚያስተሳስሩ የራስ ቅርፆች ያሉትና በእነዚህ የዓለም አስተሳሰቦችና የአገላለፅ ጠገጎች ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግና የሚደርግበትም በመሆኑ በተገቢው መንገድ ከተያዘ ታዳሽ ጥሬ ሀብት እንደሆነ ያመላክታል፡፡

ባህል የምጣኔ ሀብታዊ ልማትም አንቀሳቃሽ ኃይል በመሆኑ ሥራና የገቢ ምንጭን በወፍ በረር በባህላዊ ቱሪዝም ፣ በማክሮ ኢንተርፕራይዞች ፣ በባህላዊ መሠረት ልማቶችና ተቋማት ጠንካራ ዓለም አቀፋዊ የምጣኔ ሀብት ምንጭና ሃይል እንደሆነም ያስረዳሉ፡፡ በባህሎች መካከል ያሉት ብዙህነትን እውቅና በመስጠት መልካም ግንኙነትን በመፍጠርና ዕውቀትን በማስፈን ፣ ለማህበራዊ ኑሮ መረጋጋትና ዘላቂነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክት መሆኑን የዩኔስኮ ሰነድ ያትታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሰዎች ከአካባቢያቸው ጋር ያላቸውን ዝምድና እንዴት እንደሚጠብቁትና እንደሚያስተዳድሩ የሚኖራቸው አተያይ የተቀረፀው በባህላቸው በመሆኑ ባህል ለዘላቂ የአካባቢ ጥበቃና ልማት አንቀሳቃሽ ኃይል ነው፡፡ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎችና ግጭቶች ጥለውት ከሚያልፉት በጎ ያልሆነ አሻራዎች ስሜቶችና መጥፎ ትዝታዎች ማህበረሰቡ እንዲያገግም ባህል ዋነኛ መሣሪያ እንደሆነ

በመዘርዘር ባህል ለልማት የሚጫወተውን አዎንታዊ ሚና በስፋት ያስረዳል (UNESCO, 2010)፡፡

ከዚህም በላይ የባህል ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ለአገራት ልማት ዓይነተኛ አበርክቶ እንደሚኖረው "Culture: a driver and an enabler of sustainable development" በሚል ርዕስ በ2012 የተዘጋጀ ሌላ የዩኔስኮ ሰነድ በምሳሌ አስደግፎ እንደሚከተለው ያትታል፡፡

> ባህላዊና የፈጠራ ኢንዱስትሪዎች በዓለም ምጣኔ ሀብት ውስጥ በአብዛኛው በፈጣን ሁኔታ በመስፋፋት ላይ ካሉ ሴክተሮች ዋነኞቹ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ ለዚህም በመካከለኛው ምስራቅ 17.6 ፣ በአፍሪካ 13.9 ፣ በደቡብ አሜሪካ 11.9 ፣ በኢስያ 9.7 ፣ በኦሽኒያ 6.9 ፣ በስሜንና በመካከለኛው አሜሪካ እንዲሁ 4.3 በመቶ የተገኘውን የምጣኔ ሀብታዊ እድገት ይሸፍናሉ፡፡ እነዚህን ዘርፎች ለማስፋፋት የሚጠይቀው ወረት/ካፒታል/ የተወሰነ ከመሆኑም ባሻገር ሴቶችን ጨምሮ የተለያዩ ህዝቦችን ማሳተፍ የሚያስችሉና ከፍተኛ የሥራ ዕድልን የሚፈጥሩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በ2010 በኢኳቶር ከአመታዊ ገቢያቸው ከመደበኛው የግል ባህላዊ እንቅስቃሴዎች የተገኘው 2.6 በመቶው ህዝባቸው በባህላዊ ኢንዱስትሪዎች የሚሠራ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 60 በመቶው ደግሞ ሴቶች ናቸው (UNESCO,2012,4 ትርጉም የእኔ[5]) ፡፡

ከዚህ በላይ ከተገለፀው የዩኔስኮ ሰነድ የምንረዳው ባህል ለአገር ልማት የሚያበረክተውን ከፍተኛ አስተዋፅዖ ነው፡፡ በመሆኑም ባህልን ኋላ ቀርና ለልማትና ለዘላቂ ቴክኖሎጂዎች መስፋፋት እንቅፋት እንደሆነ አድርጎ ከመቁጠር ይልቅ ባህላዊ ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋትና በማልማት ለአንድ ሀገር የገቢ ምንጭ የሚፈጥር ፣ለዜጎች የሥራ ዕድል እንደሚቻል ነው፡፡

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱነትን የባህልና የልማት ትስስርን የሚያሳዩ ማስረጃዎች የሚያመላክቱት የዘመናዊነት አስተሳሰብ/አተያዩ አቀንቃኞች እንደሚሉት ለአንድ ሀገር ልማት የሚበጀው ጉዳይ ዋነኛ መሰናክሎች ናቸው የሚሏቸውን ባህላዊ ሁኔታዎች አሽቀንጥሮ በመጣልና ዘመናዊነትን በመጠማት ሳይሆን ይልቁንም ለባህላዊ መሠረቶች

ትኩረት ሰጥቶ ከልማቱ ጋር በማዋሃድ ሁለንተናዊ እድገት ማምጣጥ እንደሚቻል ነው፡ ፡ ስለዚህም ባህል የማይነካው ማህበረሰባዊ ጉዳይ ስለሌለ ስለ አንድ ማህበረሰብም ሆነ አካባቢ ልማት ስናወራ ባህሉን አብሮ ማየትና ራሱን እያለሙ የልማት መሣሪያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑም መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም ይህ የባህልና ልማት ትስስር በዋግኽምራ ብሔረሰብ እንዴት ባለ ሁኔታ እንደሚገለፅ ማመልከት ላይ ይሆናል፡፡

## 2.2.4. ግብርና ኤክስቴንሽን

የግብርና ኤክስቴንሽን ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገራችን ብቅ ያለው እ.ኤ.አ በ1931 ዓ.ም በአምቦ ትምህርት ቤት እንደሆነ የመስኩ ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡ የግብርና ኤክስቴንሽኑ አገልግሎቱ የታወቀው ግን እ.ኤ.አ በ1953 በቀድሞው ዓለማያ እርሻ ኮሌጅ በአሁኑ መጠሪያው ሀሮማያ ዩኒቨርስቲ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ (Spielman and Others, 2011)፡፡ አገልግሎቱም የሚሰጠው የተሻሻሉ ዘሮችን ፣ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያንና ብድርን በአነስተኛ አርሶ አደሮች በማቅረብና ከኋላቀር አስተራረስ ዘዴ አላቆ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ግቡ አድርጎ በመነሳት ነው፡፡

በ1960ዎቹ የኤክስቴንሽን አገልግሎች እየተጠናከረ መጥቶ በተቀናጀ ፓኬጅ ፕሮጀክት አማካኝነት ለበርካታ ገበሬዎች ይሰጥ ጀመር፡፡ በ1980ዎቹ የኤክስቴንሽን አገልግሎቱ በፍጥነት እየታወቀና እየተለመደ ስለመጣ ስልጠናና ጉብኝት (Training and visit) የተሰኙትን አገልግሎቶች አካቶ በአለም ዓቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች እየተገዛ መስፋፋት ቀጠለ፡፡ ቆየት ብሎ ደግሞ አሳታፊ ሰርቶ ማሳየትንና የኤክስቴንሽን ስልጠና ዘዴ (Participatory demonstration and extension system (PADETS) መርሀ ግብርን ከስልጠናና ጉብኝት ጋር በማቀናጀት ምርጥ ዘሮችን እና ሰው ሰራሽ የኬሚካል ማብቀያዎችን ለአርሶ አደር በማሰራጨት በተካሄደው እንቅስቃሴ ከ2007-2008 ለዘጠኝ ሚሊዮን አርሶ አደሮች እንደተዳረሰ ያስረዳሉ (Spielman and Others, 2001)፡፡

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ያለው የግብርና ኤክስቴንሽን ዘዴ ከላይ የተጠቀሰው የPADETS መርሃ ግብር ሲሆን በአርሶ አደሩ ማሳ ላይ ትኩረት በማድረግ የግብርና ግብዓቶችንና ብድር በማቅረብ እና በገጠር የልማት ኮሚቴዎችን በማደራጀት ለሴቶችን ለወጣቶች ትኩረት በሚሰጥ መልኩ እየተተገበረ እንደሚገኝ ከላይ የተጠቀሰው ማስረጃ

ያመለክታል። በኤክስቴንሽን አገልግሎቱ የተካተቱ የምግብ እህል ፓኬጆች ፤ በቆሎ ፣ ስንዴ ፣ ጤፍ ፣ ገብስ ፣ ማሽላን ለገበያ አዋጭ የሆኑ ቡና ፣ ለውዝ ፣ ቀይ ሽንኩርት ፣ ቲማቲም ፣ ጥቅል ጎመን ፣ ካሮትና ስኳር ድንች የመሳሰሉት ሰብሎችና አትክልቶች ናቸው። ከእነዚህም በተጨማሪ የእንስሳት እርባታ ፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃ ፣ የድህረ ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ፤ ለኤክስቴንሽን ፓኬጆቹ ተግባራዊነት እንዲረዱ የቀረቡት ግብዓቶች ደግሞ ሰው ሰራሽ (ኬሚካል)ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ናቸው። (Carlssol and Others, 2005)።

አርሶ አደሩ እነዚህን ግብዓቶች ለመግዛት እንዲችል ከመንግስት የብድር አገልግሎት የሚቀርብለት ሲሆን በግብርናም ሆነ በዲፕሎማ ደረጃ የሰለጠኑ እስከ ሶስት የሚደርሱ የልማት ሰራተኞች በአካባቢው ተመድበውለት ፓኬጆቹን እንዴት እንደሚተገብር ስልጠናና ድጋፍ ይሰጠዋል ። ይሁን እና ይሄ በአገር ዓቀፍ ደረጃ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ እየተተገበረ ያለው የግብርና ኤክስቴንሽን መርሀ ግብር በአንዳንድ አካባቢዎችና በብሄራዊ ክልላዊ መንግስቱ ዝቅተኛ መሆኑ ማህበረሰቡን በልማት ወደኋላ የቀሩ ካሰኙት ምክንያቶች አንዱ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ የዋግኽምራ ብሄረሰብ ባህል ያደረገው አስተዋፅኦ በጥናቱ ይፈተሻል።

## 2.2.5. ጤና ኤክስቴንሽን

የልማት ጉዳይን ስናነሳ ለማህበረሰቡ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ልማትን የሚመለከት እንደሆነ ቀደም ብሎ በስፋት ተገልጿል። ማህበረሰቡ በተገለፀው መልኩ እንዲለማ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች አንዱ ደግሞ ጤንነቱ የተጠበቀ እንደሆነ ነው። ጤንነቱ ያልተጠበቀ ማህበረሰብ እራሱንም ሆነ አካባቢውን ለማልማት አይችልም። ስለሆነም የጤና ጉዳይ አንዱ የልማት ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ከባህል ጋር በጣሙን ስለሚገናኝ የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር አፈፃፀም ከዋግኽምራ ባህል ጋር ተያይዞ በዚህ ጥናት አንዱ የሚተኮርበት ጉዳይ ይሆናል። በሀገር ዓቀፍ ደረጃ በመንግስት ታቅደው እየተሰሩ ካሉት የልማት መርሃ ግብሮች የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር አንዱ ነው። መርሃ ግብሩ የተጀመረው የኢፌድሪ የጤና ጥበቃ ሚንስቴር በ1995 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አጠባበቅ ሽፋንን ለማስፋፋት አዲስ የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር እቅድ

በማድረጉ ነው (የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 1995 ዓ.ም)፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር በማህበረሰብ ጤና ላይ የተመሰረተ የግል የጤና እንክብካቤ አቅርቦት ስርዓት ሲሆን አስፈላጊ የሆኑ የጤና የማስፋፊያና የመከላከያ አገልግሎቶችን ማቅረብ ላይ ያለመ ነው፡፡ በመጀመሪያ ላይ እንዲተዋወቅ የተደረገው በሀገሪቱ ከከተማ ራቅ ባሉ አካባቢዎች ለሚገኙ ማህበረሰቦች አስፈላጊ የሆነ የጤና አገልግሎት ለማቅረብ አለመቻሉ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቢሆንም አሁን ግን በከተሞችም የጤና ኤክስቴንሽን አገልግሎት እየተካሄደ ይገኛል፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን መርሃ ግብር አገልግሎቶች የአርብቶ አደሩን ፣ የአርሶ አደሩን እና የከተማ ነዋሪ ህዝቦችን ፍላጎቶች ፣ ጥያቄዎችና የሚጠብቋቸውን ሁኔታዎች ለማሟላት እንዲቻል ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህ መርሃ ግብር የሚሊኒየሙን የልማት ግቦች ለማሳካት በጣም ወሳኝ ተቋማዊ ማዕቀፍ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

የጤና ኤክስቶንሽን መርሃ ግብር አላማ ብዛት ያለው የሃገሪቱ ህዝብ ወደሚኖርባቸው ገጠራማ አካባቢዎች ተፈላጊ የጤና አገልግሎቶቸን ማዳረስ ነው፡፡ በዚህ ዓላማ ስርም አስፈላጊ የጤና አገልግሎቶችን በፍትሐዊነትና ባልተማከለ አሰራር የማግኘት እድልን በመንደርና በአባወራ ደረጃ በማሻሻል የጤና ግንዛቤን ፣ እውቀትንና ክህሎትን በማህበረሰቡ አባላት መካከል በማሳደግ ባለቤትነትንና ተሳትፎን በማረጋገጥ የጤና አገልግሎቶችን በማግኘት ረገድ የፆታ እኩልነትን ማራመድ ፣ በማህበረሰቡና በጤና ተቋማት መካከል ያለውን ክፍተት በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በኩል ለማገናኘት ፣ የአካባቢው ጤና አገልግሎቶችን አጠቃቀም ለማሻሻል ፣ የወሊድና ህፃናት ሞትን ለመቀነስና ጤናማ የህይወት ዘይቤን ለማራመድ የሚውሉ አላማዎችን ይዞ የተዘጋጀ ነው (የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 1995 ዓ.ም)፡፡

በመርሃ ግብሩ የሚተገበሩት የጤና አገልግሎቶች በዋናነት በስራቸው ብዙ አገልግሎቶችን የያዙ አራት የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ናቸው፡፡ ከእነሱም ውስጥ አንደኛው በሽታን የመከላከልና የመቆጣጠር ፓኬጅ ሲሆን በስሩም ኤች አይቪ ኤድስን እና በፆታ ግንኙነት ሳቢያ የሚተላለፉ በሽታዎችንና ቲቪን መከላከል ፣ ወባን መከላከልና መቆጣጠር ፣ የመጀመሪያ እርዳታና አስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎች የተሰኙ አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የቤተሰብ ጤና ክብካቤ ፓኬጅ ነው፡፡ ይህም የእናቶችና የህፃናት ጤና እንክብካቤ ፣ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ፣ በሽታን መከላከል ፣ የተመጣጠነ ምግብ አዘገጃጀትና የወጣቶች የስነ ተዋልዶ ጤና እንክብካቤ

የተሰኙ አገልግሎቶችን ያካተተ ነው፡፡ በሶስተኛነት የተቀመጠው ደግሞ የግል ጤናና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ፓኬጅ ሆኖ በስሩ የአይነ ምድር አወጋገድ ፣ የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ፣ የንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና አቀራረብ ፣ የጤናማ ምግብ አያያዝ ፣ ንፁህ የመኖሩያ አካባቢ እንክብካቤና የግል ንፅህና አጠባበቅ የተሰኙ አገልግሎቶችን ይዟል፡፡ አራተኛው የጤና ትምህርት አገልግሎትና ተግባቦት ላይ የሚያተኩር አገልግሎት ነው (የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 1995 ዓ.ም ፣ Path Finder, 2008)፡፡ ይህንን አገልግሎት ከግብ ለማድረስ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ካላቸው ግዜ 75 በመቶ ያህሉን ቤት ለቤት በመዘዋወር የማስተማር ተግባራትን በማካሄድ ማሳለፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በእነዚህ ጉብኝቶች ወቅት ባለሙያዎቹ እናቶች ለህፃናት እንክብካቤ ሲያደርጉ መርዳት ፣ የተመጣጠኑ ምግቦች ሰርቶ አብስሎ ማሳየት ፣ የመፀዳጃ ቤት እና የቆሻሻ ማስወገጃ ጉድጓዶች አብሮ መስራትና የመሳሰሉትን ስራዎች ከማህበረሰቡ ጋር አብረው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ ይሄ ተግባር ደግሞ ማህበረሰቡ እስከ ዛሬ ሲጠቀምበትና ሲፈፅመው ከነበረው የአኗኗር ባህል ጋር በእጅጉ የሚያያዝ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ስለ ግልና የአካባቢ ጤና እንክብካቤ ፣ ስለ ተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥርና ህክምና ፣ ስለቤተሰብ ምጣኔና የአመጋገብ ስርዓት የራሱ የሆነ እምነት ፣ ልማድና ባህላዊ ወይም ሀገር በቀል ዕውቀት (Indigenous knowledge) አለው፡፡ አሁን ደግሞ ዘመናዊ አገልግሎቶችን እንደ አዲስ እየተማረ እንዲተገብር እየተደረገ ነው፡፡ በመሆኑም በነባርና በአዲሱ የአኗኗር ብልሃቶች መካከል ትግልና ተቃርኖ ስለሚፈጠር የአዲሱን ተግባራዊነት ተግዳሮት ይገጥመዋል፡፡ በዚህ ተግዳሮት ምክንያት ደግሞ ልማቱ ወደኋላ እንዲጎተት መንስዔ ሊሆን ይችላል ተብሎ ስለሚታሰብ የጤና ኤክስቴንሽን አተገባበር እንደ ግብርናው ሁሉ በዚህ ጥናት የሚፈተሽ ሁለተኛው አብይ ጉዳይ ይሆናል፡፡

## 2.3. ንድፈ ሃሳባዊ መሠረቶች

በአንድ አካባቢ/ብሔረሰብ የሚሰበሰብ መረጃ በሁለት መልኩ ሊተነተን ይችላል፡፡ የባህሉ ባለቤት ስለ ባህሉ ምንነት የሚሰጠውን ገለፃ መሰረት በማድረግና የባህሉ ባለቤት ባልሆነው በተመራማሪው የምንነት መገለጫ ፤እነዚህም እንደቅደም ተከተላቸው በተከታታይ ውስጣዊ እና ውጫዊ እይታ ይባላሉ (Dundes,2007:88 ፡፡ ውስጣዊ እይታ አንድ የፍክሎር/ባህል ጥናት በባህሉ ባለቤት አመለካከት የሚሰጠው ትርጉም ሲሆን ይህም የአንድን ባህል ማህበረሰባዊ ፋይዳ ሊገልጽ የሚችለው የባህሉ ባለቤት ነው

የሚል ነው ፤ ውጫዊ እይታ ደግሞ ስለ አንድ የተወሰነ አካባቢ ባህል ፣ የባህሉ ባለቤት ባልሆነው የሚሰጥ ግንዛቤ ወይም ትርጉም ነው፡፡ ውስጣዊ እይታን ከውጫዊ እይታ የሚለየው ተመራማሪው ለረጅም ጊዜ በጥናት ቦታዊ ቆይታ በማድረግ መረጃውን በተሳትፏዊ ምልከታ እና በቃል መጠይቅ በመሰብሰብ አጥኚው ይህንን ባህል ከኢኮኖሚ ወይም ከስነ-ምህዳር ጋር ሳያስተያይና አንድን ንድፈ ሃሳብ ለመፈተሸ ሳያውለው የባህሉን ባለቤቶች ስለ ባህላቸው የገለጹትን ብቻ በስራው ሲያሰፍር ነው፡፡

እኔም ጥናቱን ያከናወንኩት በሁለቱም እይታዎች ነው፡፡ ምክንያቱም የመረጃ አቀባዮቼ ስለ ፎክሎርቹ ልዩ ልዩ ዘውጎች የገለጹትን አደራጅቼ ገለፃ አድርጌያለሁ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በመስኩ/ፎክሎር ያለኝን ግንዛቤ መሠረት በማድረግ የፎክሎሮቹን ክዋኔ ከተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች አንፃር አብራርቻለሁ፡፡ ለውጥና ቀጣይነታቸውን ገልጫለሁ፡፡ በባህሎቹ/ፎክሎሮቹ ዘውጎች ክዋኔ ወቅት የሚታዩ አሉታዊ ተግባራትንም ጠቁሜያለሁ፡፡ ስለዚህ ባህሉን እንደማወቁ የማውቀውንና የተመለከትኩትን እንዳለ አላቀረብኩም፡፡ ስለሆነም የባህሎቹን ክዋኔና አውድ ከመግለጽ በተጨማሪ (Durnti,1997) እንደገለፁት ግንዛቤ ተኮር የማብራራት ዘዴን በመጠቀም መረጃውን ከተለያዩ ንድፈ ሃሳባዊ ጠገጎች (Theoretical form work) አንፃር ስለተነተንኩ ውጫዊና ውስጣዊ እይታን ተግባራዊ አድርጌያለሁ፡፡

ተመራማሪው የሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን የመረጣቸውን ንድፈ ሃሳቦች ለምን እንደመረጣቸው በምክንያት አስደግፎ መግለፅ ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን አስመልክተው ያለው (1998 ፣ 452) እንዳሰፈሩት ተመራማሪው የመረጃ መተንተኛ ዘዴን ሲመርጥ ምን ሊያደርግበት እንደሆነና ለምን እንደመረጠው መግለፅ ይኖርበታል፡፡ በተለያዩ ዘመናት በፎክሎር ላይ ጥናትና ምርምር ያደርጉ ባለሙያዎች የሰበሰቧቸውን የፎክሎር ዘውጎች መረጃ ለመተንተት የተጠቀሙባቸውን አስራ ሁለት ንድፈ ሃሳቦች/እይታዎች (Dorson, 1972) ዘርዝረዋል[7]፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ክበራ ስነ ስርዓቶች ላይ ጥናት የሚያደርግ ደግሞ የተለያዩ እይታዎችን በመጠቀም መረጃውን ሊተነትን እንደሚችል (Suoboda, 2010) በማስረገጥ የአንድን ባህላዊ ክዋኔ ከታሪክ ጋር አጣቅሶ

[7] እነዚህም Historical geographical, Historical-reconstraction, ideologics functional , psyco analytical, structural, oral formatic, cross-cultural, folk cultural, mass-cultural, hemisoheric and contextual ናቸው፡፡

የሚመለከትበት ዝግመተ ለውጥ እይታን ለማህበረሰቡ ባህላዊ ክዋኔው ምን ጠቀሜታ እንዳለው/ እንደሚሰጠው/ የሚመለከትበት ፋይዳዊ እይታን ፣ ዘውጉ በሚከወንበት ወቅት የሚታዩ ውቅራቸውንና ትስስራቸውን የሚመለከትበት መዋቅራዊ እይታን ፣ በክዋኔው ወቅት የሚተገበሩ ድርጊቶችንና የቁሳቁሶችን ተምሳሌታዊ ፍቺ የሚተነትንበትን ተምሳሌታዊና ትርጓሜያዊ እይታን በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ የመተንተኛ ሥልቶች እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

በባህል/ፎክሎር ጥናት የንድፈ ሀሳብ ጠገግ አጠቃቀም ዙሪያ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ አመለካከት አላቸው፡፡ አንዳንዶቹ ሌሎች የጥናት መስኮች የሚከተሏቸውን የንድፈ ሀሳብ መሠረቶችን ተጠቅሞ ባህልን ማጥናትና በዚያ ማዕቀፍ ውስጥ መገዛት እንደሚገባ ይገልፃሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የባህሉ ባለቤት እንደሆነው ማህበረሰብ ፣ እንደሚገኝበት አካባቢና ሁኔታ የተለያዩ መልክ ስላለው የባህል ጥናት የግድ በተለመዱት የንድፈ ሃሳብ ጠገጎች (Theoretical Framework) መገዛት የለበትም ፤ መጠናት ያለበት እንደተገኘበት ማህበረሰብ ሁኔታ የራሱ በሆነ የንድፈ ሃሳብ እይታ ነው የሚሉም አሉ፡፡

Ben Amos (1975) “Folklore in Africa society” በሚል ርዕስ በፃፉት መጣጥፍ በመነሻ ላይ ያቀረቧቸው ፎክሎር በአፍሪካ ምንድን ነው? አፍሪካዊው በባህሉ ውስጥ ስላሉት ትረካዎችና ቃል ግጥሞች ምን ያውቃል? በኀሊናውስ እንዴት ይቀርፃቸዋል? ከቅርፃቸውና ከይዘታቸውስ ምን ይርዳል? በማህበረሰቡ ውስጥስ እንዴት በአግባቡ ይገለገልባቸዋል? ለእርሱስ ምን ማለት ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች በቅድሚያ በማንሳት መልሶቹ ከአንዱ የአፍሪካ ማህበረሰብ ወደ ሌላው ስንሄድ ሊለያዩ እንደሚችሉ የተለያዩ ሀገራት ምሳሌ በማቅረብ የባህል/የፎክሎር ጥናት በአንድ ወጥ ንድፈ ሃሳባዊ ቀመር ሊካሄድ እንደማይችል በዝርዝር ያስረዳሉ፡፡ ይህም የአፍሪካ ፎክሎር የተለየ ባህሪ ፣ ቅርፅና ይዘት ያለው መሆኑን በመገንዘብ የሚያጠናው እንደራሱ ባህሪ እንጂ በአውሮፓዊ መንገድ መሆን እንደሌለበት ለመረዳት ያስችላል፡፡ በመሆኑም በአፍሪካ የእያንዳንዱ ባህል ተግባቦት ሥርዓት የሚመሠረተው የፎክሎር ዘውጎችን የመገንዘብ (Cognitive) ፣ የመግለፅና (Expressive) የማህበራዊ ገፅታዎችን (Social features) በመለየትና በመተንተን ላይ እንደሆነ በማሳየት ፎክሎር ሲጠና እነዚህን ገፅታዎች

ከግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚገባና ይህ ሲሆን ደግሞ የአፍሪካ ፎክሎር[8] መጠናት ያለበት በራሱ አፍሪካን በሚገልጽበጽ ነባራዊ ሁኔታ እንጂ ከሌሎች ንድፈ ሃሳቦች ጋር አስገድዶ ለማዘመድና ለማስገዛት በመጣጠር እንዳልሆነ ያስገነዝባሉ (Ben Amos,1975)

Alan Bamard በበኩላቸው የFranz Boasን አንፃራዊ የባህል አስተሳሰብ ወይም ባህላዊ አንፃራዊነት (Cultural relativism) ንድፈ ሀሳብ ለባህል ጥናት ያለውን ጠቃሚነት ሲያብራሩ Boas እንደሚለው እያንዳንዱ ባህል ከሌላው የሚለይበት የራሱ የሆነ ባህሪ ስላለው መታየት ያለበት ከዚህ ከራሱ ባህሪ አንፃር እንጂ ከሌላ ባህል ጋር እየተነፃፀረ መሆን የለበትም፡፡ ባህል በራሱ ማህበረሰቡ ዓለምን እንዴት እንደሚገነዘበው የሚወስን ነው፡፡ ስለዚህ የተለያዩ ባህሎች እንደራሳቸው ውስጣዊ ሁኔታዎች ይታያሉ እንጂ ሁሉን በአንድ የሚለካና ደረጃ የሚሰጥ ዓለማቀፋዊ መለኪያ የለም፡፡ አንዱ ባህል ውስጥ ያለ ጠንካራ ነገር ሌላው ዘንድ ቢጎድል ያኛውም የራሱ ጠንካራ ነገር አለውና እርስ በእርስ አወዳድሮ አንዱን የሰለጠነ ሌላውን ኋላ ቀር ማለት አይቻልም፡፡ ሁሉም አንፃራዊ በሆነ መልኩ መታየት አለበት የሚል አተያይ እንደሚራመድ ገልፀው ይህም ለባህልም ሆነ ለስነ ሰብእ ጥናት ጠቃሚ አካሄድ ነው ይላሉ (Bamard, 2004; 100-101)፡፡ በሌላ እይታ ደግሞ እነ (Sims and Stephens) ባህልን ለመተንተን የተለያዩ ንድፈ ሃሳቦችን መጠቀም እንደሚቻል ጠቅሰው ፤ አንዱ መንገድ ፎክሎር ለማህበረሰቡ ከሚሰጠው ጥቅም አንፃር እየተመለከቱ መተንተን ሲሆን ይህን ትንታኔ ስልት መነሻ የሚያደርገው ተግባራዊነት ንድፈ ሃሳብ እንደሆነና በዚህም የBascom[9]ን አራት የፎክሎር ተግባራት ወይም ጠቀሜታዎች መሠረት በማድረግ ባህሉ ለማህበረሰቡ ከሚሰጠው ጠቀሜታዎች አንፃር ሊጠና እንደሚችል በመጥቀስ ያብራራሉ (Sims and Stephens,2005)፡፡

---

[8] Ben Amos ለፎክሎር ጥናት ያነሱት ሃሳብ ለባህል ጥናትም የሚያገለግል ስለሆነ ነው እዚህ የተጠቀሰው፡፡

[9] William Bascom በ1954 እ.ኤ.አ ባሳተመው መጣጥፍ "Bascom argued that folkore can serve four primary functions in a culture" folklore lets people escape from repression imposed up on them by society folkoire validates culture, justifying its ritual and institutions to those who perform and observe them. Folklore is pedagogivdevive which reinforces moral and builds withFolklore a means of applying social pressure and exercising social control (Wikipedia folklore (creative commons).

ከዚሁ ጋር በማያያዝ በአሁኑ ሰዓት የባህል ጥናት ትኩረት ሰዎች ባህላዊ መገለጫቸው በሆነው በአንድ የተለየ የክዋኔ አውድ ውስጥ እርስ በእርስ እንዴት እንደሚግባቡ ተንትኖ ማሳየት ነው፡፡

በባህል/በፎክሎር ጥናት የትንታኔ አከል የሆኑት ነገሮችም ነገረ ይዘቱና የክዋኔው አውድ ፣ በዚህም የሚንጸባረቁ አስተሳሰቦች መስተጋብሮች ውስብስብነት ፣ የክዋኔው ተያያዥነት ፣ ታዳሚዎቹ ፣ ተመራማሪዎቹና ማህበረሰቡ ናቸው፡፡ ስለሆነም አጥኚው ከዚህ አኳያ ትንታኔውን ለማድረግ ከተለያዩ ንድፈ ሃሳቦች አንፃር ተመልክቶ መረጃውን መሰብሰብ አለበት ይላሉ (Sims and Stephens, 2005)፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት የBen Amosንና የFranz Boasን አስተሳሰብ ከግምት ውስጥ አስገብቶ የሚጠናው ባህል የራሱ ቅርፅ ካለው በዚያው የንድፈ ሃሳብ ማዕቀፍ እንደሚገዛ ከግምት ውስጥ በማስገባት ፣ የእነ Sims and Stephensንም አተያይ በመቀበል የሚገዛባቸውን የንድፈ ሃሳብ ማዕቀፎች መነሻ አድርጎ የሚሠራ ይሆናል፡፡

### 2.3.1. ተግባራዊነት ንድፈ ሃሳብ (Functionalist Theory)

በየትኛውም ቦታና በማንኛውም ማህበረሰብ የሚከወን የፎክሎር ዘውግ ክዋኔ በከዋኙ ማህበረሰብ እይታ ለዚያ ማህበረሰብ የሚሰጠው ጠቀሜታ አለ፡፡ Oring (1976:68) የፎክሎርና ፋይዳ ምንነት አስመልክተው የሚከተለውን አስፍረዋል፡፡ የማህበረሰቡን የህልውና ሂደት ለመጠበቅና ለማህበራዊ አወቃቀሩ ቀጣይነተት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ነው፡፡ ባህል/ፎክሎር ለማህበረሰቡ የሚፈይደው ነገር ካልኖረ ኅልውና ሊኖረው እንደማይችል ነው፡፡ Vansina (1985:100) እንደሚከተለው የገለጹት ማንኛውም ባህላዊ የሆነ መልዕክት ዓላማና የሚፈይደው ነገር አለ ፤ ካልሆነ ኅልውና አይኖረውም፡፡ ያ የባህል ነገረ ይዘት ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ጥቅም ፍይዳ ይባላል፡፡ Wilson1 (1965:234)ም ለፎክሎር ኅልውና ምክንያቱ የሰዎችን መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላቱ ነው በማለት ተመሳሳይ ሃሳብ አስፍረዋል፡፡

ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ አንድ ባህል ፣ ባህል ሆኖ ለመቀጠል ለማህበረሰቡ የሚያበረክተው አንዳች ፋይዳ መኖር እንዳለበት የሚያመለክት ሲሆን ባህል ማህበረሰቡን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የሚገልፅበትና ማህበረሰቡም ለማስተማር ፣ ንቁና ጥበበኛ

ለማድረግ ፣ ውስጣዊ ስሜቱን ለመግለፅና ከራሱ ከማህበረሰቡ ህግና ደንብ ለማምለጥ እንዲሁም ባህሉ ራሱን ስሩን ለማጠንከር ያገለግላል፡፡ ስለሆነም ባህል ለማህበረሰቡ ከሚሰጠው ፋይዳ አኳያ ታይቶ መዳኘት አለበት (Sims and Stephens, 2005:174; Bascom, 1954 : 334; Okpewho, 1992 :10)፡፡

በዚህ ረገድ ባህል ለማህበረሰቡ ከሚሰጣቸው ጥቅሞች አንፃር እየተመለከቱ ማጥናት ማህበረሰቡ ስለራሱ ፣ ስለአካባቢውና ስለዓለም ያለውን አተያይ ለማወቅ ዋነኛ ስልት ነው (Sims and Stephens, 2005 :1974-176 ፣ ፈቀደ ፣ 1991 ፣ 18-20)፡፡ ማህበረሰቡ ባህሉ ለሚደነግጋቸው ሥርዓትና ደንቦች ይገዛል ፣ የተገዛውን ያህል ደግሞ ያፈነግጣል፡፡ ማፈንገጡን የሚገልፅበት መንገድ ደግሞ በባህሉ/ፎክሎሩ ዘውጎች በራሳቸው ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ባህላዊ ደንቦች እንዳይጣሱ ባህሉ ራሱ ያስጠነቅቃል ፣ ይቆጣጠራል ፣ ቅጣትም ይጥላል፡፡ በዚህም የማህበረሰቡን የጋራ ሕይወት በመጠበቅ ባህላቸው ዘላቂነት እንዲኖረው በማስቻል የማህበረሰቡን የሕይወት ዑደት እንዲጠብቅ የማድረግ ተግባራትን ይፈፅማል፡፡ Finnegan (1984:330)ም አንድ የፎክሎር ዘውግ ስነ-ቃል በርካታ ፋይዳዎች ሊኖሩት እንደሚችል ተረትን በመጥቀስ ህፃናትን የማስተማር ፣ ማህበራዊ ግንኙነት እንዲጠነክር ፣ ሕፃናት የማህበረሰቡን ወግና ልማድ እንዲጠብቁና መልካም ሥነ-ምግባር እንዲላበሱ የማድረግ ፋይዳ እንዳለው ገልፀዋል፡፡ ማህተመ ሥላሴም (1961 ፣ 47-48) ቃል ግጥም ስራን ለማፋጠንና ድካም እንዳይሰማ ለማድረግ ፋይዳ እንዳለው እንዲህ አስፍረዋል ፣ "... ከዚህም በቀር ገበሬዎች በማህበር በሚሰሩበት ጊዜ ድካማቸውን በግጥም ያቃልላሉ ፤ እረኞች ከብቶቻቸውን በሚጠብቁበት ወቅት ብቸኝነት እንዳይሰማቸውና ቀኑ እንዳይረዝምባቸው ልዩ ልዩ ግጥሞችን ያሰማሉ፡፡" Alembi (2002:50) ም Kabira እና Mutahi (1988 : 10-41) በመጥቀስ እንዳሰፈሩት ከቃል ግጥሞች ተግባራት መካከል ማስተማር ፣ መረጃ መስጠት ፣ ማዝናናት ፣ ባህልን ማዳበርና ማስተላለፍ ፣ መምከርና ማሰልጠን ይጠቀሳሉ በማለት ከማህተመ ሥላሴ ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ አስፍረዋል፡፡

Jabbour (2004:18-19) የፎክሎርን ፋይዳ በባህል ውስጥና ከባህል ውጭ መመልከት እንደሚቻል ሲገልፁ ደግሞ ወደ ባህል ውስጥ ስንመለከት ፍክሎር የአንድን ማህበረሰብ ልማድ ያንፀባርቃል ፤ እንዲህ በማድረጉም የማህበረሰቡን የማንነት ስሜት ያጠናክራል ፤ ከማህበረሰቡ ውጭ ብንመለከት ደግሞ ለተለያዩ ማህበረሰቦች ባህል ልውውጥ ፣

መስተጋብር እና ትስስር ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል ብለዋል (Jabbour, 2004:18-19)፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የመስኩ ምሁራን እንደሚያስረዱት ባህሉ በራሱ የማስተማሪያና የመግባቢያ መሣሪያ በመሆኑ አዲስ የመጣውን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንደየቤተሰብ ምጣኔ ዘዴ ያለውን ለማህበረሰቡ ለማስተማርና እንዲቀበለው ለማድረግ በዚያው በባህሉ አማካይነት ሥራ ላይ መዋል አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን ንድፈ ሃሳብ ተጠቅሞ ከዚህ ጥናት ዓላማ ጋር በማያያዝ መፈተሽ ተገቢነት አለው፡፡ ከዚህም በላይ ባህሉ በራሱ ስለ ልማት አቅጣጫ ያለው ቀዳሚ አገር በቀል ዕውቀት (Indigenous knowledge) ካለና የመጣውን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የማህበረሰቡ ባህል የሚቀበለው ወይም የሚቃወመው መሆኑን ለማየት ይህ ንድፈ ሃሳብ ለጥናቱ ተመርጧል (Green, 1997;386)፡፡ ሆኖም የBascom ንድፈ ሃሳብ የራሱ የሆነ እጥረት እንዳለበት Sims Mullen ጠቅሰው "…Bascom's system ignores the way folklore questions, critiques, protests, and sometimes undermines stability" ይላሉ፡፡ Mullen (2003) in Sims and Stephenes (2005, 175) ሌሎች ደግሞ ንድፈ ሃሳቡ ባህልን ከሚሰጠው ጠቀሜታ አንፃር ብቻ የሚመለከት በመሆኑ የተሟላ እንዳልሆነ ያነሳሉ፡፡ "Functionalism is a theory which treies to explain social and cultural institutions and relation interms of the functions they perform within the systems; heavily criticized because it fails to talk accunt of historical factors such as change, conflict and disintegration (Gardener and David,1996).

ከዚህ እንደምንገነዘበው ባህሉ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ብቻ በማየት ጥናቱን የተሟላ ማድረግ እንደማይቻል ነው፡፡ ስለሆነም ከተግባራዊነት ንድፈ ሃሳብ በተጨማሪ የባህል ዋነኛ መገለጫ የሆነውን የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ በደጋፊነት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

### 2.3.2. የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ /Performance Theory/

ለአንድ የባህል/ፎክሎር ዘውግ ኅልውና መሠረቱ ክዋኔ ነው፡፡ ክዋኔ የምንለው ደግሞ ቁሳዊው ቦታ ከሰብዓዊ ንክኪ ጋር ባለ ግንኙነት በአካላዊ እንቅስቃሴና ድምፅ አማካኝነት የሚበለጽግ ንግግር ነው፡፡ Sims and Stephens (2005:26) Roger Abramsን ጠቅሰው እንደገለጹት Roger Abrams የክዋኔን ጽንሰ ሀሳብ የሚገልጹት የአንድ

ማህበረሰብ አባላት ማንነታቸውን የሚገልጹበትና የሚያጠናክሩበት ባህላዊ ድንጋጌ ነው፡፡ ስለዚህ ያለ ክዋኔ የፎክሎር ዘውግ ምንነት በትክክል ሊገለጽ ወይም ሊታወቅ አይችልም፡ ፡ ህያው የሚሆነውም ሲከወን ነው፡፡ Finnegan (1977:28) የፎክሎር ዘውግ አካል ስለሆነው ቃል ግጥም ክዋኔ ሲገልጹ ቃል ግጥም ያለ ክዋኔ ኅልውናውም ሆነ ዘላቂነት አይኖረውም ብለዋል፡፡

ይህም በመሆኑ በአንድ ባህላዊ/ፎክሎራዊ ጥናት የማህበረሰቡን ቃላዊ ጥበባት /Verbal arts/ ብቻ ሰብስቦ የተወሰኑ ንድፈ ሃሳቦችን በመጠቀም እየተነተኑ ስለማኅበረሰቡ ፎክሎር ውሱን የሆነ ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ ይቻል ይሆናል፡፡ ሆኖም እነዚህን የባህል ዘውጎች ማህበረሰቡ ሲተረካቸው ፣ ሲዘፍናቸው ፣ ሲያንጎራጉራቸው ፣ ሲያከብራቸው በጥቅሉ የራሱን ሥርዓት ተከትሎ ሲከውናቸው ስናይ የሚሰጡት ትርጓሜ የተለየና ሚዛን የሚደፋ ይሆናል፡፡ ለባህል ጥናት ክዋኔ ብቻ ሳይሆን የክዋኔው አውድ /Context/ ከዋኙና /Performer/ ተሳታፊዎቹ /Audiences/ ትልቅ ድርሻ አላቸው (Green, 1997; Sims and Stephens, 2005)፡፡ ክዋኔው ብቻም ሳይሆን ማህበረሰቡ ስለክዋኔው ምንነትና ፋይዳ የሚሰጠውን ትርጓሜ ምን እንደሆነ መገንዘብም አስፈላጊ እንደሆነ አጽንኦት ሰጥተው ያስረዳሉ፡፡

የፎክሎርን ነገረ ይዘት /text/ ስናጠና ከአውዱ ነጥለን ለቡድኑ የሚሰጠውን ጥቅም በቀላሉ መናገር አይቻልም፡፡ ነገረ ይዘቱን /text/ ከሰፊ የክዋኔ አውድ ላይ ሲከወን መመልከትና መገንዘብን የግድ ይላል፡፡ አንድ የፎክሎር ነገረ ይዘት /text/ ከሰፊው የፎክሎር ባህር ውስጥ አንድ ቅንጣት እንደሆነና ለምን እንደሚጠቅም የሚያውቁትና መግለፅ የሚችሉት የፎክሎር ቡድኑ አባላት ናቸው፡፡ በመሆኑም ፎክሎረኛው ነገረ ይዘቶቹን /texts/ ሌጣቸውን ይዞ ለትንታኔ ከመነሳቱ በፊት በክዋኔ አውዳቸው ላይ በጥንቃቄ መመልከትና የቡድን አባላቱን ስለነገረ ይዘቱ /text/ ትርጉምና ጠቀሜታ መጠየቅ ፣ ማወያየትና ለመገንዘብ መሞከር አለበት (Sims and Stephens, 2005 ፣ 138)፡፡

በዚህም መሠረት አንድ ፎክሎረኛ በትክክል የፎክሎር ጥናት አደረገ የሚባለው ያ የፎክሎር ዘውግ እንዴት ፣ የት ቦታ ፣ በምን መሣሪያዎች ታጅቦ ፣ በእነማን ፣ ወዘተ እንደሚከናወን ሂደቱንና ቅደም ተከተሉን በዝርዝር ሲገልጽ ወይም ክዋኔ ተኮር ጥናት

ሲያደርግ ነው፡፡ የክዋኔ አውዶች ማህበረሰቡ በዕለት ተዕለት የዘወትር እንቅስቃሴዎቹ የሚያከናውነውን ድርጊትና ስለሚከናወነው ነገር ያለውን አስተያየት የመግለፅ ጉልበት ስላላቸው በየደረጃው የሚደረገውን ክዋኔ ከአውዱ ፣ ከከዋኖቹ ፣ ከተሳታፊዎቹና ከታዳሚዎቹ አንፃር ጭምር በደንብ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ጥናቱን የተሟላ ለማድረግ የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ በዚህ ጥናት ሥራ ላይ ይውላል፡፡ በክዋኔ አውዶች ላይ በማተኮር ንቁ ተሳታፊ በመሆን የሚሰበሰቡ መረጃዎች በኋላ ለሚደረገው ትንታኔ የሚኖራቸው ጉልበት ከፍተኛ ነው፡፡ የፎክሎር የመስክ ተመራማሪው ተቀዳሚ ተግባሩ የሚሆነው ክዋኔዎቹ እንዴት ፣ በማን ፣ የት እና መቼ እንደሚከወን በጥልቀት መመልከትና መረዳት ነው ፤ ለዚህም ነው Vansian (1985:39) ክዋኔ የሚፈፀምባቸው ጊዜያት ዘፈቀዳዊ አይደሉም ፤ የሚከወኑበት ወቅትም የተወሰነ በመሆኑ ምልከታቸው መስክ ላይ ተገኝቶ መሆን አለበት በማለት የገለጹት፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው መስክ ላይ ተገኝቶ ክዋኔውን ካልተመለከቱ በተገቢው መንገድ መከወኑን ለመግለፅ እንደማይቻል ነው፡፡ Ben-Amos “context in context” በሚለው መጣጥፋቸው የነገረ ይዘትን ትርጉም ከሚከወንበት አውድ ጋር አስተሳስሮ ማየት ለተዋጣላት ትንታኔ እንዴት እንደሚጠቅም እንዲህ ይገልፃል፡፡

> የነገረ ይዘት ትርጓሜ ማለት አውዳዊ ትርጉም ማለት ነው፡፡ ማንኛውም ፎክሎር ወደ ተለያዩ ጥበባዊ ፣ ታሪካዊ ፣ ወይም ባህላዊ አውዶች ሲተረጎም አዳዲስ ትርጉሞች ይኖሩታል፡፡ በፎክሎሩ ቋሚ ባልሆነ ባህሪ የተነሳም የፎክሎር ነገረ ይዘት /text/ አንድ ነጠላ ትርጉም ብቻ አይኖረውም፡፡ የተዋጣለት ትንታኔ የሚባለውም ነገረ ይዘቱ ከአውዱ ጋር ተሰናስሎ የተተነተነ እንደሆነ ነው (Ben-Amos, 1993, 209)፡፡

ከዚህ በመነሳት የነገረ ይዘት ትርጓሜ በሚከወንበት አውድ ውስጥ የሚታይ ሆኖ የተዋጣለት ትንተና የሚባለውም ነገረ ይዘቱን በክዋኔ አውድ ውስጥ እየተመለከቱ የሚደረግ ትንተና ነው፡፡ በባህል ጥናት ጥልቅ የሆነ ትንታኔ ለማድረግ ከላይ እንደተገለፀው መረጃዎቹ በዳጎሰ መልኩ መሰብሰብ ይኖርባቸዋል፡፡ ይኼ ደግሞ የባህሉን/ፎክሎሩን ነገረ ይዘት በጥልቀት መመርመርን ይጠይቃል፡፡ የባህል መረጃ ነገረ ይዘት /text/ የምንለው የተለያዩ የባህል ዘውጎችን ይዘት በሙሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ ይኼ የባህል ዘርፉን ክዋኔ ፣ አውዳዊ ቁሶች ፣ ከበራዎችን ፣ መረጃዎችን ወዘተ. ሁሉ

ይጨምራል፡፡ "ማንኛውም ነገር እንደ ነገረ ይዘት /text/ ሊቆጠር ይችላል፡፡ ጨዋታዎችና ቅደም ተከተሎች ፣ የማስታወቂያ ሰሌዳዎችና ጥቁር ሰሌዳዎች ፣ የተለያዩ መሣሪያዎችና አሰራሮች ፣ አልባሳትና አለባበሶች ፣ ቀመሮችና ደረጃዎች ወዘተ ነገረ ይዘቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ነገረ ይዘቶች ሁልጊዜ የፎክሎር ንባቦችንና ትንታኔዎችን የተለያዩ የሚያደርጉ ቁሶችና መረጃዎች ናቸው ማለት ይቻላል" (Sims and Stephens, 2005; Cavallaro, 2001:59)፡፡

የክዋኔ አውድ የሚባለው ደግሞ ባህሉ የሚከወንበት መቼት ፣ የባህሉ ባለቤቶች የሚጋሩት ማህበራዊ ሁኔታ ፣ በታዳሚው ፣ በአባላቱና በከዋኞቹ መካከል ያለ ግንኙነትና በአጠቃላይ በነገረ ይዘቱ በክዋኔው ዙሪያ የሚገኙ ማናቸውም ነገሮች ማለት ነው፡፡ የክዋኔ አውድ አንድ ባህላዊ ጉዳይ የሚቀርብበትና የሚከወንበት በመሆኑ ልዩ ልዩ ገፅታዎች እንዳሉት የመስክ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡

Sohoemaker (1990) Baumanን ጠቅሰው ሁለት ዓይነት የክዋኔ አውዶች እንዳሉ ያስረዳሉ፡፡ አንደኛው ባህላዊ አውድ /Cultural context/ የተሰኘው ሲሆን የሚከወነው ባህል/ፎክሎር ባህላዊ ትርጉም ፣ የትርጉም ዘዴ ትዕምርታዊ ግንኙነቱ ፣ የሚወክለው ነገርና የሚያስተላልፈው መልዕክት እንዲሁም በወካዩና በተወካዩ መካከል ያለውን መስተጋብር የሚመለከት ነው፡፡

በዚህ ውስጥ የፍቺ አውድ /Context meaning/ የባህሉን ይዘት ፣ ፍቺና ጭብጥ ለማወቅ የሚያስፈልግ የሰዎቹ መረጃና ዕውቀት ፣ ተቋማዊ አውድና /Institutional context/ ባህላዊ ተቋማቱ/ቤተሰባዊ ፣ ምጣኔ ሀብታዊ ፣ ሃይማኖታዊ ፣ ትምህርታዊና ፓለቲካዊ/ ቁመናን በማህበረሰቡ ጠባይ አስተሳሰብ ፣ ስለዓለም ባለ አመለካከት ነው፡፡ የመግባቢያ ሥርዓት አውድ /Communicative system context/ ደግሞ የባህላዊ ቡድኑንና የባህል/ፎክሎር ዘውጉን ክፍፍል የሚመለከት ሆኖ አንድ የባህል/ፎክሎር ዘውግ በዚያው ባህል ከሌላ ዘውግ ጋር ያለውን ዝምድና የምንመለከትበት ነው፡፡ ሁለተኛው ማህበራዊ አውድ /Social context/ ደግሞ ማህበራዊ መሰረትን ፣ ግለሰባዊ አውድና ሁኔታዊ አውድን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ባህላዊ አውድ / Cultural context/ እና ማህበራዊ አውድ /Social context/ አጠቃለን ስንመለከታቸው ከላይ በሁለቱም ውስጥ ያሉትን መሠረታዊ አውዶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ተፈጥሮዓዊ አውዶች

ላይ በመገኘት ከተለያዩ አቅጣጫ ትኩረት ሰጥቶ በመመልከት ፣ ጥያቄ በማዘጋጀት ከዋኞቹን ፣ ታዳሚዎቹንና የባህል ባለሙያዎቹን በመጠየቅና የተገኘውን መረጃ ለማረጋገጥና ክፍተቶችን ለመሙላት በቡድን በማወያየት መረጃው ተሰብስቧል፡፡ ይህም ስለተሰበሰበው ባህል የተሟላ ስዕል ማግኘት ያስችል (Scheomarker,1990;8)፡፡ Ben-Amos በበኩላቸው የክዋኔ አውድን የሁኔታዎች አውድ (Context of situation)እና የባህል አውድ /Context of culture/ በማለት በሁለት ይከፍሉታል፡፡

‹‹የባህል አውድ (Context and culture) የከዋኞቹን የጋራ እውቀቶች ፣ የባህሪ ስምምነቶች ፣ የእምነት ስርዓቶች ፣ የቋንቋ ዘይቤዎች ፣ የንግግር ዘውጎች ፣ ታሪካዊ እውቀቶች ፣ ስነምግባራዊ ህጋዊ መመሪያዎችን ዋቢ የሚያድርግ ነው በማለት ሰፊና ብዙ ጉዳዮችን እንደሚያካትት ይገልፃል (Ben—Amos 199;215-216)፡፡ ፡፡ በባህል መረጃ ስብሰባ ሶስተኛው ዋነኛ ጉዳይ ነገር ሁነት (Texture) ነው፡፡ ነገር ሁነት /Texture/ የፎክሎር ዘውግ ሥነ ዕሁፋዊ ፣ ሥነ ልሳናዊ ፣ ተፈጥሯዊ ባህሪና የከዋኙ አቀራረብ ሁኔታ ፣ የአከዋወን አይነት ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ ፣ የፊቱ ገፅታ ፣ የማይዛቸው ቁሳቁስና እንቅስቃሴያቸው ፣ ለነገሩ ይዘት /Text/ ታዳሚው የሚሰጠው ምላሽ በቃላዊ ይዘት ነገሬታ ወይም /Texts/ የዜማ አወራረዱ ፣ የድምፁን ቅላፄዎች ፣ የዘይቤ አጠቃቀሙን ፣ የቃላቱን የእርስ በእርስ ግንኙነትና የሚሰጡትን ትርጉም ሁሉ የሚመለከት ሆኖ ስለ አንድ የባህል ወይም የፎክሎር ዘውግ ፣ ስለ ከዋኙ ስለ ቡድኑና ስለ ዘውጉ ስለራሱ ሳይቀር ብዙ ሊናገር የሚችል ነው (Sims and Stephens ,2005;139; Shcoemaker, 1990,7; Green, 1997,791; Lewandowski, 2001,7)፡፡

በመሆኑም አንድ የፎክሎር ዘውግ በሚከወንበት ወቅት አንዳች አይነት ድባብ ይፈጥራል፡፡ ያ ድባብ በከዋኙ ወይም በታዳሚው ላይ የሚፈጥረው ስሜት ይኖራል ፤ ሊደሰትበት ፣ ሊያዝን ፣ ሊያስቆጭ ፣ ሊያናድድ ፣ ሊያስጨፍር ወዘተ ይችላል፡፡ Bauman and Briggs (1990:68)Dundesን በመጥቀስ እንዳሰፈሩት የአንድ ፎክሎር/ባህል አውድ ማለት ያ ዘውግ የሚከወንበት ማህበራዊ ሁኔታ ነው፡፡ Ben-Amos (1988:4) ደግሞ አውድ በክዋኔው ላይ የሚጫወተውን ሚና ሲገልፁ አውድ በክዋኔ ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ክዋኔው እንዳይቋረጥ ፣ እንዲቀጥል ፣ እንዲሞቅ ፣ እንዲቀዘቅዝ ወዘተ ሁሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ምክንያቱም የፎክሎር ህልውና የተመሰረተው በማህበራዊ አውድ ነው ይላሉ፡፡ ስለሆነም አውድ ለክዋኔ ሂደትና

ቅድመ ተከተል ብቻ ሳይሆን ለዘላቂነቱ እና ለህልውናው የጎላ ሚና ይጫወታል። በዚህ ምክንያት አንድን የባህል/ፎክሎር ዘውግ ከአንዱ ነጥሎ መመልከት ትክክለኛ መልዕክቱን ለመግለፅ አያስችልም። ለዚህ ነው Bauman and Briggs (1990፡72) የአንድን ፎክሎር ዘውግ ቅርፅ ፣ ፋይዳ እና ፍቺ ከአውዱ ውጪ መረዳት አይቻልም። ክዋኔ ተኮር ላይ ጥናት የሚያደርግ አጥኚ ትኩረቱ በሁኔታው አውድ ወቅት የሚኖረውን ክዋኔ መሠረት አድርጎ ነው በማለት አውድና ክዋኔ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን አስፍረዋል። Dundes (1980፡30)ም አውድን መመልከት ለሁሉም የፎክሎር ዘውጎች አስፈላጊ ነው ብለዋል። ይህ አስፈላጊነትም አውድ ከክዋኔ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ሊገለፅ የተፈለገውን ይዞታን ለማሳየት የሚረዳ መሳሪያ መሆኑን ያመለክታል። የባህል መገለጫው ክዋኔው በመሆኑ ባህልና ክዋኔ እንደ ነፍስና ስጋ መነጣጠል የማይችሉ ናቸው። ባህል ወይም ፍክሎሩ ነፍስ የሚዘራው በሚተገበርበት ፣ በሚከበርበት ፣ በሚመለክበት ፣ በሚዘፈንበት ፣ በሚተረክበት በአጠቃላይ ወቅት ነው። ክዋኔው ደግሞ እንደባህሉ ገፅታ የራሱ የሆነ አውድ ይፈልጋል። በአንድ ክዋኔ አውድ ሌላ የባህል ዘውግ አይከወንም። በለቅሶ ግዜ የሰርግ ዘፈን እንደማይዘፈነው ማለት ነው። በመሆኑም ስለ ባህሉ ዘውግ የተሟላ መረጃ ለማሰባሰብና የጠለቀና የተዋጣለት ትንታኔ ለማድረግ ህያው በሚሆንበት የክዋኔ አውድ ላይ ተገኝቶ በጥንቃቄ በንቃትና በጥልቀት መረጃውን ከሁነኛ ምንጭ አሳምኖ መሰብሰቡን በመጠየቁ መረጃዎች ከክዋኔው አውድ ላይ በሚገባ ተሰብስበው ተተንትነዋል። በዚህ ጥናት በዋናነት ከሚነሱ ጉዳዮች መካከል አንዱና ዋነኛው ባህሉ ከልማቱ ጋር ያለውን ቁርኝት ማሳየት በመሆኑ ይህንን ለመፈተሽ የሚያስችሉ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው የዘመናዊነት ንድፈ ሀሳብ /Modernization theory/ እና የልማታዊ ንድፈ ሃሳባዊ /Developmental theory/ በተጨማሪም ከጥቅም ላይ ውለዋል።

### 2.3.3 የዘመናዊነት ንድፈ ሃሳብ (Modernization theory) እና የልማት ንድፈ ሃሳብ (Developmental theory)

ባህልና ልማት ያላቸውን ቁርኝት አስመልክቶ ሁለት አይነት አመለካከቶች አሉ። አንዱ የተዋጣለት ልማት ለማምጣት ከታሰበ ባህላዊ አመለካከቶችን ሰብሮ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም አቋራጭ መፍትሔ ነው የሚለው የዘመናዊነት አመለካከት ሲሆን ከዚህ አስተሳሰብ በተቃራኒው ባህል ለልማት ያለውን አወንታዊ አበርክቶ

የሚያሳዩና የዘመናዊነት አስተሳሰብ የምዕራባዊያኑ የዘረኝነት አስተሳሰብ ወይም አመለካከት እንደሆነ የሚከራከሩ አስተሳሰቦች ናቸው፡፡ እነዚህ አስተሳሰቦች ቀደም ሲል ለማንሳት የተሞከረ በመሆኑ[10] እዚህ ላይ የምናነሳው የዘመናዊነትን አመለካከት ነው፡፡ የዘመናዊነት ንድፈ ሀሳብ አንድን ግለሰብም ሆነ ማህበረሰብ ከልማድ እስረኝነት ለማህበራዊ እኩልነት ፣ በአዳዲስ ፈጠራዎችና ለውጦች በከፍተኛ ደረጃ ማርቀቅ ነው፡፡ ይህም ከካፒታሊዝም ፣ ኢንዱስትሪያላይዜሽን እና ከከተሜነት ጋር የሚያያይዝ አስተሳሰብ ነው፡፡ የዘመናዊነት ንድፈ ሃሳቦች በጣም የተስፋፋ የልማት ፅንሰ ሃሳቦች እንደሆነና የምዕራባውያን ትኩረት የሆነው የልማት አመለካከት መገለጫዎች እንደሆኑ ዘመናዊነትን ከልማት ጋር መለየት እስኪያቅት ድረስ የተሰሳሰሩና ከካፒታሊዝምና ከምጣኔ ሀብታዊ እድገት ጋር የተጋመዱ ናቸው የሚሉ አሉ፡፡ በዘመናዊነት ንድፈ ሃሳብ አቀንቃኞች እይታም ዘመናዊነት ማለት በስነቃልና ሁለንተናዊ ለውጥ የሚመራ ሂደት ሆኖ ኢንዱስትሪያላይዜሽኑን ፣ ከተሜነትን ፣ ማህበራዊ ንቅናቄን ፣ የሚዲያ ፓለቲካ ተሳትፎ ፣ የትምህርትና የተማረ ሰው መስፋፋትን የሚያጠቃልል ውስብስብ ሂደት ተደርጎ እንደሚታይ ይገልፃሉ (Schech and Haggis, 2000:3 9)፡፡ ይህ የዘመናዊነት አመለካከት ለባህላዊ ጉዳዮች ተገቢ ቦታ የማይሰጥ ከመሆኑ በቀር ባህልን የልማት ፅንቅፋት እና ከድህነት አዘቅት ውስጥ የሚያስገባ አድርጎ የሚመለከት በመሆኑ ድሃ ሃገራት ከድህነት አዘቅት ተላቀው በሁለንተናዊ መልኩ ለልማት ከጎታች ባህሎቻቸውና ከኋላቀር አስተሳሰባቸው ተላቀው ዘመናዊነትን መላበስ አለባቸው የሚል ነው፡፡ ይሁንና ከዚህ አመለካከት በተቃራኒው በኢስያ ሀገሮች የመጣው የሚያስገርም የልማት መነሻ ባህላዊ ጉዳዮችን ከልማት ጋር አያይዞና መሳሪያ አድርጎ የመጣ እንደሆነ ቀደም ሲል ለማመልከት ተሞክሯል፡፡ ይህ የዘመናዊነት ንድፈ ሃሳብ እና በተቃራኒው የሚነሱት የልማት ንድፈ ሃሳቦች /Developmental theory/ አመለካከቶች በዋግኽምራ ባህላዊ መሠረቶች ላይ በምን መልኩ እንደሚሰራ ለማሳየት በዚህ ጥናት ትንታኔ ከጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ጥናቱ እነዚህን ከላይ የተገለፁ ንድፈ ሀሳቦች መሰረት አድርጎ ንድፈ ሃሳቦቹን በየራሳቸው ምሉዕ ባለመሆናቸው የአንዱን ክፍተት በሌላው ጥንካሬ በማሟላት የተሰራ ነው፡፡ በጥናቱ የክዋኔን ንድፈ ሃሳብ ባህላዊ ዘውጉ አውን ሳይሆን የሚሰጠውን ትርጉም

---

[10] በጥናቱ ዳራ ላይ ተቃኝቷል፡፡

ለመመርመር የባህላዊ ዘውጉ ለብሔረሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ ደግሞ በተግባራዊነት ንድፈ ሃሳብ ተደግፎ ተተንትኗል፡፡ የብሔረሰቡ ባህል አካባቢ ልማት ጋር ያለውን ትስስር ለማሳየት እና ባህሉ በልማቱ ላይ የሚያሳድረውን አወንታዊ እና አሉታዊ እንደ ቅደም ተከተላቸው አበርክቶና ተፅእኖ እንዲሁም ባህሉን መሳሪያ በማድረግ የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን እንዴት ጥቅም ላይ መዋል እንደሚችል ለማየት የዘመናዊነትና የልማት ንድፈ ሃሳቦችን ተጠቅሞ ትንታኔ ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# 3.የጥናቱ የአሰራር ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

አንድ ተመራማሪ ስለ አንድ ጉዳይ ጥናት ለማድረግ በሚዘጋጅበት ወቅት አስቀድሞ ማዘጋጀት የሚገባው የጥናት ንድፍ ነው፡፡ ይህም ጥናቱን በምን መንገድና እንዴት እንደሚያከናወነው የሚያመለክተው ንድፍ ነው፡፡ Yin (2003:20) የጥናት ንድፍ በሚመለከት እንደሚመለከተው አስፍረውታል ፤ ጥናቱ በቅድሚያ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ ትስስር ባለው መንገድ አዋህዶ ማቅረብ ነው፡፡ ስለዚህ የጥናት ንድፍ ለአንድ ጥናት አጀማመር ፣ አካሄድና አጨራረስ የጎላ ሚና ይኖረዋል፡፡

የጥናት ንድፍ አራት ጉዳዮች እንደሚያካትት (Punch, 2000:52) ገልፀዋል ፤ እነዚህም ስልት (ዘዴ) ፣ የፅንሰ ሀሳብ መዋቅር (አፅም) ፣ ምን እንደሚጠና እና የምርምሩን መረጃ ለመሰብሰብና ለመተንተን የሚያገለግሉ መሣሪያዎችና ሂደቶች ናቸው፡፡ ከዚህ የምንረዳው በጥናቱ ዘዴነት የሚካተቱ ይዘቶች እርስ በእርሳቸው የተያያዙና ጥናቱ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ለማስገኘት አበርክቶ የሚኖራቸው መሆናቸውን ነው፡፡

በዚህ ምዕራፍ የሚገለፀውም ጥናቱን ለማካሄድ የተከተልኩት የጥናት አቀራረብ እና የጥናት ዘዴ ነው፡፡

## 3.2. የጥናቱ አቀራረብ

አንድ ጥናት በሶስት ዘዴዎች ሊቀርብ ይችላል፡፡ በዓይነታዊ ፣ በመጠናዊ ወይም በጥምር ዘዴ (Creswell, 2009; 3-4)፡፡ መጠናዊ ዘዴ በቁጥር የሚገለፅ መረጃን የሚጠቀም ሲሆን ፣ ዓይነታዊ ዘዴ ደግሞ መጠናዊ ወይም አሃዛዊ የሆነ መረጃን የማይጠቀም ነው፡፡ የተለመዱትና በዓይነታዊ መረጃዎች ስር የሚካተቱትም ትራንስክራያብ የሆኑ ቃለ መጠይቆች ፣ በሚጠናው ቦታ የተያዙ የመስክ ማስታወሻዎች ፣ በቪዲዮ ፣ በቴፕ የተቀዱ መረጃዎች ፣ ፎቶ ግራፎች ፣ ቃለ ጉባኤ እና ዘገባዎች

የመሳሰሉት ሰነዶች ናቸው፡፡ እነዚህን ዓይነታዊ መረጃዎች በመጠቀም የሚካሄድ የትንተና ዓይነትም ዓይነታዊ ትንተና ይባላል፡፡

የዚህ ጥናት ዘዴ ዓይነታዊ ነው፡፡ የመረጥኩበት ምክንያትም (Thomson,2011:78) እንዳስፈሩት አንድ ጥናት የሚከናወነው የአንድ ሁኔታ ፍቺ ወይም አንድ ሁኔታ በተወሰነ የሰዎች ስብስብ ላይ የሚኖረውን ገጠመኝ ለመረዳት ከሆነ ትክክለኛው የጥናት ዘዴ ዓይነታዊ ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ከመስክ በምልከታ ፣ ማስታዎሻ በመያዝ ፣ በቃለ መጠይቅና በቀረጻ የሰበሰብኳቸው መረጃዎች ዓይነታዊ ናቸው፡፡ እነዚህን ዓይነታዊ መረጃዎች በመረጥኳቸው የመተንተኛ ዘዴዎች የተነተንኳቸው ዓይነታዊ ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ ምክንያቱም ያለው (1998 ፣ 250) እንዳሉት መረጃዎቹ ዓይነታዊ ሆነው በገለፃና በሀተታ የቀረቡ ከሆነ ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችን መጠቀም የግድ ይላል፡፡ በንድፈ ሀሳብ ላይ በመመርኮዝ የተከናወነ ገለፃም ይገኝበታል፡፡

## 3.3. ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች የተሰበሰቡበት አውድ

ክንዋኔና አውድን መሠረት አድርጎ የሚሰበሰብ መረጃ በኢትኖግራፊ ላይ ይመሰረታል፡፡ ኢትኖግራፊ ደግሞ አጥኚው ጥናቱን ወደሚያከናውንበት ማህበረሰብ ውስጥ ዘልቆ በመግባት መረጃውን ከሚሰበስብበት ማህበረሰብ ጋር ቆይታ ማድረግ ከመስክ የሚሰበስባቸውን መረጃዎች ለጥናቱ የሚጠቀምበት ዘዴ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት የሚያገለግለው መረጃም በኢትኖግራፊ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ምክንያቱም መረጃው የተሰበሰበው ወደ ተጠኚዎቹ አካባቢ በመግባትና ቆይታ በማድረግ ነው፡፡ መረጃውም የተሰበሰበው ከቀዳማይ ወይንም የመጀመሪያ ደረጃና ካልዓይ ሁለተኛ ደረጃ ምንጮች ነው፡፡ በዚህም መሰረት አብዛኛውን መረጃ የሰበሰብኩት አራት ጊዜ ወደ ጥናት ቦታው የመስክ ጉዞ በማድረግና ለስድስት ወራት ያህል በዚያው በመቆየት የመጀመሪያ ደረጃ ምንጮችን በመሰብሰብ ነው፡፡ ስለ ጥናት ቦታውና ማህበረሰቡ ስለ ጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ፅንሰ ሀሳብን ተዛማጅ ስራዎች የሚገልጹ ውስን ካልዓይ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ምንጮችን ደግሞ ከቤተ-መፅሀፍት አግኝቼ ተጠቅሜያለሁ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ደግሞ ከተለያዩ አውዶች ሊሰበሰብ ይችላል፡፡ ፈቃደ (1991፣122-123) እንደገለጹት የፎክሎር መረጃ ከመስክ የሚሰበሰቡባቸው ሶስት የመቼት አይነቶች አሉ ፤ እነዚም

ተፈጥሮአዊ መቼቶች ፣ አርቴፊሻል መቼቶች እና ቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼቶች ናቸው፡ ፡ የመጀመሪያው መቼት አንድ የፎክሎር ዘውግ በማህበረሰቡ ሲከወን በቦታውና በጊዜው በመገኘት መረጃን የሚሰበሰብበት ሲሆን ፣ ሁለተኛው ደግሞ መረጃ ሰብሳቢው የፎክሎር ዘውጉ በተፈጥሮአዊ አውድ (በቦታና በሚፈፀምነት ጊዜ) ሲከወን መረጃውን መሰብሰብ በማይቻልበት ወቅት መረጃ አቀባዮቹ የተፈጥሮአዊ መቼትን አስመስለው እንዲከውኑለት የሚፈጥረው አውድ ነው። ሶስተኛው ደግሞ ተመራማሪው ማንኛውም መረጃ አቀባይ በተገኘበት ቦታና ጊዜ ከአውዱ ውጪ መረጃ የሚሰበስብበት የመቼት አይነት ነው። ቀዳማይ ወይም የመጀመሪያ መረጃዎችን የሰበሰብኩት ተፈጥሮአዊ እና አርቴፊሻል መቼቶችን በመጠቀም ነው። ዋናው ግን ተፈጥሮአዊ መቼት ነው ምክንያቱም (Willson, 1989 : 32) እንደገለፁት ከሌሎቹ የትምህርት መስኮች ይበልጥ ፎክሎር/ባህል በተፈጥሮአዊ መቼት መታየት አለበት። በዚህ አውድም ሃያ ሁለት ማለትም ስምንት የወሊድ ፣ ስምንት የጋብቻ እና ስድስት የሞት ሥነ ሥርዓቶችን ምልከታና ቀረፃ ለማካሄድ ባቅድም ምክከታና ቀረፃ ያደረኩት ግን ሀያ አንድ ማለትም አምስት የወሊድ ፣ አስር የጋብቻ እና ስድስት የሞት ስነ ስርዓቶችን ነው። ክንውኑ ካቀድኩት በአንድ እንዲያንስ ያደረጉ ምክንያቶች አሉ። እነዚህም በመስክ ቆይታዬ ወቅት የሥነ ሥርዓቶቹ አለመከሰት ፣ ቢከሰቱም ምልከታ እንዳደርግ የመረጃ አቀባዮቹ ፍቃደኛ አለመሆን (ለአብነት ያህል ቤት ውስጥ የሚከናወንን ወሊድ)። ሥነ ሥርዓቶቹ በሚከናወኑበት ቦታና ጊዜ ወይም በተፈጥሮአዊ መቼት በመገኘት በምልከታ ፣ ማስታወሻ በመያዝና በምስልና በድምፅ በመቅረፅ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ መሰብሰብ መቻሌን ፣ የሥነ ሥርዓቶቹን ክዋኔ ፣ አውድና መዋቅር ለመረዳትና ለመግለፅ አስችሎኛል። ከዚህም በተጨማሪ ተገቢ የሆኑ የመረጃ አቀባዮችን እንዳገኝና በቃለ መጠይቅ ተጨማሪ መረጃ እንድሰበስብ እረድቶኛል። በሌላ በኩል አርቴፊሻል መቼትን የተጠቀምኩት ደግሞ ስለ ሥነ ሥርዓቶቹ ሂደት እና ምንነት ማብራሪያ በምፈልግበት ወቅት ፣ ለሥነ ሥርዓቶቹ አገልግሎት ላይ የዋሉ ቁሳቁሶችና የተከናወኑ ድርጊቶች ተምሳሌትነታቸው ምን እንደሆነ ለማወቅ ፣ ሥነ ሥርዓቶቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ጥቅሞችና ሃይማኖታዊ ትስስርን ለመረዳት ፣ መረጃ አቀባዮቹ በሚገኙበት በየትኛውም ቦታና ጊዜ በቃለ መጠይቅ መረጃ በመሰብሰብ በኩል መረጃ በሰበሰብኩበት ወቅት ነው።

### 3.3.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች

አንድ ተመራማሪ ለጥናቱ በግብዓትነት የሚያገለግሉትን መረጃዎች የሚሰበስብባቸው የተለያዩ ስልቶች አሉ፡፡ ይህም እንደ ጥናቱ ርዕስ የሚወሰን ቢሆንም ዋና ዋና የሚባሉት ምልከታ ፣ ቃለ መጠይቅ እና መጠይቅ ናቸው (ፈቃደ ፣ 1991 ፣ 90)፡፡ እነዚህን ስልቶች እንደ አስፈላጊነቱ በተናጠል ወይም በጥቅል መጠቀም ይቻላል፡፡ ተመራጩ ግን አጣምሮ መጠቀም ነው፡፡ ምክንያቱም በአንድ ስልት ማግኘት ያልተቻለውን መረጃ በሌላ ማግኘት ከመቻሉ በላይ የመረጃዎችንን ትክክለኛነት ለማረጋገጥም ያስችላል፡፡ Murchison (2010;49) እንደገለፁት በኢትኖግራፊክ ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ጥናት እንደ ጥናት ስልትነቱ ሶስት ቁልፍ ዘዴዎችን በጥምረት ይጠቀማል ፤ እነዚህም ተሳትፎአዊ ምልከታ ፣ ቃለ መጠይቅና መሰሎችን ማካተት ናቸው፡፡ ለጥናቴ የተጠቀምኩትን መረጃ የሰበሰብኩት ቅይጥ ወይም ድብልቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶችን በመጠቀም ነው፡፡ እነዚህም ምልከታ ፣ ቡድን ተኮር ውይይት ፣ ቃለ መጠይቅ (የግል እና የቡድን) ናቸው፡፡ ምክንያቱም ቅይጥ ወይም ድብልቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም አስተማማኝነት ያላቸውን መረጃዎች ለማሰባሰብ ያስችላል፡፡ መረጃ ለማሰባሰብ የተጠቀምኩባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች አጠቃቀም ቀጥሎ እንደተገለፀው ነው፡፡

#### 3.3.1.1 ምልከታ

በሁሉም ተመራማሪዎች ዘንድ በስፋት የሚታወቁት የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች ምልከታ ፣ ቃለ መጠይቅና ፅሑፋዊ መጠይቅ ናቸው፡፡ Pauline and Calvin (1998:163); Yin (2003:93); Matthews and Lizross (2010:55) እንዳስፈሩት ደግሞ ምልከታ በሁለት መንገዶች ሊከናወን ይችላል፡፡ በተራ ምልከታ እና በተሳትፏዊ ምልከታ፡፡ መስከኛዉ ፋይዳ ያለዉ በተግባር የተፈተነ መረጃ ለማሰባሰብ እና የማህበረሰቡን ጠባይ ለመግለፅ የሚያስችለውን መሰረታዊ መረጃ መሰብሰቢያ ስልትም ተሳትፏዊ ምልከታ ነው ፤ በዚህም ምልከታ አይነት መረጃ የሚሰበስብ ተራ ተመልካች ሳይሆን በድርጊቱ ክዋኔ ላይ ተሳታፊ የሚሆን ነው፡፡ Yin (2003;93-94) ሰባት የተለያዩ የተሳትፎአዊ ምልከታ ዓይተቶች አሉ ፤ እነዚህም በዓይነትነት የተጠቀሱት ሁለት መስፈርቶችን በመጠቀም ነው ፤ አንዱ የመረጃ ሰብሳቢው በመረጃ አቀባዮቹ መረጃ

መሰብሰብ መታወቅና አለመታወቅ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ደግሞ መረጃ መሰብሰቡ ታውቆ በድርጊቱ ላይ የሚሳተፍበትን መጠን የሚመለከት ነው፡፡ መረጃ ሰብሳቢው መረጃ እንደሚሰበሰብ በመረጃ አቀባዮቹ በኩል በመታወቅና ባለመታወቅ መስፈርት ተሳትፏዊ ምልከታ በግልፅና በድብቅ ሊከናወን ይችላል፡፡ እንደ Dawson (2002:147) ገለፃ ግልፅ የሚባለው ተመራማሪው በተሳትፏዊ ምልከታ መረጃ እንደሚሰበሰብ በተጠኚዎቹ የሚታወቅበት ሲሆን ፤ ድብቅ ደግሞ ሳይታወቅ በድብቅ መረጃ የሚሰበሰብበት መንገድ ነው፡፡ አንድ መስክኛ መረጃውን መሰብሰብ ያለበት በግልፅ እንጂ በድብቅ መሆን እንደሌለበት ፤ ሰዎች ተሞክሯቸውን በሚያጋሩበት ወቅት ባህል ተሸካሚዎች ናቸውና ሊከበሩ ይገባል ፤ ማለትም መረጃህን ተደብቀህቸውና ያለ ፈቃዳቸው መሰብሰብ የለብህም ይላሉ (Wilson, 1989:228)፡፡

መረጃ የሰበሰብኩት በድብቅ ሳይሆን መረጃ አቀባዮቼ ለምን እንደማጠና አውቀውት በግልፅ የተካሄደ ነው፡፡ ስለዚህ ቀደም ሲል ከተገለፁት ሁለት የተሳትፏዊ የምልከታ አይነቶች መካከል እኔ የተጠቀምኩት ግልፅ ተሳትፏዊ ምልከታ ነው፡፡ ወደ መረጃ መሰብሰብ ያመራሁትና የሰበሰብኩት መረጃንውን ለምንና በምን መሳሪያ እንደምሰበስብ ለመረጃ አቀባዮቼ ገልጬና ፍቃደኝነታቸውን አረጋግጬ ነው፡፡

Spradlley (1990) እንደገለፁት የመረጃ ሰብሳቢውን የምልከታ ተሳትፎ መጠን መለኪያ በማድረግ ደግሞ ተሳትፏዊ ምልከታ በአምስት አይነት ይከፈላል፡፡ በእነዚህም የተሳትፎውን መጠን ማነስና መብዛት በቅድም ተከተል የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት የመጀመሪያው ውጫዊ ተሳትፎ ሲሆን ይህም መረጃ ሰብሳቢው ከቪዲዮ ወይም ከቴሌቪዥን መረጃ የሚሰበስብበት እንጂ እሱ በቀጥታ በድርጊቱ የማይሳተፍበት ነው፡፡ ሁለተኛው አይነት ደግሞ መረጃ ሰብሳቢው በክዋኔው ተገኝቶ ነገር ግን በንቃት የማይሳተፍበት የተሳትፎ አይነት ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ መረጃ ሰብሳቢው በክዋኔው እንደ ውጫዊም እንደ ውስጣዊም ሰው ሆኖ በድርጊቱ የሚሳተፍበት ተመጣጣኝ ወይም መካከለኛ ተሳትፎ ነው፡፡ አራተኛው ተሳትፎ ደግሞ ሌሎች የክዋኔው ተሳታፊዎች እንደሚሳተፉት ንቁ ሆኖ የሚሳተፍበት ሲሆን አምስተኛው ደግሞ መረጃ ሰብሳቢው ከፍተኛ የሆነ ተሳትፎ የሚያደርግበት ሙሉ ተሳትፏዊ የሚባለው የተሳትፏዊ ምልከታ አይነት ነው፡ እኔም ከመስክ መረጃ የሰበሰብኩት በፎክሎር/ባህል ጥናትና ምርምር ትክክለኛ መረጃ ሊያስገኙ የሚችሉትን ሁሉንም የተሳትፏዊ ምልከታ አይነቶች

በጥምረት በመጠቀም ነው፡፡ ይኸውም ማህበረሰባዊ ሁኔታዎች እንድሳተፍ በማይፈቅድልኝ ንቁ ያልሆነ ምልከታን ተጠቅሜያለሁ ፤ በመሆኑም በዚህ ምልከታ መረጃ የሰበሰብኩት እኔ ተሳታፊ ለመሆን በማልችልበት ባህላዊ ክዋኔ ወቅት ነው፡፡ ለአብነት ያህል በወሊድ ሥርዓት በምጥ ወቅት ፣ በሰርግ ወቅት ሴቶች በሚያከናውኗቸው ሥርዓቶች ፣ በቀብር ሥነ ሥርዓቶች ፣ ሀዘንተኞች በአንድ ማልቀሻ ቦታ ክብ ሰርተው በሚዞሩበት ወቅት ፣ ወዘተ ነው፡፡ በክዋኔዎቹ ውስጥ ባለመሳተፌ የጎደለን የመረጃ ክፍተትም በቀረፃ አመካኝነትና በቃለ መጠይቅ እንዲሟሉ አድርጌያለሁ፡ ፡ በእነዚህ ክዋኔዎች ከተሳትፏዊ ምልከታ መካከል ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ የተጠቀሱትን ተጠቅሜያለሁ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ማህበረሰባዊ ሁኔታውና አውዱ እንድሳተፍ በሚፈቅድልኝ ሁሉ መረጃ የሰበሰብኩት ንቁና ሙሉ ተሳትፏዊ ምልከታ በማድረግ ነው፡፡ ለአብነት ያህል በሰርግ አመጋገብ ፣ በጭፈራ ፣ በቀብርና በቀጠሮ (አጎበር) ለቅሶ ተሳታፊ በመሆን መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ ለአካባቢና ለባህሉ ብዙም እንግዳ ባለመሆኔና ቀደም ሲል በተለያዩ ጊዜያት በስራ ምክንያት ስሄድ በሰርግና በቅሶ ሥነ ሥርዓቶች ስለተሳተፍኩ ማህበረሰቡ በእነዚህ ሥነ ሥርዓቶች ተሳታፊ በሚሆን ሰው ላይ የሚጠብቀውን እና የማይጠብቀውን ፣ የሚወደውን እና የሚጠላውን አውቃለሁ፡፡ ስለሆነም መረጃ በምሰበስብበት ወቅት ተሳትፏዊ ምልከታ ለማከናወን የጎላ ችግር አላጋጠመኝም፡፡

### 3.3.1.2. ቃለ መጠይቅ

ሶስት የቃለ መጠይቅ አይነቶች አሉ፡፡ እነዚህም ውስን ቃለ መጠይቅ ፣ ነፃ ቃለ መጠይቅ እና ከፊል ነፃ ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው በቅድሚያ የተዘጋጀ ጥያቄዎች ብቻ መልስ የሚሰጥበትና ተመራማሪው ሌላ ጥያቄ የማያክልበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተመራማሪው በቅድሚያ ጥያቄዎችን ሳያዘጋጅ ርዕሱን ለመረጃ አቀባዩ በመግለፅ ተጠያቂው ዘና እያለ በነፃነት ሀሳቡን የሚገልፅበት ነው፣ ሶስተኛው የሁለቱም ቅልቅል ነው (O'reilly, 2005; 116; Pauline and Calvin, 1998; 183 እና ያለው ፤ 2001 ዓ.ም ፤178)፡፡

እኔ ውስንና ነፃ የቃለ መጠይቅ ዓይነቶችን ተጠቅሜያለሁ፡፡ ምክንያቱም Thomson (2011;78) እንደገለጹት ለአይነታዊ የጥናት ዓይነት የሚሰበሰበውን መረጃ በቃለ

መጠይቅ ፣ በመስክ ምልከታ ፣ በመስክ ማስታወሻ ፣ በምልከታ ፣ በቪዲዮና በሌሎች ምስላዊና ፅሁፋዊ ነገሮች ቢሆንም ዋናው ግን በቃለ መጠይቅ ነው፡፡ ውስን ቃለ መጠይቅን የተጠቀምኩት በሥነ ሥርዓቶቹ (የወሊድ ፣ የጋብቻና የሞት) ክዋኔ ላይ ምልከታ እና ቀረፃ ከማድረጌ በፊት ፣ በሂደት እና በኋላ ነው፡፡ ይህም ስለ ሥርዓቶቹ አከባበር ውስን ቃለ መጠይቅ ያደረግሁ ሲሆን ፤ ነፃ ቃለ መጠይቅን ደግሞ የሥነ ሥርዓቶቹ ክዋኔ ሃይማኖታዊ ዳራ እንዳለውና እንደሌለው ለማጣራት ስል በሃይማኖት መረጃዎች ቃለ መጠይቅ ባደረግሁበትና የመረጃ ክፍተት የታየባቸውን ጉዳዮች በሞላሁበት ወቅት ነው፡፡ ቃለ መጠይቅ ያደረኩትም የግል እና የቡድን ነው፡፡ የቡድን ቃለ መጠይቁም በርከት ላሉ ሰዎች በአንድ ላይ ነው፡፡ በዚህም የአንድ ወረዳና ከተለያዩ ወረዳዎች የመጡ የመረጃ አቀባዮችን እና የተወሰኑ ሴቶችን በአንድ ላይ በማድረግ የቡድን ቃለ መጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡ መረጃዉን በሰበሰብኩበት ወቅት ለ16 ሴቶችና ለ29 ወንዶች በአጠቃላይ ለ45 ሰዎች የግል እና የቡድን ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸዋል፡፡

### 3.3.1.3. ቡድን ተኮር ውይይት

ሌላው ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀምኩት ቡድን ተኮር ውይይት ነው፡፡ Dawson (2002:29-30) እንዳስፈሩት ቡድን ተኮር ውይይት ማለት የተወሰኑ ሰዎች ለሚለጠየቁት ጥያቄ በቡድን ሆነው በመወያየት መልስ የሚሰጡበት መንገድ ሲሆን ውይይቱን የሚመራ ሰውም ይገኝበታል፡፡ ቡድን ተኮር ውይይት ያደረኩትም ከስድስቱም ወረዳዎች እና ከሰቆጣ ከተማ አስተዳደር ለተወጣጡና ስለ ጥናቴ ምንነት ግንዛቤ ይኖራቸዋል ለተባሉ ሰዎች ነው፡፡ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ በነፃነት ለመወያየት እንዲችሉም ወንዶቹን ለብቻ ሴቶቹን ለብቻ አወያይቻለሁ፡፡ የውይይቱ መሪ እኔው ነበርኩ፡፡ በአብዛኛው መረጃው የተሰበሰበው በአማርኛ ቢሆንም የተወሰነው ደግሞ በኽምጥኛ ተሰብስቧል፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳን የዞኑ የስራ ቋንቋ አማርኛ ቢሆንም በሥነ ሥርዓቶቹ ክዋኔ ወቅት ማህበረሰቡ በሁለቱም ቋንቋዎች ሀሳቡን በመግለጹ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ የመረጃ አቀባዮቼ ለጥያቄዎቼ መልስ በመስጠት የሚቸገሩ ባለመሆናቸው ብዙውን ቃለ መጠይይ ያደረግሁት እና መረጃ የሰበሰብኩት በአማርኛ ነው፡፡ በአማርኛ መልስ ለመስጠት የሚቸገሩ የተወሰኑ መረጃ አቀባዮቼን ስጠይቅ ደግሞ አስተርጓሚ በመጠቀም መረጃውን ተቀብያለሁ፡፡ በሥነ ሥርዓቶቹ ክዋኔ ወይት ኽምጥኛ የተገለፁትንም (ለአብነት ያህል በሰርግ ሥነ ስረዓት (ሸኙነ ሸኙነ) አጠቃቀማቸውን በአፍ

መፍቻ ቋንቋ ለማሳየት እንዲቻል በኽምጠኛ ትርጉማቸውን ደግሞ በአማርኛ አስፍሬዋለሁ፡፡ ከተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተጨማሪ ከሰነዶችም መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ በመሆኑም ሶስት ጎንዮሽ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴን ተጠቅሜያለሁ ፤ ይኸውም Reichardt and Thomas D.cook (1985:94) እንደገለፁት ይህ መንገድ በአንዱ ዘዴ ያልተገኙትን መረጃ በሌላው ዘዴ እንዳገኝ አስችሎኛል፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልገዉን መረጃ ለመሰብሰብም ለ15 ሴቶችና ለ27 ወንዶች በአጠቃላይ ለ42 ሰዎች የቡድን ተኮር ውይይት አካሂጃለሁ፡፡

### 3.3.2. የመቅረጫ መሣሪያዎች አጠቃቀም

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይህ ጥናት የተከናወነው አጥኚው ወደ ተጠኚዎቹ አካባቢ በመሄድና ከእነሱ ጋር ቆይታ በማድረግ ምልከታና ገለፃ በማድረግ ነው፡፡ መረጃ የሰበሰብኩባቸው የዋግኽምራ ብሄረሰብ ዋና ዋና የባህል/ፎክሎር ገጽታዎች/ዘውጎች ናቸው፡፡ የፎክሎር/ባህል መረጃ ደግሞ በተለያዩ መሳሪያዎች እገዛ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡ በመቅረፀ ድምፅ ፣ በፎቶና በመቅረፀ ምስል፡፡ በእነዚህ መሳሪያዎች መረጃ መሰብሰብ የሚሰጠውን ጠቀሜታ አስመልክተው የተለያዩ ባለሙያዎች እንዲህ ይላሉ (Pink,2007:163)፡፡ በእነዚህ መሣሪያዎች መረጃ መሰብሰብ በፅሁፍ ለመግለፅ አስቸጋሪ የሆኑትን ቅርፅ ፣ ቀለምን እና ንድፍን ለመቅረፅ ከማስቻለውም በላይ በአንድ ወቅት የተቀረፀ ነገር ለማንኛውም ጊዜ እንዳለ ሆኖ ሊያስረዳ ይችላል፡፡ O'Reilly (2005:161) የመረጃ መሳሪያዎችን ተጠቅሞ መረጃን መሰብበስ ለባህል ጥናት የሚኖረውን ጠቀሜታ አስመልክተው ሲገልፁ የፅሁፍ መረጃን ለመደገፍና እና ትንታኔው ጥንካሬ እና ጥልቀት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ባህል/ፎክሎር/በቃላት ብቻ የሚገለፅ አይደለም ፤ በአካልና በድርጊትም እንጂ ፤ ስለዚህም ፎቶ መጠቀም እነዚህን ለመግለፅ ያስችላል፡፡ ይህም በቃላት የሚገለፀውን ሀሳብ ጥንካሬ እንዲኖረው ያደርገዋል ብለዋል፡፡ Gottlieb (2006:570)ም በፎቶ መረጃ መሰብሰብ ያለውን ጠቀሜታ አስመልክተው እንዲህ ይገልፃሉ፡፡ በቃላት ሊገለፅ የማይችለውን በፎቶ መግለፅ በመቻሉ ኢትኖግራፈሮች በስራቸው ውስጥ ፎቶዎችን ማካተት ጀምረዋል ብለዋል፡፡ ከዚህ ለመረዳት የሚቻለው የባህልን ጥናት በተገቢው መንገድ ለማከናወን የሚያስፈልገው መረጃ በቃላት ብቻ መግለፅ ሳይሆን በምስልም ተደግፎ መቅረብ እንደሚገባው ነው፡፡ ይህም የሚጠናውን አንዱን የፎክሎር ገፅታ በመግለፅና በማሳየት በኩል ፋይዳው ላቅ ያለ መሆኑን ነው፡፡

እኔም መረጃ የሰበሰብኩት የተሟላ የፎክሎር/ባህል መረጃ ሊያስገኙ የሚችሉትን የመቅረጫ መሳሪያዎች ፤ መቅረፀ ድምፅ ፣ ፎቶ ካሜራ እና መቅረፀ ምስል በመጠቀምና ማስታወሻም በመውሰድ ነው፡፡ ቀረፃውን ያከናወነልኝም በዞኑ የተለያዩ መስሪያ ቤቶች (በዞንና በወረዳ ማስታወቂያ ፅህፈት ቤቶች) የሚሰሩ የቪዲዮ ካሜራ ባለሙያዎች ሲሆኑ ፣ እነሱን ለማግኘት ባልቻልኩበት ወቅት ደግሞ ቀረጻውን እራሴ አከናውኛለሁ፡፡ በዚህ ወቅት እኔ በተወሰነ ክዋኔ ቀረጻ ላይ ስሆን በሌላ አካባቢ የሚከናወነውን እና ማስታወሻ በመውሰድ ሊያዝ የሚችል የድርጊት መረጃ ሊያመልጠኝ መቻሉ የሚታወቅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ መረጃን የቀረጻ ባለሙያ ባገኘሁበት በሌላ ሥነ ሥርዓት ክዋኔ ወቅት አሟልቼዋለሁ፡፡ ሌላው መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀምኩበት ዘዴ ማስታወሻ መያዝ ነው፡፡ ፎቶና ቀረፃ በፅሁፍ ለሚሰበሰብ መረጃ አጋዥ ቢሆኑም በማስታወሻ የሚያዝ መረጃን ግን አይተኩም፡፡ ለዚህ ነው Dawson (2002:107) የመስክ ማስታወሻ መሰረታዊ መረጃ መሰብሰቢያ መንገድ ነው ያሉት፡፡ በተለይ ቀረፃው በሌሎች ባለሙያዎች ሲከናወን እኔም ጎን ለጎን ማስታወሻ ይዣለሁ፡፡ ቀረፃውን እራሴ በማከናወንበት ወቅት ደግሞ ከቀረፃ በኃላ ማስታወሻ ወስጃለሁ፡፡

### 3.4 የመስክ ጉዞ

ለዚህ ጥናት ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸትና መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ጥናት ቦታው የተጓዝኩት ስድስት ጊዜ ነው፡፡ የመጀመሪያው ጉዞ በሚያዚያ ዘጠኝ ተከናውኖ እስከ ሰኔ ሶስት 2010 ዓ.ም ለ54 ቀናት በመስክ ቆይታ የተደረገበት ነው፡፡ በዚህ ጉዞ መረጃ ከትምህርት ክፍሉ የተፃፈልኝን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ ወደ ዋግኽምራ ዞን አስተዳደር ፅህፈት ቤት በመሄድ የጥናቴን አላማ ለዋና አስተዳዳሪው ካስረዳሁ በኂላ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እንድችል የተፃፈልኝን የትብብር ደብዳቤ ይዤ ወደ ስድስት ወረዳ አስተዳደር ፅህፈት ቤቶች አመራሁ፡፡ የብሄረሰቡን ባህል በወል የሚያሳውቁ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮችን እንዲጠቁሙኝ ጠየቅኂቸው፡፡ እነሱም የየወረዳዎች ባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርጉልኝ ገለጹላቸው፡፡ እኔም ለእነዚህ ባለሙያዎች የብሔረሰቡን ባህል ልቅም አድርገው ሊያውቁ የሚችሉትን በየወረዳቸው ሊገኙ የሚችሉ ግለሰቦችን እንዲጠቁሙኝና እንዲተባበሩኝ እንዲገልፁልኝ ነገርኳቸው፡፡ በዚህ የመጀመሪያ ጉዞዬ ያጋጠሙኝን የተለያዩ ገፅታዎች (የሰርግ ፣ የሞት ፣ የልደት ፣ የእርሻ) በመመልከት እና ቀረፃ በማድረግ መረጃ ያዝኩ፡

፡ ከዚህም በተጨማሪ ቁልፍና ቁልፍ ላላሆኑ የመረጃ አቀባዮችም ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃ አግኝቻለሁ፡፡ ሁለተኛውን የመስክ ጉዞ ያደረኩት በታህሳስ 25 ፣ 2011 ዓ.ም እስከ ጥር 29 ፣ 2011 ዓ.ም ለ34 ቀናት በመስክ ቆይቻለሁ፡፡ በዚህም ጊዜ የተለያዩ ሀገር ሰብዓዊ ልማዶችን ፣ ሥነ ሥርዓቶችን ፣ ባህላዊ እውቀቶችን የብረት ስራ ፣ የሸማ ስራ ፣ የቅል ስራ ወዘተ. ለመመልከት ፣ ለመቅረፅና ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ችያለሁ፡፡ ሶስተኛው የመስክ ጉዞዬ ደግሞ በሁለቱ ጉዞዎች የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ትርንስክራይብ አደረግሁ ፣ በዘውግ በዘውጋቸው ፣ በይዘት ካደራጀሁና ከተነተንኩ በኋላ የተካሄደ ነው፡፡ ይህም በግንቦት ሶስት ፣ 2011 ዓ.ም በመንቀሳቀስ እስከ ሰኔ አምስት ለአንድ ወር አካባቢ በመስክ ቆይታ አድርጌያለሁ ፤ ይህም ጉዞ የተደረገው በአብዛኛው የመረጃ ክፍተትን ለመሙላት የተደረገ ነው፡፡ በአጠቃላይ የመስክ ቆይታ ያደረኩት ከስድስት ወር በላይ ነው፡፡

## 3.5 የጥናቱ አካሄድና አተናተን ዘዴዎች

ማንኛውም ዓይነት የባህል መረጃ ከመስክ ከተሰበሰበ በኋላ የተገኘውን መረጃ አደራጅቶ የመተንተን ሥራ ከአጥኚው በዋነኛነት የሚጠበቅ ጉዳይ ነው፡፡ የሚደረገው ትንታኔ የጠበቀ እንዲሆን ደግሞ መረጃው ታስቦበትና በቂ ዝግጅት ተደርጎበት የተሰበሰበ መሆን ይኖርበታል፡፡ እንዲሁ እንደተገኘ በስሱ የሚሰበሰብ መረጃ ለትንታኔ ሲዘጋጅ የጠለቀና የጠበቀ ትርጉም ያለው ትንታኔ ለማድረግ ካለማስቻሉም በላይ ትንታኔው እንዲሁ ላይ ላዩን የሚደረግ ገለፃ ብቻ ይሆናል፡፡ ይህንንም Bronner እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡ "…Naive analyses can result from inadequate or inaccurate identification." (Bronner, 2007, 70)

ከመስክ የተገኘን የባህል መረጃ በሁለት መልኩ ልንገልጸው እንደምንችል ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ (Schoemaker,1990, p8, Geertz,1973,p6, Lewandowski,2001,p6) አንደኛው ስስ ገለፃ (Thin description) ሲሆን የታየውን ወይም የተሰበሰበውን መረጃ እንዳለ ከላይ ከላይ መግለጽ ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው የዳጎሰ (Thick description) የሚባለው ገለፃ የተገኘውን መረጃ ትርጉም በሚሰጥ መልኩ በጥልቀት መተንተን ማለት ነው፡፡ Lewandowski የሚተነተኑትን የፎክሎር ነገረ ይዘቶች (Texts) ራሳቸው ከመነሻው ስስና የዳጎሱ ሊሆኑ እንደሚችሉ በመጥቀስ "Planar and Deep texts''

በማለት ገልፆአቸው የሚደረገውን ትንታኔ ስስነትና ጥልቀትም ሊወስኑ የሚችሉ መሆናቸውን ያስረዳል፡፡ ጥልቅ ትንታኔ የሚባለውም ለአጠቃላይ ባህላዊ ክንውኑ ፍቺ መስጠት የሚችልን ትንታኔ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ (Lewandowski,2001,p6)

በባህል ጥናት ጥሩ ትንተና የሚባለውም የተገኘውን መረጃ ይዞ የዳጎሰ ትንተና (Thick description) የተደረገ እንደሆነ ነው፡፡ የዳጎሰ ትንተና ለማድረግ ደግሞ መረጃው ገና ከመነሻው እንደሚገባው መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ አጥኚው መረጃ በሚሰበስብበት ጊዜ ለሚሰበሰበው ፎክሎር ነገረ ይዘት (Text)፣ ለክዋኔ አውድ (Context) እና ነገረ ሁኔታ (Texture) ትኩረት ሰጥቶ መረጃውን መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ (Schoemaker,1990, p7) እነዚህ ጉዳዮች በውል ከተጤኑ መረጃውን በበሰለ መንገድ ለመተንተን አይቸግርም፡፡

ስለ አንድ ማህበረሰብ ባህልና ከልማት ጋር ያለውን ቁርኝት ለማጥናት በቅድሚያ የማህበረሰቡን ዋና ዋና ባህላዊ መልኮች በጥልቀት ማጥናትን የግድ ይላል፡፡ ጥናቱንም አስተማማኝና ወጥ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ሰፊ መረጃዎችን በጥልቀት በመሰብሰብ የገለፃና የትንተና ዘዴዎች ከጥቅም ላይ በማዋል የቀረበ ነው፡፡ ይህም የባህሉንና የልማቱን ቁርኝት ከማንሳት በፊት ስለብሔረሰቡ አጠቃላይ ባህል መረዳት ጠቃሚ በመሆኑ የብሔረሰቡን ዋና ዋና መገለጫዎች፣ የህይወት ዑደቶችና ሀገረሰባዊ ልማዶች የሚገልፁት ሁለት ምዕራፎች በቅድሚያ ቀርበው ስለ ብሔረሰቡ ባህል አጠቃላይ ገፅታ ግንዛቤ እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡ እዚህ ላይ ከጥቅም ላይ የዋለው ዘዴ ባህሉን እንዳለ መግለፅ እንጂ ትንታኔ ማድረግ አይደለም፡፡

ቀጥለው የሚመጡት ሁለት ተከታታይ ምዕራፎች ደግሞ ተሰብስበው ከተደራጁት አጠቃላይ የብሔረሰቡ ባህላዊ መረጃዎች በመነሳት ለአካባቢው ልማት ያሉ አሉታዊና አዎንታዊ ባህላዊ ሁኔታዎች ከላይ ከተጠቀሱት ቲዎሪዎች ጋር በማገናዘብ በጥልቀት ተተንትነው የቀረቡባቸው ናቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም ባህሉን ራሱን በማልማት ልማቱን ማፋጠን እንዴት እንደሚቻል አመላካች ሃሳቦችም ይቀርባሉ፡፡ ከጥናቱ በተገኙ ውጤቶች ማጠቃለያነት በመነሳትም ወደፊት ማን ምን ማድረግ እንዳለበት በመጠቆም ጥናቱ ይደመደማል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# 4.የዋግኽምራ ብሔረሰብ ዋና ዋና ባህላዊ ገፅታዎች

የጥናቱ አላማ የሆነው የዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህል ለአካባቢው ልማት ያደረገውን አበርክቶ ወይም ተፅዕኖ ለመመርመር ከመነሳት በፊት በቅድሚያ የማህበረሰቡን ባህል በጥልቀት ማጥናት ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ በስፋት በግብዓትነት የሚያገለግሉት የብሄረሰቡን ባህል አጠቃልይ ገፅታ የሚያሳዩ ባህላዊ እሴቶች በጥቅሉ በቅድሚያ ይዳሰሳሉ፡፡ ለአቀራረብ እንዲያመችም የዋግኽምራ ብሄረሰብ ማህበረ ባህላዊ /Socio Cultural/ ህይወትን የሚመለከቱ ጉዳዮች በዚህ ምዕራፍ ይቀርባሉ፡፡ የአንድ ማህበረሰብ ማህበረ ባህላዊ / Socio Cultural/ ህይወት መገለጫዎች ከሌላው የሚለዩበት ሁነቶች የሚጀምሩት የማህበረሰቡን አባላት በግልም ሆነ በጋራ ከሚለዩባቸው የራሳቸው የሆኑ መስተጋብሮች ናቸዉ፡፡ ከግለሰቡ አካላዊ አቋም ፣ አለባበስ ፣ አጊያጊያጥ ፣ አመጋገብ ፣ አነጋገር/ቋንቋ/ በመነሳት አንድን ሰው በማየት ብቻ ከየትኛው ብሄረሰብ እንደሆነ ለመለየት የሚያስችሉ የተለያዩ ባህላዊ መገለጫዎች አሉ፡፡ የዋግኽምራ ብሄረሰብም የራሱ ባህላዊ መገለጫዎች አሉት፡፡ እነዚህም በዚሁ ክፍል ይቀርባሉ፡፡

## 4.1. ቁሳዊ ባህል

### 4.1.1. አለባበስና አጊያጊያጥ

የዞኑን ማኅበረሰብ አለባበስና አጊያጊያጥ የወንዶችና የሴቶች በማለት በጾታ ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

**የወንዶች አለባበስና አጊያጊያጥ፡-** የወንዶቹን አለባበስ የሕፃናት ፣ የወጣቶችና የትላልቆች በማለት በሶስት ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ ሕፃናት ወንዶች የሚለብሱት ኪታ ነው፡፡ በዛጎልና ድባ ይዋባል፡፡ ጸጉራቸውንም ከመሃል ቁንጮ አስቀርተው ሌላውን ይላጯሉ፡፡ ወጣት ወንዶች ደግሞ ቁምጣ ሱሪና እጅጌው አጭር ሆኖ በጀርባና በፊት ለፊት በልብስ ቁልፍ (መከተሪያ)እና በዛጎል ያጌጠ ሸሚዝ ኳርቶ[11] ይለብሳሉ፡፡ በቁምጣቸው ላይ

[11] ሶራ የተሰኘውን ዘፈን የሚያቀነቅነውም ሆነ የሚቀበሉት ወንዶች ይህንን/ኳርቶ በመልበሳቸው በአሁኑ ጊዜ ሶራ ተብሎ እየተጠራ ነው፡፡

ለውበትና እሾህ ሲወጋቸው ለማውጣት የሚጠቀሙበትን ወረንጦም ያንጠለጥላሉ፡፡ በሥራ ጊዜ በአካባቢው አጠራር አንደርታ ወይም በረባሶ ያደረጋሉ፡፡ ጸጉራቸዉንም ጎፈሬ ያደርጋሉ፡፡ አንዳንዶቹም ለጌጥ ጥርሳቸውን ሙሉ በሙሉ ወይም ጉራማይሌ ይነቀሳሉ፡፡ ክንዳቸው ላይም የመስቀል ቅርፅ ይነቀሳሉ ፤ ክንዳቸውንም የክብ ቅርፅ ያለው አድርገው በእሳት በማቃጠል (በምስር ቂጣ) በማቃጠል የጀግንነት ምልክት ተብሎ የሚገመት ጠባሳ ያደርጋሉ፡፡





ኳርቶ የለበሰ ወጣት (ፎቶ በ.ጋዝጊብላ ወረዳ ባቱ)

ምስል 1፡- ፀጉራቸውን ቁንጮ የተላጩና ኪታ የለበሱ ልጆች ኳርቶ የለበሰ ወጣት

የአባቶች አለባበስ ደግሞ በክትና በዘወትር የሚከፋፈል ነው፡፡ ዘወትር የሚለብሱት በእርሻ ሥራ ወቅት ቆሸሽ ያለ ቁምጣ ሱሪና እጅጌው አጭር የሆነ ሸሚዝ ነው ፤ ዝናብ ሲመጣ ለመከላከል ያስችላቸው ዘንድ ትከሻቸው ላይ ጣል የሚያደርጉት ደግሞ በአካባቢው የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ከቆዳ የተሠራ ቁርንጮ[12] (በ'ኽምጣኝ በልበል)ነው፡፡ የክት ልብሳቸው ግን ባተ ሁለት ሱሪ ወይም ሌላ ሱሪና ኮት በቀጭኑ ተከፍሎ የተሠራ ጋቢ ከጭራ ጋር ነው፡፡ ፀጉራቸውንም እንደ ወጣቶቹ በጣም አያጎፍሩትም ፤ ያሳጥሩታል ፣ በዕድሜ የገፉት ግን አያሳድጉም ፣ ይላጩታል፡፡

**የሴቶች አለባበስና አጊያጊያጥ፡-** የሴቶችን አለባበስም የሕፃናት ፣ የወጣቶችና የትላልቆች በማለት በሶስት ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ ሕፃናት ሴቶች ያልተሸበሸበ ቀሚስ

[12] ቁርንጮ ከልብስነቱም በተጨማሪ ለምንማፍነትም ታገለግላለች፡፡

(ጥብቆ)ይለብሳሉ። ይህም በአብዛኛው ከጥጥ የተሠራና በመቀነት የሚታጠቁት ነው። ጸጉራቸውንም ሌላውን ተላጭተው አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ፀጉር መሃል ላይ ብቻ ትተው በመሠራት በሰለላ ጀምረው ፣ ሁለት ዙር ጋሜና ቁንጮ ይሠራሉ።





ምስል 2፡- ጋሜና ቁንጮ ሁለት ዙር ጋሜና ቁንጮ

ወጣቶች ደግሞ ቀሚስ በመቀነት ታጥቀው ይለብሳሉ። እስከሚወልዱ ድረስ ሰፋ ያለ ቁንጮና ጋሜ ይሰራሉ። ደጋግመው ከወለዱ በኃላ ሳዱላ (ቅርቅር) ይሠራሉ። ይህም ከመሃል ራሳቸው ፀጉራቸውን በክብ ቅርጽ በመላጨት ሌላውን ሹሩባ የሚሠሩት ነው። ትልቅ ሴት ወይም እናት ሲሆኑ ደግሞ ጸጉራቸውን ሙሉ በሙሉ ሳይላጩ ያሳድጉና ሹርባ ይሠራሉ/ድፍን ያደርጋሉ/። በአሁኑ ጊዜ ግን ዘመናዊ ትምህርት ጋር ተያይዞ ሕፃናትም ሆኑ ወጣቶች ፀጉራቸውን ድፍን እያደርጉ ነው።

ይህም ቀደም ሲል የዕድሜ ልዩነት መገለጫና መለያ የነበረው የፀጉር አስተዳደግና አለጫጨት ሙሉ በሙሉ ባይጠፋም እየቀነሰ መምጣቱን ያመላክታል (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ፣ ቃመ 25/02/2010 ዓ.ም)።

ሴቶች ሹሩባቸውን በተለያየ ዓይነት ይሰራሉ። ይህም መደረቢያ የሌለው በወፍራሙ የሚሰራ ሹሩባ/እሽም/፣ መደረቢያ ያለው በወፍራሙ የሚሰራ ሹሩባ/አልባሶ/፣ ገፅታ ተገልብጦ የሚሠራ ሹሩባ/ግልብጥ/፣ገፅታው ሳይገለበጥ የሚሰራ ሹርባ/ግጫ ፣ በጣም ወፍራም ሹርባ/ጉንጉን/ ወይንም ዱርላው ተሰብስቦ የሚሰራ ሹርባ/ድርማም/እና ወፍራምና ቀጭን ተደባልቆ የሚሰራ ሹሩባና በቅርብ የሚታይ ጎበዝና ቆንጆ ይሰራሉ፤ በተለይም በቆላው አካባቢ ደግሞ ቃቂዳ የምትባል ከሳር የምትሰራ የፀጉር ጌጥ ይሰራሉ።

እነዚህ የፀጉር አሰራር ዓይነቶች ወቅትንና ሴቷ የምትገኝበትን ሁኔታ መሠረት ያደርጋሉ። እሽምና ጉንጉን ለአጣዳፊ ጊዜና በሀዘን ወቅት የሚሠሯቸው ናቸው ፣ ድርማም ደግሞ ሴትየዋ በእድሜ በመግፋቷ በዱርላዋ ላለማጌጥ ስትፈልግና የሀዘን ጊዜዋን ወደ ማጠናቀቅ ደረጃ ላይ ስትደርስ የምትሰራው ነው። አልባሶ በማንኛውም ጊዜ የሚሰሩት ሲሆን ግልባጭና ግጫ ግን ሴቶች ከሌላው ጊዜ በተለየ ሁኔታ ተውበው መታየት በሚገባቸው በክብረ በዓላት ፣ በሠርግ ፣ በክርስትና በመሳሰሉት የሚሰሯቸው ናቸው። እነዚህ የፀጉር አሰራሮች ረዘም ያለጊዜ የሚጠይቁ ናቸው። በተለይ ፀጉራቸው ብዙ የሆነ ሴቶች ቀኑን ሙሉ ሲሰሩ የሚውሉበት ጊዜ አለ። ለዚህም ነው በአካባቢው በባህላዊ ዘፈን:

> አንድ ቀን ተሰርቶ አያልቅም ራሷ፣
>
> ላምባዲና ይገፔ ልቁም ከትራሷ።

የሚል የፍቅር ቃል ግጥም የሚገጠምላቸው (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ፣ ቃ.መ 25/02/2010 ዓ.ም)። አለባበስን በሚመለከት ወጣቶቹም ሆኑ እናቶች ከጥጥ ፈትል የተሠራ ወይም ከዝሃ የተሠራ (እሱበሱ) ወይም ከፈትልና ከዝሃ ተደባልቆ የሚሰራ (ጀበርባሬ) ይለብሳሉ ፣ ቀሚሳቸውንም ሆነ ኩታቸውን የተለያየ ቀለም ባላቸው የክር ዓይነቶች/እዳይቶች/ያስውቡታል። በአካባቢው ተዘውትረው የሚመረጡት የክር ዓይነቶችም አረንጓዴ/ቅጠልያ/ወይም ወንዝ አይፈሬ እና ሰማያዊ/ድባ አይነት ናቸው። ቀሚሳቸውንም በጥልፉ ያሳምሩታል። ጥልፉ የቀሚሱ ግማሽ ብቻ የተጠለፈ/ፍቅር ቁምጥ/ወይም ሙሉ ጥልፍ ሊሆን ይችላል። በቀሚሱ ጥልፍ ላይ የሚያያዝ መልጎምም ያደርጋሉ። መልጎም ከብር ወይም ከኒኬል የሚሰራ ክብ ቅርፅ ያለው ነው። የሚታጠቁት መቀነትም ተራ ወይም እስከ ስድስት ዓይነት በሚደርሱ የተለያየ ቀለም

ባላቸው ክር የተዋበ ሰፊ ጥለት ያለውና ዋጋው በጣም ውድ የሆነ /ቃንጃ መትር[13] ሊሆን ይችላል፡፡ ነጠላም ይደርባሉ ፡፡ አጊያጊያጣቸውን በሚመለከት እንደ እድሜ ደረጃቸው ከእራሳቸው እስከ እግራቸው ከተለያዩ ቁሶች የተሰሩ ጌጣጌጦች ይጠቀማሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ቀራንዮ መስቀል ትንሹና ትልቁን በአንገታቸው ያስራሉ፡፡ ድሪና ድንብል ቀለበትም የተለያየ ቀለም ባላቸው ክሮችና ለስላሳ በሆነ ጥቁር ክር ወይም ካሎስ በሚባለው ክር ታስሮ መዋቢያ ነው፡፡ ጣታቸው ላይም ቀለበት ያደርጋሉ፡፡ ክንዳቸው ላይም ባለማፈኛና ማፈኛ የሌለው ሁለት አይነት ድኮት ያደርጋሉ፡፡ እግራቸው ላይም አልቦ ያስራሉ በጣታቸው ከክር ፣ ከኒኬል ወይም ከመዳብ የሚሰራ ቀለበት ፣ በግንባራቸው ላይ ደግሞ ከስንደዶና ከአሸንክታብ ወይም ቅጠታ ትንንሽና የሚያጣብቅ የሆነ የተክል ፍሬ በክር ተደርድሮ ወይም ከሳር የሚሰራ የጌጥ አይነት (ቃቂዳ) ያስራሉ፡ ፡ በዙሪያቸው ደግሞ በታችኛው ክፍል ቀለበት (አላድ) ወይም ጉትቻ ፣ በላይኛው ጫፍ ደግሞ ሽንብር ያደርጋሉ፡፡(ወ/ሪት ወርቃለማሁ ቸኮል ፣ ቃመ. 25/02/2010 ዓ.ም)፡፡



ምስል 3፡-ቃንጃ መትር የለበሰች የብሔረሰቡ ሴት

ሌላውየሴቶች ማጌጫ ንቅሳት ወይም ውቅራት የሚባለው ነው፡፡ ግንባሮቻቸውን ፣ የአይኖቻቸውን ጎንና ጎን ፣ አገጫቸውን ፣ ጥርሶቻቸውን እና በተለይ እናቶች ደግሞ ከአንገታቸው ጀምሮ ወደታች እስከ ጡታቸው ጫፍ ድረስ ይነቀሳሉ (ይወቀራሉ)፡፡ የግንባራቸውንና የአገጫቸውን ንቅሳት ቅርፅ በሚመለከት ከፍያለው (1992፡13) ሕዝቡ

[13] ቃንጃ መትር ማለት ከዋጋው ውድነት የተነሳ ከአንድ በሬ ዋጋ ጋር እኩል ነው ለማለት ነው፡፡

ከሚከተለው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ጋር መስፋፋት ጋር የተያያዘ መሆኑን በመግለፅ በሥዕል አስደግፈው አቅርበዋል፡፡



ምስል 4፡- የብሔረሰቡ ሴቶች ባህላዊ አለባበስ (ፎቶ ዋግኽምራ ዞን ባቱ)

### 4.1.2. የምግብ አሠራርና አመጋገብ

በዋግኽምራ ብሔረሰብ ተዘውትሮ የሚበላው እንጀራ ሲሆን ይህም ጣቢታ ወይም ደገሎ ሊሆን ይችላል፡፡ጣቢታ ከጤፍ ብቻ የሚሰራ/የሚዘጋጅ ሲሆን ደገሎ ደግሞ ከስንዴ ፣ ከማሽላና ከገብስ ቅልቅል የሚዘጋጅ ነው፡፡ የደገሎ አገጋገር ከጣቢታ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም አቦካኩና አቀጣጠኑ ግን የተለያየ ነው፡፡ የጣቢታ ሊጥ/ብሆ/ የሚቦካው ዱቄቱ ታምሶ ሲሆን የደገሎ ግን አይታመስም ፤ የጣቢታ ሊጥ ቀጠን ያለ ሲሆን የደገሎ ደግሞ ወፈር ያለና በተደጋጋሚም የሚታሽና የሚደኅል[14] ነው፡፡ ሊጡ የሚቀጠነው የጣቢታ በቀዝቃዛ ውሃ ሲሆን የደገሎ ግን በፈላ ውሃ ነው፡፡

ሌላው ተዘውታሪ ምግብ ቂጣ ነው፡፡ ቂጣው የስንዴ ወይም ከባቄላ ዱቄት ቅልቅል የሚዘጋጅ ነው፡፡ ሌላው ቦትቧቴ ነው፡፡ ልክ እንደ ቂጣ ሆኖ ነገር ግን ማታ በጥበጥ/ቦትቦት/ተደርጎ ተቦክቶ ያደረ ነው፡፡ አነባበሮም ሌላው የምግብ ዓይነት ነው፡፡

[14] ስያሜውን ያገኘው ከዚህ ከአሰራሩ ሂደት ነው፡፡

ይህም ሁለት ቦትቧቴ አንድ ላይ ተደራርቦ የሚጋገር ነው፡፡ አረጦ ደግሞ ባይዘወተርም በበዓልና በውቂያ ጊዜ ይጋገራል፡፡ አዘገጃጀቱም ሁለት አነባበሮን በተልባ ፣ በኑግና በድልህ ቀብቶ/ለምጥጦ/ በሀብታሞች ቤትም በመደራረብ ቅቤ ይቀባል፡፡ ሌላው የምግብ ዓይነት አምባሻ ነው፡፡ በሌላው አካባቢ ዳቦ ተብሎ የሚጠራው ስለሆነ የተለየ አዘገጃጀት የለውም፡፡ ትኩሴ የሚባለው ደግሞ በተወሰኑ በዓላትና በተለይም በሁሉም ቤት በጸሎተ ሀሙስ ፣ በዝ ክር ፣ እንግዳ ለመቀበልና ወደ ክርስትና ድግስ ቤት ይዞ ለመሄድ ይጋገራል፡፡ ማታ ትንሽ የስንዴ ዱቄት በጥበጥ ተደርጎ /ተገብጦ/ያድራል ፤ በማግሥቱ ለብ ባለ ውሃና በዛ ባለ ዱቄት ይለወሳል/ይሸበለላል/፡፡ ለማጣፈጫም የአብሽ ዱቄት ይጨመርበታል፡፡ ሶስት ጊዜ ከተነሳ/ኩፍ ካለ/በኃላ ሰፌድ ላይ ይጠፈጠፍና ቅርፅ ወጥቶለት/ተሸልሞ/ወፋፍራም እንጨት በተማገደበት ምጣድ/የብረት ምጣድ/ ላይ እንዳሁላ /የተክል ዓይነት /ወይም የቁልቋል /የበለስ/ ትልታይ ይደለደላል/ይረበረባል/፡፡ ከዚያም ከሸክላ ወይም ከጭቃ የተዘጋጀ ክዳን ይከደንና ትኩሴው ጢስ እንዳይገባበትና እንዳይቀላ ዙሪያው በጭቃ ይደፈናል፡፡ በአካባቢው የታወቁ ቄሶችን ወይም ዲያቆናትን ስም በመጥራትም ከወዛንታው ላይ በነዲዱ የመስቀል ቅርጽ ይደረግበታል፡፡ ይህም በደንብ እንዲነፋ ለማድረግ ነው ተብሎ ይታመንበታል፡፡ በሌላው አካባቢ ድፎ ሲጋገር ክዳኑ ላይም እሳት በተለይም ኩበት እንዲነድበት ሲደረግ ፣ ትኩሴ ሲጋገር ግን ወዛንታው ላይ እሳት አይነድም፡፡ ሌላው ባህላዊ ምግብ ቃተኛ ነው፡፡ የሚዘጋጀውም ለተወሰኑ ቀናት ነው፡፡ አዘገጃጀቱም ትኩስ እንጀራን በአዋዜና በቅቤ ፣ ጾም ከሆነም ከኑግ ወይም ከሱፍ የሚሠራ ባህላዊ ዘይት/ቅባኑግ/በመቀባት ነው፡፡ ለምግብነት የሚዘጋጀውም ለአራስ ፣ ለሙሽራ ፣ ለእንግዳ ወይም ሀብታሞች ቤት ለቁርስ ነው፡፡ በአስቸኳይ የሚፈለግ ሌላው የምግብ ዓይነት ቋቋቴ ነው፡፡ የሚጋገረውም በብረት ምጣድ ወይም በምጣድ ላይ ነው፡፡ ሊጡም በወፍራሙ ሆኖ በጣት ጌጥ ይወጣለታል፡፡ ምስስ ደግሞ ለስንቅነት የሚዘጋጅ የምግብ ዓይነት ነው፡፡ አዘገጃጀቱ ትኩስ እንጀራ በአዋዜ ይቀባና ተጨባብጦ ነው፡፡ ብርኩታ ደግሞ እሩቅ ተጓዦች ወይም ከቤታቸው ርቀው የሚሄዱ ከብት ጠባቂዎች የሚያዘጋጁትና የሚመገቡት ነው፡፡ አዘገጃጀቱም የስንዴ ወይም የማሽላ ዱቄት በተገኘው ሁሉ በገበታ ፣ በጎድጓዳ ድንጋይ ይለወስና የጋሉ ድንጋዮች ላይ ተጠፍጥፎ እሳት ውስጥ በመክተት ይጋገራል፡፡ ጋጋሪዎቹም ወንዶች ናቸው፡፡ ንፍሮና ቆሎም ባይዘወተሩም ለምግብነት የሚውሉ ናቸው፡፡ ንፍሮ በልደታ (በመባቻ) ይቀቀላል፡፡ ቆሎ ለቡና ቁርስነት ፣ ለመክሰስ/ለመቆያ/ እና ለመተከዣነትም

ያገለግላል፡፡ እርሶ አደሩ በሥራ የደከመ አእምሮውን ለማሳረፍ በጠላ እያወራረደ ይቆረጣጥማል፡፡ ዳቦ በማርም ይበላል፡፡ ለማጣፈጫነትም የተለያየ የወጥ ዓይነቶች ይዘጋጃሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ዋናው ስልስ ነው፡፡ የሚዘጋጀውም ከእርጎና ከበርበሬ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ስቅስቆ ነው፡፡ ይህም የሚዘጋጀውም በደቃቁ ከተከተፈ ስጋ ሲሆን ማቁላሊያውና ማብሰያው /መከለሻው/ቅቤ ብቻ ነው ፤ ምንም ውሃ አይጨመርበትም፡፡ በዚህም ምክንያት የሚሰራው በተወሰኑ ሀብታሞች ቤት ብቻ ነው፡፡ የምስር ፣ የአተርና የባቄላ ክክ ወጥም ተዘውታሪ ሲሆን ፍልቅልቅም አልፎ አልፎ ለችኮላ ከተልባና ከአዋዜ ብቻ ይዘጋጃል፡፡ ዶሮ ወጥም በዓመት በዓልና እንግዳ ለመቀበል የሚዘጋጅ ነው፡፡ ሀብታሞች ግን አዘውትረውም ይመገቡታል ፤ የበግ የፍየልና የከብት ስጋ ወጥም ይሰራል፡፡ ለፆም ወቅትና ለድግስ እልበት[15] (በኽምጥኛ አዞ) ይዘጋጃል፡፡



ምስል 5፡- የብሔረሰቡ ባህላዊ የምግብ አቀራረብ (ፎቶ ዝቋላ ወረዳ ባቱ)

[15] እልበት የሚዘጋጀው ሱፍ ተነክሮ ያድርና ይቀቀላል ፤ በማግስቱ ታጥቦ ይደቆሳል ፣ በሚቀጥለው ቀን ደግሞ ይጠመቃል፡፡ለማወፈሪያነትም የባቄላ ክክ በሱፍ አስር ውሃ ይጠመቃል፡፡ በአንዳንድ አካባቢ ደግሞ ባቄላ ሲታጣ የማሽላና የስንዴ ንፍሮ ተጠምቆ ወይም የገብስ ቂጣን ፍትፍት በመጥመቅ ይጠቀሙበታል፡፡ ለማጣፈጫም ቃሪያ ፣ ነጭ ሽንኩርትና ዝንጅብል ተደቁሶ ይቀላቀልበታል፡፡ ለጥሩ ጣዕም ሲባልም በርከት ያለ ነጭ ሽንኩርት ተልጦና በእንጨት ተሰክቶ ከጤና አዳም ቅጠል ጋል ጣል ይደረግበታል፡፡ ከሶስተኛው ቀን ጀምሮ በጣም ቀጭን ከሆነ ውሃው ተጠሎ ፣ ወፍራም ከሆነም ሳይጠለል እየተቀዳ ለመመገቢያነት ይቀርባል /መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ፣ ቃመ. 25/02/2010 ዓ.ም/፡፡

ለመጠጥነት ተዘውታሪው ጠላ/በኽምጣኝ ሽላ/ነው፡፡ ይህ ከገብስ ብቻ የሚዘጋጅ/ኮረፌ ፣ ከኮረፌ የጠራ ጠላ ፣ ከበቆሎ ወይም ከማሽላ የሚዘጋጅ ቀጠንና ጠራ ያለ ጠላ/ዝልል/ ነው፡፡ ለአራስና ለእንግዳም ወፍራም ኮረፌ/ዱቃ ይጠመቃል ፤ ከተገኘም ማር ጣል ይደረግበታል፡፡ ባይዘወተርም ጠጅም አልፎ አልፎ የሚጠጣ ነው፡፡ ወተትና የወተት ተዋጽኦዎችም በተለይ በገጠሩ ተዘውትረው የሚጠጡ ናቸው (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ፣ ቃመ. 06/07/2010 ዓ.ም ፣ ወ/ሮ አለምነሽ በላይ ፣ ቃመ. 06/07/2010 ዓ.ም ፣ ወ/ሮ ታምር አሰፋ ፤ ቃመ. 08/10/2010 ዓ.ም)፡፡

### 4.1.3 የእደ ጥበብ ዕውቀቶች

የሰው ልጅ ለመኖር ቁሳዊ ፣ መንፈሳዊና ሌሎች ፍላጎቶቹ ሊሟሉለት ይገባል፡፡ እነዚህን ፍላጎቶች ለማሟላት ሰዎች ከተፈጥሮ ጋርና እርስ በርስ የማያቋርጥ መስተጋብር ያደርጋሉ፡፡ በዚህም የግንኙነት ሂደት ወቅት ዕውቀት ይመነጫል/ይዳብራል ፣ ልምድ ይጠራቀማል ፣ ክህሎች ይገኛል ፣ ግንዛቤ ይሰፋል ፣ ወዘተ እነዚህ የሰው ልጅ ለመኖር የሚረዱትን ከአካባቢው ያገኘ ዘንድ የሚረዱ እሴቶች በባህላዊ ዕውቀት ስር ይመደባሉ፡፡ በመሆኑም ሀገራዊ/ባህላዊ/ ዕውቀትን በማጎልበት ከልማት ጋር ማጣጣም ይቻላል፡፡ ስለሆነም የዚህ ጥናትዊ ጽሁፍ ዓላማ የዋግኽምራ ብሔረሰብን ባህል ለአካባቢው ልማትም ሆነ በልማት ወደኂላ መቅረት ያደረገው አስተዋፅኦ ወይም ተፅዕኖ ይኖር እንደሆነ መመርመርና ባህላዊ ሁነቶችን የልማት መሳሪያ በማድረግ የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን አስተዋፅኦ ማድረግ እንደሚችሉ ማመላከት ነው፡፡ ስለሆነም የተለያዩ የእደ ጥበብ ዕውቀት ዓይነትን እንደ ምሳሌ በመወሰድ የብሔረሰቡ አባላት እንዴት እንደሚጠቀሙባቸውና ለምን እንደሚገለገሉባቸው ፣ ከምን እንደሚሰሯቸውና የነዚህን ጥበባት ባለሙያ የሆኑትን ሰዎች እንዴት እንደሚገነዘቧቸው እንመለከታለን፡፡

ዋግኽምራዎች የራሳቸው ባህላዊ ስራት የሆኑ ልዩ ልዩ የእደ ጥበብ ውጤቶችን ሰርተው ይገለገሉባቸዋል፡፡ ይህንን ሀገራዊ/ባህላዊ የዕውቀት ውጤቶችን አስመልክተው የዞኑ የባህልና ቱሪዝም ባለሙያ የሆኑት አቶ ባዬ አስምሮም እንዲህ ያብራራሉ፡-

> አገራዊ ዕውቀት የሚባለው በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚፈጠር ከትውልድ ትውልድ የሚወራረስ በጊዜ የተፈተነና የኅብረተሰቡ ተሳታፊ አባላት ለተለያየ ጉዳይ የሚጠቀሙበት ሀብት ነው፡፡ ሀገራዊ ዕውቀት በአንድ ባህል ውስጥ

የሚገኝ ልዩ አካባቢያዊ እውቀት ነው። እነዚህ ሀገራዊ ዕውቀቶች በዚህ በዋግኽምራ ብሔረሰብ ዘንድ ትልቅ ድርሻ ያላቸው ህዝባዊ ሀብቶች ሲሆኑ ገበሬው ሕይወቱን የመሰረተባቸው የሚያረስባቸው መሳሪያዎች ፣ የሚወቃባቸው ፣ የሚያራግብባቸው ወዘተ የሚሰሩት በዚህ በባህላዊ ጥበብ ነው። ባህላዊ ጥበቦቹም በአብዛኛው በማህበረሰቡ የታወቁት እና አገልግሎት ላይ ያሉት ለአብነት ያህል የብረት ፣ የቆዳ ፣ የልዩ ልዩ ጌጣጌጥ ፣ የሽመና ፣ የስፌት ፣ የሸክላ ፣ የቅል ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች /መሰንቆ ፣ ክራር ፣ ዋሽንት ፣ ከበሮ/ እና የስብ ስራዎች ናቸው። እነዚህ ዕውቀቶች ዛሬም ድረስ የራሳቸው ባለሙያ አላቸው። ሌሎቹ የማህበረሰቡ አባላት እንደሚፈልጓቸውና እንደ አገልግሎታቸው ከባለሙያዎቹ በመግዛት ለግልጋሎት ያውሏቸዋል። ባለሙያዎቹም ለገበሬው የእርሻ መሳሪያዎች /ወገል ፣ ማረሻ ፣ ዶማ ፣ ማጭድ ፣ ገጀራ ወዘተ/ ከብረት ፤ ምራን ፣ መረገጥ ፣ የማነቂያ ጠፍር ፣ ጫማ ፣ መጫኛ ጠፍር ፣ ጅራፍ በጠቅላላው የገበሬ የእርሻ መሳሪያዎች በጥቅል መጠሪያው ጥቅል የሚባለውን ከበሬ ቆዳ ያዘጋጃሉ። ማንኛውም ዓይነት የገበሬ የእርሻ መሣሪያዎች እርጥብና ደረቅ መሳሪያዎች የሚሰሩት በባህላዊ ዕውቀት ባለቤት በሆነው በዚያው በብሔረሰብ ውስጥ የሚኖር ግለሰብ ነው። ይህ ባለሙያ ለገበሬው ትልቅ ጥበበኛ ነው። ለገበሬውም በጣምም አስፈላጊ ሰው ነው። ባለሙያው ለገበሬው ችግር ፈቺ ነው። ማረሻው ቢበላሽ ይሠራል ፣ መጥረቢያው ቢዶለዱም ስለት ያወጣል ፤ ማጭዱን ይጠረጥራል[16] ፣ የወገሉ ብረት ቢጣመም ያስተካክላል ፤ በዚህ የተነሳ የባህላዊ ዕውቀት ባለሙያዎች አስፈላጊ ሰዎች ናቸው (ቃመ. 09/10/2010 ዓ.ም)።

አቶ ባዬ ስለባለሙያዎቹ የሚከተለውን ገልፀዋል። እነዚህ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ከጥንት ጀምረው ቅር የሚያሰኛቸውና የማይቀበሉት ጉዳይ አለ። ይኼውም አሁን አሁን ይሻላል እንጂ የእጅ ባለሙያዎቹን ሌሎች የብሔረሰቡ አባላት ከሰው የተለዩ አድርገው ሌላ ሰውን ከነሱ ውጪ እንደሆኑ በመቁጠር ፣ ባለጅ ፣ ጠይብ ፣ ቡዳ ፣ ወዘተ እያሉ

[16] በአካባቢው አገላለፅ ‹‹መጠርጠር›› ማለት ለማጭድ ጥርስ ማውጣት ማለት ነው። ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ ስለሚያጭዱበት የማጭዱ ጥርስ ያልቅና ባዶ ይሆናል በዚህ ጊዜ የብረት ስራ ባለሙያው እንደገና ጥርስ ሲሰራለት ነው ‹‹ይጠረጥራል›› የሚባለው።

ይሰድቧቸው ነበር። አሁንም በግልፅ ባይሆንም ህብረተሰቡ በተለየ አይን እንደሚያዋቸው ፣ በቀትር ፀሃይ ወደ ቤታቸውና መስሪያ ቦታቸው እንደማሄዱ ፤ ቢሄዱ እንኳን እንደ ምስርና የቡዳ መድሃኒት የሚባል ቅጠል ወይም ፌጦ ጨብጠው እንደሆ እና በፍርሃትና በጥርጣሬ እንደሚመለከቷቸው ገልፀዋል። ይገርምሃል! በእነሱ መሳሪያ እየተጠቀሙ ፣ እየተገለገሉ ባለሙያውን መጥላት ፣ እንኳሶና አሳንሶ ማየት እጅግ የሚያሳፍር ነው። በዚህ በዘመናችን የልዩ ልዩ እደ ጥበባት ባለሙያዎች ያሉ ቢሆንም በእርሻ ማረስ ስራ ተሰማርተው እንደ ሌሎቹ መሆን እንጂ የሚፈልጉትን ሙያ እየጠሉት ነው ለማለት ይቻላል። ለዚህም ማሳያው ድሮ ከተወራው የእደጥበብ ውጤት ለምሳሌ ማጭድ ፣ ቢላዋ ፣ ማረሻና ወገል ፣ ወዘተ የተሻሻለ ሌላ ሲሰራ አይታይም። እድገትም አላመጣም ፤ የባለሙያዎቹም ኑሮ አልተለወጠም ፤ ዕውቀቱም አላደገም ፤ ይህ “ለምን ይመስልሃል?” ይህን እደጥበባዊ ስራ የሚሰሩትን ሰዎች ብሄረሰቡ በጥቅል ፤ የተለያዩ ሰዎች በግል ስለሚያገሏቸው ፣ ስለሚጠሏቸውና ስለሚያንኳሱኳቸው ነው። ኅብረተሰቡ በዚህ በኩል ያለው ግንዛቤ ለህብረተሰብ ለማስጨበጥ ጥረት እያደረግን ነው። አሁን አሁን ይሻላል ፤ ይሁን እንጂ እስካሁንም ድረስ በተለይ በብረት ቀጥቃጭና በሸክላ ሰሪዎች ላይ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለመቅረፍ ከባድ ፈተና እንደሆነ ቆይቷል። ከነሱ ጋር ጋብቻ ወይም ሌላ ዝምድና በፍጹም ለመቀጠል አይፈልጉም። የሚጋቡት ራቅ ካለ ቦታ በመሄድ እንደነሱ ተመሳሳይ ሙያ ያላቸውን ፈልገው ነው። የዚህን ያህል ስር የሰደደ አጉል የሆነ አስተሳሰብ አለ። ይህም በመሆኑ ሙያውን ራሳቸው ባለሙያዎቹ እየናቁትና እየጠሉት በመምጣቱ በዚህ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኘው የብረት ቀጥቃጭና የሸክላ ስራ ባለሙያዎች ቁጥር በጥም ጥቂት በጣት ሊቆጠሩ የሚችል ብቻ ናቸው። ስራውን የሚሰሩት በግድ ተለምነው ነው። እንደውም አሁን አሁን ገበያ ሌላ ቦታ በመሄድ ነው ማረሻና ሌላ የብረት ውጤቶችን እየገዙ ያሉት ገበሬዎች በማለት ገልፀዋል (ቃመ. 09/10/2010 ዓ.ም)።

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ለመረዳት የሚቻለው የእደ ጥበብ ባለሙያዎቹ በዕውቀታቸው እንደማይኮሩና በስራቸው እንደሚያፍሩ ነው። በዚህም የተነሳ ዕውቀታቸውን የበለጠ ከማሻሻል ፣ ከማበልፀግና ከማሳደግ ይልቅ እሱን በመተው በሌላ ስራ ላይ መሰማራትን እንደሚመርጡ ነው። በዚህም የተነሳ የተጠቀሱት የባህላዊ ዕውቀትና ጥበቦች እየጠፉ እንደሆነ ለመገንዘብ አያዳግትም። ስለሆነም ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ይዞት ለተነሳው

የባህልና የልማት ትስስር ያለውን አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖዎች በትንታኔው ላይ በሰፊውና በጥልቀት ለማየት ማሳያ ሆኖ ስለሚያገለግል በቦታው ከነማሳያው ይብራራል ፤ እያንዳንዳቸው በምሳሌነት በማቅረብ በብሔረሰቡ እንደመገለጫነት የሚታወቁትን እንመልከት፡፡

ሀገረ-ሰብዓዊ ዕውቀት በአንድ መልክዓ ምድራዊ መቼት የሚኖሩ ማህበረሰቦች ከተፈጥሮ አካባቢያቸው የተሻለ ጥቅም ለማግኘት የሚያስችላቸው ዕውቀት ፣ ብልሃቶችና ክሂሎችን የሚያጠቃልል እሳቤ ነው፡፡ ይህ የእውቀት ስርዓት አንድ ማህበረሰብ በኑሮውና በደህንነቱ ውስጥ ለሚገጥሙት ፈተናዎች ፣ እክሎችና ማነቆዎች መፍትሔ ለመፈለግ ካደረጋቸው የረጅም ዘመናት ጥረቶች ፣ ሙከራዎች እና ውድቀቶች ነጥረው የወጡ ለበቀለበት ስነ-ምህዳራዊና ማህበራዊ መቼት ስለ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ተገቢነት እንዳላቸው የሚታመንባቸውን እምነቶችን ፣ ግንዛቤዎችንና ተፈጥሮአዊ ፍላጎቶችን ለማሟላትና አካባቢያዊ የኢኮኖሚያዊ ዕድሎችን ለመለወጥ የሚያስችሉ የአሠራር ስልቶች የመገልገያና የማምረቻ መሣሪያዎች አበጃጀት ዘዴዎች ይጠቀልላል[64]፡፡ በመሆኑም የዋግኽምራ ብሔረሰብ አባላት ስለ አካባቢያቸውና ስለተፈጥሮ ያካበቱትን ዕውቀት በእለት ከእለት ሕይወታቸው ከሚገለጥባቸው የእርሻ ዕውቀት ፣ የቤት አሰራር እና ከህክምና (ባህላዊ) እውቀታቸው አንፃር ከዚህ ጥናት ጋር የሚበጁትን ወስደን እንመልከት፡፡

**የብራና ስራ**

በዋግኽምራ ብሔረሰብ ብራና ፍቀው መጽሐፍ የሚያዘጋጁ አባቶች እንዳሉ መረጃ አቀባዮቼ ገልፀውልኛል፡፡ እነዚህ የብራና ስራ ባለሙያዎች ዕውቀቱን ያገኙት ከአባቶቻቸው ሲወርድ ሲወራረድ በልምድ እንደሆ ይናገራሉ፡፡ ይህንን የብራና ስራ ዕውቀት አስመልክተው አባ አሸብር አለሜ እንደሚከተለው ገልፀውልኛል፡-

> ብራና ፍቀው ቀለም በጥብጠው መጽሀፍትን ማዘጋጀት ከጥንት ከአባቶቻችን አክሱማውያን ያገኘነው ዕውቀት ነው፡፡ የሃይማኖት አባቶች ብራናን ከፍየል ቆዳና ከበግ ቆዳ ፍቀው ፣ ቀለም ጠቅሰውና ፊደል ቀርፀው የሃይማኖት መጽሐፍትን ማዘጋጀት ዋና ተግባራቸው ነበር፡፡ መጽሐፍቱም በውስጣቸው የሚይዙት የእግዚያብሔር ቅዱስ ቃል በመሆኑ ረድኤት ያደረባቸው ናቸው፡፡ የብራና

መጻሕፍቱም ዋነኛ አገልግሎቱ በቤተክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ግልጋሎት መስጠት ነው፡፡ አሁን አሁን ስራው እየተዳከመ ሄዶ እንጂ በብራና ላይ የተፃፉ መጽሐፍት ሃይማኖታዊ ግልጋሎት ብቻ ሳይሆን የታሪክ ፣ የህግና ደንብ ፣ የህክምና ፣ የፍልስፍና ፣ የባህረ ከዋክብት እና ሌሎችም ብዙ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ የብራና መጻህፍት ይዘጋጁ ነበር፡፡ አሁን ያሉት ግን ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውሉ ብቻ ናቸው የሚገኙት፡፡ የብራና መጽሐፍት ለማዘጋጀት ቆዳ ያስፈልጋል፡፡ ለብራና አገልግሎት የሚውለው የፍየል ወይም የበግ ቆዳ ነው፡ ፡ ያልተጎዳ ፣ ያልተጫጫረና ያላረጀ ጥሩ ቆዳ ተፈልጎ ይመጣል፡፡ ይህም ቆዳ የሸክላ ጋን ውስጥ በውሃ ተዘፍዝፎ ለሶስት ቀናት ይቆያል፡፡ ከጋኑ ውስጥ ሲወጣ መሬት ላይ ይዘረጋና እየተለካ ስቁረት[17] ይወጣለታል፡፡

ከዚያም አራት ማዕዘን እንጨት ላይ ይገተራል፡፡ የተገተረው ቆዳ ላይ ሆጻ[18] ይነሰነስና በማረመም[19] በደንብ ይታሻል፡፡ ይህም ሰግለጡን[20] ለማስለቀቅ የሚደረግ ነው፡፡ በመቀጠልም በሞረድ ካራ ይፈገፈጋል፡፡ እንደተገተረ ለአንድ ቀን ያህል ፀሐይ ላይ እንዲውል ይደረግና ሲደርቅ የቆዳው ፀጉር በተሞረደ መጥረቢያ ይፋቃል፡፡ ፀጉሩ ለቆ ሲያበቃ በውሃ ታጥቦ ሆፃ ይደረግበትና በማረመሚያ ይታሻል፡፡ ከዚህ በኋላ ቆዳው ጥራዝ ለማዘጋጀት የተስተካከለ ዝግጁ ይሆናል (ቃመ. 12/09/2010 ዓ.ም)፡፡

---

[17] ስቁረት ቆዳውን ለመገተር ችካሮቹን ለማስገባት በቆዳው ዙሪያ የሚበጁ ቀዳዳዎች ናቸው፡፡

[18] ከወንዝ ዳር የሚገኝ አሸዋ/ድንጋይ ተቀጥቅጦ የሚዘጋጅ ዱቄት ማለት ነው፡፡

[19] ከወንዝ ውስጥ የሚገኝ ነጭ ጠፍጣፋ ድንጋይ፡፡

[20] ከቆዳው ጋር ተጣብቆ የሚገኝ ስብ ስጋ ነው፡፡



ምስል 6፡- የብራና መጽሐፍ ባለሙያው በስራ ላይ

ከዚህ በላይ ከተገለፀው ዝርዝር የብራና ስራ ለመገንዘብ የሚቻለው ባህላዊ ዕውቀቱ የተገኘው ከጥንት አክሱማውያን አባቶቻቸው እንደሆነና እስካሁን ድረስ ሙያው እና ዕውቀቱ ተጠብቆ መኖሩን ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የባህላዊ ዕውቀቱ ባለቤቶች እንዳይጠፉ ሃይማኖታዊ በረከት እንደሚያገኙበት በማመን ከስራው ከሚያገኙት ገቢ ሳይሆን ረድዔቱን በማሰብ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ባህላዊ ዕውቀቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ሆኗል፡፡ ብራናውን ፍቀው ካዘጋጁ በኋላም መጽሐፉን ለመጻፍ የሚያገለግሉት የመፃፊያ ቀለምና መቃም የሚያዘጋጁት ራሳቸው ስለሆኑ ተያያዥ ልዩ ልዩ ዕውቀቶችን በውስጡ የያዘ በመሆኑ ይህ የብራና ሥራ ዕውቀት ከፍተኛ ጥቅም አስገኚ ነው ማለት ይቻላል፡፡

**የቆዳ ስራ**

ዋሻች ከከብት ቆዳ በባህላዊ መንገድ በማልፋትና በማዘጋጀት የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመስራት ይጠቀማሉ፡፡ በዚህ ባህላዊ የቆዳ ስራ በሰቆጣ ወረዳ በተለይም ጫው በሚባል ቀበሌ የሚገኙ የብሔረሰቡ አባላት በስፋት ተሰማርተው እንደሚገኙ ከመረጃ ሰጪዎችና እኔም ባደረኩት ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የቆዳ ስራ የመጀመሪያው ምዕራፍ ቆዳ ከያለበት ማሰባሰብ ነው፡፡ ባለሙያዎቹም የቆዳ ፍላጎታቸውን የሚያሟሉት በከተማ /ሰቆጣ/ ከሚፈፀም እርድ የሚገኘን ቆዳ በመግዛት ነው፡፡ የተሰበሰበውን ቆዳ ጋምቃ/ጋን/ውስጥ ለሶስት ቀናት ያህል በውሃ

ይዘፈዘፋል፡፡ ከዚያም ቆዳውን ከጋን በማውጣት መሬት ላይ ዘርግተው በስጋው በኩል እምቧይ ተደርጎበት ቆዳው ይጠቀለልና በድንጋይ ይደበደባል፡፡ ይህም እምቧዬቹ እንዲፈርጡ ያደርጋል፡፡ ተዘርግቶ የከብት ሽንት ይደፋበትና በእጅ ይታሻል፡፡ ቆዳውን መልሶ በመጠቅለል ለግማሽ ቀን ያህል ታፍኖ እንዲቆይ ይደረጋል፡፡ ይህም ቆዳው/ፀጉሩ እንዲለቅ ያደርጋል፡፡ ቆዳው ተዘርግቶ እንቧዩ እንዲረግፍ ይደረጋል፡፡ በመቀጠልም የከብት ሽንትና የእምቧይ ውህድ ፈሳሽ ውስጥ ቆዳዎቹን በማስገባትና በመክደን ለሶስት ቀናት እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡ ከዚያም ቆዳዎቹን ከጋን ውስጥ በማውጣት ወደ ወንዝ በመውረድ በደንብ ከታጠቡ በኃላ በፀሐይ እንዲደርቅ ይደረጋል፡፡ ቆዳው እዚህ ደረጃ ሲደርስ የቡሻ ዱቄት[21] ይዘጋጃል፡፡ ቡብሻው ተልጦ ቅርፊቱ በፀሐይ ከደረቀ በኃላ ተሰባብሮ በትልቅ ሙቀጫ ተወቅጦ በወንፊት ይነፋል፡፡ በጋን ውስጥ በውሃ ይበጠበጣል፡፡ ፀጉሩ የለቀቀውን ቆዳ ብጥብጡ ውስጥ በመጨመር በእጅ በሚገባ ይታሻል፡፡ የቡሻው አገልግሎት ቆዳውን ማቅላት/ቀላ ያለ መልክ እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡ ከዚያም መሬት ላይ ይቸነከርና ለአንድ ቀን ይውላል፡፡ ከዚያ ለስራ የተዘጋጀ ቆዳ ይሆናል፡፡ ነጭ መልክ ያለው ቆዳ ከተፈለገ የተመለጠው ቆዳ በቡሻ መነከሩ ይቀርና በተልባና በከብት ሽንት ውህድ ይታሻል (አቶ ብርሃኑ አወቀ ፣ ቃመ. 03/06/2011 ዓ.ም)፡፡

የቆዳ ስራ ዕውቀት በዋግኽምራ ብሔረሰብ አባላት ዘንድ የብዙ ባህላዊ ዕውቀቶች ጥምርም የሆነ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም ቀለም ከአካባቢያቸው ከሚገኙ እፅዋትና አዝዕርት ቀምመው በማዘጋጀት ቆዳውን በመቀባት ያማረ መልክ እንዲኖረው ያደርጋሉ፡፡ በዚህም እንደፈላጊው ምርጫ ልዩ ልዩ የቆዳ ተፈላጊ ቁሳቁሶችን ይሰራሉ፡፡ የሰዎችንም ፍላጎት ከማርካታቸውም በላይ ባለሙያዎቹ በመሸጥ ገንዘብ ያገኙባቸዋል፡፡ ኑሮኣቸውንም ይደጉሙበታል፡፡ በመሆኑም የቆዳ ሥራ የገቢ ምንጭ የሚያስገኝ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

---

[21] የቡሻ ዱቄት የሚባለው በብሔረሰቡ አካባቢ አጠራር ‹‹ተኬይቡቡሻ›› እየተባለ የሚጠራ ቁጥቋጦ መሳይ የዛፍ ዓይነት ነው፡፡ የዚህን ዛፍ ቅርፊት ሰብስበው አድርቀውና ወቅጠው አልመው ከዚያ በጥብጠው ቆዳውን እንዲቀላ/ቀይ መልክ እንዲኖረው ሊያደርግ የሚችል ነው፡፡



ምስል 7፡- አንቀልባ

## የጌጣ ጌጥ ስራ

በዋግኽምራ ብሔረሰብ አባላት ዘንድ የጌጣጌጥ ስራ ዕውቀት በስፋት የሚገኝ ነው፡፡ የጌጣጌጥ ስራውን አስመልክተው ስለ አጀማመሩና ስለ እደጥበቡ አመጣጥ የሙያ ባለቤት የሆኑት አቶ ግርማይ አባዲ እንዲህ ይገልፃሉ፡፡

> የጌጣጌጥ ስራ ዕውቀት ከሰለሞን ጥበብ የተገኘ ነው፡፡ በአገራችን/ዋግኽምራ ውስጥ የተጀመረው ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር አብረው በመጡ የእጅጥበብ ባለሙያዎች አማካኝነት ነው፡፡ ከመጡት ሙያተኞች አብዛኞቹ መሬት ተሠጥቷቸው ነገስታቱን ማገልገላቸውን ሲቀጥሉ ፤ የጌጣጌጥ ስራ ባለሙያዎች ግን መሬት ስላልተሰጣቸው ሙያውን እንደመተዳደሪያ ይዘውት ዘለቁ፡፡ እውቀቱን ያገኘነው ከቀደሙት አባቶቻችን በልምድ ነው፡፡ ነገር ግን አሰራሩና የሚዘጋጁት ጌጣጌጦች እንደየአካባቢው ይለያያሉ፡፡ የምናዘጋጃቸው ጌጣጌጦች ቀለበት ፣ ማርዳ ፣ ጠልሰሞች ፣ አምባሮች ፣ ድንብል ፣ መስቀል ፣ የጆሮ ጉትቻ/ቀለበቶች ፣ የእግር አልቦዎች የመሳሰሉትን ነው፡፡ ጌጣጌጦቹን ለማዘጋጀት የሚያስፈልገው ብርና መዳብ ሲሆኑ የምናገኘውም ከድሮ ሳንቲሞች ነው፡፡ በተለይም የማርትሬዛና የአፄ ኃ/ስላሴ ሳንቲሞች ናቸው፡፡ ሳንቲሞቹን በማቅለጥ ለተፈለገው የጌጥ አይነት እናውለዋለን፡፡ ጌጣጌጦቹን ለመስራት

የምንጠቀምባቸውን መሳሪያዎች ራሳችን ነው የምንሰራቸው፡፡ የተለያየ መጠን ያላቸው እርሳስ ፣ ብሩሽ ፣ ችንካር ፣ ሚዛን ፣ መዶሻ ፣ መቆንጠጫ ፣ መቀሶች ፣ ጉጠት ፣ የሚበሉ መሳሪያዎች ያስፈልጋሉ፡፡ እነዚህም እኛው የምንሰራቸው ናቸው፡፡ አሁን አሁን እንደ ድሮው አልሆነም፡፡ ከዘመኑ ስሪት እየተጠቀሙ ጌጣጌጦችን የሚፈልጋቸው ቀንሷል ፤ የምንሰራበትንም ብር ፣ መዳብ እና ነሃስ የመሳሰሉትን ማግኘትም እየከበደን ነው፡፡ በመሆኑም ስራው እየቀነሰና ተፈላጊነቱም እየቀረ ሄዷል፡፡ የአባቶቻችን ውርስ ስለሆነና እኛም ሙያ ሆኖብን እንሰራዋለን እንጂ እንዳይጠፋ ብለን ጥቅምም እያገኘንበት አይደለም (ቃመ. 23/08/2010 ዓ.ም)፡፡

ከላይ ከባለሙያው ገለፃ ለመረዳት የሚቻለው ባህላዊ የጌጣጌጥ ስራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰና በመጥፋት ላይ እንደሆነ ነው፡፡ ሙያው/ዕውቀቱ/ እንዳይጠፋና ቀጣይነት እንዲኖረው ልጆች ሙያውን ለመማር ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን ከባለሙያው ለመረዳትም ተችሏል፡፡ ለመጥፋት ምክንያት የሆኑትም ሁኔታዎች እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡ ‹‹የዘመናዊ ጌጣጌጦች በፍጥነት መስፋፋት የባህላዊ ጌጣጌጥ ጠቀሜታና ስራ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ አድርጓል ፤ ሌላው ስራው በራሱ አሰልቺ ፣ አድካሚ እና የሚያስገኘውም ጥቅም ከዚህ ግባ የሚባል ባለመሆኑ ሙያውን ለመማር ልጆቻችንም ፍላጎት የላቸውም ፤ በመሆኑም ተቀባይ ወይም ተተኪ እያጣን ነው (አቶ ግርማ ግደይ ፣ ቃመ. 23/08/2010 ዓ.ም)፡፡

የባህላዊ ባለሙያው ስጋታቸውን ከላይ በጠቀሱት መልኩ ቢያስረዱም ይህ ባህላዊ ዕውቀታቸውና ሙያቸው እንዳይጠፋ ለቅርሱ ቀጣይነት የበኩላቸውን እየተወጡ እንደሆነ የተለመደውን ስራቸውን ሲያከናውኑ ለመመልከት ችያለው፡፡



ምስል 8፡- የጌጣጌጥ ባለሙያው እና የጌጣጌጥ አይነቶች

**የሽመና ስራ**

የሽመና ስራ በዋግኽምራ ብሔረሰብ ዘንድ ከሚከናወኑ የእደ ጥበብ ዕውቀቶች አንደኛው ነው፡፡ ይህ ሀገራዊ ዕውቀት ከረጅም ዘመናት ጀምሮ በመከወን ላይ የሚገኝ የእውቀት ዘርፍ እንደሆነ የብሔረሰቡ አባላት ይገልፃሉ፡፡ ይህንን ባህላዊ የእውቀት ትግበራ በተመለከተ አቶ ጥጋቡ ምርቴ የተባሉ አርሶ አደር እንዲህ ይገልፃሉ፡-

> የሽመና ስራ ሙያ በዚህ በሀገራችን አገልግሎቱ ብዙ ነው፡፡ ሸማኔ ባይኖር መቼም ራቁታችንን እንሄድ ነበር፡፡ የነሱ ስራ ሰው ያናንቀዋል እንጂ ከፍተኛ ነው፡፡ መቼም ባላገር በምርቱ እየተጠቀሙና ገበናቸውን እየከተቱ ስራቸውን ይንቃሉ ፤ ይገርማል እኮ ልጄ! ማስተዋል የለንም፡፡ ሁላችንም የለበስነው ኩታ ፣ ጋቢ ፣ ነጠላ ፣ ቀሚስ ፣ እንዲሁም ጀበርባሬ[22] ፣ እረ ብዙ ነው የሚሰራው

[22] ጀበርባሬ ማለት በብሔረሰቡ አጠራር ወፈር ያለ ነጠላ/ጋቢ ማለት ነው፡፡

በሸማኔ ነው። ይህንን እነሱ ባይሰሩልን ከየት እናገኘው ነበር። መቼም ሁሉም አንድ አይነት ዕውቀት የለውም ፤ ሁሉም የየራሱ ሙያ አለው ፤ የእነዚህም ሸማኔዎች ብልሃት መቼም የተለየ ነው። ግን አናከብራቸውም ‹‹ቁጢት በጣሽ›› እያልን እናዋርዳቸዋለን ግን አለማወቅ ነው። እነሱም ከአባቶቻቸው ወርሰው ያገኙት ሙያ ነው አሁን አሁን ግን እንደድሮው አይደለም ፤ ሰው ገብቶታል። መሳደቡንም ፣ ማግለሉንም ትቷል። ከነሱ ጋርም መጋባት መዛመድ ጀምሯል። እረ እንደውም ጥንት በዘር የማይሰራው ሁሉ እየለመደው ሸክላ ሁሉ መስራት ጀምሯል። ማወቅ መልካም ነው (ቃመ. 26/09/2010 ዓ.ም)።

ከዚህ በላይ ከቀረበው ገለፃ ለመረዳት የሚቻለው የሽመና ጥበብ እውቀቶችና እውቀቱን የሚተገብሩ ሰዎች በብሔረሰቡ ዘንድ የተለያየ ቦታ (ክብር) እንደሚሰጣቸው ነው። ይኼውም ከስራው ባህሪ ፣ ስራው ከሚከወንበት ቦታ ፣ ስራው ከሚያስገኘው ገቢ አልያም ከተሳሳተ ግንዛቤ በመነሳት ሙያውን የሚነቅፉ ወገኖች አሁንም እንዳሉ ነው። ይህም በሌላ ወገን ሙያውን የሚደግፉ ፣ የሚያዳብሩ ሙያተኞችንም የሚያበረታቱ ወገኞች አሉ። ለስው ያላቸውን አክብሮትም በሰነቃሎቻቸው ጭምር እንዲህ ይገልጡታል፡-

- እየንሰብድ ቀሶውየን (ኽምጥኛ)
  የስራ ጥሩ ሽመና (አማርኛ)
- አየን ፈር ቅጥድ ሽጋ አቀንድ (ኽምጥኛ)
  የሸማኔው ኩታ አቤት ማማሩ (አማርኛ)[23] እያሉ ሙያውን ያሞግሳሉ ፤ ሙያተኛውንም ያበረታታሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ‹‹ቶርዳ ቁጢጥ ቅዘውይ ዘሆር/የቁጢት/የድር በጣሽ ልጅ/›› እያሉ የሙያው ባለቤቶችን መንቀፍ ስራው እንዳይስፋፋ የሚያደርጉ ወገኖችም እንዳሉ መረጃ ሰጪዎች ይገልፃሉ። እነዚህ ወገኖች ለሽመና ስራና ለሙያው ያላቸውን የተሳሳተ

[23] ትርጉሙ በመ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል የብሔረሰቡ ተወላጅ። ብዙዎቻችን የኽምጣኝ አባበሎች/ንግግሮችን የተረጎሙልኝ እሳቸው ናቸው)።

አመለካከት በቃላዊ ግጥሞቻቸው ሳይቀር እንዲህ እያሉ እንደሚገልፁ ከሰበሰብኩት መረጃ ለማወቅ ችያለሁ፡፡ የሚከተሉትን ቃላዊ ግጥሞች እንመልከት፡-

| ኽምጣኝ | አማርኛ |
| --- | --- |
| ኢያሌም ጨወመኒ | አሞሌም ጨው ነው ወይ፣ |
| ትርባም ትርማቹ | ተልባም እህል ነው ወይ፣ |
| ሳሆም ብረ ትማዩ | ሆም ጠመንጃ ነው ወይ፣ |
| ሸማኔም አጃር እየውም | ሸማኔም ሰው ነው ወይ፡፡.(ትርጉም መ/ት ወርቃፈራሁ)፡፡ |

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ቃላዊ ግጥሞች የሚያመላክቱት የሸመና ስራና ባለሙያው እንዳይሻሻልና እንዳይከበር የሚያደርጉ አሉታዊ አባባሎች ናቸው፡፡ በመሆኑም በብሔረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ወገኖች ለባህላዊ ዕውቀቱ/ጥበቡ ያላቸው ግንዛቤ የተዛባ እንደሆነ ለመረዳት አያዳግትም፡፡ ይህንን የተዛባ አስተያየት ከዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዓላማ ጋር አስተሳስሮ ለማየት በትንታኔው ውስጥ በጥልቀት ይቀርባል፡፡ ከዚህ ላይ ለማሳያ ያህል ያሉትን ባህላዊ ገፅታዎች ለአብነት ማቅረብ ብቻ ነው፡፡

**የሸክላ ስራ**

በዋግኽምራ ብሔረሰብ አባላት ዘንድ የሸክላ ስራ በስፋት የሚከወን የእደ ጥበብ የስራ ዘርፍ ነው፡፡ በሰቆጣ ከተማ ውስጥ ጫወ በሚባለው ሰፈር ውስጥ የሚኖሩ የብሔረሰቡ አባላት ዋና የኑሮ መሠረታቸው በሸክላ ስራ ነው፡፡ እነዚህም የሸክላ ስራ ባለሙያዎች ለስራቸው የሚሆነውን አፈር በብዛት ወደ ቆላማው የዞኑ አካባቢ በመሄድ ተስማሚ ነው የሚሉትን መርጠው ይዘው ይመጣሉ፡፡ የሚመርጡትም የአፈር ዓይነት ነጭ አፈር እና ጥቁር አፈር የሚባሉትን የተለያዩ የአፈር ዓይነቶችን ያመጣሉ፡፡ በመቀጠልም ጥቁሩን በዛ፣ ነጩን አነስ አድርገው ይደባልቃሉ፡፡ በማስከተልም ከወንዝ ዳር የሚገኝ ብልጭልጭ አሸዋ በዓይነጠባብ ወንፊት ተነፍቶ ከአፈሩ ጋር ይደባለቃል፡፡ እንዲሁም ቀደም ብለው ሲሰሩ የተበላሸ ወይም የተሰበሩ የሸክላ ቁሳቁሶችን በድንጋይ ወፍጮ ፈጭተው ይጨምራሉ፡፡ በማስከተልም የሁሉንም ድብልቅ በወንፊት ነፍተው ሲጨርሱ መሬት ላይ የላስቲክ ሸራ አንጥፈው በላዩ ላይ አፈሩን አድርገው በውሃ ይለውሱታል ፣ በሚገባም ደጋግመው ያሹታል፡፡ ጭቃው እጅ መያዝ/እጅ ላይ መጣበቅ/ሲያቆም እሽቱ

በቂ መሆኑ ይረጋገጣል፡፡ ከዚያ በኃላ ጭቃው የሚፈለገውን ቁሳቁስ ለማዘጋጀት ዝግጁ ይሆናል በማለት መረጃ ሰጪዬ እንዴት አይነት ዝግጅት እንደሚያደርጉ መረጃ ሰጪዬ ወ/ሮ ማንጠግቦሽ ደሳለኝ[24] ገልጸውልኛል፡፡

የተዘጋጀው ጭቃ ወደ መገልገያ ቁስነት ለመቀየር የሚደረገውን ቀጣይ ሂደት እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡ መጀመሪያ ጭቃውን ለስራ እንዲያመች በእጃችን እናድቦለቡለዋለን፡፡ ከዚያም ጭቃው የሸክላ ዕቃዎችን ለማዘጋጀት የሚያገለግል ከጭቃ ፣ ከአመድና ገለባ የሚዘጋጅ ክብ ቅርፅ ያለው ዝርግ የሆነ መስሪያ ቁስ ላይ ይደረጋል፡፡ ይህ ለመስራት የተፈለገውን ቁስ ቅርፅ እንዲይዝ ነው፡፡ ከዚያም ዕቃዎቹ ሲሰሩ የእጅ ጣቶቻችን የነካባቸውን የጎባበጡ ቦታዎችን በባህር ማሽላ ቆረቆንዳ በመዳበስ እናስተካክላቸዋለን፡፡ በመቀጠልም በቅል ስባሪ ውሃ ውስጥ እየነከርና የማለስለስ ስራ እናደርጋለን ፤ በተጨማሪም በከብት የጎን አጥንት ወይም በጎማ ቁራጭ የማለስለስ ስራን እናደርጋለን፡፡ ከዚያም ለትንሽ ሰዓት/ደቂቃ ነው/ያህል ከቆየ በኃላ በሻማ እየተዳበሰ ይስተካከላል፡፡ በመቀጠልም በሸንበቆ የምንፈልገውን ዓይነት ቅርፅ /ንድፍ/እናበጅለታለን፡፡ በመጨረሻም ላስቲክ በውሃ በማርጠብ ዕቃውን በማሽከርከር የመጨረሻውን የማለስለስ ስራ እናከናውናለን፡፡ ዕቃው በጥሩ ሁኔታ ከለሰለሰ በኂላ ቀይ አፈር በውሃ በጥብጠን ዕቃውን እንለቀልቀዋለን፡፡ ይህም ዕቃውን ቀላ ያለ መልክ እንዲኖረው ስለሚያደርግ ነው፡፡ ከዚህ በኃላ በእሳት የመተኮስ ስራን እናደርጋለን፡፡ በመተኮሻው ቦታ ጭራሮ /አነስተኛ የደረቀ እንጨት/ይከመራል ፣ በላዩ ላይም ኩበት ይደረግበትና እሳት ይለኮሳል፡ ፡ ከዚያም የተዘጋጁት የሸክላ ዕቃዎች ከእሳቱ ላይ ይደረጉና ለተወሰነ ጊዜ በሚነደው እሳት ይለበለባሉ ፤ ይህም የሚደረገው ጥንካሬ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው (ወ/ሮ ማንጠግቦሽ ደሳለኝ ፣ ቃመ. 22/10/2009 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ በላይ በስፋት ከተገለፀው የአሰራር ሂደት ለመረዳት የሚቻለው የሸክላ ስራ ባለሙያዎች የሚገለገሉባቸውን የመስሪያ መሳሪያ ከዚያው በአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች መጠቀማቸውን ፣ እንዲሁም ለሸክላ ስራው የሚሆነውን ጥሬ ሀብት ራሳቸው ባለሙያዎቹ የሚገኙበት ቦታ አስሰው የሚያገኙ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን የዓፈር

[24] ወ/ሮ ማንጠግቦሽ ደሳለኝ ራሳቸው የሸክላ ስራ ባለሙያ ናቸው፡፡ የአሰራር ሂደቱን የሚገልጹት በተግባር የሚከወኑትን ነው፡፡

ዓይነቶቹን በመምረጥ ለስራ ዝግጁ ማድረጋቸው ነው። ይህም የሸክላ ቁሳቁሶችን መስራት ብቻ ሳይሆን ጥሬ ሀብቱን ለይተው ማወቃቸው ምን ያህል ብልሆች እንደሆኑ ለመገንዘብ ያስችላል።



ምስል 9፡- የብሄረሰቡ የክሸላ ድስት ዓይነት

ከላይ በተጠቀሰው መንገድ የሚዘጋጁት/የሚሰሩት የመገልገያ ቁሳቁሶች ምን ምን ዓይነቶች እንደሆኑ እና ስማቸውን እንደሚከተለው ገልፀዋል። ጀበና ፣ ድስት ፣ የተለያዩ ዓይነትና መጠን ያላቸው እጣን ማጨሻ ፣ የአበባ ማስቀመጫ ፣ የከሰል ማንደጃ ፣ ምድጃ ፣ ጉልቻ ፣ የዳቦ መጋገሪያ የሸክላ ምጣድ ፣ የእንጀራ መጋገሪያ ምጣድ/ምጎጎ/ ፣ እንስራ ፣ ገንቦ ፣ ጋንና፣ ማንኮሪያ ናቸው (ቃመ. 22/10/2009 ዓ.ም)፡ ፡

እነዚህ የተዘረዘሩት የቤት ውስጥ የሸክላ እቃዎች በእያንዳንዱ በዋግኽምራ ማህበረሰብ ቤት ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን በምልከታ ወቅት አይቻለሁ። የተሰማሩት አባላትም ገቢ ለማግኘት ሕይወታቸውን እንደሚመሩበት ከመረጃ ሰጪዎች ለማወቅ ችያለሁ ፤ እኔም በሚሸጡባቸው ቦታዎች የራሱ የሸክላ ተራ በሚል መጠሪያ ደርድረው ሲሸጡ አይቻለሁ። የሸክላ ስራ ትልቅ ጥበብ ነው ፤ ባለሙያዎቹም የገቢ ምንጫቸው የተመወረተው በዚሁ ስራ ነው። የስራው ውጤት/ምርትም ለማህበረሰቡ በቤት ውስጥ ለሚገለገሉበት ማንኛውም የቤት ውስጥ ስራ ዋነኛው መገልገያቸው የሸክላ ስራው

ውጤት ነው ፤ ይሁን እንጂ የሙያው ባለቤቶች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ማህበራዊ ደረጃ ዝቅ ያለ እና በጥርጣሬ ዓይን የሚታዩና የሚገለሉ ናቸው፡፡ ከሌላው የማህበረሰቡ አባላት ጋር በእኩል አይታዩም፡፡ የተለያዩ አግላይ ስሞችን ይሰጧቸዋል ለአብነት ያህል በጣም ተስፋፍቶ የሚገለፀው ስያሜያቸው "ጠይብ" ፣ "ቡዳ" ፣ "ባለጅ" የተሰኙ መጠሪያዎችን በመስጠት ከሰው የተለዩ አድርገው እንደሚያዋቸው የዚህ ሙያ ባለቤት የሆነችው[25] ወ/ሮ ማንጠግቦሽ ደሳለኝ ምርር ብለው ገልፀውልኛል ፤ በዚህም የተነሳ ሙያው መሰደቢያ ሆኗል፡፡ ሙያው ጥቅም የሚያስገኝ ፣ ዕቃዎቹም ለሰዎች ትልቅ ጥቅም የሚሰጡ መሆናቸው እየታወቀ ባለሙያውን "ማጣጣል" ማራከስ ፣ እንደነሱ ሰው መሆናችንን ረስተው የሌለ ስም መስጠትና መሳደብ ውስጥን ያማል፡፡ ይገርማል የመኖሪያ ቦታችን ሳይቀር የተለየ ነው ፤ መቼም ዛሬ ዛሬ ከመንግስትም ከሃይማኖትም ይመስለኛል በይፋ መናገሩ መሳደቡ ቢቀርም የጥንቱ ግን አልቀረም፡፡ የቻለ መሬት ማግኘት የሆነለት ይህንን ዕውቀት እየተወ መሬቱን እያረሰ ይኖራል ፤ አካባቢው በእርሻ ሰብል በኩል ጥሩ ባለመሆኑ እራሱን ለመደጎም ተመልሶ ይህንኑ ሙያውን ይሰራል፡፡ አዝመራው ደግ ሲሆን ደግሞ ይተወዋል፡፡ እንዲህ እያለ ይኼው ሙያው ሳይጠፋም ሳይለማም አለ፡፡ እኛም ያሉትን ቢሉንም ሆደ ሰፊ ሁነን ኑሮኣችንን ለመግፋት እንደነገሩ እየሰራን ይዘነዋል፡፡ አልተውነውም ፤ ዕውቀት አይደል! ሙያ በጄ አይልህም ልተወው ብትለው አይለቅም (ቃመ. 22/10/2009 ዓ.ም ፣ ቃመ. 18/08/2010 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ በላይ ከተገለፀው ሀሳብ የምንረዳው የእደ ጥበብ ባለሙያዎች በማህበረሰቡ ዘንድ በዝቅተኛ ደረጃ መታየታቸው ሙያውን የበለጠ ሊያስፋፉት ፣ ሊያበለፅጉትና ሊያሳድጉት አለመቻላቸውን ፤ እንዲሁም ከነጭራሹም ሌላ የስራ መስክ ለምሳሌ እርሻ ካገኙ ሊተውት እንደሚችሉ ነው፡፡ በመሆኑም በእደጥበብ ሙያ በብሔረሰቡ ዘንድ ያለው ግንዛቤ አናሳ ብቻ ሳይሆን መሰደቢያም እንደሆነ ነው፡፡ የጥበቡ ባለቤቶችም በዚህ የተዛባ አስተሳሰብ ሳቢያ ውስጣቸው የተከፋ ፣ ኅሊናቸው የተጎዳ መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡ ሆኖም ለሙያው ካላቸው ፍቅር የተነሳም እንደነሱ አገላለፅ ሙያውን "ሳይጠፋም ፣ ሳይለማም" አቆይተውታል፡፡ የሚሰጣቸውን አግላይ ስም ሁሉ ችለው

---

[25] ወ/ሮ ማንጠግቦሽ ደሳለ፣ ሙያውን ከልምድ ያገኙ ሲሆን አቶ አበበ ያለው ደግሞ የጌጣጌጥ ባለሙያ ናቸው፡፡ የሰጡኝ መረጃ/ሀሳብ በአጠቃላይ የባህላዊ ዕውቀት ሽክላ ስራ፣ ሽመና፣ ብረት ቅጥቀጣ፣ አንጥረኛ ወዘተ የተባሉት ሁሉ ባለሙያዎቹ በሌላው ዘንድ ያላቸው ማህበራዊ ደረጃ ዝቅተኛ እንደሆነ ነው፡፡

ለሙያቸው ሆደ ሰፊ ሁነው እንዳይጠፋ ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረጋቸውን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

**የቅል ስራ /ለቅሽማ/**

በዋግኽምራ አካባቢ ለተለያዩ ግልጋሎቶች ከሚውሉ የቤት ቁሳቁሶች ውስጥ አንዱ ቅል ነው፡፡ ቅል የተለያዩ መገልገያዎችን ለማዘጋጀት ፣ ለጌጥነት እና ለስጦታ ዕቃነት ያገለግላል፡፡ የቅል ዕቃዎችን የማዘጋጀት ስራ በአብዛኛው በሴቶች የተያዘ ነው፡፡ ለልዩ ልዩ ተግባር የሚውሉትን የቅል ዓይነቶችን ማሳመር ፣ ማስዋብና በላያቸው ላይ የተለያዩ ንድፍ ወይም የቆዳና የዛጎል ጌጣ ማስጌጥ እና ማስዋብ የሁሉም የብሔረሰቡ ሴቶች ተግባር ነው፡፡ ይህንን የቅል ስራ ጥበብን የስራ ሁኔታ አስመልክተው መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል የሚከተለውን ነግረውኛል:-

> ‹‹የቅል ዕቃዎችን የማዘጋጀት ሂደት የሚጀምረው ቅሉን ከማብቀል ነው፡፡ ገበሬዎች በዘር ወቅት /ሰኔ እና ግንቦት /ዘር ሲዘሩ ከመሬታቸው ዳርዳር የቅል ፍሬዎችን ይተክላሉ፡፡ የተተከለው የቅል ፍሬ በቅሎ ፣ አድጎና ፍሬ ቅል ሆኖ ከመስከረም ወር ጀምሮ የተተከለው ቅል ለመቆረጥ ይደርሳል፡፡ በዚህ ወቅት ትላልቅ እና ትናንሽ ቅሎችን ሰብስበው ያጠራቅማሉ፡፡ ከዚያም ቅሉ ይነደላል /አንገቱ ይቆረጣል/፡፡ በውስጡም ያሉት ፍሬዎች እና እንሽጡ እንዲወጣ ደረጋል፡ ፡ ፍሬዎቹ በቀላሉ አልላቀቅም ካሉ ሐምግሊና የሚባል ተክል ቅጠሉ ተጨቅጭቆ ከውሃ ጋር በመደባለቅ ቅሉ ውስጥ ይደረግና ለሶስት ቀናት ያህል ይቆያል፡፡ ቅጠሉን እንደ መርዝ /ኬሚካል ለማለት ነው/ በመጠቀም የቅሉን ውስጠኛ ክፍል ከፍሬው ጽዱ ያደርጋሉ፡፡ በመቀጠልም መገፊጅ በሚባል ትልቅ ድስት /የሸክላ ነው/ውሃ ይሞላና ቅሎቹን በመክተት እንዲፈላ ይደረጋል፡፡ ይህም የቅሎቹን የውጭ ክፍል ላይ የሚገኘውን ሻካራ ቅርፊት በማንሳት ቅሎቹን ለስላሳ ያደርጋቸዋል፡፡ የተጨቀጨቀው የሐምግሊና ቅጠል ጥቅሙ ማለስለስ ነው፡፡ ከዚያም ጠላ ተጠምቆበት በነበረ ጋን ውስጥ በመክተትና ጋኑን እፍን አድርጎ በመክደን ለአራት ቀናት እንዲቆይ ይደረጋል፡፡ ይህም ቅሉ በሙቀቱና በእንፋሎቱ ቀይና የሚያምር መልክ እንዲኖረው ማድረጊያ ዘዴ ነው፡፡ ከዚያም ቀጥሎ ቅሉ ውስጥ ትንሽ አሬራ በማድረግ በአክማ ቅጠል ጢስ ይታጠናል፡፡ ይህም የቅሉ የውስጥ ክፍል እንዲለሰልስና ጥሩ ቃና እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ቅሎቹን በቆዳና በሌሎች ቁሳቁሶች ማስዋብና ለአገልግሎት ምቹ የማድረግ ስራ ይቀጥላል (ቃመ. 20/10/2009 ዓ.ም)፡፡



ምስል 10፡- በውበት ያጌጠ የቅል ስራ (ለወተት እና ለቅቤ ማስቀመጫነት የሚውል)

እነዚህን የዝግጅት ሂደቶች አልፈው ከቅል ከሚዘጋጁት ቁሳቁሶች መካከል ምን ምን እንደሆኑ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን መረጃ ሰጪዬ ጠቅሰውልኛል፡፡ እነዚህም ይላሉ “ሰበጹቃ ንጥር ቅቤ ማስቀመጫ አነስ ያለ ቅል ስትሆን የምትቀመጠውም ማድ ቤት ውስጥ ነው ፤ ለቅሽማ ሙሽሪት ወደ ባሏ ቤት ስትሄድ የሚያስፈልጓትን የመዋቢያና የግል ቁሶቿን የምትይዝበት፡፡ አሰራሯም ስፌት መቀመጫ/መሰረት/ ይሰራላታል ፤ በቆዳና በዛጎል ትዘመዘማለች ፤ ማንጠልጠያም ይደረግላታል፡፡ ስቅጣ ሽቶ ፣ ቅቤና ጥሩ ጠረን ያላቸው ቅጠሎች ተደባልቀው የሚቀመጥባት አነስ ያለች ቅል ፤ በቆዳና በጉንጎና የተዋበችና ማንጠልጠያም ያላት ነች፡፡ ስንቅ መያዣ የሚባሉትም ከቅል የሚዘጋጁ መገልገያዎችም አሉ፡፡ ሚስት ለባላ በቅል ወተት ታቀርባለች፡፡ ይህም ለባሏ ያላትን ፍቅር እና ክብር መግለጫ ተደርጎ ይቆጠራል” (ወ/ሮ ወዳጅ ወ/ኪዳን ፣ ቃመ. 21/10/2009 ዓ.ም)፡፡

ከመረጃ ሰጪዎች ለመረዳት እንደተቻለው ከቅል የተለያዩ መገልገያዎችን በማዘጋጀት ለጌጥነት ፣ በስጦታ ዕቃነት ፣ ለሴቶች ልዩ ልዩ የመዋቢያ ቁሶችን መስራት እንደሚቻልና የስራ ውጤቱም እንደ ትልቅ የባህላቸው ዓይነተኛ መገለጫ መሆኑን ነው፡ ፡ እንዲሁም ሴቶች በተዋበና ባጌጠ ቅል ወተት ለባሎቻቸው ካቀረቡ ፍቅርና አክብሮት መግለጫ መሆኑን የመጠቆም አንድምታም እንዳለው ነው፡፡ ስለሆነም እነዚህ የቅል ስራዎች በሴቶች እንደመዘጋጀታቸው መጠን የሚያስተላልፉትም መልዕክት ትልቅ ፋይዳ ያለው ነው ለማለት ይቻላል፡፡

በዋግኽምራ ብሔረሰብ ሴቶች ዘንድ የሚዘጋጁና የሚሰሩ ባህላዊ የእደ ጥበብ ስራዎች የቅል ስራ ብቻ አይደለም፡፡ ሌሎችም እንደ የስፌት/ሳቀነ/ እና የሸክላ ስራም አሉ፡፡ በብሔረሰቡ ሴቶች የሚሰሩ እና ለቤት ውስጥ አገልግሎት ከሚውሉ ቁሳቁሶች ውስጥ ከፍተኛ ሚና ከሚጫወቱት ውስጥ የስፌት ስራ ዕውቀት አንዱ እንደሆነ የሙያው ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ታምር አሰፋ እንዲህ ይገልፃሉ፡-

> የስፌት ስራዎች ብዙ ዓይነት ናቸው፡፡ የሚሰሩትም ከተለያዩ ነገሮች ነው፡፡ ከአንድ ብቻ አይሆንም፡፡ለስፌት ስራ ከሚያገለግሉት ዕፅዋት ውስጥ የቁልቋል ስር ፣ ጭረት/ቃጫ እና እጃራ ከሚባል ተክል ነው፡፡ የእነዚህን ዛፎች ስር በመንቀል ፣ በመፋቅ ፣ በመሰንጠቅ እና በውሃ እያራስን የፈለግነውን ዓይነት ስፌት እናዘጋጃለን፡፡ አሁን አሁን እነዚህ ዛፎች እየጠፉ ስለመጡ ከኬሻ ፣ በማዳበሪያ ተተልትሎ የሚፈለገውን ዓይነት መስራት ተለምዷል፡፡ የሚሰሩትም ዕቃዎች ሰፌድ ፣ መሶብ ፣ ወስከንቢያ ፣አገልግል ፣ ወንፊት ፣ የመሳሰሉት ሲሆኑ ለቤት ጌጣጌጥ የሚሆኑም ይሰራሉ (ቃመ. 08/10/2011 ዓ.ም)፡፡



ምስል 11፡- የስፌት ስራ ዓይነቶች

### 4.1.4. የቤት አሠራር

በብሄረሰቡ ዘንድ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ ባህላዊ የቤት አሰራር ዕውቀት አላቸው፡፡ እነዚህም የቤት አሠራር ዓይነቶች አምስት ናቸው፡፡ እነዚህም ክብ ፎቅ ቤት/ህድሞ/፣ ባለአራት ማዕዘን ፎቅ ቤት/ደብር/ ፣ ባለአንድ ወለል ቆርቆሮ ክዳን ቤት ፣ አዳራሽና ጎጆ ቤት ናቸው፡፡ ህድሞ በምድር ቤቱ ሶስት ክፍሎችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህም ጓዳ/የእቃ ቤት/፣ የእንግዳ መቀበያ/ሳሎን/እና የምኝታ ክፍል ናቸው፡፡ ደብር ደግሞ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ሲሆን በምድር ቤቱ ሶስት ወይም ሁለት ክፍሎች ሊኖሩት ይችላል፡፡ ባለሶስቱ ጓዳ/የእቃ ቤት/፣የእንግዳ መቀበያ /ሳሎን/ እና የምኝታ ክፍል ናቸው፡፡ በባለሁለቱ ደግሞ ሳሎንና አንድ ጓዳ ብቻ ይኖረዋል (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቃመ. 10/09/2009 ዓ.ም ፣ መ/ት ወርቃፈራሁ ፣ ቃመ. 25/02/2010 ዓ.ም)፡፡ የህድሞም ሆነ የደብር ወደ ሁለተኛው ፎቅ መውጫ ደረጃ በቤቱ ውስጥ ወይም በውጭ በኩል ሊሆን እንደሚችል እነዚሁ መረጃ ሰጪዎች ገልፀዋል፡፡



ምስል 12፡- ህድሞ /ጽራ/ ቤት

የህድሞን ቤት ለመሥራት በአንድ ሰው ብቻ የሚከናወን አይደለም፡፡ ቤት ሰሪው ግለሰብ በቅድሚያ አሠራሩን የሚችለውን ባለሙያ ይፈልጋል፡፡ ባለሙያው ከተገኘ በኃላ ደቦ/ወበራ/[26] ይጠራል፡፡ የተጠሩት የሰፈሩ ሰዎች ቤቱን ለመሥራት የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች ባላ ፣ ወራጅ ፣ ማገር ፣ ልጥ ፣ ምሰሶ ፣ ሣርና ድንጋይ ይዘው በመምጣት ከባለሙያው በሚሠጣቸው ወይም በሚያሳያቸው የአሠራር መሠረት በመተጋገዝ ህድሞውን በጋራ ይሰሩታል፡፡ ቤቱን የጎጆ ቅርፅ እንዲይዝ ካደረጉ በኋላ ጣሪያውን በማገሮች በመረብረብ በልጥ ያስሩታል፡፡ በመቀጠልም በሳር ይሸፍኑታል፡፡ ጣሪያውን ለመሸፈን የሚያገለግሉ የተለያዩ የሣር አይነቶችን ይጠቀማሉ ፤ ሰንበሌጥ ሳር ፣ ጠጅ ሣር ፣ ወዘተ ለቤት ክዳንነት የሚያገለግሉ የሳር ዓይነቶች ናቸው፡፡ የቤቱ ግድግዳ ከውስጥና ከውጭ ከአፈርና ከሳር በሚዘጋጅ ጭቃ ይመረጋል፡፡ ቤት ውስጥ መደብ ፣ የሰዎች መቀመጫ /ጉደታ/እና የዕቃ ማስቀመጫ ቦታ እንዲኖር ተደርጎ ይከፋፈላል፡፡ ከቤቱ ጋር ተያይዞ ከከብት ቤት/ጊበዶ/የጥዶች ጓሮ/ንቆጥር/ይሠራል፡፡ ህድሞውም የሚሰራው ሰው የተሻለ አቅም ካለው ቤቱ እረጅም እድሜ እንዲኖረውና በቀላሉ ለእሳት

[26] ደቦ/ወበራ/ ማለት ቤቱን ለመስራት የሚያግዙት ሰዎችን እንዲረዱት መንገር ማለት ነው፡፡ ይህ በባህሉ የተለመደ የመረዳዳት ባህል ነው፡፡ የሰፈሩ ሰውም ለመሳሪያነት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን፣እንጨት ፣ ድንጋይ ፣ማገር ወዘተ እየያዙ ነው የሚመጡት፡፡ ባዶ እጃቸውን ይዘው አይመጡም፡፡

አደጋ እንዳይጋለጥ ሲፈልግ የተገለፀው የቤቱ አሠራር እንዳለ ሆኖ ጣሪያውን በቆርቆሮ ይከደናል (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቃመ. 10/09/2009 ዓ.ም)፡፡ እንደ መረጃ ሰጪው አቶ ደርበው ታረቀኝ አገላለፅና እኔም እንደተመለከትኩት የህድሞ ቤቶች የአሰራር ጥበባቸው ጎልቶ የሚታየው ከውጭ ይልቅ በውስጥ ገፅታቸው ነው፡፡ ውስጡን በእበትና በጭቃ ይለቀልቁታል፡፡

የአካባቢው አፈር እንደ ሙጫ አጣብቆ የሚይዝ በመሆኑም ህድሞ ቤቶች እስከ ሁለት መቶ ዓመታት ድረስ ማገልገል የሚችሉ እንደሆኑ ከዞኑ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተገኘው ማስረጃ ያስረግጣል፡፡ ባህላዊ ቤቱ የብሄረሰቡ አባላት ለብዙ ዘመናት ለመኖሪያነት ሲጠቀሙበት የኖሩበት መሆኑን ቁልፍ የመረጃ ሰጪዎቹ እና ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው የብሔረሰቡ ልዩ ልዩ ግለሰቦች ገልፀውልኛል፡፡ አሁንም በመኖሪያነት በማገልገል ላይ እንደሚገኝ ተመልክቻለሁ፡፡

የብሔረሰቡ ባህላዊ ቤት/ህድሞ/ አሁንም በስፋት አገልግሎት ላይ እየዋለ ቢሆንም ጣሪያቸው በቆርቆሮ የተሸፈኑ ዘመናዊ ቤቶች ባህላዊውን የቤት አሠራር በመተካት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህም የባህላዊው ቤት/ህድሞ/ አሰራሩና ዕውቀቱ እንዳይጠፉ ያሰጋል ሲሉ ስጋታቸውን ገልፀዋል (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቃመ. 10/09/2010 ዓ.ም ፣ ወ/ሮ ወርቅአፈራሁ ቸኮል ፣ ቃመ. 25/02/2010 ዓ.ም ፣ አቶ አሥራት ፣ ቃመ. 01/06/2011 ዓ.ም)፡፡

ሶስተኛው የቤት አሠራር ዓይነት ደግሞ ባለአንድ ወለል ቆርቆሮ ክዳን ቤት ነው፡፡ ይህ ቤት ጓዳም ሊኖረው ይችላል፡፡ አዳራሽም እንደ ህድሞ ሁሉ ክብ ሲሆን በውስጡም በርካታ ክፍሎች ማለትም ጓዳ ፣ የእቃ ቤት ፣ የእንግዳ መቀበያ እና ምኝታ ክፍል ያለው ነው፡፡ ጎጆ ቤት በአብዛኛው አንድ ክፍል ብቻ ያላት ትንሽ ቤት ስትሆን ክዳኗም ሣር ነው፡፡ ይህች የቤት ዓይነት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች ቤት ናት፡፡ ህድሞና ደብር የሀብታሞች ፣ ባለ አንድ ወለል የቆርቆሮ ክዳን እና አዳራሽ ደግሞ መካከለኛ ኑሮ የሚኖሩ ሰዎች ቤት ነው፡፡ ስለዚህ አብዛኛውን ጊዜ ቤቶቹን በመመልከት የባለቤቶቹን የሀብት ደረጃ ለማወቅ ይቻላል በማለት መረጃ ሰጪዎቹ ገልፀውልኛል፡፡ ቀደም ሲል በገጠሩ አብዛኞቹ የቤት ዓይነቶች ክዳናቸው ሳር የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ለክዳን የሚሆን ሰንበሌጥ እየቸገረ በመምጣቱ ምክንያትና የአርሶ አደሩ አቅም ከፍ እያለ በመሄዱ የሳር ክዳን የነበራቸው ቤቶች በቆርቆሮ ክዳን እየተቀየሩ ነው፡፡ በመሆኑም

በገጠር ቀበሌዎች በርካታ የቆርቆሮ ክዳን ያላቸው ቤቶች ይገኛሉ። ለአብነት ከሰቆጣ ዙሪያ ወረዳ የቀበሌ መንደሮች መካከል የስሬን መንደርን መጥቀስ ይቻላል።



ምስል 13:- የስሬን ቀበሌ ከፊል ገፅታ (ፎቶ በእኔ)

ዞኑ ደን የተራቆተበት አካባቢ በመሆኑ በአካባቢው የሚሠሩ ቤቶች ግርግዳቸው እንጨት የሆነ ጥቂት ቢኖሩም በብዛት ግርግዳቸው የሚሠራው ከድንጋይ ግንብ /ናስ/ ነው።



ምስል 14፡- የድንጋይ ግንብ (ናስ ቤት)

የቤቶቹ የግቢ አጥር የሚሰራውም በግንብ ፣ አልፎ አልፎም በካብ ሲሆን ከእንጨትና ከቅጠል በተለይም ጥድና ደደሆ ያላቸው ቤቶችም አልፎ አልፎ ይገኛሉ፡፡ የቦታ ጥበት ያለባቸው ሰዎች ቤቶች ደግሞ ያለ አጥር ይገኛሉ፡፡

## 4.2 ሀገረ ሰባዊ ልማዶች

በአንድ ማህበረሰብ ባህል ውስጥ በጋራ ከሚታመንባቸው እና በኅብረት ከሚከወኑ የዕለት ተዕለት ተግባራት ውስጥ ወቅትን ጠብቀው የሚከበሩ ባህላዊ ክብረ በዓላት ፣ ባህላዊ መዝናኛዎችና ውድድሮች ፣ ባህላዊ መድሃኒቶች እና ልዩ ልዩ አምልኮዎች የማህበረሰቡ መገለጫዎች ናቸው፡፡ የዋግኽምራ ብሔረሰብ የራሱ መለያ የሆኑ እነዚህን መሰል ሀገረሰባዊ ልማዶች አሉት፡፡

### 4.2.1. ደቦ /ወበራ/

የዋግኽምራ ብሔረሰብ ተለይቶ ከሚታወቅበት አንዱ ተደጋግፎ በሕብረት የመስራት ባህሉ ነው፡፡ በብሔረሰቡ የጋራ ስራው/ደቦው/ የተለያየ ስያሜ ያለው ሲሆን የብዙ ሰዎችን እገዛ የሚጠይቀው ሰፊ የሕብረት ስራ ዘመቻው በብሔረሰቡ አጠራር “ወበራ” የሚባለው ሲሆን አጨዳ ከሆነ የአጨዳ ወበራ ፣ እርሻ ማረስ ከሆነ የእርሻ ወበራ ፣ አረም ከሆነ የአረም ወበራ በሚል ስያሜ ስራው በሕብረት የሚከናወን ነው፡፡ ለዚሁ የሕብረት ስራ ሲወጣ ለአጨዳ ወበራ ጊዜ ማጭድ ፣ ለእርሻ ወበራ ጊዜ ያለው ጥንድ በሮቹን ፣ የሌለው ቀንጃ በሬም ቢሆን ከነሞፈርና ቀንበሩ ይዞ በመውጣት የሚያግዝ ሲሆን ለዚህ የሚፈለገውን የሰው ገልበት ብቻ ሳይሆን ፣ እገዛውም ዛሬ እንደኛው ለሌላኛው ከሰራለት ሌላኛው ደግሞ ብድሩን በሌላ ቀን የሚመልስበት አሰራር ነው፡፡ ሶስተኛው ደግሞ “መቀናጆ” የሚሉት ሲሆን እገዛውም አንዱ ገበሬ አንድ በሬ ቢኖረው ከሌላው ጋር አቀናጅቶ በጋራ በመስራት የሚያከናውኑት ነው፡፡

በዚህ የጋራ ስራ ወንዶቹም ሆኑ ሴቶቹ የሚሳተፉበት ሲሆን የሴቶቹ ተሣትፎ ከማረሻ የዘለለውን በመንቀል አራሹን ተከትሎ በመጎልጎልና ሳሩን ከአፈሩ በመለየት ከእርሻው ውጭ በመጣል ነው፡፡ ስለዚህ ስራው የሚሰራለት አካል መብልና መጠጥ ያዘጋጃል (ቡ.ተ.ው ፣ 4)፡፡

በስራ የመተጋገዝ ባህል የብሔረሰቡ ዋነኛ መገለጫ ነው፡፡ የብሔረሰቡ አባላትም በሕብረት በመስራታቸው ግንኙነታቸውን ያጠናክሩበታል፡፡ የብሔረሰቡ አባላት ለደቦ ወይም ወበራ ሲጠሩ እንደ ሁኔታው ማጭድ ፣ በሬ ፣ ሞፈርና ቀንበር እንዲሁም በስራ ላይ ለተሰማሩ አባላት መብልና መጠጥ ያቀርባሉ፡፡

ለጋራ ስራው/ወበራ/ በሚወጡበት ወቅት የተለያዩ የስራ ቃል ግጥሞችን እየተቀባበሉ በማዜም ስራውን የሚያስኬዱበት በእርሻ ወቅት ማረሻና ድግሩን በመያዝ ጅራፍ እያጮሁ የሚያርሱበት ፣ ሴቶቹም አራሹን እየተከተሉና እየጎለጎሉ ሳሩን ከእርሻው ላይ በመልቀም ከእርሻ ውጪ በመጣል አፈሩን ንፁህ የሚያደርጉበት እገዛ ሰፊ አካላዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡

## 4.2.2. በቁም የመረዳዳት ባህል/እርጥባን

የዋግኽምራ ብሔረሰብ በሀዘን/ችግር/ ጊዜ ከመረዳዳት ባለፈ በቁም የመረዳዳት የቆየ ባህል አላቸው፡፡ በብሔረሰቡ አንድ ሰው ችግር ሲደርስበት ለችግሩ መድረስ እንደ ትልቅ ጉዳያቸው የሚወስዱት እሴታቸው ነው፡፡ በዚህ ስርዓት የጾታና የእድሜ ገደብ የለውም፡፡ ባህላዊ ስርዓቱ የሚጋብዘው ሁሉ ይሳተፋል፡፡ የብሔረሰቡ የሰብዓዊነት አስተሳሰብ “ለሰው መድሃኒቱ ሰው ነው” በሚለው ሕዝባዊ ፍልስፍና ይገለጣል፡፡ ይህ በሰው ልጅ ላይ የመተማመን መንፈስ የዋግኽምራ ብሔረሰብ ማህበራዊነት መሠረት እንዲሁም በግለሰቦች መካከል ያለው ጥብቅ ቁርኝትና ትስስር ሚዛን ጠብቆና ጸንቶ እንዲቆይ ምሰሶ ሆኖ ያቆመው ጉዳይ ነው፡፡ ከፍ ብለን እንደተመለከትነው ለሃዘንም ፣ ለደስታም ፣ ለተስካርም ሰዎች ተደጋግፈው ይቆማሉ፡፡ ድግግፉን መልክና ስርዓት ለማስያዝ ፣ ዘላቂና ሁሉንም በእኩልነት የሚያስተናግድ ይሆን ዘንድም ደንብ አበጅቶ ፣ ልክ ወስኖ ያቋቁማል፡፡ ባህላዊ ስርዓቱ ‹‹ከሞተ ወዲያ ምን ያደርጋል መረዳዳት በቁም ነው እንጂ›› የሚሉት አባባል አላቸው፡፡ ይህንን አስመልክተው አቶ ደርበው ታረቀኝ እንዲህ ይገልጹታል፡፡

> በብሔረሰቡ በቁም የመረዳዳት ባህሉ የሚከናወነው በህመም ጊዜ ፣ የእርሻ በሬው ለሞተበት ሰው ፣ ስራው እንዳይስተጓጎል በሚል አነስተኛ ኑሮ ያላቸውና የተቸገሩ ሰዎች ካሉ ፣ ቤት ሲቃጠል ፣ ንብረት ሲዘረፍ ፣ ወዘተ. ሲሆን ሂደቱም ወዲያውኑ ችግር የደረሰበትን አካል “ችግሩ ችግራችን ነው” በማለት

የማስተባበር ስራ ይሰራል፡፡ የማስተባበር ስራው እርጥባን/ምርቃት/ይባላል፡፡ እርጥባን የገንዘብ ስጦታ ማለት ሲሆን ፣ የሚያስተባብረው የቅርብ ወዳጅ አሊያም ችግር የደረሰበት ግለሰቡ ሊሆን ይችላል፡፡ ችግር የገጠመው ሰው እርጥባን አድርጉልኝ ብሎ ጥሪ ያስተላልፋል፡፡ ለእርጥባን ማሰባሰቢያውም ከለላ የምትሆን "ዳስ" ይጥላል፡፡ የተወሰነ መብልና መጠጥም በተለይም ንፍሮና ጠላ/ኮረፌ ያዘጋጃል፡፡ በህመም ላይ ያለን ሰው ደግሞ ጊዜ ሳይወስዱ ወደ ህክምና ሄዶ የሚታከምነትን በማመቻቸት ፣ በሬ የሞተበትን በሬ ገዝቶ እንዲያርስ ፣ ቤቱ የተቃጠለበትን እሳቱን ከደረሱበት የቻሉትን ያህል ለማጥፋት በመሞከርና በመረባረብ ፣ ይህ ካልሆነ ሙሉ በሙሉ ከወደመ ጊዜ ሳይሰጡ እርዳታውን የማሰባሰብ ስርዓቱ ይከናወናል፡፡ የመጀመሪያው እርዳታ መጠለያውን በጋራ በመስራት ይሆናል፡፡ እንጨት ያለው እንጨቱን ፣ የሳር ቤትም ከሆነ ሳር በማምጣት ይሰሩለታል፡፡ ወዲያውም ጊዜ ሳይሰጠው የ"እርጥባን" ስነ-ስርዓት ይከናወናል፡፡ እርጥባን የተሰበሰበለት ተጎጂም የወገኑን እርዳታ ከንቱ ላለማድረግ የጎደለበትን በመተካት ይፅናናል (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቁ.መ.አ. 15/10/2010 ዓ.ም)፡፡

ለሰርግና ለተስካር ሲሆን ደግሞ የቅርብ ዘመድ ፣ ቤተሰብና ወዳጅ የሆኑ ሁሉ መጠጡን ፣ ምግቡን ፣ እርዱን ፣ ገንዘቡንና ሌሎችንም መጪዎች በመከፋፈል ያለምንም ችግር እርዲያልፍ ያደርጉታል በማለት መረጃ አቀባዮቼ ገልጸውልኛል (ቡ.ተ.ው ፣ ቁ.4)፡፡

ከላይ ከተገለጸው የመረዳዳት ስርዓት የምንረዳው በብሔረሰቡ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣው ተባብሮና ተጋግዞ የመስራት ባህል በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ያሉ ሰዎችን ከማፅናናት በዘለለ መልኩ አገር ጥሎ ከመሰደድ ፣ቤተሰብም ከመበተን ያድናል፡፡ የእርስ በርስ ግንኙነትና ትስስርንም ያጠናክራል፡፡

### 4.2.3 የጋብቻ ጥያቄ እና የማጨት ሂደት

በዋግኽምራ ብሄረሰብ የተለያዩ ሰነ-ስርዓቶች አሉ፡፡ በብሔረሰቡ በተለይም በገጠሩ ባህላዊና ሀይማኖታዊ የጋብቻ ዓይነቶች ብቻ ይፈፀማሉ፡፡ በብዛት የሚከናወነዉ ባህላዊ የጋብቻ ዓይነት ሲሆን በሃማኖታዊ የጋብቻ ዓይነት ጋብቻቸዉን የሚፈፅሙት ግን የተወሰኑ ተጋቢዎች ሲሆኑ አብዛኞቹ ወንዶች የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ናቸዉ (ቄስ

ደምሴ መኮንን ፤ ቃመ.26/06/2011 ዓ.ም)፡፡ ምልከታ ካሄድኩባቸዉ ሦስት የዞኑ ወረዳዎች[27] ዉስጥ አስራ ሁለት የሰርግ ስነ-ስርዓቶች መካከል ሃይማኖታዊ ጋብቻ የገጠመኝ አራት ብቻ ናቸዉ፡፡ ስምንቱ በባህላዊ የጋብቻ ዓይነት የተፈፀሙ ናቸዉ፡፡ በዚህ የጋብቻ ዓይነት ስር ልዩ ልዩ የጋብቻ ዓይነቶችም አሉ፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸዉ፡፡ የመጀመሪያዉ የጋብቻ ዓይነት የሁለቱም ተጋቢዎች ሰርግ በአንድ ቀን ተደርጎ የጋብቻ ፍጥጥማቸዉ/ዉላቸዉ /በጎጆ ወይም በሲሶ ተብሎ በዚያዉ በሰርጉ እለት በዳስ ዉስጥ የሚፈፀም ነዉ፡፡ በጎጆ ማለት ሙሽራዉ ፤ ሙሽራዋን ወደ ቤተሰቦቹ ቤት ከወሰደ በኋላ ከመልስ እንደተመለሱ የግላቸዉ ወደ ሆነ ቤት በመግባት ራሳቸዉን ችለዉ ጎጆ የሚወጡበት ነዉ፡፡ በሲሶ ማለት ደግሞ ቤት ኖሯቸዉ ጎጆ የሚወጡበት ሳይሆን ከሙሽራዉ ቤተሰቦች ጋር አብረዉ እየሰሩ ከርመዉ በሚቀጥለዉ/በሚቀጥሉት አመት/ዓመታት ፤ ከተገኘዉ ምርት አንድ ሶስተኛዉን በመካፈል ጎጆ የሚወጡበት ነዉ፡፡ በአንዳንድ የደጋዉ አካባቢ ይህ የጋብቻ አፈጻጸም በአፈረ-ፈጪ ወይም በኩራሚ በመባል ይታወቃል (አባ አሸብር አለሜ ቃመ. 26/06/2011 ዓ.ም)፡፡ የስያሜዉ ምክንያት ሙሽራዎቹ በተዳሩበት ራሳቸዉን ችለዉ ጎጆ አለመዉጣታቸዉ ወይም የእርሻ ስራ እየሰሩ መክረማቸዉ ነዉ ሲሉ መረጃ ሰጪዎች አብራርተዋል (አባ አሸብር አለሜ ቃመ. 26/06/2011 ዓ.ም)፡፡ ሁለተኛዉ የጋብቻ አይነት ደግሞ የምስል ጋብቻ ፤ አግብተሽ/ህ ክረሚ/ክረም (በኽምጣኝ ድዉር ጫር )የሚባለዉ ነዉ፡፡ ይህ የጋብቻ ዓይነት ከሁለቱ ተጋቢዎች መካካል በአንዱ/በአንዷ የሰርግ ዳስ ላይ በጎጆ ወይም በሲሶ ተብሎ ዉሉ የሚፈጸምበት ነዉ፡፡ የምስል ጋብቻ የሚፈጸመዉ አዝመራ ሲያንስ የልጁን ወዝና ባህሪ እንድትለምድና እንደቤተሰብ ሆና አብራ እንድታድግ ታስቦ የሚደረግ ነዉ፡፡

ቤተሰቦች ለመደገስ የሚያስችል ምርት በሚያገኙበት ዓመት ይደገስላታል/ይደገስለታል፡፡ ይህም ከአንድ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ሊቆይ ስለሚችል ሴቷ ሁለት ከወለደች በኋላም ሊከናወን የሚችል መሆኑን ነዉ ከገጠመኛቸዉ በመነሳት መረጃ አቀባቹ የገለጹልኝ፡፡ ከረጅም ጊዜ በኋላ ሰርግ መደገስ ያስፈለገዉም ሴቷን ሌሎች ሴቶች “ጥፍርሽን ያልተቆረጥሽ” ብለዉ በየወንዙ እንዳይሰድቧት ወንዱንም ‹‹ሰርግህን

[27] ደሃና ወረዳ ፤ስቆጣ ዙሪያ እና ዛግብላ ወረዳ ከተመልከትኳቸዉ አስራ ሁለት የሰርግ ስርዓቶች አራት ብቻ ናቻዉ በሃይማኖታዊ ጋብቻ የሚፈጸሙት፡፡

አልበላንም›› ብለዉ እንዳይሰድቡት ነዉ (ወ/ሮ ወርቂ ቸኮለ ፤ *ቃመ*. 26/06/2011 ዓ.ም ፤ አባ አሽብር አለሜ *ቃመ*. 26/06/2011 ዓ.ም ፤ መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ፤ *ቃመ*. 26/06/2011 ዓ.ም)፡፡ ለአብነት ያህል በ 20/05/2010 ዓ.ም ምልከታ ባደረኩበት የጋብቻ ስርዓት ላይ በሙሽራዉ በበላይ ዝናቡ[28]ምንም ዓይነት ድግስ አልነበረም፡፡[29] የሰርግ ድግስ ሳይኖር ልጃቸዉ ጋብቻዉን ለምን እንደፈጸመ አባቱ አቶ ዝናቡ ጣምተዉ ሲገልጹ፡-

> ልጅቱም ለአቅመ ሔዋን ፤ እሱም ለአቅመ አዳም ስለደረሱና ልጁ በዚህ አመት ሲሶዉን ስጠኝ ራሴን መቻል አለብኝ ብሎ ሲሶዉን ስለወሰደ ነዉ፡፡ እኔ ግን ዘንድሮ ለመደገስ አቅም ስለሌለኝ ከእኔ ቤት ድግስ የለም፡፡ በሚስቱ ቤት ግን አለ፡፡ ዉሉም/ሰማንያዉም ዛሬ በሴቷ ሠርግ ዳስ ላይ ይፈጸማል፡፡ የሱ ሰርግ የሚሆነዉ ግን በሚቀጥለዉ ዓመት ከታላቅ ወንድሙ ተስፋዉ ጋር ነዉ ብለዋል (አቶ ዝናቡ ጠምተዉ ፤ *ቃመ*. 2/05/2010 ዓ.ም)፡፡

ተስፋዉ ፤ ጋብቻዉን የፈጸመዉ ከሁለት ዓመት በፊት በ 2008 ዓ.ም ነዉ፡፡ ለሚስቱ የሰርግ ድግስ ተደግሶላት ለሱ ግን ሳይደገስ ሰማንያዉ በሲሶ ተብሎ በ 2007 ዓ.ም ባልና ሚስት ከወንድ ቤተሰብ ጋር አብረዉ ሲሰሩ ከከረሙ በኋላ ሲሶዋቸዉን ወስደዋል፡፡ ከወላጆቹ አጠገብም አስራሽ ሰርተዋል ፤ ጎጆ ወጥተዉ ለብቻቸዉ እየኖሩ ነው፡፡ ሚስቱን ወደ ቤተሰቦቹ ቤት ካመጣና ጎጆ ከወጣ ሶስት ዓመት ቢሆነዉም የእሱ ሰርግ ግን ገና በ2010 ዓ.ም ነዉ የሚሆነዉ፡፡ ስለዚህ የሁለቱ ወንድማማቾች የጋብቻ ዓይነት በአግብታችሁ ክረሙ /ድዉርጫር/የጠፈፀመ ነዉ፡፡

በዋግኽምራ የሰርግ ሥነ-ሥርዓት ከመፈፀሙ አስቀድሞ በርካታ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ይኼዉም ወደፊት በተጋቢዎቹ መካካል ያለዉን የዝምድና ርቀት ማጣራት ፤ የእጮኝነት ሂደትና አፈጻጸም ፤ የሰርግ ቀን አወሳሰን/አቀራረጥ እና ሰርግ ድግስ ዝግጅት ናቸዉ፡፡ እነዚህን በቅደም ተከተል እንመለከታለን፡፡

---

[28] በላይ ዝናቡ ለወላጆቹ አምስተኛ ልጅ ነዉ ሲሆን ለመዳር ደግሞ ሦስተኛ ነዉ፡፡እድሜዉ 21 ስራዉም ግብርና ነዉ፡፡

[29] ሰርግ አለ ተብየ ብዙ ተጉገ፤አቦታዉ ስደርስ ምንም አልነበረም፡፡እቤት ስገባም በትንሽ እንስራ ኮረፋ ተጠምቆና በአንዲት ድስት የክክ ወጥ ተሰርቶ ነበር፡፡ይህም ከሙሽራው ጋር ወደ ሴቷ ቤት የሚዘምቱት ሽማግሌዎች እንዲቀምሱ የተዘጋጀ መሆኑን ነው የሙሽራው እናት የተለፁልኝ፡፡

የጋብቻ ሁኔታ ከቦታ ቦታ ፤ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ የተለያ ቢሆንም አንደ አብዛኛዉ የኢትዮጵያ የገጠሪቱ ክፍል ማህበረሰብ ሁሉ በዋግኽምራም ፤ የወደፊት የትዳር ጓደኛ ምርጫ የሚከናወነዉ በወደፊት ተጋቢዎች ሳይሆን በወላጆዎች አማካኝይነት ነዉ፡፡ በመሆኑም የዝምድና ማጣራት ሥራ የሚያከናዉነዉ በወላጅ ነዉ፡፡ አንዳንድ የወደፊት ተጋቢዎች በግል ትዉዉቅና ምርጫ ወደ ጋብቻ ሊያመሩ ቢፈልጉ እንኳ ፤ የተጋቢዎቹ ተገቢነት ወይም ትክክለኛነት ምርጫ በቤተሰብ በኩል ስምምነት እዲያገኝ ይደረጋለል፡፡ የማን ልጅ ነዉ/ናት የሚለዉን የማጣራት ሥራ ይከናወናል፡፡ ከሚጣሩት ሁኔታዎች መካካል አንዱ ደግሞ በተጋቢዎቹ መካካል ዝምድና መኖር አለመኖሩን ነዉ፡፡ አንዲትን ሴት ልጅ ለአንድ ወንድ ልጅ ለማጋባት የማጨት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ የዝምድና ርቀቱ ተጠንቶ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ከመረጃ አቀባዮቹ እንደተገኘዉ መረጃ ከሆነ ቀደም ሲል በዋግኽምራ ለጋብቻ የስጋ ዝምድና ርቀት የሚቆጠረዉ እስከ አስራ ሁለት ቤት ነበር፡፡

ከቅርብ ጊዜ ደግሞ ተቀባይነት አግኝቶ ሲሰራበት የነበረዉ እስከ ሰባት ቤት ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን የዝምድና ረቀቱ ወደ ሶስት እና አራት ቤት ወርዷል (አቶ ደርባዉ ታረቀኝ ፤ 22/04/2010 ዓ.ም ፤ ወረቃፈራሁ ቸኮል ፤ 26/06/2010 ዓ.ም)፡፡ ለዚህ የመጀመሪያዉ ምክንያት ተጋቢዎቹ ቤተሰብ እንዲጠየቅ ሳያደርጉ እርስ በርስ ተጠያይቀዉ በመጋባታቸዉ ነዉ፡፡ ማህበረሰቡ ግን እነዚህን ተጋቢዎች እያገለላቸዉ ነዉ፡፡ ይህንንም አቶ ብረሃነ መስቀል ይርጋ የተባሉ የስቆጣ ዙሪያ ወረዳ ነዋሪና የሰማንያ ዓመት ዓዛዉንት አርሶ አደር እንደሚከተለዉ ገልፀዋል፡፡ "እኛም ከነዚህ ዘመድ ጋር ተጋቢዎች ጋር በሃዘኑና በደስታዉ እንዳንገናኝ መስቀል መተን እየተማማልን ነዉ፡፡ በህግ ግን የፈለጉትን ያግቡ አየተባለ ነዉ፡፡ እኛ ግን እስከምንሞት ድረስ የአባቶቻችንን አደራ መወጣት አለብን እያልን ነዉ" (ቁ.የ.መ.አ)፡፡ ለጋብቻ የዝምድና ርቀት ወደ ታች መዉረድ ሌላዉ በምክንያትነት የሚገለፀዉ የተጋቢዎች አለመተዋወቅ ነዉ፡፡ ይህም ቀደም ሲል የስጋ ዝምድና ያላቸዉ የቤተሰብ አባላት ቁጥራቸዉ የተወሰነ ስለነበር ሁሉም በየድግሱ እየተጠራሩ ይገባበዙ ስለነበር እርስ በርስ ይተዋወቁ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን የእያንዳንዱ ቤተሰብ አባላት ቁጥር እየጨመረ ስለሄደ ፤ ለመተዋወቂያነት በሚያገለግለዉ ድግስ ላይ የሚሳተፉት ሰዎች የተወሰኑት ናቸዉ፡፡ በዚህም የተነሳ ባለመተዋወቅ ምክንያት የቅርብ የስጋ ዝምድና ባላቸዉ ሰዎች መካካል ጋብቻ

እየተፈፀመ ነዉ፡፡ ይህም አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱን ነዉ አቶ ተቀባ አሸብር የተባሉት የመረጃ አቀባዬ የገለጹልኝ፡፡ ለማሳያነት የገለጹትም በራሳቸዉ ቤተሰብ ዉስጥ በሶስት ቤት የዝምድና ርቀት መካከል የተካሄደዉን ጋብቻ ነዉ፡፡ ስለዚህ ዘመድ ከዘመድ ጋር የመጋባትን ችግር ለመቅረፍ እንዲቻል የቤተሰብ መሰባሰቢያ ማህበር መመስረት/መቆርቆር አስፈላጊ ነዉ ይላሉ፡፡ ይህም የቤተዘመዱ ዋና ዋና ወይም የመጀመሪያ ተጠሪዎች እየተገናኙ ማን ማንን ማግባትና አለማግባት እንዳለባት የመመካከር ስራ ለመስራት ያስችላል፡፡ የስጋ ዝምድና ያላቸዉንና የማይተዋወቁትን ሰዎችንም ያስተዋዉቃል ፤ ያቀራርባል ይላሉ (አቶ ተቀባ አሸብር ፤ ቃመ. 22/02/2010 ዓ.ም)፡፡ በዋግኽምራ ጋብቻ የማይፈፀመዉ የስጋ ዝምድና ባላቸዉ ሰዎች መካካል ብቻ ሳይሆን በክርስት አባትና እናትና በንሰሃ ልጅ ቤተሰቦችም መካካል ነዉ፡፡ የክርስትና አባትና እናት እንደ ወላጅ አባትና እናት ይቆጠራሉ፡፡ ይህንንም በብሄረሰቡ ምሳሌያዊ አባባሎች ‹‹ሴት ከወለዱት ቀን የወለዱት ይበልጣል›› በሚለዉ የዝምድናዉን ጥልቀትና ጥንካሬ የሚያስረዱት፡፡ በሁለት ቤተሰቦች መካከል ዝምድና ባይኖርም በክርስትና ልጅነትና አባትነት ወይም እህትነት ምክንያት ጠንካራ የመንፈስ ዝምድና ያለ መሆኑን ያጠናክራሉ፡፡ በዘመድ መካካል ደግሞ ጋብቻ አይፈፀምም፡፡ በንሰሃ/የነፍስ/አባትና ልጅም ጋብቻ አይፈፀምም፡፡ ስለዚህ አንዲትን ሴት ለማጨት የዝምድናን ርቀት የማጣራት ስራ የሚከናወነዉ የስጋ ዝምድናን ብቻ ሳይሆን በወደፊት ተጋቢዎቹ መካካል የንሰሃ አባት እና የክርስትና አባትነትና እናትነት መኖር አለመኖሩንም ጭምር ነዉ፡፡ ይህ በሚገባ ከተጣራና ከተረጋገጠ ቡኃላ ወደ ማጨት ስርዓቱ ይገባል፡፡ የማጨትን ሥርዓት ሂደትና በስርዓቱ የሴቶች/የእናቶች ተሳትፎ በሚል እነደሚከተለዉ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀዉ በወግኽምራ የመተጫጨት ሂደት የሚከናወነዉ በወላጆች አማካኝነት ነዉ፡፡ በዚህ ባህላዊ የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት መሰረት ሴት እጮኛን ፍለጋ ግንበር ቀደም እንቅስቃሴ የሚያደርጉት የወንዱ ልጅ ቤተሰቦች ናቸዉ (አያሌዉ ፤ 2009 ፤ 19)፡፡ ስለዚህ የወንዱ ቤተሰብ የስጋ ዝምድና ወደ ተጠቆመች ፤ ለጋብቻ ወደ ተመረጠችዉና ወይም ተፈላጊዉ ሴት ቤተሰብ ሽማግሌዎችን በመላክ ፍቃደኝነታቸዉን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ አንድ አባት ለልጁ ሚስት ልትሆን የምትችለዉን ልጅ ፍለጋና ጥቆማ የሚያከናዉነዉ የወደፊት ተጋቢዎች ሳይወለዱ (ሳይጸነሱ) ቃል በመግባባትና ከተወለዱ በኂላም ለአቅመ ሄዋን ሳይደርሱ በህፃንነታቸዉ ነዉ፡፡ ቃል መግባት(በኽምጥኛ ቃልጥዉ ነዉ)ይባላል፡፡ ይህም የወደፊት ተጋቢዎች ወላጆች ሀብታም ወይም ጓደኛሞች ከሆኑ ፤

ልጅቷ ገና ሳትወለድ ወይም ሳትፀነስ "አንተ ወንድ ከወለድክ ፥ እኔም ሴት ከወለድኩ ልጄን ለልጅህ ፥ ወይም የአንዱ ሚስት ነፍሰጡር ከሆነች ወንድ ልጅ ያለዉ ጓደኛ ሚስትህ ሴት ከወለደች ለልጄ ትሰጠኛለህ" ይባባሉና ቃል ይገባባሉ፡፡ ቃል የተገባቡት ወላጆች ቢሞቱም እንኳ ይህ ቃል በሚስታቸዉ አማካኝነት ተከብሮና ተጠብቆ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ባሁኑ ጊዜ ቃል ገብቶ ልጆችን ማሳጨት እየቀነሰ ቢሆንም ከመረጃ አቀባዮቼ ያገኘሁት መረጃ የሚያመላክተው ግን ሙሉ በሙሉ እንዳልቀረ ነው (ቡ.ተ.ው.1)፡፡

ሁለተኛው የሚስት መፈለጊያ መንገድ ደግሞ ወንድ ልጅ ያለው አባት ለልጁ የምትሆነውን ሴት በመፈለግና በመጠቆም የሚከናወን ነው፡፡ ፍለጋውና ጥቆማውም የሚከናወነው በቤተሰብ አማካይነት ነው፡፡ የወንድ ወላጅ አንድ ዘመድ በሚኖርበት አካባቢና በሌላ አካባቢ በጠቋሚዎች አማካይነት ያጠያይቃል፡፡ ጠቋሚውም ልጅቷ ለሌላ አለመታጨቷንና የወላጆቿን የዘር ሐረግ ፣ ሀብት ፣ ወዘተ ያጠናል፡፡ ስለ እሷና ስለቤተሰቦቿ ሁኔታ በስለላ ያገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግም የትዳር ጓደኛ ለሚፈልጋት ልጅ ሚስት ልትሆን እንደምትችል ያመነባትን ልጅ "ያልታጨች የእከሌ ልጅ አለች" ብሎ ለወንድ ቤተሰብ ይጠቁማል፡፡ የወንድ ቤተሰብም ቃል የተገባለትም ሆነ የተጠቆመችውን ሴት ለማግኘት የቤተሰቦቿን ፈቃደኝነት የማረጋገጥ ሥራውን ይቀጥላል፡፡ በመሆኑም ሽማግሌዎችን በመላክ የጋብቻ ፍላጎት ጥያቄውን ያቀርባል፡፡ እጮኛ የመለመኑን ሂደት በቀጣይነት የሚጀምርና ክትትሉን በኃላፊነት የሚወስድ አማጭ/ወኪል/ሽማግሌዎች ይመረጣሉ፡፡ በሽማግሌነት /በአማጭነት የሚመረጡትም ሰዎች የሴቷን ልጅ ወላጆች ይሁንታና ተቀባይነት የሚያገኙ ታዋቂና የማሳመን ብቃት ያላቸው በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ታዋቂነት ያላቸው ፣ የሚከበሩ ፣ የሚፈሩ ተብለው የሚታመንባቸው ናቸው፡፡ ይህም የሚሆነው አስቀድሞ ቃል ለተገባለት ወዲያው እንደተወለደች ሲሆን ፣ በጥቆማ ለታወቀችው ደግሞ በሽማግሌነት የሚሄዱት ሰዎች ተመካክረው አመቺ ግዜ በማመቻቸት ነው፡፡ የሽምግልና ወራቱና ቀናቱም አብዛኛውን ጊዜ አርሶ አደሩ በብዛት በእርሻ ሥራ በማይጣደፍባቸው ወራት ሲሆኑ ቀናቱ ደግሞ ፣ ሰኞ ፣ ማክሰኞና ሐሙስ ናቸው፡፡ የእነዚህ ቀናት መመረጥ ምክንያት ፣ ረቡዕ እና ዓርብ የፆም ቀናት ፣ ቅዳሜና እሁድ ደግሞ በዓላት በመሆናቸው ሽማግሌዎች ለጋብቻ ጥያቄ ወደ ሴቷ ቤት አይሄዱም (ቡ.ተ.ው.4)፡፡ የሽምግልና ሂደቱም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

በመጀመሪያ ሶስት አማጭ/በኽምጣኝ ዘርና/አንዱ የነፍስ አባት ወይም ቄስ መሆን አለበት ፣ የልጁ አባትና አንድ የቅርብ ዘመድ ሽማግሌዎች (በኽምጣኝ ሽመቅል) አማጭ ሆነው በጧት ተነስተው ወደ ሴቷ ቤተሰቦች ቤት ይሄዳል፡፡

ሽማግሌዎች ከሴቷ ቤተሰብ ቅጥር ግቢ እንደደረሱ "እዚህ ቤት" በማለት ድምፅ ያሰማሉ፡፡ የሴቷ ቤተሰቦችም ውሻ ያላቸው ከሆነ ውሻው ሲጮህ ከሌላቸውም የሽማግሜዎቹን ድምፅ በመስማት አባት (ሟች ከሆነም የእንጀራ አባት ፣ አሳዳጊ አጎት ፣ አያት ወይም ታላቅ ወንድም) ማነው በማለት ከቤት ወጥቶ ይጠይቃል፡፡ ‹‹ማነው›› ማለቱ የመጣው ሰው ማን እንደሆነ ያላወቀ ለመምሰል እንጂ ጠቋሚው ሽማግሌዎቹ ለጥየቃ የሚመጡበትን ቀን አስቀድሞ አሳውቀዋቸው ፣ ወደ ሌላ ቦታ ሳይንቀሳቀሱ ተዘጋጅተው በመጠበቅ ላይ ናቸው፡፡

ሽማግሌዎቹ በሴቷ ወላጆች ቤት ደጃፍ እንደደረሱ ልብሳቸውን መስቀልኛ አጣፍተው በመልበስ ሶስት ጊዜ ፣ "እንደምን አደራችሁ! እንደምን አደራችሁ! አንደምን አደራችሁ!" በኽምጣኝ "አውግሪሩ! አውግሪሩ! አውግሪሩ!" ይላሉ፡፡ የሴት አባትም "እግዚያብሄር ይመስገን" በኽምጣኝ "እምዜናና" በማለት የአጸፋ መልስ ይሰጧቸዋል፡፡ ሠላምታ እንደተለዋወጡም ፣ የሴቷ አባት ውጭ ላይ ምንጣፍ አንጥፎ ፣ ሽማግሌዎቹን "ተቀመጡ" ይላቸዋል ፣ ሽማግሌዎቹ ግን የጋብቻ ዝምድና መፈለጋቸውን ተናግረው ተጠያቂው እሽ እስካላላቸው ድረስ አይቀመጡም፡፡ እንዲያውም አደግድገው በመቆምና ትህትና በተላበሰ ቅላፄ እንዲህ ብለው ጥያቄ ያቀርባሉ ፤ ‹‹እኛ የመጣነው እናንተን ፈልገን ፣ ከእናንተ በረት ፣ ከእናንተ ፍግ ልንቀመጥ ፣ ልንወድቅ ብለን ነው ይላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ልጅቷ ያልታጨች ብትሆንም እንኳ አባት ወይም ተጠያቂው ባንድ ጊዜ "እሺ ሰጥቻለሁ" አይልም፡፡ የሚጠየቅለትን ልጅና የቤተሰቦቹን ሁኔታ ለመመርመር ፣ ለማጣራትና ለክብር ሲባል "ለሰው ሰጥተናል ፣ ተቀድማችኃል" በማለት መልስ ይሰጣል ፣ ሽማግሌዎቹም ከሴት ወገኖች ለመጀመሪያ ጥያቄያቸው ለሌላ ሰጥተናል የሚል መልስ ያገኙት በቀጥታ ሰጥተናችኃል ላለማለት መሆኑን ስለሚረዱ "የእናንተ ልጂ የሺህ ወገን እንደሆነች እናውቃለን ፣ ለሰው ከሰጣችሁም እኛንም እጣ ጣሉብን ፣ እኛንም ከእጣው አስገብታችሁ ቁጠሩን" በማለት የተማፅኖና የልመና ቃላቸውን አሰምተው ይመለሳሉ፡፡

በዚህ ጊዜ ደንብ ስለሆነ ፣ በውጭ አነጋግረው ፣ ደጅ ረግጠው ይመለሳሉ እንጂ ወደ ቤት አይገቡም፡፡ የመጀመሪያውም የሽማግሌዎቹ ጉዞም ደጅ መረገጫ/ቢዘ ደደነው/ይባላል፡፡

ሽማግሌዎቹ ለመጀመሪያ ጥያቄያቸው “ተቀድማችኃል” ቢባሉም አሉታዊ መልስ ተሰጥቶናል ብለው ተስፋ አይቆርጡም ፣ ባንድ ጉዞ በተካሄደ ጥያቄ ተስፋ ቆርጠው አያቆሙም፡፡ በድጋሚ የሴቷ ቤተሰቦችም መስጠት ቢፈልጉም በሁለተኛውም “እስቲ እንግዲህ መቼም ሀሳቡን ለቤተሰቦቻችን ነግረናልና ከእነሱ መልስ እንጠብቅ ፣ ተመካክረን እንቆያለን” ብለው አሁንም ለሶስተኛ ጊዜ በመቅጠር ሽማግሌዎቹን ይመልሷቸዋል፡፡ ይህም ለመጨረሻ ደጅ ጥናት ቀጠሮ የሚሰጥበት ነውና ቀን መቅጠሪያ/ግርዬቃድረነው/ይባላል፡፡ ልጅቷ ለሌላ ሰው ቃል ያልተገባላት ከሆነና ቤተሰቦቿ መስጠት ከፈለጉ እሺ ከማለታቸው በፊት በወንዱ ቤተሰብ ሁኔታ ላይ ጥናት ያካሂዳሉ፡፡ ጥናቱም ትኩረት የሚያደርገው የወንዱ ቤተሰብ ከእነሱ ጋር በሀብት አቻ መሆን አለመሆኑን ፣ የወንድ ቤተሰቦች ከሴቷ ቤተሰቦች ጋር ደም ያልተቃቡ መሆናቸውን/ባላንጋራ አለመሆናቸውን/በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል የቆየ ፀብ አለመኖሩን ፣ እከሌ በልቶኛልና[30]፣ እከሌ በድሎኛል እና በዘር ሀረጉ የማን ወገን እንደሆነ ይጣራል፡ ፡ ቀደም ሲል “የሸክላ ሰሪ ወይም የቀጥቃጭ ዘር ያልሆነና አጥንቱ የጠራ”[31] የሚለውም ይጣራ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ይህ መስፈርት ሙሉ በሙሉ ባይጠፋም የጎላ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በብሔረሰቡ ዘንድ ለተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍል ተለይቶ ይሰጥ የነበረው የእደ ጥበብ ስራ በአሁኑ ጊዜ ሌሎችም እየተሳተፉበት ነው፡፡ ለአብነት ያህል በሰቆጣ ወረዳ ስሬል በሚባለው ቦታ ይኖሩ የነበሩ በሸክላና በብረት ቅጥቀጣ ይተዳደሩ የነበሩት በአካባቢው አጠራር “ካይላ” ይባሉ የነበሩት የእደ ጥበብ ባለሙያዎች የሸክላና የቅጥቀጣ ስራውን በማከናወን ላይ እንደሚገኙ እና እነዚህ ማህበረሰቦች “ጨዋ” ይባሉ የነበሩ

---

[30] በልቶኛል ማለት ከዚህ በፊት በተለያዩ ጉዳዮች በክርክር የወሰደው ገንዘብ አለና ይመልስልኝ ማለት ነው፡፡ በባህሉ በአፋላማ፣በካሣ፣ወዘተ የተወደሰ ገንዘብ ለስሙ እንጂ አይበላም፡፡ ሳይመልስ ወስዶ ካስቀረው የተወሰደበት/ከፋይ/ሰው እንደጠላት ወሳጁን ይቆጥረዋል፡፡

[31] ከነዚህ ቤተሰቦች ጋር ዛሬም ድረስ በጋብቻ አይጠላለፉም፡፡እንደ ዝቅተኛ ዘር ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው፡፡ በዚህም ባለሙያዎቹ ሥራውን ከማሳደግ ይልቅ እየተውት፣ እንደሆነ ራሳቸው ገልፀውልኛል፡፡

ሰዎች እንደሆኑ መረጃ አቀባዬ (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ፣ 26/10/2009 ዓ.ም)ገልፃልኛለች፡፡

የዝምድና ማጣራት ስራው እርግጠኛ ይሆን ዘንድም አያት ካለ ለአያት ይነገርና ጥናቱ ይቀጥላል፡፡ ከዚህ የማጣራት ሂደት በኃላ የሴት ቤተሰቦች ለጋብቻ የሚከለክል ነገር ካጋጠማቸው ወደ ሌላ አካል ሳይመሯቸው እራሳቸው "ተቀድማችኃል ፣ ለሌላ ሰጥተናታል" በማለት ቁርጠኛ የሆነ አሉታዊ መልሳቸውን አጠንክረው ገልፀው ይመልሷቸዋል፡፡ ለጋብቻ የሚከለክል ነገር ካላጋጠማቸውና ለመስጠት ፍቃደኛ ከሆኑ ግን ፣ በሁለተኛው ሽማግሌዎቹን "ከእኔ በላይ ወዳለው ወደ እከሌ ሂዱና ጠይቁ" ይሏቸዋል(ቡ.ተ.ው.3)፡፡ ሽማግሌዎቹም በሴቷ ቤተሰቦች ወደ ተጠቆሙበት ዘመድ ቤት የሚሄዱበትን ቀን ሄደው ይጠይቃሉ ፤ ከነሱ ያገኙትን መልስም ወደ ወላጆቿ ቤት በመሄድ ይገልፃሉ ፡፡ መልሳቸውም አዎንታዊ ከሆነ ወላጆችም ‹‹ሰጥተናል››ይላሉ፡፡ ለእጮኝነት ጥያቄው ከሴቷ ቤተሰቦች ለሽማግሌዎቹ የእሽታ መልስ የሚሰጠው ቢያንስ በሶስተኛው ጉዟቸው ነው ማለት ነው፡፡ ይህም ቀን መቁረጫ/ግርዬ ቋርደነው/ይባላል፡፡ ምክንያቱም እርግጠኛው መልስ የሚሰጥበትን የሽማግሌዎች ምልልስ የሚያቆምበት ዕለት ነው፡፡

> የሽማግሌዎች የመመላለስ ድግግሞሽ እንደ ተጠያቂው ሰው ፈቃደኝነት የሚወሰን ነው ይህንንም አቶ ደርበው ታረቀኝ ሲገልጹ እንደሚከተለው ብለዋል፡፡ የሽምግልና ቀናት መጠን በሚመለከት ይህን ያህል ቀን ይጨርሳል ፣ ብሎ መናገር ይደብዳል ፤ ምክንያቱም እናትና አባት "ዝምድና ጥብቅ ነው ፣ እናጣራ" እያሉ ብዙ ጊዜ ያመላልሱናል፡፡ በአንደኛው እሺ እንደማይባል እናውቃለን ፤ በሁለተኛው ወደ አያት ወይም ወንድም እህት ሂዱ ተብለን ከሆነም ፣ ወደ እነሱ ሄደን ጥያቄያችንን እናቀርባለን ፣ እነሱ እሺ ካሉን ተመልሰን ወደ እናትና አባት በመሄድ "በዚህም በዚያም ጠይቀናል ፣ ለግቢ የሚከለክል ነገር የለም ፤ ልጃችንን እንሰጣለን ብለዋል" እንላለን፡፡ አንዳንዶች ግን "ግቢውን አንፈልግም" ብለው ይከለክሉናል፡፡ እኛም ምክንያቱን እንዲገልፁልን አጥብቀን እንይዛቸዋለን፡፡ ከወገን ከዘመድ ጠብ እንዳላቸው እንዲነግሩን እንጠይቃቸዋለን ፤ ንክኪ አለ ካሉንም መጀመሪያ እንዲታረቁ እናደርጋለን፡፡ ከዚያ በኋላ የሴቷ ወላጆችም

"እነሱን ካስታረቃችሁማ እኛም  ሰጥተናል" ይላሉ፡፡ እኛም "ቃል ግቡልን" እንላቸዋለን (ቁ.የ.መ.አ.)፡፡

በዚህ ጊዜ የሁለቱም ቤተሰቦች ለሽማግሌዎቹ መጠነኛ ግብዣ ያደርጉላቸዋል፡፡ በመጀመሪያ ፣ ለሽምግልናው ወይም ለአማጭነቱ አዎንታዊ መልስ ለመስጠታቸው በምልክትነት የሚያገለግለውን የተጋበዙልን ጥያቄ ለሽማግሌዎቹ የሚያቀርቡት የሴት ቤተሰቦች ናቸው "ተቀመጡ ፣ እንጀራ ብሉ" ይሏቸዋል፡፡ ሽማግሌዎቹም በደስታ ግብዣቸውን ይቀበላሉ፡፡ ከተስተናገዱ በኋላም በዚህ ጊዜ በሴቷ ወላጆች የተወሰነ እርቀት ይሸኛሉ፡፡ ይህም የሴት ወገን ለሽማግሌዎቹ ያላቸውን አክብሮት ለመግለፅ ነው፡ ፡ በመቀጠልም ሽማግሌዎቹ ወደ ወንድ ቤተሰብ በመሄድ ከሴት ወገን ያገኙትን የእሽታ መልስ ያበስራሉ፡፡ የወንድ ቤተሰቦችም በተገኘው መልስ ተደስተው ይጋብዟቸዋል በአካባቢው አገላለፅ እህል ውሃ ይሏቸዋል (ቡ.ተ.ው.4/5)፡፡

ከላይ ከተመለከትናቸዉ ‹‹ልጅህን ለልጄ›› በጥቆማ ከሚከናወን መተጫጨት በተጨማሪ ዝምድናን ለማጠናከር ሲባል በአያት ቅድመ አያት ፍቅር መነሻነትም መተጫጨት ይፈፀማል፡፡ ይህንን አስመልክተዉ አቶ በላዩ መንገሻ የተባሉ መረጃ አቀባዩ ሲገልጹ በጥር 2009 ዓ.ም ጋብቻዉን የፈፀመዉ ልጄ ጌጤ በላዩ የታጨችዉ በ1991 ዓ.ም የአራት ዓመት ልጅ እያለች ነበር፡፡ በዚህ እድሜ እንድትታጭ ምክንያት የሆነዉ ቀደም ሲል የእኔ እና የልጁ ወላጆች በነበረን የፀና ወዳጅነት ነዉ፡፡ ይህም በሁለታችን ቤተሰቦች መካከል ቤተሰባዊ ግንኙነት ስለነበር ያንን ወዳጅነታችንን እንዲመሰረት አደረግን (ቁ.የ.መ.አ)ብለዋል፡፡

ይሁን እንጂ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቤተሰብ ያለቸዉ ሴት ልጆች ግን በሕፃንነታቸዉ አይታጩም፡፡ ይህንንም ወ/ሮ ታምር አሰፋ የተባሉ መረጃ አቀባዬ እነደሚከተለዉ ይገልፃሉ፡፡

> እዚህ በከተማችን ዉስጥ የድሃ ልጅ የሆነችዉ የወ/ሮ ወርቂ ልጅ (እናቷ ጠላ ሻጭ በመሆኗ ) በልጅነቷ ሳትታጭ ዘንድሮ (2009 ዓ .ም ) በ18 ዓመቷ ታጨች ወዲያዉ ዲቃላ ሳታመጣ በሚል ተዳረች፡፡ ዲቃላ ሳታመጣ እናቷም ጠላ ሻጭ በመሆኗ ከሚጠጣዉ ጋር መሳቅ መጫወት ስላለባት በዚያዉ ደቀለች የሰዉም ፊት ጠበሳት ‹‹የልጇም እድል እንደሷ እንዳይሆን በማሰብ

እንደተጠየቀች ዉጣ ዉረድ ሳታበዛ እሺ በማለት በእጮኝነትና በሰርግ ጊዜ መካከል ረጅም ግዜ ሳይኖር አገባች (ቡ.ተ.ዉ.9/02/2010 ዓ.ም) በማለት ገልፀዋል፡፡

የወንዱ ቤተሰቦች ልጅቷ ከፀነሰች በኃላ የሴት ቤተሰቦችን ቤት ለየማት ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡ ይህም የቅርብ ቤተሰብ የሚሳተፍበት ነዉ፡፡ ወደ ሴቷ ቤተሰብ የሚሄዱት ሰዎች መጠናቸዉ ሊለያይ ቢችልም አነስተኛ የሚባለዉ ግን ሰባት ነዉ፡፡ ይዘዉ የሚሄዱትም እንደ አቅመቸዉ ይወሰናል፡፡ እስከ ሁለት መሶብ ትኩሴ ፤ ሁለት መሶብ እንጀራ ሊሆን ይችላል፡፡ ወደ ሴቷ ቤተሰብ ቤት ሄደዉም ለሁለት ቀናት ያህል እየበሉና እየጠጡ እርስ በርሳቸዉ እየጠዋወቁ ቆይተዉ ይመለሳሉ፡፡ ይህ የሴት ቤተሰቦችን ቤት የማየት ጉዞም መተዋወቂያ (በኽምጣኝ አርቅርሽተነ) ይባላል (ቁ.መ.አ (ቁ) እና ቡ.ተ.ዉ.2)፡፡

ከእጮኝነት እስከ ሰርግ ባለዉ ጊዜ ዉስጥም ተጋቢ ቤተሰቦች በክፉም ሆነ በደጉ ይጠያየቃሉ፡፡ የአንዱ ቤተሰብ ዘመድ ሲሞት ልላዉ ለዘመዶቹ በመንገር “የአማች” ተብሎ በርከት ያለ እንጀራ ይወሰዳል የሴቷ ወይም የወንዱ እናት ስትወልድም እንደ አቅም ፍየል ፤ ትኩሴና ዳቦ በመያዝ ይጠያየቃሉ፡፡ በተለይም በብሄረሰቡ ጎልቶ በሚታወቀዉ በክብር በዓል ድግስ ወቅት የሴቷ ወገን በወንዱ ወገን የወንዱ ደግሞ በሴቷ ወገን እየተጠራሩ ይበላሉ ፤ ይጠጣሉ ፤ ይጠያየቃሉ (ቡ.ተ.ዉ 3 እና 4)፡፡

እጮኝነቱ የተከናወነዉ በህፃንነቷ ከሆነ ልጅቱ ከፍ እንዳለች ወይም እግር ተክላ መሄድ ከጀመረች የወንድ ወገኖች የእጮኝነት ምልክት የሆነዉን ልብስ ፤ ጫማ ፤ መሀረም/ባዉንድ ወደ ሴቷ ቤት ይወስዳሉ፡፡ ከዚያም ማርዳ ያመጣሉ፡፡ ማርዳ የሁለት ነገር ቅልቅል ነዉ ፤ ከብር ወይም ከኒኬል የሚሰራዉ የጠልሰምና የድባ ከብር ወይም ከኒኬል የሚሰራዉ ጠልሰም ሶስት ዓይነት ቅርፅ አለዉ፡፡ የሦስት ማዕዘን ፤ የክት እና የአራት ማዕዘን ጠልሰምን ድባዉ በጥቁር ለስላሳ ክር /ካሉስ /የሚደረደር ሲሆን ከመሃልም ትልቅ የቀራኒዮ መስቀል ይቀላቀሉበታል፡፡ በተጨማሪም ከብር የተሰራ ክብ የጆሮ ጌጥ /አላድ /አብሮ ይኖራል፡፡ በማርዳዉ ዉስጥ የሚገኘዉ የጠልሰም መጠን እንደ ወንዱ ቤተሰብ አቅም የሚወሰን ቢሆንም ዝቅተኛዉ ግን 30 ነዉ፡፡ ይህም በእያንዳንዱ ቅርፅ አስር አስር ሲሆን ድባዉም 30 ይሆናል፡፡ በስጦታዉ ወቅት የሴት ወገንም /እናትና አባት እነዚህን በስነ-ስርዓት ይቀበላሉ፡፡ ልጅቱም ትቀርብና እንድታጌጥበት

ይደረጋል፡፡ በዚህም አጋጣሚ ለመጀመሪያ ግዜ አማቾቿን ታያቸዋለች፡፡ እነሱም መርቀዋት ይሄዳሉ (ወ/ት ወርቃፈራዉ ቸኮል ፤ ቁ ፤ መ ፤ አ 26/05/2010 ዓ.ም)፡፡



ምስል 15፡- ማርዳ የለበሰች የታጨች ልጅ (ፎቶ የፀመራ ልጅ)

አማቾቿ የወሰዱላትን ልብስ መልበስና ማርዳ ማሰር ስትጀምር ልጅቷ መታጨቷ በገሃድ ይታወቃል፡፡ በዋግኽምራ ባህል ለሴት ልጅ የመታጨት ምልክት ሆኖ ያገለግል የነበረዉ ማርዳ ነበር፡፡ አሁን ግን መታጨቷ የሚታወቀዉ ማርዳ በማሰር ብቻ ሳይሆን በወሬም ጭምር ሆኖዋል ሲሉ ቁልፍ መረጃ አቀባዬ መምህርት ወርቃፈራሁ ቸኮል ገልፀዉልኛል (መ/ት ወርቃፈራሁ ቁ.መ.አ 26/05/2010 ዓ.ም)፡፡ ማርዳዉ እየቀረ የመጣዉም በተለያዩ ምክንያቶች ነዉ፡፡ የመጀመሪያዉ ዋና ምክንያት ጠልስም የሚሰራበት ክር በመወደዱና ቱባዉም በገበያ ላይ ባለመገኘቱ ነዉ፡፡ ሌላዉ ምክንያት ደግሞ ‹‹ከዉድነት በተጨማሪ እንደ ቀድሞዉ ሁሉም ሴቶች ስለማይታጩ ነው  ይላሉ (ቁ.መ.አ.11 እና ቡ.ተ.ዉ.4 )፡፡ ቀደም ሲል በልጅነቷ የታጨች ልጅ እጮኛዋን እና ዘመዶቹን ስለምታፍራቸዉ አታያቸዉም ነበር፡፡ የእጮኛዋ ወገኖች መሆናቸዉን ካወቀች ወይም ከሰማችም ላለማየት ትሸሻለች፡፡ ወንዱም ቢሆን ከሰርጉ በፊት አማቾቹን አያያቸዉም፡፡ ለዚህም በድሃና ወረዳ ልዩ ስሙ ሲልዳ በሚባለዉ አካባቢ አንድ ገደል አለ፡፡ የገደሉ ስምም የሙሽራ ገደል በመባል ይታወቃል፡፡ ይህን ስም አገኘ የሚባለዉም

አንድ ሙሽራ አማቾቹ ከፊት ለፊቱ ሲመጡ ተመልክቶ ፣ ሊሸሽ ሲል በዚያ ገደል በመዉደቁ ነዉ ይባላል(ቡ.ተ.ዉ.2)፡፡ ከእጮኝንት እስከ ሰርግ ቀን መቁረጥ ድረስ ባሉት ጊዜያትም የተለያዩ ሥራዎችን እንዲሰራ የሴት ወገን የወንድ ወገንን ያዝዛል፡፡ ስራዉም አማች (በኸምጣኝ አሰንጥ እዝ) በመባል ይታወቃል፡፡ የስራዉ አይነትም አረም ፣ አጨዳ ፣ ወይም ቤት የሚሰራ ከሆነ ለቤት መስሪያ የሚሆን እንጨትና ሰንበሌጥ እንዲያመጣ የሚታዘዝበት ነዉ (ቁ.የ.መ.አ/እና ቡ.ተ.ዉ.4)፡፡ ይህም ከሙሽራዉ ወደ አማቾቹ በተወሰነ ጊዜ ወደ ሙሽራዋ ቤተሰቦች የሚተላለፍ የጉልበት አገልግሎት ነዉ፡፡ ይህም የደቦ ፣ ጅጌ (ወበራ)ዓይነት ነዉ፡፡ ሂደቱም እንደሚከተለዉ ነዉ፡፡ የሴት አባት የሚሰራዉ ስራ ምን ያህል ሰዉ እንደሚያስፈልገዉ በመጥቀስ ይህን ያህል ሰዉ ፣ ለምሳሌ ያክል ሰላሳ ሰዉ ፣ ይዘህ እንድትመጣና ከዚህ ቦታ የሚገኘዉን ስራ እንድትሰራ በማለት የወንድ አባትን ያዝዛል፡፡ የወንድ አባት ግን ስራዉ በተገለፀዉ ሰዉ መጠን ላይጠናቀቅ ይችላል የሚል ጥርጣሬ በማሳደር በስራዉ የሚሳተፉትን ከማሰባሰቡ አስቀድሞ እንዲሰራ የታዘዘዉን ማሳ ዞሮ ይመለከታል፡፡ ከዚህ በኃላ በዚህ ቀን በዚህ ቦታ የአማች እዝ ስላለብኝ እንድትመጡ ብሎ በስራዉ ይሳተፉልኛል ለሚላቸዉ ሰዎች ጥሪዉን ያስተላልፋል፡፡ ከተጠቀሰዉ የሰዉ መጠን ላይም ጨምሮ ይወስዳል፡፡ ስራዉንም የሚሰሩት እንደማንኛዉም የወበራ ስራ የተለዩ ዘፈኖችን በመዝፈን ነዉ፡፡ ማታ በሴቷ ቤተሰብ ቤት ድግስ ተደግሶ ይጠብቃቸዋል፡፡ እነሱም ሆ! እያሉ ወደ ቅጥር ግቢዉ ገብተዉ ትንሽ ከዘፈኑ/ከጨፈሩ በኂላ በልተዉና ጠጥተዉ ቢመሽም እንኳ ወደ ቤታቸዉ ይመለሳሉ እንጂ በአማቾች ቤት አያድሩም፡፡ የሴት ቤተሰቦችን አማቾቻቸዉ የሰሩበትን የጉልበት ዋጋ ግምት እንደአቅማቸዉ ቀንጃ በሬ ወይም ጥንድ በሬ ይሰጧቸዋል፡፡ ስጦታዉ ሥራዉ በተሰራበት እለት ሊሰጥ ካልሆነም በሠርጉ ዕለት በሚሰጠዉ ስጦታ ወቅት ሊሰጥ ይችላል (ቡ.ተ.ዉ.3)፡፡

**በእጮንነት ሂደት**

በመጀመሪያዉ የእጮኝነት ጥያቄ ቀን ሴት በሽማግሌነት አትሄድም ፣ የተጠያቂዋ ልጅ እናትም ለሽማግሌዎቹ በሚሰጠዉ መልስ አትሳተፍም፡፡ ከቤቷም አትወጣም ፣ ከቤት ወጥቶ መልስ የሚሰጠዉ አባት ወይም አሳዳጊ የሆነዉ ወንድ ነዉ፡፡ ለዚህ ምክንያት መረጃ አቀባየ የሆኑት መምህርት ወርቃፈራሁ እና አቶ ደርበዉ ታረቀኝ እንደተናገሩት

ሴቶች ወጥተዉ መልስ መስጠት በብሔረሰቡ/በአካባቢዉ ያልተለመደ ባህል በመሆኑ ነዉ (ቁ.የ.መ.አ.1 እና 4)፡፡

አቶ ጥጋቡ ምርቴ ሴቶች ሽማግሌ ሆነዉ የማይሄዱበትን ምክንያት አስመልክቶዉ እንደሚከተለዉ ገልፀዋል፡

> *ድሮ የአንድ ደብር ልጆች ፤ የወንዝ ልጅ ናቸዉ ስለሚባል አይጋቡም ነበር ፤ ወንዝ ተሸግሮ ነበር የሚጋቡት ፤ ይህም ወንድ ባንድ አካባቢ ችግር ቢፈጥር ለመደበቂያነት ያገለግል ነበር፡፡ ስለዚህ ሴት ወንዝ ተሽግራ አትሄድም ሽማግሌ መሆን አትችልም፡፡ ይሁን እንጂ እሺ ወይም እምቢ ለማለት ሚስቱን ስለሚያማክራት ዘራቸዉ ችግር ካለበት ጋብቻዉን ማስቀረት ትችላለች (ቃ.መ .26/05/2010 ዓ.ም)፡፡ ይሁን እንጂ እናት ሽማግሌ ሁና ባትሄድም ልጇን የሚጠይቁ ሽማግሌዎች ሲመጡ መልስ ባትሰጥም ለጥያቄዉ እንግዳ አትሆንም፡፡ ምክንያቱም ባለቤቷ ‹‹ልጃችንን ለእገሌ ልንሰጥ ነዉ›› ብሎ ያማክራታል፡፡ የተጠያቂዉ ሚስት ለትዳር የምትፈልገዉን ልጅ የማትወልዳት ከሆነም ሽማግሌዎቹ ወላጅ እናቷ ወደምትኖርበት አካባቢ ሂደዉ እንዲጠይቋት ይደረጋል፡፡ እሷም በጋብቻ በሚጠይቋት ቤተሰቧ መካከል ያለዉን ሁኔታ በማጠያየቅ ሀሳብ ትሰጣለች፡፡ በእጮኝነት ወቅትም አባት ለሽማግሌዎቹ "ባለቤቴ ትምጣና እሷም ትጠየቅ" ይላል፡፡ በዚህ ግዜ በሷ ወገን ጠብ ካለ ለእሽታዉ እንቅፋት የሚሆንበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ስለዚህ የመጨረሻዉ የእጮኝነት ስምምነት የሚፈፀመዉ ሁለቱ (አባትና እናት )ባሉበትና ባመኑበት ነዉ (ቁ.የ.መ.አ.2 ፤ እና ቡ.ተ.ዉ.4)፡፡ ሴቶች ለማጨት ሽማግሌ ባይሆንም "ያልታጨች የእከሌ ልጅ አለች" ብለዉ ለወንድ ወገን መጠቆም ይችላሉ፡፡ ጠቋሚ ሆነዉም ቤት ለማሳየት ወደ ሴቷ ቤተሰብ ሽማግሌዎቹን ይዘዉ መሄድ ይችላሉ (ወረወቃፈራሁ ቸኮል ፤ ቃመ.06/05/2010 ዓ.ም)፡፡*

**የሠርግ ቀን ቆረጣ**

ከእጮኝነት እስከ ሰርግ ቀን ድረስ የተወሰነ ቋሚ የጊዜ ርዝማኔ የለዉም፡፡ ይህም የሆነዉ በተለያዩ ምክንያቶች ስለሚወሰን ነዉ፡፡ የመጀመሪያዉ ምክንያት የተጋቢ ቤተሰቦች ለመደገስ ያላቸዉ አቅም ነዉ፡፡ የወንድ ወገን "ልጃችንን በዉሃ አጥበህ ስጠን

፤ ዘንድሮ ብርም ድግስም አልፈልግም" ብሎ የሴት ወገንን በሚጠይቅበት ወቅት የሴት ወገን ለመደገስ አቅም ባይኖረዉም ልጆቹ ይጋባሉ፡፡ ጥሩ ምርት ሲገኝ ሠርጉ/ድግሱ ይካሄዳል ፤ ሌላዉ ምክንያት የተጋቢ ቤተሰቦች የሚገኙበት የዕድሜ እና የጤንነት ሁኔታ ነዉ፡፡ የልጁ ወይም የልጅቷ ወላጆች በዕድሜ የገፉ ከሆኑና "ሣንሞት የልጃችንን ዓለም ማየት አለብን" በማለት ሴቷ ለአካለ መጠን ባትደርስም እንኳ እንድትዳርና ከባሏ ቤተሰቦች ጋር እንድታድግ የሚደረግበት ሁኔታ አለ (ወ/ሮ አለምነሽ በላይ ፤ ቃ.መ 06/05/2010 ዓ.ም)፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሚያገባዉ ልጅ "በዚህ አመት ዳሩኝ ራሴን መቻል አለብኝ" ካለም በድግስ ባይሆንም በአግብተህ ክረም ጋብቻዉ ሊፈፀም ይችላል፡፡ ልጅቷ የታጨችዉ በአቅመ ሄዋን ከደረሰች በኂላ ከሆነና የተጋቢዎቹ ቤተሰቦች ለመደገስ አቅም ከሌላቸዉም የምርት ወቅት ሳይጠበቅ በታጨበት አመት በመጠኛ የሰርግ ድግስ ሊዳሩ ይችላሉ፡፡ የሰርግ ቀን ቆረጣ የሁለቱ የወደፊት ተጋቢዎች ቤተሰቦች ሰርጉ የሚደረግበትን ወርና ቀን የሚወስኑበት ነዉ፡፡ የሰርግ ቀን የሚቆረጠዉም በሁለቱ ተጋቢ ቤተሰቦች ስምምነት ነዉ፡፡ በመጀመሪያ "ልጄን ስጡኝ" በሎ የሴት ቤተሰብን የሚጠይቀዉ ግን የወንድ ቤተሰብ ነዉ፡፡ ለዚህም ፍቃደኝነታቸዉን የሚጠይቅ ሰዉ ይላካል፡፡ ሰዉዬዉ "ወንድማችሁ እከሌ ልጁ ደርሷልና ልጃችሁን ስጡኝ ይላቸዋል" ብሎ ይጠይቃል፡፡ የሴት ቤተሰብም "እሺ ከቤተሰብ ጋር ተማክረን መልሱን እንሰጣለን" ይላሉ፡፡ የሴት አባት ቀኑን እራሱ ከመቁረጡ በፊት ቤተሰቦቹን ያማክርና መቼ መሆን እንዳለበት ለወንድ ቤተሰብ ቀኑን ያሳዉቃል፡፡ የወንድ ቤተሰብም የተቆረጠለትን ቀን መቀየርም ሆነ እምቢ ማለት አይችልምና ይስማማል፡፡ ከዚያም ሁለቱም ዝግጅታቸዉን ይቀጥላሉ፡፡ የሴቷ ሠርግ ከወንዱ አስቀድሞ ይደረጋል፡፡ በዋግኸምራ ብሄረሰብ በርካታ ጋብቻዎች የሚፈፀሙት በጥርና በየካቲት ነዉ፡፡ አልፎ አልፎ ከፋሲካ በኂላ በሚያዚያ ወር ይካሄዳል፡፡ በግንቦት ወር የሚካሄድ ጋብቻ ግን አይፀናም የሚል ልማዳዊ እምነት አላቸዉ፡፡ በሌላ በኩል ግንቦት ሰዉም ሆነ መሬቱ የእርሻ (ማሳዉ) እህል የሚፈልግበት በአብዛኛዉ አርሶ አደር ቤት የእህል እጥረት የሚገጥምበት ወር በመሆኑ ሙሽራዋንም በምግብ መንከባከብ አይችሉም ፤የሥራ ወቅትም ስለሆነ በቀጥታ ወደ ስራ ትገባለች፡፡ ይህ ወቅት ለክረምትም ከጫካ እንጨትና ከሜዳ ኩበት የሚሰበሰብበት ወቅት ስለሆነ ሙሽራዋ ላይ የስራ ጫና ይበዛባታል (አቶ ደርበዉ ታረቀኝ ፤ ቃመ. 10/06/2010 ዓ.ም)፡፡ በብዛት ሠርግ የሚደገሰዉ በጥርና በየካቲት ወራት ነዉ፡፡ እነዚህ ወራት የሚመረጡበት ዋነኛ ምክንያት አርሶ አደሩ ምርት የሚያስገባባቸዉ እና ከእርሻ ስራዉም

እረፍት የሚያገኙባቸዉ በመሆናቸዉ ነዉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቆላዉ አካባቢ በእነዚህ ወራት ዉሃ እንደልብ የሚገኝባቸዉ ስለሆኑ ነዉ፡፡ በሚያዚያና በግንቦት ወራት ግን ብዙ ሰርግ አይደረግም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ትናንሽ ወንዞችና ምንጮች ስለሚደርቁ የዉሃ ችግር ያጋጥማል ፤ አርሶ አደሩም ወደ እርሻ ስራዉ ይገባል፡፡ የሠርግ ቀናቱም የተመረጡ የበዓል ቀናት ናቸዉ፡፡ ከሳምንቱ ቀናትም ሰኞ ፤ ማክሰኞና ሓሙስ ናቸዉ፡፡ በገጠሩ ማህበረሰብ እሁድና ቅዳሜ ተዝካር እንጂ ሠርግ አይደረግም[32]፡፡ ለዚህም ዋና ምክንያቱ ቀደም ሲል ዳስ ሲሰራ በዕለቱ አሜካ (ከበረሃ )እርጥብ የዶዶሃ ቅጠል ስለነበርና ለማገዶ የሚሆነዉንም በዚያዉ እለት እየተሰበረ ይመጣ ስለነበር በዓል እንዳይሻር ነዉ፡፡እሮብና አርበም የፆም ቀናት በመሆናቸዉ በእነዚህ ቀናት ሠርግ አይደረግም፡፡ የጋብቻ ዉልም አይፈፀምም (ቡ.ተ.ዉ.2)፡፡ የሠርጉ ቀን ሲቃረብም የወንድና የሴት ቤተሰቦች እንደ ድግሳቸዉ መጠን ታዳሚያቸዉን ይጠራሉ፡፡ ጥሪዉ የሚከናወነዉም ዘመድ በሚገኝበት አካባቢ ሁሉ በቃል ነዉ፡፡ የሠርግ ቀን ከተቆረጠ በኃላ ሙሽራዎች ወንዝ አይሻገሩም፡፡ ብቻቸዉንም ከቦታ ቦታ አይንቀሳቀሱም ፤ ለዚህም ምክንያት ከሌላዉ ቀን ይበልጥ በሰርጋቸዉ ሰሞን እርኩስ መንፈስ በእነሱ ላይ ያድራል ተብሎ በባህሉ ስለሚታመን ነዉ፡፡ ለዚህ መከላከያ ይሆን ዘንድም ሴቷ በእጇ የብር ድኮት ታደርጋለች ፤ ወንዱም የብረት ዘንግ ይይዛል ሲሉ ገልፀዉልኛል (አቶ ደርባዉ ታረቀኝ ፤ ቃመ ፤10/06/2010 ዓ.ም)፡፡

በዋግኽምራ በተለይም በገጠሩ አካባቢ ሚዜ የሚያስፈልገዉና ምልመላ የሚያከናዉነዉ ወንዱ ሙሽራ ብቻ ነዉ፡፡ ሴቷ ሙሽራ ሚዜ አይኖራትም፡፡ ምልመላዉን የሚያከናዉነዉም የሠርጉ ቀን እንደተቆረጠ ነዉ፡፡ ሙሽራዉ ሚዜዎቹን የሚመርጠዉ ብቻዉን ሳይሆን ከአባቱና ከወንድሞቹ ጋር በመመካከር ነዉ፡፡ ሚዜነት ዝምድና ማከልም ነዉ፡፡ ለምልመላ የሚያገለግሉትም መስፈርቶች ጓደኝነትና አብሮ አደግነት ፣ የማጫ እና የስጦታ አጠያየቅና የመዝፈን ችሎታ መኖር ሲሆኑ ፣ ዋናውና ትልቁ መስፈርት ግን ከቤተሰብ የሚመጣ ወዳጅነት ነው፡፡ የሚዜ ጥቅሙ ብዙ ነው፡፡ አንደኛው ለሙሽራው አክብሮት ለመስጠት ነው፡፡ ሁለተኛው ሙሽሪትን ለማለማመድ ነው፡፡

[32] እሁድ ሠርግ አለ ከተባለ የእስላም እንጂ የክርስቲያን አይደለም፡፡ (አቶ ደርበዉ ታረቀኝ ፤ቁ. መ.አ. 21/10/2010)፡፡

ሶስተኛው በሰርግ ወቅት በስራ ማገገዝ ነው፡፡ ዳስ በመስራት ፣ እቃ በማጓጓዝ ፣ በመላላክ ወዘተ ያግዛሉ (አቶ ወንድምሰን ጌታሁን ፣ ቃመ. 28/06/2010 ዓ.ም)፡፡

**የሰርግ ድግስ ዝግጅት**

የሰርግ ቅድመ ዝግጅቶች ከተከናወኑ በኂላ የሚቀጥለው ተግባር የሰርጉን ድግስ ማዘጋጀት ነው፡፡ በብሔረሰቡ ለሰርግ ድግስ ይደግሳል ቢባልማም ወጭው ግን ይህን ያህል ተብሎ የሚወሰንና የተወሰነ መጠን የለውም ፤እንደ ደጋሾቹ አቅም የሚወስን ነው፡፡ ምልከታ ካደረግሁባቸው ሰርጎች መካከል ዛንዚራ ተክለሀይማኖት በተሰኘው ቀበሌ በ20/06/2010 ዓ.ም የነበረው የወ/ሮ ተወዳጅ ወ/ኪዳን ልጅ ለአብነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ድግሱም በአንዲት ትንሽ ፍየል ስጋና በሁለት ጋን ጠላ ብቻ ነው፡፡ ይህ ድግስ በጣም አነስተኛው ነበር፡፡ መረጃ አቀባዬ የሆነችው መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ይህንን አስመልክታ "ከፍተኛ የሚባለው የሰርግ ድግስ ወጪ ከቤት ካለው የእርሻ ምርት ውጭ የሆነውን የእህል ዋጋ ሳይጨምር ለሙሽራዋ አልባሳት ፣ ለዘይት ፣ ለበርበሬ እና ቅመማቅመም በጥቅሉ ከሌላ ቦታ ለተገዙ ነገሮች ብቻ ከሰላሳ ሺህ ብር በላይ ወጭ ተደርጎ በሰፊ ዳስ ሁለት ልጆች/አንድ ወንድና ሴት/ የተዳሩበት የቅርቡን የ29/05/2010 ዓ.ም ማስታዎስ ይቻላል" ብለዋል (ቁ.መ.አ 20/11/2010 ዓ.ም)[33]፡፡

የሰርግ ድግስ የሚዘጋጀው በደጋሹ ወጪ ብቻ አይደለም፡፡ በድግሱ ዝግጅት ወቅት የዘመድና የጎረቤት እገዛም ይኖራል፡፡ እገዛው ለደጋሹ ምክር በመለገስና በሃሳብ በመደገፍ ፣ በጉልበትና በገንዘብ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም የሰርጉ ድግስ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሚቀጥል ነው፡፡ እገዛውንም የወንዶች ፣ የሴቶችና የወዳጅ ዘመድ በማለት ሊለይ ይችላል፡፡ እነዚህን ለየብቻ እንደሚከተለው ጠቅለል አድርጌ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡

**የሴቶች የስራ እገዛ**

ሴቶች በሰርግ ድግስ ወቅት ከአማካሪነታቸው በተጨማሪ በጉልበት እገዛ በኩልም ልዩ ልዩ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ዋነኞቹን ስንመለከት ለሰርግ ድግስ የሚወጣው እህል በአብዛኛው መጠኑ ብዙ ነው፡፡ ይህንን የሰርጉ ደጋሽ ሴቶች ብቻቸውን አበጥረው የሚጨርሱት አይደለም ፤ የግድ የሌሎችን እገዛ ይጠይቃልና ለጎረቤቶችና

[33] ሰርጉ የተካሄደበት ቀበሌ ሰሬን በምትባል ሰቆጣ ወረዳ ነው፡፡

ዘመዶች የእህል ማበጠሪያው እለት ይገለጻል፡፡ የሰሙትም ‹‹የእከሌ ሰርግ የእህል ማበጠሪያ ቀን በዚህ እለት ነው››እያሉ ላልሰሙት ሴቶች በመንገር ተጠራርተው ወደ ሰርጉ ቤት ያመራሉ፡፡ ለጠላ/ለዝልልና ለኮረፌ/የሚሆነውን እህል ፣ ማሽላ ፣ በቆሎና ገብስ ቆሻሻውን በመልቀም ፣ ለእንጀራ/ለጣቢታና ለድጎሎ የሚሆነውንም እህል ያበጥራሉ፡፡ ለዚህ አገልግሎት የሚረዱትን እንደ ሰፌድ ፣ ወንፊት ፣ ማንዘርዘሪያ አና የመሳሰሉትን ቁሳቁሶች ከየቤታቸው የሚያመጡትም የስራው ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ የጉልበት ብቻ ሳይሆን የቁሳቁስም እገዛውም የሚጠበቅና የማይቀር ነው(መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል፣ ቂ.መ.አ 29/08/2010 ዓ.ም)፡፡ እንደ አሁኑ ጊዜ የእህል ወፍጮ ባልነበረበት ቀደም ባለው ወቅት ደግሞ ለሰርግ ድግስ የሚውለውን እህል ደጋሽ ሴቶች ብቻቸውን ፈጭተው የሚጨርሱት አልነበረም፡፡ ሌሎች ሴቶች ተከፋፍለው ወደ ቤታቸው በመውሰድ ይፈጩት ነበር፡፡ ባሁኑ ጊዜም እህሉ ቀደም ሲል ‹‹አስክር›› እየተባለ በድንጋይ ወፍጮ ይፈጭ የነበረው ብቅል ሳይቀር በወፍጮ ቢፈጭም ፣ ሴቶቹ ግን የወፍጮ ማስፈጫ እያሉ ለደጋሽዋ እገዛ የሚሆ ብር ይሰጧታል፡፡ ሊጡ/ብሆው/የሚቦካውም እንዲሁ በሴቶች ነው፡፡ ብዙ ከሆነና ከሴቶቹ አቅም በላይ ከሆነም ወንዶቹም በማቡካቱ ስራ ላይ ይሳተፋሉ ፣ ለወጥ የሚሆነውም አተር ወይም ባቄላ የሚከካውም እንዲሁ በሴቶች ነው፡፡ በሰርጉ ወቅት ከክክ ወጥ ጋር የሚቀርበው እልበት/አዛም/ የሚዘጋጀው በሴቶች እገዛ ነው ፣ ሴቶቹ ለእልበት የሚሆነውን ሱፍና ሌሎች ማጣፈጫዎችን ይደቁሳሉ፡፡ በእንጨት ሙቀጫ ይወቀጥ የነበረው በርበሬ በአሁኑ ጊዜ በወፍጮ ቢፈጭም ፣ ለወጉ እንደ ቀድሞው ጨው ድቆሳ ተብሎ ሴቶች ወደየሰርጉ ቤት እንጀራ ይወስዳሉ ፤ እልል እያሉ መጠነኛ የሆነ ዘፈንም ይዘፍናሉ፡፡

ከሚዘፈነው ዘፈን ቃል ግጥም መካከልም የሚከተለውን አዝማች ቁልፍ መረጃ አቀባዩ ፣ ‹‹ በእልልታ ታጅቦ እንዲህ ይዜማል››ብለው አዚመውልኛል

አቀንቃኝ፡- ሙሽራ አበባ ፣ ሙሽራ አበባዬ!

ተቀባይ፡- ነይማ ነይ፡፡ (ወ/ሮ መሰረት አጠና፣ ቂ.መ.አ 20/06/2010 ዓ.ም)፡፡

ለድግሱ የሚሆነው ኮረፌ ወይም ዝልል አብሽሎ[34] የሚጋገረውም በሴቶች እገዛ ነው፡፡

የጠላ ዝግጅቱ ከተጀመረ ጀምሮ (በሰርጉ ዋዜማና በዕለቱ)ከወንዝ ወይም በአቅራቢያው ከሚገኝ ቧንቧ ውሃ ያመጣሉ፡፡ በእነሱ አቅም ሊሸፈን የማይችል ከሆነ ወንዶች በትከሻቸው ወይም በአህያ በመጫን ያመጣሉ፡፡ የድግሱ እንጀራ በምጣድ /ምጎጎ/[35] የሚጋገረውም በሴቶቹ ነው፡፡ በበርሜል ወይም በጋን ጠላ/ኮረፌ/የሚጠመቀውም በሴቶች ነው፡፡ በዋግኽምራ በሰርግ ድግስ የሚቀርበው ወጥ ሁለት ዓይነት ነው፡፡ የስጋ /በአካባቢው አጠራር የመረቅ/እና የክክ/የእህል ወጥ/፡፡ የክክ ወጡ የሚሰራውም በሴቶች ሲሆን አሰራሩ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ በመሆ በባልቴት ሴቶች በትዕግስትና በማያቋርጥ ክትትል ነው የሚሰራው፡፡ ስለሆነም የአሮጊት/ባልቴት ሴቶች ስራ ተብሎ ይመደባል፡፡ የስጋ ወጡ በወንዶች ቢሰራም ወጡን ከሚሰራበት እቃ ለማስተናገድ ወደሚቀርብበት ድስት የሚቀዱት/የሚጨልፉት ግን ሴቶች ናቸው፡፡ በተዘረዘሩት የስራ እገዛዎች ወቅት ደጋሾቹ ለሴቶቹ ኮረፌ እና እንጀራ በአዋዜ ያቀርቡላቸዋል፡፡

## የወንዶች የስራ እገዛ

ሰርጉ በሚከወንበት አካባቢ የሚገኙ ወንዶችም እንደ ሴቶቹ ሁሉ ድግሱ ከተጀመረ ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ እገዛቸውን ያደርጋሉ፡፡ ለድግሱ የሚሆነውን እህል አህያ ወይም በቅሎ በመዋስ ወደ ወፍጮ ቤት ወስደው ያስፈጫሉ፡፡ የበርበሬ ወፍጮ ባልነበረበት ጊዜ ወንዶቹ በእንጨት ሙቀጫ በርበሬ ይወቅጣሉ፡፡ ለድግስ የሚቦካው ሊጥ ብዙ ከሆነም በማቡካትና ውሃ በማምጣት ሴቶችን ያግዛሉ፡፡

የማገዶ እንጨት ጫካ[36] በርሃ ሄደው ያመጣሉ፡፡ የዳስ ስራውም የሚከናወነው በወንዶች ሲሆን እንደ ሰርጉ ድግስ መጠን ከፍ ያለ ከሆነ በሬው፣ ዝቅ ካለም ፍየሉ የሚታረደውም ፣ ስጋው የሚቆራረጠው ፣ የስጋ ወጡም በትልልቅ ብረት ድስት/በጎላ/የሚሰራው ዳሱ ውስጥ በወንዶች ነው (አቶ ባዬ አስምሮም፣ ቃመ 9/10/09

[34] የጠላ ቂጣ ሲሆን በጣም ያልደረቀ ነው፡፡

[35] በብሔረሰቡ ለስላሳውና ጠቆር ያለ ቀለም ያለው እንጀራ ብቻ የሚጋገርበት ከሸክላ የሚሰራው ምጣድ መጠሪያ ሲሆን፣ ሻከር ያለውና ለቂጣና ለጠላ አብሽሎ የሚጋገርበት ግን ምጣድ ተብሎ ይጠራል፡

[36] ደንን እንደተፈለገ መጨፍጨፍ በአሁኑ ጊዜ ስለተከለከለ፣ በገፍ መጨፍጨፍ የማገዶ እንጨት ማጓጓዝ ስለማይቻል ለቀበሌው የደን ኮሚቴ ቀድመው ያስፈቅዳሉ፡፡

ዓ.ም)፡፡ ወንዶች ለድግሱ የሚያስፈልጉ ዕቃዎችን በመፈለግም ይሰበስባሉ፡፡ ኮረፌውን ወይም ዝልሉን ከጋን ወይም ከበርሜል የሚቀዱትና ለተስተናጋጆች የሚያድሉትም ሆነ ወጥ የሚያወጡት/የሚጨልፉትም ፣ ለማስተናገድ እንዲቻል እንጀራውን ስድስት ስድስት ወይም አምስት አምስት በመቁጠር በመሶብ በመሶብ ወይም በሌማት በሌማት የሚመድቡት ፣ አጣጥለው ለብሰብ ከዳሱ መግቢያ ላይ በመቆም ታዳሚውን/ተስተናጋጆችን ቦታ ቦታ የሚያሲዙት አጋፋሪዎች/አስተናባሪዎች ወንዶች ናቸው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን የድግሱን መጠን፣ ማጫውንና ስጦታውን አስመልክቶ ለወንዱም ሆነ ለሴቷ ወገኖች የሚያማክሩትና ስጦታውንና የጋብቻውን ውል የሚያከናውኑትም ወንዶች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በሰርጉ ድግስ የሚበላውንና የሚጠጣውን ደጋሾቹ ቢያወጡም ስራው ሙሉ በሙሉ የሚሰራው ግን በጎረቤትና በቤተ ዘመድ እገዛ ነው፡፡ በ20/06/2010 ዓ.ም ሰቆጣ ወረዳ ይሰይደ በተባለ የገጠር ቀበሌ ላይ የሰርግ ድግስ ልጃቸውን የዳሩት አቶ ተቀባ አሸብር የታገዙትን ሲገልጹ ‹‹የእኔ ጉልበት ብዙም አይደለም ፣ ሲሶውን /አንድ ሶስተኛውን/አልሸፈነም ፣ የድግሱን ስራ የሰራው ዘመድና ጎረቤት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ለጉልበት ያወጣሁት ወጪ አነስተኛ ነውመ (ቁ.መ.አ.4)፡፡

በጾታ በመለየት ከተገለጸው እገዛ በተጨማሪም በሁለቱም ፃታዎች የሚታገዝም አለ፡፡



ይህም የቅርብ ወዳጅ እና ዘመድ እገዛ ነው፡፡

ምስል 16፡- የአውራጅ ምግብ አቀራረብ (ፎቶ ዋግኽምራ ዞን ባቱ)

**የወዳጅ ዘመድ እገዛ**

ለሰርግ ደጋሾች የሚደረገው እገዛ በሃሳብና በጉልበት ብቻ አይደለም፡፡ ድግስ በመደገስም ነው፡፡ ይህም አጋሮቹ ለደጋሾቹ ባላቸው ዝምድና እና ቀረቤታ ይወሰናል፡፡ በጣም ቅርብ ዘመድ ወይም ጥብቅ ወዳጅ የሆኑ አውራጅ ይይዛል፡፡ ይህም ዝቅተኛው አስራ ሁለት ድስት ወጥ፣ ከፍተኛው ደግሞ አስራ አራትና አስራ አምስት ድስት ወጥ ፣ አንድ ጋን ጠላና መቶ ሃያ እንጀራ ነው ፤ ስልሳ እንግዳም ይስተናገድበታል[37]፡፡ ባንድ ሰርግ አራት አውራጅ ያገኘ ቢኖሩ 240 እንግዶች ያስተናግዳሉ፡፡

ቀደም ሲል ግን በአንድ አውራጅ የሚስተናገደው ሰው መጠን የተወሰነ እንዳልነበር አቶ ደርበው ታረቀኝ የተባሉት የመረጃ አቀባዬ ገልጸውልኛል (ቁ.መ.አ.2)፡፡ አውራጅ ያገፑ የክክ ወጥና አዞ ወይም እልበትም ያዘጋጃል፡፡

ቀደም ሲል የአውራጅ ምግብ አቀራረብ በሁሉም ቦታ የደደሆ ቅጠል በተደለደለበት ላይ እንጀራ ተደርጎ እዛ ላይ ወጥ በማድረግ ነበር፡፡ አሁን ግን አልፎ አልፎ እንደከተሜው ሰርግ በሳህን እየቀረበ ነው፡፡

አውራጅ ለመያዝ አቅም የሌላቸው ደግሞ ጋን ጠላ በመጥመቅ ያግዛሉ፡፡ መጠኑ እንደ ደጋሹ ቀደም ሲል እንደጠመቀው ጠላና አውራጅ መጠን የሚወሰን ነው፡፡ ምልከታ ባደረኩበት ሰሬል ቀበሌ ሰርግ ሶስት አውራጅ ተይዞ አይቻለሁ፡፡ በ3/05/2010 ዓ.ም ሰቆጣ ወረዳ ፣ ሰላምጌ በተባለው ቦታ በተመለከትኩት ሰርግ ደግሞ ሁለት አውራጅ ተይዟል ፣ ሰላሳ ጋን ጠላም በሌሎች ተጠምቋል፡፡

ከድግስ እገዛ በተጨማሪ ለደጋሹ የገንዘብ ድጋፍም ይደረጋል፡፡ ይኼውም በሰርጉ ዕለት ታዳሚው ብር ወይም በዓይነት ከብት ይሰጣል፡፡ በተለይ የምትዳረው ሴት ከሆነች ፣ ለወንድ ወገን ለሚሰጠው ስጦታ ድጋፍ እንዲሆ የሚጣላው ብር በዛ ያለ ይሆናል፡፡ ይህ ብር ውድቂት ይባላል፡፡ ብሩ የሚሰበሰበውም በአገልግል ወይም በመሶብ ነው ፣ ይህ አገልግል ወይም መሶብ ብሩ ከመጣሉ አስቀድሞ እንጀራ ይደረግበትና በካህን ጸሎት

[37] በዝቋላ ወረዳ አንድ አውራጅ ሁለት ጋን ጠላ፣ አስራ ሁለት ድስት ወጥና 160 እንጀራ ሲሆን የሚስተናገደው ሰው 32 ነው፡፡

ተደርጎበት ለገንዘብ ማሰባሰቢያነት ይዘጋጃል፡፡ እንጀራውም ተቆራርሶ በዳሱ ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች ይታደላል፡፡

ከሰርጉ ታዳሚዎች መካከል አዋጅ ነጋሪና ፀሃፊ የሚሆኑ ሰዎች ይመደባሉ፡፡ አዋጅ ነጋሪ የሰርጉ ታዳሚያን ለደጋሹ የሚሰጡትን ፣ የሚጥሉትን ወይም የሚመርቁትን ብር ከእያንዳንዱ ሰው እየተቀበለ ሳይበዛ የተወሰነ የተወሰነውን የሚያሰባስብ ነው ፤ ይህንን የሚያደርገውም ነጠላውን አጣጥሎ/አጣፍቶ በመልክና በታዳሚዎቹ መካከል በመንቀሳቀስ ነው፡፡ ብር የሚሰጠው ሰው አድራሻው የት እንደሆነ ድምጹን ከፍ አድርጎ በመናገር የተቀበለውን ብር ለሌላ ተረካቢ ሰው ያስረክባል፡፡ አዋጅ ነጋሪ ልምድና ጥሩ ድምፅ ያለው መሆን አለበት፡፡ ማን ምን ያህል ብር እንደጣለ የማስተጋባቱ አዋጅ አስፈላጊነትም እያንዳንዱ ታዳሚ በዚያ ሰርግ ምን ያህል ብር እንደጣለ እንዲታወቅ ነው፡፡ አዋጅ መባሉም ለዚህ ነው፡፡ አዋጅ ነጋሪ መሆን ያለበትም ወንድ ነው፡፡ ምክንያቱም መረጃ አቀባዮቹ ሲገልፁ ‹‹በባህላችን ሴቶች አዋጅ ነጋሪ አይሆንም፡፡ የሚል ነው(ቡ.ቃ.መ 3 እና 5 )፡፡

በሰርግ ላይ የሚጣለው የገንዘብ መጠን እኩል አይደለም፡፡ እንደ ሰው አቅምና እንደቀረቤታቸው ይወሰናል፡፡ ወዳጅና ቤተ ዘመድ የሚጥለው የገንዘብ መጠን ከሌላው የሰርግ ታዳሚ በዛ ያለ ነው፡፡ የመረጃ አቀባዬ የሆነው አቶ ደርበው ታረቀኝ ይህን አስመልክተው ‹‹የጣለው/ለችው ሰው ሲድር/ስትድር ደግሞ ሲሆን ጨምሮ/ሃምሳ ብር ለጣለው ስልሳ ተደርጎ/ካልሆ ደግሞ የሰጠውን ካልተመለሰ ያወቃቅሳል›› ይላሉ (ቁ.መ.አ.1)፡፡



ምስል 17፡- አዋጅ ነጋሪ ገንዘብ ሲሰብስብ (ፎቶ ዋግኽምራ ዞን ባቱ)

ብር የሚጥሉት አብዛኛዎቹ ወንዶች ሲሆኑ ሴቶች ግን በብዛት ብር አይጥሉም፡፡ ሴቶች እንጀራ በመሶብ አሸክመው ወደ ሰርጉ ቤት ይወስዱ ነበር ፤ አሁን አሁን ግን የሚወስዱት ዱቄትና እህል ነው፡፡ ይህም የተጀመረው ከ1980ዎቹ ወዲህ መሆኑንና ምክንያቱም ብክነትን ለመከላከል መሆኑን የመረጃ አቀባዬቹ ገልፀዋል፡፡ ደጋሾቹ ከታዳሚው የሚመጣውን የእንጀራ መጠን ግምት ውስጥ ሳያስገቡ ብዙ እንጀራ ስለሚያስጋግሩና ከታዳሚው በርካታ እንጀራ ስለሚመጣ ብዙ እንጀራ ተበላሽቶ ይቀር ነበር፡፡ ዱቄቱና እህሉ ግን ቢቀመጥም ስለማይበላሽ ደጋሾቹ ወደፊት በሚያስፈልጋቸው ወቅት ሊጠቀሙበት ይችላሉ (ቁ.መ.አ.4 እና 12)፡፡ የዱቄቱ ወይም የእህሉ መጠንም የሚወሰነው ታዳሚዎቹ ለደጋሾቹ ባላቸዉ ቀረቤታ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ሴቶች የሚያመጡትና የሚያስረክቡት በግላቸው ሳይሆን ተሰባስበው በጆንያ /ኬሻ/ወይም አቅማዳ ፣ የማን የማን እንደሆነ በመንገር ነው፡፡ ተረካቢዎቹም የሚመጣውን ዱቄትና እህል እየተቀበሉ ከመዘርገፍ በስተቀር መጠኑን ለክተው ሲቀበሉ አልተመለከትኩም፡፡





ምስል 18:- ወጥ ከተሰራባቸው የሸክላ ድስቶች በከፊል ወንዶች ወጥ ሲሰሩ

**የሰርግ ታዳሚዎች አቀባበልና በዳስ ውስጥ አቀማመጥ**

የሰርግ ታዳሚዎች ወደ ሰርግ ቤት የሚሄዱት እንዳቅማቸው ጸዳ ያለ ልብሳቸውን ለብሰው ነው፡፡ ሴቶቹ ጸጉራቸውን አዲስ ሹሩባ ይሰራሉ ፤ ቅቤ ይቀባሉ ፤ ንጹህ ቀሚሳቸውንና ነጠላቸውን ይለብሳሉ ፤ የክት መቀነታቸውንም ይታጠቃሉ፡፡ እመጫት ከሆኑም በዛጎልና በድባ በተዋበው አንቀልባ ልጆቻቸውን ያዝላሉ፡፡ ወንዶቹም በተለይም በዕድሜ ገፋ ያሉት ሱሪ ይለብሳሉ ፤ ኩታቸውን ይደርባሉ ፤ ወጣቶቹም ቁምጣቸውንና ኳርቶ ሸሚዛቸውን ይለብሳሉ፡፡ የሰርጉ ታዳሚዎች በቀጥታ ሰተት ብለው ወደ ዳሱ አይገቡም ፤ከዳሱ ፊት ለፊት ተደርደርው ይቆማሉ ፤ በዚህ ጊዜ የዳሱ አስተናባሪዎቸች/አጋፋሪዎች ሰላምታ ከሰጧቸው በኃላ ከወንዶቹ የሰርጉ ታዳሚዎች በትራቸውን ፣ ከሴቶቹ ደግሞ ያመጡትን ዱቄት ወይም እህል የተቋጠረበትን ከረጢት በመቀበል ፣ ወንዶቹን በወንድ ቦታ ፣ ሴቶቹን ደግሞ በሴት ቦታ ያስቀምጧቸዋል፡፡ አቀማመጣቸውም እንደ እድሜያቸው ከፍ ያሉት ከፍ ባለ ፣ ዝቅ ያሉት ዝቅ ባለ ቦታ ላይ ነው (አቶ አስራት ታደሰ ፣ ቃመ. 22/08/2010 ዓ.ም)፡፡

ለመቀመጫነት የሚያገለግለውም በረድፍ በረድፍ ሆኖ መሬት ላይ የተደለደለ ገለባ ፣ የማሽላ አገዳ ፣ ከተገኘም አግዳሚ እንጨት ወይም ጣውላ ነው፡፡ ተስተናጋጆች ቦታ ቦታቸውን እንደያዙም በጆንያ የመጠጪያ ፎሌ/ሸክና/ይዘው የሚያስተናግዱ ወጣቶች

ለታዳሚያኑ በማደል ኮረፌ ለሚፈልገው ኮረፌ ዝልል ለሚፈልገው ደግሞ ዝልል ይቀዳሉ፡፡ በአብዛኛው ከምግብ በፊት የሚቀርበው ግን ኮረፌ ነው፡፡ ምክንያቱም "ዝልል ሆድን ይሸረሽራል" ስለሚባል ከምግብ በፊት አይቀርብም፡፡



ምስል 19፡- ዳስ ውስጥ የወንዶች አቀማመጥ በፎሌ/በሽክና ኮረፌ እየጠጡ (ፎቶ ዋግኽምራ ዞን ባቱ)

በዋግኽምራ በሰርግ ድግስ ላይ ሴቶች ፣ ወንዶችና ህፃናት ባንድ ቦታ ላይ አብረው ተቀምጠው አይመገቡም ፤ ሶስቱም ለየብቻ ነው የሚስተናገዱት፡፡ ዳሱ ጠባብ ከሆነ ወንዶች ዳስ ውስጥ ሲስተናገዱ ሴቶችና ህፃናት ደግሞ ከዳስ ውጪ ይስተናገዳሉ፡፡ ከተመለከትኳቸው የሰርግ ድግሶች መካከል ዳሶቻቸው ጠባብ በነበሩባቸው ሰርጎች ወንዶች ዳስ ውስጥ ሆነው ሲመገቡ ሴቶችና ህፃናት የተመገቡት ከዳስ ውጪ ነው፡፡ ሴቶች ለምን ለብቻቸው እንደሚመገቡ አቶ አስራት ታደሰ ሲገልጹ "ምክንያቱም ወንዱ እንጀራውን ወደ አፉ ለመውሰድ እጁ ፈጣን ነው ፤ ሴቶቹ ግን ትንሽ ትንሽ ስለሚቆርሱ እና ቀስ ብለው ስለሚመገቡ ይጎዳሉ ፤ ብዙ እንጀራ ጠቅለል አድርገው እንዳይጎርሱም ወንዶቹን ያፍሯቸዋል" ብለዋል (ቁ.የ.መ.አ.3)፡፡



ምስል 20፡- ሴቶች ሲመገቡ በከፊል

የእንጀራው አቀራረብ ቀደም ሲል በአውራጅ አቀራረብ እንደተመለከተው ነው ፤ ወንድ ባንድ ረድፍ ፣ ሴት በሌላ ረድፍ ተቀምጠው በርካታ እንጀራ በደደሆ ቅጠል ላይ ይደረግና በዛያ ላይ ወጡ እየፈሰሰ ነው፡፡

በሴቷ ዳስ የወንድ ወገን አመጋገብ እና የወጥ አሰራሩም የተለየ ነው፡፡ ወጣቸው የሚሰራውም ፍርምባው ሳይቆራረጥ ተዘልዝሎ በአንድ ላይ ነው፡፡ መጀመሪያ እንዲመገቡ የሚደርጉት ሽማግሌዎቹ ናቸው፡፡ ሽማግሌዎቹ ከተመገቡ በኃላ ሚዜዎች የእነሱን ትራፊ እንጀራ በመጨመር ይመገባሉ፡፡



ምስል 21፡-ለሽማግሌዎች የቀረበ ዝልዝል ፍሪምባ (ፎቶ ሰቆጣ ወረዳ ባቱ)

የልጆች አመጋገብ እንደ እድሜያቸውና ጾታቸው የተለያየ ነው፡፡ ከአምስትና ከስድስት ዓመት በታች ለሚሆኑት ህፃናት እናቶቻቸው አጠገብ ተቀምጠው ይመገባሉ፡፡ ከነሱ ዘለል/ተለቅ/ያሉት ልጆች ግን ወላጆቻቸው ከተመገቡ በኃላ ከተረፈው ላይ ተጨማሪ እንጀራ ፣ የክክ ወጥና እልበት ተደርጎ ሴቶችና ወንዶች ለየብቻ ቀርቦላቸው ይመገባሉ፡፡ እነዚህ ታዳጊዎች ከትርፍራፊው ይቀምሳሉ እንጂ ለብቻቸው የስጋ ወጥ አይቀርብላቸውም፡፡



ምስል 22፡- ልጆች ሲመገቡ በከፊል

### 4.2.3.1. እርግዝናና ልደት

በዋግኽምራ ብሔረሰብ አንዲት ሴት ነፍሰጡር መሆኗ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ የሚደረግላት እንክብካቤና አክብሮት ከፍተኛ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ለነፍሰጡር ሴት የሚያደርገው እንክብካቤ ወይም አክብሮት ነፍሰጡር ከመሆኗ በፊት ከሚደረግላት ለየት ያለ ከመሆኑም በተጨማሪ በጥንቃቄና በርህራሄ ዐይን ነው፡፡ ነፍሰ ጡር ከመሆኗ በፊት በማንኛውም ግላዊና ቡድናዊ ስራ ትሳተፋለች ፣ ነገር ግን ነፍሰጡር መሆኗ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በአረም ፣ በአጨዳ ፣ ወዘተ በመሳሰሉት የህብረት/ወበራ/ስራዎች እንድትሳተፍ አይደረግም፡፡ የሴቶችም የስራ እገዛ የሚጠይቁ በጎረቤት የሰርግ ፣ የክርስትና ፣ የተስካ ር፣ የዝክር ፣ ወዘተ ስራዎች በሚኖሩበት ወቅት ስራ እንድትሰራ አይደረግም፡፡ አቅም ካላትና የመውለጃ ጊዜዋ ካልደረሰ ባትሰራም ብቅ ብላ ትታያለች እንጂ እንድትሰራ አይደረግም (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ፣ ቃመ 18/10/2009 ዓ.ም)፡፡ ቀለል ያሉ ስራዎችን በቤቷ ውስጥ ብታከናውንም እንዳትሰራቸው የምትከለከላቸው የስራ ዓይነቶች አሉ፡፡ እነዚህም በሙቀጫ እህል መውቀጥ ፣ ክብደት ያላቸውን ዕቃዎች እንዳታነሳ ፣ ከባድ የሆኑ ሸክሞችን እንዳትሸከም ትመከራለች ፤ይህንንም እንዳትፈፅም ይከታተሏታል ፣ ይጠብቋታል፡ ፡በሙቀጫ መውቀጥ እንደሌለባት የምትከለከልበት ምክንያት አስመልክተው መረጃ አቀባዬ የሚከተለውን ገልፀውልኛል፡

> ሙቀጫ መውቀጥ የለባትም ፤ ምክንያቱም ስትወቅጥ የህፃኑ ጭንቅላት ያብጥና በምጥ ጊዜ እናትየዋ እንድትቸገር ያደርጋታል ይባላል፡፡ በመስከረም ተልባ ነቀላ ስራ ላይ መሳተፍ የለባትም ይባላል ፤ምክንያቱም መሬቱ ሞቃት ስለሆነ በማህፀኗ በኩል ምች ይመታትና ለአደጋ ትጋለጣለች ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህም አባባል ብቻ ሳይሆን እኔ እራሴ ነፍሰጡር ሴቶች ሲጋለጡ አይቻለሁ፡፡ በመስከረም መሬቱ ርጥበቱ ስለማይደርቅ እንፋሎቱ ወደላይ ስለሚጨስና ስመሚጎንፋት ነፍሰ ጡሯ ህይወቷን የምታጣባት አልያም ፅንሱ የሚጨነግፍበት አጋጣሚ አለ (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ቃመ 18/10/2009 ዓ.ም)፡፡

ስለሆነም ለነፍሰጡሯም ሆነ ለፅንሱ እንክብካቤ የሚደረገው በግሏ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የማህበረሰቡ አባላት ትብብር ጭምር ነው ፤ በተለይ ‹‹ይህን ስሪ ይህንን አትስሪ›› የሚሉ ልምድ ያላቸው እናቶች እገዛና ምክር ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል፡፡

አንዲት ሴት ነፍሰጡር መሆኗን ካወቀች ማጥባት የለባትም፡፡ ይህን ክልከላ አስመልክተው የልምድ አዋላጅ የሆኑት መረጃ አቀባዪ ምክንያቱን እንደሚከተለው ገልጸውልኛል፡-

> ነፍሰጡር ሴት ማጥባት የለባትም ፣ ወተቱ ለሚጠባው ህፃን ደግ አይደለም ፤ ምክንያቱም የሚጠባው ህፃን ሆዱ ይነፋል ፤ ማለትም ይቆዘራል ፣ ተቅማጥም ይይዘዋል ፣ ይጎዳል፡፡ ፅንሱም ይቀጭጫል፡፡ ስለዚህ ጡት ያልጣለ/ያላቆመ/ህፃን የያዘች እናት/ሴት/ በላዩ ላይ ከፀነሰች የሚጠባውን ህፃን ጡት እንዲተው ማድረግ አለባት፡፡ ስለዚህ ጡት ለማስጣል ስንዴ ቆሎ በመቁላት የእናትየዋን ጡት ወተት ከላይ በማፍሰስ ‹‹እርም ነው›› ሲባል ይተዋል፡፡ አንዳንድ እናቶች የጡቱን ጫፍ እሬት የሚቀቡም አሉ፡፡ ይህም ሲመረው ይተዋል በሚል ነው (ወ/ሮ አለምነሽ በላይ ቃመ. 20/08/2010 ዓ.ም)፡፡

በዚህ ምክንያት ነፍሰጡር ሴት ከፀነሰች እስከ ሶስት ወር ድረስ እንድታጠባ ሲደረግ ከዚያ በኃላ ግን ህፃኑ ለመጥባት ፈልጎ ጡቷን አለቅ ቢልም የግድ ታስጥለዋለች፡፡

ነፍሰጡር ሴት እንዳትበላ የምትከለከላቸው የምግብ ዓይነቶችም አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ሰናፍጭ አንዱ ነው ፤ ሰናፍጭ እንዳትበላ የምትከለከለው ፅንሱን ለውርጃ ስለሚዳርግ ነው (ቃመ. 20/08/2010 ዓ.ም)፡፡ነፍሰጡር ሴት አረቄም አትጠጣም ፤ አረቄ ጠንካራ መጠጥ ስለሆነ ፅንሱን ይጎዳዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ የስንዴ ፣ የሽንብራ ቆሎና ሽምብራ እሸትም እንዳትበላ ትከለከላለች ፤ ምክንያቱም እነዚህን ከበላች ከወሊድ በኃላ ጭራም የሚባል ከባድ የሆድ ቁርጠት አለና እሱ እንዳያማት ነው፡፡ ከነዚህም ሌላ እርጉዝ ሴት የመውለጃዋ ጊዜ ሲቃረብ ደግሞ ድፍድፍና ገንፎ እንዳትበላ ትከለከላለች፡፡ የምትከለከልበት ምክንያትም ድፍድፍና ገንፎ ከህፃን ጭንቅላት ተለጥሮ ይገኛል ተብሎ ስለሚታመን ነው (ቡ.ቃ 4/09/2011 ዓ.ም)፡፡ ሌሎች መረጃ አቀባዬቼ ደግሞ ነፍሰጡር አንድን ምግብ መብላት ሲያስጠላት ብቻ ነው እንጂ ሁሉንም የምግብ ዓይነቶች ልትበላ ትችላለች ፤ ነገር ግን የስንዴ ቆሎና ያልበሰለ ነገር መብላት የለባትም ለፅንሱ ደግ አይደለም ፤ በምጥ ወቅትም ያስቸግራታል የሚል መልስ ሰጥተውኛል፡፡ እነዚህ ሴቶች ነፍሰጡር ሴት እንዳትበላና እንዳትጠጣ የምትከለከላቸውን የምግብ ዓይነቶች ሲገልፁም ጠላ ፣ አንት ፣ ቂቤ የመሳሰሉት መሆናቸውን ገልፀዋል (ቡ.ቃ 20/10/2011 ዓ.ም)፡፡ በአንድ አካባቢዎች ደግሞ ነፍሰጡር ቃሪያና አገዳ/ጥንቅሽ አገዳ/ ሸንኮራ/ እንዳትበላ

ትከለከላለች ፤ ለዚህም ምክንያቱ ቃሪያው ፅንሱን እንዳያቃጥለው ሲሆን አገዳው ደግሞ የሚወለደው ልጅ ልጋግ የሚያንጠባጥብ እንዳይሆን ነው ያሉ የመረጃ አቀባዬች አሉ (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ቁ.መ.አ. 18/10/2011 ዓ.ም ፣ ወ/ሮ መሰረት አጠና ፣ ቃመ (19/10/2011 ዓ.ም)፡፡

ለአንዲት ነፍሰጡር ሴት በቅድመ ወሊድ የሚደረግላትን እንክብካቤና ለእሷና ለፅንሱ ደህንነት ሲባል እንዳትሰራ የምትከለከላቸውን ስራዎችና እንዳትበላ የሚደርጉ የምግብ ዓይነቶችን አይተናል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ በወሊድ ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራትን እንመልከት፡፡ አንዲት ሴት የመውለጃ ቀኗ መቃረቡን ካወቀች ምጡ ሳይጀምራት በፊት የምታደርጋቸውን ተግባራት ወ/ሮ መሰረት አጠና እንዲህ ይገልጹታል፡-

> ነፍሰጡሯ የመውለጃ ቀኗ መቃረቡን ካወቀች ምጡ ሳይጀምራት ፀጉሯን ሹሩባ ትሰራለች ፣ ቅቤ ትቀባለች ሀብት ያለት ከሆነችም እናቷ ብዙ ቅቤ ታስቀምጣለች፡፡ የመውለጃ መደቧንም ታፀዳዳለች ፣ ለምኝታዋም ከቆዳ የተዘጋጀውን ምንጣፍ/ነት/ ታመቻቻለች ፣ በቤቷ ውስጥ የሚገኙትን ዕቃዎች እሳት በማንደድ ቤቱ ሙቀት እንዲኖረው ያደርጋሉ፡፡ ቡናም ይፈላል፡፡ ምጡ ሊጀምራት ሲልም የቅርብ ቤተሰቦች ፣ የልምድ አዋላጅና ጎረቤቶች እንዲጠሩ ይደረጋል፡፡ አስቀድማ ባዘጋጀችው ምንጣፍ ላይ በጉልበቷ በመንበርከክ የልምድ አዋላጅዋ በግርጌዋ ፣ የቅርብ ዘመድ የሆኑ ሴቶች በህይወት ካለችም እናቷ ደግሞ በራስጌዋ በመሆኑ የልጁን መምጣት ይጠባበቃሉ፡፡ በአጠገቧ እንዲገኙ ወይም ምጥ ወደ ያዛት ሴት ቤት እንዲገቡ የሚፈቀድላቸው የወለዱ ሴቶች ብቻ ናቸው፡፡ ገና ያልወለደች እና መካን የሆነች ሴት ወደ ቤት መግባትም ሆነ አጠገቧ እንድትደርስ አይፈቀድላትም፡፡ ለዚህም ምክንያቱም በማህበረሰቡ ባህል ያልወለዱ ሴቶች ድፍን ቅሎች ናቸው ተብሎ ይታመናል (ቃመ. 20/10/2010 ዓ.ም)፡፡

ያልወለደች ወይም መካን ሴት የምጥን ጭንቀትና ስቃይ ስላልቀመሰች አሁንም የጭንቀቱ ተካፋይ ሆና የምጡ ጊዜ እንዲያጥርና ምጥ የተያዘችው ሴት ቶሎ እንድትወልድ ልታደርግ አትችልም ተብሎም ይታመናል፡፡ በምጥ ወቅት ሴቶች መቀነታቸውን ፣ ውጪ የሚገኙት ወንዶች ደግሞ ቀበቷቸውን እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡ የተቆለፈ ሳጥን ካለም እንዲከፈት ይደረጋል ፤ ምጡ ከዘገየ ቀይ ወንድ ዶሮ በነፍሰጡሯ

በማዞር ይታረድና በነፍሰ ጡሯ ጀርባ ላይ ደም እንዲፈስ ይደረጋል፡፡ ባልዬውንም ቀበቶህን አላላ ፣ ተንቀሳቀስ ይባላል፡፡ እሱም እስከሚደክመው ድረስ ይሮጣል፡፡ ይህም ፅንሱ ይገላበጥና ምጡ እንዲቀልና ሚስትየዋ ቶሎ እንድትወልድ የሚያደርግ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ሴቶችም ባንድ ቦታ ላይ ዝም ብለው መቀመጥ የለባቸውም ፤መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡ በጉልበታቸው ተንበርክከው "ማርያም ማርያም" በማለት ማርያም በሰላም እንድታገላግላት በጭንቀት ይለምናሉ ፤ ይማፀናሉ (መ/ት ወርቃፈራሁ ቾኮል ቁ.መ.አ 21/09/10 ዓ.ም)፡፡ በዚህ መልክ በፀሎትም በምልጃም ተብሎ ነፍሰጡሯ ልጇን በሰላም ትገላገላለች፡፡ አራሷ በሌሎች ሰዎች እየተጠበቀች የምትቆየው እንደ አቅሟና የአራሷ ቤተሰብ ሁኔታ ነው፡፡ አንዳንዶቹ በሰባት ቀናቸው የሚነሱ አሉ ፤ እስከ አስራ ሁለት ቀን ድረስ የሚቆዩም አሉ ወርቃፈራሁ ፣ ቁ.የ.መ.አ 1)፡፡ በአራስ ቤት ርኩስ መንፈስ እንዳይቀርባት ተብሎ መጥፎ ጠረን ያለው ስራስር በአዲስ ቅል እንዲዘፈዘፍ ይደረግና ከበር ላይ እንዲሰቀል ይደረጋል፡፡ ስራስሩም የሚዘጋጀው በወንድ ነው፣ ሴት ልትነካው አይገባም፡፡ እስከ ሰባት ቀን ከአራስ ቤት እሳት አይጫርም ፤ ምክንያቱም ከተጫረ ልጁ ጨቅጫቃ ይሆናል ተብሎ ይታመናል (ቁ.መ.አ.1)፡፡

በዋግኽምራ ወንድ ሲወለድ ሰባት ጊዜ ሴት ስትወለድ ደግሞ ሶስት ጊዜ እልል ይባላል፡፡ የእልልታው መጠንም ከሴት ይልቅ ለወንድ ልጅ ከፍተኛ ስለመሆኑ በመረጃ አቀባዩቹ የተገለፀውም ምክንያት የተለያየ ነው፡፡ አቶ ደርበው ታረቀኝ ይህንን አስመልክተው የሰጡኝ አስተያየት "ቀደም ሲል በብሔረሰቡ ወንዶች በዋግሹምነት ፣ በፊታውራሪነት ፣ በቀኛዝማችነት ማዕረግ በአስተዳደር ስራ ላይ በመሾም ህዝቡን ያስተዳድሩ ፣ ይፈርዱ ይቀድሱ ስለነበር ወንዶች ፍርድ ይችላሉ ፤ ከሴቶች የበለጠ ናቸው የሚል አመለካከት ስለነበር ከዚህ ጋር ተያይዞ የመጣ ይመስለኛል፡፡ ምንም ሴት ብልህና አዋቂ ብትሆን ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ" የሚባለው የአባቶቻችን አባባል ዕውቅናውን ለወንዶች የሚሰጥ ስለሆነ ከዚህ ጋር ተያይዞ የመጣ ሳይሆን አይቀርም የእልልታውም ቁጥር መጨመሩ (ቁ.መ.አ.18/10/2010 ዓ.ም)በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ሌሎች መረጃ አቀባዬች ደግሞ ወንድ ሩቅ ቦታ የሚሄድና ወንዝ የሚሻገር ጠንካራ ነው ፤ ሴት ግን ብቻዋን ወንዝ መሻገር ስለማትችል ነው (መ/ት ወርቃፈራሁ ፣ ቁ.መ.አ 20/10/10 ዓ.ም)፡፡ ወ/ሮ ተወዳጅ ወ/ኪዳን የተባሉ የሰባ ዓመት ዕድሜ ባለፀጋ የሰቆጣ ከተማ ነዋሪ

እናት የእልልታው መጠን የተለያየው ከአባቶቻችንና ከእናቶቻችን የወረስነው ባህል ስለሆነ ነው (ቃመ 18/10/2010 ዓ.ም)በማለት ይገልፃሉ፡፡

በብሔረሰቡ ዘንድ ከሴት እናቶች ይልቅ ለወንድ እናቶች የሚሰጠው አክብሮት ላቅ ያለ ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ እንደ መረጃ አቀባዬቼ "ሴት ስታገባ ለወንድ ቤተሰብ ስጦታ ይዛ የምትሄድ ናት ፤ ወንድ ግን በጋብቻው ወቅት ለእናት አባቱ በሬ ወይም በቅሎ የመሳሰሉትን ንብረቶች ወይም ብር የሚያመጣ ነው" (ቡ.ቃ.4)፡፡ ይህንን አስመልክተው የሃይማኖት አባቶች በማህበረሰቡ ያለውን አስተሳሰብ እንዲህ ይገልፃሉ "እከሌ ወንድ ልጅ ወለደ ሲባል በቤት ውስጥ የሴት ልጅ ጥቅም እና አገልግሎት ቢበልጥም ፣ ወንድ ልጅ በውጭ በእርሻ ስራ ስለሚያግዝ በወንድ ልጅ የመከበር የመታፈር ፣ ሴትን ግን አሳንሶ የማየት ሁኔታ ስለነበር ነው፡፡ ይህንን አስተሳሰብ ይዘውት ዛሬም ድረስ ቆይቷል፡ ፡ በእምነታችን በሃይማኖት ግን ሁሉም እኩል ነው" (ቄስ ደምሴ መኮንን ፣ ቃመ.18/10/2010 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ በላይ ከተገለፀው ለመረዳት እንደተቻለው በማህበረሰቡ ዘንድ ለወንድ ልጅ ከፍተኛ የሆነ ክብርና ቦታ የሚሰጡ መሆኑን ነው፡፡ ይህም በደስታ መግለጫቸው በሆነው እልልታ በሚሰማበት ጊዜ የተወለደችው/ደው ወንድ ወይም ሴት መሆኑን/ኗን በእልልታው ድግግሞሽ ብዛት ይለዩታል፡፡ በመሆኑም በወሊድ ጊዜው በቦታው ያልነበረው ሁሉ የተወለደው/ችው ህፃን ፆታውን /ዋን ይለያል፡፡

## 4.2.3.2 አራስን መጠየቅ ፣ ግርዛት እና የስም አወጣጥ

የወለደችውን ሴት/አራስ መጠየቅ በብሔረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ማህበራዊ ግዴታ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ለመጠየቅ ወደ አራሷ ቤት የሚመጡ ወይም ወደ ቤት የሚገቡ ሰዎች በብሔረሰቡ ዘንድ የሚታወቀውን አባባል "ማርያም ዋርዝና" ወይም "ማርያም ታጫውትሽ" ፣ ወይም  እንኳን ሁለት ራስሽን አደረገችሽ› ይላሉ፡፡ ጠይቀዋት ሲመለሱም ወይም  ሲወጡ ደግሞ "ሞልቶ ዳስ ያድርገን" ማርያም ጭንሽን ታሙቀው የምታዝይው ያድርገው ይላሉ፡፡ አራሷን የሚጠይቁ ሴቶችም ለአራሷ ምግብና መጠጥ ያመጡላታል፡፡ የሚወስዱትም በቅርብ የሚገኙ ጎረቤቶች ከሆኑ ገንፎ በስልስ ወጥ እንጀራ ሲሆን ራቅ ካለ ቦታ የሚመጡት ደግሞ እንደቀረቤታቸው የፀጉር ቅቤ፣

ትኩሴ/ድፎ ዳቦ/እና አንባሻ ነው፡፡ የሚጠጣ ከሆነ ደግሞ ያላቸው ወተት ፣ ከሌላቸው ኮረፌ በመውሰድ ይጠይቋታል (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል፣ ቂ.መ.አ. 20/10/10 ዓ.ም)፡፡

በብሔረሰቡ ሴቶች ዘንድ ለአንዷት አራስ የሚያደርጉት ተግባር ልብሷን በጋራ ወደ ወንዝ ይዘው ሄደው ማጠብ ነው፡፡ የአራሷ ልብስ የሚታጠብበትን ሁኔታ አስመልክተው መረጃ አቀባዩ የሚከተለውን ገልፀውልኛል፡፡

> የአራስ ሴት ልብስ በጎረቤቶቿና በሌሎች ሴቶች የሚታጠበው ሁለት ጊዜ ነው፡፡ በወለደች በሶስተኛውና በሰባተኛው ቀን ፤ ደም የነካውን የአራሷ ልብስ በሶስተኛው ቀን የሚታጠብበት የልብስ አጠባ ‹‹የስርቆት አጠባ›› ይባላል ፤ የሰርቆት አጠባ የተባለበትም ማርያም የማትወደው አጠባ ስለሆነ ነው፡፡ በዚህ የልብስ አጠባ ላይ የሚሳተፉት የአራሷ እናት ፣ እህት እና አያት ናቸው፡፡ በቁጥር የተወሰኑ የቅርብ ዘመዶችና ጎረቤቶች ናቸው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የሚታጠበው ልብስ ደም የነካ ስለሆነ ቤተ ዘመድ ያልሆኑት ለማጠብ እንዳይጠየፉ በማለት ነው ፤ ልብስ አጣቢዎቹ ወደ ወንዝ ሲሄዱ ሌሎች ሴቶች እንዳይሰሙ ድምፅ ሳያሰሙ ፀጥ ብለው ይሄዳሉ በእጃቸው ማጭድ ወይም ቢላዋም ይይዛሉ፡፡ በሰባተኛው ቀን የልብስ አጠባ ላይ ግን የአራሷ ቤተሰቦች ብቻ ሳይሆኑ ጎረቤቶችና ሌሎችም ይሳተፉበታል፡፡ የሰባተኛው ቀን አጠባ መሆኑን ለሌሎች ለማስታወስ እና ጥሪ ለማድረግና ወደ ወንዝ እየሄዱ መሆናቸውን ለማሳወቅም ከቤት ሲወጡ ጀምሮ ወንዙ እስከሚደርሱ ድረስ ‹‹እልል›› ይላሉ፡፡ በዚህ ወቅትም ቢላዋ ፣ ብረት ነገር ይያዛል፡፡ የተወሰኑት ሴቶች ወደ ወንዝ ሲሄዱ የተወሰኑት እቤት ቀርተው ገንፎ ያገነፋሉ፡፡ ሴቶቹ ልብሱን አጥበውወደ ቤት ሲመለሱ ይዘውት የሚመጡት ነገር የተወለደችው ሴት ከሆነች ወደፊት ጎጆ ስትወጣ ከቤተሰቦቿ የምትወስዳቸውን እንዝርት ፣ ወንፊትና ፣ ማንዘርዘሪያ ፣ ቅል ፣ ሙዳይ ፤ የተወለደው ወንድ ከሆነ ደግሞ ጠብመንጃ ፣ ከእርሻ መሳሪያዎች ቀንበር ፣ ማረሻ ፣ በአካባቢው ካገኙት ስራስር ፣ ልጥ ፣ ቅጠል ወዘተ አስመስለው በመስራት ያመጣሉ (ወ/ሮ ተወዳጅ ወ/ኪዳን ፣ ቃመ 23/10/2010 ዓ.ም)፡፡

እነዚህ ቁሳቁሶች እንደየ ፆታቸው ተለይተው የመጡ ናቸው፡፡ ዕቃዎቹም ህፃኑ ወይም ህጻኗ ወደፊት በምን ዓይነት ሙያ ላይ ሊሳተፉ እንደሚችሉ መተንበያ ናቸው፡፡

ሴቶቹ ልብስ አጥበው ሲመለሱም እስከ አራሷ ቤት ድስ ያለማቋረጥ “እልል” ይላሉ፡፡ አራሷንም “ከመኝታሽ ተነሽ ውጪውን እይ” ይሏታል፡፡ አጣቢዎቹ እንደ ተመለሱም አራሷ ካላት በቅቤ ከሌላት በአካባቢው በሚዘጋጀው ቅባኑግ በሰሊጥ ወይም በተልባ ልጥልጥ በትልቅ ሳህን ወይም ቅባት በጠገበ ገበታ በጋራ ገንፎውን ይበላሉ ፣ ለአራሷም ለብቻዋ ይሰጧታል፡፡ ከዚያም ወደ ደጅ ወጥታ እራሷ ልብሾቿን ታጥባለች (ወ/ሮ ተወዳጅ ወልደኪዳን ቃመ 23/10/2010 ዓ.ም)፡፡

**ግርዛት**

በዋግኽምራ ብሔረሰብ የሕፃናት የግርዛት ጊዜ ወጥነት የለውም፡፡ በደጋውና በቆላው አካባቢ የተለያየ ነው፡፡ በደጋው አካባቢ ሴትም ወንድም የሚገረዙት በተወለዱ በሰባተኛው ቀን ነው፡፡ ይህንን አስመልክተው መረጃ አቀባዩቼ እንደሚከተለው ገልፀውልኛል፡፡

> ሰነፍ እናትና አባት ካልሆኑ በስተቀር ግርዛቱ ከሰባት ቀን ማለፍ የለበትም ፣ ለዚህ ምክንያቱም የህፃናቱ ቆዳ እንዳይገረዝዝና ነፍስ አውቆ ቁስሉን እየነካካ ማልቀስ ከጀመረ ወደፊትም አልቃሻ ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ በግርዛት ጊዜም ሶስት ትንንሽ ቂጣ ይጋገርና ቁስሉን በትኩስ ቂጣ ተኮስ ተኮስ አድርጎ ለውሻ ይሰጣል፡፡ “የውሻ ቁስል ያድርግልህ/ሽ” ይባላል፡፡ ውሻው ቂጣውን ከበላው ቁስሉ ቶሎ ይድናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚያ ልብስ ባልተለበሰበት ባዶ ጫንቃ ላይ ይታዘላሉ፡፡ ይህም ሽንታቸው ቁስሉን እንዲያደርቅ ያደርጋል ተብሎ ስለሚታመን ነው (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ቃመ 20/10/2010 ዓ.ም እና ወ/ሮ ተወዳጅ ወ/ኪዳን ቃመ 23/10/2010 ዓ.ም)፡፡

የቆላውን በሚመለከት ወ/ሮ ህዳጋ መስፍን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> በቆላው ቋሚ የግርዛት ቀን የለም ፤ ፍየል ለመጠበቅ እስከሚበቃ ይቆያል፡፡ የቻለም በሰባት ቀን ሊያስገርዝ ይችላል፡፡ ቁስሉ ቶሎ እንዲድን ቀቀባ የምትባል ቅጠል ቀጥቅጠን ፣ ጨምቀንና ኩል ደቁሰን ቁስሉ ላይ ይተመተማል የፍየል ቅልጥም መቅኔም ከቁስሉ ላይ እንቀባለን፡፡ ይህም ቁስሉን ቶሎ እንዲደርቅ ያደርጋል ፤ በአካባቢያችን የግርዛት ድግስ ቀድሞም የለም አሁንም የለም (ቃመ 16/10/10 ዓ.ም)፡፡

ከላይ እንደተገለፀው በዝቋላ ወረዳ ሴትም ወንድም የሚገረዙ ሲሆን ቋሚ ወይም የተወሰነ ቀን ግን የለውም። ሴቶች አይገረዙም እየተባለ በመንግስት ቢከለከልም እንዲገረዙ የምናደርገው ካልተገረዙ ሲያድጉ እቃ ይሰብራሉ ፣ ባህሪያቸውም መጥፎ ይሆናል የሚል እምነት በባህላችን ስላለ ነው። ስለዚህ ያባቶቻችንና የእናቶቻችንን ልማድ ለመጠበቅ ስንል ሴት ልጃችን በድብቅ ማስገረዛችንን አልተውንም (ወ/ሮ ህዳጋ መስፍን ቃመ 16/10/10 ዓ.ም)።

**የስም አወጣጥ**

በዋግኽምራ የህፃኑ/ኗ ስም እከሌ ነው ብሎ ለቤተሰብ ከመግለፅ ውጭ የተለየ የስም አወጣጥ ስርዓት /ልምድ አይከናወንም። ይህንን አስመልክተው ቁልፍ የመረጃ አቀባዩ የሆኑት አቶ ደርበው ታረቀኝ እንዲህ ይገልፃሉ፡

> ለህፃኑ/ኗ አለማዊ ስም ለማውጣት የተለየ ጊዜና ዝግጅት በእኛ ባህል የለም። የሚወጣው ስም ግን ዝም ብሎ በዘፈቀደ አይደለም ፤ መነሻ ምክንያት አለው ፤ ከነዚህ ምክንያቶች መካከል ልጁ/ልጇ ሲወለድ/ስትወለድ ቤተሰቦቹ/ቿ ከሚያጋጥማቸው ሁኔታ ጋር ተቆራኝቶ የልጁ መወለድ በቤተሰቦቹ ላይ ያሳደረውን ስሜት መነሻ ተደርጎ ፣ የሟችም ሆነ በህይወት ያሉ ቤተሰቦችን ስም ለማውሳት ወይም የመልክ ተመሳሳይነት ለመጠቆም ተፈልጎ ፣ ልጅ አላድግላቸው ብሎ እንደነበር ለማስታወስ ፣ ወዘተ መጥቀስ ይቻላል። ልጅ ወልደው በተከታታይ ሲሞትባቸው ኖሮ አሁን የተወለደውን በአብዛኛው ካሳ ፣ ካሳወይ ፣ ደባሽ ፣ ደባሱ ፣ አስረስ፣ ማስረሻ ፣ መርሻ ፣ አወጣ ፣ አወጡ ይሏቸዋል። እናት ከገበያ ውላ ስትመለስ የተወለደን ገብያነሽ ፣ ገበያው ፣ ቤተሰቦች ከመጥፎ ዘመን ወደ ጥሩ ዘመን ሲሸጋገሩ የተወለዱትን መለስ ፣ መላሱ ፣ ጥጋቡ ፣ ሙላቱ ፣ ሙሉ ፣ በብሔረሰቡ ለቀይ ልጅ ከሚሰጡ ስሞች መካከል ስንዴ ውሃ ፣ ስንዴ ወይ ፣ ጸሃዩ ፣ ጸሃይነሽ ፣ የሚሉ ስሞች ይወጣላቸዋል (ቁ.መ.አ. 20/10/2009 ዓ.ም)።

አቶ ደርበው አክለው በቆላው አካባቢ ስም የሚወጣው በተክቶ ማውጣት ነው። ይህንንም ሲያብራሩ፡-

በቆላው አካባቢ ህጻኑ የመጀመሪያ ልጅ ከሆነ ወይም ከሆነች ስም የሚወጣው በተከቶ ማውጣት ነው፡፡ ወንድ ልጅ ከሆነ የአባት የወንድ ወገን ስም ይወጣለታል ፣ አለማዊ ስሙም የክርስትና ስሙም የወንድ ወገኑ ስም ይሆናል ፤ ሴት ከሆነች ደግሞ የእናት ሴት ወገን ስም ይወጣላታል ፤ የእሷ የአለማዊውም ሆነ የክርስትና ስሟ የእናቷ ወገን ስም ይሆናል፡፡ የሚሰጠውም ስም በህይወት ያሉ ወይም የሌሉ ሊሆን ይችላል (ቁ.መ.አ. 20/10/2010 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ አሰያየም ለመገንዘብ የሚቻለው የእናት ወገን ስም ለመጀመሪያ ሴት ልጅ ፣ የአባት ወገን ስም ደግሞ ለመጀመሪያ ወንድ ልጅ በመስጠት አባትና እናት ወላጆቻቸዉን ወይም ወገኖቻቸውን በልጆቻቸው አማካኝነት ሲወሱ እንዲኖሩ ለማድረግ መቻላቸውን ነው፡፡ ይህም የቤተሰቦቻቸው ስም እንዳይረሳ ፣ እንዳይጠፋ ቀጣይነት እንዲኖረው አድርገው መትከላቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

### 4.2.4 ሞትና የሀዘን ስርዓት

በዚህ ንኡስ ምዕራፍ የሚቀርበው የዋግኽምራ ዞን የሞት ስርዓት ገለፃ ነው፡፡ በመሆኑም ብሔረሰቡ ስለሞት ያለው እይታ የቀብር የሀዘን ክዋኔ በምን ዓይነት አውድ እንደሚከወን ይቀርባል፡፡

#### 4.2.4.1. ብሔረሰቡ ስለሞት ያለው እይታ

የዋግኽምራ ብሔረሰብ ቀደም ብሎ በምዕራፍ አንድ እንደተገለፀው የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ ነው ፤ ይሁን እንጂ አብዛኛውን ለሞት ያለው እይታ ግን ከእምነቱና ቅኖና የተለየ ነው፡፡ አብዛኛው ሰው ‹‹በሰማይ ህይወት አለ›› ሲባል ቢሰማም ሞትን የሚረዳው ግን ከዚህ በተለየ ሁኔታ ነው፡፡ ይኼውም ዘላለማዊ እረፍትና መለየት ነው ብሎ ያምናል፡፡ ሞቱንም የስጋ ብቻ ሳይሆን የነፍስም ነው ብሎ ያምናል፡፡ በዚህም ምክንያት ሀዘኑ የመረረ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን የምታወግዘውን ሴቷ ሹሩባዋን መንቀል እና ፊቷን መላጥ ወይም ማቁሰል ፤ ወንዱም ፊቱን መላጥ ወይም ማቁሰል የተለመደ ተግባር ነው፡፡ ይህንን ተግባር መፈጸም እንደሌለባቸው የእምነቱ አባቶች ቢመክሩም ፣ ቢገስጹም የአብዛኛው ማህበረሰብ አመለካከት የሚለወጥ አልሆነም፡፡ የእምነቱ መሪዎች ሞት ከምድራዊው አለም ወደ ሰማያዊ መንግዝ መሆኑንና ጸጉር መንጨትና ፊት

መላጥ አስፈላጊ አለመሆኑን ቢያስተምሩም ሊቀበሏቸዉ አለመቻላቸውን ገልጸዋል (ቄስ ደምሴ መኮንን ቃመ 20/10/2010 ዓ.ም)፡፡

በዋግኽምራ ብሄረሰብ ‹‹አገሌ ሞቷል እና የቀብሩ ቦታ በዚህ ቦታ ነውና ሄዳችሁ እንድትቀብሩ›› ብሎ የሚያሳውቅ የእድር ለፋፊ የለም፡፡ በብሄረሰቡ በሞት እና በሀዘን አስገዳጅ የሆነ ተቋም ወይም እድር የለም፡፡ በብሄረሰቡ እድር የሚወደድም አይመስልም፡ ፡ ይህንንም አስመልክተው ቁልፍ የመረጃ አቀባዩ የሆኑት ለአብነት ይሆን ዘንድ የሚከተለውን ቃል ግጥም ጠቅሰውልኛል፡-

አዙረህ አዙረህ ካገሬ መልሰኝ

በሹም የታዘዘ አፈር አታልብሰኝ፡፡ (አቶ ደርበው ታረቀኝ ቃመ 20/10/2010 ዓ.ም)፡፡

ብሔረሰቡ ስለ እድር ያለውን አመለካከት በሚገልጽ መንገድ በባህላዊ ዘፋኞች ዘንድ በተደጋጋሚ ይገጠማል፡፡ የቃል ግጥሙ ጭብጥ አንድ ሰው ሲሞት ሰዎች ወደ ቀብር ቦታው መሄድ ያለባቸው በራሳቸው ፈቃድ ተነሳስተው እንጂ በሌላ ጎትጓች (የእድር ለፋፊ) ታዘው መሆን የለበትም የሚል ነው፡፡ ሰውን ያህል ፍጡር ከዚህ ዓለም ሲለይና ሲነጠለን "ሞቷልና ውጡና ቅበሩ" ተብሎ እንዴት ይነገራል እንኳን ሰው ይቅርና የቤት እንስሳ እንኳን መሞቱን የሰሙ/ያወቁ/ ቤተሰቦች ፣ ጎረቤቶች የቤተክርስቲያን ደወል ያስደውላሉ ወይም ይደውላሉ ፣ የሰማም ሰው ያለወቅቱ በመደወሉ ሰው መሞቱን ይረዳል፡፡ ከዚያም ሲወጡ ተጠያይቀዉ ሁሉም ዘመዴ ነው ፣ ወገኔ ነው ሳይል አልቅሶ ይቀብራል እንጂ በአስገዳጅ ውጡ ቅበሩ ማለት በእኛ የሚወደድ አይደለም ፤ እስካሁን ድረስ ይህ ቅሬ/እድር የሚባለውን አልተቀበልነውም በማለት ገልጸዋል (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ቃመ. 18/10/2009 ዓ.ም)፡፡ ማህበረሰቡ እድር አይኑረው እንጂ የቀብርና የማስተዛዘን ባህላዊ ስነ ስርዓት አለው፡፡

## 4.2.4.2. የቀብርና የሀዘን ሥርዓት

ሞት በተለያየ ምክንያት ሊከሰት ይችላል ፤ በእርጅና ፣ በአደጋ ፣ በህመም ፣ ራስን በማጥፋት ወዘተ፡፡ በህመም ሲሰቃይ የቆየ ሰው ወደ ሞት እያመራ ወይም ጣዕረ ሞት ላይ መሆኑን የሚያመለክቱ ምልክቶች አሉ፡፡ እነዚህን ምልክቶች አስመልክተው አቶ

ደርበው ታረቀኝ እንዲህ ይገልፁታል ‹‹ጣዕረ ሞት ላይ የሚገኝ ታማሚ ሰው አተነፋፈሱ ወደ ላይ ወደ ላይ ነው ፤ በመጨረሻ ግን ህቅ ሳይል ነፍሱ አትወጣም ፤ ስለዚህ አስታማሚዎች በዚህ ምልክት ሰውየው እንደሚሞት ያውቃሉ›› (ቁ.መ.አ 18/10/2010 ዓ.ም)፡፡

አንድ ሰው መሞቱን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች ከታዩበትና በመድከም ላይ ከሆነ የነፍስ አባት ወይም በአቅራቢያው የሚገኝ ቄስና ሌሎች ሁለት ምስክሮች በተገኙበት ሀብትና ንብረቱን በሚመለከት እንዲናዘዝ ያደርጋል፡፡ የኑዛዜውን አስፈላጊነት በተመለከተ መረጃ አቀባዬቹ እንዲህ ገልፀውልኛል “ከሞተ በኃላ ቤተሰቦቹ ለጭቅጭቅና ለጥላቻ እንዳይዳረጉ ነው፡፡ ሳይናዘዝ ከሞተ ‘እኔም ያገባኛል! ከሀብቱ መካፈል አለብኝ’ የሚለው ይበዛል፡፡ ለማቹ ቅርበት ያለው ቤተ ዘመድ ሁሉ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በዚህም ከፍተኛ ጠብና ክርክር ይፈጠራል፡፡ ስለሆነም ይህንን ለማስቀረት ሟቹ ከመሞቱ በፊት ኑዛዜውን በትክክል ይገልጹልኛል የሚላቸውን ዘመዶችና ጎረቤቶች ተጠርተው የኑዛዜውን ቃል ያፈሳል፡፡ ሚስትና ልጆችም ገብተዉ ኑዛዜዉን ያዳምጣሉ፡፡የኑዛዜዉን ቃል የሚፅፍ ካልተገኘ ኑዛዜዉን በቃል ይፈፀማል” (አቶ ደርበዉ ታረቀኝ ቃመ.18/10/2009 ዓ.ም)፡፡ በድንገትም ሆነ በህመም ሲሰቃይ የነበረ ሰዉ ሲሞት ካጠገቡ ሆነዉ በመጠባበቅ ላይ በሚገኙት ቤተሰቦች ለቅሶ ሞቱ ይስተጋባል ፤ ጎረቤትም ለቅሶዉን ሲሰማ በድንጋጤ እያለቀሰ ወደ ሟች ቤት ይኬዳል ፤ ከየአቅጣጫዉ ለቀስተኛዉ ይሰበሰብና ለቅሶዉ ተሟሙቆ ይቀጥላል፡፡ አስከሬኑ ወደ ቀብር ቦታ ከመወሰዱ በፊት ቀደም ብሎ የቀባሪዎች ጥሪ ይካሄዳል፡፡ ይህም ቡታ ነገሩ ወይም እሪታ (በኽምጣኝ ድቆኩ)ይባላል (ቡ.ተ.ዉ. 1 ፣ 4 እና 5)፡፡ የቀባሪዎቹ ጥሪ ቡታ ነገሩ የሚያስፈልግበት ዋና ምክንያት “ወገን ከያለበት ተሰብስቦ በመምጣት እንዲቀብር ለማድረግ ነዉ፡፡ በገጠር ደግሞ ቤተሰብ የሚገኘዉ በተለያየና በተራራቀ ቦታ ነዉ፡፡ መቅበር ይኖርበታል ይገባዋል የሚባል ወገን ይኖርበታል ወደ ተባለበት ቦታ ሁሉ የሞተዉን ሰዉና የሚቀበርበትን ቦታ በመግለፅ ጥሪዉ ይደረጋል፡፡ ለዚህም ቡታ (እሪታ)ነጋሪዎች ይላካሉ፡፡ የሚላኩትም ሰዎች በትክክል ጥሪዉን ማስተላለፍ ቁርጥ መልክተኛ የሆኑ ናቸዉ፡፡ የቡታ ነጋሪ ቁጥራቸዉ ሁለት ነዉ፡፡ ጥሪው የሚደረገው ሁለቱ ቡታ ነጋሪዎች ከፍተኛ ቦታ ላይ ሆነው በጎጡ ውስጥ ታዋቂ የሆነውን የአንድ ሰው ስም በመጥራት ‘እገሌ አባባሉ ተጎድቷል’ ቀብሩም እዚህ ቦታ ነው እንድትመጡ ፤ እናንተም ወገን ዘመድ ወዳለበት ቦታ ቡታውን

አስተላልፉ የሰማው ላልሰማው እንዲነግር ያሳስባል፡፡ የሰሙት ደግሞ ከነሱ አጠገብ ለሚገኙት እየተቀባበሉ በመንገር ቡታው እንዲዳረስ ያደርጋሉ" (አቶ አስራት ታደሰ ቃመ 20/10/2009 ዓ.ም)፡፡

የቡታ ነጋሪው በተጠቀሰው መንገድ ሲቀጥል እሬሳውን ለቀብር የማዘጋጀቱ ስራ ደግሞ በቤት ውስጥ ይከናወናል፡፡ ይህንን ሁኔታ አስመልክተው መረጃ አቀባዩ ሂደቱን እንዲህ ይገልጹታል፡-በመጀመሪያ እሬሳው ይታጠባል ፣ የሚታጠበውም በእንቧጮ ፣ በደደሆ ወይም በእርጥብ ቅጠል ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል እሬሳው ይገነዛል፡፡ የሚገነዘውም በአዲስ ሻሽ ወይም አቡጀዴ እና በሰሌን ነው፡፡ በመጀመሪያ እሬሳው በሻሽ ወይም በአቡጀዴ ይጠቀለልና ወደ ሰሌኑ ገብቶ በገመድ ይታሰራል፡፡ ግነዛው እንደሚቹ ጾታ እና ማንነት የተለያየ ነው ፤ ይኼውም ወንድን ወንድ ፣ ሴትን ሴት ነው የሚገንዘዉ፡፡ በግነዛው ወቅት የእሬሳውን አፍ በክር ይታሰራል ፤ የእጁና የእግሮቹ አውራ ጣቶችም ባንድ ላይ ይታሰራል፡፡ ከዚያም ሬሳው በጀርባው ተስተካክሎ እንዲተኛ ይደረጋል፡፡ ሚቹ በህመሙ ምክንያት ለረጅም ጊዜ የአልጋ ቁራኛ ሆኖ በመቆየቱ ምክንያት እግሮቹ ቢተጣጠፉም እንኳ ኃይልን ተጠቅሞ እንዲዘረጋ ይደረጋል እንጂ እንደታጠፈ አይገነዝም (አቶ ደርበው ታረቀኝ ቃመ 18/10/2009 ዓ.ም)፡፡

የህፃናትን አገናነዝ በተመለከተ አቶ ደርበው ሲገልጹ ‹‹ከሰባት ዓመት በላይ የሆናቸው ይገነዛሉ፡፡ ከሰባት ዓመት በታች የሆኑ ግን አይገነዙም በጨርቅ ተጠቅልለውና ታቅፈው ይወሰዱና ቤተክርስቲያን ውስጥ ይቀበራሉ፡፡ ያልተጠመቁ ከሆነ ግን ለቀብር ወደ ቤተክርስቲያን አይወሰዱም ፤ በመኖሪያ ቤት ጓሮ ውስጥ ይቀበራሉ›› (አቶ ደርበው ቃመ 18/10/09 ዓ.ም)፡፡

በሚች ቤት ውስጥ ለቀብር ሥነ-ሥርዓቱ የሚያስፈልጉ ነገሮች ዝግጅትም ይደረጋል፡፡ ቤተክርስቲያን የሚወሰድ የግብር ስንዴም ዝግጅት ይደረግና ይወሰዳል፡፡ ሚች በሚቀበርበት ደብር ሰው በመላክም የቀብር ቦታ እንዲዘጋጅ ይደረጋል ፤ ለቀባሪዎች የሚቀርብ ቆሎም ይቆላል ለቀስተኛውና ሀዘንተኞቹ የሚቀመጡበት የዳስ ስራም ይከናወናል፡፡ አስክሬኑ ከቤት ሲወጣ በመጀመሪያ እግሩ ነው፡፡ ይህም የሚደረግበት ቤቱ ከዚህ በኃላ የሚቹ አለመሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ አስክሬኑ ከቤት ሲወጣ ለቅሶው በጣም ምርር ያለ ይሆናል፡፡ ታሞ ለሞተና በድንገት ለሞተ ሰው ሀዘኑም ሆነ ለቅሶው የተለያየ ነው፡፡ በድንገት ሲሞት ያስደነግጣል ፣ ዝምድና ያለውም ሆነ የሌለው በጣም

ስለሚያለቅስ ለቅሶው ይደምቃል ሀዘኑም የጠነከረ ይሆናል ሲሉ አቶ ደርበው ታረቀኝ ገልፀዋል (ቃመ. 18/10/2009 ዓ.ም)፡፡ ለቀብሩ ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡት ቀባሪዎች አንዳንዶቹ እንጀራና ወጥ ፣ ሌሎቹ ደግሞ እንጀራና ቆሎ በአህያ ጭነው ወደ ቀብሩ ቦታ ይመጣሉ፡፡ ለሟቹ የቅርብ ዘመድ የሆኑት እንጀራና ቆሎ ያመጣሉ፡፡ ይህ የሚመጣበት ምክንያት ለቀስተኛው ከሩቅ ቦታ በጠዋት ተነስቶ ስለሚመጣና እርቀት ወዳለው የሀዘንተኞች ቤት ሳይሄድ ከዚያው ተነስቶ ወደቤቱ ስለሚመለስ ከቀብር መልስ ምግብ ቀምሶ ወደቤቱ እንዲሄድ ነው፡፡



ምስል 23፦ የማርገጃ ቦታ ለቅሶ ሲካሄድ

ለቅሶው በከፍተኛ ሁኔታ የሚበረታው በቤተክርስቲያን አካባቢ በሚገኝ የማርገጃ ቦታ ላይ ነው፡፡ በዚህ የማርገጃ ቦታ ላይ የቅርብ ዘመድ እየዘለለ በማልቀስ ሀዘኑን የሚያሳይበትና የሚወጣበት ነው፡፡ በዚህ ቦታ ሀዘንተኛውም ቀባሪውም ተሰብስቦ ክብ በመስራት ለቅሶው ይቀጥላል፡፡ የለቅሶውን ሥርዓት የሚያስከብሩ ወይም የሚያስቀጥሉ አስተባባሪ ወንዶች በመሃል ይኖራሉ፡፡ በዚህ ቦታ ላይ አስለቃሽም ይኖራል፡፡ በአንድ የቀብር ስርዓት ላይ አስለቃሽ መኖሩ የተለያዩ ጥቅሞች አሉት፡፡ ይኼውም አስለቃሹ ሲያለቅስ ሌላው ማዳመጥ ስላለበት ሀዘንተኞቹ እረፍት ያገኛሉ፡፡ አስለቃሹ ስለሟቹ ማንነት በመግለፅ የማያውቁት እንዲያውቁት ይሆናል፡፡ በሆድ ውስጥ የሚብሰለሰል ሀዘን ገንፍሎ

እንዲወጣ ያደርጋል። በዚህ ምክንያት አስለቃሹ ማስለቀሱን ሲያቆም ሌላው ማልቀስ ሲጀምር ለቅሶው የደመቀ ይሆናል (ወ/ሮ አለምነሽ በላይ፣ ቃመ. 22/10/2010 ዓ.ም)።

በአስለቃሹ አማካይነት ቃል ግጥሞች እንደሟቹ ማንነትና ሙያ በዜማ ታጅበው ይደረድራሉ። ከሚደረደሩ ቃል ግጥሞች መካከል ለአብነት ያህል የመረጃ አቀባዮቼ ከጠቀሱልኝና ምልከታ ሳደርግ ካዳመጥኳቸው መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

## ሀ. እናት ስትሞት የሚደረደሩ

01.እናት የሌለው ልጅ ቀላል እንደ ጌሾ፣
ቢበላም ሆዳም ነው ቢናገርም ዋሾ።
02.እባክሽ እናቴ ጥሬ ቆልተሽ በገል፣
ታውቂዋለሽና የሰውን ቤት ነገር።
03.አወይ ይህ መጥረቢያ ስለቱ መብዛቱ፣
የወላጅን አንጀት የቆረጠበቱ።
04.እንዴት እናት ትሙት ትሄድ አጎንብሳ፣
እንኳን ቁማ ሄዳ ታማ ብትተኛ
ለልጇ ናትና ወስከንቢያ መክደኛ።
05.እንዴት እናት ትሙት ትኑር አጎንብሳ፣
ትገድላለች ቅማል በጨለማ ዳሳ።

## ለ. አባት/ባል ሲሞት የሚደረደር

06.እንዴት ባል ይሙት ያሞኝ ተላላ
አበጥሮ ግሮ ካልሰጡት አይበላ።
07.ቆርቆሮ ቢመታ ቢሰራ ደብር፣
ባለቤት ከሌለ የለው ቁም ነገር።
08.ግልገል በቅሎ ገዛሁ በጣሙን አጉድዬ፣
ደግ አባት በቅሎ አይገኝም ብዬ።
09.እጁን አትሰሩት እኔ እዋሰዋለሁ፣
በዚያ በክፉ ቀን በልቼበታለሁ።
10.ጮማን እንደ ጎመን የበላንባቱ፣

ጠጁን እንደ ውሃ የጠጣንበቱ፣
እገሌ ፈረስ በጀ አለ ለሞቱ፡፡

ሐ. ልጅ ሲሞት የሚደረደሩ

11.አትቅበሩኝ አለ ካንገቴ በላይ፣
ናፋቂ ነኝና እናቴን እንዳይ፡፡
12.የትናትም ሞት ቢሆን የየቅል የየቅል፣
የወንድም ሞት ቢሆን የየቅል የየቅል፣
የልጅ ሞት ክፉ ነው ካንጀት የሚበቅል፡፡ (ደርበው ታረቀኝ ቂ.መ.አ 20/10/2010 ዓ.ም)፡፡

ለቀስተኛው በተገለፀው መንገድ እየተለቀሰ የሀዘኑን ድባብ ሞቅ እንዲል ያደርጉታል ቀብሩ በዚህ ሁኔታ ከተከናወነ በኋላ የሚከተሉት ይከናወናሉ፡፡

**ስንብት ፣ ማስተዛዘንና የተይዞ ለቅሶ፡-** የቀብር ሥርዓቱ ከተፈፀመ በኋላ በንስሃ አባት ባጋጣሚ እሳቸው ባይኖሩም በሌላ ካህን አማካኝነት የቀብር ስርዓቱ መጠናቀቁን የሚያሳውቅ የፀሎት ሥርዓት ይከናወናል፡፡ በዚህ ሁሉም ሀዘንተኛውም ጭምር ፀጥ ብሎ ያዳምጣል ከዚያም የቀጠሮ ለቅሶ (አጎበር) ቀንና ቦታ ይገለፃል፡፡ ለቀስተኛው ከመበታተኑ በፊትም ከሟች ቤት በመጣው ቆሎ ፣ እንጀራ ፣ እልበትና ወጥ እንዲሁም ቀባሪዎች ባመጡት እንጀራና ቆሎ ይስተናገዳሉ፡፡ ሀዘንተኞቹም እንዲበሉ ይደረጋል፡፡ ለመብላት ቢያንገራግሩም እንኳ ‹‹እየተበላ ነው የሚለቀሰው ካልተበላ እንባ አይወጣም ፣ አይፈስም›› እየተባሉ በቁጣ በልመናም እንዲበሉ ይደረጋል፡፡ በቀብር ወቅት ወደ ቀብር ቦታ የሚመጣውና ለቀስተኞቹ የሚመገቡትም ንፍሮ ሳይሆን ቆሎ ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል የስንብት ሥነ-ሥርዓት ይካሄዳል፡፡ ስንብቱም የሚካሄደው ቀብሩ ከተፈፀመበት ቤተክርስቲያን ወጣ ብሎ ሜዳማ ቦታ ላይ በማርገጃው ቦታ ነው፡፡ ከዚህም ለስንብት እንዲያመች ወንድ ሀዘንተኞች ለብቻ ሴት ሀዘንተኞች ደግሞ ለብቻ ይቀመጣሉ፡፡ እንዲህ ተለያይተው መቀመጣቸው ወንዶቹ ወንድ ሀዘንተኞችን ፣ ሴቶቹ ደግሞ ሴት ሀዘንተኞችን እንዲያስተዛዝኑና እንዲሰናበቱ ነው፡፡ የሚሰናበቱትም ሰው ብዙ ከሆነ በተናጠል ሳይሆን በጎጥ በጎጥ በመሆን በአንድ ትልቅ ሰው መሪነት ብቻ በአንድ ላይ ሆነው ይሰናበታሉ፡፡ በስንብት ወቅት ከሚነገሩ ማስተዛዘኛ ቃላት ወይም ሀረጋት

መካከል “እግዚያብሔር ያጥናህ ፣ ተው ይበቃሃል ፣ ያስችልህ ፣ ከሞት ጋር መታገል እርባና የለውም ፣ ይበቃል ፣ ተለቅሷል ፣ የመሳሰሉት ይገኙበታል” (አቶ ጥጋቤ ምርቴ 20/10/2010 ዓ.ም ፣ አቶ ደርበው ታረቀኝ ቃመ. 18/10/2010 ዓ.ም)፡፡



ምስል 24፡- ስንብትን በከፊል የሚያሳይ

ስንብት ማድረግ ሃዘንተኞቹን ከማስተዛዘኑም በተጨማሪ ሀዘንተኞቹ በቀብሩ ላይ የተገኘውንና ያልተገኘውን ወገን ለመለየትም ያስችላል፡፡ ለዚህም ወደ ቀብሩ መምጣት ሲገባው ያልመጣው ወገንም ፣ ያልመጣበትም ምክንያት ከአቅም በላይ የሆነ ችግር አጋጥሞት መሆኑን በመልዕክተኛ በኩል ለሀዘንተኞቹ ያሳውቃል (ይህንን ሁኔታ በምልከታየ ወቅት በተገኘሁበት በአንድ የሀዘን ቦታ ላይ ለመመልከትና ለማወቅ ችያለሁ)፡፡

አብዛኛው ቀባሪ ወደ መጣበት ሲመለስ ፣ የቅርብ ዝምድና ያላቸውና ጎረቤት የሆኑት ግን የሀዘንና የማስተዛዘን ስርዓቱን ለመቀጠል ወደ ሟቹ ቤት ያመራሉ፡፡ ወደቤት እንደተመለሱም እሬሳ ወደ ወጣበት ቤት በቀጥታ አይገቡም፡፡ በሴቶች ቤቱ እንዲፀዳ ይደረጋል ፤ የሚፀዳውም በቅጠል ፣ በውሃ እና በእሳት ነው፡፡ ሶስቱንም ይዘው ወደ ቤት በመግባት በመጀመሪያ ውሃ ይረጫል ፣ በመቀጠልም እሳት በማንደድ በቅጠሉ ይጠርጋሉ (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ቁ.መ.አ 24/10/2010 ዓ.ም)፡፡

በዋግኽምራ ብሔረሰብ ለቀብርም ሆነ ለማስተዛዘን የተቋቋመ እድር የለም። በመሆኑም ሀዘንተኞችን የሚስተዛዘኑት በተራ ሳይሆን በግለሰቦች በጎ ፈቃደኝነት ነው። ሀዘንተኞች በቶሎ ተነስተው ወደ ስራቸው ይሄዳሉ። ለማስተዛዘን ብለው ለብዙ ቀናት ባይቀመጡም ለሰባት ቀናት ያህል ማስተዛዘኛ እህል ውሃ ይወሰድላቸዋል። የሚወሰደው ነገር ዓይነትና መጠን እንደአስተዛዛኞቹ ለሀዘንተኞቹ ባለው የዝምድናና የጉርብትና ሁኔታ የሚወሰን ነው። በአብዛኛው የሚወሰደው እንጀራ ፣ ጠላና ቡና ነው። ጎረቤቶችና የቅርብ ዘመዶች እስከ ሰባት ቀን ድረስ ወደ ቤታቸው ሳይሄዱ ሀዘንተኞቹ ጋር ያድራሉ። ለሀዘንተኛው የጉልበት እገዛም ያደርጉለታል ፤ ወቅቱ የእርሻ ፣ የአረም ወይም የአጨዳ ከሆነ ጎረቤቶችና የቅርብ ዘመዶች እርሻውን ያርሱለታል ፣ ያርሙለታል፣ ያጭዱለታል(አቶ ደርበው ታረቀኝ ቁ.መ.አ 18/10/2010 ዓ.ም)።

በዋግኽምራ ብሔረሰብ ሌላው ለየት ያለው ስርዓት የሞተውን ሰው መቅበር ያልቻሉ ወገኖች ተሰብስሶው የሚያለቅሱበት የቀጠሮ ለቅሶ (አጎበር) የሚደረግ መሆኑ ነው። አጎበር ማለት በተለያየ ምክንያት ቀብር ያልተገኙ ሰዎች በአንድ ቦታ ላይ ተሰብስበው እንደገና የለቅሶ ስርዓት የሚከናወንበት የተይዞ/የቀጠሮ ለቅሶ ነው። መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል የአጎበርን ምንነትና የሚደረግበትን ምክንያት እንዲህ ይገልፃሉ “አጎበር ማለት መገናኛ ነው ፣ አንድ ሰው ሞቶ ከሩቅ ያሉ ሰዎች ለቀብር ስለማይደርሱ እየተንጠባበቡ የሚመጣ የለቅሶው ደራሽ የሟች ቤተሰቦችን ፣ ተደራሾችንም እንዳናስቸግር ተሰባስበን የምንሸኝበት አባቶቻችን ያቆዩልን ስርዓት ነው። ይኼውም የድንገት ሞት ከሆነና ሬሳው የማያድር ሆኖ የቀብሩ ጥሪ /ቡታ/ ለወገን ሳይነገር ከተቀበረ እና የቀብር ስርዓቱ እዚህ የትውልድ ቦታው ሳይሆን በሌላ አገር ለተከናወነ ነው” (ቁ.መ.አ 17/10/2010 ዓ.ም)።

አጎበር ዝግጅት የሚጠይቅ ነው። ሀዘንተኞቹ ለአጎበር የሚሆን እንጀራ ይጋግራሉ ፤ ወጥ ይሰራሉ። የአጎበር ታዳሚዎችም ሲመጡ በወገን በወገናቸው አንድ ላይ በመሆን እንጀራና ወጥ ይዘው ይመጣሉ። ራቅ ያሉት እንጀራ ብቻ ፣ ቀረብ ያሉት ደግሞ ወጥ በዛ ካለ በቶፋ/ገንቦ መሳይ ከሸክላ የሚሰራ እቃ አነስ ካለም በቅል ያመጣሉ። በአገልግል እንጀራ ይዘው የሚመጡትም የለቅሶው ስርዓት ተጠናቆ እርክክብ እስኪደረግ ድረስ አገልግላቸውን ዛፍ ላይ ያንጠለጥላሉ። ለአጎበር ስርዓቱም በቅሎ እንዲያጌጥ ይደረጋል ፣ ሰንደቅ ዓላማ ይያዛል ፣ ጥሩባም ይነፋል። ሁሉም የአጎበሩ ለቀስተኛ መምጣቱ ከተረጋገጠ በኃላ ሜዳማ ቦታ ላይ የለቅሶ ስርዓቱ ይጀመራል። ለቅሶው የሚከናወነው

ክብ ተሰርቶ ወንዱ ለብቻ ሴቱ ለብቻ ተራ በተራ ክቡን በመዞር ነው። ይህንንም የሚያስተባብሩና የሚያስፈፅሙ ሰዎች ይኖራሉ ፤ ወንዶቹም ሆኑ ሴቶቹ ሀዘንተኞቹ ፊት ለፊት በመሆን ለቅሷቸውን ይቀጥላሉ። ሁሉም አንድ ጊዜ በክብ ዞረው ከተላቀሱ በኃላ በካህን ፀሎት የለቅሶ ስርዓቱ ይጠናቀቅና ለቅሶው ቆሞ ያመጡትን እንጀራ ወደሚያስረክቡበት እና ወደሚመገቡበት ቦታ ያመራሉ።



ምስል 25፡- ለአጎበር የመጣው እንጀራ ከርክክብ በፊት

በዚህ ጊዜ ሀዘንተኞቹ ከፍተኛ ቦታ ላይ ይቀመጣሉ ፤ ለቀስተኞቹ ያመጡትን እንጀራና የወጥ መጠኑን ለአስረካቢዎች በመንገር ይሰጣሉ።

እንጀራና ወጥ የሚያመጣው ሰው እየታየ ከማስረከቡ በስተቀር ስም ዝርዝር እና የመጣው እንጀራና ወጥ መጠን አይመዘገብም። የዚህን ምክንያት አቶ አስራት ታደሰ ሲገልጹ ‹‹ምዝገባ የለም ፣ ምክንያቱም እንኳን ለአጎበር የመጣው የቀብሩም እንኳ አይረሳም ፤ ተረካቢዎቹም ከተለያየ ቦታ የሚመጡ ወገኖች በመሆናቸው የአካባቢየቸውን ሰው የሚያውቁ ናቸው። አብሯቸው የመጣውን ሰው የሚያስታውሱ ናቸው። ስለዚህ ምዝገባ አያስፈልገውም ይላሉ (ቁ.መ.አ 23/10/2009 ዓ.ም)።



ምስል 26፡- የአጎበር እንጀራ ርክክብ

የአጎበሩ ለቀስተኞች ያመጡት እንጀራና ወጥ እርክክብ መጠናቀቁ ሲረጋገጥ ሀዘንተኞቹ "ያመጣችሁትን አውቀነዋል ፤ እንግዳችሁን ሸኙበት›› ይሏቸዋል ለመመገቢያ የሚሆን መሶብ ወይም ሰሀን ስለማይኖር በየራሳቸው አገልግል ለለቀስተኞቹ ይሰጧቸዋል፡፡ አመጋገባቸው ወንዶች ለብቻ ሴቶች ለብቻ ነው፡፡ የሚስተናግዱትም ከየጎጡ ከመጡት መካከል ለሟች ዝምድና ያላቸው እና ወጣት የሆኑት ወንዶች ናቸው፡፡ ተከትሏቸው የመጣውን እንግዳ ከሸኙና ራሳቸውም ከተመገቡ በኋላ የተረፈውን እንጀራ ለሀዘንተኞቹ ትተውላቸው ይሄዳሉ፡፡ የተረፈውም ምግብ ለቀስተኛው ወደ ቤቱ ይዞ አይገባም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ሀዘንተኞቹ ሀዘናቸዉን ለመረሳት ሲባል ብቻ ሳይሆን ለሀዘን የተወሰደ እንጀራ ትራፊ ስለሆነ ለሚወስደው ሰው ‹‹ሀዘን ይድረስብህ" እንደማለት ይቆጠራል (አቶ ደርበው ታረቀኝ፣ ቁ.መ.አ 18/10/2009 ዓ.ም)፡፡





ምስል 27፡- ወንዶች ሲመገቡ በከፊል ሴቶች ሲመገቡ በከፊል

**የሟች መታሰቢያዎች፡-** ለሟች ተብለው የሚደረጉ በርካታ መታሰቢያዎች አሉ ፤ እነዚህም የሚጀምሩት ሟች በተቀበረ በሶስተኛው ቀን በሳልስት ነው፡፡ ይህንን የሟች መታሰቢያ አስመልክተው ቄስ ደምሴ መኮንን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

> በሳልስት አንድ ገንቦ ጠላና አምስት እንጀራ ወደ ቤተክርስቲያን ይወሰዳል ፤ ከዚያ በሰባት አንድ እንስራ ጠላና አስር እንጀራ ይወሰዳል ፤ በአስራ ሁለት እና በሰላሳ አንድ ጋን ጠላና ሃያ እንጀራ እና በአርባው ደግሞ ከፍተኛ ድግስ ተደግሶ ይዘከራል፡፡ ከነዚህ መካለል በአርባው የግድ በግ ፣ ፍየል ፣ አቅም ካለም በሬ መታረድ ወይም ደም መፍሰስ አለበት ፤ ከእነዚህም በተጨማሪ በአመቱ የሚደገስ አመታትም ይደረጋል (ቃመ 25/10/2010 ዓ.ም)፡፡ አንድ ሰው ለሟች ወላጆቹ የሚጠበቅበትን መዘከሪያ ካላደረገ በማህበረሰቡ በኩል ‹‹የአባቱን ወይም የእናቱን አፍ ያላበሰ ወይም እናቱን ከወደቀችበት ያላነሳ›› ተብሎ ሀሜትና ስድብ ይደርስበታል፡፡ እንደ መረጃ አቀባየ አገላለፅ “ለእናት ለአባቱ ያለሆነ ምን ሰው ነው ተብሎ ከሰው ስለማይቆጠር ከማህበረሰቡ ይገለላል”(አቶ ደርበው ታረቀኝ ቁ.መ.አ 20/10/2010 ዓ.ም)፡፡ ከዚህ የምንረዳው የተለያዩ የሟች የመታሰቢያ ተስካር/ዝክር የሚከረጉት ለሟች ነፍስ ይማርነት ሲባል ብቻ ሳይሆን ለቋሚም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ነው፡፡ የሟች ቤተሰብ ይህንን ያልፈፀመ ከሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ መዘባበቻ ይሆናል ፤ አፉን ሞልቶ ከሰው እኩል አያወራም ፤ በልዩ ልዩ ማህበራዊ ተሳትፎዎች ውስጥ አይሳተፍም ፤

ቢሳተፉም የሚሰጠው ግምት አናሳ ነው። በነገር ዘወትር ይወርፉታል። ሌላው ለሟች የመታሰቢያ ድግስ መደገስ ከፍተኛ የሆነ ደጋሹን የሚያራቁት መሆኑ ነው። ከፍተኛ ወጪን ስለሚያስከትል ደጋሹን ለችግር ይዳርጋል (አቶ ደርበው ታረቀኝ፣ ቃመ 20/10/2010 ዓ.ም)።

## 4.2.5 ክብረ በዓላት

### 4.2.5.1 ሻደይ

ሻደይ የዋግኽምራ ብሔረሰብ መለያ የሆነ ባህላዊ ጨዋታ ነው። በየዓመቱ ከነሐሴ 16-18 ባለው ጊዜ ከፍስለታ ፆም በኋላ የሚከወን ነው። በቀደምት ዓመታትና አሁንም በገጠሩ አካባቢ እስከ ነሐሴ 21 ክብረ በዓሉ ይከበራል። ክብረ በዓሉ የተጀመረው በአፈ ታሪክ እንደሚነገረው በኖህ ዘመን ከዘመን መለወጫ ፣ከፍስለታ በዓል አጀማመር ጋር ተያይዞ እንደሆነ ይነገራል። የጨዋታው መነሻ አንዳንዶቹ ሃይማኖታዊ መሠረት አለው ሲሉ ሌሎች ደግሞ የብሔረሰቡ የራሱ የሆነ ባህላዊ ሃብት በመሆኑ ከሃይማኖት ጋር ግንኙነት የለውም በማለት ማስረጃቸውን ያቀርባሉ[38]። መቼ ተጀመረ ለሚለውም ባህላዊ ጨዋታው እጅግ ጥንታዊና ከክርስቶስ ልደት በፊትም ይካሄድ እንደነበረ ሲገልጹ ሌሎች መረጃዎች ደግሞ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ ጋር አያይዘው በ4ኛው ክፍለ ዘመን እንደተጀመረ ያስረዳሉ (አቶ ባዮ አስምሮም ፣ ቃመ 7/10/2009 ዓ.ም)።

የጨዋታው አከባበር መነሻ ከክርስትና እምነት ጋር ተያይዞ የቅድስት ድንግል ማርያም "ሞቷ በጥር በነሐሴ መቃብር" በሚል ፍለጋዋን ምክንያት በማድረግ አስራ ስድስቱን የፍስለታ ፆም ጊዜ ሱባኤ በመግባትና መገኘቷን ምክንያት በማድረግ እንደ የምስራች ከነሐሴ 16 ጀምሮ በዓሉ ይከበራል። የበዓሉ ዝግጅት ቀደም ብሎ ከወራት በፊት ይጀመራል። የቡድን ምስረታውም ደብርን ወይም ጎጥን መሠረት በማድረግ በዓብዛኛው ከ20-30 /እንደ ሁኔታው ቁጥሩ ከፍና ዝቅ ሊል ይችላል/በሆኑ የቡድን አባላት ይደራጃል። የቡድኑ ዓባላትም ዘፈን አውጪ ፣ ገንዘብ ያዥና ፣ አለቃ ፣ ከበሮ መቺና እስክስታ አውራጅ በማለት የሥራ ድርሻ ይሰጣቸዋል። የጨዋታውም ባለቤቶች ያላገቡ ልጃገረዶች ቢሆኑም እናቶች ለትዝታ ወይም ለአውራሽነት የሻደይ ቅጠሉን

---

[38] ሻደይ-ወንዝ አይፈሬ፣2003፣ የዋግኽምራ ዞን- ልዩ እትም መፅሄት፣ላይ የተገኘ ሀሳብ ነው

በርችነትት/ለምልክት ብቻ/አስረው ሲጫወቱ ሕፃናት ደግሞ ከእናቶቻቸውና ከህቶቻቸው ጨዋታውን በመመልከት በተደራጀ መልኩ ሳይሆን እንደ ፍላጎታቸው ይጫወታሉ፡፡ የጨዋታው አጀማመር ከነሐሴ 15 ጀምሮ የቡድኑ አባላት በወገብ ላይ የሚታሰር ሻደይ ቅጠል/ቄጤማ መሰል/ከበረሃ በመሰብሰብ ወይም ደግሞ በግዥ በመሰብሰብ ዝግጅት ይደረጋል፡፡ ማታውኑ የሻደይ ቅጠሉን ጫፍ በገመድ ላይ እርስበርስ እየተሳሰረ ስሩን ወደታች በማድረግ በልዩ ሁኔታ እየተጎነጎነ ይዘጋጃል፡፡ ወቅቱ ክረምት ቢሆንም እንዳይጠወልግ ወይም እንዳይወይብ የተሰራው የሻደይ ጉንጉን ጤዛ ባለው ሙጃ[39] ውስጥ ተሸፍኖ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ከጨዋታው በኋላ ከጠወለገና ተበጣጥሶ ካለቀ አዲስ በመግዛት ወይም ተገዝቶ ከሙጃ ውስጥ ከተቀመጠው እንደአዲስ ይሠራል፡፡ በማግሥቱ የቡድኑ አባላት በተቀጣጠሩበት ቦታ በመሰባሰብ የተለያዩ ጨዋታዎችን እየተጫወቱ ወደ አቅራቢያቸው በሚገኝ ደብር ወይም ቤተክርስቲያን ያመራሉ፡፡ በጉዞ ወቅት የሚከተሉትን ባህላዊ ጨዋታዎችን እየተጫወቱና እየጨፈሩ ጨዋታውን ይጀምራሉ (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ፣ቃመ. 15/10/2010 ዓ.ም ፣ ወ/ሮ ታምር አሰፋ ፣ ቃመ. 16/10/2010 ዓ.ም)፡፡ ለአብነት ያክል የሚከተሉትን ማጤን ይቻላል፡፡

| አውጪ | ተቀባይ |
|---|---|
| እቴ አደይ ነሽ አሉ እቴ አደይ | እቴ አደይ ነሽ አሉ እቴ አደይ! |
| እቴ አደይ ነሽ አሉ በየአገሩ | እቴ አደይ ነሽ አሉ  በየአገሩ! |
| አሽከር አበባዬ | አሽከር አበባ (2 ጊዜ) |
| ይኼው ከዚያ ማዶ ግራሩ ግራሩ | አሽከር አበባ! |
| እሰይ የኔ ጌታ ሲታጠቅ ማማሩ፡፡ | አሽከር አበባ! |
| ምድርጭሬ ጭሬ አወጣሁ ማሰሮ፣ | አሽከር አበባ! |
| አሰይ የኔ እመቤት ድልድል ወይዘሮ፡፡ | አሽከር አበባ! |

[39] ሙጃ በአካባቢው የሚገኝ የሳር ዓይነት ነው፡

እያሉ በመዝፈን በየቤቱ የቀሩ ልጅአገረዶችን እየቀሰቀሱ ጨዋታቸውን ያደምቃሉ፡፡ በዚህ ጨዋታ መጀመሪያ በሚሄዱበት በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ ቤተክርስቲያን ደጃፍ ሲደርሱ ወደ ቤተክርስቲያኑ እንዲያስገቧቸው እንደሚከተለው ያዜማሉ፡፡

| አውጪ | ተቀባይ |
|---|---|
| አስገባኝ በረኛ | አስገባኝ! |
| አስገባኝ ከልካይ | አስገባኝ! |
| እመቤቴን ላይ | አስገባኝ! |

እያሉ ይጫወታሉ፡፡ ቤተክርስቲያን እንደገቡም “የከርሞ ሰው በለኝ” እያሉ አበባ! ይላሉ፡፡ እዚህ ያደረሳቸውን ታቦት ስም እየጠሩ የተለያዩ ከሃይማኖት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ግጥሞች በመደርደር ምስጋናቸውን ያቀርባሉ፡፡ ለቤተሰባቸው ፣ ለወዳጅ ዘመዳቸው መልካሙን ሁሉ እንዲሰጣቸው ቀጣይም በሰላም እንዲያደርሳቸው ይማፀናሉ፡ ፡ የቤተክርስቲያን አባቶችም “እደጉ! የከርሞ ሰው ይበላችሁ!” እያሉ ይመርቋቸዋል፡፡ ከቤተክርስቲያን ቀጥለው የሚሄዱት በዕድሜ/በስልጣን/ከፍ ወዳሉ ግለሰቦች ቤት ነው፡፡ በመንገድ ላይ የተለያዩ ለመንገድ ተስማሚ የሆኑትን ከጨዋታው ዘፈኖች መካከል በመምረጥ ይጫወታሉ፡፡ወደ ግለሰቦች ግቢ አጥር ቢኖረውም ባይኖረውም ዘው ተብሎ አይገባም፡፡ በመሆኑም ከደጅ ሆነው እንዲገቡ እስኪፈቀድላቸው ድረስ “አስገባኝ በረኛ” እያሉ ይጫወታሉ፡፡

| አውጪ | ተቀባይ |
|---|---|
| አስገባኝ በረኛ | አስገባኝ! |
| አስገባኝ ከልካይ | አስገባኝ! |
| እመቤቴን ላይ | አስገባኝ! |

እያሉ ያዜማሉ (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል፣ቃመ15/10/2010 ዓ.ም)፡፡

የሻደይ ጨዋታ ሁሉም ተሳትፎ ያለው ቢሆንም ጨዋታው በዋናነት የልጃገረድ ወይም ያላገቡ ወጣት ሴቶች ቢሆንም እናቶችና ሕፃናጽ በየእድሜ ክልላቸው ቡድን መስርተው ይጫወታሉ፡፡ የወንዶች ሚናና ተሳትፎ ማድነቅ ፣ ማጀብ ፣ ማሽኮርመምና መጠበቅ ነው፡፡ እንደ ዕድሜ ክልላቸው የሻደይ ተጫዋቾች ቡድኖች የራሳቸው መሪና ተከታይ አላቸው፡፡




ምስል 28፡- የዐዋቂዎች የሻደይ ጭፈራ የወጣቶች የሻደይ ጭፈራ

የተጫዋቾችን የአለባበስ ሁኔታ ስናይ ሕፃናት ከሆኑ አለባበሳቸው እንደነገሩ ነው ፤ ለአለባበሳቸው አይጨነቁም ጆሮኣቸው ላይ ግን ከቆርቆሮ የተሰራ ክብ ቀለበት ያንጠለጥላሉ፡፡ ከሕፃናት ዕድሜ ከፍ የሚሉት ልጃገረዶች ደግሞ ለመታጨት ስለደረሱ ለአለባበሳቸውም ሆነ ለጌጣጌጦቻቸው ይጨነቃሉ፡፡ የተሻለ የጆሮ ጉትቻም ያደርጋሉ፡፡ የታጩ ከሆኑ ደግሞ “ማርዳ” ከጠልስምና ከክር ተሰርቶ አንገት ላይ የሚደረግ ጌጥ ያደርጋሉ፡፡ ያላገቡ ከሆኑ ፀጉራቸው “ጋሜና ቁንጮ” ይሆናል፡፡

“ጋሜና ቁንጮ” ፣ ዲኮት/የእጅ አምባር/፣ አንገቷ ላይ በማተብ የተሰራ መስቀልና ማርዳ ታደርጋለች፡፡ ከነዚህ በላይ ከፍ የምትለዋ ደግሞ ፣ ጎበዝና ቆንጆ ፣ ሹርባ ፣ ግልብጥ እንዲሁም ሳዱላ ፣ ቅርድድ የተባለ መሃል አናቷ ላይ ይላጭና ሌላው በሙሉ ሹሩባ/የተባሉ የፀጉር ስሬቶችን እንደፍላጎቻቸው ይሰራሉ፡፡



ምስል 29፡-የሴቶች የፀጉር አጊያጊያጥ

በአጊያጊያጥም ደረጃ ከ "ጋሜና ቁንጮ" ከፍ ስለምትል አለባበሷ ይለያል፡፡ ድሪ ፣ ሁለት መስቀል/ትንሹና ትልቁን ቀራንዮ/ማርዳ/የአንገት ጌጥ/እና ዲኮቱ/የእጅ አምባር/ታደርጋለች፡፡ በዚህ መልኩ ከለበሱ በኋላ ጨዋታውን ለሶስት ቀናት ያህል ያከናውናሉ፡፡ በቆይታቸውም በየቤቱ እየዞሩ ከበሮ እየመቱና እየጨፈሩ እንኳን አደረሳችሁ እያሉ ይጫወታሉ፡፡ በጨዋታው ማጠናቀቂያ ላይ ሁሉም ቡድኖች በአንድ አደባባይ ላይ ተሰባስበው የየራሳቸውን ጨዋታ ፤ ሁሉንም የሻደይ ጨዋታዎች በተለየ ድምቀት በውድድር መልክ ከፍተኛ ሕዝብ በተሰበሰበበት ይጫወታሉ፡፡ ሕዝቡም በጥሩ ሁኔታ ባህሉን ጠብቆ ለተጫወተው ቡድን የራሱን ዳኝነትና ክብር ይሠጣል (አቶ ደረበው ታረቀኝ ፣ ቃመ. 10/09/2009 ዓ.ም)፡፡

የሻደይ ጨዋታ የሚጠናቀቀውም ሁሉም ቡድኖች ወንድና ሴት በማድረግ በማህበረሰቡ ክብር የሚሰጠውንና ለወደፊትም ወጣቶች ይህን ማኅበራዊ ሥርዓት እንዲፈጽሙት በሚያመለክት መልኩ የሙሽራ መዳር ስነ ስርዓት በማካሄድ ነው፡፡ እውነተኛ ሰርግ ለማስመሰል ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ጨዋታው ይቆምና አመቺ ሜዳ ተፈልጎ በየቡድናቸው ይሰባሰባሉ ፤ ተሰባስበውም የስድብ ግጥም እየገጠሙ ይጫወታሉ፡፡ ድብድብም ይኖራል፡ ፡ በዚህ ጨዋታ ተደብድቦ ለፖሊስ የሚያመለክት የለም ፤ ተፈንክቶ ቢደማ አሜን ብሎ ወደ ቤቱ መሄድ ነው፡፡ ቂምም ሆነ በቀል የለም፡፡ በዚህ ጨዋታ አየል ብሎ የታየ አጃቢ ሲያገኝ ፣ ፈዘዝ ያለው ደግሞ ስድብ ይደርሰዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ጨዋታው ሲጠናቀቅ

የተፈነከተው ፍንክቱን ይዞ ያለቅሬታ የከርሞ ሰው ይበለን እያለ ወደ ቤቱ ሲሄድ ፣ ወንዶች ወጣቶች የሻደይ ቅጠል ያሰሩትን ሴቶች እየተከተሉ ቅጠሉን ይበጥሱባቸዋል፡፡ ይህን ማድረጋቸው አንድም ለማበሳጨት ሌላውም የፈለጓትን ሴት እንደማባበያ መሆኑን መረጃ ሰጪዎች ገልፀዋል (አቶ ደረበው ታረቀኝ ቃመ. 10/9/2009 ዓ.ም ፣ አቶ ባየ አስምሮም ቃመ. 7/10/2009 ዓ.ም)፡፡

የሻደይ ባህላዊ ጨዋታ የብሔረሰቡ ዋነኛ መገለጫ ሆኖ በየዓመቱ በጉጉት እየተጠበቀ የሚከበር ነው፡ ፡ክዋኔው በየዓመቱ በደመቀ ሁኔታ እየተተገበረ ሲሆን ከበራው በዕድሜ ክልል ተከፍሎ የሚከናወንና በዚህም ወላጆች ህፃናት ልጆቻቸው ከታላላቆቻቸው ታላላቆችም ከወላጆቻቸው እየቀሰሙ እንዲማሩ ወደ ጨዋታው ገፍተው እንዲሄዱ ማድረጋቸው በተደረገው ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የባህሉ ባለቤቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዞኑ በሁሉም ወረዳዎች በእያንዳንዱ ቀበሌዎች በደመቀ ሁኔታ የሚከበር ሲሆን አባቶች እና እናቶች ባህሉ ተጠብቆ እንዲቀጥል ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርጉም በዚህ ጥናት ላይ ባደረኩት ቃለ መጠይቅ፣ ቡ ድን ተኮር ውይይትና በከበራው ላይ በመሳተፍ ለማወቅ ችያለሁ፡፡

### 4.2.5.2 ዋርዳ ሆዬ

በዋግኽምራ ብሔረሰብ ከሚከበሩ በዓላት መካከል እንቁጣጣሽ እና መስቀል ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በእነዚህ በዓላት ብዙውን ጊዜ ያላገቡ ወንድ ወጣቶች በየአካባቢያቸው በመሰባሰብ በዓላቱን በዋርዳ ሆዬ/አሽከሌለቻ ጨዋታ ያደምቁታል፡፡ ጨዋታውን አስመልክተው አቶ ደርበው ታረቀኝ እንደሚከተለው ገልፀውልኛል፡፡

> ዋርዳ ሆዬ/አሽከሌለቻ በብሔረሰቡ ወንድ ወጣቶች ወቅት ተጠብቆ ከሚጫወቱት በዓላዊ ጨዋታዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ “ዋርዳ” ማለት በብሔረሰቡ ቋንቋ በኽምጣኝ ጨዋታ ማለት ነው፡፡ ለጨዋታው የሚፈለገው ክብና አንድ ጭብጥ የሚያክል ቡላ መልክ ያለው ድንጋይ ሲሆን ከባህር ወይም ከወንዝ ዳር የሚገኝ እና እሳት ላይ ሲገባ የማይፈነዳ ወይም የማይሰበር ነው፡፡ ለጨዋታው ጥቁር ድቡልቡል ድንጋይ የሚያስፈልግ በመሆኑ ነው፡፡ ዋርዳ ሆዬ/የጥቁር ድንጋይ ጨዋታ/በየዓመቱ በዘመን መለወጫ ከጳጉሜ አምስት ጀምሮ እስከ

መስከረም አስራ አምስት ባሉት ቀናት እስከ መስቀል ዋዜማ የሚጫወቱት ነው፡፡ጨዋታውን የሚጫወቱት ከ10-18 ዓመት የሆናቸው ህፃናት ፣ወጣት ወንዶች እና ሴቶች ሲሆኑ በዋናነት ግን በወንዶች የበላይነት ይይዛል፡፡ አልፎ አልፎ አዋቂ ወንዶችም ይጫወቱታል፡፡ ጨዋታው ሌሊት ላይ በተለይም ከስራ መልስ የሚከናወንና ለተጨዋቾች አመቺ ሲሆን የተለየ የጨዋታ ሜዳ ያስፈልገዋል፡፡ ከ20 በላይ በሆኑ የቡድን አባላት በጎጥ ፣ በቀበሌ ወይም በደብር ቡድኖች የሚመሰርቱ ሲሆን በአንድ ጨዋታ ሁለት ቡድን ነው መጫወት የሚችለው፡፡ እያንዳንዱ ቡድን ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ የሚካሄደውን ጨዋታ ለማሸነፍ ከፍተኛ ትግል ይደረጋል፡፡ የጨዋታው ሥርዓት የሚጀምረው ጳጉሜ ማታ ላይ ሲሆን ፣ አጀመመሩም የአካባቢው እረኞች አንድ ላይ በመሰባሰብ እሳት እያነደዱ “ለውፈረ ፣ ለውፈረ”/አንተ ልጅ ና ፣ አንተ ልጅ ውጣ/ እያሉ ጨዋታውን እየተጫወቱና ድቡልቡል ድንጋይዋን በእሳት እያሞቁ ተጫዋቾቹ እንዲወጡ የጨዋታ ቅስቀሳ ያደርጋሉ ፤ በዚህም ጨዋታ ሳይወጣ የቀረን ደግሞ እንደሚከተለው በመስደብ ይሆናል፡፡

አሆሆ ሽረሮ፣

እንትና ሲፈራ፣

ከማጀቱ ሲያራ፣

እናቱ ተነሽ፣

ቅዘኑን አብሽ፣

በዚያውም ቅመሽ፣

አዋዜ መስሎሽ፡፡

በሚል ዜማና ጨዋታ ማንኛውም ፈቃደኛ የሆነና ለመጫወት የፈለገ ሁሉ ከእረኞች ጋር በመሆን ደመቅ ባለ ሥነ-ሥርዓት መጫወት ይችላል (አቶ ደርበው ታረቀኝ ቁ.መ.አ.20/08/2010 ዓ.ም)፡፡

የቀሩ ወጣቶችንም እየሰደቡ እንዲሰበሰቡ ያደርጋሉ፡፡ ከተሰበሰቡ በኂላ በየዓመቱ ጨዋታዉ ወደ ሚካሄድበት ስፍራ እየጨፈሩ ይሄዳሉ፡፡ ከተጫዋቾቹ መካከል በእድሜና በአነጋገሩ የተሻለዉ ቆም ይልና በማጨብጨብ እንጨት ካለበት የሚያመጡ ወጣቶችን መርጦ ይልካል፡፡ አብዛኛዉን ጊዜ እንጨት በማንጣት ስራ ላይ ሴቶች አይሳተፉም፡፡ ወንዶች ብቻ ናቸዉ፡፡ ከጓሮ ፣ ከበርሃ ሰዉ ሳያየቸዉ የቻሉትን ያህል እንጨት ይዘዉ ይመጣሉ፡፡




ምስል 30፡-የጨዋታዉ አጀማመር ሂደት

ከዚያም እሳት ያነዱና በዕድሜና በጉልበት የሚቀራረቡ ወጣቶች የቡድን አለቃ ሆነው ይመረጡና ለመጫወት ፈቃደኛ የሆኑትን ወጣቶች በማሻኮት ለቡድኑ ስያሜ በመስጠት ሁለት ሁለት እየሆኑ ወደ ቡድን አለቆች እየቀረቡ “ከእንትና እና ከእንትና” በማለት ለምርጫ ያቀርባሉ፡፡ ተረኛው አለቃም የፈለገውን ጠርቶ ይመርጣል፡፡ የቀረው ለቀረው ቡድን አባል ይሆናል፡፡ የቡድኑ አባላት እርስ በርሳቸው ከተዋወቁ በኃላ መጫወት የማይችል አንድ ሰው “አቃቢ” ተብሎ ለምትወረወረው ድቡልቡል ድንጋይ ይመደባል፡፡ ይህ አቃቢ ድቡልቡሏን የመጫወቻ ድንጋይ ከእሳቱ እያወጣ ወደ ተጫዋቾቹ የሚወረውር ነው፡፡

### 4.2.5.3 በዓላዊ ዘፈኖችና ውዝዋዜዎች

አብዛኛው የዋግኽምራ ብሔረሰብ የክርስትና እምነት ተከታይ ነው፡፡ በመሆኑም ሰሞነ ህማማት/ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ የተቀበለበትን ሳምንት ከሃይማኖታዊ ይዘቱ ባሻገር በባህላዊ ክዋኔም ጭምር ያከብሩታል፡፡ የክዋኔውን ሁኔታ አስመልክተው ቁልፍ የመረጃ አቀባዬ መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል እንደሚከተለው ገልፀዋል፡-

> የበዓሉ ክዋኔ የሚጀመረው በአቢይ ፆም አጋማሽ ቀናት ላይ እሁድ ቀን ነው፡፡ ሴቶች ሕፃናት ከቤታቸው የተነከረ ባቄላ (በቆልት) ይዘው ከመንደራቸው ወይም ከአካባቢያቸው ወጣ ብለው በሚያገኙት ዛፍ ላይ ከከብት ቆዳ በተሰራ ባህላዊ በሆነ ጠፍር ኸዋኸዌ በመስራት በዚህ በሰቆጣ እና አካባቢዋ በአማርኛ ፤ በሌሎች ወረዳዎች ደግሞ በኽምጣንኛ ቋንቋ እንደሚከተለው እየዘፈኑ እለቱን ያከብሩታል፡፡

| | |
|---|---|
| ሸውዮ ምርዬ… ሸውዮ ምርዬ<br>አደ… አየ<br>ይቃመቀ ደደሱን… አውል<br>አውል አውሌ ወሬት ቃሚል | አውል አውሌ ወፊት ቃሚል |
| አደት ማልወጠድ ሲያሁ…<br>ናንል ጠምሳይንድ ቃንዙ… | አደት ማል ወጣድ ሊያሁ  ናንል ጣምጎይድ ቃንዙ |
| አቀቅም ድረድ ይሌሻት…<br>ብረላይ ሰላይ ሞት… | አቀቃን ድረይ ይከተሻት<br>ብረት ላይ ሰላይ ሞት |

ከዚያ በወሩ የስቅለት ቀን ዋዜማ ወይም የፀሎተ ሃሙስ ሁሉም የአካባቢው ህፃናት አንድ ላይ በመሰባሰብ ከአንደኛው ቤት ሲጫወቱ ያድሩና ከዚያም ሌሊት ዘጠኝ ሠዓት አካባቢ ሲሆን ከእንቅልፋቸው በመነሳት በእጃቸው ነጭ የሚያበራ ድንጋይ ይዘው በማጋጨት በየቤቱ አበባ እየጣሉ በኽምጣንኛና በአማርኛ እንደሚከተለው እያሉ ይዘፍናሉ፡-

- ሳ ስብርብር ስብርብር
  የመቤቴ ጥርስ ምን ያምር ምን ያምር
  ሳ ስብርብር፡፡
- ሳ ሰምበሌጣ ሰምበሌጣ
  የመቤቴ ጥርስ ምን ይነጣ ፣
  ሳ ሰምበሌጣ፡፡
- እመቤቴ ይነሱ ፣
  ያድሉ ዱቄት ያንሱ ፣
  የእመቤቴ አዳራሽ ፣
  ተከፍክፏል በሻሽ፡፡
- አንድ አውራ ዶሮ…
  እግሩን ተሰብሮ ፣
  ያንኩቱለት ፣
  ስለ ስቅለት፡፡
- ዛቅ ዛቅ ከዱቄቱ ፣
  ዛቅ ዛቅ ከዱቄቱ፡፡

እነዚህን ዜማዎች በየቤቱ እየገቡ በሚያዜሙበት ሰዓት እንደየቤቱ እንደ አቅማቸው ያላቸውን ድቁስ ፣ በርበሬ ፣ ዱቄት ፣ ዘይት ፣ ጥሬ ጨው ሌላም ይሰጧቸዋል ፤ ሲሰጧቸውም እንዲህ እያሉ ያወድሷቸዋል፡፡

አሙሾ ቡሾ ሙሾ

ላም በበረቴ

ልጅ በደረቴ

እመቤቴ ይስጥልኝ ሰንበቴ፡፡

ካልሰጧቸውም ደግሞ እንደሚከተለው በዜማ እንደሚሳደቡ መረጃ ሰጭዬ እንደሚከተለው ገልፀዋል፡-

አልሰጥም አለች… ማናት

አሚዶ … እራሷን በሚዶ

የተቀበሉትን ስጦታ ወስደው አንድ ላይ ጋግረው ይበሉታል ፤ የተረፈውን ደግሞ ቅዳሜ ወጥ ሰርተው ይበሉታል፡፡ ወንዶቹም በተራቸው ቅዳሜ ወደ ማታ ላይ፡

እዮኒ ኒቅላ ያመቱ ይሙላ

እዮ ኒቅላ በየአመቱ ጠላ

የእመቤቴ ደጅ ይሸታል የወይን ጠጅ

አንድ አውራ ዶሮ.. እግሩን ተሰብሮ

ያንኩቱለት … ስለ ስቅለት

የደራ ዳቦ… ስለ አቦ

የደራ ትኩሴ… ስለነፍሴ

የደራ ጉርሻ ስለ ጉርሻ፡፡

እያሉ በየቤቱ እየጨፈሩ የተሰጣቸውን እየተቀበሉ እሁድ ማለዳ ላይ ድሮ ድሮ ፍየል ወይም ዶሮ ሰርቀው ይመጡና አንድ ላይ ማታ ካሰባሰቡት ዱቄት ወይም ዳቦ ጋር አሰርተው ይበሉ ነበር ፤ አሁን አሁን ግን ስርቆቱ ቀርቶ ገንዘብ አዋጥተው ወይም ከወላጆቻቸው ጠይቀው ፍየልም ሆነ ዶሮ ያርዱና አሰርተው እስካለቀ ድረስ ይበሉታል (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ፡ ቃ.መ.አ.10/10/2010 ዓ.ም)፡፡

ወጣቶቹም ይህንን ባህላዊ ጨዋታ በመከናወናቸዉ መንፈሳዊ እርካታንና ሃሴትን ያገኙበታል ፤ ማህበራዊ ግንኙነታቸዉንም ያጠናከሩበታል ፤ እንዲሁም ሃይማኖታዊ በረከትም እንደሚያገኙበት መረጃ ሰጪዎቹ ገልፀዉልኛል፡፡ መረጃ ሰጪዎቹም ስለባህላዊ ጨዋታዉ ያላቸዉን ስጋትም ሲገልጹ፡-

ባህላዊ ጨዋታዉ በአሁኑ ሰዓት ቀንሷል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ወጣቶቹ የዘመናዊ አስተሳሰብ ሰለባ በመሆናቸዉ ነዉ፡፡ ዘመናዊ አስተሳሰብ ከፍተኛ ተጽኖ

አድርሶባቸዋለዋል፡፡ ክዋኔዉን እንደኋላቀርነት እያዩ በሚጫወቱት ልጆችም ላይ ሳይቀር መጥፎ ቃልን ይናገሯቸዋል፡፡ የዉጪ ባህል ወረራዉ ከፍተኛ ነዉ፡፡ ይህም የቴክኖሎጂ መስፋፋት እንደሆነ መቼም አያጠራጥርም፡፡ ባህሉን እንደማይጠብቅም እና እንደኃላቀርነት እያዩት ስለሆነ የሚከዉኑት ወጣቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸዉ እየቀነሰ መምጣቱን እያየን ነዉ (አቶ ደርነዉ ታረቀኝ ቃ.መ. 07/10/2010 ዓ.ም)፡፡

በዋግኽምራ ብሔረሰብ በባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ የተቀነባበሩ እና ያለሙዚቃ መሳሪያ የሚዜሙ ተወዳጅ ዘፈኖች አሉ፡፡ እነዚህን መንፈስን የሚያነሳሱ ዜማዎችን በሚከወኑበት ጊዜ የማህበረሰቡ እስክስታዎች አሉ፡፡እነዚህም ጋኪ ምት ፣ ዋንጫ ልቅለቃ ፣ መንትግ እና ስራምት በመባል የሚታወቁ ናቸው (አቶ ባዬ አስመሮም ፣ ቃ.መ. 07/10/2010 ዓ.መ)፡፡

ከላይ መረጃ ሰጪዉ እንደተገለፀዉ ዉዝዋዜዎቹ ስያሜያቸዉን ያገኙት ከሚያዩት እንቅስቃሴና ከታወቁበት ወይም ከተገኙበት ቦታ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡

እነዚህም ውዝዋዜዎች በማንኛውም ቦታ በሰርግ ፣ በክብረ በዓላት እንዲሁም በሎሌች ውዝዋዜ በሚጠይቁ ክስተቶች ላይ በማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ያለገደብ በህብረት በሙዚቃ መሣሪያ ወይም ያለሙዚቃ መሳሪያ ሲከወኑ ይታያሉ፡፡ እነዚህ ውዝዋዜዎች ሲከወኑ የራሳቸው የሆነ የአከዋወን ስልትና ይዘት አላቸው፡፡ይህም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

**ጋኪ ምት፡-** ይህ ውዝዋዜ ስያሜውን ያገኘው በብሔረሰብ ዞኑ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል ደሃና ወረዳ ውስጥ ከሚገኘው የጋኪ አካባቢ ተወላጆች በተለያየ አጋጣሚ ሲከወኑ በመታየታቸው ፣ ከጊዜ በኋላ እንደ ጋኪ ልጆች እየተባለ ሲወርድ ሲዋረድ ጋኪ ምት እንደተባለ መረጃ ሰጪዎች ገልፀዋል (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ አስራት ታደሰ ፣ ቃመ. 20/10/2010 ዓ.ም)፡፡

በሚከወኑበት ጊዜ መንትግ ከሚባለው የውዝዋዜ ዓይነት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም የዚህ ውዝዋዜ መለያ ባህርይ ግን እጅን በወገብ በማድረግ ከአንገት በላይ ወደፊት ወደኃላ በማድረግ ከጉልበት አልፎ አልፎ ዝቅ እያሉ ትከሻን ከፍ ዝቅ በማድረግ የሚከውኑት የውዝዋዜ ዓይነት ነው፡፡

***መንትግ፡-*** ይህ የውዝዋዜ ዓይነት የሚከወነው አንገትን ግራና ቀኝ ሰያፍ በማድረግ አንድ ጊዜ ወደ ቀኝ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ግራ በማንሳት ወይም ደግሞ በአካባቢው አጠራር በመመንተግ ከትከሻ እንቅስቃሴ ጋር የሚከወን ሲሆን ስያሜውም ከክዋኔው እንደተገኘ መረጃ ሰጪዎች ገልፀውልኛል፡፡

***ሶራ ምት፡-*** ይህ የውዝዋዜ ዓይነት የሚከወነው ሁለቱንም እጆች እንደ ቡጢ ጠንከር አድርጎ ወደ ፊት በመዘርጋትና በማጠፍ ከትከሻ እንቅስቃሴ ጋር ከታች ከጉልበት በታች ትንሽ ጎንበት እያሉ የሚከወን የውዝዋዜ ዓይነት ነው፡፡

***ዋንጫ ልቅለቃ፡-*** ስያሜውን ያገኘው የውዝዋዜውን ክንውን በትከሻ መሆኑ ሲሆን ከዋንጫ ስራ አንዱ የሆነው ዋልጫ ልቅለቃ ጋር ስለሚመሳሰል እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ገልፀዋል፡፡ ውዝዋዜው የሚከወነውም ትከሻን በማፈራረቅ አንዴ ቀኝ አንዴ ግራን ወደታች ወደላይ በማድረግ ነው፡፡

እንዚህ ከላይ የተጠቀሱት ውዝዋዜዎች በሁለቱም ፆታ በማንኛውም ጊዜ በከበሮ እና በመሰንቆ በመታጀብ በህብረት እንደሚከውኑት በመረጃ አቀባዮቼ ተገልጧል፡፡ ውዝዋዜዎቹ ሲከወኑ በዜማውና በእንቅስቃሴው የነሸጠው ሁሉ ምንም የተለየ አለባበስና ጌጣጌጥ ሳያስፈልገው የክዋኔው ተሳታፊ መሆን እንደሚችል በምልከታየ ወቅት ለመገንዘብ ችያለሁ፡፡

እነዚህን የውዝዋዜ አይነቶች የብሄረሰቡ አባላት በመከወናቸው ከፍተኛ የሆነ ፋይዳ እንደሚያስገኝላቸው ከመረጃ አቀባዮቼ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ እኔም ራሴ ባደረኩት ምልከታ የሚያገኙትን ማህበራዊ ፋይዳ ለማወቅ ችያለሁ፡፡ የብሔረሰቡ ልዩ ልዩ አባላት በውዝዋዜዎቹ ሲሳተፉ ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ያጠናክራሉ ፤ ራሳቸውን ከማዝናናትና ከማስደሰት በላይም ማህበረሰቡን ወይም በወቅቱ የተገኘውን ታዳሚ እና ተመልካቹን በማዝናናት ከጭንቀትና ከሃሳብ ለጊዜውም ቢሆን እንደሚያላቅቁት በክዋኔው ወቅት ተሳታፊ የነበሩት አዛውንት ገልፀውልኛል፡፡

> ”የኔ ልጅ” አሉኝ ይህ የአገራችን እስክስታና ጭፈራ በሰርግ ፣ በክብረ በዓላት በጥምቀት ፣ በስቅለት ፣ በፅዋ ማህበር ሳይቀር ሰው በሚደሰትበት ሁሉ ሲበላ ሲጠጣ አንድ ሰው ነሸጥ አድርጎት ማዜም ከጀመረ ሁላችንም በጭብጨባ ፣ አብሮ በማቀንቀን እያጀብን ሁላችንም እንደየአቅማችን ትከሻችንን እናሳያለን፡፡

> ወጣቱ ደግሞ ሁለት ሁለት እየሆነ ላለመሸነፍ ውዝዋዜውን ያስነካዋል፡፡ እኛም አባቶች አይዞህ/ሽ እያልን እያበረታታን እናስቀጥለዋለን፡፡ መቼም የሰው አሳሩ ብዙ ነው ፤ ሀሳቡ የትየለሌ ነው ፤ በዚህ ወቅት ሁሉን ረስተን በልጆቻችን ጭፈራ ፣ ዘፈን ፣ ጨዋታ እኛም እንደ ልጅ ሆነን በማዜም ፣ በመወዛወዝ ከተጫነን የሀሳብ ሸክም እንገላገላለን ፤ ሁሉም ይጠፋል፡፡ ይህማ ባይኖር ጭንቀቱ ፣ አሳሩ ፣ ኸረ ስንቱ ባጭር ያስቀረን ነበር እያልኩ እኔ ለራሴ እገረማለሁ፡፡ ልጆ ነፍሳችን ታርፋለች ትደሰታለች፡፡ እንዳየኸው አያምርም ነፍስን ያስደስታል (ቄስ ደምሴ መኮንን ፣ ቃመ. 20/08/2010 ዓ.ም)፡፡

ከላይ ቄስ ደምሴ መኮንን እንደገለፁት እነዚህ የውዝዋዜ አይነቶች ለብሔረሰቡ አባላት የሚያስገኙት ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ ማህበረሰቡን ከሃሳብ ፣ ከትካዜና ከጭንቀት ይታደጋሉ፡፡ ለጊዜውም ቢሆን ማህበረሰቡን የነፍስ መንፈሳዊ ደስታን እና ንፃትን ሰጥተውታል፡፡ በክዋኔው ውስጥ የሚሳተፉት ወጣቶች ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡን በማዝናናታቸውና በማስደሰታቸው ከፍተኛ የሆ ደስታ  እንደሚሰጣች በምልከታዬ ወቅት አረጋግጫለሁ፡፡

የዞኑ ባህልና ቱሪዝም ባለሙያ የሆኑት አቶ ባዬ አስምሮም እንደገለጹልኝ፡-

> እነዚህን የውዝዋዜ ዓይነቶች የሚከውኑት እና በድምፅና በመሳሪያ የሚያጅቧቸው አማተር  ወጣቶች ይህን በማድረጋቸው የሚያገኙት ክፍያ የለም፡፡ በሰርግና በአንዳንድ በዓላት ደስ ያለው ግለሰብ ሊሸልማቸው ይችል ይሆናል፡ ፡ከዚያ ባለፈ እንደ ባለሙያ ተቆጥረው ገንዘብ አያገኙም፡፡ አሁን አሁን በየወረዳው ባሉ የባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት የባህል ቡድኖች ተቀጥረው ብቃት ያላቸው እንደመተዳደሪያ እየያዙት መጥተዋል ፤ በዞን ደረጃም ይኸው መዋቅር አለ፡፡ ክዋኔውን የሚያጅቡ አንደ ከበሮ እና መሰንቆ አልፎ አልፎም ዋሽንት ይጠቀማሉ ፤ እስካሁን ብዙም ትኩረት ሳይሰጠው ቆይቷል፡፡ እነዚህን ተወዛዋዥ ወጣቶች ተጨማሪ ስልጠና በመስጠትና በማገዝ ራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለዞኑም ትልቅ የገቢ ምንጭ ሊያስገኙ እንደሚችሉ እየታመነበት መጥቷል፡፡ በመሆኑም ለብሔረሰቡ ብቻ ሳይሆን ውዝዋዜዎቹ በአገር አቀፍም በክልልም እየታወቁ መጥተዋል ፤ ለምሳሌ "ሶራ ምት" የተባለው በሁሉም ታዋቂ እየሆነ ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን ለማሳደግ ጥረት እናደርጋለን፡፡ ተወዛዋዦቹንም የበለጠ በስልጠና

እናግዛለን፡፡ ገቢም እንዲያገኙ እና ባህላወዊ ውዝዋዜውን የበለጠ በማበልፀግ ለመንፈሳዊ ደስታ እና ለተዝናኖት ብቻ ሳይሆን ለኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማግኛም እንዲሆን እንጥራለን (አቶ ባዬ አስምሮም ፣ ቃመ. 07/10/2010 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ በላይ ከብሔረሰቡ አባቶችም ሆነ ከዞኑ የባህልና ቱሪዝም ባለሙያ ለመረዳት የሚቻለው ቅርሱ/የባህል ውዝዋዜው/ተፈላጊነቱና ተከዋኝነቱ እየጨመረ መምጣቱን ነው፡ ፡ ለዚህም በዞኑ ውስጥ የተቋቋመው የባህል ቡድኖች ቅርሱን በማስተዋወቅና በመተግበር የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አባቶቸችም ሆነ ወጣቶቹ ስጋታቸውን ይገልፃሉ፡፡

> … በአብዛኛው ቅርሱ ጊዜ በወለዳቸውና በግለሰቦች ፈጠራ በሆኑ ውዝዋዜዎች ታክሎ ስለሚከወን የቅርሱ ቀደምት ክዋኔ አደጋ ውስጥ ነው፡፡ ባህላዊ ይዘቱንና ቅርጹን ጠብቆ እየተከወነ አይደለም፡፡ቅርጹንም ሆነ ይዘቱን ከትውልድ ወደ ትውልድ መዝለቅ አለበት፡፡ ዋናው ነገር ይህ ነው፡፡ ከባህላዊው ክዋኔ በተለየ መልኩ ከግለሰቦች ፈጠራ ጋር እየተቀላቀለ በመቅረቡ ባህላዎ ይዘቱ ቀስበቀስ ሊጠፋ ይችላል፡፡ መቼም አባት ለልጁ የሚያወርሰው ከቅድመ አያቶቹ ያገኘውን ሳያጓድል እንጂ ቀንሶ ወይም አሳንሶመሆን የለበትም፡፡ መሰረቱን ማሳጣት አይገባም ፤ ይህ እየተስተካከለ ቢሄድ መልካም ነው፡፡ ይህን ይህን ስናይ እናዝናለን በዞኑ መቋቋሙ ቢያስደስተንም፡፡ መቼም አሳመርን ፣ አሻሻልን ብለው ይሆናል ፣ አውቀው መቼም አይሆንም፡፡ (አቶ ብርሃኑ ወርቁ ፣ ቃመ. 08/10/2009 ዓ.ም ፣ አቶ ቸኮለ ካሳው ፣ ቃመ. 08/10/2009 ዓ.ም)፡፡

ከላይ መረዳት እንደሚቻለው ብሔረሰቡ ባህሉን/ቅርሱን ቅርጽና ይዘቱን ሳይለውጥ ተጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ ያለበት መሆኑን ነው፡፡ እነሱ የተረከቡትን ለቀጣዩ ሲያስሰላልፉ እንዳገኙት ሁኔታ እንጂ አሳንሰው ወይም ቀንሰው እንዳልሆነ ሁሉ አሁን ግን እየተበረዘ በመሆኑ አምርረው ቅሬታቸውን ገልፀዋል፡፡መነሻችን አይጥፋ ማንነታችን ነውና ማለታቸው ነው፡፡

ውዝዋዜው በሚከወንበት ወቅት ልዩ የሆነ የአለባበስና የአጋጌጥ ስርዓት የለም፡፡ ውዝዋዜዎቹ የሚከወኑት ለክብረ በዓል ከሆነ ግን የክብረ በዓሉን አለባበስና አጋጌጥ ይከተላሉ፡፡ ሌሎች ሥነ ሥርዓቶችም ከሆኑ እንደዚሁ፡፡ ለምሳሌ ወጣቶች ለጥምቀት

ቀን ወንድ ወጣቶች ጸጉራቸውን ጎፈሬ አበጥረው በላዩ ላይ ማበጠሪያ ሰክተው ከላይ ኳርቶ የተባለ ልብስ ፣ ከታች ቁምጣ ለብሰው ዱላ ይዘው ወይም በባዶ ሲከውኑ ፣ ሴቶች ደግሞ ጋሜና ቁንጮ ወይም ሹሩባ ተሰርተው ጥልፍ ለብሰው ፣ መቀነት ታጥቀው ፣ ማርዳ የተባለ ጌጥ አርገው ይከውኑታል (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቀ.መ.አ. 20/08/2010 ዓ.ም)፡፡

እነዚህ ከላይ የተገለጹት ባህላዊ አልባሳት የብሔረሰቡ ወጣት ወንዶችና ሴቶች በክብረ በዓላት እና በሌሎች ልዩ በሆኑ የብሔረሰቡ የክብረ በዓል ሥነ ሥርዓት ጊዜ የሚለብሷቸው የአለባበስ ዓይነቶች በማንኛውም ጊዜ ማህበረሰቡ ደስታውን በዘፈን በሚገልፅባቸው አውዶች ላይ በማንኛው የአለባበስ እና አጋጊያጥ ሁኔታ ሊከወኑ የሚችሉ መሆናቸውን ነው፡፡ ስለሆነም ለውዝዋዜም ሆነ ለጭፈራው እነዚህን በመልበሳቸው በክዋኔው ጊዜ ከመሳተፍ የሚያግዳቸው የለም፡፡





ምስል 31፡- ባህላዊ ውዝዋዜ (ፎቶ ዋግኽምራ ዞን ባቱ)

#### 4.2.5.4. የሥራ ላይ ዘፈኖች

የዋግኽምራ ብሔረሰብ መሠረታዊ የሆኑ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ኑሮው የተመሰረተው በአብዛኛው በእርሻ ላይ ነው፡፡ የእርሻ ሥራውንም ውጤታማ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፡፡ ይኼውም የመሬት ጥበት ሲገጥመው አዲስ እዳሬ መሬት መንጥሮ ያወጣል ፤ ያንን ያለስልሳል ፤ ጥሩ ማሳ እንዲሆን ይለፋል ፤ ይደክማል ፤ ዘለግ ያለ ጊዜም ያለ

ዕረፍት በመስራት በበሬ በማረስ ያዘጋጀዋል፡፡ ይህንኑ ልፋቱንና ድካሙን ለመርሳትና ለማስታወስ በቃላዊ ግጥሞች በእንጉርጉሮ/በዜማ በታጀበ መልኩ እንዲህ በማለት ይገልፀዋል፡-

1. እሸሩሩ በርየ እሸሩሩ!
   ባልተመነጠረው ገባበት ከዱሩ፣
2. እሬቱን መንጥሮ እንዳይዘራ እህል፣
   እሾሁን መንጥሮ እንዳይበላ እህል
3. የግራሩን ስር መንጥሮ የሚያርሰው፣
   ነጭ ጤፍ አብቃይ ጊዜ የማይጥለው፡፡
4. ምን ያደርግልኛል የምላስ ጉልበት፣
   እሬቱን መንጥረህ ሻሾ ዝራበት፡፡
5. በጎብላላ በሬ ድብ ካላፈረሱ፣
   አዳራሽ አይሞቅም ኩራዝ ቢለኩሱ፡፡
6. ያርሳስ ያሳርሳል ያወጣል እዳሪ፣
   ሚስቱን አይላትም ብቅል ተበደሪ፡፡ (አቶ ቸኮለ ካሳው ፣ ቃመ. 08/10/2009 ዓ.ም)፡፡

ከነዚህ ቃል ግጥሞች መረዳት የሚቻለው መሬት ጠበበኝ ብሎ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ድህነትን እንጂ ክብረትን አያስገኝምና ዱሩን መጥሮ እዳሪ አውጥቶ አዲስ ማሳን ማውጣት አስፈላጊ ነው የሚል ሲሆን የስራ ትጋትን አስፈላጊነት ያሳያል፡፡ የስራ ተነሳሽነትን የሚሰብክና የሚያበረታታ ህዝባዊ እሴት ነው፡፡ መረጃ አቀባዮቹ ይህንን የበለጠ አጠንክረው እንደሚከተለው ገልፀውልኛል፡፡

> ከምንጣሮ ስራ ቀጥሎ የሚከናወነው መሬቱን በማረስ ማለስለስ ይሆናል፡፡ የእርሻ ሥራ ለማከናወን ደግሞ የግድ በሬ ያስፈልጋል፡፡ በሬ ከሌለው ያሰበውን ያክል ምርት በሰፊው አያገኝም ፤ መሬቱንም ማረስ አይችልም፡፡ በሬ ደግሞ ያለ ገበሬ ሊያርስ አይችልም ፤ መሬቱንም ማረስ አይችልም፡፡ በሬና ገበሬ እጅና ጓንት ናቸው፡፡ ለዚህም ነው ከግብርና ሥራዎች ገበሬው የበሬውን አስፈላጊነት በቃል ግጥሞች የሚያወድሰው በሬውን ከማወደስ በተጨማሪም ገበሬውን በእርሻ ወቅት በማበረታታት በማዝናናት በእርሻው ውጤታማ እንዲሆን ያግዛል፡፡ በብሔረሰቡ

ልዩ ልዩ ወረዳዎች በሚገኙ ቀበሌዎች ውስጥ በእርሻ ወቅት የሚባሉና የሚነገሩ የእርሻ አስፈላጊነትን የሚገልፁ ቃል ግጥሞች በርካታ ናቸው፡፡

ለአብነት ያህል የሚከተሉትን በሰቆጣ ወረዳ ዙሪያ የሚገኙ ገበሬዎች የሚገጥሟቸውን የግብርና የእርሻ ላይ ግጥሞችን እንመልከት:

1. ሚያዚያ ግም ሲል ግንቦት ሲያገሳ፣
   አከናናቢ ጉድጓድ ከማሳ፡፡
2. ሐምሌ ግም ሲል ሲነደል ባህር፣
   አሻግሮ ተኳሽ ከሞፈሩ ስር፡፡
3. ሐምሌ ሲያረበርብ ደመናው ሲመጣ፣
   በአጭር በመታጠቅ ወደ እርሻ ልውጣ፣
   የወፈፈን ሳምንት ፍልሰታ ሳትመጣ፡፡
4. እንኳንስ ፍልሰታ በሐምሌ ወፈፈን፣
   በደንብ ላላረሰ ይቸግራል አሁን፡፡
5. በዚህ አንድ በዚያ አንድ ሰላሳ ቢወራ፣
   አርሳለሁ መርሬ ዝናብም አልፈራ፡፡
6. አርሳለሁ እንጂ አልመረርም፣
   ችግር በወንጭፍ አይባረርም፡፡
   መራር ገበሬ ከቤቱ አይውልም፣
   እርሻ የሌላት ሙሃቻ አታምርም፡፡
7. እርሻ እረሱ ለእርሻ አትመለሱ፣
   አቦሉ ሲፈላ ይቸግራል ቁርሱ፣
   አበዳሪ ቢገኝ ይቸግራል ዋሱ፡፡
8. ማረስ ነው እንጂ እርፍ እስኪንጫጫ፣
   ማፈስ አይገኝ ጠላ በዋንጫ፡፡
9. ድቡን ከድቡ ካልደባለቁት፣
   አዳራሽ አይሞቅም ኩራዝ ቢያነዱት፡፡
10. ያርሳል በደመና ይቆፍራል በጉም፣
   ከሰው ማሳ ሄዶ ምራን አይዘረጉም፡፡ (ቡ.ተ.ው 20/08/2010 ዓ.ም)

ከላይ ከተገለጹት ቃል ግጥሞች የምንረዳው ጠንክሮ ማረስ አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ ካላረሱ ድህነት ሊወርሳቸው እንደሚችል ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም የሥራን አስፈላጊነት አጠንክረው የሚገልጹ አወንታዊ የሆኑ ቀስቃሽ ግጥሞች ናቸው፡፡ ፋይዳቸውም ከፍተኛ ነው፡፡ ለገበሬው ተዝናኖትን ብቻ ሳይሆን ተስፋውንም የማለምለም ከፍተኛ የሆነ ጥቅም አላቸው፡፡

ገበሬው እርሻውን ሲያረስ ፣ ሲወቃ ፣ ወዘተ የበሬውን አጋርነትና አጋዥነትም አይረሳም ያዋድሰዋል ፣ ያሞግሰዋል ፣ እያቆላመጠ በመጥራት በግጥም ምስጋናውንም ይነግረዋል ልክ እንደ አንድ ሰብዳዊ ፍጡር አስቦ፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን በቡድን ውይይት ጊዜ የነገሩኝን ብንመለከት አንድ ገበሬ የበሬውን አጋርነት ስለሚያውቀው በሬውን ይንከባከበዋል፡፡ በእርሻ ሥራ ወቅት ገበሬው የበሬውን አስፈላጊነት በቃላዊ ግጥሙ በሬውን እያወደሰ የእርሻ ሥራውን ያከናውናል፡፡ ገበሬው በሬውን የሚያወድሱበትን የበሬውን አስፈላጊነት የሚገልፅባቸው በእንጉርጉሮ የታጀቡ ቃላዊ ግጥሞች አሉት፡፡ ለአብነት ያህል ከዚህ በታች ቀርበዋል፡-

1. በሬና ገበሬ ቢጣሉም አይበጅ፣
   እንደው ስተት ብሎ ይጠመዳል እንጅ፡፡
2. ብቻ ጉሬዛ ደህና ብቻ ቡሬ ደህና፣
   እጠምዳለሁ በጧት ሳይመጣ ደመና፡፡
3. ካረሱም አይቀር ሞፈር ከበሱ፣
   እንደ ቦራ ነው እንደ ቀሲሱ፣
   የሰርዶውን ሳር እያፈረሱ፣
   ሰፋፊ ማሳ እያለበሱ፡፡
4. አረማመዱ የገደል ናዳ፣
   አያጎዳም ወይ ቡሬ ቢከዳ፡፡
5. እስኪ እናንተ ተደጋገፉ፣
   ሰው ምቀኛ ወራቱ ክፉ፡፡
6. አሰራለታለሁ ድር በድር ቀረጤ፣
   ለብርብራው መጋል ለዚህ ለቀለጤ፡፡
7. የወይኑ ጌታ የስመ ጥሩ፣

የመጋል ጌታ የስመ ጥሩ፣

ማዕበል የመታው ይመስላል ፈሩ፡፡

8. መጋል ነውና ያቀናው ቤቱን፣

በሬው ነውና ያቀናው ቤቱን፣

እንኳን ጥሬውን ይብላው ዱቄቱን፡፡ (ቡ.ተ.ው ፣ 20/08/2010 ዓ.ም)፡፡

ገበሬው እርሻውን እያረሰ በሬውን እያወደሰ ይውላል ፤ ያረሰውን ደግሞ ማጎልጎል ይኖርበታል፡፡ ሳሩን ፣ ቅጠሉንና የመሳሰሉትን አፈሩ ከሰርዶው መለየት አለበት፡፡ ይህም ሂደት ጉልጓሎ ይባላል፡፡ የሚረዳው ካለ ከስር ከስር ይከናወናል፡፡ በዚህም ወቅት ዝም አይልም ያንጎራጉራል፡፡ በጉልጓሎ ጊዜ የሚዜሙ ማበረታቻ ቃላዊ ግጥሞችም አሉ፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን መረጃ አቀባዮቼ ያቀበሉኝን እንመልከት፡-

1. ታታሪው ገበሬ ወረደ ወደ እርሻ፣

   ውራኑን ልቀመው ጓሉን ከስክሰው፡፡

2. ሳጎለጉል ውዬ ሳጎለጉል መሸ፣

   ማታ ምን ላቀይ ነው ለዚያች ለትንቡሼ፡፡

3. ሳርስ ሳርስ ውዬ እጎለጉላለሁ፣

   ምንም አልተረፈኝ ማታ ምን እላለሁ፣

   ድንቡሼን ሳላያት በእንቅልፍ እወድቃለሁ፡፡

እያለ ሲያንጎራጉር የትዳር ጓደኛውን ፍቅርም እንደሚያሳስበው እያዋዛ ሌላም ስራ እንዳለበት ይገልፃል (ሳቅ እያሉ ነገሩኝ)፡፡ በዚህም ገበሬው ራሱን ከድካሙ እየተፍታታ ስራውን ሲያቀላጥፍ ይውላል በማለት ገልፀዋል (ደረበው ታረቀኝ ፣ ቁ.መ.አ 16/09/2010 ዓ.ም)፡፡ አቶ ደርበው በመቀጠልም ለስልሶና በደንብ ታይሞና ተቀብቅቦ ማሳው ይዘራል፡፡ የተዘራውም ሲበቅል ደግሞ ጊዜውን ጠብቆ ሰብሉን ከአረም መለየት ይመጣል፡፡ በዚህም ሥራው ይቀጥላል፡፡ የአረም ጊዜም የሚነገሩ ቃል ግጥሞች አሉ፡፡ እነዚህ ቃል ግጥሞች ለሥራ ማነቃቂያና ማቀላጠፊያ እንዲሁም ድካምን ያስረሳሉ፡፡ አረም ማረም ምርትን ከማሳደግ በተጨማሪ የምርት ጥራትን ይጨምራል፡፡ ገበሬው ይህንን ተግባር በቃል ግጥሙ እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡፡

1. ማለዳ ተነስተን አረሙን እናጥፋ፣

ቡቃያው እንዲያምር እህሉ እንዲፋፋ፡፡

2. ቅንጨ አረምን አጥፉ እንዲሁም ዋሪቶች፣
   በግብዣችሁ እለት እንዳይሆን እሬት፡፡
3. ጤፉን አረም በላው ቀለባችንን፣
   አንቺ ልጅ አርሚ እንጣላለን፡፡
4. አባቱ ነበር ክምር ከማሪ፣
   ልጁ ደረሰ እርሻ አሳማሪ፡፡ (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቃመ 16/09/2010 ዓ.ም ፣ አፅንኦት የኔ ነው)፡፡

የብሔረሰቡ አባላት የቃል ግጥሞቻቸውን የሚያንጎራጉሩት ለተዝናኖት ብቻ ሳይሆን ገና ከእርሻ ሥራው ጀምረው በጥንቃቄና በጥራት ያልታረሰ መሬት ከፍተኛ ምርት ሊሰጥ እንደማይችል ምክራቸውን ለመግለፅና ለማስጠንቀቅ ነው፡፡ በተጨማሪም አረሙ ካልታረመ ሰብሉ መቀጨጩን ፣ የቀጨጨው ደግሞ ከሰው ፊት ሊያሳፍር እንደሚችል ሀሳባቸውንና ልምዳቸውን እንደሚገልጹ ብሎም ሌላውም ጠንካራና አስተዋይ እንዲሆን ልምዳቸውንና እውቀታቸውን እንደሚያስተላልፉ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

አብዛኛው የዋግኽምራ ብሔረሰብ አባላት በገጠር የሚኖርና በግብርና ስራ የሚተዳደር በመሆኑ የእርሻ ስራ የተለመደ ነው፡፡ ይህንን ስራ የሚያከናውኑበት ጊዜ ከየካቲት እስከ ሰኔ ባሉት ወራት ነው፡፡ ወንዶች ወጣቶችና ጎልማሶች አልፎ አልፎም ሽማግሌዎች በሬዎቹን ለማነቃቂያ እነሱም በልበ ሙሉነት ሥራቸውን ለመስራት የእርሻ ጊዜ ዘፈኖቹን ምን እያሉ እንደሚገልጹ የዝቋላ ወረዳ ነዋሪ የሆኑት አቶ አምዴ ተክሉ እንዲህ ያብራሩታል፡-

> በዚህ እኛ አገር እርሻ ሲታረስ ገበሬው ከፍየል ቆዳ የምትሰራ ከለሜዳ ለብሶ ሞፈር ቀንበሩን ማረሻውን ገጥሞ ዕርፉን ጨብጦ መሬቱን እያረሰ አልፎ አልፎ በመሃል በፉጨት እና በንግግር በሬውን ‹‹ቀና በል›› ፣ “ውጣ” ፣ “ግባ” እያለ የእርሻ ጊዜ ዘፈኖቹን በግጥምና በዜማ አምላኩን በሬዎቹንና ላሞቹን ፣ ሃገሩንና ወዳጆቹን እያወደሰ ፍቅሩን ጥላቻውን … ኸረ ምኑ ቅጡ… ትዝብቱን እንዲሁም አስተሳሰቡን በዘፈን በሬዎቹን “ሃይ” እያለ እንደሚከተለው ይላል፡፡

| | |
|---|---|
| - ይቢረቺለይ ሃርጉን ዳምረነው<br>ጨውናኒዝ ጭናነው ይቢረ<br>መላኩ ቀሰው ግርየተር ኩ | -ሌት ተነስቼ የሚጠምድህ<br>ባደረ እጂ የማገኝህ በሬየ ነህ<br>በሬዬ መላኩ ጥሩ ዘመን |
| - ይልሆ ብርዙዎ ኟርትን ቆሾነይ<br>ጋውነ ጋቁር ድቁ ጋልብነ ዝይነይ<br>ጋቅም እፍትን ግዘይን ይወነይ | ማለዳ ተነስቼ ማልብሽ<br>ከልጆቼከ ሚስቴ ጋር እንደፈለኩ ወተት የምጠጣብሽ<br>ከኛም ተርፎ ለጎረቤት የተረፍሽ ላሜ ነሽ፡፡ |
| - ይኟግር ዝቋላ እነ አልምድ ጊፍተ<br>ሰነድ ያናናኒል ሰየድ ይናናኒል<br>ይኟገር ዝቋላ እነ አልምድ ጊፍተ | - ወተት ማሩ ቅቤው በእጃችን<br>የሆነበትን ይህን አገር ይህን አለም<br>ዝቋላ አትንሳን ጌታችን፡፡ |
| - ያንቀናንትነድ ክትም ቀንድረሽ<br>አርበጆው ጥማይዘን ሽመቅል በርሽ | -እኔ እንደምወድሽ ትወጅኛለሽ ወይ<br>ጨረቃ በሌለበት ጨለማን ሽማግሌ ላኪ፡፡ |
| - ትዝን ገዝው እጅር እርከነ ኒንቀው<br>እጉድ ጥርድ ኮኩሉኝ ሚስኪረም ዚልቃው፡፡ | - እርሻ ያረሰ እርፍ የነቀነቀ<br>ወፍጮው እንዳጓራ መስከረም<br>ዘለቀ፡፡ |

(አቶ አምዴ ተክሉ ፣ ቃመ. 23/08/2010 ዓ.ም ፣ ትርጉም የሳቸው ነው)፡፡

የስራ ላይ ዘፈኖች በሚዜሙበት ጊዜ ለገበሬው የሚያስገኙትን ጥቅም/ፋይዳ/ አቶ አምዴ ተክሉ ሲያብራሩም ‹‹ሞቅ ይለዋል ፤ ይዝናናል ፤ ይደሰታል ፤ ከሃሳብና ከትካዜ በመላቀቅ ስራውን በትክክልና በንቃት በልበ ሙሉነት ይሰራል፡፡ እንደ ኃይል ሰጪነት ያገለግላሉ፡፡ በሬውም እርሻውን የሚያረሰው እራሱም ሲደክመው እንደሚነቃቃ ይረዳዋል›› በማለት ገልፀዋል (ቃመ. 23/08/2010 ዓ.ም)፡፡

የእርሻ ስራ ዘፈን በሚዘፈንበት ጊዜ አራሹ በሬውን ከእርሻ መሳሪያዎቹ ጋር አጣምሮ እያረሰ በፉጨት እና በንግግር በሬውን “ቀና በል” ፣ “ውጣ” ፣ “ግባ” እያለ የእርሻ ዘፈኖቹን ቢዘፍንም ስጋት ያለባቸው መሆኑን መረጃ ሰጪዎቹ እንዲህ ይገልፃሉ፡፡

> የእርሻ ላይ እንጉርጉሯችን አሁንም ልማዱ አልቀነም ፤ ነገር ግር ከአማርኛ ቋንቋ ጋር ተያይዞ እየተቀላቀለ የአባት አደሩን የቀድሞውን መልክና መጠን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ በኽምጣኝ የሚባለውን ይዞ ባይቀጥልም አሁንም ድረስ በአማርኛና በኽምጣንኛ ተቀላቅሎ እየተባለ ነው፡፡ መቀላቀሉ መጥሮ ሆኖ ሳይሆን የአባቶች ልማድ ፣ ለዛ ባይጠፋ ፣ ባይስት ጥሩ ነው፡፡ አረኞች ሳር ሲያግጡ የሚነፉት ዋሽንት ፣ አለባበስ ፣ ውዝዋዜ ቀደም ሲል ይተቹ ነበር፡፡ አሁን ግን እሱ በመልካም ቀጥሏል፡፡ በሬዎቻቸውን ሳር እያበሉ ፣ ቀና ብለው በዓይናቸው እያዩ ይጫወታሉ፡፡ የእርሻ ላይ ዘፈኑን በተገቢው ለመተግበር የጎረቤት አካባቢዎ ቅልቅል ብቻ ሳይሆን ሌላም ችግር እየገጠመው ነው፡፡ አካባቢው በድርቅ አልፎ አልፎ ስለሚመታ ቅርሱ በወቅቱ የመተግበሩ ነገር አደጋ ውስጥ ነው፡፡መቼም ስራው በከፊልም ቢሆን እየተዳከመ ከመምጣቱ በስተቀር ልማዱ የዚያን ያህል ስጋት ውስጥ አለመሆኑንም አክለው ገልፀዋል (አቶ ተፈሪ አስማረ ፣ ቃመ. 20/08/2010 ዓ.ም ፣አቶ ባዬ አስምሮም ቃመ. 7/10/2009 ዓ.ም ፣ አፅንኦቱ የኔ ነው)፡፡

ከዚህ በላይ ከተገለፀው ለመረዳት የሚቻለው የብሄረሰቡ አባላት ባህላቸውን /እንደነሱ አባባል “የአባት አደሩ”/ እንዳይበረዝና እንዳይጠፋባቸው በንቃት የሚከታተሉ መሆናቸውን ፤ በክዋኔው ወቅትም የአከዋወኑ ቅርፅ/መልክ ፣ መጠንና የሚያስተላልፈው ይዘት እንዳይለወጥ አጥብቀው ይሻሉ፡፡ የሌሎች አካባቢ የጎረቤት ቋንቋ ተፅዕኖው እንዳይበረታ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው መሆኑ በአፅንኦት ገልፀዋል፡፡ sባህላቸው የማንነታቸው መገለጫ መሆኑን ተረድተው ለዘላቂነቱ ወሳኝ ጉዳይ ቅርጹና ይዘቱ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

## 4.3. ሀገረሰባዊ እምነቶችና መድሀኒቶች

ኽምራዎች ሁሉም ማለት በሚቻል ሁኔታ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡ በ2007 ዓ.ም በተካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሪፓርት እንደሚያሳየው ከዋግኽምራ

ነዋሪዎች መካከል 426,213 (99.6% ) የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ ነው ፤ ይሁን እንጂ በጥንት ጊዜ የነበሯቸው ባህላዊና መንፈሳዊ እምነቶችን ዛሬም ቢሆን ከክርስትናው እምነት ጋር አጣምረው በገጠሩ አካባቢ ይተገብሯቸዋል፡፡ እነዚህ ባህላዊ እምነቶች በተለይም በገጠሩ አካባቢዎች ጨርሰው እንዳልጠፉና ዛሬም በሽታን ለመፈወስ ፣ ነገን የሚተነብዩና ከሚመጣው ክፉ ነገር እንዲጠበቁ አስቀድመው የሚያስጠነቅቁ መፍትሔ የሚሰጡ አዋቂዎች/ጠንቋይ በቁጥር ትንሽ ቢሆኑም አሁንም ድረስ አሉ (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ፣ ቁ.መ.አ 21/10/2009 ዓ.ም)፡፡

እነዚህን አዋቂዎች/ጠንቋይ "አዋቂ" አልፎ አልፎም ‹‹ሴቦች›› እያሉ ይጠሯቸዋል፡፡ ትርጉሙ ጠንቋይ በአማኞቹ "ሁሉንም የሚያውቅ ፣ አዋቂ ፣ ምንም ነገር የማይጠፋው ፣ የሚታያቸው ፣ አዳኝ" ማለት ነው፡፡ በተከታዮቹ ዘንድ እንደ መንፈሳዊ (ዛር) አባት የሚታዩና የሚከበሩ ፣ መጪውን የሚነግሩ እና ታሞ ወደነሱ የሚሄድን በባህላዊ መድሃኒት የሚያድኑ ናቸው ተብለው የሚታመንባቸው ናቸው፡፡ ይህንንም የመፈወስ ኃይል ያገኙት ከዘራቸው/ከአባቶቻቸው የተላለፈ እንደሆነ እና የተመረጡ መሆናቸውንም ራሳቸው ይናገራሉ፡፡ ከተማ ነዋሪው እና አንዳንድ ሰለጠን የሚሉ ሰዎች ሴቦች ናቸው! አጭበርባሪ ናቸው! ምንም አያውቁም እያሉ ቢሏቸውም በተለይም በዚህ በስሬ ቀበሌ ያሉት "አዋቂዎች" ምንም አይመስላቸውም፡፡ እንደውም ራሳቸው "የአባት የእናቴ ውቃቢ በቅርብ ቀን ያሳየኛል ፣ ተሳድበው አዋርደው አይቀሩም ፣ እዚህ መጥተው ያንደፋደፏታል" በማለት ይዝታሉ፡፡ ይህንን የሚሰማም ሰው "ተው" ከነዚህ ጋር አትጣሉ ፣ ደግ አይደለም ፣ ትቀጠፋላችሁ›› በማለትም ሌሎችን ይመክራሉ፡፡ እኔ እስከማውቃቸው ድረስ የታመሙ ሰዎች ወይም ዕቃ የጠፋባቸው ወይም የተሰረቀባቸው ሰዎች ወደነሱ ሄደው ዕቃውን አስመለሰላቸው ፣ ሌባውን አስቀባጠሩ ፣ ወዘተ እያሉ ሰዎች ስለነሱ ሲያወሩ ሲገረሙ አሰማለሁ ፤ እኔ ግን ባይኔ ወይም በአካል ድርጊቱንም አይቼ አላውቅም፡፡ ዋናው ግን ሰዎቹ እንደ አጠቃላይ ይፈራሉ ፣ ይታመናሉ ፤ ብሎም በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ በክብርም በፍርሃትም ይታያሉ (አቶ መለስ ታረቀ ፣ ቃመ.15/09/2011 ዓ.ም)፡፡

እነዚህ አዋቂዎች በብዛት የሚሰሩና የሚገኙ ባይሆኑም ማህበረሰቡ በስፋት በሚኖርባቸው የገጠር አካባቢዎች ዛሬም እንደሚገኙ በመረጃ ስብስበው ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ዛርና የጥንቆላ ሥራዎች እንደሚከናወኑ እንደ አመታዊ በዓልም

ጥቅምት 12 ቀን/ሚካኤልን/ በከፍተኛ ደረጃ ደግሰው እንደሚያከብሩም ተረጋግጧል፡፡ ዛር ያለባቸው/የተነሳባቸው ሴቶችም አጉርተው በዛር አባታቸው አማካኝነትም ተገዝቶ እና ምሱን ተሰጥቶት ያለ ዓመት ላይነሳ ተገስጾ ስነ ስርዓቱ መቋጨቱንም ገልፀውልኛል (መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ፣ ቁ.መ.አ 12/02/2010 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ ሌላ በዋግኽምራ ብሔረሰብ የባህል መድሃኒት አዋቂዎች ሲኖሩ ለልዩ ልዩ በሽታዎች መድሃኒቶችን በባህላዊ መንገድ በማዘጋጀት ይሰጣሉ፡፡ እነዚህ ከጠንቋዮቹ የሚለዩት "ረጋ ተናጋሪ"/የወደፊቱን ተንባይ /ባለመሆናቸው ነው፡፡ የወደፊቱን እናውቃለን ብለው የሚተነብዩ አይደሉም ፤ እንዲህ መሳይ ስራን አይሰሩም፡፡ በዚህ ጥናት የባህል መድሃኒት አዋቂዎች ተሳትፈዋል[40]፡፡ የብሄረሰቡ የባህል መድሃኒት አዋቂዎች ከተለያዩ በሽታዎች ሰዎችን የሚፈውሱባቸው እንስሶቻቸውን ከህመም የሚታደጉበት በርካታ ባህላዊ መድሃኒቶች አሏቸው፡፡ አብዛኞቹ መድሃኒቶች የሚዘጋጁት ከተለያዩ እፅዋት ነው፡፡ መድሃኒቶቹን የሚያዘጋጁት የባህል መድሃኒት አዋቂዎች ሲሆኑ በትላልቅ ሽማግሌዎችና በሁሉም የብሔረሰቡ አባላት የሚታወቁና የሚዘጋጁ አንዳንድ መድሃኒቶችም አሉ (አቶ አስራት ታደሰ ፣ ቃመ. 18/10/2010 ዓ.ም)፡፡



ምስል 32፡- ለፎረፎር መድሃኒትነት የሚያገለግለው ግሸ ዛፍ (ፎቶ ዋግኽምራ ዞን ባቱ)

[40] የባህል መድሃኒት አዋቂ አሠራር በትንታኔው ላይ በዝርዝር እዚያው ይቀርባል፡፡ ድግግሞሽ እንዳይኖር በሚል እዚህ ላይ አልተገለፀም፡፡

ከዚህ ላይ ለመገንዘብ የሚቻለው በዋግኽምራ ብሔረሰብ ከኦርቶዶክሳዊ እምነት ጎን ለጎን የሚተገብሯቸው ሀገረሰባዊ እምነቶችን የሚጠቀሙባቸው ባህላዊ መድሃኒቶች መኖራቸውን ነው፡፡

## 4.4. ሥነ-ቃላዊ መገለጫዎች

የዋግኽምራ ብሔረሰብ በቃል በሚነገሩ ፣ በሚተረቱ ወይም በሚዜሙ በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ ታሪካቸውንና የሕይወት መልኮቻቸውን የሚገልጹባቸው ቃላዊ ጥበቦች አሏቸው፡፡ ይህም ብሔረሰቡ በረጅም ዘመን ታሪካቸው ያጠራቀሙት እና የሚያጠራቅሙት ቅርስ ከመሆኑም በላይ ለህልውናቸው ሲሉ በሚያደርጉዋቸው እንቅስቃሴዎች ምክንያት እሚከሰት ፣ ከአካባቢያቸው ከተፈጥሮ ጋር ካላቸው መስተጋብር እና ትግል የሚፈጠር የአያሌ ገጠመኞች ክምችትና የገጠመኞችም ማንፀባረቂያ ነው፡፡ በዚህ ቃላዊ ጥበብ ማህበረሰቦች ማንነትንና ምንነትን ፣ እምነትን ፣ የኑሮ ዘይቤንና ፍልስፍናን በጥቅሉም አመለካከታቸውን ቀርጾ ለተተኪው ትውልድ የሚያስተላልፉበት ነው፡፡ እነዚህም አፋዊ ስነ-ጥበቦች ወይም ስነ-ቃሎች በርካታ ቢሆኑም ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ለማሳያ ማንሳት ይቻላል፡፡ ተረት ፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች ፣ እንቆቅልሽ ፣ እንካ ሰላንቲያ ፣ አፈ-ታሪክ ፣ ምርቃት ፣ እርግማን ፣ ፉከራ ፣ ቀረርቶ ፣ የሰርግ ፣ የሙሾ ፣ የቡሄ በሉ ፣ የእንቁጣጣሽ ፣ የእርሻ ፣ የአጨዳ ፣ የውቂያ ፣ የጣውንት ፣ የልመና ፣ የብሶትመግለጫ ፣ የህፃናት ማባበያ ፣ የጨዋታ ግጥሞች ፣ ቀልዶች ፤ ስለ ሰው ፣ ስለ እንስሳትና ተፈጥሮ አመጣጥና ባህሪ የሚገልፁ ሀተታ ዘፍጥረት (myth) የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ የአኗኗር ዘይቤ የሚገልጹ ቃላዊ መገለጫዎች ትኩረት ሰጥተን ስንመለከታቸው በሁለት ዋና ዋና ቅርጾች ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ ይኼውም በቃል በዝርው ቅርፅ የሚገለፁና በቃል በግጥም ቅርፅ የሚባሉ ወይም የሚነገሩ ናቸው፡፡ በቃል በግጥም የሚገለፁ በልዩ ልዩ የማህበረሰቡ ማህበራዊ አውዶች/በሰርግ ፣ በለቅሶ ፣ በእርሻ ስራ ወቅት አጨዳ ፣ ውቂያ ፣ አረም ፣ ወዘተ/ውስጥ በዜማ በመታጀብ ይከናወናሉ፡፡ በዝርው የሚቀርቡት ወይም የሚከሰቱት ደግሞ በመተረት ፣ በመተረክ ፣ በቀልድ ፣ በምሳሌያዊ አባባሎች ፣ የአንድን ነገር ወይም ፍጥረት አመጣጥ በመግለፅ ወዘተ መልክ በመቅረብ የማህበረሰቡን እምነት ፣ ፍልስፍና ፣ አስተምህሮ ያሳያሉ፡፡ እነዚህ የተዘረዘሩት ስነ-ቃላዊ መገለጫዎች የማህበረሰቡን የአሠራርና የአኗኗር ጥበቡን ፣

ደስታና ሀዘኑን ፣ ፍቅሩንና ጥላቻውን ከመግለፃቸውም ባሻገር ስራውን ለማፋጠን ፣ ድካሙን ለመርሳት ራዕዩን ከግብ ለማድረስም ይጠቀሙታል፡፡ በመሆኑም ሥነ-ቃላዊ መገለጫዎች ልማትን ለማምጣት ሊኖራቸው የሚችለውን አዎንታዊና አሉታዊ አንድምታ ካላቸው ለማየት የተወሰኑትን በቅርፃቸው ከፍለን ለማየት እንሞክራለን፡፡ ይህንንም ስናደርግ የሥነ ቃልን ማህበራዊ ፋይዳነት ለመግለፅና ለማወቅ ይረዳናል ከሚል እሳቤ በመነሳት ነው፡፡ ሥነ-ቃላዊ መረጃዎች የተገኙት በቃል መጠይቅና በቡድን ውይይት/ቡድን ተኮር ውይይት/ በተደረገበት ወቅት ነው፡፡

### 4.4.1. ቃል ግጥም

የዋግኽምራ ብሔረሰብ ዋነኛ መተዳደሪያው ግብርና እና ከፊል ንግድ በመሆኑ በተለያየ የሥራ አጋጣሚዎቻቸው ላይ የሚጠቀሙባቸው /የሚገልጹዋቸው ቃላዊ ግጥሞች አሉዋቸው፡፡ ቁልፍ የመረጃ አቀባዬ የሆኑት አቶ ደርበው ቃረቀኝ የሚከተሉትን ከግብርና ሥራ ጋር የተያያዙ ቃላው ግጥሞችን ነግረውኛል፡፡

ገበሬው እርሻ እያረሰ የሚያንጎራጉረው ስንኞች:

1. በጎባባ ሞፈር በለሰለሰ፣
   አፈሩ ሞልቶ ገደል ፈሰሰ፡፡
2. ዝናቡ መጣ ከአየር ርቆ፣
   ሂድ ግፋ ይላል መርገጥ አጥብቆ፡፡
3. ማረስ ነው እንጂ እስኪቆስል፣
   ስርቆት ምንድነው ውሻ ይመስል፡፡
4. ሲያርሙ አያርም ሲዘሩ አይዘራ፣
   ይገመግማል የሰው አዝመራ፣
   ይቀነቅናል የሰው ጎተራ፡፡
5. አርሳለሁ እንጂ አላማርርም፣
   ችጋር በወንጭፍ አይባረርም፡፡
6. በወይና በሬ ካላሉት ላይ ላይ፣
   እንጀራ አይገኝ ከመሶቡ ላይ፡፡
7. እርሻ እረሱ ለእርሻ አትመለሱ፣

እርሻ ያረሰ ሰው እረጅም ነው ዳሱ፡፡

8. እርሻ ያረሰ እርፍ የነቀነቀ፣

   ወፍጮው እንዳጓራ መስከረም ዘለቀ፡፡ (ቁ.መ.አ ፣ 6/10/2009 ዓ.ም)፡፡

ከወረዳው ገበሬዎች/የሰቆጣ ዙሪያ ወረዳን ማለታችን ነው/እርሻውን በመቀናጆ ፣ አረሙን በወንፊል ፣በደቢያት/ሌላውን በማገዝ/አልፊው ለአጨዳ በሚደርሱበት ጊዜ ያሳለፏቸውን የስቃይና የደስታ ጊዜያት እንዲህ እያሉ በዜማ በታጀበ መልኩ መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቁ.መ. አ፣6/10/2009 ዓ.ም)፡፡

9. ማጭዱን ስደደው እስከ ውላጋው፣

   እያጨደ ይምጣ እየጨረሰው፡፡

10. አይዞሽ አልቤኔ አይዞሽ ማጭዴ፣

   አጎርስሻለሁ ገብስና ስንዴ፡፡

11. እርሶአደር ቢኮራ ምርቱን አምርቶ ነው፣

   ተማሪ ቢኮራ ውጤት አምጥቶ ነው፣

   እረኛ ቢኮራ ፍየል ጠብቆ ነው፣

   ሴት ብትኮራ ቤቷን መስርታ ነው፣

   የሌባ ኩራቱ ከምን የመጣ ነው፡፡

12. የጎበዝ ማጭድ ከጎበዝ ያውቃታል፣

   እንደ ጉሽ ጠላ ፉትም ይሏታል፡፡

13. የጎበዝ አልቤን ደም የለመደው፣

   እየበላው መጣ እየጎመደው፡፡

14. ማጭዴ ሞኙ አልቤኔ ሞኙ፣

   ከመከር ጀምሮ የሰው ጤፍ ከዋኙ፡፡

**በውቂያ ጊዜ**

15. በሬ በሬ ብየ የምወዘውዘው፣

   እንጀራ አይበላም አምላክ ካላዘዘው፡፡

16. ኸረ በሬ ሆይ! ኸረ በሬ ሆይ!

   ያልሰራ ሲበላ እምቢ አትልሞይ!

17.አዝናለሁ ለበሬ አዝናለሁ ለበሬ፣
በገዛ ጅራፉ ሲገርፈው ገበሬ፡፡
18.የበሬ ቀላሽ የወንድም ትንሽ፣
እንኳን በሰላሳ አይገኝም በሺ፡፡
19.ኸረ በሬ ማሩ ላብላህ ከድንበሩ፣
ላጠጣህ ከባህሩ፣
አንተ በሬ ሙዝ አትውረድ ከወንዝ፣
አለቅት አለ አሉ የሚወዘውዝ፣
እኔና በርየ እንሂድ ምናኔ፣
አንተም ልኩራ በል እኔም ልሁን ሎሌ፡፡ (ቡ.ተ.ው ፣ 20/08/2010 ዓ.ም)

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ቃላዊ ግጥሞች የስራ ላይ ግጥሞች ናቸው፡፡ የስራ ላይ ግጥሞቹም የሚዜሙት የማህበረሰቡ መተዳደሪያ ግብርና/እርሻ እንደመሆኑ በስራ ላይ የሚከወኑ ናቸው፡፡ የስራ ግጥሞቹ በተናጠልና በሕብረት ሊደረደሩ ይችላሉ፡፡ ይኼውም ገበሬው ሲያርስ ብቻውን ከበሬዎቹ ጋር ለበሬዎቹ ወይም ለራሱ ድካም እንዳይሰማው ሊገለገልባቸው ይችላል፡፡ ሲያጭድ ፣ ሲወቃ ፣ ሲያርም ከሌሎቹ አጋሮቹ ጋር በህብረት ሊደረድሩ ይችላሉ፡፡ የስራ ላይ ግጥሞቹ ለስራው ብርታትን በመጨመር እንደስራ ማስኬጃ ያገለግላሉ፡፡ያለድካም ስሜትም ስራቸውን በተቀላጠፈ መልኩ ለማከናወን ይረዳቸዋል፡፡

ገበሬዎቹ በስራ ላይ እያሉ ግጥሞቹን በሚደረድሩበት ጊዜ ጅራፍ ሞፈርና ቀንበር ፣ ማጭድ ፣ መንሽ ፣ ላዳና የመሳሰሉትን የእርሻ መገልገያ መሳሪያዎች በመያዝ የሚከውኑት መሆኑን በግጥሞቹ ውስጥ ስማቸው ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ ይህም የመገልገያ መሳሪያዎችን ሲያወድሱም ይታያል፡፡ ግጥሞቹን በተናጠልና በሕብረት እንዲሁም በመቀባበል የታዳሚዎችን አዕምሮ ለመያዝ እየተንጎራደዱ የሚከውኑት ሲሆን እልልታና ጭብጨባም የስራው ክዋኔ ማድመቂያና ማበረታቻ ናቸው፡፡

### 4.4.2 ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ምሳሌያዊ ንግግሮች ሥነ-ምግባርንና የስራ ክቡርነትን ያስተምራሉ፡፡ በዋግኽምራ ብሔረሰብ የስራ ክቡርነትን የሚያስተምሩ ወይም የሚያስገነዝቡ ምሳሌያዊ ንግግሮች የሚያሳዩ ከተሰበሰቡት የተወሰኑትን እንይ:

1. ያረሰ ለልጁ አጎረሰ፡፡
2. በእርሻ ጊዜ ያላረሰ በመኸር ጊዜ አያጭድም፡፡
3. ስራ ካልሰራችሁ የት ይምጣ ምሳችሁ፡፡
4. የጥቅምት እርሻ የእናት ጉርሻ፡፡

ከምሳሌያዊ ንግግሮቹ የምንረዳው የስራን አስፈላጊነት አበክረው መግለፃቸውን ነው፡፡ ስራን በወቅቱ ተግቶ የሰራ ችግር እንደማይገጥመው ያስተምራሉ፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሚዘወተሩትም በአዛውንቶችና በጎልማሳ የዕድሜ ክልል ባሉ ሰዎች ሲሆን በተለያዩ ድርጊቶች መነሻነት ቦታና ጊዜ ሳይገድባቸው ለጨዋታ እንዲሁም በአጋጣሚ ሰዎች በተገናኙበት /በተሰበሰቡበት/ ወቅት እንደሁኔታው ሀሳብን ለማስረገጫ ፣ እያዋዙ ቁም ነገርን ለማስተላለፊያ ፣ በለተይ ደግሞ አስተዳደራዊ በደሎች ሲኖሩ ነገርን ለማስተካከያ ፣ በሽምግልና ወቅት ጠበኞችን ወደ መስመር ለማስገቢያ ፣ የዳኝነት አካሄዱንም ለማሳመሪያና ወደ መፍትሄ ለመውሰጃ እንደ ትልቅ መሣሪያ የሚገለገሉበት እንደሆነ መረጃ አቀባዮቼ ገልፀውልኛል (አቶ አስራት ታደሰ ፣ 9/10/2009 ዓ.ም ፣ መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ፣ 6/10/2009 ዓ.ም ፣ አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቁ.መ.አ 06/10/2009 ዓ.ም)፡፡

አቶ ደርበው ታረቀኝ የምሳሌያዊ ንግግሮች ፋይዳ በርካታ መሆኑን የሚከተሉትን አባባሎች በመንገር በሰፊው ጥቅማቸውን ነግረውኛል፡፡

> ምሳሌያዊ አነጋገሮች ስለ ሃይማኖት ያስተምራሉ ፣ ማህበራዊ ልማዳቸውን ጠብቀው እንዲኖሩና ከሥርዓቱ እንዳያፈነግጡ ያስጠነቅቃሉ ፣ ሲያፈነግጥም የታየውንም ይቆጣጠራሉ ፤ የሥነ-ልቦና ተግባርም አላቸው፡፡ አስተዳደራዊ በደልና የፍርድ መዛባትን ለማስተካከል እንዲችሉ መሪዎችን ይገስፃሉ፡፡ እንዲስተካከልም ምክር ይሰጣሉ፡፡ እንደው በጠቅላላው ምሳሌያዊ ንግግሮች

ወይም አባባሎች ባህላዊ ሰነዶቻችን ፣ መመሪያዎቻን ናቸው ብል እውነቴን ነው፡ ፡ አላጋነንኩትም በማለት የፋይዳቸውን ዘርፈ ብዙነት አብራርተው የሚከተለውን ለአብነት ያህል ጠቅሰውልኛል፡፡

5. ሃይማኖት የሌለው ሰውና ልጓም የሌለው ፈረስ አንድ ናቸው፡፡
6. ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ስርቆት፡፡
7. ሃይማኖት ከግብር ጸሎት ከፍቅር፡፡

ምሳሌያዊ አነጋገሮች የማህበረሰቡን አባላት ማህበራዊ እሴታቸውን እንዲጠብቁና ከልማድ እንዳያፈነግጡ ይሰብካሉ ፤ ያፈነገጠውንም ይቆጣጠራሉ፡፡

8. የራሷ አሮባት የሰው ታማስላለች፡፡
9. የቅልብልብ አማት ሲሶ በትር አላት፡፡
10. ሁሉ አማረሽን ገበያ አታውጧት፡፡ (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቁ.መ.አ 6/10/2009 ዓ.ም)፡፡

ሥነ-ልቡናዊ ተግባር፡-

11. ልብ ደስ ሲለው ፊት ይበራል ፤ ልብ ሲያዝን ፊት ይጠቁራል፡፡
12. ሂድ አትበለው እንዲሄድ አድርገው፡፡
13. ሰው ማንን ያህላል ቢሉ የተናገረውን፡፡
14. እንዳያማ ጥራው እንዳይበላ ግፋው፡፡

ምሳሌያው አነጋገሮች በዘፈቀደ የሚነገሩ ሳይሆኑ በዕድሜ የሚገኝ ፣ የአዋቂነትና የብስለት ምልክት ናቸው፡፡ሊያመሰግኑ አሊያም ደግሞ የሚታመን ነገር ለመጠቆም ሲፈለግ ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡ መልካም የሰራን እንደስራው ለማወደስ ፣ ጥፋተኛውንም እንደ ጥፋቱ ለመገሰፅ ትልቅ መሣሪያ በመሆናቸው የብሔረሰቡ አባቶችና ጎልማሶች በከፍተኛ ሁኔታ ይገለገሉበታል፡፡ ፋይዳቸውም ከፍተኛ ነው፡፡

### 4.4.3. እንቆቅልሽ ጨዋታ

ወጣቶችና ልጆች እንቆቅልሽ የሚጫወቱት ከአእምሯቸውን ሊያሰሉና ሊያዝናኑ ነው፡፡ በጥያቄና መልሱ ሂደት መልሱን ለማግኘት የሚደረገው ጥረት ተጠያቂ የነበረ በተራው

ጠያቂ ሆኖ የተሻለ ጥያቄ ለመጠየቅ የሚደረገው ፉክክር ፣ ለጥያቄዎቹ የሚሰጡት መልሶች ፣ ተጠያቂዎች መልስ ሲሰጡ የሚጠብቁት ስድብ ሁሉ እርስ በርስ ከመጋጨት ይልቅ ያዝናናቸዋል፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን በዋግኽምራ ብሔረሰብ የሚጫወቱትን የእንቆቅልሽ ጨዋታ እንመልከት፡-

ጠያቂ፡-እንቆቅልህ!

ተጠያቂ፡-ምን አውቅልህ?

ጠያቂ፡-የጅብ አር ላሙቅልህ!

ተጠያቂ፡-በወይራ ዱላ ልጠቅልህ!

ጠያቂ፡-ትጠይቅ እንደሁ ጠይቅ!

ተጠያቂ፡-እሽ እጠይቃለሁ

ጠያቂ፡-እንቆቅልህ!

ተጠያቂ፡-ምን አውቅልህ?

ጠያቂ፡-ምን ቢወዷት እቤት አያውሏት!

ተጠያቂ፡-እሳት

ጠያቂ፡-አይደለም

ተጠያቂ፡-ዶሮ

ጠያቂ፡-ዋለብህ! አደረብህ!

ሰርዶ በቀለብህ!

እንደ እንጀራ ነፈሰብህ!

ተጠያቂ፡-እሺ ይግባልህ

ጠያቂ፡-እንኳን የገባልኝ

ጠያቂ፦የተንቧለለልኝ

ከሸዋ እስከ ጎንደር የተነጠፈልኝ

አገር ስጠኝ!

ተጠያቂ፦ኮረም

ጠያቂ፦ አውቀዋለሁ

ተጠያቂ፦ ወሎ

ጠያቂ፦ እሱንማ!ብዙ ዘመን ኖርኩበት

ተጠያቂ፦ አዲስ አበባ

ጠያቂ፦ አዲስ አበባ ሂጄ

ምን አጥቼ

ሁሉ በጄ ሁሉ በደጄ

ግርድ ግርዱን ለፈረሴ

ምርት ምርቱን ለራሴ

እንዳልሰድብህ ወንድሜ፣

እንዳልተውህ ጠላቴ፣

ከቤትህ በታች ያለው ልምጭ

እንዳንተው ነጭ

እንደ ሰፌድ ይዘርጋህ

በእኔ ጉሮሮ ጠጅ ይንቆርቆር

በአንተ ጉሮሮ አጥንት ይሰንቀር

ና! እንሂድ ጓሮ ለጓሮ

አበላሃለሁ የገማች ዶሮ፡፡ (ቡ.ተ.ው 20/8/2011 ዓ.ም)

በእንቀቅልሹ ወጣቶች ስለ አካባቢያቸው ምን ያህል እንደሚያውቁ መፈታተሻቸው አዕምሯቸውን ከማሰራታቸው በተጨማሪ ከጨዋታው ተዝናኖትን እና እርካታን እንዳገኙ መገመት አያስቸግርም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የሚጫወቱት ወጣቶችና ልጆች ናቸው፡፡ በፆታ ረገድ ልዩነት የለም፡፡ በለተይ እረኞች ከብቶቻቸውን እያገዱ ዛፍ ጥላ ስር በመሆን እንዲሁም ከብቶቻቸውን ሲያስገቡ እናት መቆያቸውን/መክከሳቸውን ሰጥተዋቸው እየበሉ የሚከውኑት እንደሆነ መረጃ አቀባዮቼ ገልጸውልኛል (ቡ.ተ.ው ፣ 20/8/2011 ዓ.ም)፡፡

የብሔረሰቡ ወጣቶች እንቆቅልሹን እየተዝናኑ የሚማሩበት ፣ የብሄረሰቡን ባህልና ወግ የሚያውቁበት እና በባህሉ ውስጥ የሚገኙትን ልዩ ልዩ የመገልገያ ቁሶች ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ የሚገነዘቡበትና ስለ አካባቢያቸው አጠቃላይ ሁኔታ ሰፋ ያለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አዕምሮአቸውን ለመፈተሽ የሚገለገሉበት በመሆኑ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

### 4.4.4 በትረካ መልኩ የሚቀርቡ

በዝርው ወይም በሃተታ የሚነገሩ ዋና ዋና የቃላዊ ጥበባት ዓይነቶች ሀተታ ዘፍጥረት ፣ አፈታሪክ እና ተረት በመባል የሚታወቁ ናቸው፡፡ የሀተታ ዘፍጥረት አተራረክን ሊያሳይ የሚችል ደብረ ወይላ ማርያም “የግራኝ እመቤት” በመባል የምትታወቀውን ገዳም እና ይህንን ስሟን እንዴት እንዳገኘች የሚተርከውን ትረካ እንመልከት፡፡ ትረካውን የተረኩልኝ አቶ ተፈሩ አስመራ የተባሉ የወረዳው የትምህርት ባለሙያ ናቸው፡፡ ደብረ ወይላ ማርያም ገዳም ብዙ ተዓምራት እንዳሏት እንደሚከተለው ያወሳሉ፡፡

> አንደኛውና “የግራኝ እመቤት” የሚል ስያሜ ያሰጣት እንዲህ ነው፡፡ በአጼ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግስት (በ1527 ዓ.ም) ግራኝ መሀመድ ንጉሱን ከሸዋ አሰደዳቸው፡፡ ከሸዋ ሸሽተው ያመለጡት አፄ ልብነ ድንግልም ወደ ደብረ ወይላ ማርያም መጥተው ለሶስት ቀን ያህል ተደብቀው ቆይተው ነበር፡፡ ግራኝ ንጉሱን ማግኘት ሳይቻለው ሲቀር ልጃቸውን ማርኮ በግዞት ስም አሰረው፡፡ አባቱ የት

> እንዳለ ይነግረው ዘንድም ሌት ተቀን በጅራፍ ሲገርፈው ከረመ፡፡ በመጨረሻም ንጉሱ በደብረ ወይላ ገዳም መሸሸጋቸውን የጭምጭምታ ወሬ ከግራኝ ጆሮ ደረሰ፡ ፡ በንዴት ገዳማትንና አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ እያቃጠለ ደብረ ወይላ ድረስ ሄደ ፡፡እሷን ሊያቃጥላት ሲሞክር ግን ከየት እንደመጣ ያልታወቀ ደም የቤተክርስቲያኗ የሳር ክዳን ላይ ተንጠባጠበ፡፡ ዘንዶ ወጥቶም ዙሪያዋን ተጠመጠመ፡፡ አንድ ትልቅ ዛፍ ላይ የነበረ የንብ መንጋም የግራኙ ሠራዊትና ፈረሶቹ ላይ መዓት አወረደባቸው፡፡ ግራኝ መሀመድ በመዓቱ ተገርሞ ለመሸሽ ሲሞክር የወይላ ወንዝ ሞልቶ አላሻግር አለው፡፡ በዚህም ግራ ተጋባ፡፡ በተአምሯ ስለተደነቀም ለክተት ከሚጎሰመው አንድ ነጋሪት ፣ የፈረሱን ማጠጫ ገንዳ ፣ ከነሃስ የተሰራ የእጅ መታጠቢያ ሳህን ፣ ወታደሮቹ ከለበሱት የወርቅ ለምድ ጨምሮ በስጦታ አበረከተላት፡፡ “ከዛሬ ጀምሮ የግራኝ እመቤት በሏት” ብሎ ተናግሮም ሄደ፡፡ ከዚያ ግዜ ጀምሮ ይህ መጠሪያዋ ሆነ፡፡ (አቶ ተፈሪ አስማረ ፣ ቃመ.20/08/2010 ዓ.ም) በማለት ተርከዋል፡፡ ከግራኝ መሃመድ የተበረከቱላት ስጦታዎች ዛሬም ድረስ እንዳሉ ጨምረዉ ገልጸዋል፡፡

ሌላዉ በዝርዉ ከሚገለጹት ቃላዊ ጥበባት ዉስጥ አፈ ታሪክ ሲሆን በሰቆጣ ከተማ ሰሜናዊ ምዕራብ በ40 ኪሎሜትር ርቀት ላይ “አባ ጠፍጣፋ” (በአገውኛ ጠፍጣፋ ተራራ ማለት ነው) በተባለ ተራራ አናት ላይ በአገውኛ ቋንቋ “ስርቁ” ወይም “አሰንጥ” በአማርኛ “ሙሽሮች” ተብለው የሚጠሩ ቁም ድንጋዮች ይታያሉ፡፡ እነዚህ ቁም ድንጋዮች እንዴት ሊፈጠሩ እንደቻሉ አቶ ደርበው ታረቀኝ እንዲህ ተርከውልኛል፡፡

> ሙሽራውና ሚዜዎቹ ሙሽራዋን ይዘው እየሄዱ ሳለ ዝናብ ዘነበና ደበደባቸው፡፡ “ምን ቁርበት ዝናብ ነው” ሲሉም ሰደቡት፡፡ በዚህም ምክንያት በዚያው ባሉበት ደርቀው ቀሩ እየተባለ በአፈታክ ይነገራል፡፡ ስያሜያቸውንም ያገኙት ከዚህ አፈታሪክ ነው፡፡ ሙሽሮቹ በሰልፍ የሚሄዱና ሰዎችን የሚመስሉ አምስት ድንጋዮች ናቸው፡፡ ከርቀት ሲመለከቷቸው ሙሽራዋን በበቅሎ ላይ አስቀምጠውና አጅበው በአካባቢው የባህል ስርዓት መሰረት ወደ ሙሽራው ቤት የሚለለሱ የአንድ ሰርገኛ ቡድን አባሎችን ይመስላሉ (ቁ.መ.አ ፣ 6/10/2009 ዓ.ም) ብለዋል፡፡

### 4.4.5 ምርቃትና እርግማን

በማንኛውም የማህበረሰብ ክፍል መልካም የሰራ እንደሚመሰገንና እንደሚመረቅ ሁሉ መጥፎ የሰራም እንደስራው የሚወገዝበትና የሚረገምበት ስርዓት አለ፡፡ በዋግኽምራ "ምርቃትና እርግማን" በተለያዩ ጉዳዮች መነሻነት ይከወናል፡፡ በብሔረሰቡም ምርቃት የሚከናወነው በወላጆች በእናትና አባት ፣ በሽምግልና ወቅት ፣ እንዲሁም ሥራን በደቦ ወይም በህብረት ተጋግዘው ከሰሩ በኋላ እርስ በርስ የሚመራረቁበት ልማድ አላቸው፡፡ ይህን አስመልክተው ቃለ መጠይቅ ያደረኩላቸው የዝቋላ ነዋሪ የሆኑት ቄስ ደምሴ መኮንን እንደሚከተለው ያብራራሉ፡

> ምርቃት ብዙ መልክ አለው፡፡ ዋናው ጉዳይ ለሚመረቀው አካል ጥሩ ነገር እንዲገጥመው ሲሆን መራቂው ለተመራቂው ከሰራው በጎ ነገር በመደሰት የተሻለ መልካም ነገር እንዲገጥመው ከልብ በሆነ መርካት የሚሰጥ በረከት ነው፡፡ መራቂው አባትና እናት ለልጃቸው/ለልጆቻቸው ታዛዥ ሲሆኑ ለበጎ ስራ የተጉና ወላጆቻቸውን የሚያግዙ ከሆነ "በጎ ይግጠማችሁ ፣ ትምህርታችሁን ይግለፅላችሁ ፣ ጉልበታችሁ የተባረከ ይሁን ፣ ለወግ ለማዕረግ ብቁ ፣ እደጉ ተመንደጉ፣ ክብር አግኙ" ብለው ይመርቃሉ ፤ በተቃራኒው ደግሞ ወላጆችን የሚገፉ ፣ የማይታዘዙ ፣ የሚያንጓጥጡ ፣ የማያከብሩ ለበጎ ስራ ያልተጉና ቤተሰቡን የሚያዋርዱ ከሆነ እርግማን አይቀርም፡፡ "የእጃችሁን አግኙ ፣ ወልዳችሁ አትሳሙ" በማለት ይረግማሉ፡፡ ሌላው የምርቃትና የእርግማን ሁኔታ ደግሞ በሽምግልና ወቅት የሚካሄደው ወግ/ባህል/ ነው፡፡ ይኼውም ጠበኞቹ በሽማግሌ ፊት ቀርበው የሽማግሌን ቃል አክብረው ‹‹አዎ በድያለሁ አጥፍቻለሁ ፣ ባጠፋሁት እክሳለሁ ፣ ወይም ይቅር ይበለኝ ይቅር ብያለሁ ከናንተ ከአባቶቼ ቃል አልወጣም የሚሉ ከሆነ›› ለሽማግሌ ቃል በመታዘዛቸው ከዐይን ያውጣችሁ ተብለው ይመረቃሉ፡፡ ለሽማግሌዎች ታዛዥ ባለመሆን እርቁን ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩና ገፍተው ከሄዱ ይወገዛሉ ፤ ይረገማሉ ፤ ይገለላሉ፡፡ ሌላው በሀገራችን (ዋግኽምራ ማለታቸው ነው) ሰዎች ሀዘን ሲገጥማቸው ወይ ደግሞ ሲቸገሩ ብቻ ሳይሆን በቁም በህመምና በሌሎችም ጊዜ የመረዳዳት ትልቅ ልምድ አለን፡፡ በዚህ ጊዜ ምርቃት ይደረጋል፡፡ ስራን በሕብረት/ደቦ /የመስራት ትልቅ ባህል ስላለን ስራው የተሰራለት ግለሰብ ከመብል

ከመጠጥ አቅርቦት ውጪ በስራው የተሳተፉትን ሁሉ የመመረቅ ሥነ-ስርዓት ያከናውናል፡፡ ያው እንደነገርኩህ ምርቃት አይነቱ ብዙ ነው፡፡ እርግማኑም እንዲሁ ነው፡፡ ለምርቃኑም ሆነ ለርግማኑ ዓይነቱ ይለያያል፡፡ የሠርግ ጊዜ ምርቃት አለ ፤ የተስካር ምርቃት አለ ፤ የክርስትና ምርቃት አለ ፤ አዲስ ቤት ሲሰራ የሚሰጥ ምርቃት አለ ፤ ሰዎች ለበጎ ምግባራቸው የሚሰጥ ምርቃት አለ፡ ፡ በግብርና ስራ ሲከናወን በሬውና ገበሬው ይመረቃሉ ልጄ! ማረሻው ሳይቀር ይመረቃል ፣ በአውድማ/ውቂያ ላይ የሚሰጥ ምርቃት አለ ፣ ሲዘራም እንዲሁ ምርቃት ይፈፀማል፡፡ ለዚህ ነው ብዙ ዓይነት የመመረቂያ ሁኔታዎች አሉ ብየ ያልኩህ (ቃመ. 28/06/2010 ዓ.ም)፡፡

ቄስ ደምሴ መኮንን ከላይ በገለጹት መሰረት ለአብነት ያህል የተወሰኑ የምርቃት ዓይነቶችን እንመልከት:

**የሰርግ ምርቃት**

ያጣምረን!

የአብርሃም የሳራ ጋብቻ ያድርግላችሁ!

በመጀመሪያ ተዋደዱ!

በኋላም ውለዱ!

ውለዱ ፤ ክበዱ፡፡

በወንድ ልጅ ተበከሩ!

በሴት ልጅ ተዘከሩ፡፡

ለእናት ለአባታችሁ የምታገለግሉ ሁኑ፡፡

የእውነት ጋብቻ ያድርግላችሁ፡፡

አባት ሁኑ ፣ አብራችሁ አርጁ፡፡

በአባት በእናታችሁ ደረጃ የምትገኙ ያድርጋችሁ፡፡

ለሰው የምትጠቅሙ ያድርጋችሁ፡፡

ማዳችሁ ሰፊ ይሁን፣

ስትወልዱ የወለዳችሁት የተባረከ ይሁን!

አሸቶ መቃምን!

ወልዶ መሳምን ለናንተ ይበለው፡፡

እንግዳ የምትሸኙ፣

ጌታችሁን የምታመሰግኑ፣

የምትቆርቡ የምትፀድቁ ያድርጋችሁ፡፡ (ቄስ)

**የግብርና ሙያን በሚመለከት የሚሰጥ ምርቃት**

- **ለበሬው የሚሰጥ ምርቃት**

ሽሆናህን ብረት፣

ጫንቃህን አለት ያድርገው፡፡

ስላንገላታሁህ ማረኝ

ሣሩ አይነቅህ

ከሣር ከገደሉ ያድንህ

እድሜውን ጨርሶ በድድ የሚያገለግል ያድርግህ

የማረሻውን ላንቃ ለምለም

የበሬውን ጫንቃ አለት ያድርገው፡፡

- **አውድማ ላይ የሚደረግ ምርቃን**

ሃይማኖት ያውርድ፡፡

እረድኤቱን ፣ በረከቱን ያውርድበት።

የጤና ቀለብ ያድርግልን።

ለጣረ ፣ ለጋረ ፣ ለለፋ ይበል።

ለዝክር የሰጠን አምላክ ፣ እህል ነስቶ አይጣለን።

ለሱ አፈሩ ፣ ለኛ ቀለባችን መሆኑን አውቆ ፣ ፈጣሪያችን ይባርክልን

ያበርክትልን ፣ ይንጨፍጨፍልን።

አህያ ይድከምበት፣

የጫነ ይድከምበት።

ክንድህን ምርት ይሸው።

ብዩን በልታችሁ፣

ዘሩን ዘርታችሁ፣

ከርሞ እዚህ ለመድረስ ያብቃችሁ።

- **በዘር ጊዜ**

በስመዐብ ወወልድ፣

ከወፍዐላፍ ፣ ከንዳድ ፣ ከበረድ ወጥተህ ለመበላት ያብቃህ

በእግሩ አፍልቶ፣

በራሱ አፍርቶ ፣ ለመበላት ፣ ለመታጨድ ያብቃህ።

በራሪ ወራሪ ፣ ናድ በረድ አለና ከዚህ ሁሉ አውጥተህ አብላኝ።

ከናድ ከበረድ ፣ አድንልን፣

ከውርጭ ከነፋስ ሰውርልን።

ከላይ ለአብነት ከተገለጹት የምርቃትና የእርግማን የብሔረሰቡ አፋዊ ጥበብ ቃላት ለመረዳት የሚቻለው መጥፎ ስራ ሰርቶ ከመወገዝ ጥሩና መልካም ስራ ሰርቶ መመረቅ ማህበራዊ ግንኙነትን ያጠናክራል፡፡ የስራ ተነሳሽነትን ይጨምራል፡፡ መንፈስ ጠንካራም ያደርጋል፡፡ በዚህም የቅርሱ ክዋኔ ከተጠቀሰው አንፃር በብሄረሰቡ ዘንድ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡

## 4.5. ሀገረ ሰባዊ የዕውቀት ትግበራ

ሀገረ-ሰብዓዊ ዕውቀት በአንድ መልክዓ ምድራዊ መቼት የሚኖሩ ማህበረሰቦች ከተፈጥሮ አካባቢያቸው የተሻለ ጥቅም ለማግኘት የሚያስችላቸው ዕውቀት ፣ ብልሃቶችና ክሂሎችን የሚያጠቃልል እሳቤ ነው፡፡ ይህ የእውቀት ስርዓት አንድ ማህበረሰብ በኑሮውና በደህንነቱ ውስጥ ለሚገጥሙት ፈተናዎች ፣ እክሎችና ማነቆዎች መፍትሔ ለመፈለግ ካደረጋቸው የረጅም ዘመናት ጥረቶች ፣ ሙከራዎች እና ውድቀቶች ነጥረው የወጡ ከትውልድ ለበቀለበት ሥነ-ምህዳራዊና ማህበራዊ መቼት ስለ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ተገቢነት እንዳላቸው የሚታመንባቸውን እምነቶችን ፣ ግንዛቤዎችንና ተፈጥሮአዊ ፍላጎቶችን ለማሟላትና አካባቢያዊ የኢኮኖሚያዊ ዕድሎችን ለመለወጥ የሚያስችሉ የአሠራር ስልቶች የመገልገያና የማምረቻ መሣሪያዎች አበጃጀት ዘዴዎች ይጠቀልላል፡፡ በመሆኑም የዋግኽምራ ብሔረሰብ አባላት ስለ አካባቢያቸውና ስለተፈጥሮ ያካበቱትን ዕውቀት በእለት ከእለት ሕይወታቸው ከሚገለጥባቸው ከእርሻ ዕውቀት ፣ የቤት አሰራር እና ከህክምና (ባህላዊ) እውቀታቸው አንፃር ከዚህ ጥናት ጋር የሚበጁትን ወስደን እንመልከት፡፡

### 4.5.1 ሀገረ ሰባዊ የቤት አሰራር

በዋግኽምራ ብሔረሰብ ዘንድ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ ጥንታዊና ባህላዊ የቤት አሰራር ዕውቀት አላቸው፡፡ ይህ ጥንታዊ የቤት አሰራር ዕውቀታቸው ከሌሎች አጎራባች ማህበረሰቦች ይለያቸዋል፡፡ ቤቱም ድራ ወይም ህድሞ በመባል ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ቤት እና አሰራር ዝርዝር መግለጫ የሰጡኝ አቶ አስራት ታደሰ እንዲህ ይገልጹታል፡፡

> ህድሞ በመባል የሚታወቀው የቤት አሰራር በዚህ በሰቆጣ ከተማ ጋዝ ቢቢላ ሰፈር በብዛት ይገኛል፡፡ ህድሞ ቤት በድንጋይና በጭቃ ብቻ የሚሰራ ሲሆ

አብዛኛውን ጊዜ ክብና ባለ አንድ ደርብ/ፎቅ/ ነው፡፡ ህድሞ ቤቶች የምድር ቤታቸውም ሆነ ደብራቸው ባለ አንድ ክፍል ሆኖ ይሰራል ፤ አልፎ አልፎ ባለሁለት ክፍልም ይገኛል፡፡ ወደ ፎቅ የሚያወጣው መወጣጫ/ደረጃ/ የአንዳንዶቹ ከውስጥ ፣ የአንዳንዶቹ ደግሞ ከውጭ ይሰራል፡፡ በብዛት የሚሰሩት ከታች በጭቃ ነስንሰው ከላይ በጭቃ አረብርበው ከራሱ ላይ አፈርና ጭቃ በመደልደል ከዚያ ቀጥለው ለመገንባት ከላይ ጣሪያውን ይጥሉታል፡፡ አልፎ አልፎም ጣሪያውን የሚይዙ ከአምስት እስከ ሰባት የሚደርሱ ምሰሶዎች ይተከላሉ፡፡ ጣሪያው ደግሞ የሰንበሌጥ ሳር ይለብሳል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ወደ ቆርቆሮ ክዳን እየተለወጠ ነው፡፡ በጣም ሞቃታማ በሆኑት እንደ አበርገሌና በመሳሰሉት አካባቢዎች ጣራቸውን በአፈር ማልበስም የተለመደ ነው፡፡ የህድሞ ቤቶችን ጣራ በቆርቆሮና በአፈር ማልበስም የተለመደ ነው፡፡ የህድሞ ቤቶችን ጣራ በቆርቆሮና በአፈር ማልበሱ የሚጠቅመው ሌላው ነገር በተለያዩ ምክንያት ከሚከሰት የእሳት አደጋ የንብረት ውድመት ለማዳን ሲባልም ነው፡፡ የህድሞ ቤቶቹ የአሰራር ጥበብ ጎልቶ የሚታይባቸው ከውጭ ገፅታቸው ሳይሆን ከውስጥ ክፍሎቻቸው ነው፡፡ ከውስጣቸው የሚታዩት አምዶች ፣ የመኝታ መደብና ጓዳን የመሳሰሉት የሚከፋሉባቸው መክፈያዎች ፣ እቃና ኩራዝን የመሳሰሉትን ለማስቀመጥ የሚያገለግሉት ድምድማቶች አሰራር ውብና አስገራሚ ነው፡፡ የዋግኽምራ ህድሞ ቤቶች ሳይታደሱም ብዙ ዓመታትን መቆየት ይችላሉ፡፡ የዚህ ምክንያቶች የህንፃ ጥበባቸው ድንቅነትና አፈሩ ማለትም ለጭቃ የሚሆነው የማይፈረፈርና እንደ ሙጫ አጣብቆ የመያዝ ተፈጥሮ ያለው በመሆኑ እንደሆነ አባቶች ይናገራሉ በማለት ገልፀዋል (አቶ አስራት ታደሰ*ቃመ*.12/10/2009 ዓ.ም )፡፡ አቶ አስራት አክለውም ዛሬም ድረስ ከመቶ ዓመት በላይ ዕድሜ ያስቆጠሩ ህድሞ ቤቶች ይገኛሉ፡፡ በአንድ ወቅት ዛሬ በሕይወት የሌሉት አቶ ብርሃኑ ፈለቀ "የአለቃ ማጥንቱ" እየተባለ የሚጠራ ጥንታዊ ህድሞ ቤትን በምሳሌነት ጠቅሰው ሲናገሩ፣ "ህድሞው ትልቅ ቢሆንም ፣ በትንንሽ ድንጋዮች የተሰራ ነው፡፡ በትናንሽ ድንጋይ የተሰራበት ምክንያት በጊዜው የድንጋይ መስበሪያ መዶሻ ስላልነበረና ድንጋይ በድንጋይ እየተሰበረ የተሰራ በመሆኑ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ሲታይ ደግሞ ምናልባት የመናድ አደጋ ቢያጋጥም በሰው ላይ የከፋ ጉዳት እንዳያደርስ ታስቦ ነው" ብለው ገልጸዋል፡፡ (*ቃመ*.12/10/2009 ዓ.ም)፡፡

ይህ አለቃ ማጥንቱ በተባሉ ሰው እንደተሰራ የሚነገርለት ጥንታዊ ክብና ውስጣዊ የአሰራር ጥበቡ አስገራሚ የሆነው ህድሞ ቤት ዛሬም ድረስ በሰቆጣ ከተማ ውስጥ ቆሞ እንደሚገኝ ገልፀውልኛል፡፡ ይህንን ህድሞ ቤት ቆሞ ለመገኘቱ እኔም ካለበት ድረስ በመሄድ አረጋግጫለሁ፡፡ መረጃ አቀባዬ የነገረኝን እውነታም ከሌሎች የብሔረሰቡ አባላት በመጠየቅም እውነት መሆኑን አረጋግጫለሁ፡፡

ከዚህ በላይ በተገለፀው የጥንታዊ የህድሞ ቤት አሰራር ለመረዳት የሚቻለው ብሔረሰቡ በአካባቢው ከሚገኙ ተፈጥሮኣዊ ነገሮች በመጠቀም ረጅም ዕድሜ ሊያስቆጥሩ የሚችሉ ውብና ድንቅ ቤቶችን ለመኖሪያነት ሊሠሩ መቻላቸውን ነው፡፡ በዚህም በተጠራቀመ የረጅም ዕድሜ እውቀት በመታገዝ የማንነታቸውን ማሳያ የሆነውን ባህላዊ ቤታቸውን በመገንባት ጥበባቸውን ለትውልድ ያስተላልፋሉ ፤ የአሰራር ብልሃታቸውንም ለተተኪው ትውልድ ያወርሳሉ፡፡ ይህን የህድሞ ቤት የብሔረሰቡ አባላት ለብዙ ዘመናት በመጠለያነት ሲጠቀሙነት የኖሩበትና ዛሬም ቢሆን ደረጃው ሳይወርድ በክብር በመኖሪያነት እየተገለገሉነት እንደሚገኝም ተገንዝቤያለሁ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ባህላዊ ቤቱ የብሔረሰቡን ባህላዊ ዕውቀት ደረጃው ምን ያህል ከፍ ያለ ጥበብ/ብልሃት/ የተመላበት እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይኸውም አካባቢውን በሚገባ ተገንዝቦ ፣ ተረድቶና አጥንቶ የብሔረሰቡን ባህልና የአኗኗር ዘይቤውን የሚያሳይ ቋሚ የታሪክ ምስክር ሊሆን የሚችል ማስረጃ ተክሎ ማስቀመጡን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ሀገረሰባዊ ዕውቀቶችን ለዘመናዊ ዕውቀት መሠረት ሊሆኑ እንደሚችሉ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ባህላዊ ዕውቀቶች ይህ ምርምር "ባህልና ልማት በዋግኽምራ ብሔረሰብ" በሚል ርዕስ ለሚሠራው ምርምራዊ ስራ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ አበርክቶ ይኖረዋል፡፡

### 4.5.2 የእርሻ ዕውቀት

በዋግኽምራ ብሔረሰብ ዘንድ እርሻ ለብዙ ዘመናት ሲከወን የቆየ ዋነኛው የኑሮ መሰረት ነው፡፡ ዋግኽምራ የተለያዩ የአየር ንብረቶች ባለቤት ናት፡፡ ይህ ጥናት በሚካሄድበት ጊዜ ቆላማ የአየር ንብረት ባለበት የዝቋላ ወረዳ አርሶ አደር የገለጹልኝን እንደሚከተለው እንመልከት፡-

እንደምታየው አካባቢው ቆላ ነው፡፡ አካባቢው ቆላ ቢሆንም በርካታ ሰብሎች የሚመረቱበት የእርሻ ቦታ አለ፡፡ የእርሻ ሥራው የሚጀምረው ለስራው አስፈላጊ የሆኑትን መሣሪያዎች ቁሳቁሶችን በማዘጋጀት ነው፡፡ እርሻው የሚታረሰው በሁለት በሬዎች ስለሆነ ለዚሁ የሚያገለግሉ የእርሻ መሣሪያዎች ሞፈር ፣ ቀንበር ፣ ማረሻ ፣ ምራን ፣ ማነቂያ ጠፍር ፣ አቤ/ሞፈሩንና ቀንበሩን የምታገናኝ እንጨት/ ፣ ቅቅርት /ሞፈሩንና ድግሩን የምታያይዝ ብረት/ ፣ መርገጫ ጠፍር እና ሌሎችም አስፈላጊ ቁሳቁሶች ይዘጋጃሉ፡፡ እነዚህ ቁሳቁሶች ዝም ብለው ማንኛውም እንጨት ወይም ብረት አይደሉም፡፡ ሞፈሩ የሚዘጋጀው ከካሙዛ ወይም ከወይራ ፣ ህክማ እንጨቶች ነው፡፡ ቀንበሩ ደግሞ ከሺሻ ወይም ከምለላ ምልጣ እንጨት ይዘጋጃል፡፡ እንጨቶቹ ከእርሻው የመሬት ርጥበት ይዞታ ፣ ድርቀት ፣ ለበሬዎቹ ደግሞ ክብደት ፣ ጉዳት የማያመጣ መሆናቸው በልምድ ካገኘነው ዕውቀት በመነሳት የምንመርጣቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ ለቀንበር የሚሆነው እንጨት የበሬዎቹን አንገት በመተሻሸት ቢላጥ ለበሽታ የማያጋልጥ ገር እንጨት ነው ፤ የማንመርጣቸው የሚያሳምሙና የሚያሳብጡ ክፉ እንጨቶች አሉ፡፡ የተጠቀሱት እንጨቶች በጣም የምናውቃቸው ችግር የማያመጡና ጠንካሮች ናቸው (አቶ ተፈሪ አስማረ ፣ ቃመ. 20/10/09 ዓ.ም)፡፡

ከላይ በመረጃ አቀባዬ እንደተገለፀው የማህበረሰቡ አባላት የእርሻ መሳሪያዎችን ከምን አይነት እንጨቶች መዘጋጀት እንዳለባቸው በዘመናት በተጠራቀመው ልምዱ ዕውቀት አግኝቶበታል፡፡ ለዚህም ነው ዝም ብለው እንጨት አይደሉም ያለው፡፡ በመሆኑም የእርሻ /ግብርና ዕውቀቱ ፣ ብልሃቱና ጥበቡ የተገኘው ከዚሁ ከባህሉ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ መሣሪያዎቹ ከተዘጋጁ በኋላ የሚቀጥለው መሬቱን በምን ወቅትና ጊዜ እንደሆነ ስለሚያውቅ ወቅቱን ጠብቆ የመሬት ዝግጅቱን ለመጀመር ዝግጁ ሆኖ ይጠባበቃል፡፡

የእርሻ ዝግጅቱ አጀማመር አስመልክተው አቶ ብርሃነ መስቀል ይርጋ እንዲህ ያብራራሉ፡-

የእርሻ ዝግጅቱ የሚጀምረው በአብዛኛው በመጋቢት ወር መጨረሻ ነው፡፡ ከዝናብ ቀድሞ ወይም ዘግይቶ መምጣት ጋር በተያያዘ የተወሰነ ለውጥ ይኖራል፡፡ መጀመሪያ የድበላ ስራ ይካሄዳል፡፡ ድበላ የእርሻ የመጀመሪያው ምዕራፍ ሲሆን

የመከስከስ ስራ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ እርከን ይሠራል፡፡ የእርከን አሠራሩ እንደ መደብ ያለ ሲሆን ውሃ ልኩን ጠብቆ መሠራቱን ለማረጋገጥ መደቡ ላይ ውሃ ደፍተው መንሳፈፉን ያስተውላሉ፡፡ መሬቱን እስከ አራት ጊዜ መላልሰው የሚያርሱ ሲሆን ድግግሞሹ እንደሚዘራው ሰብል ይለያያል፡፡ በኛ በዚህ አካባቢ የሚዘወተሩት የሰብል ዓይነቶች ጤፍ ፣ ማሽላ ፣ አደንጓሬ ፣ ሰሊጥ ፣ ገብስ ፣ አተር ፣ ሽንብራ ፣ ምስር ፣ ስንዴ ፣ ኑግ ፣ ሱፍ ፣ በቆሎ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ ከመዘራታቸው በፊት የየራሳቸው የሆነ የአስተራረስ ዙር አላቸው ፤ እኩል አይደለም፡፡ ለጤፍ ከሶስት እስከ አራት ዙር ፤ ለስንዴ ሶስት ዙር ፤ ለገብስ ፣ ማሽላና በቆሎ ሁለት ዙር ይታረሳል፡፡ ምስር ፣ አደንጓሬና የመሳሰሉት ደግሞ በመጀመሪያ ዙር እርሻ የሚዘሩ ሰብሎች ናቸው፡፡ መሬቱ ተዘጋጅቶ ሲያበቃ በመጋቢት ወር መጨረሻና በሚያዚያ ወር ዘር መዝራት ይከናወናል፡፡ ከሰኔ ወር መጨረሻ ጀምሮ ደግሞ የአረም ስራ ይከናወናል፡፡ በመስከረም የገብስ አጨዳ ይጀመራል፡፡ በጥቅምትና በህዳር ወራት ደግሞ የጤፍ ፣ የስንዴና የበቆሎ ሰብሎች አጨዳ ይካሄዳል ፡፡ በመቀጠልም የታጨደው ሰብል ይከመራል፡፡ መሬት ላይ ድንጋይ በመደርደር ትንሽ ከፍ ሲል እንጨት ይደረደርበትና በላዩ ላይ ይከመራል ፤ ይኼውም ከመሬት ያለው ከፍታ ሰብሉን ከምስጥና ከልዩ ልዩ ነፋሳት የሚከላከል ሲሆን ንፋስ እንዲያገኝም ይረዳል፡፡ ከዚህ በመቀጠል አውድማ ይዘጋጃል፡፡ አውድማ የሚዘጋጅበት ቦታ ድንጋዮች ተለቅመው በአካፋ ተሸርሽሮና ተስተካክሎ እበት ይለቀለቃል፡፡ በመቀጠልም እህሉ ወደ አውድማ ይጋዛል፡፡ በሬዎች አፋቸው ተለጉሞ አንድ ሰው በሰብሉ ላይ ያዞራቸዋል፡፡ ስንዴ ፣ ገብስና ጤፍ ከገለባው ፣ ማሽላና በቆሎ ደግሞ ከቆረቆንዳው እንዲላቀቅ ይደረጋል፡፡ ውቂያው ሲያበቃ በሬዎቹ ይወጡና በመንሽ እና በንፋስ በመታገዝ ምርቱ ከገለባው ይለያል፡፡ ምርቱና ግርዱም ይለያሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ ስራዎች ማረሱ ፣ ማረሙ ፣ አጨዳው ፣ ሰብሉን ወደ አውድማ ማጓጓዙና ውቂያው ሁሉም የሚከናወኑት በደቦ/በወበራ ነው፡፡ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ስራን በጋራ ለማከናወን የፈጠሩት ደንብና ስርዓት ያለው ሕብረት ነው (አቶ ብርሃነ መስቀል ይርጋ ፣ ቃመ. 23/08/2010 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ በላይ በስፋት ከተዘረዘሩት የእርሻ ስራ ዝግጅት ለመረዳት የሚቻለው ገበሬው ሀገረ ሰባዊ እውቀቱን ተጠቅሞ በምን ወቅት ምን ዓይነት ሰብል ፣ ለስንት ዙር ታርሶ መዘራት እንዳለበት ከባህሉ ሲወርድ ሲወራረድ ከመጣው ከተጠራቀመው ባህላዊ ዕውቀቱ መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ በላይ ሳልጠቅስ ለማለፍ የማፈልገው ትልቅ ጉዳይ አለ፡፡ ይኼውም በአውድማ ላይ ተመርቶ የተቆለለውን ምርቱን በስልቻ/በአቅማዳ ፣ በኬሻ ወዘተ እያስገባ ወደ ቤቱ ከማጓጓዙ በፊት የምርቃት ሥነ-ስርዓት የሚከናወን መሆኑን ነው፡፡ የምርቃት ሥነ-ሥርዓቱን ለማከናወን ካህን/ቄስ/ ካለ ካህኑ ካልሆነ በእድሜ አንጋፋ የሆኑ ሽማግሌ ያናውናሉ፡፡ በምርቃትም አንድ ሙሉ እንጀራና አንድ ሙሉ ሽክና ጠላ ይቀረባል፡፡ ሽማግሌው ሁሉንም ይመርቃሉ፡፡ ከዚያም እንጀራውና ሽክና ጠላውን በመያዝ ለምርቱ ሃምሳ እንጀራና አንድ ጋን ጠላ ሰጥተናል በማለት ምርት ማፈስ መጀመሩን ያበስራል ፣ የቀረበው አንድ እንጀራና ሽክና ጠላ ሆኖ ሳለ እንዲህ የሚባልበት ምክንያት አንድም ቀኑን በሙሉ ምንም ሳይራቡ ሲበሉና ሲጠጡ መዋላቸውና በማጣቀስ የመገቧቸውን ሴቶች ለማመስገን ሲሆን ሌላኛው መልዕክት ደግሞ ምርቱ እንደ ሃምሳ እንጀራና ጋን ጠላ በርክቶ ዓመቱን ይዝለቅ የሚል ምርቃት ያስተላልፉ እንደሆነ በምልከታዬ ወቅት ለመረዳት ችያለሁ፡፡

> የብሔረሰቡ አባላት አብዛኛውን ለኑሮው የሚያስፈልጉትን የማምረቻ መሣሪያዎች የሚያገኙት በአካባቢያቸው ከሚገኙ ተፈጥሮኣዊ የእፅዋት ተዋፅኦዎች ነው፡፡ እነዚህም የልዩ ልዩ ዛፎች እንጨት ለግብርና መሣሪያ እንዲሆኑ በተጠራቀመው ዕውቀታቸው ተጠቅመው ጠርበው ፣ ፍቀው ፣ አርቀውና ለክተው ከእርሻ መሬቱ ጋር ተስማሚ ከአየር ንብረቱም ጋር የሚስማማ አድርገው መርጠው ለስራ መሳሪያነት ያዘጋጃሉ፡፡ ይህም ሲሆን ማንኛውንም እንጨት ሳይሆን ምርጥ የሚሉትን በልምድ ካገኙት ዕውቀትና ብልሃት ተጠቅመው መርጠው እንደሚገለገሉባቸው ለመረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም የብሔረሰቡ አባላት ልማዳዊ ዕውቀት ቀጣይነት እንዲኖረውና እንዳይጠፋ ብርቱ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ይኼውም ትውልዱ የባህላዊ የእርሻ አስተራረስ ዕውቀትንና ክህሎትን እንዳይረሱት ወንድ ልጆቻቸውን ከጎናቸው በማሰለፍ በስራው እንዲሳተፉ ያደርጓቸዋል፡፡ ቀስ እያደረጉ በተግባር ያሰለጥኗቸዋል፡፡ ሲያርሱ ፣ ሲያጭዱ ፣ ሲያርሙ ፣ የእርሻ

መሣሪያዎችን መርጠው ድርግ ሲጠርቡ ፣ ሞፈር ሲያርቁ ፣ ምራን ሲያለሰልሱ ፣ ወዘተ ከጎናቸው አያርቋቸውም፡፡ በዚህም የባህላዊ ዕውቀቱን ቀጣይነት ለትውልዱ ያስተላልፋሉ፡፡ የትውልዱንም የስራ ፍቅር ፣ ታታሪነትና ትጋት በውስጣቸው እንዲፀነስ መሰረት ይጥላሉ (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቃመ. 08/10/2009 ዓ.ም)፡፡



ምስል 33፡- የግብርና መሳሪያዎች (ፎቶ ዋግኽምራ ዞን ባቱ)

### 4.5.3 የሙዚቃ መሳሪያዎች ስራ

ዋግኽምራዎች ጭፈራዎቻቸዉንና ዘፈኖቻቸዉን የሚያደምቀበትና ሕዝባዊ በዓሎቻቸዉን የሚያጅበበት የሙዚቃ መሳሪያዎች አሏቸዉ፡፡ እነዚህም መሳሪያዎች የሚዘጋጁት በአካባቢዉ ከሚገኙ ጥሬ እቃዎች ነዉ፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድ የተለመዱ አምስት የሙዚቃ መሳሪያዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም መሰንቆ ፤ የእጅ ከበሮ ፤ ዋሽንት ፤ ከራር እና ቱልቱላ ወይም ጡሩንባ ናቸዉ፡፡ የእነዚህን የሙዚቃ መሳሪያዎች አዘገጃጀት እና ከምን እንደሚዘጋጁ የሙዚቃ ባለሙያዉ አቶ ታፈረ ሰለፍ የሚከተለዉን ገልፀዋል፡፡

በአካባቢዉ የምንጠቀምባቸዉ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከእንጨት ፤ ከሸንበቆ ዛፍ ፤ ከፈረስ ጭራ ፤ ከቆዳ ፤ ከቆርቆሮ ፤ ከነሃስ ፤ ከከብት ቆዳ ፤ ከመሳሰሉት ሲሆን እነዚህን

መሳሪያዎች የሚሰሩ ባለሞያዎች አሉ፡፡ የዚሁ የብሔረሰቡ አባላት የሆኑ በተለያየ ሙያ ልምድ የሚታወቁ አሉ፡፡ የመሰንቆ መሳሪያ መስራት የሚችሉ ለብቻ አሉ፡፡ ጡሩንባ/ቱልቱላ የሚሰሩ ፤ ከበሮ መወጠር የሚችሉ ፤ ክራር የሚሰሩ አሉ፡፡ ሁሉም በየሙያዉ በዚሁ ስለሚገኙ ከነሱ እናሰራለን፡፡ ለእብነት ያህል እኔ የምጫወትበትን መሰንቆ የሚሰሩ ሰዎች የሚገለገሉበትን የመስሪያ ዕቃ ቁሳቁስ ራሳቸዉ አዘጋጅተዉ በምፈልገዉ ሁኔታ እነዲሰሩልኝ እናገራለሁ ይሰሩልኛል፡፡ዕቃዉ/የመስሪያ ቁሳቁስ ከሌለዉ እኔዉ ፈልጌ ላመጣ እችላለሁ ፤ ከዚያ መሰንቁዉን ይሰሩልኛል፡፡ የሚከፈለዉን የጠየቁኝን እከፍላለዉ፡፡ በጉርብትናና በወዳጅነት እንዲሁ በብላሽ ሊሽራልኝም ይችላል፡፡ የመስሪያ ቁሳቁሱን ግን የግድ እኔ ማቅረብ አለብኝ፡፡ መሰንቆ የሚዘጋጀዉ ከእንጨት እና ከፈረስ ጭራ ነዉ፡፡ እንጨቱም ማጣ ወይራ ወይም ሌላ ጠንከር ያለ ማንኛዉም እንጨት ሊሆን ይችላል፡፡ አዘገጃጀቱም እንጨቱ ተቆርጦ ፣ ተጠርቦ ፣ ተፈቅፍቆና ለስልሶ በሚፈለገዉ መጠን ይቆረጥና ከራሱ ላይ የመስቀል ቅርፅ እንዲይዝ ይደረጋል፡፡ ከታች ይበሳል፡፡ በመቀጠልም አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለዉ ትንሽ ሳጥን ይሰራና አንዱ ጎን በቆዳ ይሸፈናል፡፡ ከመሃሉ ትንሽ ቀዳዳም ይተዉለታል፡፡ ቋሚዉ እንጨት በቀዳዳዉ ዘልቆ እንዲገባ ይደረጋል፡፡ በቋሚዉ እንጨት የላይኛዉ ጫፍና በሳጥኑ ጫፍ ላይ ትንሽ እንጨት ተደርጋ ትታሰርና በመካከል ከፈረስ ጭራ የተዘጋጀ ገመድ ይወጠራል፡፡ ገመዱ እንዳይፈታ ከሁሉም ጫፎች ይጎነጎናል፡፡ የተወጠረዉን ገመድ/ጭራ በመገዝገዝ ድምጽ እንዲወጣ የሚያደርግ ቀልመም ያለ እንጨት ላይ የፈረስ ጭራ ተወጥሮ ይዘጋጃል (ቃመ. 07/10/2009 ዓ.ም)፡፡

የእጅ ከበሮ ለመስራት የሚያስፈልገዉ የእንጨት ዓይነት ከወይራ የተለየ ነዉ፡፡ እነዚህም እንደ ወይራ በጣም ጠንካራ የሆኑ መሆን የለባቸዉም ፤ ግንዳቸዉ ተቆርጦ በቀላሉ በመሮ የሚቦረቦሩ እንደ ዋንዛ ፣ ዋርካ እና ባምባ የመሳሰሉ ዛፎች ናቸዉ፡፡ ለዚህ የሙዚቃ መሳሪያ ጥሬ እቃ የሚሆኑት ከእነዚህ ዛፎች መካከል የተገኘዉን አንዱን ቆርጦ ዉስጣቸዉን በመሮ ቦርቡሮ ክፍት እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የግንዱን ሁለቱን ክፍተቶች በተዘጋጀ የከብት ቆዳ ዉጥር ተደርጎ ይሸፈናል፡፡ ከዚያም በተተለተሉ ቆዳ እርስ በረሱ በማጠላለፍ እንዳይፈታ ተደርጎ ይታሰራል፡፡ ከዚያም ለተወሰኑ ቀናት ፀሃይ ላይ ወይም ቤት ዉስጥ ተሰቅሎ እንዲደርቅ ይደረግና ለአገልግሎት ዝግጁ ይሆናል፡፡ የከበሮዉ ቁመት ከአንድ ክንድ/ግማሽ ሜትር/እስከ ሁለት ክንድ ሊደርስ

ይችላል፡፡ አሁን አሁን እንጨቱ እየጠፋ ስለመጣ የተለያዩ ፈሳሾች መያዣነት በፋብሪካ ከሚሰሩ ትላልቅ ጣሳ መሰል ቆርቆሮዎች ከበሮዉን ማዘጋጀት ተለምዷል (አቶ አበባዉ ያለዉ ፣ ቃመ.09/10/2009 ዓ.ም)፡፡

የትንፋሽ መሳሪያ በመባል የሚታወቀዉ ዋሽንት የሚዘጋጀዉ ከሸንበቆ ዛፍ ነዉ፡፡ ይህንን የሙዚቃ መሳሪያ አስመልክተዉ አቶ አስራት ታደሰ እንዲህ ይገልፁታል፡፡

ዋሽንት ባለሁለት ቅልጥም ፣ ባለሶስት ቅልጥም እና ባለ አራት ቅልጥም የሚባሉ የዋሽንት ዓይነቶችን ባለሙያዎቹ /ዋሽንት ተጫዋቾቹ /የዘጋጃሉ፡፡ የተዘጋጀዉን ሸንበቆ ምስማር ወይንም ሌላ መሰል ብረት እሳት ላይ በማጋል የዋሽንቱን ቀዳዳዎች ይበሳሉ፡፡ ሶስቱም የዋሽንት ዓይነቶች ባለ ኣራት ቀዳዳዎች ሲሆኑ የተለያዩ ቅላፄ ያላቸዉ ድምፆችን ለማዉጣት ያገለግላሉ (ቃመ. 11/10/2009 ዓ.ም)፡፡

አቶ አስራት በመቀጠልም ‹‹ዋሽንትን በተለያየ መጠን እና ዓይነት ማንኛዉንም ዋሽንት መጫዎት/መንፋት የሚችል ሁሉ በግል ሊሰራዉ የሚችል ቀላል የሙዚቃ መሳሪያ ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት ከእረኛ እስከ አዋቂ ድረስ በብሔረሰቡ አባላት የሚወደድና የሚጫወቱት መሳሪያ ነዉ፡፡ የመስሪያ ጥሬ እቃዉን ካገኙ ሁሉም ሰዉ ማለት ይቻላል ዋሽንት ማዘጋጀት ይችላሉ፡፡ አባቶች ለልጆቻቸዉ /ለወንዶች ብቻ ነዉ/ ሸንበቆ ፈልገዉ ወይም ሸንበቆ ካለበት ገዝተዉ እንኳ ቢሆን አዘጋጅተዉ እንዲለምዱ ይሰጧቸዋል፡፡ ፍየሎቻቸዉንና ከብቶቻቸዉን እየጠበቁ ቁጭ ብለዉ በራሳቸዉ ለመልመድ ይጣጣራሉ፡፡ ከዚያም ማታ ለቤተሰብ ያሰማሉ፡፡ አባት ወይም የሚችል ታላቅ ወንድም ዕድሜዉ ከፍ ያለ ሁሉ በማበረታታትና ጣት በሸንቁሮቹ ላይ በሚያርፈዉ በማይካዉ መካከል ያለዉን ክፍተት ጣቶቹን በየተራ አነሳስና አጣጣል ወዘተ ሁሉ አስተያየት እየሰጡ በተግባርም እያሳዩ የዋሽንት አነፋፍ ስልጠና ይሰጣሉ፡፡ በዚህም የባህላዊ መሣሪያ ዕዉቀት እንዳይጠፋ ፤ ቀጣይነትም እንዲኖረዉ ዕዉቀታቸዉን ያስተላልፋሉ (ቃመ.11/10/2009 ዓ.ም)፡፡





ምስል 34፡- ዋሽንቶች እና ማሲንቆ

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የሙዚቃ መሳሪያዎች በተጨማሪ ቱልቱላ/ጡሩንባና ክራርም የሚዘጋጁት በአካባቢዉ በሚገኙ ከተፈጥሮ እፅዋት እና ከወዳደቁ ብረቶችና ቆርቆሮዎች ወዘተ ነዉ፡፡ በመሆኑም እነዚህን መሳሪያዎች በማህበረሰቡ ልማዳዊ ዕዉቀት ተሰርተዉ መልሰዉ ማህበረሰቡን ከነሱ በሚወጣዉ ድምፅ /ቃና/ መንፈሳቸዉን ያድሱላቸዋል ፤ ሥነ ልቦናዊ እርካታም ይሰጧቸል፡፡ ስለሆነም የሙዚቃ መሳሪያዎች የብሔረሰቡ ስሪት ብቻ ሳይሆኑ የማንነታቸዉ ማሳያም ጭምር ናቸዉ ለማለት ይቻላል፡፡ ይህን ለማለት ያስቻለዉ መረጃ ለመሰብሰብ በምዘዋወርበት ወቅት በየቤታቸዉ ከተጠቀሱት ቢያንስ ሁለቱ ዋሽንትና መሰንቆ አልፎ አልፎም ክራር መገኘታቸዉ ነዉ፡፡

## 4.5.4 የብረታብረት ስራ

በዋግኽምራዎች ዘንድ የብረታብረት ስራ ሰፊ አገልግሎት የሚሰጥ የእጅ ጥበብ እዉቀት ነዉ፡፡ ለእርሻ ስራ ግልጋሎት የሚዉሉ ዋና ዋና የተባሉ ማረሻ ፣ ወገል ፣ ዶማ ፣ መጥረቢያ ፣ ማጭድ ፣ መጎልጎያ ፣ ወዘተ በአብዛኛዉ ከብረት የሚሠሩ ሲሆኑ ባለሞያዎቹም የብሔረሰቡ አባላት ናቸዉ፡፡ እነዚህም የብረታብረት የተጠቀሱትንና ሌሎችንም እንደ ቢላዋ ፣ መሮ ፣ ወስፌ ፣ ወዘተ ዓይነቶችን ራሳቸዉ በባህለዊ መንገድ ከሚገኝ አጭነ ከሚባል ድንጋይ አቅልጠዉ ወደ ብረትነት ቀይረው የሚሰሯቸዉ ናቸዉ፡፡ ይህንን ባህላዊ የብረት ማቅለጥ ተግባር አስመልክተዉ ሂደቱን አቶ አበበ ያለዉ

የተባሉ የሙያዉ ባለቤት እዲህ ይገልፃሉ፡፡ይህንን እዉቀት የወረስኩት ከአባቴ ነዉ፡፡ አባቴ ጎበዝ የብረት ሠራተኛ ነበር፡፡ ሁሉም የአካባቢዉ ሰዉ ስራዉን ይወዱለት ነበር፡፡ እሱም እዉቀቱን ያገኘዉ ከአባቱ እንደሆና ሌላ ስራ/እርሻ ፤ ንግድ ፤ ወዘተ እኛ መስራት ስለማይፈቀድልን ይህንን እየተቀባበልን እንሰራዋለን ፤ ሙያችን ይኸዉ ነዉ ፤ መኖሪያ ቤታችንም ይችዉ የምታያት ጫወ[41] ናት፡፡ በዝችዉ መንደር ድንጋይ አቅልጠን ፤ ወደ ብርትነት ቀይረን የእርሻ መሳሪያዎችንና የቤት ዉስጥ አገልግሎት የሚዉሉ ካራ/ቢላዋ ፣ መርፌቁልፍ ፣ ወረንጦ ሌላም እየሰራን ኑሮኣችንን እንገፋለን፡፡ ድንጋዩን አቅልጦ ወደ ብረትነት መቀየር አድካሚ ስራ ነው፡፡ ብዙ ድካም ልፋት አለዉ፡፡ አሁን አሁን ግን ብረትን ከድንጋይ አቅልጦ መስራት ቀርቷል፡፡ ያለብዙ ድካምና ልፋት ካረጁ መኪናዎችና ከወዳደቁ ቁርጥራጭ ብረቶች መገኘት ተችሏል፡፡ ከገበያም መግዛት ተችሏል፡፡ ገዝተን በአካባዉ የሚፈለጉ የብረታብረት ቁሶችን ማረሻ ፣ ገጀራ ፣ ዶማ ፣ ማጭድ ፣ ወገል ፣ ወስፌ ፣ ካራ ፣ ወረንጦ ፣ ብረት ምጣድ ፣ የቡና መዉቀጫ ዘነዘና ፣ ፋስ በአንድ በኩል ለእንጨት መቁረጫነት በሌላ በኩል ለመቆፈሪያነት የሚያገለግል መጥረቢያ ፣ የቀበቶ ቀዳዳ መብሻ ፣ የመሳሰሉትን እነሰራለን፡፡ እነዚህን በመሸጥ ገንዘብ እናገኛለን፡፡ ኑሮዓችንን እንደጉማለን፡፡ ገዢዉም የአካባቢዉ ነዋሪ ፤ ዕቃዎቹን በቀላል ዋጋ ገዝተዉ ይጠቀማሉ፡፡ ግልጋሎታቸዉም ጠንካራ ነዉ፡፡ አይሰበሩም ፤ ከዘመን አመጣሽ ሰራ ይበልጣሉ፡፡ ስለታቸዉ ቢበርድ /ቢዶልሙ/እንደገና ቀልጠዉ ይሠራሉ፡፡ካልፈለጓቸዉ ማረሻን ቢለዋ/ካራ ፣ ማጭድ ፣ ሌላም አስደርገዉ እንሰራላቸዋለን፡፡ ወይም ለኛ ይሰጡንና በምላሹ የፈለጉትን ወስደዉ ይጠቀማሉ፡፡ እኛም በሌላ መልክ ሰርተን ድጋሚ እንሸጣቸዋለን (ቃመ.14/10/2009 ዓ.ም)፡፡

[41] ጫወ ሰቆጣ ከተማ ውስጥ የምትገኝ ትንሽ መንደር ናት፡፡ በዚች መንደር በብዛት የሚኖሩት የብረታብረትና ጌጣጌጥ ባለሙያዎች ናቸው፡፡





ምስል 35፡- ቀልጦ ብረት የሚሆነው አጭነ ድንጋይ የብረታብረት ባለሙያዎች በስራ ላይ

ከዚህ በላይ ከተገለፀዉ ሀሳብ ዉስጥ የምንረዳዉ ቁም ነገር አለ፡፡ ይህም የባህላዊ እጅ ጥበብ ባለሞያዎች ምን ያህል ሁገብ የሆነ ሞያ ያላቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ይኸዉም ተፈጥሮን ዓይተዉና ተገንዝበዉ ፤ በዉስጡ የሚገኙትን ማዕድናት ለይተዉ ለብረት መሳሪያዎች መስሪያ ሊሆን የሚችለዉን መርምረዉ አዉቀዉ መጠቀማቸዉ ፤ እንዲሁም ማዕድኑን ወደተፈለገዉ ጥሬ ሃብትነት ለመለወጥ የሚያስችሉ መሳሪያዎችን እራሳቸዉ መፍጠራቸዉን ልብ ልንል እንችላለን፡፡ ጫወ ሰቆጣ ዉስጥ የምትገኝ ትንሽ መንደር ናት፡፡ በብዛት በዚች መንደር የሚኖሩት የብረታብረትና ጌጣጌጥ ባለሞያዎች ናቸዉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በልምድ ያገኙትን ሙያ ተጠቅመዉ ማህበረሰቡ እንዳይጎዳ ራሳቸዉ ሰርተዉ የሸጡላቸዉን እንደገና መልሰዉ እንዲጠቀሙባቸዉ መስራታቸዉ እና ከፈለጓቸወ ደግሞ ሌላ መዉሰድ እንደሚችሉና የማይፈልጉትን እነሱ ወስደዉ ቅርፃቸዉን ለዉጠዉ እንደሚሰሯቸዉ ነዉ ፤ ይህም አንድን ያገለገለ የብረት ዕቃ ከመጣል ይልቅ ለመልስ ጥቅም ላይ ማዋል የባለሞያዎቹን ብልሃት ያሳያል፡፡ አንድም ያገለገለ እቃ ከመጣል ይልቅ መልሶ መጠቀም አካባቢን ከብክለት መታደግ ብቻ ሳይሆን ቁጠባን ያስተምራል፡፡ ይህም አንድን የተፈጥሮ ሀብት በከንቱ ከማባክን ብልሃትን እስከ መጨረሻዉ አቅም ድረስ አሟጦ መጠቀምን ያሳያል፡፡ የጥሬ ዕቃ ችግርን/መጥፋት በዚህ መንገድ ማቃለል እንደሚቻልም ያመለክታል፡፡

የባህላዊ የብረታብረት ስራ በአሁኑ ወቅት ቀስ በቀስ የመጥፋት አደጋ እያጋጠመዉ እንደሆነ የዞኑ የባህልና ቱሪዝም ባለሞያ የሆኑት አቶ ባዬ አስምሮም ይገልፃሉ፡፡ የብረታብረት ስራ በመጥፋት ላይ ነዉ፡፡ ለመጥፋት ምክንያት ናቸዉ የሚባሉት ዋና

ዋናዎቹ አብዛኞቹ የብረታብረት ዉጤቶች/ቁሳቁሶች በፋብሪካ ተዘጋጅተዉ በሚመጡ ቁሳቁሶች እየተተኩ በመምጣት ፤ በጥሬ ዕቃነት የሚያገለግለዉ ብረት በቀላሉ መገኘት አለመቻሉ የሚጠቀሱ ናቸዉ (ቃመ. 07/10/2009 ዓ.ም)፡፡ አቶ ባዬ የብረታብረት ስራዉ ለመጥፋት ምክንያት ናቸዉ ያሏቸዉ የብረታብረት ቁሶች በፋብሪካ ተመርተዉ መምጣታቸዉ እና ጥሬ ዕቃነት የሚያገለግለዉ ብረት በቀላሉ አለመገኘት ሳይሆን ባለሞያዎቹ ለመጥፋቱ/በመጥፋት ላይ ያለ መሆኑ ዋናዉ ምክንያት ማህበረሰቡ ለሙያተኛዉ ያላቸዉ በጎ ያልሆነ ግንዛቤ ትልቁን ድርሻ እንሚዲይዝ በአፅንኦት እንደሚከተለዉ ይገልፃሉ፡፡

የአካባቢዉ ሰዉ እኛን በዚህ ሙያ የተሰማራነዉን ሰዎች እንደሌላዉ ከዚህ ስራ ዉጪ በሌላ ሙያ/እርሻ/ ከተሰማሩት ጋር እኩል አያዩንም፡፡ ሙያዉንም ሆነ እኛን አሳንሰዉ ነዉ የሚያዩን ፤ በብዙ ማህበራዊ ጉዳዮች ያገሉናል፡፡ እንደእነሱ የእነሱ ዘር መሆናችንን አይቀበሉንም፡፡ ይሰድቡናል ፤ ልጆቻችንን ልጆቻቸዉ ይሰድቧቸዋል፡፡ የቆዳ ሠራተኛ የሆነዉን አራቢ/ፋቂ ፤ ፊቅፋቂ እያሉ ይሳደባሉ፡፡ እኛንም ብረት ሠራተኞችን ባለጅ ፣ ቡዳ ፣ ሰዉ ይበላሉ ፣ ወደ ሌላ ነገር ይለወጣሉ/ይሰወራሉ ፣ ከነሱ እራቁ! ተጠንቀቁ! ፣ ኸረ! የማይሉን የለም! በአምልኮ ቦታና በትምህርት ቤት ሳይቀር ከነሱ ጋር አይቀላቅሉንም ፤ ያገሉናል፡፡ በዚህ በኛ ቀበሌ ጫወ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለሌለ ወደ ሰቆጣ ልጆቻችን ሲሄዱ ከፍተኛ መገለልና ስድብ ይደርስባቸዋል፡፡ በዚህ የተነሳም ልጆቻችን ትምህርታቸዉን ለማቋረጥ ይገደዳሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ማንነታቸዉን ደብቀዉ ይማራሉ (አቶ ምስጋና ገ/ኪዳን ፣ ቃመ. 08/10/2009 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ በላይ ከተገለፀዉ ሃሳብ በመነሳት የብረታብረት ዕዉቀት በመጥፋት ላይ እንደሚገኝና ዕዉቀቱ ቀጣይነት እነዳይኖረዉ ምክንያት የሆኑት ቀደም ብለዉ የተጠቀሱት ብቻ ሳይሆኑ ዋናዎቹ የብሔረሰቡ አባላት የሙያዉ ባለቤቶችንና ቤተሰቦቻቸዉን ማግለላቸዉ እና ተተኪ ወራሽ እንኳ እንዳይኖር የባለሞያዎችን ልጆች ሳይቀር የሚሰድቧቸዉ መሆኑና ከሌሎች የብሔረሰቡ ልጆች ጋር ሳይቀር አብረዉ እንዳይማሩ ጭምር ማግለላቸዉ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም የሙያዉ ባለቤቶች እና ልጆቻቸዉ ሙያዉን መጥለታቸዉ ለቅርሱ እየጠፋ መሄድ ዋና ምክንያቶች እንደሆኑ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ ሌላ በዋግኽምራ የእጅ ጥበብ ባለሞያዎች ሲኖሩ ልዩ ልዩ የእደ ጥበብ መሣሪያዎችን ፤ ቁሳቁሶችንና እና ጌጣጌጦችን በባህላዊ

እዉቀታቸዉና ጥበባቸዉ በመስራትና በማዘጋጀት የገቢ ምንጫቸዉ በማድረግ ነዉ፡፡ በዚህ ጥናት የሸክላ ስራ ባለሙያ ፤ የቆዳ ስራ ባለሞያ ፤ ብረት ስራ ባለሞያዎች በተለየ መልኩ የተገለሉና የሚሰደቡ መሆኑ ፤ የስራ ዉጤታቸዉን ግን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚፈልጉትና እንደሚገለገሉበት በመረጃ ተረጋግጧል፡፡ ይህም ሆኖ ግን አሁንም ባለሞያዎቹ ሥራዉን ከነ አካቴዉ እርግፍ አድርገዉ መተዉ አለመቻላቸዉን ራሳቸዉ ባለሞያዎቹ ገልፀዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# 5. የብሔረሰቡን ልማት ለማፋጠን ያለው አዎንታዊ ባህላዊ/ፎክሎራዊ ገፅታዎች

ቀደም ባሉት ምዕራፎች የዋግኽምራን ብሔረሰብ ማንነት የሚገልፁ ዋና ዋና ባህላዊ ገፅታዎች በስፋት ቀርበዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ባህሉ በአካባቢው ልማት አኳያ ያለውን አዎንታዊ ሚና የሚገልፁ ጉዳዮች ይቀርባሉ፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡት ጥሬ መረጃዎች በየመልካቸው ተደራጅተው ሲታዩ በእያንዳንዱ ዘውግ ውስጥ በዋነኛ ጉዳይነት የሚነሱ ቁም ነገሮች በሌሎችም ዘውጎች በሌላ መልክ ተደጋግመው በመምጣት እርስ በእርስ እየተደጋገሙ ሲገለጡ ይታያሉ፡፡ ይህ የጭብጥ መተሳሰር ደግሞ የማህበረሰቡን ማንነት ፣ ዕምነት ፣ ልማድ ፣ እና ስለ ዓለም ያለውን አተያይ ግልጽ አድርጎ ያመለክታል፡፡ በዚህ መልኩ የተጋመደው ባህላዊ ጭብጥ በክዋኔ አውድ ላይ በተደጋጋሚ በተግባር ሲከወን ደግሞ እራሱን እያፀና/እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ በዚህ ሁኔታ የደረጀው የዋግኽምራ ባህል ለልማት የሚኖረው አወንታዊ አበርክቶ ቀጥሎ ይተነተናል፡፡

## 5.1. የዋግኽምራ ብሔረሰብ ሁለንተናዊ የጋራ ሕይወትና አኗኗር

የዋግኽምራ ብሔረሰብ አባላት የአኗኗር ባህል የተመሰረተው በጋራ በመተባበር አብሮ በመኖር ላይ ነው፡፡ ይኼውም ደስታንና ችግርን በጋራ መወጣት ፣ እርሻንና ቤት መስራትን በደቦ/በወበራ መስራትን ፣ ጋብቻንና ግጭት አፈታትን ፣ የሰርግና የማህበር ድግስን ፣ በመሳሰሉ የማህበረሰቡ ዋነኛ ጉዳዮች ላይ በጋራ መስራትና መወሰን የብሔረሰቡ ዋነኛ መለያ ነው፡፡

ከላይ በቀረቡት ምዕራፎች በስፋት እንደተዘረዘረው እነዚህ ባህላዊ እሴቶች እርስ በእርስ የተጋመዱ የማህበረሰብን ወግና ልማድ ሳያዛቡ በመቀጠል ዘወትር የሚከወኑ ናቸው፡፡ በሠርግ ፣ በሞት ፣ በወሊድ ፣ ወዘተ ጊዜ ሲያከናውኗቸው የኖሩ ስርዓቶች ፣ ወጎችና ልማዶች ዘመናዊነትና ሌሎች ሁኔታዎች ሳያግዱት እስከዛሬ ጠብቋቸው ይኖራል፡፡

የብሔረሰቡ አባላት አኗኗር በጋራ ትብብር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ዋጎች በመንደር ሰብሰብ ብለው የመኖሪያ ቤታቸውን በእድሞና በደርብ ከሰንበሌጥ ፣ ከሳርና ከእንጨት

ሰርተው ይኖራሉ፡፡ የየግል ቤታቸውን ዙሪያም አጥር ያጥራሉ፡፡ ለቀንድና ለጋማ ከብቶቻቸው ማደሪያም ከቤታቸው ጋር አያይዘው ጉሮኖ እና ግርግም ተብሎ የሚጠራ ስርጥ ቤት ይሰራሉ፡፡

በአንድ መንደር የሚኖሩ የማህበረሰቡ አባላት የስጋ ዝምድና ያላቸው የቅርብ ሰዎች ሊሆኑም ላይሆኑም ይችላሉ፡፡ ዝምድና ባይኖራቸውም የብሔረሰቡ አባል የሆኑ ወይም ያልሆኑ በጋራ በአንድ መንደር ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የመንደሩ ጥንቅር ዝምድናን መሰረት ያደረገ ሳይሆን መግባባትን ፣ ጓደኝነትንና ትውውቅን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህንን የአኗኗር እሴታቸውን በምሳሌያዊ ንግግራቸውም እንዲህ ያጠናክሩታል፡፡

"የሰው ሀገሩ ምግባሩ፡፡"

"አብሮ መብላትን ቅዱስ ዩሐንስ አይሽረውም፡፡"

"ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት፡፡"

(አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቃመ. 10/09/2009 ዓ.ም)

ከላይ የቀረቡትን የዋጎች ምሳሌያዊ አነጋገሮች ስንመረምራቸው አብሮ መብላትና አብሮ መኖር የብሔረሰቡ እሴት እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አብሮነት ነጠላነትን ይጠየፋል፡፡ አብሮ መብላት መተማመንን ፣ መተጋገዝን ፣ ቃል መገባባትን እና ቃል መጠበቅን የሚያሳይ ነው፡፡ ለክፉም ሆነ ለበጎው ምግባር የሚያስተሳስር መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም በአንድ መንደር የሚኖሩ ማህበረሰቦች ስብስባቸው ዝምድናን ያማከለ ሳይሆን ትብብርንና መረዳዳትን የሚያስቀድም ነው፡፡ ለዚህም ነው የመንደራቸው አባላት ስብስብ የስጋ ዝምድናን መሰረት ያላደረገው ፤ መርሃቸው አብሮ ለመኖር "የሰው ሀረሩ ምግባሩ" መባሉ ነው፡፡ ዋጎች አብረው ከሚኖሩት ጋር ተባብረውና ተረዳድተው ፣ ያለው ከሌለው በማካፈል ተስማምተውና ተዋደው ይኖራሉ፡፡ ስስታምንና ተካፍሎ አብሮ የማይበላውን ሰው "ዘግቶ በላ ፣ እንጀራ ፍሪዳው!" ይሉታል፡፡ "ዘግቶ በላ" መባል በብሔረሰቡ ዘንድ በጣም የሚጠላ ፣ የተገለለና የሚያሳፍር ነውር ምግባር ነው፡፡ "እንዴት የዚህን ያህል ስስታም ይሆናል!" በማለት ሰው ሁሉ በመልካም ዐይን አያየውም፡፡ አብሮ መብላት ፣ ያለውን ተካፍሎ መብላት እና መረዳዳት የብሔረሰቡ የቆየ ልማድ በመሆኑ ማህበረሰቡ ይህንን ዓይነት ስግብብነት/ስስታምነት የሚተገብር ሰውን ፍጹም ይጠላል፡፡ አብሮ

ተካፍሎ መብላት ፣ መረዳዳት እና መተጋገዝ እርካታ የሚሰጥ ፣ ነፍስን የሚያስደስት እንደሆነ ሲገልፁም "ከመብላት ማብላት" ይላሉ በምሳሌያዊ አነጋገራቸው። በመሆኑም አብሮ መብላት ወይም ቸር ለጋስ መሆን እርካታን ያስገኛል ማለት ነው።

ይኼን ስስትን መጠየፍ እና ተካፍሎ መብላትና መረዳዳትን በተረቶቻቸውም ሆነ በምሳሌያዊ አነጋገሮቻቸው እንደዚህ ይገልጹታል።

"ይዝን ጭቃ ይጮ ባግራ ኹርስጉዝ መች ዘው"

"አሬራ ጠጥቶ የሰከረና ብቻውን በልቶ የበለፀገ የለም።"

(አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቃመ.10/09/2009 ዓ.ም)

ከላይ የቀረበውን የዋጎች ምሳሌያዊ አነጋገር ስንመረምረው አብሮ መብላትና አብሮ መኖር የብሔረሰቡ እሴት እንደሆነ እንገነዘባለን። አብሮነት ነጠላነትን ይጠየፋል ፤ ነጠላነት ራስ ወዳድነት ፣ ስግብግብነትና ግለኝነት ነው። በዋግኽምራ ይህ የዘመናዊነት /modernization/ መለያ የሆነው ግለኝነት ፈጽሞ አይደገፍም።ኽምራዎች ሁልጊዜም "ብቻውን በልቶ የበለጸገ የለም" የሚለውን ምሳሌያዊ አነጋገራቸው አብረን እንብላ ፣ አብረን እንኑር ያለንን ተካፍለን እንደር ባይ ናቸው። እንደውም ስስታምን ፣ የማያበላንና የማያካፍልን ሰው ‹‹ኼይረኼትግር አጉሽኩ›› "ሆዳም ከበላ በኃላ ይፀፀታል" ይሉታል። እንኳንስ ለሌላው ሲያበላ ራሱም በመብላቱ ምነው ባልበላሁት ብሎ እንደሚቆጨው ለራሱም በራሱ ሆድ የሚጸጸት መሆኑን ያሳያል። ባልበላ ኖሮ አያልቅም ነበር እያለ የሚሰስት ሰቀቀናም ነው። ሌላውን ሊያበላ ቀርቶ ለራሱም በመብላቱ ይቆጨዋል ይሉታል። በዚህም ሆዳም በልቶ የማይጠረቃ ሆደ ጠባቃ ከመባሉም በላይ ብቻውን በልቶም የማያረካውና የማያስደስተው ነው። ብሔረሰቡ አብሮ መብላት የሚያረካ የሚያስደስት መሆኑን የሚቀበል ነው። በዚህም የተነሳ ለስስታም ሰው ያላቸው አስተሳሰብ ከፍተኛ ጥላቻ ነው። በዚህም ምክንያት እንደዚህ ያለ ሰው ምንም ክፉ ሆነ ጥሩ ነገር ቢያጋጥመው የመከራውም ሆነ የደስታው ተሳታፊ አይሆኑም ። በክፉም ሆነ በበጎ መልኩ ለሚከሰትበት ማህበራዊ ተግዳሮቶች አብረውት አይቆሙም። ለዚህም "ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል" በማለት እንዳላዩ እንዳልሰሙ ሆነው ያገሉታል። ከዚህ ልንረዳው የሚገባው ቁም ነገር አብሮ መብላትና ያለውን ማካፈል እርካታ የሚያስገኝ ብቻ ሳይሆን ይህንን አብሮነት የማይጋራ የማህበረሰቡ አባል በቡድኑ

አባላት ዘንድ መገለልን ሊያስከትልበት እንደሚችል ነው። ከዚህ የመገለል ሁኔታ ለማምለጥ ግለሰቡ የቡድኑን የጋራ እሴት የሆነውን አብሮነት ወደደም ጠላም መጋራቱ አይቀሬ ግዴታው ይሆናል። በዚህም የተጠናወተውን ስስታምነት በመተው የብሔረሰቡን እሴት ይተገብራል። ይህንን ስስትን መጠየፍ በተረቶቻቸውም እንዲህ ይገልፁታል።

> በድሮ ጊዜ ሁለት ወንድማማቾች ይኖሩ ነበር። አንደኛው ሃብታም ሌላኛው ደሀ ነበሩ። ሃብታሙ ሲበዛ ስስታም ሲሆን ደሀው ደግሞ ያለውን የሚያካፍል ነበር። ከእለታት አንድ ቀን ሶስት ሰዎች ደሀው ቤት መጥተው "እባካችሁ የመሸብን እንግዶች ነን አሳድሩን" ብለው ይጠይቁታል። በጣም ይደነግጥና "እንደምታዩት ቤቴ ጠባብ ነው ለናንተ አይበቃችሁም ፤ ይልቅ የወንድሜ ቤት ሰፊ ስለሆነ እሱ ጋ ሄዳችሁ ብትጠይቁት ይሻላላ" ብሎ ቤቱን ያሳያቸዋል። እንግዶቹም ወደዚያው አምርተው "አሳድረን" ይሉታል። ወንድሙ ግን "ማሳደሪያ የለኝም" ብሎ ያባርራቸዋል። እንግዶቹም ወደ ደሃው ቤት ይመለሱና "ግድ የለም ከውጭ በርህ ላይም ቢሆን እናድራለንና አንተ ብቻ ፍቀድልን" ሲሉት ወደ ሚስቱ ይገባና ጉዳዩን ያዋያታል። እሷም "አትጨነቅ እኛ መኝታ ላይ ያድራሉ ለሚበሉትም አትሳቀቅ የኛን እራት ይበላሉ ፤ ለነገ ፈጣሪ ያውቅልናል" ብላ ታፅናናውና ለሰዎቹ ያላቸውን አስተናግደው ምኝታቸውን በመልቀቅ ያስተኟቸውና እነሱ ወጥተው ከውጪ ያድራሉ። ባልና ሚስቱ በጧት ተነስተው እንግዶቹን ለመሸኘት በሩን ሲከፍቱ እንግዶቹ ሄደው ቤታቸው ግን በወርቅ ተሞልቶ አገኙት ይባላል (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቂ.መ.አ 10/09/2009 ዓ.ም)።

ኽምራዎች የስስትን ነውርነት በተረቶቻቸውና በምሳሌያዊ አነጋገሮቻቸው በተደጋጋሚ የሚያነሱት ስለሆነ ኑሮዋቸው በመረዳዳትና ተካፍሎ በመብላት ላይ ያላቸው ፅኑ እምነት እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል። ከላይ በቀረበው ተረት እንደሚታየው ስስታሙ ለሶስቱ እንግዶች ማደሪያ የነፈጋቸው ለራታቸውም የሚሆን ምግብ ላለመስጠት እና ለምኝታቸውም የሚያገለግል ቁሶች ላለመስጠት ነው። ይህንን ማድረግ ፍጹም የማይወድ ስስታም በመሆኑ ነው። ያለውን ለሌለው አካፍሎ ምኝታውን ለቆ በማስተናገዱ በበጎነት ቤቱ በወርቅ ተሞልቶ መገኘቱ "ስጥ ይሰጥሃል" የሚለውን አባባላቸውንም ያሳያል። ስትሰጥ ይሰጥሃል። ስታካፍል አብረህ ስትበላ ዋጋህ

ይከፈልሃል የሚለውን እሴት የበለጠ የሚያጠነክር ነው፡፡ መተጋጋዝንና መረዳዳትን ያዳብራል፡፡

ኽምራዎች ስስታምነት ራሱን ባለቤቱን የሚጎዳውን ያህል ለጋስነትና ቸርነት ለሰው በጎ ማድረግና ያለውን ተካፍሎ መብላት ጥሩ ማድረግ የሚያስገኘውም ጥቅም በተረቶቻቸው ያሳያሉ፡፡

## 5.2 ግጭቶችን በጋራ መፍታት

ይህ የጋራ አስተሳሰብና አኗኗር ባህላዊ እሴት በብሔረሰቡ በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ ውስጥ እየተደጋገመ በመምጣት እየሰረፀ የኖረ በመሆኑ ግጭቶችን ለመፍታትና የአካባቢውን ሰላም ለማስከበር እንዴት ያለ ምቹ አስተዋፅኦ እንዳለው በተለያዩ መገለጫዎች ማሳየት ይቻላል፡፡

ኽምራዎች በተለያዩ መንስኤዎች የሚከሰቱ ከቀላል እስከ ከባድ ግጭቶች የሚፈቱበት የራሳቸው የሆነ የሽምግልና ስርዓት/መርከባ/አላቸው፡፡ ከነዚህ መካከል የባልና ሚስት ግጭቶች ፣ የቤተሰብ /የአባትና ልጅ/ ግጭቶች ፣ የጎረቤት ግጭቶች የሚባሉት ከቀላል ግጭቶች የሚፈርጇቸው ሲሆኑ መንስኤዎቻቸውም ቂም በቀል ፣ የዕለት ግጭትና ሞቅታ እንደሆነ መረጃ አቀባዮች ገልፀውልኛል (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቂ.መ.አ 10/10/2009 ዓ.ም)፡፡ እርስ በእርስ በተፈጠረ አለመግባባት እንደ አጋጣሚ የሰው ሕይወት ቢያልፍ ግድያውን የፈፀመው ይደበቃል፡፡ አካባቢውን ለቆ ይሄዳል፡፡ የሞተው ከተቀበረ በኋላና የሟች ቤተሰብ ሰከን ሲሉ ምስጢረኛ ለሆነው ለቅርብ ጓደኛው መልዕክት ልኮ ገዳዩ እሱ መሆኑን ይናገራል፡፡ በሽምግልና ጉዳዩ እንዲያዝለት ፤ መፀፀቱንና በዕለት ግጭት ቀን ጥሎት የተፈጠረ መሆኑን በመንገር እርቅ እንዲፈፀምለት መልዕክት ያስተላልፋል፡፡ ሽማግሌዎቹም የሟቹ ቤተሰቦች በቀል እንዳያስቡ "አንዱን አጥተናል ፤ ሁለተኛውን ደግሞ እንዳናጣ ገዳዩን ስላወቅነው የፀቡን መነሻ ምን እንደሆነ እስከምናጣራ የሞተውን ልጃችንን ሀዘን እንወጣ"[42] ብለው ሁኔታውን በማረጋጋት የሀዘን ስርዓቱን በባህሉ መሰረት ያካሂዳሉ፡፡

---

[42] አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቃመ. 07/10/09 ዓ.ም ፤ አቶ ባየ አስምሮም ፣ ቃመ. 07/10/2009 ዓ.ም ፤ አቶ አስራት ታደሰ ፣ 05/10/2009 ዓ.ም

ሟችም ገዳዩም የጋራ ልጃቸው/ወገናቸው ስለሆኑ ከሀዘኑ በኋላ በጋራ ሁነው ጉዳዩን ያጣራሉ፡፡ በምን ምክንያት ሊገድለው እንደቻለ ገዳዩን እንዲያስረዳ ከተደበቀበት ድረስ በመሄድ ይጠይቁታል፡፡ በባህሉ መሰረት ለሽማግሌ መዋሸት መቅጠፍና መደበቅ በእርቅ ወቅት ስለማይፈጠር ነውር ስለሆነ ገዳዩ እውነቱን ያስረዳል፡፡ ሽማግሌዎቹም ለመግደል ያነሳሳውን ጉዳይ ያጣሩና ጥፋቱ የሟቹ ከሆነ የሞተው በራሱ ጥፋት መሆኑን ገዳዩን መክረውና ገስፀው መታገስ እንደነበረበት አስጠንቅቀው ጉዳዩን በእርቅ/በሽምግልና ይፈቱታል ከትንሽ ማንገራገር በኋላ ሽማግሌዎቹን አክብረው ይቅር ይላሉ፡፡ ለበቀልም አይነሳሱም፡፡ ወደ ህግ ቦታም አይሄዱም፡፡ በባህሉ መሰረት የሽምግልናው ስርዓት ተካሄዱ እርቁ በሰላም ይፈፀማል፡፡

ገዳዩ እውነቱን ካልተናገረና ከዋሸ እውነቱን ሽማግሌዎቹ አጣርተው ከደረሱበት ሽምግልናውን አያካሂዱም፡፡ኃላፊነቱንም አይወስዱም፡፡ እውነቱን መደበቅ በባህሉ የተወገዘ ስለሆነ ሽማግሌዎቹ ከሟች ቤተሰብ ጋር በመነጋገርና በመተማመን የረጃት እርቅ[43] ያደርጋሉ፡፡ በሌሎቹ ቤተሰቦቹ ላይ ብቀላ እንዳይፈፅሙ ቃል ያስገቧቸዋል፡፡ ገዳዩንም አገሩን ለቆ ራቅ ወዳለ ቦታ እንዲቆረር[44] ተመልሶ እንዳይመጣ ፣ ከሟች ቤተሰብ ጋር ፊት ለፊት እንዳይተያይ ፣ ቤተሰቡንም ለመጠየቅ ፣ ለማየት ፣ እንዳይመጣ በማለት ከማህበረሰቡ አካባቢ እንዲርቅ ያደርጉታል፡፡ እሱም ላይመለስ አገር ጥሎ ይሄዳል፡፡ ይህም ከማህበረቡ መገለል ወይም መገንጠል እንደ ትልቅ ቅጣት ስለሚቆጠርና ሀሰተኛ መሆኑም ሆነ ሰው መግደል በባህሉ ስለሚያስወግዝ ማንም ሰው ጥፋቱን ከነምክንያቱ ለሽማግላቹ ያስረዳል እንጂ አይደብቅም፡፡ ከዚህ አልፎ ሰውን ገድሎ ቢደበቅ ፈጣሪ ራሱ ያጋልጠዋል ብለው ያምናሉ፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆን ከተረቶታቸው እንመልከት፡፡

> በድሮ ጊዜ ነው አንድ ጨካኝና አረመኔ ሰው ነበር፡፡ ይህም ሰው የሚኖረው የሰዎችን ሀብትና ንብረት እየዘረፈ ወደ ሌላ ነገር በመውሰድ በመሸጥ ገንዘብ በማከማቸት ልዩ ልዩ የጦር መሳሪያ በመግዛትና በመሳሪያው ሰዎችን በመግደል ያለ ጥሪታቸውን በመውሰድ በድብቅ ዋሻ ውስጥ በማከማቸት ለራሱ

[43] የረጃት እርቅ ማለት የገዳዩ ቤተሰብ እርቅ ከገዳዩ ውጭ የሚደረግ

[44] መቆረር ከቦታው ተነጥሎ ሌላ አገር ቦታ በቅጣት መሄድ

በማጠራቀም ነበር፡፡ ገንዘብ የሌላቸውን ሰዎችም ለምን የላችሁም እያለ አሰቃይቶ ይገድላቸዋል፡፡ ቢለምኑትም የፈጣሪን ስም እየጠሩ ቢለማመጡትም በፍፁም ርህራሄ የሌለው አረመኔ ስለሆነ አይምራቸውም፡፡ በዚህ የተነሳ እሱ በሚገኝበት አካባቢ ማንም ደፍሮ የሚሄድ የለም፡፡ የሚሮርበትም ቦታ ጫካና እልም ያለ በረሃ ስለሆነ ወደዚያ ደፍሮ የሚሄድም አልነበረም፡፡ ከዕለታት በአንድ ቀን አንድ ሰው እሱ በሚኖርበት በረሃ ቦታ ብቻውን አቋርጦ ሲሄድ አረመኔው ሰውዬ አገኘው፡፡ በድፍረቱ በጣም ይገረማል፡፡ ያስቆመውና "አንተ በዚህ መንደር ብቻህን በድፍረት ስትሄድ አትፈራምን ብሎ በንቀት ጠየቀው፡፡" እንግዳውም ሰው ለምን እፈራለሁ ምንስ እንዳልሆን እፈራለሁ አለው እኔ ብገድልህ ማን ይደርስልሀል እኔ መግደሌንስ ማን ያውቃል አለው፡፡ ማንስ ይመሰክራል፡፡ እንደምታየው ምንም የለም፡፡ እንኳን ሰው የወፍ ዘር እንኳን አይታይም በማለት ንቀት በተሞላበት እና በትዕቢት ተናገረ፡፡ ሰውየውም ምንም አላደረግኩህ ፣ አልበደልኩህ ፣ ዝም ብለህ ብትገድለኝ ደሜን እግዚያብሄር ፣ መሬትና ንጉስ ይበቀሉልኛል አለው፡፡ በል እግዚያብሄር ፣ መሬትና ንጉስ ሲበቀሉልህ አያለሁ ብሎ ያን ሰው ገድሎ ከዚያም ከመንገዱ ዳር ቀበረው፡፡ ከብዙ አመታት በኃላ ያ ነፍሰ በላ ጨካኝ ሰው በዚያው መንገድ ሲሄድ ደከመውና ከመንገዱ ዳር ጥላው ደስ የሚል ዛፍ አየና እረፍት ለማድረግ ዛፍ ስር ተቀመጠ፡፡

ትንሽ እንደተቀመጠ ወደ ዛፉ ቀና ብሎ ሲመለከት የዛፉ ፍሬ በጣም የሚያስጎመዥ ሆኖ አየው፡፡ ተነስቶ ወደ ዛፉ ፍሬ ሲመለከት በጣም ያማረ ብሉኝ ብሉኝ ብሉኝ የሚያሰኝ የትርንጎ ፍሬ ሆኖ ያገኘዋል፡፡ ትርንጎውም እስካሁን አይቶት የማያውቀው በጣም ያማረ ነበር፡፡ ይህንንስ ላገረ ገዢው በስጦታ ብሰጠው ይደሰታል ፤ እኔንም ይሾመኛል ይሸልመኛል ብሎ በማሰብ በመልካም ዕቃ ሰብስቦ ወስዶ ይሰጠዋል፡፡ አገረ ገዢውም ሲያየው በጣም ደስ አለው፡፡ ይህንን የመሰለ ትንርንጎ አይቼም ሰምቼም አላውቅም እንዴት ያለ መሬት አፈራው ብሎ ጠየቀው፡፡ ሰውየውም የለም ይህ ዛፍ ብቻ ነው ይለዋል፡፡ ትንርጎው የበቀለበትም ቦታ አንድ መንገደኛ ገድሎ የቀበረበት እንደሆነ ነገረው ፤ ሟቹም ሲገድለው የተናገረውን ነገረው፡፡ ንጉሱም ፍርዱን አስፈፃሚው እኔ ነኝና ብሎ የደሀውን ደም በእግዚያብሄር ዘሪነት፣ በመሬት አብቃይነት ፣ በኔ ፍርድ ሰጭነት ደሙ

ይመለሳል ብሎ ሞት ፈረደበት ይባላል (አቶ ባየ አስምሮም ፣ ቃመ. 10/10/2009 ዓ.ም)፡፡

በዋግኽምራ ባህል ከመነሻውም ሀሰት መናገር ክልል ነው፡፡ ነገር ግን ሰውን አጥፍቶ/ግድሎ ለመደበቅ የሚፈልግ ቢኖር እንኳ ሁሉን የሚመለከት እግዚያብሬር ያጋልጠዋል ማለት ነው፡፡ እውነቱ የታወቀ ዕለት ደግሞ ከብሔረሰቡ ተነጥሎ አገር ጥሎ መሰደድን የመሰለ ከባድ ቅጣት ስለሚያስከትል ማንም ሰው የሰውን ህይወት ካለ አግባብ ለማጥፋት እንዳይነሳ ተረቱም በምሳሌያዊ ንግግሩም እንዲህ እያስጠነቀቀ ሰላምን በአካባቢው ያሰፍናል፡፡ በብሔረሰቡ ውስጥ የተፈጠረን ግጭት እንዲህ በመሰለው ባህላዊ መንገድ መፍታት በአንድ በኩል ሰላማዊ ኑሮን የበለጠ እንዲጎለብት ያግዛል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የፍርድ ቤቶችንና የፀጥታ አካሎችንም የስራ ጫና ይቀንሳል፡፡ ራሱና አካባቢው ሰላም የሆነ ማህበረሰብ ደግሞ አካባቢውን ለማልማት መነሳሳት በቀላሉ ሊከወን የሚችልና ለዘላቂ ልማትም ዋነኛ ምቹ ሁኔታ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የዩኔስኮ የ2012 ሰነድ እንደሚገልፀው ለባህላዊ ሁኔታዎች ለማህበረሰቡና ለአውዱ የተለየ ትኩረት የሚሰጡ የልማት ተግባራት ዘላቂና እርስ በእርስ የተዋሃዱ ፣ ፍትሃዊና ስኬታማ/አመርቂ የልማት ውጤቶችን ያስገኛሉ፡፡ ለባህል እሴቶች ትኩረት መስጠት የሰብዓዊ መብት አከባበር ሂደቶችን ፣ ያለመግባባትንና ግጭቶችን ለማስወገድ ይረዳል፡፡ ይህ ሲፈፀም ደግሞ የልማት ዓላማዎችን ለማሳካት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ፤ ባህላዊ እሴቶችን በበጎ መልክ መረዳት ለዘላቂ ልማት ዓይነተኛ መሳሪያ ነው (ዩኔስኮ ፣ 2012 ፣ 5)፡፡

ኽምራዎች ሰላማዊ ሰዎች መሆንና በአጋጣሚ የተከሰቱ ግጭቶችን በራሳቸው ባህላዊ መንገድ መፍታታቸው በአካባቢያቸው ሰላማዊ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ ለልማት አስፈላጊ ምቹ ሁኔታ እንደሆነ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ከላይ በተለያዩ መገለጫዎች የተወሳው የኽምራዎች ሁለንተናዊ የጋራ ህይወት ከአኗኗራቸው ጀምሮ በሁሉም የእለት ከእለት መስተጋብራቸው ተደጋግሞ እየተከሰተ በመስፋፋትና ስር በመስደድ የብሔረሰቡን አስተሳሰብ እየተከለ ፣ እያደረጀ እያስረገጠም የሚሄድ ነው፡፡ ይህ የጋራ አኗኗር ሕይወት ደግሞ በጋራ የእርሻ መሬቶችን አልምቶ በጋራ ተጠቃሚ ለመሆን ፣ በጋራ ስለ አካባቢ ልማቶች ተወያይቶ የጋራ ውሳኔዎችን ለማሳለፍና የጋራ ህይወትን የተሻለ ለማድረግ ጠንካራ ባህላዊ መሰረት ስለሆነ እንደምቹ

አጋጣሚ ቆጥረው ቢገለገሉበት የአካባቢውን ልማት ለማሳደግ ዓይነተኛ መሳሪያ መሆን ይችላል፡፡

## 5.3. ሀቀኝነት ፣ ግልፀኝነትና ያልተገባ ጥቅምን አለመፈለግ

በዋግ ኽምራ ብሔረሰብ ታማኝነት ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል፡፡ እውነት መናገር ፣ አለማታለልና ሀቀኝነት ያላቸው ቦታ ከፍተኛ ነው፡፡ ሀሰት መናገር ነውር ነው ፤ ጥፋት እንኳን ቢሆን ያጠፉሁት እኔ ነኝ ብሎ ዕውነቱን ይናገራል እንጂ አይዋሽም፡፡ በግልፅ ይሰራል ፣ ሲጠየቅ የሚያውቀውን ይናገራል፡፡ ይኼውም ጭብጥ ከዕለት በዕለት ኑሮዋቸው በዘለለ በስነቃሎቻቸውም በተደጋጋሚ ሲነገር ይሰማል ፤ ሲፈፀምም ይታያል፡፡ ለዚህ ማሳያ እንዲሆን ምሳሌያዊ አነጋገራቸውን እና አንዱን ተረታቸውን ቀጥለን በየተራ እንመልከት፡፡

> አንድ ሰው ነበር፡፡ በሬዎቹን ጠምዶ እያረሰ ነበር፡፡ እያረሰ እያለ ሁለት ሰዎች ነብር ሊገድሉ ብለው ያባርሩታል ፤ ሲያባርሩት ፣ ሲያባርሩት ፣ ሲያባርሩት ወደ ሰውየው እርሻ ይደርሳል፡፡ ሰውየው ደሞ ለበሬዎቹ የማታ እራታቸውን የሚበሉት ጭድ የሚይዝበት ትልቅ ስልቻ/አቅማዳ አፉን እንደከፈተው አስቀምጧል ፤ ነብሩ ሲደርስ እያባረሩኝ ነው! ሊገድሉኝ ነው! አድነኝ! ሲለው ሂድ እዚያ አፉን ከከፈተው አቅማዳ ውስጥ ግባና ተደበቅ ጫፉን ቀስ ብየ አስረዋለሁ ይለዋል፡፡ ሰዎቹ ሲደርሱ አንተ ሰውዬ ነብር በዚህ አላለፈም ብለው ሲጠይቁት ያው እዚያ አቅማዳ ውስጥ ተደብቋል ይላቸዋል፡፡ ምን ይቀልዳል! የማይሆን ነገር ይናገራል እንዴ! እንዴት አቅማዳ ውስጥ ነብር ሊደበቅ ይችላል ብለው ጥለውት ይሄዳሉ፡፡ ሰዎቹ ሲሄዱ አይቶ ትንሽ ቆይቶ አያ ነብር ሰዎቹ ሄደዋል ውጣ ይለዋል፡፡ ነብሩም ሳይወጣ ውስጥ እንዳለ አልወጣም፡፡ ትደብቀኛለህ ስል ታጋልጠኛለህ እንዴ አንተን አምነው አቅማዳውን ቢከፍቱ እኮ ያገኙኝ ነበር ሲለው አያ ነብር እውነት ካላዋጣህ ውሸት አያዋጣህም እኔ የለም ብል ይፈትሹና ያገኙህና ይገድሉህ ነበር፡፡ እውነት ስለተናገርኩ ነው አንተ የዳንከው አለው ፤ ነብሩም አንተ በስልቻ ውስጥ አፍነኽኝ ምግቤን እንዳልፈልግ አስርበኽኛል፡፡ አንዱን በሬህን ስጠኝ አለዚያ አንተን እበላሃለሁ ይለዋል፡፡ ገበሬውም በጣም ይናደድና ደግ ስላደረኩ ይኼን አሰብክ በል ተያይዘን ፍርድ

የሚሰጠን እንፈልግ ይለዋል፡፡ ነብሩም እሺ ብሎ ከነአቅማዳው ተሸክሞት ትንሽ እንደሄዱ ነብሩ ቢገድለኝስ ብሎ አሰበና አውርደኝ እኔ በራሴ መሄድ አለብኝ አለው፡፡ ሰውየውም መልካም ሰው ነበርና አውርዶት ከስልቻው ካወጣውና ጎን ለጎን ሻሚያ መሄድ እንደጀመሩ ቀበሮን አገኟት፡፡ በል ቀበሮን እንጥራትና ትዳኘን አለ ሰውየው፡፡ እሽ ብሎ ቀበሮ ተጠራችና ዳኛ እንድትሆናቸው ጠየቋት፡፡ ቀበሮም በነገሩ ተገርማ በሉ ክሳችሁን ልስማ ትላለች፡፡ ነብር ቀድሞ ተናገረ ፤ ሰውየው ሊናገር ሲል በል ሰውየው ያደረከውን አሳየኝ ትለዋለች፡፡ ነብርም ልትፈርድብኝ ነው ብሎ ተሸቀዳድሞ ከስልቻው ሲገባ ሰውየው ግጥም አድርጎ አፉን አሰረው፡፡ ቀበሮም በል ሰው ዱላ በጅህ ነብር ከስልቻህ ስትለው ነገሩ ገባውና በያዘው ዱላ ራስ ራሱን ብሎ ገደለው ያባላል (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቃመ. 15/10/2009 ዓ.ም ፣ ተረት ቁ. 6)፡፡

ይህ ተረት እንደሚያመለክተው ተሳዳጁን ነበር አልደብቅም ብሎ አልከለከለውም እውነቱንም ጠቆማቸው እንጂ ‹‹አላየሁም›› ብሎ አልዋሸም፡፡ እነሱ ውሸት ነው ብለው በመደምደማቸው ግን ሳይፈትሹ ጥለውት ሄዱ፡፡ የተደበቀው ነብር ግን “ለምን እውነቱን ተናገርክ ልታስገድለኝ ነበር፡፡” ነብሩም ተናዶ ታማኝ መሆኑን ትቶ ሊበላው ፈለገ፡፡

በተረቱም የታየው የኽምራዎችን እውነት ተናጋሪነት ነው፡፡ ኽምራዎች እውነቱን ተናግሮ እመሽበት ማደር የሚል ብሂል የሚከተሉ ናቸው፡፡ በዚህ ተረትም የታየው ለእውነት ሲሉ ሀሰትን ከመጠየፋቸው የተነሳ እውነትን ተናግሮ ለማውጣት እስከ ፍትህ ድረስ የሚሄዱ መሆናቸውን ያጠይቃል ፣ በተራዛሚውም እውነትን በሃሰት ሊያጠፋት የሚሻውንም እንኳ በራሳቸው ፍትህ ለማግኘት የሚፈልጉ ሳይሆን በዳኝነት ተፋርደው ለማስረገጥ የሚጥሩ መሆናቸውንም ያመላክታል፡፡

ይህ የታማኝነትና የዕውነተኝነት ጭብጥ በሌሎችም ተረቶችና በምሳሌያዊ አነጋገሮቻቸው ተደጋግሞ ይነሳል፡፡

በአንድ መንደር አንድ እጅግ ብልህ የሆነ ሰው በጣም ከሚወዳት ሚስቱ ጋር በፍቅር በሰላም ይኖሩ ነበር፡፡ ባልና ሚስቱም ግቢያቸውን የሚጠበቅ ውሻ የፈሰሰውን ጥራጥሬ ጭረው የሚበሉ ዶሮዎች ነበሯቸው፡፡ ውሻው ጌታውን በጣም ይወደዋል ፤ ዶሮዎቹም ደግሞ ጥራጥሬ ስለምትሰጣቸው ጭልፊት

እንዳያነሳቸው የምትጠብቃቸው ሴትዮዋ ስለሆነች እሷንም ይወዷታል፡፡ ሌላ ምንም ልጅም ሆነ ከብቶች አልነበራቸውም፡፡ ሰውየው የቤት እንስሳትም ሆነ የዱር አራዊትን የጩኸት ድምፅ የሚያወጡትን መስማትና መተርጎም ይችላል፡፡ በአካባቢው መልካምም ሆነ መጥፎ ነገር የሚመጣ መሆኑን በእንስሳቱ ጩኸት ያውቃል፡፡ የአካባቢው ሰዎች እንዲጠነቀቁ ፣ ጦርነት ከሆነም እንዲዘጋጁ ለህዝቡ ይናገራል፡፡ በዚህም በጣም የተከበረና የተወደደ ሆነ፡፡ ሁሉም ሰው የሚነግራቸውን ይሰሙታል፡፡ ያከብሩታል፡፡

ከዕለታት በአንድ ቀን አንድ ጅብ ሲጮህ ይሰማል፡፡ በጩኸቱ የሰማው ነገር በጣም የሚያስቅ ነበርና ከት! ብሎ ይስቃል፡፡ ሚስቱም በሳቁ ደንግጣ ትነቃና ምነው ምን አሳቀዎት ብላ ትጠይቃለች፡፡ባልዬውም ሊነግራት አልቻለም፡፡ በዚህ የተነሳ ካልነገሩኝ እያለች ትጨቀጭቀዋለች፡፡ እሱም ሊናገር ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ በዚህ የተነሳ ጠባቸው ሊቆም ባለመቻሉ ሰውየው በጣም ተጨነቀ፡፡ የሰማውን ነገር ቢነግራት ይሞታል፡፡ ይህንን ጉዳይ ካልነገሩኝ እያለች መጨቅጨቋን ባለመተዋ ለመንገር ወሰነ፡፡ እንዲህም አላት እንድነግርሽ ከፈለግሽ ትልቅ ድግስ ደግሽ ፤ ያንቺም የኔም ቤተ ዘመዶች ይጠሩና በዚያን ጊዜ እነግርሻለሁ ይላታል፡ ፡ ድግሱ ተደግሶ ዘመዶችም በበነጋው ሊመጡ ተወሰነ፡፡ ሌሊት ላይ ጌታቸው የሚወደው ውሻ ያላዝናል፡፡ ዶሮ ሰማና ለምን ታላዝናለህ ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ ውሻውም ነገ ጌታችን ይሞታል ይለዋል፡፡ ዶሮም ደንግጦ በምን ምክንያት ነው የሚሞተው? ይለዋል ፤ ጌታችን የሁሉንም የቤትና የዱር እንስሳ ድምፅ ያውቃል፡፡ በሚሰማውም ድምፅ ክፉና በጎውን ይለያል፡፡ ሌሊት የጅብ ጩኸት ሰምቶ ስለሳቀ ለምን ሳቁ ብላ ጠይቃው ሊነግራት ስላልቻለ በዚህ ተጣሉ፡፡ የሰማውን ከተናገረ ይሞታል፡፡ ነገ ቤተሰብ በተሰበሰበበት ሊናገር ነው፡፡ እውነቱን ነግሯት ይሞታል ይለዋል ለዶሮው ፤ ዶሮውም ትንሽ አሰብ አድርጎ "መፍታት ሳለ መሞት" ምን ይሉት ሞኝነት ነው አለ፡፡ ይህንን የውሻውንና የዶሮውን ንግግር የሰማው ባል ያላሰበው መዳኛ ዘዴ ከዶሮው ስለሰማ ደስ አለው፡፡ ሁሉም ቤተሰብ በተሰበሰበበት ሀሳቡን ለውጦ ሚስቱን እንደፈታት ለሁሉም ነገራቸው፡፡ የተሰጠውን እውነት በታማኝተት ጠብቆ ለሚስቱ እንኳ ሳይናገር ቃሉን ጠብቆ

በሰላም ኖረ ይባላል። (አቶ አስራት ታደሰ ፣ ቃመ. 07/10/2009 ፣ ተረት ቁ. 8)።

ሚዳቋ ከነብር ጋር ላይበላት አብረው በወዳጅነት ሊኖሩ ይተማመናሉ። ነብር እምነቱን ክዶ ሊበላት ሲሞክር ከእንጨት ጉማጅ ላይ እሷን ያዝኩ ብሎ ተሰክቶበት ሲያጣጥር ፣ ሲሰቃይ ቃሉን ያፈረሰ በልጄ ወይም በልጅ ልጄ ቢደርስ ነው አላልሽም ሲላት ሚዳቋም አባትህ የሰራውን ምን አውቃለሁ ትለዋለች ፣ እሱም ተሰቃይቶ ሞቶ ይደመደማል (አቶ አስራት ታደሰ ፣ 07/10/2009 ዓ.ም ፣ ተረት ቁ. 9)።

በዋግኽምራ ብሔረሰብ ያልተገባ ጥቅምን መፈለግና በሰው ላይ ተንኮል መስራት የተወገዙ ናቸው። የተንኮልን መጥፎነት የሚያሳየው ተረታቸው ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል።

በድሮ ዘመን አንድ በጣም የታወቀ ደሀ ሰው ነበር አሉ። ይህ ሰው ድህነቱ በጣም ስላሳሰበው አንድ ብልህ ቤት ምክር ፍለጋ ይሄዳል። ብልሁ ሰውም ሃብቱን ለማፍራት ቀን ቀን ብዙ ህዝብና እንስሳት ከሚቀዳበትና ከሚጠጣበት ወንዝ ዳር ሶስት ሌሊት በተከታታይ በመተኛት የምታገኘው እንግዳ ሰው የሚሰጥህን ምክር በትክክል ፈፅም አለው። ደሀውም በተነገረው ነገር ከልቡ በመደሰት የሚሆነውን በጉጉት መጠባበቅ ጀመረ። በሶስተኛው ሌሊት እንደተነገረው እባብ ያገኘዋል። እባቡም በመገረም አንተ ሰው በአሁኑ ሰዓት እዚህ የተገኘሽው ለምንድን ነው ከአውሬ በስተቀር በጨለማ ወንዝ ዳርቻ ሰው ይኖራል? በማለት ጠየቀው። ደሃውም ሰው ነገሩን በእርጋታና በደስታ አስረዳው፡ ፡ እባቡም በሁኔታው በጣም ስለተሰማው ሃብትን ለማግኘት ያደረከው ነገር ከሆነ እንደማትክደኝ ቃል ግባልኝና ሃብት እንድታገኝ አደርጋለሁ አለው። ድሃውም ከልቡ በመደሰት ቃል ኪዳን ገባለት። እባቡም በአካባቢው ያሉትን ሰዎች በመንደፍ መድሃኒቱንም እራሱ እንደሚሰጠው ለድሃው ቃል ገባለት። ድሃውም እባቡ በሚሰጠው መድኃኒት ሰዎችን በማከም ትልቅ ሃብት እንደሚያገኝ በማሰብ ፍጹም አውነተኛ ጓደኛ ለመሆን ከልቡ ተመኘ። እባቡም የሰውየውን ድህነት በማየቱ ከልብ ለመርዳት ወሰነ። በሌላኛው ምሽት በአካባቢው ያሉትን ሀብታሞች አንድ በአንድ በመንደፍ አዳረሳቸው። በአካባቢው ያሉት ህዝቦችም እጅግ

በመገረምና በመደንገጥ ፈዋሽ ለማግኘት ሲሯሯጡ ደሀው ሰውዬም እንደሚያክማቸው በመግለፅ ነገር ግር ካላቸው ሃብት እሩብ እንዲያካፍሉት በኩራት ተናገረ፡፡ ሰዎቹም በድሀው ውሳኔ ቅሬታ ያላቸው ቢሆንም ሕይወታቸውን ለማትረፍ ሲሉ በሃሳቡ ተስማሙ ፤ ደሃውም የእነሱን ሕይወት በማትረፉ ከፍተኛ ዝናና ተሰሚነት በህዝቡ ዘንድ አተረፈ ፤ እንዲሁም በሃብት አሉ ከሚባሉት ሰዎች አንዱ ለመሆን በቃ፡፡ ከዚያ በኋላ ትዳር በመመስረት የተንደላቀቀ ኑሮ ለመምራት ቻለ፡፡ ነገር ግን ይህ ድሃ የነበረ ሰው በሃብቱ በመኩራት አንድ ቀን ሳይታሰብ ይህ እባብ ይህንን ሀብት ሊነጥቀኝ ስለሚችል እሱን መግደል አለብኝ በማለት እባቡ ወዳለበት ቦታ በመሄድ በጥይት ለመግደል ሞከረ፡፡ ነገር ግር እባቡን ጥይት ስላላገኘው ሳይሞት ቀረ፡፡ እባቡም ከልቡ በመናደድ የሰውየውን ወንድ ልጅ ገደለበት፡፡ ሰውየውም እንደገና በመፀፀት ጓደኝነታችንን ዳግም እንመስርት በማለት ቢጠይቀውም እባቡ እንዲህ በማለት መለሰለት "ስማኝ አንተ የሰው ልጅ! ልጅህ ዳግም አይመለስም ፤ አንተ ተኩሰህ የሳትከው ጥይትም ዳግም አይገድለኝም" አለው ይባላል፡፡

ስለዚህ ተንኮል መስራት የሚጎዳው ተንኮለኛውን ስለሆነ ተንኮል መስራት እንዳታስቡ (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቃመ 10/10/2009 ፣ ተረት ቁ. 10)፡፡

ከላይ የቀረበው ተረት እንደሚያሳየው ደሃው ሰውዬ እና እባቡ በቅንነት ለመረዳዳት ላለመከዳዳት ቃል ገብተው ነበር፡፡ በደሃው ሰው ትዕቢትና ተንኮል ግን ስምምነታቸው ፈረሰ፡፡ ደሀው ሰው እባቡ በሰጠው መድሃኒት ሃብታም ፣ ታዋቂና ባለዝና ሲሆን እባቡ የሰጠኝን መድሃኒት መልሶ ሲወስድብኝ ይችላል ፤ እውቀቱ የሱ ነው የሚል ክፉ ሃሳብ ፀንሶ የመድሃኒቱን ባለቤት ገድሎ ያለሃሳብ መድሃኒቱን የራሱ ብቻ ለማድረግ ስለፈለገ ሊገድለው ሞከረ፡፡ ነገር ግር ሳይሳካለት ቀረ፡፡ ቃላቸው ግን ፈረሰ፡፡ ጠላትነታቸውም ቀጠለ፡፡ እባቡም የሰውየውን ልጅ በመግደል ተበቀለው፡፡

በተረቱ አማካኝነት የተተከለው ባህላዊ እሴት ክህደትና ተንኮል ለሞት ያበቃሉና አታድርገው የሚል ሲሆን የእባቡ ከሞት መዳን በሃቅና ቃሉን ሳያጥፍ የሚፀና ሰው በተንኮለኞች ሄራ የማይጠመድና የማይሞት መሆኑን ያሳያል፡፡

እነዚህ እውነተኛና ታማኝ የመሆን ተገቢነት የሚያጎሉ ጭብጦች በኽምራዎች ትረካዎችና ምሳሌያዊ ንግግሮች በስፋት ተደጋግመው ይመጣሉ፡፡ ስለድመትና ዓይጥ ጠላትነትና ተፈጥሮአዊ ሁኔታ የሚተርከው ትረካ የሚያሳየው ይህንኑ ታማኝና ሀቀኛ የመሆንን ተገቢነት ነው፡፡

> በጥፋት ውሃ ጊዜ ኀህ ከፍጥረታት ሁሉ ወንድና ሴት እያደረገ ወደ መርከቡ ካስገባ በኂላ አንድ ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡ ይኼውም አምላክ ምህረቱን እስኪልክልን ድረስ በመርከቢቱ ውስጥ የሩካቤ ስጋ ግንኙነት የተከለከለ በመሆኑ ማንም ይኼንን እንዳይፈፅም ብሎ ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡ ሌሊት ላይ ድመት ተደብቆ ሚስቱን ሲገናኝ አይጥ አይታ ኖሮ ሲነጋ ለኖህ ትናገራለች፡፡ ድመት ተጠርቶ ሲጠየቅ አላደረኩም ብሎ ይክዳል፡፡ ኖህም ደግ ሰው ስለነበር ሁለተኛ እንዳይፈፅም ድጋሚ ያስጠነቅቃል፡፡ ማታ ድመት እንደለመደው ሲሰርቅ ሚስቱ ከረካች በኂላ በንዴት ስትነክሰው ሲጮህ ኖህ ይሰማኛል ብሎ ሲሮጥ እሷም(ሚስቱ) በብስጭት ተከትላው ስትሮጥ ኖህ ይይዛቸዋል፡፡ ድመት ከግብረ ስጋ ግንኙነት በኂላ ሚስቱ ስለምትገለው እሷ በስሜት ውስጥ በርካታ ስትተኛ/ጥኂት በመሸሽ ለተወሰነ ጊዜ ይደበቃል፡፡ ሚስቱም እሱን በፍለጋ ትራወጣለች ፣ ትጮሃለች ፣ በፍለጋ ትናውዛለች፡፡ይህም እምነቱን በማጉደሉና በመዋሸቱ ነው፡፡ ድመትና ዓይጥም የማይስማሙት በዚህ የተነሳ ነው (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቃመ. 10/10/2009 ዓ.ም ፣ ተረት ቁ. 11)፡፡

ከላይ የቀረበው ትረካ በተፈጥሯዊ ጉዳዮች ሳይቀር መልስ እየሰጠ ሃቀኝነትን የሚተክል ነው፡፡ ድመት አልታየሁም ብሎ ሰረቀ ፤ ሲጠየቅም ካደ ፣ ስላልተቀጣ ስህተቱን ደገመ፡፡ በድብቅ የተሰራውን በግልፅ የሚመልስ አምላክ ግን ሀሰትን /ክህደትን/ ስለሚፀየፍ እጅ ከፍንጅ እንዲያዝ አደረገው፡፡ ስለዚህ ሰው አላየንም ብለን ብንሰርቅ ፣ ትዕዛዝ ብንተላለፍ ሁሉን የሚያይ አምላክ ያጋልጠናል ነው የትረካው መልዕክት ፤ ባህሉ ብሔረሰቡ ውስጥ የዕውነተኛነትን እሴት በዚህ መልኩ ነው እንዲሰርፅ የሚያደርገው፡፡ ይህ ደግሞ የሥነ-ቃል ዋነኛው ተግባር ነው፡፡

በዋግኽምራ ብሔረሰብ ተረቶች ፣ ትረካዎችና ምሳሌያዊ ንግግሮች ተደጋግመው እንደታዩት ክህደት ፣ ሃሰትና ያልተገባ ጥቅምን መፈለግ በብሔረሰቡ ዘንድ ነውር ነው፡፡ ይኼ በመሆኑም በአካባቢው የሌባ ስጋት የለም፡፡ሴቶችና ልጆች በባህሉ የሚሰሩ ልዩ ልዩ

ጌጣጌጦች ፣ እህል ፣ የጋማና የቀንድ ከብቶችን ብቻቸውን ተሸክመውና እየነዱ ረጅም መንገድ ሄደው ሸጠውና ለውጠው በሰላም ወደቤታቸው ይመለሳሉ። ምንም ጥበቃና ከለላ በሌለው በጠራራ ፀሐይ በክፍት የገበያ ቦታ ላይ ተራ ይዘው ግብይቱ ይከናወናል። ያለ ምንም ማጭበርበር ፣ ቅጥፈት ፣ ክህደትና ሽፍጥ ሸጠው ገዝተው በሰላም ይመለሳሱ። የሸጡትንም ሆነ የገዙትን ሲጠየቁ እውነቱን ይናገራሉ እንጂ እብለት የለበትም። የሚገርመው ደግሞ ሻጮቹ ልጆች ወይም በጣም ያረጁ ሰዎች ከሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። ላለማጭበርበርና ላለማታለል መኖሩን በትክክል ግብይቱ መፈፀሙን ሌሎች በገበያው የተገኙ ሰዎችን ዋቢ ያቆማሉ። ነገ አታለው ገዟቸው ወይም ሸጡ መባልን አጥብቀው ይፈራሉ። ይህንን ሁኔታ በሰቆጣ ከተማ ባለው የገበያ ቦታ ባደረኩት ምልከታ ለመታዘብ ችያለሁ።

ከላይ እንደተመለከትነው የእነዚህ ትረካዎችና ተረቶች ሚና ደግሞ የመስኩ ምሁራን የፎክሎር ተግባራት ብለው ከሚያነሷቸው ጉዳዩች ውስጥ የማስተማር ፣ የመትከል ፣ የመቆጣጠርና የመግታት ሁነቶችን የሚያሳዩ ናቸው (sims and stephens, 2005 ፣ ፈቃደ 1991, 20 ፣ Finnegan, 1992)።

በዋግኽምራ ባህል የሰው ንብረት መንካትና ሌብነትም ፈፅመው የተወገዙና የሚያስነውሩ ናቸው። መረጃ ሰጪዬ አቶ ባየ አስምሮም የሰው ምኩት ፍየል  ሰርቆ ያረደው ሰው የደረሰበትን ሁኔታ እንዲህ ያስረዳሉ።

> አንድ ጊዜ አንድ ሰው የሰው ምኩት ፍየል  በቤቱ በር ሲያልፍ ቤቱ አስገብቶ ያርደዋል። የምኩቱ ባለቤት ምኩቴ ጠፋብኝ ብሎ ቢፈልግ! ቢፈልግ! ቢፈልግ! ያጣዋል። በዚህ ጊዜ በወቅቱ የነበሩት ዋግሹም ጎበዜ የሆነውን ይሰማሉ። ዛሬ ምኩትም ሆነ በሬ ያረደ ስለሌለ ትኩስ ስጋ እማን ቤት እንዳለ በየቤቱ እየገባችሁ በርብሩ ብለው ትዕዛዝ ያስተላልፋሉ። የታዘዙትም አሽከሮች ፍተሻ ሲያደርጉ ሰውየው ምኩቱን አርዶ ስጋውን ግርግዳው ላይ ሲሰቅልና ሚስቱ ዱለቱን ለመጥበስ ስታዘጋጅ ያገኙዋቸዋል። ወዲያው ሰውየውን ይዘው ለዋግሹም ያቀርቡታል። ያረድከው ምኩት የማነው ብለው ሲጨይቁት በቤቴ በር ሲያልፍ ስላገኘሁት ቤቴ ውስጥ አስገብቼ ደብቄ አረድኩት ፤ ሰው ያየ አልመሰለኝም ነበር ይላል። በዚህ ጊዜ ዋግሹም ጎበዜ ፍርድ አዋቂ ነበሩና የምኩቱን ስጋ በቆዳው ጠቅልላችሁ ስጋውን ተሸክሞ ሌባ ነኝ እያለ ገበያ ውስጥ ይዙር ብለው አዘዙ።

ሰውየውም ስጋውን ተሸክሞ ሌባ ነኝ እያለ ሲዞር የገበያው ሰው ሁሉ ሲሰድቡትና ሲያነውሩት ከፊሉ ሲመቱት ዋሉ፡፡ ከዚያም ምኩቱን ያረደው ሰው በማፈሩና በሰው ሁሉ ፊት ሌብነቱ ስለተጋለጠ አገሩን ለቆ ጠፋ ይባላል፡፡ በዚህ ከባድ ቅጣት የተነሳ በኛ አካባቢ ሌብነት በጣም ጠያፍ ስለሆነ ማንም ሰው እንኳን ሊሰርቅ ይቅርና ወድቆ ቢያገኝ እንኳ አይነካም (አቶ ባየ አስምሮም ፣ ቃመ. 07/10/2009 ዓ.ም)፡፡

በጋራ ወይም በጉርብትና መኖር ባህላቸው ለሆነው ኽምራዎች ከማህበረሰባቸው መነጠል መገለል የሞት ሞት ነው፡፡ ይህንን ከባድ ቅጣት ሊያስከትሉ የሚችሉትን ሁነቶች ፈፅመው ይጠየፏቸዋል፡፡ በምሳሌያዊ ንግግራቸውም "ሰርቆ ከማፈር እጅን መሰብሰ" እና "አንድ ጊዜ ሲሰርቀኝ ካየሁት ቢጨምርልኝ አላምነው" ይላሉ፡፡ ስለሆነም እጃቸውን ወደነዚህ ጥፋቶች ለመዘርጋት ከቶውንም አያስቡም፡፡ ይህ በመሆኑ ነው ሌብነት ፣ ማጭበርበርና ቅጥፈት በብሔረሰቡ ዘንድ የማይታየው፡፡

እነዚህ የዋግኽምራ ማህበረሰብ ባህላዊ እሴቶች የሆኑት ግልፅነትና ታማኝነት በዕለት ተዕለት ህይወታቸው የሚከወኑና በተግባር የሚታዩ ትውልዱ ጠብቆ እንዲያቆያቸውም ከላይ እንደተመለከተው በኑሮ ዘይቤያቸውም ሆነ በሥነ ቃሎቻቸው ተደጋግመው የሚመጡ እውነታዎች ናቸው፡፡ ስለ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ የሚያነሱት የመስኩ ምሁራን እንደሚያመላክቱት (Bascom, 1954; Okpewho, 1992; ፈቃደ, 1991) ባህል የመትከል ፣ የማጠናከርና የመግታት ተግባር እንደዚህ በባህላዊ እሴቶች ሁሉ ተደጋግሞ በመምጣት የሚገለፅ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡

በዋግኽምራ ብሄረሰብ ውስጥ የሰረጹት እነዚህ ባህላዊ መልኮች/ገጽታዎች ልማትን ለማፋጠን አወንታዊ ገጽታ ያላቸው ባህላዊ እሴቶች ናቸው፡፡

እነዚህ ምቹ ገፅታዎች ቢዳብሩ ፣ ቢለሙና ወደ ሌላውም ብሄረሰብ ቢስፋፉ ዛሬ ዋነኛ የልማት ፀር የሆኑትን ንቅዘት ፣ ብልሹ አሰራሮችና የአስተዳደር በደሎች ሊቀርፉ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም፡፡ ክቡር ገና "የሙስና ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቱ" በሚል ርእስ ያቀረቡት መጣጥፍ ላይ እንዳስቀመጡት የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ምክንያት የባህል ንጥፈት/ድርቀት እንደሆነ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

… ከልክ በላይ ትርፍ ለመሰብሰብ መሻት ፣ ሳይሰሩና ሳይደክሙ ሀብት ማካበት ፣ ጎረቤትና ሰፈር እንደ ሀገር ሲጎዳ አይመለከተኝም ብሎ መቀመጥ ከሙስና የፈለቁ ሙስናን የሚያስፋፉ ባህሪዎች ናቸው። ቀድሞ በሀገራችን የነበረው ከዘመድ ፣ ከጎረቤትና ከአካባቢ ማህበረሰብ ጋር ተሳስቦና ተፋቅሮ የመኖር ልማድ በተለይ በከተሞች አካባቢ እየተዳከመ ነው። ከዚህ ቀደም ሀብታምና ደሀው ባንድ ሰፈር ውስጥ በእድር ፣ በዕቁና በማህበር ተሰባስቦ ይኖር ነበር ፤ ዛሬ ያ መልካም ባህል ደብዝዟል ፤ግብረገብነት እየተዳከሙ የባህል መዝቀጥ ተምሳሌት በሆኑት ራስ ወዳድነት ፣ አስመሳይነት አመለካከቶችና እኩይ ባህሪያት እየተተኩ ናቸው (ክቡር ፣ 2004 ፣ 62)።

እነዚህ ከላይ በክቡር ገና የተነሱት ሙስናንና ብልሹ አሰራርን የሚያስፍኑ አሉታዊ ሁነቶች በዋግኽምራ ባህል በገጠሩ አካባቢ የሚታዩ አይደሉም። ከልክ በላይ ትርፍ ማግበስበስ ነውር ነው።

ቀድሞ በማሳያነት እንደቀረበው ጎረቤት ፣ ሰፈር ፣ ሀገር ሲጎዳ አይመለከተኝም ብሎ ማለፍ ፈፅሞ አይታሰብም። በኽምራ ችግሩም ሆነ ደስታው ጉዳቱም ሆነ ጠቀሜታው የጋራ ነው። የሁሉም የጋራ ችግርና የጋራ ጉዳይ ነው ፤ ለብቻ መቸገር የለም። ሀብታሙም ደሃውም በጋራ አብረው ተረዳድተው ይኖራሉ። የባህል መዝቀጥ ተምሳሌት የተሰኙት ራስ ወዳድነትንና አስመሳይነትን የመሳሰሉ የሰብዕና ንጥፈት ባህሪያት ማህበረሰቡ የሚያነውራቸው ናቸው። ከዚህ ይልቅ የጋራ መረዳዳቶችና መተሳሰቦቹ ጎልተው ይታያሉ። በተለያየ መልኩም ሰርፀው ይገኛሉ። ስለሆነም እነዚህን የኽምራን አዎንታዊ ባህላዊ እሴቶች በውል ተገንዝበው ቢያዳብሯቸው የማህበረሰቡን ህይወት ለመለወጥ አብይ ባህላዊ መሳሪያ ናቸው።

## 5.4 የዘመዳሞችና ጎረቤታሞች የጋራ ትብብሮች

የዋግኽምራ ብሔረሰብ የሰብአዊነት አስተሳሰብ “ለሰው መልኩ ሰው ነው” ነው በሚለው ባህላዊ እሴቶች ውስጥ የሚገለጥ ፍልስፍና ነው። ይህም የዘመዳሞች ፣ የጓደኞችና የጎረቤታሞች የጋራ ትብብሮች የአካባቢውን ልማት ለማሳደግ አወንታዊ መልካቸው መጠቀስ የሚችሉ ሌሎች ማሳያዎች ናቸው። ይህ በሰው ልጅ ላይ የመተማመን መንፈስ የዋግኽምራ ማህበረሰብ ማህበራዊነት መሰረት ነው። እንዲሁም በግለሰቦች

መካከል እርስ በእርስ በግለሰቡና በማህበሩ መካከል ያለው ጥብቅ ቁርኝትና ትስስር ልክኛ ሚዛን ጠብቆና ፀንቶ እንዲቆይ ምሶሶ ሆኖ ያቆመው ገንዘብ አሰባስቦ ችግርን ለመሸፈን ፣ ወጪ ሳይከብድ ተባብሮ ለመወጣት እንዲሁም ለተለያዩ ድንገተኛ ጉዳዩች አቅም ቢያንስ ተደጋግፈው ይቆማሉ። ድግግፉም መልክና ስርዓት ይዞ የሚከወን ሲሆን ዘላቂና ሁሉንም በእኩልነት የሚያስተናግድ ይሆን ዘንድም ደንብ አበጅቶ ፣ ልክ ወስኖ ያቆማቸዋል።

## 5.4.1. የደቦ ስራ (ወበራ)

የዋግኽምራ ብሔረሰብ ተለይቶ ከሚታወቅበት ተደጋግፎ በጋራ ስምምነትና በመረዳዳት በህብረት የመስራት እሴቱ ነው። በብሄረሰቡ የጋራ ስራው/ደቦው/የተለያየ ስያሜ ያለው ሲሆን የበርካታ ሰዎችን እገዛ የሚጠይቀው ሰፊ የህብረት ስራ ዘመቻው በብሄረሰቡ አጠራር ወበራ በመባል ይታወቃል። ይህም አጨዳ ከሆነ የአጨዳ ወበራ ፣ እርሻ ከሆነ የእርሻ ወበራ ፣ አረም ከሆነ የአረም ወበራ በሚል ስያሜ ስራው በህብረት የሚከናወን ነው። ለዚሁ የህብረት ስራ ሲወጡ ለአጨዳ ወበራ ጊዜ ማጭድ ፤ ለእርሻ ወበራ ጊዜ ያለው ጥንድ በሬውን የሌለው ያለውን አንድ በሬም ቢሆን ከነሞፈርና ቀንበሩ ይዞ በመምጣት የሚያግዘው ሲሆን ፣ በአረም ወበራ ወቅት ደግሞ የስራ ልብስ ብቻ ለብሶ በመገኘት ለሚከናወን የህብረት ስራ ነው። ሌላው “ልፍንት” የሚባለው የደቦ ስራ ሲሆን ለዚህ ስራ የሚፈለገው የሰው ጉልበት ብቻ ሲሆን እገዛው ዛሬ አንደኛው ለሌላኛው ከሰራለት ሌላኛው ደግሞ ብድሩን በሌላ ቀን የሚመልስበት አሰራር ነው። ሶስተኛው ደግሞ “መቀና”' የሚሉት ሲሆን እገዛውም አንዱ ገበሬ አንድ በሬ ብቻ ቢኖረው ከሌላኛው አንድ በሬ ካለው ገበሬ ጋር አቀናጅቶ ወይም አጣምሮ በመስራት የሚያከናውኑት ተግባር ነው።

በዚህ የደቦ ስራ ወንዶቹም ሆኑ ሴቶቹ የሚሳተፉበት ነው። የሴቶች ተሳትፎ ከማረሻ የተዘለለውን በመንቀል ፣ አራሹን ተከትሎ በማጎልጎልና ሳሩን ከአፈሩ በመለየት ከእርሻው ውጪ በመጣል ነው። ደቦ/ወበራ/ በማህበረሰቡ አባላት መካከል ካለው መጠቃቀም አንፃር ልዩ ልዩ መልኮችና አፈፃፀሞች ሊኖሩት ይችላሉ።ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ መገለጫዎች ደቦ እንደ ጉልበትና አገልግሎት ልውውጥ ስርዓት እና ደቦ እንደ ማህበራዊ የጉልበት ድጋፍ አሰጣጥ ስርዓት የሚኖረው ጠቀሜታዎች ናቸው።

ደቦ/ወበራ/ እንደ ጉልበት ልውውጥ ስርዓት በሚያገለግልበት ጊዜ ሰዎች ወረፋ ገብተው በቅደም ተከተል ለአንድ የቡድኑ አባል ጥቅም የሚሰሩበት ሁኔተታን ይፈጥራል፡፡ በዚህ ሁኔታም ውስጥ እጅግ በጣም አድካሚና አሰልቺ የሆነውን የግብርና ስራ በመተጋገዝና በመተባበር ለማከናወን ብዙ የሰው ሀይል በሚፈልጉ የስራ ተግባራት አጨዳ ፣ አረም ፣ ወዘተ የተወሰነ ቡድን በማቋቋም ወረፋ ገብተው ይሰራሉ፡፡ እያንዳንዱ የቡድኑ አባልም ለሌሎች አባላት የሰጠውን አገልግሎት በተመሳሳይ ሁኔታ ከእያንዳንዱ አባል መልሶ ስለሚጠይቅና ስለሚያገኘው ደቦ ማህበራዊ የጉልበትና የአገልግሎት ልውውጥ ስርዓት ተቋም ነው ለማለት ያስችላል፡፡ ዓላማቸው በጋራ መስራት ሆኖ የሴትና የወንድ ትብብሮች የሚመሰረቱበት ሁኔታ አለ፡፡ ወንዶች ብዛት ባላቸው ጥንድ በሬዎች መሬታቸውን ለማረስ ፣ ለመዝራት ፣ ቤት ለመስራት ፣ አጥር ለማጠር እና ሰብል ለማረም ደቦ በመጥራት እርስ በእርስ ይጠቃቀማሉ፡፡ ሴቶች ደግሞ ጥጥ ለመፍተል ፣ ቤት ሲሰራ ውሃ ለመቅዳት ፣ የሰርግ ድግስ ለመደገስ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ትብብሮችን በማቋቋም በጋራ ይሰራሉ፡፡[45]

ደቦ እንደ ማህበራዊ መረዳጃ ተቋም በሚያገለግልበት ወቅት በአባላቱ መካከል ከሚኖር እርስ በእርስ የጉልበትና የአገልግሎት ልውውጥ ይልቅ ለማህበረሰቡ አባላት ደህንነትና ጥቅም ሲባል ግለሰቦች በፈቃዳቸው በአጸፌታው ምላሽ ሳይጠብቁ የሚያከናውኑት ማህበራዊ ነፃ አገልግሎት ይሆናል፡፡ ግለሰቦች ከማህበረሰባቸው አባላት ጉልበት አገልግሎት የሚጠይቁባቸውና የሚያገኙባቸው ሁኔታዎች ብዙ ናቸው፡፡ ተዘውትረው ከሚተገበሩት ውስጥ አቅመ ደካሞች ፣ በእድሜ የገፉ አዛውንቶችና ባል የሌላቸው ሴቶች ቤታቸውን ለመጠገንና ለማደስ ፣ አጥር ለማሳጠር ፣ አረም ለማሳረም ፣ ሰብል ለማሰበሰብ ወይም እነዚህን ለመሳሰሉት የህብረት ስራን ለሚጠይቁ ተግባራት ወዳጅ ዘመድና ጎረቤት ማህበራዊ የነፃ አገልግሎቶች የሚሰጡባቸው ሁኔታዎች ይገኙበታል፡፡ ለዚህም ነው ወንፈል ወይም ደቦ ከምጣኔ ሃብት ጠቀሜታ ባሻገር ማህበራዊ ፋይዳ አለው የሚባለው፡፡ ወንፈል ወይም ደቦ ሰዎች እምነታቸው ፣ ቋንቋቸው፣ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ደረጃቸው ሳይገድባቸው በመረዳዳት የሚጠቀሙት ነባርና አገር በቀል የቡድን ወይም የህብረት ስራ ማህበር ነው፡፡

---

[45] አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቃመ. 13/10/2009 ዓ.ም ፣ አቶ ባየ አስምሮም ፣ ቃመ. 10/10/2009 ዓ.ም ፣ አቶ አስራት ፣ ቃመ. 07/10/2009 ዓ.ም ፡፡

### 5.4.2 የሰርግ መዋጮ

በዋግኽምራ ለሰርግ ድግስ ይደገሳል፡፡ ለዚህም የሚያወጣውን ወጪ ብቻውን አያወጣም፡ ፡ በባህሉ መሠረት ወጪውን የአካባቢው ህዝብ ፣ ዘመድ ፣ ጎረቤት ሁሉ የቻለውን ያህል በግልና በጋራ በማዋጣት ያግዛሉ፡፡ ይህም የሰርግ ድግስ መዋጮ በመባል ይታወቃል፡፡ ሴቶች ለሙሽራዋ/ው እናት ወንዶች ለሙሽራው/ዋ አባት በሰርግ ድግስ ወጪቸውን እንዲሸፍኑበት አዋጥተው የሚሰጡት ገንዘብ ነው፡፡ ይህ ትብብር ልጃቸውን የሚድሩ ሰዎች በሰርግ ወጪ እንዳይቸገሩና ካለ ስጋት ልጆቻቸውን ደግሰው እንዲድሩ የሚያስችል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ሁሉም ሰው ያለውን ከየቤቱ ሰርቶ ይዞ በመምጣት የሰርግ ዕድምተኞችን የማስተናገድ ባህልም አላቸው፡፡

### 5.4.3 እርጥባን

የዋግኽምራ ብሔረሰብ የሀዘን (በሞት) ጊዜ ከመረዳዳት ባለፈ በቁም የመረዳዳት የቆየ ባህል አላቸው፡፡ በማህበረሰቡ አንድ ሰው ችግር ሲደርስበት ለችግሩ መድረስ እንደ ትልቅ ጉዳያቸው የሚወስዱት እሴታቸው ነው፡፡ በዚህ ስርዓት የጾታና የዕድሜ ገደብ የለም፡፡ ባህላዊ ስርዓቱ የሚጋብዘው ሁሉ ይሳተፋል፡፡ “ከሞት ወዲያ ምን ያደርጋል መረዳዳት በቁም ነው እንጂ” የሚሉት አባላት አላቸው፡፡ በብሔረሰቡ በቁም የመረዳዳት ባህሉ የሚከናወነው በህመም ጊዜ ፣ የእርሻ በሬው ለሞተበት ሰው የእርሻ ስራው እንዳይስተጓጎል በሚል ፣ አነስተኛ ኑሮ ያላቸውና የተቸገሩ ሰዎች ካሉ ፣ ቤት ሲቃጠል ፣ ንብረት ሲዘረፍ ፣ ወዘተ. ሲሆን ሂደቱም ወዲያውኑ ችግር የደረሰበትን አካል “ችግሩ ችግራችን ነው” በማለት የማስተባበር ስራ ይሰራል፡፡ የማስተባበር ስራውን እርጥባን/ምርቃን/[46] ይሉታል፡፡ የሚያስተባብረው የቅርብ ወዳጅ አልያም ችግር የደረሰበት አካል/ግለሰብ/ ሊሆን ይችላል፡፡ ችግሩ የደረሰበት ግለሰብ “እርጥባን አድርጎል” ብሎ ጥሪ ያስተላልፋል፡፡ ለእርጥባን ማሰባሰቢያም ከለላ የምትሆን “ዳስ” ይጥላል፡፡ የተሰወሰነ መብልና መጠጥም በተለይም ንፍሮና ጠላ/ኮረፌ ያዘጋጃሉ፡፡ ሂደቱን በተመለከተም በህመም ላይ ያለን ሰው ጊዜ ሳይወስዱ ወደ ህክምና ሂዶ የሚታከምበት በማመቻቸት ፣ በሬ የሞተበትን በሬ ገዝቶ እንዲያርስ ፣ ቤቱ የተቃጠለበትን ሙሉ

---

[46] እርጥባን ፣ የገንዘብ ፣ ስጦታ ማለት ሲሆን ፤ የስጦታው ዓይነት እንደደረሰው የችግር ዓይነት የቁሳቁስ ፣ የጉልበት ስራ ፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡

በሙሉ ከወደመ ጊዜ ሳይሰጡ እርዳታውን የማሰባሰብ ስርዓቱ ወዲያውኑ ይከናወናል፡፡ የመጀመሪያው እርዳታ መጠለያውን በጋራ በመስራት ይሆናል፡፡ ይኼውም እንጨት ያለው እንጨቱን ፣ የሳር ቤትም ከሆነ ሳር በማምጣት ይሰራለታል፡፡ ወዲያውም ጊዜ ሳይሰጠው የ "እርጥባን" ስነ ስርዓቱ ይከናወናል[47]፡፡

ይህ የመረዳጃ መርሃ ግብር ለዋግኽምራ ብሄረሰብ አባላት ብቻ ሳይሆን ከሌላ ቦታ መጥተው እዚያ በቋሚነት ለሚኖሩና በእንግድነትም መጥተው ችግር ለደረሰባቸው ሁሉ የሚደረግ ነው፡፡ እርጥባን አንዳንድ ጊዜ ተቸገርኩ ላለ ሰው ብቻ ሳይሆን በአጋጣሚ በተለያየ ምክንያት አካባቢውን ለሚለቅና ለማግባት ለተዘጋጀ ሰውም መሸኛና ድጎማ ለማድረግ በማሰብ ግለሰቡ ይዘጋጅልኝ ባይልም በቅርብ ሰዎቹና ጎረቤቶቹ አነሳሽነት ሊዘጋጅ ይችላል፡፡[48]

እርጥባን በዋግኽምራ ባህል በልዩ ልዩ አውዶች የሚሰራ የማህበራዊ ዋስትና ተቋም ነው፡፡ የባህሉን ማህበራዊ ፋይዳዎችና አገልግሎቶች እንደ ማህበራዊ ዋስትና ተቋምና እንደ ማህበራዊ ማቋቋሚያ አገልግሎት የሚያበረክታቸው ፋይዳዎች አሉት፡፡

አሉላና ገብሬ ሀገራዊ ዕውቀትና የልማት ትስስርን ሲያስረዱ እንደሚሉት "የልማት ታዳሚ ህዝብ ባህላዊ ዕውቀት ስላለው ይህንን የዕውቀት ሃብት ልክ እንደ ተፈጥሮ ሃብትና ገንዘብ ለስኬት አስተዋፅኦ ያደርጋል… ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴም ሲገቡ… እንደ አካባቢው ሁኔታ የሀገራዊ ዕውቀቶችን አስፈላጊነት ተገንዝቦና አስገንዝቦ በስፋት መጠቀም የሀገራዊ ዕውቀቶች ጥራት… ሙያውንና ክህሎቱን አሻሽሎ ብክነትን መቀነስ ይቻላል፡፡" (አሉላና ገብሬ ፣ 2004 ፤ 82)፡፡

እነዚህ የጋራ ትብብሮችም በወጉ ቢያዙ ብሔረሰቡ የቁጠባን ባህል እንዲለምድና እንዲያዳብር የሚኖራቸው ሚና ቀላል አይደለም፡፡ ማህበረሰቡ በጋራ ማሳያዎች በማልማት በቀለብ ብቻ ከማምረት ለገበያ ብሎ ወደ ማምረት ፣ ሰፊ ጊዜውንም በ "በሃይማኖታዊ በዓላት" ሰበብ ከማባከን በልማት ስራዎች ላይ በመሰማራት እንዲያሳልፍ

---

[47] አቶ ባዬ አስምሮም ፣ ቃመ. 07/10/2009 ዓ.ም ፤ አቶ አስራት ታደሰ ፣ ቃመ. 10/10/2009 ዓ.ም ፤ መ/ት ወርቃፌራሁ ቸኮል ፣ 12/10/2009 ዓ.ም፡፡

[48] ዋግኽምራ ዞን ባቱ ፣ ሻደይ ወንዝ አይፈሬ ፤ 1ኛ ዓመት ፣ ቁ.1 ፤ 2003 ዓ.ም፡፡

፤ የጋራ ትብብሮቹን መነሻ አድርጎ የቁጠባን ልማድ እንዲያዳብር ለማስተማርና ወደ ተግባርም ለማሻጋገር ጠቃሚ ባህላዊ መድረኮች ናቸው፡፡ እነዚህን ተግባራት ማህበረሰቡ በቀላሉ የሚቀበለው ለመተግበርም የማያቅማማበት ይሆንለታል፡፡

በርካታ የማህበረሰቡ አባላት በአንድ ላይ ተሰብስበው የሚቀመጡበት "ሃይማኖታዊ ቅፅር ግቢ ቤተክርስቲያን" ማህበረሰቡን ስለ አካባቢው ልማት ጉዳይ ለማወያየት ፣ ለማስገንዘብና ለማነሳሳት ከስብሰባ አዳራሽ ይልቅ በጣም ምቹና ተመራጭ ስፍራ ነው፡፡ በዚህ ቅፅር ግቢ "የሃይማኖት አባቶች" ከፍ አድርጎ ምዕመናኑን/ማህበረሰቡን ከስራቸው እያዩ የሚገልጹበት መድረክ የለም፡፡ ሁሉም በቅፅር ግቢው ውስጥ እኩል ተቀምጠው ይወያያሉ ፣ ሃሳብ ይለዋወጣሉ ፣ ያልገባቸውን ይጠይቃሉ ፣ ውሳኔያቸውን በጋራ ያሳልፋሉ፡፡ እዚያው የተገኘውን እየበሉ[49] እየጠጡ ጊዜያቸውን በሚያሳልፉበት በዚህ ቦታ ተገኝቶ ስለ ነገ የአካባቢያቸው ልማት እዚያው አወያይቶ ወደ ተግባር ለማስገባትና ለውጥ ለማምጣት የቀለለ መንገድ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በዋግኽምራ ብሔረሰብ በ "በቤተክርስቲያን ቅፅር ግቢ" በሃይማኖታዊ በዓላት ቀናት በጋራ መምከር ፣ መወያየት ፣ የተጣላን ማስታረቅና ውሳኔ ማስተላለፍ ልማዱና ባህላዊ መገለጫው ነው፡፡ የልማቱ አስፈፃሚዎች ይህንን ልማዳዊ ተግባር የልማት መሳሪያ ለማድግ የምር ካሰቡበትና ግምት ሰጥተውት በብልሃት ከያዙት እጅግ ቀላሉ መንገድ ይሆንላቸዋል፡፡

የተለያዩ ጉዳዮች ሲገጥማቸው የሚረዳዱባቸው የቤተ ዘመድ ፣ የጓደኛሞችና የጎረቤታሞች የጋራ ትብብሮች የቁጠባ ልምድን ሊያዳብሩ የሚያስችሏቸው ጥሩ መሰረቶች ናቸው፡፡

ብድርን የጦር ያህል የሚፈራው የዋግኽምራ ማህበረሰብ የገጠር ብድርና ቁጠባ ተቋማትን ለማስፋፋት በሚል ለመተግበር ከመድከም ይልቅ እነዚህን የጋራ ትብብሮች እንዲጎለብቱ በማድረግ የገንዘብ አቅም የሚፈጥሩበትን መንገድ መፈለጉ የበለጠ ውጤታማ ይሆናል፡፡ ለለዚያ ግን "ተበደርና የግብርና ግብዓቶችን ግዛ ፣ ትንሽ ትንሽ እየቆጠብክ ብድርህን ክፈል" የሚለው ምን ያህል ተግዳሮት እንደገጠመው የታወቀ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ከ መንግስት ተበድሮ መክፈልን የለመደው አሰራር አይደለም ፤ በዚህም የተነሳ በግድ ማዳበሪያ በብድር እንዲገዙ በማድረግ በአከፋፈል ሂደቱ በተፈጠረው

---

[49] በዕለቱ በዋለው የቅዱሳን ፣ የመላዕክት ዝክር ፣ የሙት አመት ፣ ተስካር ማህበር ፣ ወዘተ ምክንያት የሚበሉ ምግቦችና መጠጦች ስለሚኖሩ እየተወያዩ ሊበሉ እና ሊጠጡ ይችላሉ፡፡

ያለመክፈል ሁኔታ በተቋሙና በማኅበረሰቡ መካከል ከፍተኛ የሆነ አለመግባባት በመፈጠሩ ጥላታችን ከማትረፋ የዘለለ ልማታዊ አበርክቶው ግቡን እንዲመታ ሊያደርገው አልቻለም፡፡

## 5.5. በመንደር ተሰባስበው መኖራቸው ያበረከተው በጎ ገፅታ

የዋግኽምራ አስተዳደር ዞን ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ በዞን ደረጃ ተዋቅሮ የዋግኽምራ ብሔረሰብ ዞን ተብሎ ከክልሉ ከሚገኙ ሶስት የብሔረሰብ ዞኖች አንዱ ነው (አበባው ፣ 2001 ፡ 3)፡፡ በማዕከላዊ ስታስቲክ ኤጀንሲ (2003 ዓ.ም ፣ 24) መረጃ መሰረት የዋግኽምራ አስተዳደር ዞን ስፋት 9,039.04 ካሬ ኪሎ ሜትር ነው፡፡ ዞኑ እስከ 1998 ዓ.ም ድረስ በሶስት ወረዳች ማለትም ድሃና ወረዳ ፣ ሰቆጣ ወረዳና ዝቋላ ወረዳ የተከፈለ ነበር፡፡ ከዚያን ጊዜ ወዲህ ግን በስድስት ወረዳዎች እና በአንድ የከተማ አስተዳደር ተከፍሏል፡፡ በዞኑ ውስጥ 122 የገጠርና ሶስት (3) የከተማ በድምሩ 125 ቀበሌዎች ይገኙበታል፡፡ እ.ኤ.አ 2007 የህዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሰረት የብሔረሰቡ የህዝብ ብዛት 426,213 ነው፡፡ የክልሉ መንግስትና የብሔረሰቡ አስተዳደር ዞን ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በሶስት ወረዳ ብቻ ታጭቀውና ተራርቀው የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎችን መረሰተ ልማቶች ለሁሉም ለማዳረስ እና የአርሶ አደሩን አኗኗርና የምግብ ዋስትናውን ለማረጋገጥ ከላይ በተጠቀሰው ወረዳዎቹን ከሶስት ወደ ሰባት በማሳደግና በየወረዳው ውስጥ እንደየቅርበታቸው በማጤን በ122 የገጠርና 3 የከተማ ቀበሌዎች አደራጅቶ ስራውን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም የተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃ ዞኑ 426,213 አባወራዎችንና እማዎራዎችን ለማሳተፍ ታቅዶ ነፃ የልማት ተሳትፎ ያደረገው የሰው ኃይል ብዛት 168,632 ነበር፡፡ የዞኑ ህዝብ ብዛት ከላይ የተጠቀሰው ቢሆንም ቀሪው ህፃናትና ዕድሜቸው የገፉ ስለሆኑ አልተሳተፈም፡፡

የዚሁ 2003 ዓ.ም የአፈፃፀም ግምገማ ሪፓርት እንደሚያስረዳው (ዋግ ኽምራ ግብርና ልማት፣ 2003/ሻደይ ፣ 2003 ፣ 22) በመንደር ተሰባስበው መኖር ለልማት ተሳተትፎ ከፋተኛ ጥቅም ያለው መሆኑን የግብርና ባለሙያዎቹ ይናገራሉ፡፡ ይኼውም ትምህርት ቤቶችና ጤና ጣቢያዎችም በየቀበሎዎቹ ማዕከላዊ ቦታ በቅርበት ስለሚገኙ ትምህርት ቤት ሂደው ሁሉም ይማራሉ፡፡ ሴቶቹም ስራ ሲጨርሱ ሄደው ይማራሉ፡፡ መብራት

ውሃም በቅርብ ስለሚያገኙ ጥሩ ነው (ቡ.ተ.ኮ.ው 09/10/2009 ዓ.ም ሰሬ ፣ ቡ.ተ.ኮ.ው 12/10/2009 ዓ.ም ጋዝይብላ)፡፡

ዋግኽምራዎች በባህላቸው በጋራ መኖርን ስለሚወዱ በቀበሌ መደራጀታቸውን አይጠሉትም ፤ ድሮም በጋራ ተረዳድቶና ተጋግዞ መኖሩን የለመዱት ነው፡፡ በብሂላቸውም "ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤ" የሚል የቆዬ መርህ አላቸው፡፡ ይኼን ምቹ ሁኔታ መሰረት አድርጎ የአርሶ አደሩን (የብሔረሰቡን) ሕይወት ለመለወጥ የታለመውን ዕቅድ ማሳካት የሚቻልበት ዘዴ መከወኑ ግን የብሔረሰቡ አስተዳደር ዞን የቤት ስራ ይሆናል፡፡ ማህበረሰቡ በቅሬታ የሚያነሷቸውን ጉዳዬች ፈጥኖ በማስወገድ በጋራ የማምረትና የመጠቀም ዕድሉን ማስፋፋት ይችላል፡፡ አካባቢውን ለማልማት ጥሩ መሰረትም ሊሆን እንደሚችል አጢኖ መስራት ይኖርበታል፡፡

## 5.6. ገንቢ የሆኑ የጤና ጉዳዮች

ስለ ልማት ጉዳዮች ሲነሳ በበሽታ ያልተጠቃና ጤናው የተጠበቀ ማህበረሰብ መኖር ዋነኛ አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑ እሙን ነው፡፡ መንግስታት ለዜጎቻቸው ጤና ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩት ከዚህ መነሻ ነው፡፡ በሀገራችንም መንግስት የህዝቡን ጤና ለመጠበቅ ከነደፋቸው ፖሊሲዎች ውስጥ የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ እንደሆነ ቀደም ሲል ተጠቅሷል፡፡ በጤና ኤክስቴንሽኑ ከተካተቱት ፓኬጆች ተፈፃሚነት አኳያ በዋግኽምራ ብሔርሰብ ያሉትን አዎንታዊ ገፅታዎች ቀጥለን እንልከት፡-

### 5.6.1. የግልና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ

በዋግኽምራ ባህል የግልና የአካባቢ ንፅህናን መጠበቅ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ተዘውትሮ የሚተገበር ባህል ነው፡፡ በዋግኽምራዎች የመኖሪያ ሠፈሮች ቆሻሻ ማየት የተለመደ አይደለም ፤ አካባቢያቸው ንፁህ ነው፡፡ ለመፀዳጃ የሚሆን ቦታ በቤታቸው ታዛ (ጓሮ) ጉድጓድ ቆፍረው አይነምድራቸውን በዚሁ ቦታ የመጠቀም ልምድ አላቸው፡፡ የቤተሰቡ አባላት ሆኑ ሌሎች ወደነሱ ጋ የሚመጣ ሰው የሚጠቀመው ተቆፍሮ በተዘጋጀው ቦታ ነው፡፡ በብሔረሱ ልማድ መሰረት የሆድ ህመም ካልገጠማቸው (ሆርዝማ) በስተቀር ዓይነ-ምድር የሚወጡት በቀን ሁለት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ይኼውም ጧት እና ማታ፡፡ ከዚህ ውጭ ያሉ ጊዜያት የሥራ ጊዜያት ስለሆኑ ትኩረታቸው ሥራቸው ላይ ስለሚሆን

በማንኛውም ሰዓት ወደ ሽንት ቤት የመሄድ ልማድ የላቸውም፡፡ ምንም እንኳ በምሳሌያዊ ንግግራቸው "የጧትን ዓይነ-ምድር እንደመጣ ፣ የማታን ዓይነ-ምድር አምጦ" የሚል አባባል ቢኖራቸውም ልዩ ችግር ካልገጠማቸው በቀር የተለመደው የዓይነ-ምድር አወጋገድ በቀን ሁለት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ይህ የመጸዳዳት ልመድ በማህበረሰቡ ዘንድ የተለመደ እና ተዘውትሮ የሚተገበር ነው፡፡ በዚህም ልማዳዊ ድርጊት በማንኛውም ሰዓት በየትኛውም ቦታ ዓይነ-ምድርን መውጣት ለአካባቢውም ሆነ ለግል ንጽህና አጠባበቅ ዓይነተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ከጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች አንዱ የሆነው የግል ንፅህ አጠባበቅ ፓኬጅ ዓላማ በግል ንፅህና አጠባበቅ ጉድለት አማካይነት የሚተላለፉና የሚከሰቱ በሽታዎችን በመከላከል ጤናማና አምራች ህብረተሰብ ማፍራት (የኢፌዴሪ ጤ.ጥ.ሚ ፣ 1998 ፡ 1) የሚል ነው፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎቹ እንደሚያስረዱት የግል ንፅህና አጠባበቅን አስመልክቶ በብሔረሰቡ ቀድሞውኑም የሚተገበር ባህል በመሆኑ ይህን ፓኬጅ ለመተግበር ምንም ችግር አልገጠማቸውም (መ/ት ወርቃፈራሁ ፣ ቃመ. 10/09/2009 ዓ.ም ፣ ወ/ሮ ኤደን ፣ ቃመ. 20/10/2010 ዓ.ም ፣ ወ/ሮ እመቤት ፣ ቃመ. 10/09/2010 ዓ.ም)፡፡ ከዚህ በመነሳት ለኤክስቴንሽን ፓኬጅ ያለ ችግር መተግበር ባህሉ ልማዱ ያደረገው አስተሰዋፅኦ መረዳት አያስቸግርም፡ ፡ "ሀገራዊ ዕውቀት በግርብርና ፣ በጤና አጠባበቅ ፣ በምግብ ዝግጅት ፣ በትምህርት ፣ በተፈጥሮ ሃብት አያያዝና በሌሎች በርካታ ጉዳዮች ላይ ለመወሰን መሰረት ነው" (አሉላና ገብሬ ፣ 2004 ፡ 78)፡፡ የዋግኽምራ ብሔረሰብ ፓኬጁ በዓላማነት ይዞ የተነሳውን ከግል ንፅህና ጉድለት የሚመጡ ብሽታዎችን መከላከል ለመተባበር ያልተቸገረው ንፅህናን ባህሉ አድርጎ ሲፈፅመው የኖረ ሀገረሰባዊ ዕውቀት ስለሆነና ይህንን እሴት እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመውሰድና በማበረታታት ሌሎቹንም ፓኬጆች እንዲተገብር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር ያስችላል፡፡

## 5.6.2. ለጤና ተስማሚ የሆነ መኖሪያ ቤት አሠራርና አያያዝ

ለሰዎች በመሠረታዊ ፍላጎትነት ከሚነሱ ጉዳዮች አንዱ መጠለያ ወይም መኖሪያ ቤት ነው፡፡ ቤት ለመኖሪያ ፣ ለመዋያና ለማደሪያ የሚጣቅምና ሰፊ ጊዜያችንን የምናሳልፍበት በመሆኑ ንፅህናው የተሟላና ምቹ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ከተጓደለ ግን ለቅዝቃዜ ፣ ለሙቀት ፣ ለተለያዩ አደጋዎችና ተላላፊ በሽታዎች እንድንጋለጥ ከማድረጉም በላይ ለአካላዊና ለሥነ-ልቦናዊ ቀውሶች ሊያጋልጠን ይችላል፡፡

መኖሪያ ቤት "ለሰዎች አካላዊ ፣ ምጣኔ ሃብታዊ ፣ ማህበራዊና ስነ-አዕምሮአዊ ጤንነትና ደህንነትን ለመጠበቅ አስተዋፆ ከሚያደርጉ መሠረታዊ ፍላጎቶች አንዱ ነው" ብሎ የሚነሳው ለጤና ተስማሚ መኖሪያ ቤት አሠራርና አያያዝ ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ዓላማው "ህብረተሰቡ ለጤና ተስማሚ የመኖሪያ ቤት እንዲኖረው በማድረግ እራሱንና ቤተሰቡን ከተላላፊ በሽታዎችና አደጋዎች እንዲከላከል ማድረግ" (የኢፌዴሪ ጤ.ጥ.ሚ ፣ 1998 ፣ 3) የሚል ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ኽምራዎች የግል ንፅህናቸውን ብቻ ሳይሆን ቤታቸውንና አካባቢያቸውን በንፅህና የመያዝ ባህል አላቸው፡፡ ቤታቸው በአብዛኛው በተለይም በገጠሩ አካባቢ ከእንጨት እና ከሰንበሌጥ የሚሠራ ጎጆና ደርብ ሲሆን ወደ ውስጥ ሲዘልቁ ንፅህናው ድንቅ ነው፡፡ የትኛውም ቤት ከውስጥ ጣሪያና ግድግዳው አቅም በፈቀደ መጠን በጠንበለል ማገር መሣይ ቀጫጭን እንጨቶች ተወሳስቦ የተሸፈነ ሲሆን ግርግዳው ደግሞ በቀይ ዐፈር የተለቀለቀ ቂንጠኛ ነው፡፡ ወለሉ እንዲሁ በዚሁ ዐፈር ተለውሶ በደንብ ታሽቶ በቀጭኑ ልክ እንደ ሲሚንቶ ወለል ቤት ሲሆን በየጊዜው ውሃ እየተርከፈከፈበት ይፀዳል፡፡ በውስጡም የሚገኙ የቤት ዕቃዎች በንፅህና ተይዘው በወጉ በሣጠራና ጠረጼዛ መሣይ አግዳሚ እንጨት ላይ ይቀመጣሉ፡፡ በዋግኽምራዎች ዘንድ ቤትንና ዕቃን በንፅህና መያዝ የተለመደ ባህል ነው፡፡

የኽምራ ሴቶች ሙያቸው የሚለካው የቤቷን ዕቃ በንፅህና መያዟና የቤቷን ዙሪያ ገባውን አሳምራ ፣ ጠርጋና አፅድታ መያዟ ነው፡፡ ይህም አድራጎቷ "የሴት በላይ" የሚል ስም ያሰጣታል፡፡ በመሆኑም የዋግኽምራ ሴቶች ቤታቸውን በንፅህና አጥቦና አጥኖ መያዝ ትልቅ ቦታ የሚሰጡት ነው (ወርቃፈላሁ ፣ ቃመ.12/10/2009 ዓ.ም)፡፡

የዋግኽምራ ሴቶች ሌላው ቀርቶ ለእንግዳ የሚጠጣ ውሃም ሆነ ጠላ ለማቅረብ ሲዘጋጁ በመጀመሪያ እጃቸውን በሚገባ ታጥበውና ማቅረቢያ ዕቃዎቻቸውንም በጥሩ ሁኔታ አጥበው ነው፡፡ ይህን የማታደርግ ሴት ረኽጥ ናት፡፡ ኽምራዎች "የሴት ልጅ ውበቷ ጽዳቷ" የሚል ብሂል አላቸው፡፡ ኽምራዎች የአካባቢ ንፅህናም ሆነ የግል ንፅህናቸውን በመጠበቅ ረገድ ትልቅ ዋጋ የሚሰጡት ጉዳይ ነው (አቶ ደረበው ታረቀኝ ፣ ቃመ. 19/10/2009 ዓ.ም)፡፡ በማለዳ ተነስታ የቤቷን ዙሪያ አፅድታ ፣ ቤቷን ጠራርጋ ንፁህ ካደረገች በኋላ ለቤተሰቡም ምግብ የማታዘጋጅ እሳት ፍለጋ ወደ ጎረቤት የእሳት መጫሪያ "ገል" አንቀርፍፋ የምትወጣ ሴት በባህሉ በጣም ሰነፍ የሚል ስድብ

ከመስጠቷም በላይ የመጨረሻውን ሙያቢስ/ርሽጥ/ የሚል ስም ይወጣላታል፡፡ በሴቶችም ዘንድ "ይህች ሴት አሰዳቢ ፣ አሳዳጊ የበደላት" በማለት ያንጓጥጧታል፡፡ ባሏንም ቢሆን ታሳፍራለች፡፡ "እሷ ሰንፋ ራቷን ገንፎ አድርጋ ቢያጎርሳት ተኮሳት" ብለውም በምሳሌ ያሽሙሯታል፡፡ ባሏንም ተባባሪ መሆኑን "ግም ለግም አብረህ አዝግም" ዓይነት በነገር ወጋ ያደርጓቸዋል (መ/ት ወርቃፈራሁ ፣ ቁ.መ.አ. 10/09/2009 ዓ.ም) በማለት ይገልፃሉ፡፡ ሽምራዎች ከሴት ልጅ ባለሙያነትና ትጋትን የሚጠበቁ ናቸው፡፡ የባለሙያነት ማሳያው/መስፈርቱ ደግሞ ቤትን በንፅህና መያዝ ነው፡፡ ቤት ሳይፀዳና ሳይስተካከል ወደ ውጭ መውጣት ነውር ነው፡፡ ከዚህ በኋላ እሳት አያይዞ ምግብ ይበስላል፡፡ በምድጃዋ እሳት አዳፍና ያላሳደረች ገልቱ ወይም ረሽጥ ግን ቤቷን ሳታፀዳዳ እሳት ፍለጋ ትወጣለች፡፡ ይህ የሚያመልክተን ሽምራዎች ለቤት ንፅህና ያላቸውን ቦታ ነው፡፡ ሴቶች ቤታቸውን ብቻ ሳይሆን ባሎቻቸውን ከሥራ መልስ ወይም ጧት ቀደም ብለው አረፍ የሚሉበትን የቤቱን ታዛ ንፁህ አድርገው ያፀዱትና ያስተካክሉታል፡፡ የዋግሽምራ አካባቢ በአብዛኛው ማለት ይችላል ሞቃታማ በመሆኑ ከውጭም ዛፍ ስር ምግብ ሊያበስሉ ፣ ወጥ ሲሰሩ፣ ቡና ሊያፈሉ ይችላሉ፡፡

ከቤታቸው ውጭ ያለው ሥፍራና አካባቢውም እንዲሁ በንፅህና የተያዘ ነው፡፡ በአብዛኛው ቡና የሚጠጡት ውጭ በመሆኑ ሁሌም ቀየው ሳይቀር በንጽህና ይያዛል፡፡ ይህም በመሆኑም የግልና የአካባቢን ንፅህናን አስመልክተው የተነደፉትን የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች በቀላሉ ለመተግበር ችለዋል፡፡

ይኼ ብሔረሰቡ እራሱንና ቤተሰቡን ከበሽታዎችና ከልዩ ልዩ አደጋዎች እንዲከላከሉ ያስቻለ ጠቃሚ ባህላዊ እሴት/ልማድ/ እና ሀገርሰባዊ ዕውቀት ነው፡፡ የብሔረሰቡን ባህል በጥቅሉ ጎታችና ኋላቀር ነው ብሎ በመፈረጅና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የበላይነት የሚያምኑት የዘመናዊ ንድፈሃሳብ አራማጆች እንደሚሉት ባህልና ሀገረ ሰባዊ ዕውቀቶች የልማት እንቅፋቶች ናቸው ብለው ሁሉን ለማዘመን ከመነሳት ይልቅ እነዚህንና ሌሎችን ባህላዊ እሴቶች እንደምቹ ሁኔታ በመቁጠርና በማጎልበት ጤንነቱ የተጠበቀ አምራች ዜጋ ለማፍራት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## 6. የአካባቢውን ልማት የሚያስተጓጉሉ አሉታዊ ባህላዊ ጉዳዮች

በቀደመው ምዕራፍ መንግስት የሀገሪቱን ልማት ለማፋጠን በሀገር አቀፍ ደረጃ አቅዶ በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተገበራቸው ካሉት የልማት ፖሊሲዎች ውስጥ የግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምና የማህበረሰብ ጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ለመተግበር እና የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን በዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህል ያሉትን ምቹ ሁኔታዎች ተመልክተናል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ እነዚህ የልማት ፖኬጆችን ለመተግበር የሚገዳደሩ አሉታዊ ባህላዊ ጉዳዮችን ቀጥለን በተናጠል እንመለከታለን፡፡

### 6.1. የግብርና ልማት እና የዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህላዊ ተግዳሮቶች

ኢትዮጵያ የምትከተለው ግብርና መር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ፖሊሲ መሠረት የግብርና ልማቱን ለማፋጠን የኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተቀርፆ በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ እንዲሆን እየተሰራ ይገኛል፡፡ አርሶ አደሩ ቀድሞ በልማድ ከሚያመርታቸው ሰብሎች ይልቅ የኢኮኖሚ/ምጣኔ ሀብት/ጠቀሜታ ያላቸውን ሰብሎች አምርቶ ለገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ እንዲሆን ማዳበሪያና ምርጥ ዘርን ጨምሮ ልዩ ልዩ ግብዓቶችን እንዲጠቀምና ምርትና ምርታማነቱን እንዲያሳድግ ባለሙያዎችን በማሰማራት በግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ትምህርት እና እገዛ ይሰጠዋል፡፡

#### 6.1.1. ምርትና ምርታማነትን አለማሳደግ

ከላይ የተጠቀሱት የግብርና ልማት ፕሮግራሞችን አፈፃፀም ስንመለከት ውጤታማነቱ እስከዚህም ሆኖ ይታያል፡፡ የዋግኽምራ አርሶ አደር የእርሻ ስራን የሚያከናውነው ለዕለት ጉርሱ የምትበቃውን ብቻ ባለችው አነስተኛ ማሳ ነው፡፡ ከዚያች አነስተኛ የበሬ ግንባር የምታክል ማሳው የሚያገኘው ምርት አናሳ ስለሚሆን ለዓመት ልብሱና ለሌሎች ወጪዎች ለመሸፈን ያገኘውን የጉልበት ስራ ይሰራል፡፡ የገጠሩ ገበሬ ወደ ከተማ/ሰቆጣ/ በመምጣት ይሸቅላል፡፡ በዚህም በእርሻ ስራ ሙሉ ጊዜውንና ጉልበቱን አይጠቀምም፡፡ የእርሻ ማሳው አነስተኛ ቢሆንም ሌላ በመሬት ላይ ሊለሙ የሚችሉ የተራራ ላይ ተክሎችን በአማራጭነት ሊጠቀም አይችልም፡፡ ይህን ተገንዝቦ ተራራም ማሳ ነው ብሎ

አዕምሮውንና ጉልበቱን በስራ ላይ ሊያውለው አልቻለም። በአንፃሩ ግን ደግሞ መሬት ጠበበኝ እያለ ሲያማርር ይሰማል። ስለዚህ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸውን የተራራ ላይ ዛፎች ወይም ሌሎች ሰብሎችን ለገበያ ማምረት ፣ ግብአቶችን ተጠቅሞ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ፣ ያለችውንም አነስተኛ ማሳ አለስልሶ ማረስ የእሱን ትኩረት የሚስቡ ጉዳቶች አይደሉም። የዋግኽምራ አርሶ አደር ሊለማ የሚችል 668,241 ሄክታር መሬት ቢኖርም የሰፈራ ፕሮግራም ተበጅቶለት ከእነሱ ያነሰ መሬ ወዳላቸው አካባቢዎች እንደሚሄዱ የግብርና ባለሙያ የሆነው ገለሹ በንኑ[50] ገልፀዋል። ይህንንም አስመልክተው ሰፋ ያለ ማብራሪያ የዝቋላ ወረዳ የግብርና ባለሙያ የሆኑት አቶ በለጠ ሽፈራው የተባሉ መረጃ ሰጪ የሚሉትን እንመልከት።

> ልማትን በሚመለከት አካባቢው በእርሻ ነው የሚተዳደረው ግን አልፎ አልፎ በንግድም ይሳተፋል ፤ እርሻው ግን ጠባብ ስለሆነና ኮትቻ/ደረቅ/ ስለሆነ የረባ ምርት አያስገኝም። ፍየል ፣ ንብና የመሳሰሉትንም እያረባ ይሸጣል። ኑሮው ሲከብደው ምርቱ አልገኝ ሲልና ሲቸገር ወደ ሌሎች አካባቢዎች በራሱ ይሄዳል ፤ በሰፈራም በመንግስት ይወስዳል። አሁን አሁን የመንግስት ፓሊሲዎች አሉ ፤ ኤክስቴንሽን ፕሮግራሞች አሉ ፤ የእንስሳት ፓኬጅ ፤ የሰብል ልማት ፓኬጅ ፣ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸው ሰብሎች ፓኬጅ አለ ፣ ይህ ሁሉ ይሰጣል። ነገር ግን አብዛኛው አካባቢ በነዚህ ፓኬጆች የመጠቀም ባህል ደካማ ነው። አካባቢው ድርቅ የሚያጠቃው ለብዙ ዘመናት የታረሰ መሬት ነው። ገበሬው ግን ማዳበሪያ ከመጠቀም ተገደው ካልሆነ በቀር አይፈልጉም። ለየትኛው መሬት ነው ማዳበሪያ ተበድሬ ምርትን እንዲጨምር የምባለው በማለት ባለሙያዎቹን አይቀበሉም ፤ ተግባራዊ ለማድረግም ፈቃደኞች አይደሉም። መሬቱን ማነሱን በመመልከት እንደ ማዳበሪያ ያለውን ግብዓት ተጠቅመው በትንሽ ማሳም ብዙ ማምረት እንደሚቻል አይቀበሉም (አቶ በለጠ ሽፈራው ፣ ቃመ. 20/08/2010 ዓ.ም)።

ከላይ እንደተመለከትነው ግብርናና ገጠር ልማትን መሰረት በአደረገው የሀገሪቱ ዋነኛ ፖሊሲ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተያዘው እቅድ በዋግኽምራ ማህበረሰብ

---

[50] አቶ ገለሹ በንኑ የዋግኽምራ ብሔረሰብ ዞን የግብርና ባለሙያ ሲሆኑ ቃለ መጠይቅ ሳደርግላቸው የሰጡኝ ሀሳብ ነው። የግብርና የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ቢነግሯቸውም /ቢያስተምሯቸውም ተራራ እንዴት ይታረሳል ፣ ለከብቶች ግጦሽ ሳር እንዲያድግበት ይደረጋል እንጂ እያሉ መሬት አነሰን እያሉ ይማረራሉ ሲሉ ፣ ከልማዳዊ አስተሳሰብ ሊለውጧቸው እንዳልቻለ ገልፀውልኛል።

በመሬት ጥበት ምክንያት የዕለት ጉርስ ብቻ በዚያችው ጠባብ መሬት ከማምረት ባህል /ልምድ/ ትልቅ ፈተና ገጥሞታል፡፡ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በተለይም ደግሞ በ 1994 ዓ.ም ፖሊሲ ተቀርፆለት በመላ ሀገሪቱ እየተተገበረ በሁለት አሃዝ የሚቆጠር የምጣኔ ሃብት እድገት እያስገኘ ነው የሚባለው የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ በዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ምንም የተጨበጠ ነገር የለም፡፡ ገበሬው ለስራ ወደኋላ የማይል ታታሪ ቢሆንም ብሔረሰቡ "ማሳው ጠባብ ነው፣ በሚል ሰበብ አዲስ የአሰራር ዘይቤንና ግብዓትን ከባህሉ ልማዳዊ አስተሳሰብና አሰራር ጋር አያይዞ አያስፈልገኝም" በማለት እየተቃራኑት ነው፡፡

ሀሳቡን ለማጠናከር አቶ ገለሹ በንኑ ቀጥሎ የተናገሩትን እንመልከት፡፡

> ይሄን ቴክኖሎጂ ማስፋፋትና ማስረፅ ከተጀመረ ቆይቷል፡፡ ግን በብሔረሰቡ ላይ ያመጣው ለውጥ ይህን ያህል አይደለም፡፡ እኛ የራሳችንን አንለቅም የቆየ ልማዳችን ነው፡፡ በጠባብ መሬት/ማሳ ላይ ሌላ "ባዕድ ነገር"/ማዳበሪያውን ነው/ተጨምሮበት ቀርቶ ድሮውን ምርት ሰጪነቱ አናሳ ነው፡፡ በዚያው ላይ ደግሞ ጠባብ መሬት ይዘን ለእዳ የምንደርግባት መንገድ የለም ይላሉ፡፡ በጠባብ መሬት ላይ ብዙ ማምረት ይቻላል፡፡ በሚገባ ይህችኑ አለስልሳችሁ በማረስና ማዳበሪያ ጨምራችሁ ብትዘሩ የተሻለ ከድሮው ምርት ታገኛላችሁ ስንላቸው በፍፁም የሚቀበሉ አልሆኑም፡፡ "መሬቱ ለብዙ ዓመታት የታረሰ እንደሆነ እናውቃለን ፤ ዛሬም ቢሆን ፈጣሪ ድሮ የሚሰጠንን ምርት አልነሳንም፡፡ ለምን የፈጣሪን ስራ እንፈታተናለን! መሬቷ ሰፋ ያለች በሆነች ግብርናውን ከናንተ ሳይሆን እኛ ራሳችን ለናንተ እናስተምራችሁ ነበር! በማለት ሁኔታውን ከእምነትና ከልማድ ጋር በማያያዝ በከፍተኛ ደረጃ አምርረው ይቃወማሉ፡፡ ስለመሬቱ አነስተኛ እና ጠባብ መሆን ብቻ ይናገራሉ እንጂ አፉን ከፍቶ የሚታየውን የተራራ መሬት አልምቶ መጠቀምም እንደሚቻል ስንነግራቸው "አርሰው ያልጠገቡ ራስ/ፀጉር/ ሰርተው" በማለት አሉታዊ ምላሽ ይሰጣሉ ፤ ተቃውሟቸው በፍፁም ሊቀለበስ የማይቻል ነው (አቶ ጉለሹ በንኑ ፣ ቃመ.12/8/2010 ዓ.ም)፡፡

ከዚህ የምንገነዘበው የልማት ፓሊሲው የገጠመውን ባህላዊ ተግዳሮት ነው፡፡ መንግስት ሀገሪቱን ከድህነት ለማላቀቅና በኢኮኖሚ ዕድገት መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተረታ

ለማሳለፍ እርሻና ገጠር ልማትን ቁልፍ መሳሪያ ነው እያለ ደፋ ቀና በሚልበት በአሁኑ ወቅት ያለውን መሬት ግብዓትን ተጠቅሞ የዋግኽምራ ብሔረሰብ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ብሎ ፈሊጥ ገና አልተዋጠለትም፡፡ በግብርና ስራ ብዙ ደክሞ ምርት ማሳደግ የእርሱን ጆሮና ልቡና የሚያነሳሱ ነገሮች አይደሉም፡፡ በበሬ እንደ ባህሉና ልምዱ አርሶ ማሽላውን ፣ ጤፉን ወይም ስንዴውን ከዘራ በቂው ነው፡፡ የአገር ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ፣ ምርትና ምርታማነትን መጨመር ፣ በምግብ ራሱን ችሎ ለገበያ ማምረት የሚሉት ጉዳዮች ለእሱ ምንም አይደሉም፡፡ ለራሱም ፍጆታ ቢሆን ምርቱ አጥጋቢ ካልሆነ ትቶት ወደ ጎረቤት አካባቢዎች ወይም ወደ ከተማ ለጉልበት ስራ ይገባል፡፡ በዚህ መልኩ በልማድ ተቀፍድዶ ይኖራል፡፡ “ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም” የሚል ለውጥ የሌላው ኑሮውን ይመራል፡፡ ከተማ ገብቶ በጉልበት ስራ ተሰማርቶ ገንዘብ ካጠራቀመ ወደ ቀዬው ይመለስና ያገኘውን ገንዘብ ለተሻለ ነገር ብሎ ከመቆጠብ ይልቅ ለልጆቹ ፣ ለሚስቱ ፣ ለአባት እና ለእናቱ ልዩ ልዩ አልባሳትን ሌሎች ቁሳቁሶችን ይገዛበትና ታልቃለች፡፡ ቁጠባ ይሉት ራስን አሸንፋ ለነገ የማስቀመጥ ነገር በይሉኝታ ሰበብ ይሸረሸራል፡፡ የታሰበው የማደግ ጥሪት የመቋጠር ዓላማው ይከሽፋል፡፡ በዚህም ሳቢያ የመስራት ፍላጎቱ ይቀንሳል ፤ ተስፋ ይቆርጣል፡፡ ይህንን በተመለከተ የሰቆጣ ወረዳ ገበሬ የሆኑ አቶ ደሳለኝ ታደሰ እንደሚከተለው ይገልፃሉ:

> አንዱ አሁን እዚህ ሰቆጣ ከተማ መጥቶ በጉልበት ስራ ተሰማርቶ ነበር ከሰውዬው ጋር እንግባባለን ጎበዝ የጉልበት ሰራተኛ ነው ፤ ያገኘውን ስራ ሳይጠየፍ ይሰራል ፤ ሴቶች ያስፈጩትን ዱቄት ይሸከማል ፤ ውሃ ይቀዳል ፣ ወንዝ ወርዶ እኮ ነው የሚቀዳው ፤ ይገርማል ፣ የከተማ ሰዎችን ትንሽ የለ ትልቅ የለ ስራ ይሰራል ፣ በዚህም ሰዎች ሁሉ ይወዱታል ማንም ይዘዘው ይታዘዛል ምንም ይሁን ይሰራል፡፡ የሚያገኘውን ገንዘብ እንደ ሰው ተታሎ ለምግብ ፣ ለመጠጥ ሆነ ለሌላ ነገር አይጠቀምም፡፡ የሚበላው ስራ ያሰሩት ሰዎች የሚሰጡትን እንጀራ ፣ ቆሎ ፣ ንፍሮ ሁሉ ነው፡፡ እንዲች ብሎ ሰርቶ የሚያገኛትን ብር አያጠፋም፡፡ ያገኛትን የቀን ውሎ ብር ሁሉ በየቀኑ ማታ ማታ ከኔ ጋር ባደራ ያስቀምጥ ነበር እና በሰባት ወሩ ቤተሰቦቹ ናፈቁኝ ልጆቼ በዓይኔ ዞሩ እስኪ ወደ አገሬ ልሄድ እና እነሱንም ልያቸው ትንሽ መሬትም አለችኝ እሷንም የዘር ጊዜ ደርሷል ልዝራት ይለኛል፡፡ እኔም “መልካም ነው” ብዬ

ገንዘብህን ልስጥህ አልኩት፡፡ እሺ አለ፡፡ ካስቀመጥኩለት አስጥቼ በፊቱ ዘርግፌ ስንቆጥረው "ይገርማል!" 10,000 ብር ሆኗል፡፡ ከዚያ ደስ አለኝ እኔም ፡፡ምክር ቢጤ ለገስኩት፡፡ ይህን ገንዘብ በከንቱ እንዳታጠፋ ሌላ ተጨማሪ የንግድ ስራ ስራበት፡፡ የበለጠ ይሆንልሃል ብየ መክሬ እሱም እሺ ብሎ ሄደ፡፡ ከሶስት ወር በኋላ ተገናኘን "ምክሬን ተቀብለሃል ብዬ አስባለሁ" አልኩት ፤ አዝኖ እንዳልተቀበለ ነገረኝ፡፡ የማያልቅ መስሎኝ ለዚያም ለዚያም ስሰጥ ፣ ሳበድር ለምንም ሳላውለው ባዶ እጄን ቀረሁ እና ተመልሼ መጣው አለኝ፡፡ እግዜር ካላላ ምንም የሚሆን የለም! "ሀብታም ሁን ወይም ከሀብታም ተወለድ" ይባላል፡፡ እኔ ዕድሌ እጣ ፈንታዬ ልፋት እንጂ ለሃብት አልታደልኩም ፤ ይኼው ተመልሼ ወደ ሽቅላዬ ወጣሁ ፤ "ጫን ያለው ኮርቻውን ፣ ለምን ያለው ስልቻውን" ይባላል፡፡ የኔ እጣ ፈንታ ለድህነት ነው፡፡ ያገኘሁትን እንኳ አያያዙን አላወኩበትም ብሎ አጫወተኝ፡፡ እግዚአብሄር ጉልበት ሰጠኝ ሰርቼም እንዳገኝ አደረገኝ በቃ! ለወገን ዘመዶቼ ሰጠሁ፡፡ ሲያለቅሱ ሳይ አላስችል አለኝ፡፡ አሁንም ነገ አገኛለሁ እሱ ካለ እቆጥባለሁ፡፡ ካልፈቀደውም የሱ ስራ ነው፡፡ "አርሼ ያላላፈልኝ ሽቅዬ" እያለ ያማርር ያዘ፡፡ እኔም አዝኜ ተው! ሰርተህ ያገኘኸውን ፈጣሪም በትን አጥፉ አላለህም ፣ የአንተው አጉል አስተሳሰብ ነው አልኩት፡፡ ይህ የይሉኝታ ምን ይሉን አስተሳሰብ ቢቀር ይሻላል አልኩት (አቶ ደሳለኝ ታረቀኝ ፣ ቃመ. 18/10/2010 ዓ.ም)፡፡

እንደዚህ ነው የዋግኽምራ ብሔረሰብ ይሉኝታ ያጠቃዋል፡፡ ምን ይሉኛል እሱ ዛሬ አገኘና እኛን ረሳን አዬ የሰው ነገር ይሉኛል በማለት ለሌላው ማካፈል ፣ መስጠት ፣ ማበደር የተለመደ ልማድ ነው፡፡ ለነገ ጥሪት ቁጠባ ፣ ስስት ብሎ ነገር በይሉኝታ ይታሰራል፡፡ ለነገ የሚባል ነገር የለም፡፡ ያገኘውን ያለስስት ያጠፋል፡፡ በዚህም ማንም ቢሆን አንዱ ለሌላው የሚቆጥበው ሆነ የሚደብቀው ነገር የለም፡፡ ሰፊ ጊዜውን በእርሻ መሬቱ ወይም በስራው ላይ ማሳለፍ የሚሉት ልማድ የለውም፡፡ ዋና ሰበቡ መሬቱ ጠባብና አነስተኛ በመሆኑ ነገ እሰራዋለሁ ፣ ነገ እጨርሰዋለሁ ለየተኛው ሰፊ መሬት ነውና እያለ ወደ አቅራቢያው ከተማ ቀመስ መንደር በመሄድ ጠላውን እየጠጣ በማሲንቆ ዜማ መዝናናት ያበዛል፡፡ ያለችውን የበለጠ አልሞና አለስልሶ ከመጠቀም ይልቅ የዘወትር ተግባሩ መሬት

ጠበበኝ ይሉት ንግግር አባዜው ሆኗል (አቶ ደርበው ታረቀኝ ፣ ቃመ. 20/12/2009 ዓ.ም)፡፡ ስራ የለም እንጄ ብሎ የሚታዘበውም የለም፡፡

## 6.1.2. ሰፊ ጊዜውን በእርሻ ስራ ላይ አለመገኘት እና ለትርፋማነት አለመጨነቅ

የዋግኽምራ ብሔረሰብ አርሶ አደር በእርሻ ማሳው ላይ ሰፊ ጊዜውን አለማጥፋት ከቀለብ አልፎ ለገበያ ለማምረት ብዙም አይጨነቅም፡፡ ይህ ለነገ አለማሰብና ከአለመጨነቅ የመጣ ሳይሆን የሚያርሰው የእርሻ መሬት በጣም አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳና በመጥበቡ ምክንያት ጥሪት መቋጠር የሚለውን አስተሳሰብ እንዲረሳ ሳያደርገው አይቀርም ለማለት ያስደፍራል፡፡

የዋግኽምራ ብሔረሰብ አኗኗር በመረዳዳትና በመተጋገዝ ነው፡፡ ኑሮውን አስመልክቶ በግሉ የሚያሳስበው ቢሆንም ብዙም የሚያስጨንቀው አይደለም፡፡ የፈጠረኝ አምላክ የሚገባኝን አይነሳኝም ፤ እሱ ይሰጠኛል ፤ ፍጥረቱን እንዲሁ አይተወኝም የሚል ነው፡፡ “እሱ የከፈተውን አፍ ሳይዘጋው አያድርም ፤ አትኑጥ አንጋጥ” ብሎ ስለኑሮው ለፈጣሪ አሳልፎ የሰጠ ነው (አቶ ባዬ አስምሮም ፣ ቃመ. 07/10/2009 ዓ.ም)፡፡ ለማሳያነት የሚከተለውን ተረት እንመልከት፡-

> አንድ ሰው በድሮ ጊዜ በዚህ ዓለም እኔ መድከም መጣር መጋር የለብኝ፡፡ ከፈለገ የፈጠረኝ ዓምላክ ራሱ የሚያስፈልገኝን ሁሉ በቤቴ እንዳለሁ ይስጠኝ ብሎ ምንም ሰርቶ ላለማግኘት ይወስናል፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ወደ መንገድ ሲሄድ አንድ ገንቦ ሙሉ ወርቅ ያገኛል ፤ አሁንም ይኼንን ወርቅ እኔ ተሸክሜ አልሄድም ፈጣሪ ራሱ ቤቴ ድረስ ያምጣልኝ ይልና ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡ ቤቱም ሲደርስ ለጎረቤቱ መንገድ ላይ አንድ ገንቦ ወርቅ አግኝቼ ነበር ከፈጣሪ ጋር ስለተነጋገርኩ ከፈለገ ቤቴ ድረስ ያምጣ እንጂ እኔ አልሸከምም ቤዬ ጥየ መጣሁ ሲለው ጎረቤቱ በነገሩ በጣም ተገርሞና በሰውየው ጥጋብ ተደንቆ ወርቅ ተገኝቶ ጥሎ ይመጣል ጥጋበኛ እኔ ተሸክሜ አምጥቼ የራሴ አደርገዋለሁ ብሎ ወደ ተባለው ቦታ ሄደ ገንቦውን ያገኘዋል ፤ ሲከፍተው ግን ወርቅ ሳይሆን ጊንጥ ሆኖ ያገኘዋል፡፡ በጣም ይናደድና ይኼ ሰው እኔ በጊንጥ ተነድፌ እንድሞት ፈልጎ አይደል ወርቅ ነው ያለኝ! ቆይ እሰራለታለሁ ብሎ በሌሊት ሄዶ ገንቦውን

ተሸክሞ ያመጣና በሰውየው ቤት በር ላይ አስጠግቶ ወርውሮ እሱን እንዳይነድፋት ሮጦ ይሄዳል፡፡ ሰውየው ጠዋት ተነስቶ በሩን ከፍቶ ሲወጣ ግቢው ሆነ የበሩ አካባቢ ወርቅ በወርቅ ሆኖ ያገኘዋል፡፡ ስለዚህ ሰው በፈጠረው አምላክ ካመነ ሀብት ንብረት ቤት ድረስ ይመጣለታል፡፡ መጣር መጋር ፣ መልፋት አያስፈልግም፡፡ የአንዱን ዕድልም ሌላው ሊወስደው ሊበላው አይችልም ፤ ለተፈቀደለት ብቻ ነው (ቄስ አሸብር አለሜ ፣ ቃመ. 29/10/2009 ዓ.ም ፣ ተረት ቁ. 4)፡፡

ተረቱን ስንመለከተው የሰውዬው ውሳኔ ከመነሻው ራሱንና ማህበረሰቡን ከፍ ሲልም ፈጣሪን የሚፈትን ነው፡፡ ጥያቄውን ሲያነሳ ራሱ ያመነበትን ዕውነት ይዞ የፈጠራውን አምላክ በድፍረት ከፈጠርከኝ ልትመግበኝ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ልታቀርብልኝ ይገባሀል እያለው ነው፡፡ የሚያስፈልገው ሲሰጠው ደግሞ በደስታ ፈንጥዞ በጉጉት ተሞልቶ ተሸክሞ አልሄደም፡፡ እንደገና በድፍረት በግሉ ዕውነትና እምነት ላይ በመቆም እኔ ለሸክም አልተፈጠርኩም ፤ ማን ሊሸከምልህ ነው የሚያስፈልገኝ መንገድ ላይ ያስቀመጥከው እቤቴ ድረስ አምጣት ብሎ ሄደ፡፡ ይኼ የፈጣሪውን ግዴታ የፍጡሩን መብት ያስረገጠበት ነው፡፡

ከፈጣሪ ጋር የተወያየውንና የተሰጠውን ሀብት ሊወስድብኝ ይችላል ብሎ ሳይፈራ ለጎረቤቱ መንገሩ ደግሞ አንደምታው የማህበረሰቡን ግልፅነት በራሱ ማረጋገጡ ፤ አንድም ኽምራ ሀብት ስለማይነካ ማንም እንደማይወስድበት እርግጠኛ ሆኖ ወይም እሱንም እንደፈጣሪው ሊፈትነው ነው ለማለት ያስችላል፡ ፡ጎረቤቱ ግን በፈተናው ወደቀ ፤ የኽምራን የሰው ገንዘብ ያለመሻት ባህል ሰበረና አገኘሁ ያለውን ሀብት የግሉ ለማድረግ ሄደ፡፡ የገጠመው ሁነት ግን የሚያሳየው ሰውየው ባህሉን ስላፈረሰ ፈጣሪው ቅጣት አወረደበትና ገንቦውን እንዲሸከም አደረገው ፤ በዚህም የአማኙን ጥያቄ በመመለስ የራሱን ታማኝነት አረጋገጠ፡፡ ሰውየውን ደግሞ ፈጣሪን ከተማመኑት ሳይለፉ ሳይደክሙ የሚሹትን ሀብትና ሲሰይ እቤት ድረስ አምጥቶ ይሰጣል ብሎ እንዲመሰክር አስቻለው፡፡

እንዲህ በሥነ ቃሎችና በልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶቹ የታነፀው የዋግኽምራ ማህበረሰብ ለዕለት ጉርስ እና ልብስ የሚያስገኝለትን ካገኘ ስለትርፍ ሃብት የማያስብ በመሆኑ ሰፊ ጊዜውን ማሳው ላይ በማዋል የሚያጠፋ አይደለም፡፡ በዚህም በግብርናው ዘርፍ የልማት

ዕቅዱን መተግበር አልተቻለም፡፡ ከላይ አቶ ደርበው ታረቀኝ ስለ “እጣ ፈንታ” ያነሱትም ሀሳብ ይህንኑ የሚያጎለብት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የመስኩ ምሁራን የፎክሎርን/ባህልን/ተግባሮች ከሚገለፁባቸው መንገዶች አንዱ የሆነው የባህልን የመትከልና የማጠናከር ተግባር የሚያሳይ ነው (Bascom, 1954; Okpewho, 1992; Finnegan,1992; ፈቃደ ፣ 1991)፡፡

ባህሉ ከላይ ባየነውና በኋላ በስፋት በሚነሱ ሥነ ቃሎች ራሱን እየተከለና እያጠናከረ በማህበረሰቡ ውስጥ ሰርፆ የኖረ በመሆኑ የዋግኽምራ ብሔረሰብ እንኳን በግሉ ትርፍ አምርቶ ፣ ምርትና ምርታማነቱን በማሳደግ የራሱን ጥሪት ስለመጨው ፣ የአገር ምጣኔ ሃብት በሁለት አሃዝ ስለማሳደግ ፣ ምጣኔ ሃብታዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ምርቶች መርጦ ስለማምረትና ለገበያ ስለማቅረብ ሊጨነቅ ቀርቶ ነገው በፈጣሪ እጅ ያለች ስለሆነች ምን እሆናለሁ ብሎ አይጨነቅም፡፡

ከዚህ የምንረዳው ደግሞ በክልሉ ሌሎች አካባቢዎች ተተግብሮ ውጤት እያሳየ ነው የተባለው የልማት ፖሊሲ ከተጀመረ ከአስር ዓመት በላይ ቢሆነውም በዋግኽምራዎች አካባቢ ውጤታማ ሳይሆን ለመቆየቱ የማህበረሰቡ ባህል ምን ያህል ተፅዕኖ እንዳሳደረበት ነው፡፡ በመሆኑም የብሔረሰቡን ባህላዊ ሁኔታዎች ሳያጠኑና ሳያውቁ ቀድመው ሳይሰሩና ሳይዘጋጁ አንዱ አካባቢ ተግባራዊ የሆነ የልማት ዕቅድ በሁሉም አካባቢ ሊተገበር ይችላል ብሎ መነሳት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

### 6.1.3. የስንፍና ችግር ወይስ ባህሉን አለመገንዘብ

የዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህላዊ ሁኔታዎች ከላይ ያየናቸው ሆነው ሳለ የብሔረሰቡ መስተዳድር እና የክልሉ መንግስት በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እተገብረዋለሁ ያለውን የግብርና ምርትና ምርታማነትን በእጥፍ የማሳደግና ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ስትራቴጂ የማሸጋገር ዕቅድ ተቀብሎ በሁሉም የግብርና ዘርፎች በርካታ ተግባራትን ማከናወኑንና አበረታች ውጤቶችን ማግኘቱን ይገልፃል (የአ.ብ.ክ.መ.ኮ.ጉ ፣ 2007 ፣ 10)፡፡ ይሁን እንጂ የክልሉ መንግስትም ሆነ የብሔረሰቡ መስተዳድር ይህን ቢሉም የብሔረሰቡ ነዋሪዎችና የግብርና ባለሙያዎች ይኼን ሃሳብ ይቃወማሉ፡፡ ይኼን አስመልክተው የግብርና ባለሙያ የሰጡትን አስተያየት እንመልከት፡

-

የዋግኽምራ ህዝብ ካለበት ኋላቀርነትና ድህነት ተላቆ የበለፀገና አስተማማኝ የኑሮ ደረጃ እንዲኖረው የሚያስችሉትን የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤና ጥበቃ ፣ የትምህርት ፣ የጤና እና ሌሎች የልማት መስኮች እንዲስፋፉ ለማድረግ በቅድሚያ የማህበረሰቡን የስራ ባህል አመለካከት አስፈፃሚዎቹ መገንዘብ ያለባቸው ይመስለኛል፡፡ የዋግኽምራ ህዝብ ሰነፍ ነው ባይባልም ማለቴ የስራ ታታሪነት ፣ትጋትና ትግል እንብዛም አይታይባቸውም፡፡ እንደኔ አመለካከት ህዝቡ ኋላቀር የሆነ አስተሳሰብ ላይ የሙጥኝ ያለ ነው፡፡ በርካታ በዓሎችን ያከብራል፡፡ በርካታውን ቁጥር የያዘው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ናቸው፡፡ በአፍላ የስራ ጊዜ ለምሳሌ በዘር ጊዜ ፣ በአረም ሰዓት ፣ በመሳሰሉት እንኳ በዓል ከሆነ በምንም መልኩ አይሰሩም፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በነዚህ ጊዜያት በማህበር ፅዋ መጠጣት ፣ እንዲሁም ወደ ጎረቤት ከተማ በመሄድ መሸታ ቤት (ጠላ ቤት) መግባትና መጠጣት የተለመደ ነው፡፡ ግንዛቤያቸውም ዛሬን ተደስተው ተጫውተው ጨፍረው መዋል እንጂ ለእርሻ ስራቸው "ነገ ይደርሳል" የሚል ነው፡፡ እኛም ባለሙያዎቹም ብንሆን እነሱን ለማግኘት ከማሳቸው ይልቅ በየመሸታ ቤቱ የመሄድና የበዓል ቀናትን ጠብቀን ነው የምናገኛቸው፡፡ ይህንን ለመለወጥ ግን የኛም ጥረት አነስተኛ ነው፡፡ ሰርተው ለማደግና ለመለወጥ እነሱም ግድ የላቸውም ፤ እኛም ከልብ የሆነ እገዛ እያደረግን አይደለም፡፡ የላይኞቹም/ባለስልጣኖቹ ማለቴ ነው ፤ ከኛ የተሻለ መረጃም ሆነ ዕውቀቱም የላቸው ፤ ህዝቡ ሰነፍ ነው ፣ ለስራ አይተጋም ፤ ይላሉ ፤ እኛም እንላለን ፤ ውስጤ ግን ይህን አይቀበልም፡፡ ሌላም ችግር ይኖራል ባይ ነኝ፡፡ አበረታች ውጤት ታይቷል የሚባለው ግን ፍፁም የውሸት ነው (አቶ ጉለሹ በንኑ ፣ ቃመ. 08/10/2009 ዓ.ም)፡፡ አፅንኦቶቹ የኔ ናቸው)

ከዚህ የምንገነዘበው የብሔረሰቡ ባህል/ልማድ የመንግስትን የልማት ዕቅድ እንዴት አንቆ እንደያዘው ነው፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ደግሞ እንደ መፍትሄ የተቀመጠውን ስናይ "ተከታታይነት ያለው ትምህርትና ቅስቀሳ በማድረግ ከተግባር ውጤትም እንዲማር በማድረግ አስተሳሰቡ የኖረ ባህል መሆኑ እብዛም ትኩረት አልተሰጠውም፡፡ የብሔረሰቡ መስተዳድር/መንግስት ብሔረሰቡ ስር የሰደደ ድህነት ውስጥ የቆየ እና

የተሻለ ኑሮ አያውቅም የማደግ ፣ የመሻሻል ተስፋና ተነሳሽነት የለውም ስለዚህ ለስራ ታታሪ አይደለም" ይላል።የግብርና ባለሙያውም አፅንኦት የሰጡት ይህንን ነው።

እውነታው ግን ይኼ አይመስልም ፤ ከላይ ከተገለፀው መረጃዎች እንደሚታየው ማህበረሰቡ ያለበት የታታሪነት ወይም የስንፍና ችግር ነው ብሎ ለመደምደም አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ማህበረሰቡ ያርሳል ፣ ንብ ያንባል ፣ ብረት አቅልጦ ቀጥቅጦ መሳሪያዎችን ሸጦ ገቢ ያገኛል ፤ ወደ ከተማም መጥቶ በጉልበቱ ሰርቶ ፣ ተሸክሞም ሆነ እንጨት ፈልጦ ገንዘብ ያገኛል ፤ በጣም አስቸጋሪ የሆነውን የብረት ማዕድን ድንጋይ ፈልጎ በባህላዊ መንገድ ባካበተው ዕውቀት ከሌሎች የድንጋይ ዓይነቶች ለይቶ በማውጣት ብዙ ጊዜውንና ጉልበቱን ያፈሳል። የብረት ማዕድኑን ፍለጋውም ከመኖሪያ አካባቢው ሩቅ መንገድ መጓዝን ፣ በረሃ ላይ መዋል ፣ ማደርን ይጠይቃል። ልፋት አለው ፤ ድካም አለው ፤ ሁሉንም ተቋቁሞ ያገኘውን የድንጋይ ብረት ማዕድኑን ተስፋ ሳይቆርጥ "ፈጣሪ ባይፈቅድ ነው" ብሎ ሳያማርርና ሳይሰለች ለአድካሚው ለብረት ድንጋይ ቁፋሮና ፍለጋ ይተጋል እንጂ ሰለቸኝ ብሎ አይተውም። ይህ ሁሉ ካልሆነ ደግሞ ወደ ከተማ ወጥቶ የወዳደቁ የብረት ቁራጮችን ፈልጎ ወይም ገዝቶ ስራውን ይሰራል።

ብሔረሰቡ ለፍቶ ሰርቶ የመብላትን ጥቅምና የስራ ትጋትን አስፈላጊነት በስነ ቃሉ እንዲህ በማለት ያጠናክረዋል።

"ካልረባ ሹመት ይበልጣል እርሻ፣
በሰፊ ድግር በሹል ማረሻ።"

"ያርሳል በደመና፣ ይቆፍራል በጉም፣
ከሰው ማሳ ነዶ ምራን አይዘረጉም።"

"ማረስ ያስከብራል ፣ ማግኘት ያኮራል፣
በየደረሱበት የልብ ያናግራል።"

"የሰነፍ በዓሉ ብዙ ነው።"

"ያረሰ ለልጁ አጎረሰ።"

"ስራ ካልሰራችሁ ፤ የት ይገኝ ምሳችሁ።"

እነዚህ ህዝባዊ ቃል ግጥሞችና ምሳሌያዊ ንግግሮች ስንፍናን የሚጠየፉ ፣ ሳይታክቱ መስራትንና መትጋትን የሚያበረታቱ በመሆናቸው ብሔረሰቡ ለስራ ትጋት የሚሰጠው ቦታ ከሹመት የሚስተካከል ፣ በኩራት የሚያናግርና የሚያስከብር እንደሆነ ያመለክታሉ፡ ፡ ተግቶ የመስራትን ጥቅም ተረድቶ ሳይታክት የሚማስነውን ይህን ማህበረሰብ የስራ ትጋት ይጎድለዋል ማለት ዕውነትነት ያለው አይደለም። ችግሩ ባህሉ አብሮ ተካፍሎ መብላትን ፣ ለነገ አለመጨነቅን ፣ ጥሪት አለመቋጠርን ለነገ ፈጣሪ ያውቃልን "አሞጣጣሽ ጋጋሪ ፣ የነገውን ነገር ሰጪው ለፈጣሪ" የሚሉት ብሂላቸው ስላስተማረው እስካገኝ ድረስ ተጠራርቶ ተካፍሎ ይበላል ያበላል ሲያልቅ አይማረርም ወደከተማ ሂዶ የቀን ስራ ፈላልጎ ይሰራል ፤ የእርሻ ወቅቱ ሲመጣም መሬቱን ያርሳል ፤ ቀሪውን ጊዜ ደግሞ ገዝቶ ቤቱ ይገባል። በዚህ መልኩ የዘራው አዝመራ እስከሚደርስ ይቀጥላል። ይሄ ደግሞ ጥሪት እንዲቋጥር ስላላደረገው ሌላ ዓለም ሳይመኝ ኑሮዬ ይበቃኛል ብሎ ባህሉ አስተሳሰቡን ሰርጅቶት ሰውነቱን አጠንክሮ እና መንፈሱን አደንድኖ "በቃኝ" በሚል እምነት ሕይወቱን እንዲኖር አስገድዶታል።

በዋግኽምራ ብሔረሰብ የታታሪነትን ጥቅምና የስንፍናን አስከፊነት እንደሚገነዘብ በባህላዊ ቃል ግጥሞቹ ደጋግሞ ሲያነሳው ማየት ይቻላል።

"ማረሱን ትቶ ፀሐይ ሲፈራ፣
መዝራቱን ትቶ ዝናብ ሲፈራ፣
ማረሙን ትቶ ጭቃ ሲፈራ፣
ልጁ እንጀራ ሲለው በጅብ አስፈራራ።"

"አርሳለሁ እንጂ አላማርርም፣
ችግር በወንጭፉ አይባረርም።"

"በወይና በሬ ካላሉት ላይ ላይ፣

እንጀራ የለም ከሞሰቡ ላይ።"

ብሔረሰቡ ለፍቶ ሰርቶ የመብላትን ጥቅምና የስራ ትጋትን አስፈላጊነት በምሳሌያዊ ንግግሮቹም እንዲህ በማለት ያፀናቸዋል።

"አርግዛ አላርምም ያለች ፣ አዝላ ስደት ትሄዳለች።"

"ሰነፍ አባወራ ምርት ሳያስገባ ፣ ተጋድሞ እንጀራ በወጥ ስጭኝ ብሎ ይጠይቃል።"

"ሰነፍና ዋንጫ ከወደ አፉ ይታወቃል።"

"እርሻ ላራሹ ምርት ላፋሹ።"

"ልጅ በአይዞህ አያድግም።"

ከእነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች የምንገነዘበው በጧት ተነስቶ ተግቶ በማሳ ላይ የመስራትን ጥቅም ነው። በግብርና ባለሙያው በቃለ መጠይቁ እንደሚያመላክተው ብሄረሰቡ ሰፊ ጊዜውን በእርሻ ማሳው ላይ ማሳለፉ የሚያመጣለትን ጥቅም ያልተረዳ አይደለም። ከላይ በምሳሌያዊ ንግግሮቹ በንፅፅር የቀረቡት ወንድና ሴት ናቸው። ሴቷ "አርግዛ አላርምም ካለች ፣ ሰነፍ አባወራ /ባል ለማለት ነው/ምርት ሳያስገባ ተጋድሞ/ስራ ፈቶ ለማለት ነው/ተብለው የተገለጹት ሁለቱም ታታሪ ሆነው ፣ ተግተው መስራት እንዳለባቸው በባህሉ እንደሚጠበቅ የሚያጠይቁ ናቸው። የሴቷ አርግዛም ቢሆን ካልሰራች ለስደት እንደምትደረግ እንደምትራብ ፣የወንዱም ትቢት ከወሬና ከምኞት ያልዘለለ መሆኑ ደግሞ የስንፍናን አስከፊ ገፅታ የሚያመላክት ነው።" ይኼ የታታሪነት ጥቅም በስነ ቃሎቻቸው ተደጋግሞ ሲመጣ እናየዋለን (ቃመ. 1 ፣ ምሳ. 2)።

ከዚህ ደግሞ ብሔረሰቡ ሙሉ ጊዜውን በስራ ላይ ማሳለፍ የሚጠላ እንዳልሆነ ያሳያል። ችግሩ ሰርቶ ያገኘውን በቁጠባ አለመጠቀሙ ከሁሉም ጋር ማባከኑና ለነገ ብሎ ጥሪት ያለመቋጠሩ ነው። ስለዚህ ብሔረሰቡን ሾላ በድፍኑ "የስራ ታታሪነት ይጎድለዋል" ከማለት በእነዚህ በራሱ ምሳሌያዊ ንግግሮችና ቃል ግጥሞች መነሻነት ጠጋ ብሎ በማስተማር የፈለገውን ለውጥ ማማጣት ይችላል። ቀጥሎ የቀረበው ምሳሌያዊ ንግግር

የተግቶ መስራትን ጥቅምና ጥሪት አለመቋጠር የሚያስከትለውን ችግር የሚያሳይ የዋግኽምራዎች አባባል ናቸው፡፡

"ከጎተራው አፍ ያልተቆጠበ ፣ ከጎተራው ቂጥ አይቆጠብም፡፡"

"የቋጠረ ነጠረ ፣ በክብር ተቀበረ፡፡"

"ይስጡኝ ብሎ ከሰጠ ፣ ቆጥቦ የበላ በለጠ፡፡"

"ሰነፍ ሴት ያገባ በሬው በሰኔ ገደል የገባ፡፡"

"ካጨደ የሰበሰበ፡፡"

"የወንድ ሰብሳቢ የሴት ቆጣቢ ይስጥህ፡፡"

"የቆጠበ ምሳው እራቱ ይሆናል፡፡"

"ፀሐይ የጧት አዱኛ የሸበት፡፡" (ቡ.ተ.ው.ይ 20/10/2010 ዓ.ም ፣ ምሳ. 3)

እነዚህን ምሳሌያዊ ንግግሮች የነገሩኝ በተጠቀሰው ቀን በሰቆጣ ዙሪያ ወረዳ ፣ ሰሬን ቀበሌ ወንዶች ብቻ በተገኙበት የቡድን ውይይት ላይ የታታሪነትና ጥሪት የመቋጠርን አስመልክቶ ለተነሳው ውይይት በማስረጃነት ነው፡፡ ከቡድን ውይይቱ የተረዳሁት ማህበረሰቡ ተግቶ በመስራት ያምናል፡፡ ሆኖም ስለነገ ብዙም አይጨነቅም፡፡ በርካታ ነገር በግሉ ማጠራቀምና ማስቀመጥን ብዙም አለመደም፡፡ አይበለውና እንደ 1966 እና 1977 ዓ.ም ድርቅና ሌሎች አደጋዎች ቢከሰት ብየ ስጠይቃቸው በሰጡኝ መልስ "ጎጃምም ወሎም መተከልም ሄደን እንሰራለን ፤ ጊዜው ሲመለስ ፣ ተፈጥሮው ዝናብ ሲቸር መጥተን ደግሞ እኖራለን፡፡ መሬታችን ጠባብ ፣ እንደምታየው ተራራ ነው፡፡ ያለችው የእርሻ ቦታ በገመድ ተለክቶ የሚሰጥ ነው፡፡ አይበቃም በዚያችም ላይ የምታለማው ቋሚ ተክል ሳይሆን በሰኔ አርሰህ በጥቅምትና በህዳር የሚደርስ የተለመደው 'አዝግመህ ድረስ' ሰብል ነው፡፡ ይህም ብዙም ውጤት የሚሰጥ አይደለም፡፡ የልማት ባለሙያዎቹም አልሙ የሚሉን የጋራ የሆነውን ተራራ የተፋሰስ ልማት ጥብቃ የሚሉትን ነው፡፡ ይህም ተራራውን ደን ለማስበስ ነው፡፡ ደኑ ሲለማ ዝናብ ያመጣል ፤ ከዚያ ማሳው በዝናብ አይቸገርም ይሉናል፡፡ እኛም የእኔ ብለን የምንከባከበው አይደለም ፤ ለማን

ሊሆን ብለን ችግኝ ቀብረን እንመጣለን እንጂ አንከባከበውም ፤ በዚችው በተወሰነልን ማሳ ተወስነን የምናገኘውም አነሳ ለዚያውም ድርቅ ካልመታው ፤ በዚህ የተነሳ ተስፋ ቆርጠን ስናገኝም አናውቅበት ብዙ ልማዳዊ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ሰርግ ተስካር ኧረ ልማዱ ብዙ ነው ፤ በይሉኝታ ሰው አገር ምን ይለን እያልን ከዚያችው ከምናገኛት ለብዙ ተከር እናውላታን ፤ መቼም አያልፍልን ብለን ተስፋ ቆርጠን ፣ ጥሪት መቋጠር መያዝ በምን ታስቦ! በዚያው ላይ ልማዱም ስለሌለን እንጂ ጥሪት መቋጠሩስ መልካም ነበር" (ቡ. ተ. ው. 20/10/2010 ዓ.ም) ብለዋል፡፡

ዋግኽምራዎች ተፈጥሮ በለገሳቸው ጊዜ የዕለት ጉርሳቸውንና የዓመት ልብሳቸውን ለማግኘት ወደ አጎራባች አካባቢዎች በመሄድ የቀን ስራ ይሰራሉ ፣ ያገኙትን አጠራቅመው ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ልብስና ጫማ ይገዛሉ (አቶ ታደሰለኝ ታደሰ ፣ ቃመ. 15/09/2009 ዓ.ም)፡፡ ጥሪት ለመቋጠር ያልቻሉት በባህላቸው ተካፍሎ መብላትና ለመጪው አለመጨነቅ "ፈጣሪ ያውቃል" ሲሉ እንጂ የስራ ትጋት ስላጡ አይደለም፡፡ ይልቁንም ይህን የመተግበር አስተሳሰብ ለልማት እንደ ጥሩ እድል ቆጥሮ በትብብር መብላትን ብቻ ሳይሆን በጋራ ሰርቶ በጋራ ለማደግ መሳሪያ ማድረጉ ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል፡፡

ከላይ የቀረቡትን ሥነ ቃሎች /ምሳሌዎችና ቃል ግጥሞች/ ማስተማሪያ በማድረግም በየቤተክርስትያናቱና በየሰንበቴው መጠጫ ቦታዎች ተገኝተው ህዝቡን እንዲወያይበት በማድረግ የተቀዛቀዘ የስራ ስሜት አለ ብሎ ከታሰበ ለማነቃቃት በባህሉ ያልተለመደው ቁጠባና ጥሪት የማስቀመጥንም ጥቅም በማስረዳት የተፈለገውን ለውጥ ማምጣት ይቻላል፡፡ የባህሉም የአስተማሪነት ተግባር እዚህ ላይ ጠቃሚ ሚና ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

በባህልና ልማት ቁርኝት ላይ ትኩረቱን አድርጎ የተዘጋጀው የዩኔስኮ ሰነድ እንደሚያመለክተው "ሰዎች ከተፈጥሮኣዊ አካባቢያቸው ጋር ያላቸውን ዝምድና እንዴት እንደሚጠብቁትና እንደሚያስተዳድሩት የሚኖራቸው አመለካከት የሚቀርፀው በባህላቸው በመሆኑ ባህል ለዘላቂ የአካባቢ ልማትና ጥበቃ አንቀሳቃሽ ሞተር ነው" (UNESCO, 2010) ይላል፡፡ ስለዚህ ይህን የልማት አንቀሳቃሽ ሞተር ተጠቅሞ የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን ማህበረሰቡን በጥቅሉ "የስራ ተነሳሽነት/ትጋት /የለውም" ብሎ ከመደምደም ባህሉን እንዴት የልማት መሳሪያ እናድርገው በሚለው መሰረታዊ ጉዳይ ላይ ትኩረት

አድርጎ በባህሉ ዙሪያ ልምድ ካላቸው የአካባቢው አባቶች ፣ ከሃይማኖት መሪዎች ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ተሰሚነት ካላቸው ሰዎች ፣ ወዘተ ጋር ከልብ አጥብቆ መመካከር ፣ የሚሉትን ማዳመጥና ሃሳባቸውን ተቀብሎ ከልማታዊነቱ ጋር ለማዋሃድ በሥነ-ቃሉና በሌሎች በባህላዊ ገፅታዎቹ የሚገልፁትን የብሔረሰቡን ባህላዊ ዕውቀቶች መሰረት አድርጎ መነሳትና ከዚህ አኳያ ጠንክሮ መስራት የብሔረሰቡ መስተዳድር ዋና የቤት ስራ ሊሆን ይገባል።

በደሃና ወረዳ በተዘጋጀው የወንዶች ብቻ የቡድን ውይይት ጊዜ ማህበረሰቡ ከራሱ ፍጆታ ያለፈ ምርት እንደሚያመርት ፣ ጥሪት ለምን ለነገ ብሎ እንደማይቋጥር በዚህ ክልል ልማታዊ አርሶ አደር እየተባሉ በመንግስት የሚሸለሙ ሰዎችን ምሳሌ በመስጠት እንዲወያዩበት ባደረግሁ ጊዜ አባ አሸብር አለሜ በተባሉ መረጃ ሰጪዬ የቀረበው ምሳሌ ይህንን ይመስላል።[51]

> ስማ ልጄ! ይገርምሃል የምነግርህ እንዳልከው ለልምድ ተብሎ ከየወረዳው ሰዎች ተመልምለን ወደ ትግራይ ክልል እዚሁ እኛው ማዶ ይዘውን ሄዱ ፤ ይሄ የትግራይ ጠንካራ አርሶ አደር ይሄን ያህል አምርቶ ሸጦ ይኼን ያህል ሺህ ብር አጠራቅሟል ፤ ቤቱንም ወደ ቆርቆሮ ቤት ቀይሯል ፣ ቴሌቪዥን አለው ፣ መኪና ገዝቷል ፣ መብራት አስገብቷል ፣ በባንክም ይኼን ያህል ሺህ አጠራቅሟል ፤ እያሉ ያሳዩናል ፤ ሰውየው ግን በረባሶ ጫማ ያውም የኔ ትብልጠዋለች የተበጣጠሰች ሱሪው የነተበ ፊቱ የተጠጋ/የከሳ ነው። ይኼው ዛሬ እመቤቴ ናት ፣ ማርያምን ነው የምልህ! ከዋሸሁ እዚሁ ከሄዱት ውስጥ አንዱ አለ ፣ ምንም እንኳን ያለው/ያጠራቀመ ፣ ሊመስል ፣... እየጎተቱ አምጥተው ተናገር ብለው ያስገደዱት እስረኛ ነው የሚመስለው። በልቶም የጠገበ አይመስልም። እኔም ውስጤን ተሰማኝና ለምንድንነው የምታጠራቅመው አልኩት ሳትበላ! ሳትጠጣ! እሱም ቀስ ብሎ በጆሮዬ "ለምን እንደመጡብኝ አላውቅም ፤ እኛ ስንናገር አንተ አዎ አዎ በል ነው ያሉ" አለኝ። ነገሩ ገባኝ። በመጨረሻም ውይይት ተብሎ ስንቀመጥ ፣ እንዴት ከኛ ከማይሻሉ ሰዎች ልምድ የምንወስደው ምን ልናገኝ ነው ተጨማሪ ድህነት ወይስ ስንፍና ብለን

[51] አባ አሸብር ከመናገራቸው በፊት የቡድኑ አባላት የምፀት ሣቅ ይስቁ ነበር።

እየገረመን ተመልሰን መጣን፡፡ የልምድ ልውውጡ ውሸት ነው… ሰው ሳይበላ እንዴት ይቆጥባል የነገን የሚያውቀው ፈጣሪ ነው፡፡ "ሳለ ፈጣሪ አሞጣጣሽ ጋጋሪ" ይላል ያገሬ ሰው (ቡ.ተ.ው ፣ 07/10/2010 ዓ.ም)፡፡

ዋግኽምራ ትርፍ ምርት አያስፈልግም ብሎ የሚያምን ሳይሆን ሳይተርፈኝ ልቆጥብ አልችልም የሚል አስተሳሰብ ነው ያለው፡፡ ዛሬ ያገኘኊትን በልቼ ተደስቼ ለነገው ፈጣሪ ያውቃል ባይ ነው፡፡ ይህንን ማህበረሰብ ለመለወጥ የሚያስፈልገው ባህሉን ራሱን በማልማት መሳሪያ በማድረግ አመለካከቱን ማስቀየር እንጂ የክልሉ መንስግትም ሆነ የብሔረሰቡ መስተዳድር እንደሚለው "ይህንን ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ የኖረና ስር የሰደደ ችግር የአገር አቀፍና የክልላችንን የግብርና ፖሊሲ መሰረት በማድረግ የዞኑን ህዝብ ዴሞክራሲያዊ በሆነ ትግል በታታሪነትና በትጋት በፍጥነት በማሻሻል ለአደጋ ተጋላጭነቱን ለመቀነስ እና የምግብ ዋስትናውን ለማረጋገጥ እንዲቻል መጠነሰፊ የልማት ስራዎች ይሰራሉ" (ሻደይ ወንዝ አይፈሬ የብሔረሰቡ መስተዳድር አመታዊ መፅሔት ፣ 2003 ፣ 16) እንደሚለው የሚቻል አይደለም፡፡ የቱንም ያህል ዴሞክራሲያዊ ትግል ቢደረግ ለውጥ ማምጣቱ ላይ አስቸጋሪነቱ አያጠራጥርም፡፡ ይልቁንም ባህላዊ መሰረቱን ለይቶ በማጥናት ከአካባቢው ሽማግሌዎች ጋር በጋራ መክሮ አዲሱን በነባሩ ላይ በመገንባት የሚታሰበውን ልማት ማምጣት ይቻላል፡፡ ከዚህ ውጪ የልማት መሰረት አድርጎ ይወሰድ የነበረው የሞደርናይዜሽን ንድፈ ሀሳብ አቀንቃኞች እንደሚሉ "የማህበረሰቡ ባህል ለልማት ማነቆ ስለሆነ መወገድ ይገባዋል" ብሎ መነሳት ብዙ ርቀት የሚያስኬድ አይደለም፡፡ አሉላና ገብሬ እንደሚሉት "… ልማት እንዲመጣ ከተፈለገ ህዝቡን በውሳኔ አሰጣጥ ማሳተፍ የህብረተሰቡን ፍላጎትና ባህል ግምት ውስጥ ማስገባት ፣ እንዲሁም በአካባቢው የሚገኘውን ሀብትና ዕውቀት መጠቀም የግድ ነው" (አሉላና ገብሬ ፣ 2004 ፣ 81)፡፡ ስለዚህ ከላይ ወደታች የሚወርድ የልማት እቅድና ውሳኔ ብቻ ልማትን ማምጣት አስቸጋሪ በመሆኑና ከላይ በስፋት እንደታየው የዋግኽምራ የጋራ ጉዳዮችን በጋራ የመፍታት ባህሉ የጠነከረ ስለሆነ የታሰበውን የልማት ዕቅድ በጋራ መክሮበት ፣ አስፈላጊነቱን አምኖበትና የራሱ ጉዳይ አድርጎት ለተግባራዊነቱ እንዲነሳ ለባህላዊ ሁኔታዎቹ ትኩረት ሰጥቶ መስራት የግድ ይሆናል፡፡

ይሁንና የክልሉ መንግስትም ሆነ የብሔረሰቡ መስተዳድር ለባህል ጉዳዮች የሰጠው ትኩረት አሉታዊ ጎናቸው ላይ ብቻ ያተኮረ እንጂ ለልማት የሚኖራቸውን አዎንታዊ

ሚና ያገናዘበ ባለመሆኑ ጎጂነታቸውንና ጎታችነታቸውን የሚያጎላ ነው፡፡ በክልል ደረጃ ብሔረሰቦችን ለማገዝ የሚመደቡ የግብርና ፣ የጤና ፣ የትምህርት ፣ የውሃና የመስኖ ወዘተ ባለሙያዎችን አሰራር አባላቱንና ህዝቡን እንዲያግዙ ሲያደርግ የባህልን ጉዳይ የሚመለከት ባለሙያ አለመመደቡ ለልማቱ ስራ ላይ ለባህል የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑን የሚያለመላክት ነው፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው የባህል ትስስር ለፈጣን እድገት ጠንካራ መሰረት ነው፡፡ ሃገር በቀል ዕውቀትን ፣ አካባቢያዊ ሀብትንና ጥበብን ከጥቅም ላይ ማዋልና ባህላዊ ኢንዱስትሪዎችን በማልማት ትልቅ የልማት ስኬት ማምጣት እንደሚቻል መረጃዎች ያመላክታሉ (UNESCO,2012 ;4)፡፡

በዋግኽምራ ባህል ከመነሻው ሲታይ የማህበረሰቡ የገቢ ምንጭ የተመሰረተው በእርሻ ስራ ላይ ብቻ አይደለም፡፡ ግብርናና ጥምር ግብርናንም ነው፡፡ የብሔረሰቡ ልዩ ልዩ አባላት ባህላዊ በሆነ መንገድ ወርቅ አምርቶ የመሸጥ ፣ የእደ ጥበብ ውጤቶችንና በአነስተኛ የጎጆ ኢንዱስትሪዎች የብረታ ብረት ውጤቶች ፣ የቆዳ ስራዎች ፣ ልዩ ልዩ የብርና የነሀስ ጌጣጌጦች ፣ የሸመና እና የሸመና ውጤቶችን በመስራት ለአጎራባች አካባቢዎች በመሸጥ ገንዘብ ያገኛሉ፡፡ በባህላዊ መንገድ በአካባቢው በሚገኙ ከዕፅዋት የተቀመሙ ቅባቶችን በማምረት ፣ የመዋቢያ ነገሮችንና ሽቶዎችን ቀምመው የመጠቀም እና ለሌሎችም የመሸጥ ወይም የመነገድም ልምድና ባህል ያለው ነው፡፡

ይህን ሁሉ ሀገረሰባዊ ዕውቀት ያለውን የዋግኽምራ ብሔረሰብ “የስራ ትጋት የለውም” ብሎ በደምሳሳው ከመደምደምና የኋላቀር አስተሳሰብ ባለቤት አድርጎ ከመፈረጅ እነዚህን ባህላዊ እሴቶቹን ከአኗኗር ልምዱ ጋር አስተባብሮ በማልማት ወደ ትናንሽ ኢንዱስትሪዎች በማሳደግ አካባቢውን ማልማት ከመቻሉም በላይ ተጨማሪ የስራ ዕድልን ፈጥሮ ብሄረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል፡፡ ስለዚህ አካባቢውን ለማልማት ከተፈለገ በባህሉ መልካም መሰረቶች ላይ በመነሳትና ህዝቡን አሳታፊና ተጠቃሚ በማድረግ ውጤታማ መሆን ይቻላል፡፡

## 6.2. የጤና ኤክስቴንሽንና የዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህል/ልማዶች

መንግስት ከነደፋቸው የልማት ፖሊሲዎች መካከል ከግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ ቀጥሎ የጤና ፖሊሲ ተጠቃሽ ነው። ለዚህ የማህበረሰብ ጤና እንክብካቤ ፖሊሲ ማስፈፀሚያነት በገጠር የጤና ኤክስቴንሽን ፖኬጅ ትግበራ ከተጀመረ ብዙ ዓመታት ሆኖታል። የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የነበረውን ቀዳሚ አተገባበር በመገምገም ባዘጋጀው የአምስት ዓመት የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ ትኩረት ሰጥቼ እሰራዋለሁ ያለው አንዱ ጉዳይ ይኼው የማህበረሰቡ ጤና እንክብካቤ ዕቅድን ነው። ዕቅዱ የገጠመው ተግዳሮት ቀጥሎ ቀርቧል።

### 6.2.1. ባህላዊ/ልማዳዊ ህክምና

የክልሉ መንግስት በተጠቀሰው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ በክልሉ የሚኖሩትን ብሔረሰቦች በጤና አጠባበቅ ጉዳዮች ዙሪያ ያላቸውን አመለካከት እና ወደፊት ምን መሰራት እንዳለበት እንዲህ በማለት ይገልፃል።

> ክልሉ ያልተማከለ (Decentralized) የጤና አገልግሎት ስርዓት በመዘርጋት በሶስት ዋና ዋና ምሰሶዎች የላቀ የጤና መሰረት ልማት ፣ የጤና አገልግሎትና አመራር እንዲሁም የጤናው ዘርፍ ልማት ፕሮግራም በአምስት ዓመቱ እድገትና ትራንስፎርሜሽን እስትራቴጅካል እቅድ ለማከናወን ከተያዙት የልማት ሰራዊት ግንባታ ፣ የአካባቢ ጤና አጠባበቅን ማሻሻል ፣ የእናቶችን ጤና ማሻሻል ፣ የህፃናትን ሞት መቀነስ ፣ ኤችአይቪ/ኤድስ ወባና ሌሎች በሽታዎችን መከላከልና የጤና መሰረተ ልማት ተደራሽነትን ማሻሻል የሚሉትን ግቦች ለማሳካት እንሰራለን (ኢ.ብ.ክ.መ.ከ.ት የ5 ዓመት ዕትም ፣ 2006 ፣ ገፅ 72 ፣ አፅንኦቶች የኔ ናቸው)።

ከላይ በክልሉ መንግስት ዕቅድ እንደተገለፀው የዋግኽምራ ብሔረሰብ ጤናው ሲታወክ ወደ ባህል መድሃኒት አዋቂዎችና ጠንቋዮች /እንደነሱ አባባል አዋቂዎች/ዘንድ ሄዶ መታከምን አሁንም እየተገበረው ይገኛል።ሰቆጣ ወረዳ ሰላምጌ ቀበሌ የሚኖሩ አቶ ደሳለኝ ታደሰ ይባላሉ። ሰውየውን መጀመሪያ ያገኘኋቸው ሰቆጣ ከተማ ነው። እንዲህ ዓይነት ሰው እንደምፈልግ ለመረጃ አቀባዬ ለመ/ት ወርቃፈራሁ ቀድሜ ነግሬያት

ስለነበር ገበያ ስታገኛቸው እቤት ይዛቸው መጣችና አስተዋወቀችን፡፡ እርሳቸውን ስለምፈልግበት ጉይ በሚገባ ካስረዳቻቸው በኋላ በማግስቱ ጠዋት (ዕለቱ ዓርብ ነበር) ከቤታቸው ከመጣሁ ሁሉን እንደሚነግሩኝና እንደሚያሳዩኝ ተስማማን፡፡ በቪድዮ ለመቅረፅ ግን እንደማይፈቅዱልኝ ነገሩኝ፡፡ እኔም ምንም ማድረግ ስለማልችል ተስማማሁ፡፡ በማግስቱ ጧት ቀደም ብለን ከመ/ት ወርቃፈራሁ ከተቀጣጠርንበት ቦታ ቁሜ ስጠብቅ ከሌላ ሴት ጋር መጡ፡፡ መ/ት ወርቃፈራሁም ፈጠን ብላ "ታንጉት" ትባላለች፡፡ ዘመዴ ናት፡፡እ ያመማት እንደነበርና እንደተቸገረች ነገረችኝ፡፡ ይኼው እንግዲህ እሷን አዋቂው ጋር ወስጄ በሽታዋን እንዲነግራትና እንዲፈውሳት ይዣት መጣሁ፡፡ ስለዚህ አዋቂው እንዴት እንደሚያክማት ታያለህ በማለት ተያይዘን ወደ አዋቂው ቤት ሄድን፡፡ ከዚያም አዋቂው ቤት ከደረስን በኋላ ታማሚዋ ታንጉት ወደ አዋቂው ልዩ ቤት ገባች፡፡ እኛ ግን ውስጥ ሳንገባ ግን የሚነጋገሩትን ልንሰማበት ከምንችልባት ቦታ ተቀመጥን፡፡ ታንጉትም (በሽተኛዋ) የሚያማትን የህመም ስሜት ዝርዝር አድርጋ ተናገረች፡፡ ጠቅላላ ሰውነቴን ይቆረጣጥመኛል ፤ መገጣጠሚያዬ ሁሉ ይዝላል ፤ ድካም ድካም ይለኛል፡፡ ያስፏሽገኛል ፤ ከተቀመጥኩ ተነሽ ተነሽ አይለኝም፡፡ ፍዝዝ ድግዝ ፣ አረ ምኑ ቅጡ ፤ ራሴን አላውቅም የሆነ ውርር የሚያደርገኝ ነገር አለ፡ ፡ እያለች የሚስማትን ሁሉ የህመም ስሜት ያለችውን ሁሉ ትናገራለች፡፡ አዋቂው በፅሞና ፀጥ ብሎ ያዳምጣል፡፡ ታንጉት ተናግራ ከጨረሰች በኋላ አዋቂው ትርጉሙ የማይታወቅ የማልጎምጎም ድምፅ ሲያወጣ ከቆየ በኋላ "ህመምሽ የላይትላይ" ነው ፤ ከአባት ከእናት የሚመጣ የውቃቢ /መንፈስ/ መቆጣት ነው፡፡ የሚፈልገውን "የምሱን" በማስቀረትሽ የመጣ ነው፡፡ ቁጣ ነው! አይዞሽ አሁኑኑ ለምጥቻ /ግብር/ የሚሆን ልበ ወርቅ ዶሮ ፈልገሽ እጣንሽን አጭሰሽ ትንሽ ቅቤ /ነጭ ቅቤ/ የዶሮዋን አናት ቀባ ካደረግሽ በኋላ በላይሽ ላይ ሶስት ጊዜ አዙረሽ ነቀል አድርገሽ ወደ ውጭ ጣያት፡፡ በቃ! ከዚያ ምንም የለብሽም፡፡ ወዲያው በሽታሽ ተነቅሎ ይሄዳል፡፡ ዶሮዋም በቤትሽ ትቀመጥ ጠባቂሽ ናት፡፡ ምንጊዜም ከቤትሽ እንዳጠትፋ ፤ በማለት ነገሯት፡፡ ጨርሳ ወጣች፡፡ እኔም ይህንን ሰምቼ ምን ያህል እውነት ነው ትፈወስ ይሆን በማለት ፈውሱን ለማየት ጓጓሁ፡፡ ታንጉትን እውነት መታመሟን በግልፅነት ጠየኳት ፤ እንዴ! አዎ ባይገርምህ አሁን ውስጤ ቅልል ነው ያለኝ ያ ይሰማኝ የነበረው ገና ልበ ወርቋን ዶሮ ሳላሻሽ ህመሙ ጠፍቷል፡፡ ገዝቼ ዛሬውኑ አሻሽቼ አዙሬ ስጥላት በሽታው ውልቅ እንደሚል ነው፡፡ እሳቸው እኮ የሁሉም መድኃኒት ናቸው እያለች ተናገረች፡፡ በሶስተኛው ቀን መ/ት

ወርቃፈራሁን ስለታንጉት ስጠይቃት አሁንማ ድና ስራዋን እየሰራችልህ ነው በማለት ነገረችኝ፡፡ ሌላም ባዩሽ መንግስቴ[52] የምትባል ሌላ መረጃ አቀባዬ አብራን ስለነበረች ሁለቱ እየተቀባበሉ የሚሰራውን ተዓምር ያስረዱኝ ጀመር፡፡

ማርያምን! ሰውየው ተዓምረኛ ነው ፤ ከጎረቤቴ ከወ/ሮ ትብለጥ ጋር ተጣልተን ሙልጭ አድርጌ ሰድቢያት ፤ አልወጣልሽ ቢል ንዴቴ ፍልጥ አንስቼ ወገብ ወገቧን ነርቼ ነርቼ ጣልኳት ፤ በዚህም አልበቃኝም ፀጉሯን ሁሉ ነጬኋት፡፡ ድብልቅልቅ ያለ ጠብ ሆነ ፣ ድብድብ ሆነ ሰው ግልጥ ብሎ ወጣ ፤ እኔም ንዴቴን ስለተወጣሁት ገላጋዩም ተቆጬም ሲበዛ ትቻት ወደ ቤቴ ገባሁ፡፡ ከዚያም ሰዎች (ሴቶችን ነው) አስፈራሩኝ ፤ በጣም ስለተጎዳች ልትከስሽ ነው ፤ ከዚህ ወጣ ብለሽ ተደበቂና ሁኔታውን በርቀት ተከታታይ ብለው ስለመከሩኝ ፤ ስራየንም ትቼ ሳላስፈቅድ ጨርቄን ብቻ አንጠልጥዬ አክስቴ ጋ ወደ ወልዲያ ሄድኩ፡፡ አክስቴ ጋር 15 ቀን ቆይቼ የሆነው ይሁን ብዬ ተመለስኩ፡፡ ከዚያማ ይኼውላችሁ ወ/ሮ ያለምወርቅ ጠቡን ሰምታ ስለነበር ማታ ልታየኝ መጣችና አዋቂው ጋር ሄደሽ የሆነውን ሁሉ ንገሪው እሱ መፍትሔውን ያደረግልሻል፡፡ ጠቡንም ክሱንም እንዲቀር እንዳይነሳ እንዳይወሳ ያደርጉታል፡፡ እሷም አንቺን በክፉም አታነሳሽም ፤ እውነቴን ነው የምልሽ ለአዋቂው ንገሪው ብላ ስላሳሰበችኝ ፤ ኤም በጧት ሹልክ ብዬ ሄጄ ሁሉንም ነገርኳቸው ፤ሰውነቴን በሆነ በአዲስ ጨርቅ እራፊ በተጠቀለለ ነገር አሻሽተው ግንባሬንም ሶስት ጊዜ በዚያው ነካ ነካ እያደረጉ በራሴ ዙሪያ እያዞሩ ሶስት ጊዜ አሁንም ወደመሬት ጥቅሉን እየጣሉና እያነሱ ካዞሩት በኋላ ጥቅሉን የእራፊ ጨርቅ ወደ ኋላዬ ጥለው ፊቴን ወደ መጣሁበት መንደር አዙሬ እንድቀመጥ አደረጉና ፤ ሌላ በእራፊ ጨርቅ የተቋጠረ ነገር ሰጡኝ፡፡ ይህንን መድሃኒት ጧት ቀደም ብለሽ ወጥተሽ በሴትየዋ ቤት ከግራ ወደቀኝ እየዞርሽ ሶስት ጊዜ በትኚው፡፡ ከዚያም ቤቷን ዙረሽ ሳትመለከች ቀጥታ ወደቤትሽ ተመለሽ፡፡ በቃ ይኼው ነው፡፡ ሁሉም ነገር እንዳልነበር እንዳልተፈጠረ ይሆናል፡፡ወሬውም አይነሳም ብለው ጀርባቸውን አዙረው ከኋላ ወደፊት ገፍተር አድርገው ላኩኝ፡፡ እኔም በተነገረኝ መሰረት ፈፀምኩ ሁሉምነገር ሰላም ሆነ እሷ ራሷ ይኼው ነገሩን ሁሉ ትታ ሰላም

---

[52] ባዩሽ መንግስቴ በወረዳው የምትኖር የአይን ህመም መድሃኒት የምሰጥ ነዋሪ ናት፡፡

ፈጥረን እየኖርን ነው፡፡ ሰዎችም ሁሉ በመገረም የሳቸው ስራ እያሉ ያደንቃሉ፡፡ አዎ! የሰጡሽ መድሃኒት መንፈሳዊ ኃይል አለው ፤ የበተንሽው ነገር "ነገር አርክስ" ነገረ-በትን ተብሎ ነው የሚጠራው በማለት መ/ት ወርቃፈራሁ አብራራችልን (ወ/ሮ ባዩሽ መንግስቴ እና መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ፣ቃመ. 20/10/2010 ዓ.ም)፡፡

ወ/ሮ ታንጉትን ራሴ አግኝቼ መድኃኒቱን ለማረጋገጥ ወሰንኩና አግኝቼ እንዴት እንደሆነች ጠየኳት፡፡ አረ! እሳቸው የነኩት የታወቀ አይደል፡፡ እንደምታየኝ ድኛለሁ ምንም የታመመኩም አይመስለኝ፡፡ የዚያኑ ጊዜ ነው ሁለመናየን ቅልል ሲለኝ የታወቀኝ፡፡

አሁንማ በሽታውም ታውቆልኝ መፍትሄውንም ነግረውኝ ስለፈፀምኩኝ ምንም የለብኝም ዳን ብያሁ፡፡ ዕድሜ ለሳቸው ብላ መዳኗን አረጋግጠችልኝ፡፡ እኔም በሁኔታው በጣም ተገርሜ ታንጉትን ምንም ሳልላት ዝም ብዬ በአግራሞት ቁሜ እመለከታት ነበር ፤ ታንጉት[53] ጋሼ! ብላ ስትጠራኝ ደንገጥ ብዬ እ.እ... በጣም አመሰግናለሁ ስላት ሽረ ለምኑ? የታመምኩ እኔ ነኝ ፤ የደዳንኩትም እኔ ነኝ ለምኑ ነው? ብላ መቼም የከተማ ሰው... አዋቂ አይወድም ፤ ውሸታም ነው ፤ አያድንም የምትሉት ፈሊጥ አላችሁ ፤ ተጠራጥረውኝ ነው አይጠራጠሩ ፤ እሳቸውን ዓለም ያወቃቸው የተናገሩት ከመሬት ጠብ የማይል መድሃኒታቸው ፍቱን ነው፡፡ ደግሞም የሁሉንም ሰው ሆድ ያውቃሉ አንዳች ብለው ሃጢያት ውስጥ እንዳይወድቁ ፤ ዛሬ ቀኑ ዕሮብ እማይደል ፤ አዎ ዛሬ መቼም ብዙ ሰው ነው ለመፈታት/ለመታከም የሚመጣው ዛሬ ግልጥ በግልጥ ነው የሚናገሩት ለምን ሂደው አያዩም፡፡ ሁሉም ሰው ነው የሚሄደው ፤ የታመመው ለመዳን ያልታመመው ደሞ ጉድ ለማየት... ጋሼ ግደለዎትም ይሂዱ ጥርጣሬዎትን ይተዋሉ (ወ/ሮ ታንጉት ፣ ቃመ. 24/09/2010 ዓ.ም)፡፡ ሀሳቧን ተቀብየ ቀድሞም መ/ት ወርቃፈራሁም ቀጠሮ አስይዛ ስለነበር ወደ አዋቂው አቶ ደሳለኝ ታደሰ ቤት አመራን፡፡ ከከተማው ብዙም የማትርቅ ስለነበረች ለአንድ ሰዓት ያህል በእግራችን ተጉዘን ስንደርስ

---

[53] ታንጉት ሽበሽ ፣ በሰቆጣ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ተላላኪ ሰራተኛ ስትሆን ቁልፍ መረጃ አቀባዬ መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል ወደ አዋቂው ቤት ለትውውቅ ስትሄድ ታማ ስለነበር እግረ መንገዷን ከአዋቂው ጋር ለመታከም ይዛት የመጣች ባህላዊ ታካ ናት፡፡ የተዋወቅነው በአዋቂው ቤት ለመታከም መጥታ ነው፡፡

የአዋቂው ሰፈር በሰው ተሞልቷል፡፡ ታማሚው ፣ ታማሚ ቤተሰቡንና ዘመዱን ይዞ የመጣው ሰው ብዛት ወደ ስልሳ ይጠጋል፡፡ ቀስ በቀስም ቁጥሩ እየጨመረ ሄደ፡፡

ሰውየሰው የእኛን መድረስ እየጠበቁ ኖሮ ስራ አልጀመሩም፡፡ እንደደረስን ወጥተው በፈገግታ ተቀበሉን ፤ እኔም ጎንበስ ብዬ እጃቸውን ዘይሬ (መሳም) ወደኋላ ፈቀቅ ብየ ልቆም ስል… እኮ ለምን? ና ፣ ና ፣ ልጄ ፣ ብለው እንደ አካባቢው ባህል በእጃቸው መዳፍ ግራ ቀኝ ጉንጨን ይው አገላብጠው ሳሙኝ፡፡ መረቁኝም ፤ ሳታውቀን ዝናችንን ሰምተህ ስራችንን ወደህ ስለመጣህ “የሰማይና የምድር ፈጣሪ ያክብርህ ፣ ሞገሱን ያልብስህ” ብለው መረቁኝ እና ታካሚዎቻቸውን ወደሚያዩበት ልጅ ጎጆ ቤት ገቡ፡፡ እኛም (መ/ት ወርቃፈራሁና እኔ) ለመቀመጫነት ከተደረደሩት የእንጨት  ዱካ እና ባርጩሜዎች ተቀመጥን፡፡ የአዋቂው ታዛዥ አገልጋዮች በሌማት የድፎ ዳቦ ጉማጅ በሽክና ጠላ ይርዘውልን መጡ፡፡ እንድንበላና እንድንጠጣም ጋበዙን፡፡ ተጨንቀው ተጠበው ማስተናገዳቸውን ቀጠሉ፡፡ የቤቷ ዙሪያ ደስ በሚል ሽታ ባለው ጭስ ታፍኗል፡፡ ከአዋቂው ልጅ ጎጆ ውስጥ የሚያጉረመርም ፣ የአምልኮ ፀሎት የሚመስል ድምፅ ይሰማል፡፡ ለህክምና የመጡት ታማሚም አስታማሚም ሁሉም በዝምታ ተውጦ የአዋቂውን ስርዓታዊ የአምልኮ ድምፅ ያደምጣሉ፡፡ አንዳንዱም ሳይታሰብ እህ… እህ… እህ! የሚል ያልታሰበ ድምፅ ያሰማሉ፡፡ ታማሚዎቹ ወደ አዋቂው ልዩ ጎጆ ገብተው የሚታዩት/የሚቀርቡት በአመጣጣቸው ቅደም ተከተል ሳይሆን አዋቂው/ሐኪሙ በሚያዘው መሰረት “እገሌ የተባልክ/ሽ ግባ/ቢ ተፈቅዷል” በሚል ትዝዛዝ እንጂ በወረፋ አይደለም፡፡ በዚህ መሰረት ለመታየት የመጣው ሁሉ በትዕግስትና በሙሉ እምነት ፣ ያለምንም ማጉረምረምና ጫጫታ መጠራታቸውን ይጠባበቃሉ፡፡ ተጠርተው የሚገቡት ተመርጠው በመጠራታቸው ሁሉም ታማሚና አስታማሚ ይደሰታሉ፡፡ “እድለኛ ነው/ናት እሱ አሁን ከህመሙ ተፈወሰ ፣ ዳነ ፣ ተገላገለ ፣ ይላሉ ቀሪዎቹ፡፡ ከሳቸው ከገባ በቃ ምህረትን ፈውስን የሚያገኝ ነው ብለው ቀድመው ያሳውቁታል፡፡ የማይድነው ሰው እንዲጠራ አይደረግም አዋቂው ቀድመው በመንፈስ ያውቁታል ፤ ውቃቢያቸው የማይድነውን ሰው እንዲጠራ አያደርግም ይላሉ ፤ ለህክምና የተሰባሰቡት ታማሚም አስታማሚም በአንድ ድምፅ፡፡

አዋቂው ሁሉም በሽተኞች እንዲሰሙ ዘለግ ባለ ድምፅ የአስተናባሪውን ስም ጠራ፡፡ ሶስት ጊዜም የጭብጨባ ድምፅ ተሰማ ፤ አስተናባሪው የሶስት ሰዎችን ስም ጠራና ፣

ግብራችሁን ከፍላችሁ ተፈቅዷል እና ወደ ውስጥ ዝለቁ አፋችሁ ከሀሜት ልባችሁ ከክህደት የጠራ መሆኑን ታመኑ ፤ በማለት በተጠሩበት ቅደም ተከተል ሶስቱንም አስከትሏቸው ገቡ። እነዚህ በመጀመሪያ ላይ የቀረቡት ሁለት ሴቶችና አንድ በ40 ዓመት የሚገመት ሆዱ የተቀፈተተ አርሶ አደር ገበሬ ናቸው። ከሁለቱ ሴቶች አንዷ ነፍሰጡር ስትሆን ሰባት ወሯ እንደሆነ ይዟት የመጣው ባለቤቷ ነግሮኛል። የመጣችውም እየወለደች እየሞተባት ስለሆነ በመቸገሯ ነው። ሶስት ጊዜ አርግዛ በሰላም ከተወለዱ በኋላ ወዲያው እንደተወለዱ ወይም ከአንድ ሁለት ቀን በኋላ እንደሞቱባት ባለቤቷ አቶ በለጠ ሽፈራው ነግረውኛል። እንደ አቶ በለጠ ሽፈራው ገለፃ በባህላችን ይህን ዓይነት ተወልዶ እንዳያድግ የሚያደርግ በሽታ የመንግስት ሐኪም አያድነውም። ይህ በሽታ በባህል ሐኪም/አዋቂ ነው የሚድነው መባልን ስለሰማን ይኼው ዛሬ ተሳክቶልን ዕድለኛ ሁነን በአዋቂው ተጠርተናል። ባለቤቴ እንባዋ እንደሚታበስ ወልዳ እንደምታቅፍ ልጅ እንደሚሰጡን አምናለሁ። ብዙ እናቶችን እንደታደጉ ሰምቻለሁ። ዛሬም ከዚህ ሁሉ ታማሚ በቅድሚያ መጠራቷ ምስክር ነው ፤ ሰውየው መቼም አያብልም ፤ እያለ እየነገረኝ ሳለ ነፍሰጡር ሚስቱ ገብታ ሁኔታውን ተናግራ በሰላም እንደምትወልድና እንደምታሳድግ ተነግሯት እና በጋራ ባልና ሚስቱ የሚቀምሱት መድሃኒት እንዲሰጧቸው ተናገረች። ባሏም አቶ በለጠ ባለቤቱን ዓለምወይ /ዓለም[54] ነው ስሟ) መቼም ሰውየው የሚሳናቸው ነገር የለም ፤ ለመሆኑ ይህ አስጨንግፋ/የማያሳድግ በሽታ ስሙን ነግረውሻል? በማለት ጠየቋት ፤ ወ/ሮ ዓለምም አዎ! የሴት ዛር መቆጣት ነው ፤ የአንቺና የባልሽ የላይትላይ አይስማሙም ይፎካከራሉ የኔ ይበልጥ የኔ ይበልጥ እየተባባሉ በውስጣቸው ላይ ይጣላሉ ፤ እና የጠቡ ፉክክር በሚወለደው/በምትወልጂው ልጅ ላይ መጥፎ ነገር ይፈጠራል ፤ በዚህ የተነሳ ልጁ ይሞታል። አዎ! ስሙም "ሾተላይ" ተብሎ ይጠራል አሉኝ። የሰጡኝ መድሃኒት የውስጣችንን የውቃቢ ጠብ የሚሽርና የሚያስማማ እንደሆነ ነገሩኝ። መድሃኒቱም የሚቀመሰው በቀይ ጤፍ ቂጣ ነው። ዱቄቱ ውስጥ ተዋህዶ ከዚያ ተጋግሮ ሌሊት በሰባት ሰዓት ላይ ሽንታችሁን ሳትሸኑ ፤ በቃል ድምፅ ሳታሰሙ ፊት ለፊት ሳትተያዩ ጀርባ ለጀርባ ተሰጠጥታችሁ ብሉት ፤ ከዚያ ተመልሳችሁ ተኙ። ከዚያማ በቃ! ልጃችሁ በጊዜው ተወልዶ ያለምንም

[54] ዓለም ታከለ በአዋቂው ቤት ለህክምና የመጣች የደሃና ወረዳ ነዋሪ ስትሆን "ሾተላይ" በመባል የሚታወቅ ህፃን እንዳያድግ የሚያደርግ ገዳይ በሽታ ታካሚ ሆና የመጣች።

ችግር ያድጋል ፤ አይዟችሁ ብለው ሆዴንም ጀርባየንም በጃቸው አሻሽተው አሰናበቱኝ (ዓለም ታከለ ፣ ቃመ. 20/10/2010 ዓ.ም)፡፡

አዋቂው በዕለቱ የመጡትን ታማሚዎች በዚህ ሁኔታ ወደ ልዩ ጎጆ ቤታቸው እያስገቡ ሲያክሙ ሲመክሩ ዋሉ፡፡ የተለያየ ህመም ያለባቸው ታማሚዎች በአብዛኛው በአዋቂው የሚነገራቸው የህመማቸው ዓይነት የአባት እናት ውቃቤ ነው ፤ የሴት ዘር መቆጣት ነው ፣ የውቃቢ ቅጣት ነው ፤ የሚል ሲሆን ለሁሉም የበሽታ የህመም ዓይነቶች ላም ፣ ጥጃ ፣ ቀይ ዶሮና ልበ ወርቅ ሴት ዶሮ አዙረህ ወይም አዙረሽ በቤትህ/ሽ ይቀመጥ የሚል ትዕዛዝ ይዘሰጣል፡፡ ታማሚዎቹ የተነገሩትን በፍጹም እምነት ተቀብለው ይፈፅማሉ ፤ ሲፈወሱም ይታያል ፤ ይፈወሳሉም፡፡

ሌላው አስገራሚ ነገር በሽተኛው አዋቂው መድሃኒት ነው ብሎ የሚሰጣቸውን ያለምንም መጠራጠር ያቀበሉታል፡፡ እንደሚድኑም በፍጹም አይጠራጠሩም፡፡ አዋቂውም በተመሣሣይ መልኩ የበሽተኞቹን ሰውነት ሲያሻሹ ፣ ሲደባብሱና ሲነካኩ የመጠየፍ ፣ የመሽከክ ወይም ስሜታቸው የመለዋወጥ ሁኔታ አይታይባቸውም፡፡ አዋቂው ዘንድ ለህክምና የሚመጡ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በሰውየው ቃል አምነው ከማንኛውም አካላዊና መንፈሳዊ ርኩስት ፀድተው ነው፡፡ ከማንኛውም ሀሜት ፣ ጥርጣሬና ሀኬት ሁሉ መፅዳት እንዳለባቸው አምነው ነው ወደ አዋቂው ጋር ለፈውስ የሚመጡት፡፡

ከታካሚዎቹ መካከል በመምረጥ ስለበሽታውና ስለ ህክምናቸው ጠይቂያቸው ነበር፡፡ አንድ ከደሃና ወረዳ ለመታየት የመጡት ወ/ሮ ሙቀት ወንዴ አዋቂው ጋ የመጡት ሆዳቸውን ታመው ነው፡፡ የሚያመኝ ሆዴን ነው ይነፋኛል ፣ ይወጋኛል ፣ ማህፀኔን ይሸቀሽቀኛል ፣ ምግብም መብላት ይከለክለኛል ፤ ብዙ ቦታ ሐኪም ቤት ሄጀ ብታከምም ጭራሽ እየባሰ ሄደ ፤ ምግብ ሁሉ ሲሸተኝ ሊያስመልሰኝ ሁሉ ይፈልጋል ፤ ቆይቶም ውጋት ሁሉ ጀመረኝ ፣ መንቀሳቀስ አልቻልኩም ፣ አልጋ ላይ አስቀረኝ እንጂ መዳን አልቻልኩም ፤ ሀኪም የሰጠኝ ክኒን ብውጠው ብውጠው ሆዴን ጭራሽ አቆሰለው አውንጂ መዳን አልቻልኩም፡፡ ሲጨንቀኝ እዚህ መጣሁ፤ አሁን ይሔው እንደምታየኝ ሆዴን ወገቤን ዙሪያውን በእራፊ ጨርቅ በተጠቀለለ መድሃኒት አዋቂው ሲያሽኝ ተሻለኝ ፣ በሰው ተደግፌ ለሁለት ተጋግዘው ነው ሰውየው ጋ ያስገቡኝ ታሽቼ ተነካክቼ ስጨርስ በራሴ እግር ያለምንም ደጋፊ ወጣሁ፡፡ አሁን በጣም ተሽሎኛል ፤ የሚሰማኝ ስቃይ ሁሉ የለም፡፡ እሳቸው ዘንድ መምጣት ከጀመርኩ ዛሬ ሁለተኛ ቀኔ ነው በጣም

ተሽሎኛል። እንደልብ መሄድና መንቀሳቀስ ችያሁ ፤ ምግብም መብላት ችያለሁ (ወ/ሮ ሙቀት ወንዴ ፣ ቃመ. 20/10/2010 ዓ.ም) በማለት የአዋቂውን ፈዋሽነት አስረዱኝ። አቶ እሸቱ አበራ ደግሞ የመጡት ልጃቸውን ሊያሳክሙ ነው ፤ ልጁም 10 ዓመት ዕድሜ ያለው ነው ፤ የታመመ መሆኑ በግልፅ ይታወቃል። በጣም ክስት ያለ ዓይኖቹ በጣም የረገቡ እና ጉድጉድ ያሉ ሆነው ሆዱ ከሌሎቹ የሰውነት ክፍሎች ውጥር ያለና የተነፋ ወይም ያበጠ ነው። አባትዬው ስለህመሙ ሲናገር፡-

> … ምግብ በሚገባ ይበላል ፤ የሚጠላው የለም በልቶ ግን ብዙም ሳይቆይ ይርበዋል ፤ እንጀራ ስጡኝ ነው ፤ ይሰጠዋል ይበላል ወዲያው በላ በላ አድርጎ ይተዋል ፤ መልሶ ይጠይቃል ይበላል ፤ ይሔው ሆዱ ከመቆዘር/መነፋት/ማበጥ በቀር ሰውነቱ አይጠራቃ ፊቱ አይወዛ እንደምታየው አመዱን የነፋበት ይመስላል። እያደር ሆዱ እየተቆዘረ ፣ ሰውነቱ እየጫጫ ፊቱ እየገረጣ መጣ እንጂ ለውጥ የሚባል ነገር ጠፋ። ሐኪም ቤት ወስጄ አስመረመርኩት ወስፋት ነው ብለው የሚዋጥ ክኒን ሰጡት ሊሻለው አልቻለም። ጤና ኤክስቴንሽኖች ጋ አሳየሁት እነሱም ወደ ሐኪም ቤት ጤና ጣቢያ ላኩኝ። እነሱም ወስፋት ነው ፤ የተሰጠውን መድሃኒት ይውሰድ ከዚያ ይድናል አሉኝ ፤ ግን አልዳነም። አሁን እዚህ አዋቂው ጋ ይዤው መጣሁ ፤ እሳቸውም ሰውነቱን በሙሉ እያገላበጡ በሆነ በነጭ እራፊ ጨርቅ በተጠቀለለ ነገር አሹት። በባዶ እጃቸውም በጣም አጥበው ምራቃቸውን እትፍ ፣ እትፍ እያደረጉ አሹት። ከዚያም ይኼው ሆዱ ላይ የምታየውን በፈትል ክር መድሃኒት አሰሩለት። እንደሚድንልኝም አመንኩ ይድናል ወስፋቱ ነገ ዝርግፍግፍ ብሎ ይወጣል ብለውኛል ፤ ይድናል (አቶ እሸፈቱ አበራ ፣ ቃመ. 20/10/2010 ዓ.ም)።

እንደ አቶ እሸቱ አበራ እምነት ልጁን ጤና ጣቢያ ወስደው ፈውስ ስላላዩ የሚድነው በባህላዊ ሐኪም/አዋቂ/ እንጂ በዘመናዊ ህክምና አይደለም። የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን ጠይቀው ወደ ሀኪም ቤት ጤና ጣቢያ ውስደው ተብለው ቢወስዱትም በተሰጠው ክኒን ሊድን ባለመቻሉ ከዘመናዊው ህክምና ይልቅ በባህላዊ አዋቂው ተማምነው ነው ልጃቸውን ይዘው የመጡት። አቶ እሸቱ አበራ አዋቂው ጋ ልጃቸውን ይዘው የመጡት በዘመናዊ ሐኪም ቤት በተደጋጋሚ ወስደው ሊድንላቸው ባለመቻሉ አዋቂው ጋር ሌሎች የሳቸው ልጅ ዓይነት ህመም የታመሙ መዳናቸውን ስለነገሯቸው

ነው፡፡ በዚህም አምነው ልጃቸውን ከአዋቂው ጋር አምጥተው በማሳከማቸው እንደሚድንላቸው ተማምነው በሙሉ ልብ ይድናል በማለት አምነዋል፡፡ በመሆኑም እንደሳቸው ሁሉ ልጃቸው የታመመባቸው ሰዎች ወደ ጤና ጣያ ወስዶ ማሳከም ፈውስ ሊያገኝ እንደማይችል ተረድተው ወደ ባህላዊ ሐኪም/አዋቂ ዘንድ መውሰድ የበለጠ እንደሆነ እምነት እንዲኖራቸው ሁኗል፡፡

አቶ ሞገስ ገ/ኪዳን ሌላው የአዋቂውን ፈውስ ፈልገው የመጡ ናቸው፡፡ በሽታቸው ራሳቸውን ውጥር አድርጎ ይዞ ማንቀሳቀስ እያቃታቸው ቀና ብለው ሰው ለማየት እንኳ ስላቃታቸው ተኝተው ለመዋል ለማድር እስኪገደዱ ድረስ ታመው ነበር፡፡ ሐኪም ቤት ሄደው ህክምናም ሞክረዋል፡፡ ገንዘብ ከመጨረስ ውጪ ምንም ስላልፈየደላቸው ወደ አዋቂው አቶ ደሳለኝ ታደሰ ለመታከም መጡ፡፡ ሁለት ቀናት እየተመላለሱ ህክምናውን እንደወሰዱ ጤናቸው ተሻሽሎ ራሳቸው ድነው መራመድ እነደጀመሩ በደስታ ፈገግ ብለው ይገልፃሉ (ቃመ. 20/10//2010 ዓ.ም)፡፡

ወ/ሮ ዓለም ወርቅ ጌታሁን እንዲሁ እያመማቸው ብዙ ጊዜ የባህል መድሃኒቱንም ህክምናውንም ሲሞካክሩ ቆይተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ምንም የመሻል ምልክት አላዩም፡፡ እሳቸው እንደሚሉት የሚያማቸው ጣቅላላ የሰራ አካላታቸውን ሁለመናቸውን እንደ እሳት እየፈጃቸው እያቃጠላቸው ያስቃያቸዋል፡፡ ልባቸው ይደክማል፡፡ ዓይናቸውንም ይጋርዳቸዋል፡፡ ጤና ጣቢያ ሄደው የሰጧቸው መድሃኒት አላሻላቸውም፡፡ አሁን አዋቂው ጋ ይሻለኛል ብለው እንደመጡ ይናገራሉ (ቃመ. 20/10/2010 ዓ.ም)፡፡

አራቱም ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሰዎች እንደሚናገሩት ገንዘባቸውን ፣ ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን ከመጨረስ ውጪ ዘመናዊ ህክምና ላለባቸው የጤና ችግር መፍትሔ አላመጣላቸውም፡፡ ስለሆነም በአዋቂው ህክምና ላይ ተማምነው ፈውስ ፍለጋ መጥተዋል፡፡

የክልሉ መንግስት ይሔን አመለካከት በሁሉም ህብረተሰብ ዘንድ ያለ መሆኑን በአፅንኦት የሚያነሳው ተግዳሮት ከላይ በተጠቀሰው ዕቅድ ውስጥ የሚገኘው በሽታን በዘመናዊ መንገድ በመከላከልና በዘመናዊ ሕክምና መፈወስን ሳይሆን ክልሉ ያልተማከለ የጤና አገልግሎት ርስዓትን በመዘርጋት በሶስት ዋና ዋና ምሰሶዎች /የላቀ የጤና መሰረተ ልማት የጤና አገልግሎትና አመራር ፣ እንዲሁም የጤናው ዘርፍ ልማት ፕሮግራም

በአምስት ዓመቱ የእድገትና ትርነስፎርሜሽን እስትራቴጂክ እቅድ ሊከናወኑ ከተያዙት የልማት ሰራዊት ግንባታ ፣ የአካባቢ ጤና አጠባበቅን ማሻሻል ፣ እየናቶችን ጤና ማሻሻል ፣ የህፃናትን ሞት መቀነስ ፣ በሽታዎችን መከላከልና የጤና መሰረተ ልማት ተደራሽነትን ማሻሻል የተባለው ነው፡፡ ማህበረሰቡ ደግሞ ከዘመናዊው ይልቅ ባህላዊው ፈውስ ውጤታማ ነው ይላል፡፡ በሁሉም ህብረተሰብ በባህላዊ ህክምናና በአዋቂ/በጥንቆላ የማመን ሁኔታ አለ፡፡ ፈውስ የሚያገኙት በዘመናዊ ህክምና ሳይሆን በባህላዊ ህክምና እና ጠንቋይ/አዋዊ ዘንድ በመሄድ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ወደ ጤና ተቋም ሄደው መታከምን አይመርጡም ፤ ድኅነትን እንደማያገኙ ተረድተዋል ፤ አምነዋል፡፡ ይሄ እንደ ችግር የቀረበ ጉዳይ በእርግጥ ችግር ነው? ማህበረሰቡ በባህላዊ ህክምና ታክሞ አይድንምን? ለባህላዊ መድሃኒቱና ለአዋቂዎቹ የሚሰጠው ቦታ ምን ይሆን? የሚሉት ጥያቄዎች ሲነሱ የአስተሳሰብ ተቃርኖው በጉልህ የሚታይ ይሆናል፡፡ ማህበረሰቡ እስከ ዛሬ ድረስ ጠንቋዩን እና ዩባህል መድሃኒት አዋቂውን አቶ ደሳለኝ ታደሰኝ[55] የመሰሉ ባህላዊ ሃኪሞች የሚሰጡትን መድሃኒቶች እየተጠቀመና እየተፈወሰ ኖሯል፡፡ አሁንም በእነሱ እየታከመ ነው፡፡ ከዘመናዊው ህክምና ይልቅም እነሱን እንደሚመርጥ የሚያሳየው በገጠር ጤና ተቋማት የሚታየው የሰው ብዛት በጠንቋዩ ግቢ ተሰባስበው ወረፋ እየጠበቁ ሲታይ ነው፡፡

መሪጌታ ሰሎሞን ደስታ የባህል መድሃኒት አዋቂ ናቸው፡፡ እሳቸው እንደሚሉት በባህላዊ መድሃኒታቸው ነቀርሳንና ወባን ጨምሮ አሉ የተባሉትን በሽታዎች ይፈውሳሉ፡ ፡ ፈውሳቸው ደግሞ በጤና ባለሙያዎች ሳይቀር የተረጋገጠ ነው፡፡ እሳቸውና መሰሎቻቸው በሚሠጡት መድሃኒት ያበደው ሁሉ ድኖ ትዳር መስርቶ ሲኖር መመልከታቸውን ይናገራሉ፡፡ ለማስረጃነት የሚከተለውን እንመልከት፡፡

> ሰው ሲታመም መድሃኒቶች አዘጋጅቼ ለታማሚው ራሴ ነኝ የማቀምሰው፡፡ የታመመው ሰው በራሱ መምጣት የሚችል ከሆነ ምኑን እንደሚያመው እንዴት

[55] አቶ ደሳለኝ አዋቂ/ጠንቋይም የባህል መድሃኒት ቀማሚም ናቸው፡፡ ሁለቱንም ይሠራሉ፡፡ የተለያዩ የመድሃት ዕፆችን ቅርፊቶችን ወዘተ ለልዩ ልዩ በሽታዎች መፈወሻነት ይጠቀማሉ፣ የዘር (መንፈስ) ህመም ነው፤ ብለው ደግሞ እንደ ፈልፋይ (ለይቶ ማወቅ) ደግሞ የበሽታዬን ሁኔታ ገልፀው በመናገር ምጥቻ አዙሪበተእ ቀይ ነጭ ጥቁር ዶ አርዳችሁ ብሉ ወዘተ እያሉ በሽታን ያስለቅቃሉ፡፡

እንደሚስማው ፣ መቼ እንደጀመረው ፣ እጠይቃዋለሁ። ያበጠ የቆሰለ የሚያሳክክ ከሆነ ሰውነቱን አያለሁ። ከዚያም መድሃኒቱን አዘጋጅቼ የሚጠጣ የሚታሽም ወይም በሰውነቱ ላይ የሚቀባም የሚታሰርም ከሆነ እያየሁ ራሴው በእጄ እፈፅማለሁ። መድሃኒቱን ከኔ ሌላ ሰው እንዲነካው አይፈቀድም። ለሁሉም በሽታዎች ሁሉ መድሃኒቶችን የመስጠት ወይም የመፈወስ ፀጋ ተሰጥቶኛል። እንኳንስ ታመው መጥተው ይቅርና በዚህ በዙሪያ ያሉት ሰዎች የታመሙ መሆናቸውን አውቃለሁ። ውስጤ ይነግረኛል ፤ ወይም በህልም አያለሁ። ካልወጡ ወደ ቤታቸው ሄጄ እጠይቃቸዋለሁ ፤ እነሱም ልመጣ ስል ፤ የፈጣሪ ነገር እርስዎ መጡ በማለት ህመማቸውን ይነግሩኛል። መድሃኒቱን እሰጣቸዋለሁ ፤ ይድናሉ። አሁን በቅርብ አንተ ከመምጣትህ በፊት አንድ ሰው ወጥቶ መድሃኒት ቆፍሬ ጨቅጭቄ ገላውን በሙሉ በመድሃኒቱ ውሃ አጥቤው የቆሰለውን ሰውነቱን በዚያው በመድሃኒቱ ቀብቼው ውስጤን ሁሉ በላኝ ተቃጠልኩኝ እያለ ነበር ፤ ያው አጥቤና መድሃኒቱን ቀብቼው አርፍ እንዲል አደረኩት ወዲያው እንቅልፍ ይዞታ ጭልጥ አለ። ከዚያም ሲነሳ እየመረቀኝ እያመሰገነኝ ወደቤቱ ሄደ። በሦስተኛው ቀንና ብየዋለሁ ፤ ታየዋለህ። ያሁሉ በቁስል የነገለው ሰውነቱ ድኖ ይመጣል። ራስህ ጠይቀህ ትረዳለህ። እኔ ጋ ታሞ የመጣ ሰው ከበሽታው ወዲያው ነው የሚድነው። ይህ ከቤተሰብ በዘር የተወረሰ ነው ፤ በጥሼም ሆነ ነቅየ ስሩን ቅጠሉን አሽቼ የምስጠው ሁሉ መድሃኒት ነው (መሪጌታ ሰሎሞን ደስታ ፣ ቃመ. 20/10/2010 ዓ.ም)።

ከመሪጌታ ሰሎሞን አባባል የምንረዳው ዘመናዊ ህክምና ያላደነውን በሽታ ሁሉ እንደሚፈውሱ ነው። ማህበረሰቡም ይህንን ስላመነና አይቶም ስላረጋገጠ ወደ ጤና ተቋማት ከመሄድ ይልቅ እሳቸው ዘንድ መታከምን ይመርጣል። የአእምሮ ጤና ችግር ገጥሟት በእሳቸው ህክምና የተፈወሰች ሴትን ታሪክም ነግረውኛል። ሴቷ እያስጎራትና እያስጮኻት ጨርቋን ቀዳ ያበደች እንደነበረች ነው። ቤተሰቦቿ ተጨንቀው ገደል ገብታ ትሞታለች ትጠፋለች እያሉ በመጨነቃቸው ቤት ዘግተውባት እጅ እግሯን አስረው ለሁለት ዓመት ደባቋት። ከዚያም በወሬ ወሬ መሪጌታ ሰሎሞን ሊያድኗት ይችላሉ ፤ ውሰዷት ወይም ለምናችሁ ተለማምጣችሁ እሳቸው መጥተው ይመልከቷት ተብለው እኔ ጋ መጥተው እጅግ አዝነው ሐኪም ቤትም ፀበልም አዋቂም/ጠንቋይ

መውሰዳቸውንና አለመዳኗን ነገሩኝ፡፡ ይገርምሃል ልጄ! በልባቸው ግን ላያድኗት ላትድን ይሔን ያህል መለማመጥ ይሉ ነበር እኔ አውቃለሁ ሀሳባቸውን ተረድቻለሁ፡፡ ምንም ሳልል ዝም አልኩ ፤ ቁርጡን ይንገሩን እባክዎ እንሂድና ይመልከቱልኝ ሲያዩዋት ያዝናሉ ፤ ምናምን እያሉ ተለማመጡ፡፡ እሺ! እናንተ ሂዱ እኔ ራሴ እመጣለሁ አልኳቸው፡፡ አላመኑም፡፡ ተከትያቸው ቤታቸው እኩል ገባን ደነገጡ፡፡ ስከተላቸው አላዩኝም፡፡ ልጅቷን ጠጋ ብየ ስመለከታት ከሰውነት ጎዳና ወታለች፡፡ ዓይኗን አፍጣ ከማየት በስተቀር አትናገርም፡፡ እነሱን ውጡ ብዬ በቀዝቃዛ ውሃ በጥብጬ ይዤው የነበረውን መድሃኒት ሶስት ጊዜ ግንባሯን ረጨኋት ዝርግትግት ብላ ተኛች ፤ ምንም ድምፅ አታሰማም፡፡ ከዚያ ያንኑ መድሃኒት አፏን ከፍቼ ጋትኳት፡፡ ቀሪውን ራሷንና ሆዷን አራስኳት፡፡ ምንም ሳትጮህ ድምፅ ሳተሳማ ጧ! ብላ ተኝታ ቆየች፡፡ እኔም ወጥቼ ከቤተሰቦቿ ጋር ቆየሁ፡፡ ከሶስት እስከ አራት ሰዓት የሚሆን ጊዜ ተኝታ ቆይታ ነቃች ፤ ከዚያም እኔና እሷ ማውራት ጀመርን፡፡ ቤተሰቦቿም ተገረሙ፡፡ በቃ ዳነች ጤናማ ሆነች፡፡ ይኼው ትዳር ይዛ ልጆች ወልዳ በሠላም እየኖረች ነው ፤ እኔንም እንደ አባቷ ነው የምትቆጥረኝ ፤ በበዓላት ጊዜ ሆነ በሌላ ጉዳዮች ሁሉ የምታየኝ የምጠይቀኝ ልጅ ሆነች፡፡ እኔም አባቷ ነኝ (መሪጌታ ሰሎሞን ፣ ቃመ. 20/101/2010 ዓ.ም)፡፡

ከመሪጌታ ሰሎሞን አገላለፅ የምንረዳው የአዕምሮ ጤና ችግር ገጥሟት በእሳቸው ህክምና የተፈወሰችው ሴት በመዳኗ ምክንያት በመካከላቸው የተፈጠረው ቤተሰባዊ ትስስር መጠጠሩን ነው፡፡ ይሄን ያህል ገንዘብ ተከፈለኝ ወይም አልተከፈለኝም ፤ የሚል የገንዘብ ክፍያ መደረጉን ሳይሆን ወዳጅነት ቤተሰባዊነት ዝምድናን ማጠናከሩን ነው፡፡ በዚህም የመፈወስ አቅማቸውን የበለጠ የሚያጠናክርላቸው መሆኑን ነው፡፡ በሙያቸው ተጠቅመው ሰዎችን የመበዝበዙ ሳይሆን በማዳናቸው በሰዎች ዘንድ ክብርንና ዝናን ማግኘትን ብቻ ነው፡፡ ትኩረታቸው መፈወሱ ላይ እንጂ ገንዘብ ስለማግኘትም አይደለም፡፡ ለዚህም ነው ማዳናቸውን እንጂ የሚያገኙትን ገንዘብ አስበው አይደለም ፤ ስንት ትከፍለኛለህ ወይም ታስከፍለኛለህ የሚል ምልልስ የማይሰማው ታማሚው ሲድን የፈለገውን ያህል የገንዘብ መጠን ወይም የቁም እንስሳ/ወይፈን ፣ የፍየል ወጠጤ ፣ ወይም ሌላ የእህል ዓይነት/ጤፍ ፣ ማሽላ ፣ ስንዴ ወዘተ በባህሉ የመለኪያ መጠን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ የባህል መድሃኒት አዋቂው ግን መጥኖ “ይህን ያህል” ስጠኝ አይልም፡፡ መሪጌታ ሰሎሞን ይህን አስመልክተው “ሰውን ያህል ታሞ እያጣጣረ እየተሰቃየ ስለ

ክፍያ መጠየቅ ሰው መሆንን መዘንጋት ነው ፤ ፈውስን ሲያገኝ ራሱ ደስ ሲለው የሚደርስ ነገር ነው (ቃመ. 20/10/2010 ዓ.ም)፡፡ በዚህም የተነሳ በባህል መድሃኒት አዋቂውና ታማሚው መካከል ከፍተኛ መተማመን አለ፡፡ ታማሚው እንደሚድን እንጂ የመዳን እድል የለኝም ብሎ አያምንም፡፡ አዋቂም አይከፈለኝም ብሎ አያስብም ፤ ይኼን ማሰብ ትተው ህክምናውን መፈፀም ላይ ያተኩራሉ፡፡ በዘመናዊው ህክምና ግን ለህክምና የተከፈለውን ገንዘብና መድሃኒት የተገዛበትን ብር ባይሻለው የሚመልስለት ሰው የለም፡፡ ይህም በመሆኑም ከዘመናዊው ህክምና ይልቅ በባህላዊው ህክምና ተማምኖ ወደዚያው መሄድን ይመርጣል፡፡ ከላይ እንደታየው በብሔረሰቡ ባህል መዋሸት ነውር በመሆኑም ብሩን ለማስመለስ ብሎ አልተሻለኝም የሚል ሰው አይኖርም፡፡ ይህ የሚያመላክተው ማህበረሰቡ በእያንዳንዷ ሁነት እርስ በእርሱ ተማምኖ እንዲኖር ያደረገው የባህሉ ጥንካሬ ነው፡፡ ስለዚህ በቅንነት ፣ በታማኝነትና በሀቅ የሚያገለግሉት መርጌታ ሰሎሞን እያሉ ብዙ ወጪና እንግልት የሚያስከትለውን ህክምና የሚርጥ ሰው የለም፡፡

ይህንን የብሔረሰቡን የጠነከረ ባህልና እምነት ኋላቀር አመለካከትና ችግር በማለት ብቻ ከዕምነቱ ለማላቀቅና ወደሚፈለገው ግብ ለመድረስ የሚቻል አይደለም፡፡ መፍትሔውም በአመለካከት ትግልና በኮንፈረንስ ብቻ የሚመጣም አይመስልም፡፡ ይልቁንም የብሔረሰቡ ማንነት ለተገነባበት ባህል ፣ ሀገር በቀል ዕውቀትና ልማድ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ማጥናትንና ራሱን መሰረት አድርጎ የአካባቢውን ልማት ለማምጣት ተግቶ መስራትን ይጠይቃል፡፡

ልክ እንደ መሪጌታ ሰሎሞን ሁሉ የጠንቋዩን ፈውስ ፈልገው የሚሄዱት ሰዎች ለሚሰጣቸሰው አገልግሎት የሚከፍሉት/የሚሰጡት ገንዘብ አነስተኛ ነው፡፡ እዚያ በተገኘሁበት ወቅት ታማሚዎቹ/ታካሚዎቹ በህክምናው ቦታ በተቀመጠችው የገንዘብ ማስቀመጫ ሙዳይ የሚያዘስቀምጡት ገንዘብ በአብዛኛው አምስትና አስር ብር ሲሆን ቡና እና ስኳርም ሲሰጡም አይቻለሁ፡፡ አዋቂው ግን አነሰ ጨምሩ ሲሉ አልሰማሁም፡፡ አዋቂው የሚቀመጠው ብር ወይም ስኳርና ቡና የማን ፣ የማን እንደሆነ እንኳ ልብ ብለው ስለማያዩት አያውቁትም፡፡ ስለዚህ ታካሚዎቹ ፈውሱን ለማግኘት የሚያወጡት ወጪ አነስተኛ በመሆኑ ከዘመናዊው ህክምና የሚመርጡበት አንዱ ምክንያት እንደሆነ መረጃ ሰጪዎቹ ይናገራሉ፡፡ “ጤና ጣቢያ ብንሄድ ወረፋው ፣ የካርድ አውጪዎቹ ግልምጫ ስድብ እንግልቱ እንደዚያ ታመን እየተሰቃየን የሚያዝዙልን መድሃኒት

ለመግዛት ገንዘቡም ችግር ነው ፤ የመድሃኒት ዋጋ ብዙ ስለሚሆን ከዚያ ሄዶ ከመንግላታት እዚህ በቀላሉ እንድናለን ፤ ጠንቋዩ/ሰውየው አብረን ስለምንኖር ብዙ አያስከፍለንም፤ ከሌለን በነፃ ያክመናል" (ወ/ሮ ባዩሽና ሌሎችም ፣ ቃመ. 20/10/2010 ዓ.ም)፡፡

የታካሚዎቹ ሀሳብ ዘመናዊ ህክምናው የገንዘቡ ውድነት እና የአገልግሎቱም ተደራሽ አለመሆን ወደ ጤና ጣቢያ ለመሄድ ፍላጎት እንደሌላቸው የሚያመላክት ነው፡፡

ማህበረሰቡ ጤና ጣቢያ በየአቅራቢያው ቢኖርም ተመርምሮ የሚታዘዝለትን መድሃኒት መግዣ ከሌለው ወደዚያ ከመሄድ ይልቅ ወደ ባህላዊው ልማዱ ፊቱን ያዞራል፡፡ ይኼን ሳንረዳ ግን በጥንቆላና በባህል ህክምና የማመን ችግር ነው ብለን ባለመድሃኒቶችን ለማስቀረት ብንሞክር በአደባባይ ማድረጉን ትቶ በድብቅ ይከውነዋል እንጂ ፈፅሞ ለውጥ ማምጣት አይቻልም፡፡

የጤና አገልግሎት የሚሰጡትም ታቋማት ካለ ውጤት ተገንብተው ይህን ያህል ገንብተናል ለማለት ብቻ የሚያበቁ የሪፖርት ፍሬዎች ብቻ እንጂ የሚታሰበውን ጤናማ ማህበረሰብ ከመገንባት አኳያ የሚኖራቸው ፋይዳ ከቁጥር የሚገባ አይሆንም፡፡

Cumming እንደሚሉት ድህነት ኢኮኖሚውን በማዘመን ብቻ ሊቀረፍ የሚችል የታሪካዊ ኋላቀርነት ውጤት ሳይሆን ይልቁንም "ምዕራቡ በደቡቡ" ላይ የፈጠረው ዘዴያማ የቅኝ ግዛት ውጤት ነው ፤ ለልማት ስትራቴጂዎችና ፕሮጀክቶች አለመሳካት በምክንያትነት የሚነሱ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ጉዳዮች ሳይሆኑ በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ውስጥ ያለው የባህል ልዩነትን ከዚህ አንፃር ማህስበረሰቡ የሚኖረው ፍላጎት ነው (Cumming, 1990)፡፡ ይህን የCummingን ዓለማቀፋዊ እሳቤ ወደ ተነሳንበት ጉዳይ ብናመጣው የክልሉ መንግስት የሚያነሳቸው "በሽታን በዘመናዊ መንገድ በመከላከልና በዘመናዊ ህክምና መፈወስን ሳይሆን በሁሉም ህብረተሰብ በባህላዊ ህክምናና በጥንቆላ የማመን ችግር አለ" ከሚለው ሃሳብ ጋር በቀጥታ የሚዛመድ ነው፡፡ የማህበረሰቡ ጤና እንክብካቤ ሁሉን በአንዴ በማዘመን የሚፈታ ነገር አይደለም፡፡ ይልቁን በአካባቢው ያሉትን ባህላዊ እሴቶችና በዚያም ላይ የሚመሰረተውን የማህበረሰቡን ፍላጎትና እምነት እንዲኖር ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ፈትሾ ማቀድ የተሻለ ይሆናል፡፡

### 6.2.2. የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትና ተግዳሮቶቹ

ባህል የማህበረሰቡ መሰረት የሆነው ቤተሰብ እንዲመሰረት ትውልድ እንዲቀጥልና እንዲሰፋ ዋነኛ ጉዳይ የሆኑት ልጆች እንዲወለዱ የሚያደርገው እገዛ ብዙ ነው፡፡ እያንዳንዱ ባህል ልጆችን የሚያያቸው የቤተሰቡ በረከት አድርጎ በመሆኑ ልጆች ሲረገዙ የተለየ ደስታ ይሆናል፡፡ ለእናቶቻቸውም ሆነ ለህፃናቱ የተለየ እንክብካቤ ያደርጋል ፤ እናታቸው በእርግዝናዋ እንዳትጎዳ ጤናዋ እንዳይታወክ ባህሉ የሚፈቅድላትን የመከላከያ ዘዴ ትጠቀማለች ፤ በአራስነቷ ልዩ እንክብካቤ ይደረግላታል ፤ እሷም ሆነች ልጇ ምንም ነገር እንዳይተናኮላቸው ጥንቃቄ ይደረግላቸዋል፡፡ ለመታረስ የምትቆይበት ጊዜ ወይም ለስራ በምትሰማራበት ወቅት ሁሉ በዋግኽምራ ባህል ልዩ ልዩ እንክብካቤዎች እንደሚደረግላት ከላይ ባሉት ክፍሎች በስፋት ተገልጧል፡፡

በተጨማሪም በዋግኽምራ ብሔርሰብ ልጆች ትውልድ እንዲቀጥል ዘር እንዲበዛ የሚያደርጉ በመሆናቸው ልጆች እንዲወለዱ ባህሉ ያበረታታል፡፡ ልጅ ሲወለድ ስራ ያግዛል ፤ ሲታመሙ ያስታምማል ፤ ሲያረጁ ይጦራል ፤ ሲሞቱ በክብር ይሸኛል ፤ በመሆኑም ባህሉ ልጆችንና ወላጆችን በሚገባ ይንከባከባል፡፡ በተጨማሪም የሚስት ዋነኛ ተግባር ልችን በመውለድ ዘርን መተካትና ትውልድን ማሰርቀጠል እንደሆነ በባህሉ ይታመናል፡፡ የማህረሰቡ ባህል እንዲህ ሆኖ ሳለ ወደ 16 ከሚደርሱት የጤና ኤክስቴንሽ ፓኬጆች ውስጥ አንዱ የሆነው የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ፓኬጅ የቤተሰብ ምጣኔን ያስተምራል፡፡ የፓኬጁ አጠቃላይ ዓላማ ማንኛውም ቤተሰብ ከገቢውና ከማስተዳደር አቅሙ በመነሳት ልጆችን መጥኖና አራርቆ እንዲወልድ የሚያደርግ ነው፡፡ ለተግባራዊነቱም መንግስት በገጠር የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን በማሰማራትና ኅብረተሰቡን በማስተማር ለቤተሰብ ምጣኔ የሚረዱ የወሊድ መከላከያ ዘዴዎችን በማደል መጥነውና አራርቀው እንዲወለዱ የማድረግ ተግባር እያከናወነ ይገኛል፡፡ ይህ ተልዕኮ በክልሉ እንደ አጠቃላይ መጠነኛ ተቀባይነት ቢያገኝም በዋግኽምራ ብሔረሰብ ግን ተግዳሮት እንደገጠመው ከላይ ከተመለከትነው የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽ ዕቅድ መረዳት ይቻላል፡፡

በዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህል ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ከደረሰ ሚስት ማግባት የግድ ነው፡፡ ከዚያም ከሚስቱ ልጆችን መወለድ ደግሞ ዋናው መሰረታዊ ነገር ነው፡፡ የሚወልዳቸውን የልጆች ብዛት ግን ወስኖና አቅዶ ይህን ያህል ብቻ ነው ብሎ አያቅድም፡፡ ስለአስተዳደጋቸው ብዙም አይጨነቅም፡፡ ልች የእግዚአብሔር ስጦታዎች

ናቸው የሚል እምነትም ስላለ ይወለዱ እንጂ "በዕድላቸው ያድጋሉ" የሚለው አስተሳሰብ በባህሉ የሰረፀ ልማዳዊ እሳቤ ነው፡፡ ሲያድጉ ቤተሰብ ይረዳሉ ፤ ሲታመሙ ያስታምማሉ፤ ስለዚህ ይወለዱ እንጂ ስለአስተዳደጋቸው ብዙም የሚያስጨንቅ አይደለም፡፡ ከዚህ የተነሳ እናቶች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ባሎች እንደሚከለክሉ እና ሴቶችም/ሚስቶችም ቢሆኑ እንደማይፈልጉ መረጃ ሰጪዎች ያስረዳሉ፡፡ "የአንቺ ሚስትነት የሚረጋገጠው ስትወልጂ ብቻ ነው ፤ የማትወልድ ሚስት ዘረቆርጥም ትባላለች ፤ ካልወለድን ልክ ባል እንደሌለን እንቆጠራለን ፤ በቃ ደጋግመን መወለድ ነው ፤ ደሞ ልጅ ፈጣሪ የሚሰጠውና የሚያሳድገውም የፈጠረው አምላኩ ስለሆነ እንደፈለግን ብንወልድ ችግር የለውም ፤ ልጅ ሲሳይ /ሀብት ነው ፣ ራሱ ይዞት የሚወለድ ዕድል አለው" (ቡ.ው.ይ ሰቆ.ዙሪያ ፣ 24/10/2010 ዓ.ም)፡፡

ከላይ ባየናቸው ትልልቅ ባህላዊ ጉዳዮች ምክንያት የቤተሰብ ምጣኔ ፣ አራርቆ መውለድ የሚባሉ ጉዳዮች በብሔረሰቡ ዘንድ ሰሚ ያገኙ አይመስሉም፡፡ የብሔረሰቡ መስተዳድር ባለሙያዎች "ከኋላ ቀር አስተሳሰብ ጋር የተያያዘ አመለካከት ችግር ነው" ይበል እንጂ መሠረቱን ስናየው ባህላዊ ተግዳሮት በመሆኑ የሚፈታው ባህሉን ጠንቅቆና በዚያ ላይ ጠንክሮ በመስራት እንደሆነ ከመስክ የተገኙት መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ "ከፍተኛ የግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ የአመለካከት ትግልና በምንፈጥራቸው ሞዴሎች አማካይነት ሙሉ ለሙሉ አመለካከቱን እናስወግዳለን" ተብሎ የቀረበው የመፍትሔ ሃሳብ ብዙም የሚያዋጣ አይመስልም፡፡

የዋግኽምራ ወንድ ሚስቱ የማትወልድ ከሆነ ፈትቷት ሌላ ልጅ የምትወልድ ሴት ያገባል፡፡ አቶ ተመስገን መውለድ አልቻለችም ያላትን ሚስቱን ፈቶ ስድስት ልጆችን አፍርቷል፡፡ አሁን ደግሞ እሷን ፈት ሌላ ሶስተኛ ሚስት ሊያገባ ወላድ ሴት እያፈላለገ ነው፡፡ እኔ ብዙ ልጆች እንዲኖሩኝ እፈልጋለሁ፡፡ ዘሬ እንዲበዛ ስሜ እንዲጠራ አጥብቄ እሻለሁ፡፡ በባህላችንም በሃይማኖትም አንድ ሚስት ብቻ ነው ማግባት ስለፈተባለ እንጂ ሁለት ሶስት ሚስቶችን አግብቼ ልጆችን መወለድ ነው የምሻው፡፡ በዚህም ምክንያት የመጀመሪያ ሚስቴ የማትወልድ ሆነች ፈታሁ ፤ ሁለተኛዋ ደግሞ ስድስት ወልዳ ቀጥ አለች፡፡ ሶስተኛዋን ላገባ ይሔው እየፈለኩ ነው ፤ ባይከለክ ያቺንም ሳልፈታ ይህችንም ደግሜ ሳልፈታ ፤ ሶስተኛዋን አግብቼ እወልድ ነበር፡፡ ልጅ ፀጋ ነው ፤ አራርቃችሁ አቅዳችሁ ውለዱ ፣ ሁለት ብቻ አንድ ብቻ እያሉ የማይረባ ነገር ይነግሩናል ፣ እንዴት

አትውለዱ አትዋለዱ ይላሉ! ልጅ እኮ የፈጣሪ ስጦታ ነው! አልፈልግም ይባላል እንዴ?" (አቶ ተመስገን ጌታዋ ፣ ቃመ. 24/10/2010 ዓ.ም)፡፡ አቶ ተመስገን እንደሚለውና ከላይ እንደተመለከተው የጤና ኤክስቴንሽ ፓኬጆቹን ለማስተግበር ከፍተኛ ችግር የገጠመው ቢሆንም በሰቆጣ ወረዳ ስሬ ቀበሌ እና ሰላምጌ ቀበሌ የሚገኙት የጤና ኤክስቴንስን ባለሙያዎች ግን እነሱ በሚሰሩባቸው ቀበሌዎች ያሉት አርሶ አደሮች ፓኬጆችን በሙሉ ተግባር ላይ እንዳዋሉ ይናገራሉ፡፡ "በእኛ ቀበሌ የጤና ፓኬጅን የመቀበልና የመተግበር ችግር የለም፡፡ አስራ ስድስቱንም ነገሮች በመተግባር ተመርቀዋል" (ወ/ሮ ኤደን ፣ ቃመ. 24/10/2010 ዓ.ም) ይላሉ፡፡ ይሁንና መሬት ላይ ያለው እውነት የሚያሳነው ግን በስብሰባና በስልጠና ላይ ፓኬጆቹን የተቀበሉ ቢመስልም ትግበራው ላይ ገና ብዙ የሚቀር ነገር መኖሩን ነው፡፡ ወይዘሮ ኤደን[56] እና ወ/ሮ እመቤት ጌታወይ እንደሚሉት በአንዳንድ በሰሬ እና ሰላምጌ ቀበሌዎች ያሉ እናቶች ሙሉ ለሙሉ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ሆነዋል ቢባልም ሌላ ከግንዛቤ ያልገባ ባህላዊ ሁኔታ አለ፡፡ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቱ ተግባር ላይ በመዋሉ አንድ ሴት ቀድሞ በአማካይ ከምትወልደው ከስምንት እስከ ዘጠኝ ከሚደርሱ ልጆች አሁን አገልግሎቱን በመውሰዷ በአማካይ አራት ልጆችን ብቻ ትወልዳለች፡፡ ይሄ ጥሩ ሆኖ ችግሩ የሚመጣው ከላይ እንደተጠቀሰው አንድ ወንድ ሚስቱ አራት ብቻ ወልዳ ካቆመች ስለሚፈታትና ሌላ ሚስት አግብቶ ስለሚወልድ ባሏን ላለማጣት መከላከያውን መውሰድ ታቋርጣለች ፤ የልጆች ብዛትም ይጨምራል፡፡" (ወ/ሮ ሰርኬ ፣ ቃመ. ስሬ 24/10/2010 ዓ.ም)፡፡

እውነታው ይሄ ሆኖ ሳለ ባለሙያዎቹ ሁሉም ሴቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆናቸውንና ዕቅዳቸውን ማሳካታቸውን በደስታ ይናገራሉ፡፡ ሪፖርታቸውም ይሔው "ስኬት" እንደሆነ መገመት አያዳግትም ፤ የብሔረሰቡ ባህል ልብ ሳይባል ዕቅዱንና ሪፖርቱን በተገለፀው መልኩ ሲያፋልሰው ይታያል፡፡

ስለዚህ የሚፈለገውን ግብ ለማሳካት የባህሉን ሚና ዘንግቶ በደፈናው የተዘጋጀ የስኬት ሪፖርት ማቅረብ ሳይሆን ለሴቶቹ ከሚሰጠው የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ጎን ለጎን ወንዶቹም መጥነው የሚወለዱበትን መፍትሄ ከሃይማኖት አባቶችና ከብሔረሰቡ

[56] ሁለቱም በተለያዩ ቀበሌዎች ተመድበው የሚሰሩ የጤና ኤክስቴንሽ ባለሙያዎች ናቸው፡፡

አዛውንቶች ጋር ቁጭ ብሎ መመካከር ፣ አስፈላጊና በፅናት መተግበር ያለበትም ጉዳይ በመሆኑ የክልሉ መንግስት የቤት ስራ መሆን አለበት፡፡

### 6.2.3. የቅድመና ድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎት እና ተግዳሮቶች

ሌላው የጤና ኤክስቴንሽኑ ፓኬጅ እና ሀገሪቱ በሚሊኒየም ግቡ እንድታሳካው ከሚጠበቅባት ዋነኛ ጉዳዮች  አንዱ ሁሉም እናቶች የቅድመና የድህረ ወሊድ ክትትል በጤና ተቋማት እንዲደረግላቸውና ሲወልዱም በጤና ማዕከላት እንዲወልዱ ማድረግ ነው፡፡ ይህም የማንኛውም እናት ህይወት በወሊድ ምክንያት እንዳይቀጠፍና የህፃናትንም ሞት ለመቀነስ ያለመ ግብ ነው ፤ ይሁንና የዋግኽምራ እናቶች ቅድመ ወሊድ ክትትል እንዳያደርጉም ሆነ በጤና ማዕከላት እንዳይወልዱ ባህላዊ ተፅዕኖ እንዳለባቸው ይናገራሉ፡፡

> ከባሎቻችን ውጪ ገላችንን ለሌላ ሰው መግለጥ ፣ ማሳየት ነውር ነው ፤ ይህንን እናቶቻችንም ቅድመ አያቶቻችንም አላደረጉትም ፣ እኛም አናደርገውም ባሎቻችን አስፈራርተውናል፡፡ በእርግዝና ጊዜ ጤና ጣቢያ ሄደን ምርመራ እንድናደርግ ወጋችን አይፈቅድም ፤ እኛም ይህን የአባት አደር ያልሆነ ያልለመድነውን ከባህላችን ውጪ የሆነ ተግባር አንፈፅምም፡፡ ወግ ባህላችንን ስለምናከብር እና ሽማግሌዎቻችንና ባሎቻችንን ስለምንፈራ ወደዛ አንሄድም ፤ ደሞ እኮ የሚመረምሩን ሴቶች ላይሆኑ ይችላሉ ፤ እና እንዴት ለሌላ ወንድ ሰውነትን ገልጦ ይሰጣል? ማድረጉ ቀርቶ ማሰቡ በጣም ያስፈራል ፤ አባውራዎቹም ቢያውቁ ይቆጣሉ (ቡ.ተ.ዉ.ሴ ብቻ ፣ 24/10/2010 ዓ.ም)፡፡

ይህ ከላይ የተጠቀሰው ማሳያ ሴቶች ብቻ በተሳተፉበት የቡድን ውይይት ወቅት እርጉዝ ሴቶች ቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ ምርመራ ለምን ለማድረግ እንደማይፈቅዱ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ በተደረገበት ወቅት የተነሳ ነው ፤ ሴቶቹ በእርግዝና ጊዜ ሂዶ ምርመራ ማድረግና በወሊድ ጊዜም እዛው መውለድ ከሚሰጣቸው ጥቅም በላይ ነውር ሆኖ ጎልቶ የሚታያቸው ሰውነታቸውን ለሌላ ሰው ገልጠው የማሳየታቸው ጉዳይ ነው፡፡ የሴትን ሰውነት ከባሏ ውጪ ማሳየት በባህላቸው ነውር ነው፡፡ ስለዚህ እናቶቻችን ያላደረጉትን ተግባር እኛም አንከውነውም ባይ ናቸው ፤ እናቶቻቸው እነሱን ሲወልዱ ጤና ጣቢያ ባለመሄዳቸው የደረሰባቸው ጉዳት እንዳለ ማስረጃዎቻቸው ናቸው፡፡

ባህላቸውም ስለማይፈቅድ እሱን አልፈው ስርዓት ጥሰው ስንዝር ለመራመድ አይችሉም፡፡ ጥሰው ካደረጉት ግን ሽማግሌዎችና ባሎቻቸው ይቆጣሉ ፤ ይቀጣሉ፡፡ ስለዚህ የቀረው ይቀራል እንጂ ገላቸውን ገልጦ ለሌላ ለማሳየት እንዲች ብለው ወደ ጤና ጣቢያ አይሄዱም፡፡

ይህንኑ ሃሳብ ወንዶች ብቻ በተገኙበት የቡድን ውይይትም ተነስቶ ተመሳሳይ ምላሽ ከመስጠቱም በላይ ባህላዊ መከሰቻዎችም በብሔረሰቡ አስተሳሰብ ውስጥ እንዴት የሰረፁ እንደሆኑ ለማሳየት ከቡድን ውይይት ተካፋዮች አንዱ አዛውንት በተረት አስደግፈው ያቀረቡትን ሃሳብ ማየቱ ጣቃሚ ነው፡፡

> በድሮ ጊዜ ነው አሉ አንድ ሰው የሚወዳትን ሴት ልጁን ይድርና ከባሏ ጋር ይኖሩ ነበር፡፡ ሲኖሩ ሲኖሩ ሲኖሩ በባልና ሚስቱ መካከል አለመግባባት በመፈጠሩ ሚስት ባሏን ጥላ ወደ አባቷ ቤት ትመለሳለች፡፡ አባት ልጃችሁን ጥላ ለምን እንደመጣች ሲጠይት ባሏ እንዳልተስማማት እና እንደተጣሉ ፤ ከዚያም በጣም ተናዶ በጨቤ ጉያዋ ስር እንደወጋት እና እንዳሰቃያት ትናገራለች፡፡ እንዲህ አድርጎ ከሚያሰቃየኝና በጨቤ በስለት ከወጋኝ ሰው ጋር አብራ እንደማትኖርና ሁለተኛም ወደ እሱ  እንደማትመለስ ምርር ብላ እያለቀሰች ትነግረዋለች፡፡ አባት ነገሩን በሚገባ ካደመጠ በኂላ ልጂት ማምረሯንና ወደ ባሏም እንደማትመለስ በተረዳ ጊዜ ምንም አስተያየት ሳይሰጥ ተነስቶ ወደ ውጭ ወጣ ብሎ በአካባቢው የተገኙትን ሽማግዎች ፣ እናቷን ጨምረው ወደ ቤት እንዲመጡ ይልኩባዛቸዋል ፤ የልጃቸውንም ባል ባስቸኳይ እንዲመጣ ሰው ይልኩብታል፡፡፡ ከዚያም እያዘኑ እና እየተበሳጨ ይመለሱና ከልጁ ጎን ይቀመጣል ፤ ስታያቸው አባቷ ትክዝ ብሏል፡፡ ምን እንደሆነ ትጠይቀዋለች ፤ አባትም ጉያዋን በጨቤ ወጋኝ ያልሽው በጣም አሳስቦኛል ፤ እጅግም አበሳጭቶኛል ፤ ብትሞችስ ኖሮ እያልኩ ውስጤ በጣም አሯል በግኗል ብሎ ይማረራል፡፡ በዚህ ጊዜ ልጅት ነገሩን በማቃለል የአባቷን ንዴት ለማብረድ አባቴ አትበሳጭ አሁን ሠላም ነኝ ፤ መናደድ የለብህም አሁን ሁሉም አልፏል፡፡ መቼም ተመልሼ አልሄድም አንዱን አግብቼ መኖር እችላለሁ፡፡ ባል ቢሄድ ባል ይገኛል፡፡ የኔ ያለው አይጠፋ እያለች ለማፅናናት ያባቷን ንዴት ለማብረድ ትሞክራለች ፤ አባት መልሶ የተወጋሽውስ መቼም ይድናል ፤ ድፍረቱስ ንቀቱስ ውርዴት

አይደል! እያሉ ይመልሱላታል፡፡ በዚህ መሃል የተጠሩት ሽማግሌዎች እና ባሏ አብሮ ወደ ቤት ይገባሉ፡፡ አባቷም ጉዳዩን ዘርዝረው ይናገራሉ፡፡ ልጅቷም በጣቷ እየጠቆመች የተወጋችውን አካባቢ ታሳያለች፡፡ ሁሉንም ሲያዳምጡ ከነበሩት ሽማግሌዎች መካከል በነገር አዋቂነታቸው በአስታራቂነት ጥበባቸው የታወቁት አንዱ ሽማግሌ ልጄ! አሁን ይህን የተወጋሽውን ቦታ ልታሳይን ትችያሽ? መቼም እውነቱን መርምሮ አጠርቶና አይቶ ነው ሽማግሌ የሚወሰነው ፤ ይሏታል፡፡ ልጅቷም ጠደፍ ብላ አዎ! አዎ! ውሸቴን ከመሰላችሁ አሳያችኋለሁ ስትል አባቷም በይ አሳይና! ሲሏት ወዲያው እንደማፈር ብላ የባሏን ስም ጠርታ ና! ጋቢህን ጋርድልኝ ብላ የተወጋውን የውስጥ ገላዋን ወደ ባሏ ዞራ አውልቃ ለማሳየት ስትሞክር ሁሉም ሽማግሌዎች በሳቅ ፈረሱ፡፡ ልጂቱም የሳቃቸው ምክንያት ተገለጠላት ባሏም የተጋለጠውን ገላዋን ሸፈነላትና ተስማምተው ወደ ቤታቸው ሄዱ፡፡ ስለዚህ የተበደለችው ሚስት የቆሰለውን የውስጥ ገላዋን ለአባቷም እንኳ ለማሳየት ያልደፈረችው ፤ ወደ ወጋት ባሏ ነው ያሳየችው፡፡ የሚስትን ጉያ ከባሏ በስተቀር ለሌላ ማሳየት የነውር ነውር ነው፡፡ ምንድነው እናቶቻችን እኛን ሁሉ ሲወልዱ ካዋላጅ በቀር ማን ከጉያቸው ይገባ ነበር? (የቡ.ተ.ው ሰቆጣ ቀበሌ ወብቻ ፣ 24/10/2010 ዓ.ም)፡፡

ከላይ ከቀረበው ተረት የምንረዳው በዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህል ገላን ለሌላ ባዕድ ገልጦ ማሳየት ቀርቶ የመጀመሪያ ባልን ፈትቶ ሌላ ለማግባት ላለመደው ሰው ማጋለጥ እንኳ የቱን ያህል የሚያሳዝን የሚያሳፍር ጉዳይ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ እናቶች ይህን ባህላል ተራምደው ቅድመና ድህረ ወሊድ አገልግሎት ለማግኘት ወደ ጤና ማዕከላት ለመሄድ አይፈቅዱም፡፡

የብሔረሰቡ የጤና መምሪ ባለሙያ የሆኑት ኤደን ወልዱ ከ2008-2009 ዓ.ም ከነፍሰጡር እናቶች ጋር ያደረገውን የፓናል ውይይት አስመልክቶ የቀረበው ሪፖርት ይህንኑ ሁኔታ በሚገባ የሚያጠናክር ነው፡፡

የዋግኽምራ ሴቶች በወሊድ ጊዜም የሚወልዱት በጤና ተቋማት ሳይሆን በልምድ አዋላጆች እርዳታ ከቤት ውስጥ ነው፡፡ ምጥ ጠንቶ ለመውለድ አስቸጋሪ ሁኔታ ከገጠመ አዋላጇ የማህፀን ጥበት ነው ብላ ካሰበች ከተቻለ በአውራ ጣቷ ጥፍር እምቢ ካለም በተገኘው ስለት ነገር ብልቷን ቀዳ ታዋልዳለች፡፡ የተቀደደው

ብልት ቶሎ እንዲድን በማለትም የተገኘው ማንኛውም የሚያጣብቅ ሙጫ መሳይ ነገር ይደረግበታል፡፡ እንግዴ ልጅ ካስቸገረም ወላዷን በመዘቅዘቅና ስራ ስር ወቅጦ በማጠጣት እንዲወጣ ይደረጋል (ኤደን ወልዴ ፣ ቃመ. 24/10/2009 ዓ.ም)፡፡

በዋግኽምራ ብሔረሰብ ወሊድ እስካሁን ድረስ የሚከናወነው ከላይ እንደቀረበው ፍፁም ባህላዊ በሆነ መንገድ ነው፡፡ "በጤና ተቋማት ሲወልዱ እናት ጤና ልጅም ደህና" የሚለውን መርህ ለመተግበር ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ከክልሉ የእድገትና ትራነስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም ትግበራ ሪፖርትም ማረጋጥ ይቻላል፡፡ "የእናቶችና የህፃናትን ሞት ለመቀነስ ቢታቀድም በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ግማሽ ዘመን ከመቀነስ ይልቅ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሮ ተገኝቷል" (የአ.ክ.ዕ.ት.ዕ. ፣ 2006 ፣ 75)፡፡

የዋግኽምራ ባህል ለዘመናዊው የጤና አገልግሎት እምብዛም ክፍት አለመሆኑን ከቀረቡት ማሳያዎች መረዳት ይቻላል፡፡ ፎክሎራዊ ዘውጎቹ በሥነ ቃሎቹም ሳይቀር በተለያዩ መልኮች ተደጋግመው በመከሰት በብሔረሰቡ አመለካከትና ዕምነት ውስጥ እየሰረፁ በመሄድ ልማታዊ ጉዳዩን ይገዳደሩታል፡፡ ይህንን ባህላዊ ተግዳሮት "ባህልን ጎጂና የማይጠቅም አድርጎ በመውሰድና በማጣጣል ዘመናዊ የሆነውን አገልግሎት ብቻ ተጠቀሙ በማለት መቅረፍ የሚቻል አይደለም ፤ ከዚህ ይልቅ አገልግሎቱን የሚሰጡትን ሰዎች ቢቻል ከዚያው ከብሔረሰቡ የፈለቁ ሴቶች እንዲሆኑ ማድረግና የዘመናዊውን ጤና አጠባበቅ ትምህርት በዋነኞቻቸው አማካይነት (በሃይማኖት መሪዎች በዕድሜ ባለፀጎች) ለባሎችና ለትልልቅ እናቶች ጭምር እንዲሰጥ ለማድረግ የታለመውን ግብ ማሳካት ይቻላል፡፡ ባህላዊ ሁኔታዎች በማህበረሰቡ አኗኗዘር ዘዴ እና በግለሰባዊ ባህሪ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ በመሆናቸው ለባህላዊ ሁኔታዎች እና አገላለፅ ተገቢውን ክብርና ትኩረት መስጠት መደገፍ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለን ተቀባይነት በማጎልበት መግባባት ላይ ለመድረስና የሚፈለገውን ዕድገት ለማምጣት ይቻላል (UNESCO, 2004, 6) የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡

ከላይ በማስረጃ በመደገፍ ለማሳየት እንደተሞከረው የዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህል በግብርናውም በጤናውም ኤክስቴንሽን አተገባበር ላይ የሚያሳርፈው አሉታዊ ተፅዕኖ የጎላ መሆኑን ነው፡፡ ይህን ባህላዊ ተግዳሮት ደግሞ ኋላቀርና የልማት አደናቃፊ ነው በማለት ብቻ የታሰበውን ልማት በተፈለገው ፍጥነትና መጠን ማምጣት አይቻልም፡፡

የባህሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ከላይ ወደታች በሚጫኑ “እኛ እናውቅልሃለን” ገለፃዎች በቀላሉ የሚወገዱ አይደሉም፡፡ ሁሉን ዘመናዊ በማድረግም ፈፅመው ሊቃለሉ አይችሉም፡፡ ከዚያ ይልቅ የብሔረሰቡን ባህል ጠንቅቆ በማወቅና ማህበረሰቡንም በአካባቢው ልማት ላይ ተሳታፊና ተጠቃሚ በማድረግ ለውጥ ማምጣት ይቻላል፡፡ ስለሀገር ልማት ስንወያይ ለልማታዊ ዕቅዱ ተግባራዊነትም ሆነ አለመሳካት የማህበረሰቡ ባህል የሚኖረው ሚና ከፍተኛና የማይታለፍ እንደሆነ በዋግኽምራ ባህል መነሻነት ከቀረበው ከዚህ ጥናት መረዳት ይቻላል፡፡ በጥናቱ የቀረቡት ማሳያዎችም መንግሥት በማህበረሰቡ ባህል ዙሪያ ጠንክሮ ቢሰራ ምናልባት አሁን ከሚታሰበው የበለጠ የተሻለ ውጤታማ ልማት ማምጣት እንደሚቻል የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ የክልሉም መንግስት በዕቅዱ ላይ ማነቆ ናቸው ብሎ ያስቀመጣቸው ባህላዊ ተግዳሮቶች የሚፈቱት በዴሞክራሲያዊ ትግል ብቻ ሳይሆን የብሔረሰቦቹን ባህል ጠቃሚ እሴቶች መነሻ አድርጎ ለሀገረሰባዊ ዕውቀቶች ቦታ በመስጠት አሣታፊ የሆነ የልማት አካሄድ በመከተል ነው፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

# 7. ማጠቃለያና ይሁንታ

በዚህ ምዕራፍ የሚቀርቡት ከጥናቱ ዓላማዎች አኳያ የተደረሰበት ውጤት የማጠቃለያ ሃሳቦችና በዚህ ጥናት የታየውን የዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህል ከልማት ጋር ያለውን ቁርኝት በአብነት ወስዶ ባህል/ፎክሎር በልማት ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ ከግንዛቤ በማስገባት በአጠቃላይ ለክልሉ ልማት ተፈላጊውን ለውጥ ለማምጣት ወደፊት በሚመለከታቸውና በባለድርሻ አካላት ምን መደረግ ይኖርበታል የሚሉት የይሁንታ ሃሳቦች ይሰነዘራሉ፡፡

## 7.1 ማጠቃለያ

ባህል የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ፣ ዕምነት ፣ አስተሳሰብ ፣ ስለ ዓለም ያለውን አተያይ ፣ በሕይወት ውስጥ እርስ በእርስ በሚያደርገው መስተጋብር ፣ ባህላዊ እንቅስቃሴዎችና ትዕምርቶች ለማወቅ የሚያስችል የማህበረሰቡ የተጠራቀመ መዝገበ ጥበብ (Encyclopedia) ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ሁነኛ ዓላማ አንዱ ፍሬ ነገር የነበረው የዋግኽምራን ብሔረሰብ ሁለንተናዊ ገላጭ የሆኑትን ባህላዊ እሴቶች ወይም ፎክሎራዊ ዘውጎች/ማህበረ ባህላዊ መገለጫዎች የሆኑትን አለባበስና አጊያጊያጥ ፣ የምግብ አሠራርና አመጋገብ ፣ እንግዳ አቀባበል በዝርዝር ተጠንተው ቀርበዋል፡፡

የአንድን ማህበረሰብ ባህል በግልጽ ለማወቅና የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ባህላዊ መገለጫዎች ለመለየት ከሚያስችሉት ጉዳዮች መካከል የሕይወት ዑደት/ሥርዓቶች ዋነኞቹ በመሆናችው የዋግኽምራ ብሔረሰብ የጋብቻ ፣ የልደትና ሞት ሥርዓቶች ተጠንተዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የብሔረሰቡ ሀገረሰባዊ ልማዶች የሆኑት ክብረ በዓላት ፣ የአምልኮ ሥርዓቶችና ባህላዊ መድሃኒቶች በጥናቱ ተካተዋል፡፡

ስለ አንድ ብሔረሰብ ባህል ለመግለጽ የሥነቃል ሃብቶቹ የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ አያጠያይቅም፡፡ በመሆኑም የተገኙትን ያህል ሥነቃሎች ተሰብስበው በዚህ ጥናት ውስጥ ከጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

በዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህል በተደጋጋሚ እየተጋመዱ ከሚመጡት በአጠቃላይ ስለ ብሔረሰቡ ተከባብሮ ፣ ተጋግዞና ተማምኖ የመኖር ባህል እውነተኛነት ፣ ፍትሃዊነት ፣ እንግዳ ተቀባይነትና ደግነት የሚያሳዩ ፣ እርስ በእርስ ያለውን መስተጋብርና ተባባሪነት የሚያመለክቱ ፣ ማህበራዊ ህይወቱን የሚያንፀባርቁና ከሌላው ማህበረሰብ የሚለዩት በርካታ ባህላዊ እሴቶች ያሉት ብሔረሰብ እንደሆነ ከጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህም ስለዋግኽምራ አጠቃላይ ባህላዊ መልኮች ለማወቅ ይህ ጥናት የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የዋግኽምራ ባህላዊ መልኮች ስርፀታቸውን በሁሉም ባህላዊ መከሰቻዎች (features) በመዘርጋትና በመጋመድ በአንዱ ባህላዊ መልክ የታየው አንድ ሁነት በሌላው ተደጋግሞ በመምጣት የብሔረሰቡን አስተሳሰብ (thought) እና ስብዕና የገነቡና በውስጡም ሰርፀው የኖሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ባህላዊ እሴቶች በአንድ መልኩ ብሔረሰቡን አስተሳስረው ያኖሩ ፣ ለአካባቢው ልማት በአዎንታዊ ጎናቸው የሚታዩና ሊዳብሩ የሚገባቸው ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ ብሔረሰቡን ለተሻለ ህይወት እንዳይነሳሳና የአካባቢውን ልማት እንዳይፈጥን እያሰናከሉ የሚገኙ መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡

ከባህላዊ እሴቶች ውስጥ ቢያሳድጓቸውና ቢያጎለብቷቸው ጠቃሚ የልማት መሣሪያ የሚሆኑ የጋራ ትብብሮችና የአኗኗር ልማዶች ፣ መልካም አስተዳደርን ፣ ከአድሏዊ አሠራር የፀዳ ማህበረሰብን መገንባት የሚያስችሉ ሃቀኛነትና ዕውነተኛነት መሠረታቸው የሆነና ሌብነትና ማጭበርበርን የሚጠየፉ ባህላዊ መልኮች እንዳሉ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የማህበረሰብ ጤና እንክብካቤን አስመልክቶ ብሔረሰቡ ራስንና አካባቢን በንጽህና መጠበቅ በትጋት የሚፈፅመው ሁነት በመሆኑ የግልና የአካባቢ ንጽህናን ባለመጠበቅ ከሚመጡ በሽታዎች ራሱን የሚከላከልበት በውስጡ የሰረፀ አዎንታዊ ባህላዊ እሴት እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ባህላዊ እሴት ቢስፋፋ ጠቃሚ ትምህርት ሊቀሰምበትና ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ቱሩፋት እንደሆነም ታይቷል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ ለልማትና ለተሻለ ሕይወት በሚደረገው ጉዞ ላይ ጥላቸውን የሚያጠሉ አሉታዊ ባህላዊ መልኮች እንዳሉም በጥናቱ ለማየት ተችሏል፡፡ እነዚህም

የዚህ ጥናት ትኩረት በሆኑት ግብርና ኤክስቴንሽን እና የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆችን ለመፈፀም በገጠሟቸው ተግዳሮቶች የሚገለጹ ናቸው፡፡

ግብርና ኤክስቴንሽንን አስመልክቶ የልማት ዕቅዱ ዓላማ አርሶ አደሩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና ሰፊ ጊዜውን በእርሻው ላይ በማሳለፍ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ለገበያ ተፈላጊ ምርቶችን በማምረት የራሱንና የአካባቢውን ልማት በማፋጠን በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ላይ የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ማስቻል ነው፡፡ የዋግኽምራ  አርሶ አደር ግን ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚደረገውን ጉዞ የሚገዳደሩ ባህላዊ መሠረቶች አሉ፡፡

ብሔረሰቡ በባህሉ ለነገ የማይጨነቅና ኑሮዬ ይበቃኛል ብሎ መኖር የሚያስችል አመለካከት እንዲኖረው አድርጎታል፡፡ ስለዚህ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ፣ ጥሪት መቋጠር ፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ምርቶች ማምረት ፣ ምርጥ ዘርን ፣ ማዳበሪያን የመሳሰሉትን የግብርና ግብዓቶችን በብድር ወስዶ መጠቀም ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ማረስ የሚሉትን የመንግስት ተልዕኮዎች ለመፈፀም ብዙም ተነሳሽነት የለውም፡፡ በአካባቢው በስፋት የሚለሙትን የተራራ ፍራፍሬዎች ፣ የደጋ አፕልና ማንጎ በቆላማው አካባቢ ሊለሙ የሚችሉትን ሰሊጥ ፣ ኑግና የመሳሰሉትን እንኳን ከራሱ ፍጆታና ሽጦ ከመጠቀም ባለፈ በስፋት በማልማት ለትልቅ ገበያ ሲያቀርብ አይታይም፡፡

የጤና ኤክስቴንሽንን በተመለከተም አፈፃፀሙ የገጠመው ባህላዊ ተግዳሮት ብዙ እንደሆነ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የአንድ አካባቢን ማህበረሰብ አምራች ዜጋ ለማድግ በቅድሚያ ጤናው የተጠበቀ መሆን አለበት፡፡

የጤና ኤክስቴንሽኑ ካካተታቸው ፓኬጆች ውስጥ በዋግኽምራ ብሔረሰብ ተፅዕኖ ምክንያት ተፈፃሚ ያልሆኑ አሉ፡፡ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቱን ብናይ ቀድሞ አንድ ሴት በአማካይ ከሰባት እስከ ስምንት ልጆች ትውልድ የነበረውን አገልግሎቱን በመጠቀም የወሊድ መጠኑ በአማካይ ወደ አራት እንደ ወረደ ባለሙያዎች ቢናገሩም ፣ አንድ ወንድ ሚስቱ ደጋግማ የማትወልድና የተወሰኑ ሶስት ወይም አራት ወልዳ ካቆመች እሷን ፈትቶ ሌሎች ተጨማሪ ልጆችን ለመውለድ ስለሚፈልግ ሴቶቹ መከላከያ መድሃኒቱን መጠቀሙን ያቋርጣሉ፡፡ በዚህም የተነሳ እቅዱ ስኬታማ ሊሆን እንዳልቻለ ተረጋግጧል፡፡

የእናቶችና የህፃናት ሞትን ለመቀነስ ከሚደረገው ጥረት አኳያ ወላጆች በእርግዝና ጊዜ በዋግኽምራ ባህል ሴቶች ከባሎቻቸው ውጪ ሰውነታቸውን ለሌላ ሰው ማሳየት ነውር በመሆኑ ሳይሳካ መቅረቱ ተረጋግጧል፡፡ ይህ እውነታ በክልሉ መንግሥት የዕድገትና ትራንስፎሚሽን ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ሳይቀር በዋነኛ ማነቆነት የተቀመጠ በመሆኑም ችግሩ ተጨባጭ እንደሆነም ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተለይ በገጠሩ አካባቢ የሚኖሩት የዋግኽምራ ብሔረሰብ አባላት በአካባቢያቸው የሚገኙ ጠንቋዮችና የባህል መድሃኒት አዋቂዎች በሚሰጧቸው አገልግሎት የሚተማመኑ በመሆናቸው በዘመናዊ የጤና አጠባበቅ ዘዴዎች በጤና ታቋማት መገልገል እንደማያስቀድሙ በጥናቱ ታይቷል፡፡

በአጠቃላይ ከእነዚህ በዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህል ከታዩ ለልማት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ባህላዊ እሴቶች በመነሳት ባህላዊ ጉዳዮችን ሁሉ በደምሳሳው ኋላቀርና የልማት አደናቃፊ ብቻ አድርጎ ከመውሰድ ይልቅ አዎንታዊ የሆኑትን የቤሔረሰቡን ባህላዊ መልኮች አክብሮና አስፋፍቶ ለታሰበው ልማት ጥሩ መሰረትና መሳሪያ ለማድረግ መነሳት ጠቃሚነቱ የጎላ እንደሆነ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ በ“ዴሞክራሲያዊ ትግልና ቅስቀሳ” ብቻ የታሰበውን ለውጥ ማምጣት አይቻልም፡፡ ይልቁንም በማህበረሰቡ ልማድ መሰረት “በአድባራት ቦታ እና የቤተክርስትያን ቅፅር ግቢ” ውስጥ በጋራ ቁጭ ብሎ ለመልካሞቹ ባህላዊ እሴቶች ዕውቅና በመስጠትና የሚጎለብቱበትን በጋራ በመወያየት እነሱን መነሻ አድርጎ ደግሞ “ጎጂ” የተባሉትንና አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድሩትን ቀስበቀስ የሚቀርፉበትን ዘዴ በጋራ በመምከርና በመማማር ለውጥ ለማምጣት መጣር ተገቢ ዘዴ ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ ማህበረሰቡ በጋራ ተሰባስቦ በመንደር የመኖር ልምድ ያለው ስለሆነ የልማቱ ተዋናይ ለማድረግ በጣም ቀላል ነው፡፡ ለዚህ የሚያስፈልገው ብልሃት ከላይ ወደታች ከሚወርድ የልማት ዕቅድ ይልቅ ወደ ህዝቡ ቀርቦ በአካባቢው ልማት ላይ በጋራ እንዲመክር ፣ በጋራ የትብብር ልማዶቹ ተጠቅሞ ለዕለት ጉርስ ያህል ከመስራት ይልቅ የተቆራረጡ እርሻዎችን ወደ ሰፊ እርሻዎች በጋራ እንዲያለማ ፣ አካባቢውን በጋራ እንዲንከባከብ ፣ በአጠቃላይ የልማት ዕቅዱን የእኔ ነው ብሎ እንዲገዛው ማድረግ ይቻላል፡፡

ተደራሽ አልሆኑም የሚላቸውን የጤናና የትምህርት ተቋማትና መንገድ ፣ ውሃና መብራት የመሳሰሉ መሰረተ ልማቶችን ተደራሽ በማድረግና በማሟላት በቅርብ እየተገኙ በማወያየትና በማስተማር የባህሉን ጠቃሚ እሴቶችና ሀገር በቀል ዕቅቀቶችን አንጥሮ በማውጣት ባህሉን ራሱን አልምቶ አካባቢውን ለማልማት ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንደሚቻል በጥናቱ የተገኘው ውጤት ያሳያል፡፡

በመጨረሻም ባህል/ፎክሎር የአንድ ማህበረሰብ ሁለንተናዊ መልክ /feature/ በመሆኑ ባህላዊ እሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ሰፊና ስር የሰደደ መሰረት ያላቸው መልኮች ናቸው፡ ፡ በተለይ በልማት ላይ የሚያሳድሩት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚለካው በማህበረሰቡ ውስጥ ባለው የስርፀት መጠን ነው፡፡ በመሆኑም ባህል በልማት ላይ የሚያሳድረውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅእኖ ለማጥናት የሚነሳ ተመራማሪ እነዚህ ባህላዊ መልኮች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ቦታና በልማት ጉዳዮች ላይ ያላቸውን አቅም በመመርመር በልዩ ልዩ ፎክሎራዊ ዘውጎች ተደጋግመው መምጣታቸውን ፣ እርስ በእርስ እየተሸረቡም ራሳቸውን መትከላቸውን/ስር መስደዳቸውን መመርመር ሁነኛ ትኩረት መሆን ስለሚገባው ለዚህ እንዲረዳው በዚህ ጥናት የተገኘውን የባህላዊ መልኮች ተደጋጋሚነት ተመሳስሎ ላይ ጥልቅ ትኩረት ቢያደርግ ውጤታማ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 7.2. ይሁንታ /Recommendation/

ከዚህ ጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው ባህልና ልማት ያላቸው ቁርኝት የጠበቀ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ስለ ልማት ጉዳዮች ስናወሳ የባህልን ጉዳይ ወደ ጎን መተው የለብንም፡፡ ይህ ሲባል የልማቱ አካባቢ ማህበረሰብን ባህል አዎንታዊና አሉታዊ መልኮች በሚገባ ተገንዝበው ከተጠቀሙበት አጋዥ ፣ በጭፍኑ ኋታች ነው ብለው ከፈረጁ ደግሞ አደናቃፊ መልክ እንዳለው ማስተዋል ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም በልማት ጉዳዮች የሚመለከታቸው አካላት የባህልን ጉዳይ ከምር ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ የሚከተሉት የይሁንታ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡

**የፌዴራል መንግሥት**

- ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎችን ለማገዝ የታቋቋመው የፌዴራል እገዛ ቦርድ ለክልሎቹ መንግስታት ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጡ የግብርና ፣ የጤና ፣ የመስኖ

፣ የትምህርት ፣ ወዘተ ባለሙያዎችን እንደሚልከው ሁሉ ባህል ለልማት የሚኖረውን አስተዋፅኦ ተገንዝቦ የዋግኸምራ ብሔረሰብ የአካባቢው ልማት እንዲጠና እገዛ እንዲያደርጉ የባህል/ፎክሎር ባለሙያዎች ልኮ በክልሉ በኩል ቢደገፉ፡፡

- የባህል ጥናቶችና ምርምሮች ሀገሪቱ ለምትከተለው የልማት አቅጣጫ የሚኖራቸው ጉልህ አበርክቶ ግምት ውስጥ በማስገባት የብሔር ብሔረሰቦችን ባህሎች በዕውቀት እንዲጠኑና ልማቱን ለማፋጠን ለግብዓትነት እንዲያግዙ አስፈላጊውን ድጋፍ ቢያደርግ፡፡

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሚያካሂዳቸው የድህረ ምርቃ መርሃ ግብሮች በጥቅሉ ለፎክሎር መርሃ ግብር በተለይ ደግሞ በሦስተኛ ዲግሪ በመስክ ለሚሰሩ ጥናትና ምርምሮች የሚመደበው ገንዘብ በጣም አነስተኛ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ከፋይናንስ የተንዛዛ አሰራር ውጣ ውረድና አላስፈላጊ የቢሮክራሲ መንዛዛት ፣ ግልፅና አጭር የሆነ የአሰራር ስርዓት ቢበጅለት ጥናቶቹ ለሀገር ልማት የሚኖራቸውን ፋይዳ ከግምት ውስጥ አስገብቶ ተገቢውን ገንዘብ ቢመድብ፡፡
- በሀገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦች ባህሎች ላይ የሚሰሩ ጥናቶች ለሚታሰበው ልማት የሚኖራቸውን አስተሰዋፅኦ ከግምት ውስጥ አስገብቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተባብሮ ከዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር አቅጣጫው ጋር በማስገባት ከጥቅም ላይ የሚውሉበትን መንገድ ቢያመቻች፡፡
- በድህረ ምርቃ መርሃ ግብር በባህል/ፎክሎር ዙሪያ ለሚደረጉ ምርምሮች ጠቃሚነታቸውን በውል ተገንዝቦ ለሌሎች ጥናቶችም የሚተርፉ በመሆኑ ተደራጅተው የሚቀመጡበት ስፍራ እንዲያገኙ ተገቢውን ትኩረት ቢሰጥ፡፡

## ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

- ባህል ለልማት የሚኖረውን ሚና ተረድቶ የብሔርና ብሔረሰቦች ባህል የሚጠናበትን መንገድ ትኩረት ሰጥቶት ቢሰራ ፣ የባህል ጥናቶቹም ትኩረት ባህላዊ እሴቶችን በሰነድ ላይ ብቻ ከመሆን ባለፈ ለሀገሪቱ ልማት ከሚኖራቸው አስተዋፅኦ አንፃር እንዲሆኑ ቢያደርግ፡፡

- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና በሌሎች ከፍተኛ ተቋማት በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ብሔር ብሔረሰቦች ባህል ላይ የተደረጉ ጥናቶች ከመፃህፍት መደርደሪያ ናሙናነት ተላቀው ለህዝብ በመድረስ ለባህላዊ ኢንዱስትሪው ልማት የግብዓትነት ሚና እንዲኖራቸው ብርቱ ጥረት ቢፈጠር፡፡
- የባህል ባለሙያዎችን ክህሎት ለማዳበር በአቅም ግንባታ ስራዎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ቢሰራ፡፡
- የየብሔሩና ብሔረሰቡ ባህላዊ ሀብቶችና ፀጋዎች በወጉ ከተጠኑና ከተስፋፉ የባህል ኢንዱስትሪዎችን በማሳደግ ሰፊ የስራ ዕድልን የሚፈጥሩትን ለሃገር ኢኮኖሚም ከፍተኛ የገቢ ምንጭ የሚያስገኙ በመሆናቸው ከቱሪዝም ልማቱ ባላነሰ መልኩ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚለሙበት መንገድ ቢፈለግ፡፡

**የክልሉ መንግስት**

- የክልሉን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጨምሮ ለሚነድፋቸው የልማት ዕቅዶች ተፈፃሚነት በክልሉ ያሉ ብሔረሰቦች ባህል የሚኖረውን ጉልህ ድርሻ ከግንዛቤ በማስገባት የብሔረሰቦቹ ባህሎች በዕውቀት እንዲጠኑ እገዛና ድጋፍ ቢያደርግ፡፡
- የየብሔረሰቡ ባህላዊ እሴቶች የባህልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ለማስፋፋትና ሰፊ የስራ እድልን ለመፍጠርም ስለሚያግዙ ለክልሉ ልማት የሚኖራቸውን ጉልህ አስተዋፅኦ ከግምት ውስጥ በማስገባት በዋግኽምራ ብሔረሰብ ባህል ውስጥ የተለመዱትን በባህላዊ መንገድ የሚሰሩ የዕደ ጥበብ ውጤቶች የጌጣጌጥ እና ስፌት ስራዎች ፣ መዋቢያና ቅባቶች ፣ የብረታ ብረት ውጤቶችና የቆዳ ስራ ጌጣጌጦች ፣ የብራና ስራዎች ፣ ወዘተ ከአነስተኛ የጎጆ ኢንዱስትሪዎች ተነስተው የሚያድጉበትና የሚስፋፉበትን መንገድ ቢፈለግ፡፡
- በዋግኽምራ ብሔረሰብ የተለመዱት የዘመዳሞችና ጎረቤቶች የጋራ ትብብደሮች የህብረት ስራዎችን ቁጠባና ብድር ተቋሞችን ዓላማ በብሔረሰቡ ውስጥ ለማስለመድና ለማስረፅ ጥሩ መሰረቶች በመሆናቸው በጎ ጎናቸውን በማበረታታት የአካባቢውን ልማት ለማፋጠን ቢጠቀሙባቸው፡፡

- ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ ያሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች አስፈላጊውን በጀትና ሙያተኛ ተመድቦላቸው ግብርና ፣ ጤናና ትምህርትን ከመሰሉ ተቋማት ጋር በቅንጅት የልማቱን ስራ የሚሰሩበትን ሁኔታ ቢያመቻች፡፡
- ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ ያሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ውስጥ የሚመደቡ ባለሙያዎች በባህል ልማት ዙሪያ ተገቢው ክህሎት እንዲኖራቸው በአቅም ግንባታ ስራዎች የሚታገዙበትን ሁኔታ ትኩረት ሰጥቶ ቢሰራ፡፡

## ፖሊሲ አውጪዎች

- ባህል በልማት ላይ የሚሳድረውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅእኖ ከጅምሩ በመረዳት የሚወጡ የልማት ፖሊሲዎች ፣ ዕቅዶችና ስትራቴጂዎች ባህላዊ ሁኔታዎችን ያገናዘቡ እንዲሆን ቢያደርጉ፡፡
- የባህል ፣ የግብርና ፣ የጤና እና የትምህርት ፣ ወዘተ ዘርፎች በቅንጅትና በመደጋገፍ የሚሰሩበት ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና ዕቅዶች በወጥነት የሚተባበሩበት አቅጣጫ ቢነድፍ፡፡
- የሚወጡ የልማት ፖሊሲዎች ከሚተገበሩባቸው አካባቢዎች ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚስማሙበትን መንገድ ቢፈለግ፡፡

## የዋግኽምራ ብሔረሰብ/ህዝብ

- የብሔረሰቡ መገለጫ በመሆን እስከ ዛሬ ድረስ አብረው ያኖሩትን ተባብሮ ፣ ተረዳድቶና ተማምኖ አብሮ የመኖር ፣ ዕውነተኝነት ፣ ፍትሃዊነት ፣ ለጋስነት እና ሌሎችም ማህበራዊ ሕይወቱን ፣ ባህላዊ እሴቶቹንና አካባቢውን በጋራ አልምቶ በጋራ ተጠቃሚ ለመሆን የሚኖራቸውን አዎንታዊ ሚና ተገንዝቦ ለልማቱ ውጤታማ ለመሆን እንዲውሉ ቢያደርጋቸው፡፡
- እርስ በርስ ተከባብሮና ተማምኖ በመኖር ግጭትን አስወግዶ በሰላም ለመኖር የሚከውኗቸው ባህላዊ ጉዳዮች ለአካባቢው ልማት አስፈላጊ የሆኑ መሰረታዊ ባህላዊ እሴቶች ናቸው ጠብቆ ቢያቆያቸው፡፡
- ጥሪት አለማቋጠር ፣ ለነገ አለማሳብና ምርትና ምርታማነትን አለማሳደግ የመሳሰሉትን ባህላዊ ገፅታዎች አብዝቶ ከመውሰድ ጋር ተያይዞ የተሻለ ሕይወት እንዳይኖረው አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩበት በመረዳት ካለው የስራ ትጋት

ጋር በማያያዝ አካባቢውን ለመለወጥ የሚቻልበትን መንገድ በጋራ ተወያይቶ ቢፈልግ፡፡

- ጤና አጠባበቅን አስመልክቶ የግልና የአካባቢን ንፅህና በመጠበቅ ረገድ ያሉት ባህላዊ እሴቶች ጠቃሚነታቸው የጎላና በአዎንታዊ ሚናቸው የሚጠቀሱ በመሆናቸው ቢያጎለብታቸው፡፡ እንዲሁም በጤና ተቋማት ለመገልገል አለመነሳሳትና አለመፈለግ የመሳሰሉትን ልማዶች በጋራ መክሮ የሚሻሻሉበትን መንገድ ቢፈልግ፡፡

## ዋቢ ሰነዶች


ማህተመስላሴ ወ/መስቀል፡፡ (19610፡፡ ባለን እንወቅበት፡፡ የኢትዮጵያ ባህል ጥናት፡፡ አዲስ አበባ ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ስንቅነሽ አጣለ፡፡ (2007 ዓ.ም)፡፡ **"ባህልና ልማት በበርታ ብሔረሰብ"** (ፒኤች ዲ ማሚያ) አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፣ የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር፡፡

ሽፈራሁ በቀለ ፣ (2004 ዓ.ም)፡፡ **ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፡፡** አዲስ አበባ ፣ ፎረም ፎር ሶሻልስ ስተዲስ፡፡

ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ፡፡ (1951 ዓ/ም)፡፡ **የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ-አክሱም ዛጉዬ እስከ ዓፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግስት፡፡** አዲስ አበባ ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

ታደሰ እሸቱ፡፡ (1997 ዓ./ም )፡፡ **"የሰቆጣና አካባቢዋ የርሃብ ግጥሞች"** ፣ (ቢ.ኤ ድማፅ) በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት፡፡

ታየ ገ/ማርያም ፡፡ (1951 ዓ/ም)፡፡ **የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፡፡** አዲስ አበባ ፣ ሴንትራል ማተሚያ ቤት፡፡

ኃይለ ገብርኤል ዳኜ፡፡ (2007 ዓ.ም)፡፡ **ባህልና ትምህርት በኢትዮጵያ፡፡** አዲስ አበባ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

አሉላ ፓንክረስትና ገብሬ ይንቲሶ፡፡ (2004)፡፡ ሀገራዊ ዕውቀትና ተዛማጅ ቴክኖሎጂ "በኢትዮጵያ፣ ባህልና ልማት በኢትዮጵያ" ፣ 77-95)፡፡

አላምረው ገብረሕይወት፡፡ (1986 ዓ/ም)፡፡ **"የዋግ ታሪክ በአጭሩ" ፣ ለለ ፣ ቅፅ** 1 ፣ ቁጥር 1 ፣ 11-161986 ዓ/ም፡፡

አያሌው ሲሳይ፡፡ (2007 ዓ/ም)፡፡ **የአገው ሕዝቦችና የዛግዌ ስርወ መንግስት ታሪክ፡፡** አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አፀደ ተፈራ። (1996 ዓ/ም)። **"በሰቆጣ ከተማ የክብረ በዓላት አከባበርን ባህላዊ ጨዋታዎች"** (ኤም. ኤ ዲግሪ)። በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

አፀደ ተፈራ። (1989 ዓ/ም)። **"የዋግ ታሪክ ቅኝታዊ ጥናት"** ፣ ለዋግኽምራ መስተዳድር ዞን ማስታወቂያ መምሪያ የቀረበ፣ ያልታተመ።

ከበደ ሚካኤል። (1964 ዓ.ም)። ጃፓን እንደምን ሰለጠነች። አዲስ አበባ።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። (1948 ዓ.ም)። መጽሀፈ ሰዋሰው ወግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ ።

ክቡር ገና። (2004 ዓ.ም)። "የሙስና ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳቱ" ባህልና ልማት በኢትዮጵያ። አዲስ አበባ፣ ፎረም ፎር ሶሺያል ስተዲስ።

ዋግኽምራ ዞን ገንዘብና ዞን ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ። (2002 ዓ/ም)። **"የ2001 በጀት ዓመት ዓመታዊ ስታትስቲካወኪ መፅሔት"**።

የአማራ ክልል ማስታወቂያ ቢሮ። (2001 ዓ.ም )። **"የአማራ ክልል ብሔር ብሔረሰቦች"** ፣ ባህር ዳር፣ ጎህ ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል። (1994 ዓ.ም)። **ክብረ ነገሥት** ፣ አዲስ አበባ ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

የራስወርቅ አድማሴ። (2004 ዓ.ም)። "ባህልና ልማት ምንነታቸውና ትስስራቸው።" **ባህልና ልማት በኢትዮጵያ** ፣ 1-25።

የማስታወቂያ ሚኒስቴር የፕሬስና ኦዲዮቪዢዋል መምሪያ። (1964 ዓ.ም) ። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች። አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ።

የወጣቶችና ባህል ሚኒስቴር። (1995 ዓ.ም)። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የባህል ፖሊሲ። አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ። (2006)። አማርኛ መዝገበ ቃላ። አ.አ.ዩ ፣ አ.አ.

የኢፌዲሪ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር። (1995 ዓ.ም)። የቤተሰብ ጤና አጠባበቅ ኤክስቴንሽን ፓኬጅ። አዲስ አበባ ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ያሬድ ተፈራ። (2002 ዓ.ም)። **"በሰቆጣና በአበርገሌ ገጠራማ ወረዳዎች የሴቶች እና የወንዶች አለባበስና የአጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች"** (ኤምኤ ዲግሪ ማሟያ) በቋንቋዎች ጥናት ተቋም በኢትዮጵያ ሥነፅሑፍ እና ፎክሎር።

ፈቃደ አዘዘ። (2004 ዓ.ም)። የስነቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፣ቦሌ ማተሚያ ድርጅት ፣ 1991 ዓ.ም። ። ቁዘማ፡-ፎክሎር (ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ። ባህልና ልማት በኢትዮጵያ ፣ 97-136።

Academy for Educational Developmente. (no time). Adiss Abeba: United Printers.

Adinew, Abtew. (2011)። "Poletical and Socio- Economic History of Asossa Warada, 1941 -1991", MA Thesis in History, School of Graduate Studies, Addis Ababa University.

Applleyard, D.L. (1988). "The Agaw Languages: A Comparative Morphological Perspective" Proceeding of Eighth International Conference of Ethiopian Studies. (Taddese Beyne ed.), Vol.I .581-592.

Barnard, Alan. (2004). **History and Theory in Anthropology**. Cambridge University Press, the Pitt Building, Trumpington Street, Cambridge, United Kingdom.

Bascon, willam, R. (1954). "Four functions of folklore": **The Journal of American Folklore.** American folklore society, Vol.67, No. 266, 333-349,

Ben-Amos, Dan. (1975). "**Folkolore in African Society"** Research in African litratures, Indiana University press, Vol. 6 No. 2, pp. 165-198

Bahru, Zewde. (2002). A History of Modern Ethiopia 1855-1974. Addis Ababa: Addis Ababa University Press.

Bascom, William R. (1965). "Four functions of Folklore" Alan Dundes. (edt). The Study of Folklore. Engle Wood Cliffs: N.J Prentice. 298- 305.

Bauman, Richard & Briggs L.Charles. (1990). ‘‘Poetics and Performance as critical perspectiveves on language and Social Life” Annual Rev. Anthropology, 59-88. Retrieved from: anthro.vancouver.wsu.edu

Blumenkrantz, DG., & Goldstein, MB. (2010). Rites of Passage as a Framework for Community interventions with youth. Global Journal of Community Psychology Practice, 1(2), 41-50. Retrieved from: www.gjcpp.org

Bloor, Michael, Jane Frankland, Michelle Thomas &Kate Robson. (2001). **Focus Groups in Social Research Sage.** Publications Ltd, 6 Bonhill Street, London EC2A 4PU.

Bronner, Simon J. (2007). **The Meaning of Folklore**: *The analytical essays of Alan Dandes.* Utah: Utah State University Press

Carlsson, Fredrik, Gunnar Köhlin, Alemu Mekonnen, & Mahmud Yesuf. (2005). **Are Agricultural Extension Packages What Ethiopian Farmers Want? A Stated reference Analysis.** Working Papers in Economics no.172, Department of Economics, Göteborg University.

Cox James L. (1998). Rites of Passage in contemporary Africa: Interaction between Christian and African traditional religion. Cardiff: Cardiff Academic Press.

Daniel, Kasomo. (2009). “An analysis of the Rites of Passage and their relation to Christianity.” International Journal of Sociology and Anthropology. 1(8).156-166. Retrieved from: www.academicjournals.org

Dawson, Catherine. (2002). Practical Research Methods A user friendly guide to mastering Research Techniques and projects. Trowbridge, Wiltshire & Cromwell Press.

Dundes, Alan. (2004). “Foklorstics in the Twenty First Century’’. Journal of American Folklore 118 (470).385-408.

_____. (2007). “From Etic to Emic units in the Structural Study of Folktales”. In The Meaning of Folklore: The Analytical Essays of Alan Dundes (Edited and Introdu ced by Simon J.Bronner). Logan, Utah: Utah University Press. 88-100.

______. (2007). “Structuralism and Folklore” The meanining of Folklore: The Analytitical Essays of Alan Dundes (Edited and Introduced by Simon J.Bro nner) Logan, Utah:Utah university Press.145-153.

Federal Demicratic Republic of Ethiopia Population Census Commission, Central statistics Agency. (2010).

The 2007 Population and Housing Census of Ethiopia Results for Amhara region part I: Statistical Report on Population size and characterstics. Addis Ababa: Brana printing Enterprize.

Finnegan, Ruth. (1977). Oral poetry: Its nature, significance and social context. London, New York, Melbornc: Cambrige University Press.

______. (1984). Oral Literature in Africa. Nairobi: Oxford University Press. Galaty, G, John. (1983) “Ceremony and Society: The Poetics of Maasai Ritual” in Man new Series, 18( 2) . 361-382. Retrieved from: www.siue.edu/

Gamst, Frederick. (1968). The Qemant Agaw of Ethiopia: A study in culture Change of Pagan-Hebraic people. Ph.d thesis in Anthropology. The University of California.

Gardener, Katy and David Lewis. (1996). **Anthropology, Development and Post-modern Challenge.** London, Pluto Press.

Gebre, Iniiso, (2005). Culture and Development in Africa: building on positive cultural practices Addis Ababa UNFPA and Africa Union.

Geertz, Clifford. (1973). **The Interpretation of Cultures.** New York: Basic Books, Inc, Publishers.

Gomm, Roger. (2008). Social Research Method of Critical Introduction (2nded.) Great Britain: Palygrove Macmillan.

Gottlieb, Alma. (2006). “Ethnography: Theory and Methodes” in A Hand book for Social Science Field Research: Essays and Bibiligraphic sources on research Designand Methods.by Perecman Ellen and Sara R. Curran (eds.). London: Sage Publication Inc. Retrieved from: www.sagepub.com

Goldstein, Kenneth S. (1974). A Guide for Field Workers in Folklore. Detroite: Gale Research Company.

Green, A. Thomas. (1997). FOLKLORE**.** *An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art* Santa Barbara, California: ABC-CLIO, Inc.

Hegland, Mary Elaine. (2003.) “Shi'a Women's Rituals in Northwest Pakistan: The Shortcomings and Significance of Resistance.” Anthropological Quarterly, 76(3). 4 11-442. Retrieved from: books.google.co.uk.

Hill, Jeff & Peggy, Daniels. (2008). Life Events and Rites of Passage: The Customs and Symbols of Major LifCycle Milestones, Including Cultural, Secular and Religious Traditions Observed in the united States.U.S.A: Omnigraphics Inc. Retrieved from: books.google.com

Jabbour, Alan. (2004). Interacultural and Intercultural: The Two faces of Folklore.In Folklore, Public Sphere and Civil Society. (Ed. M. D. Muthukumaraswamy and M olly 302 Kausal.New Delhi: IND COM.Press.17-22.

Kahn, Herman. (1993). **The Confucian Ethic and Economic growth**. In Mitchell A. Seligs on and Johan T. Passe-Smith, eds, Development and Underdevelopment: The Poltical Economy of Inequality, Boulder: Lynne Rienne.

Landes, David. (2001) “Culture Makes Almost All the Difference”. Culture Maters. Basic Books, Perseus Boos Group.2000. Lewandowski, Joseph D. **Interpreting Culture.** *Rethinking method and truth in social theory.* Lincoln and London: University of Nebraska Press. 2001.

Jansen, Hugh W.M. (1983). “Ethics and the Folklorists” Hand Book of American Folklore. Richard Dorson (ed.) Bloomington: Indiana University Press. 52-56

Keesing, M.Roger & Andrew J. Strathern. (1998). Cultural Anthropology: A Contempor ary Perspective 3rd ed. Fortworth: Harcourt Brace College Publishers.

Kifle, Wodajo, (2002). “Wedding Customs among the Amhara” in Alula Pankhurest (ed.) Ethnological Society Bulletin. I(II),27-29.

Kurtz, Donald V. (2001). Political Anthropology Paradigms and Power. USA: West view Press. Retrieved from: ink.springer.com

Laneri, Nicola. (2008). Performing Death: Social Analysis of Funerary Traditons in the ancient near east and Mediterranean.U.S.A:The University of Chicago. Retrieved from: https://oi.uchicago.edu

Leach, Maria. (1950). Standard Dictionary of Folklore Mythology, and Legend Vol. II. NewYork: New York Publisher.

Levine, Donald N. (2000). Greater Ethiopia:The Evolution of A Multiethnic Society. Chicago and London: the University of Chicago Press.

Lipsky, George A. (1962). Ethiopians: Its people, its society, its culture. New Haven: HRAF Press.

Malefijt, De Waal Annemarie. (1968). Religion and culture, an introduction to Anthropology of religion. London: Collier-acmillan Limited. Retrieved from: archive.org

McCann, James. (1987). From poverty to Famine in Northeast Ethiopia: A Rural History 1900-1935. Pluladelphia: University of Pennsylvania Press.

Mcleod Julie and Rachel Thomson, (2010). Researching Social Change.Los angeles/ London/New Delhi: SAGE Publication Ltd.

Murchison, Julian M. (2010). Ethnography Essentials Designing, Conducting, and

Presenting Your Research.U.S.A: John Wiley and Sons, Inc Retrieved from: www.wiley.com

O' Reilly, Karen. (2005.) Ethnographic Methods. London and New York: T. J, International Ltd.

Oringu, Elliot. (1976). "Three functions of Folklore: Traditional functionalism as Explanation Foklorstics" Journal of American Folklore. 89 (35).67-80

Ojameruaye, Emmanuel. (2005). Culture and Economic Development in Urhoboland. Unpublished paper, 6th Annual Convention & meeting of the Urhoboland Society at PTI, Warri. Nigerya, October 20-23, 2005.

Pathfinder International Ethiopia. (2008). **The Ethiopian Health Extension Program**. Ethiopia's Health Extension Program: Pathfinder International's Support 2003 - 2007.

Pink, Sarah. (2007). Doing visual Ethnography 2nded.London: Sage Publications.

Punch, F.Keith. (2000). Developing Effective Research Proposals. London: SAGE Publication Ltd. Retrieved from: www.uk.sagepub.com

Randall, Collins. (1988). Sociology of Marriage and the Family: Gender, Love, and Property 2nded. U.S.A: Nelson-Hall Inc. Retrieved from: www.scribd.com

Rappaport, A.Roy. (1999). Ritual and Religion in the making of humanity. Cambrige:Cambrige University Press.

Sergew Hable Sellassie. (1972). Ancient and Medieval Ethiopia.Addis Ababa: United Printers.

Svoboda Cynthia J. W. (2010) "Festivals and Rituals" Birx James .H.(ed.) 21st Century Anthropology A Reference Hand book.V.I and II.London: Sag Publication Inc.773-781.Retrieved from: knowledge.sagepub.com

Sims, Martha C. & Martine Stephens. (2005). Living Folklore: An introduction to the Study of people and their traditions. Logan, Utah: Utah University Press.

Spradley, p, James. (1980). Participant observation. USA: Holt, Reinehart and Winston. www.uk.sagepub.com

Schoemaker, George H. (1990). **The Emergence of Folklore in Everyday Life.** *A Field Guide and Source Book.* Bloomington, Indiana:Trickster Press.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. (2005). **Living Folklore**: An Introduction to the Study of People and Their Traditions, Utah: Utah State University Press. 2005.

Spielman, J. David, Dawit Kelemwork, and Dawit Alemu. (2011). **Seed, Fertilizer, and Agricultural Extension in Ethiopia,** International Food Policy Research Institute, Development Strategy and Governance Division,- Ethiopia Strategy Support Program II, Ethiopia.

Storey, John. (2009). **Cultural Theory and Popular Culture an Introduction.** Fifth edition University of Sunderland.

Schech, Susanne and Jane Haggis. (200). **Culture and Development**: *A Critical Introduction*, USA, Blackwell Publishing.

Taddesse, Tamrat. (1972). Church and State in Ethiopia.1270-1527.Oxford: the Clarendon Press.

**______**.1988. “Process of Ethnic Interaction in Ethiopian History: the case of the Agaw” The journal of African History. (29).1, 5-18.

**_______**. (2002). “The Mateb’’ Alula Pankhurest (ed.). Etnological Society Bulletin 1953 -1961.No.9.354-358.

Thomson, S. B. (2011). “Qualitative Research: Validity.” JOAAG, 6 (1). 77- 82 Retrieved from: joaag.com

**The 2009 UNESCO Framework for Cultural Statistics (FCS),** UNESCO Institute for Statistics, 2009. **The Power of Culture for Development,** 2010. **Culture: a driver and an enabler of sustainable development. 2012**

UNESCO. (2005). **Convention on the Protection and Promotion of the Diversity of Cultural Expressions.** Paris.

Vaughn, Lisa M. (2010). “Marriage and the Family” in H. Jamese Birx (ed) 21st Anthropology a Reference handbook vol. 1 and 2. Los Angeles/London: Sage Publication inc.pp162-173. Retrieved from: www.sage-ereference.com

Wilson, Wiliam, A. (1989). “Documenting Folklore”, in Elliott Oring, (ed.) Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction. Logan, Utah: Utah State University Press. 225- 254.

Wudu Tafete Kassu. (1998). “The Two Wagshums and the Battle,” Adwa Victory Centenary Conference 26 February-2 March 221-235.

Weber, Max. (1930). **The Protestant Ethic and the Spirit of Capitalism.** Oxford Universiy Press, New York, 1930.

Yin, K.Robert. (2003). Case study Research design and methods 3rd ed. London: Sage Publications Inc. Retrieved from: www.amazon.co.uk

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

### ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | የመረጃ ሰጪው ስም | ቦታ | ፆታ | ዕድሜ | ቃለ መጠይቅ የተደረገበት ቀን | ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ወ/ሮ ሙቀት ወንዴ | ደሃና | ሴ | 44 | 25/09/10 | የቤት እመቤት/የልምድ አዋላጅ |
| 2. | አቶ ደርበው ታረቀኝ | ሰቆጣ ከተማ | ወ | 65 | 19/09/09 | የመንግስት ሰራተኛ እና የብሔረሰብን ባህል አዋቂ |
| 3. | አባ አሸብር አለሜ | ደሃና | ወ | 80 | 12/09/10 | የቆዳና የብራና መጽሐፍ |
| 4. | አቶ እሸቱ አበራ በየነ | 1014 አቅም ሰቆጣ | ወ | 70 | 24/10/10 | አርሶ አደር/የሀገር ሽማግሌ |
| 5. | መሪጌታ ሰሎሞን ደስታ | ሰቆጣ ቀበሌ 02 | ወ | 65 | 20/10/10 | የባህል መድሃኒት አዋቂ መስተፋቅር የመንፈስ በሽታ ሲያም |
| 6. | ወ/ሮ አለም ወርቅ ጌታሁን | ሰቆጣ (02) ቀ | ሴ | 75 | 20/10/10 | የባህል መድሃኒት አዋቂ (ቁስል ሲወጣ) |
| 7. | አቶ ደሳለኝ ታደሰ | ሰቆጣ (02)ቀ | ወ | 50 | 20/10/10 | የባህል መድሃት አዋቂ የመንፈስ (ውቃቢ) |
| 8. | አቶ አበበ ያለው | ሰቆጣ | ወ | 55 | 18/08/10 | አንጥረኛ/ጌጣጌጥ ሰሪ የብረት ሠራተኛ |
| 9. | ወ/ሮ ማን ጠግቦሽ ደሳለኝ | አልቆዙ ዝቋላ ወረዳ | ሴ | 65 | 22/10/09 | የሸክላ ስራ ባለሙያ ምጣድ፣ ድስት |
| 10. | ቄስ ግርማይ በየነ | ሳቆጣ ወረዳ | ወ | 66 | 20/10/10 | ዓይነጥላ የሚያወጣ ባህላዊ ህክምና |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 11. | ወ/ሮ ባዩሽ መንግስቴ | ሰቆጣ | ሴ | 55 | 20/10/10 | ዓይን ሲያም መድሃኒት የሚሰጡና ቆሻሻ የሚያወጣ |
| 12. | አቶ ተፈሪ ስለፈ | ስቋላ ወረዳ | ወ | 45 | 07/10/09 | ባህላዊ ተጫዋች/የማሲንቆ ባለሙያ |
| 13. | አቶ ሞገስ ገ/ኪዳን | ሰቆጣ 01 ቀበሌ | ወ | 50 | 08/10/09 | የብረት ሠራተኛ |
| 14. | አቶ ተቀባ አሸብር | ደሃና | ወ | 50 | 22/02/10 | ባህላዊ/የአካባቢውን ባህል የሚያውቅ |
| 15. | ወ/ሮ ታምር አሰፋ | ደሃና | ሴ | 65 | 16/10/10 | የቤት እመቤት፣ ባህል አዋቂ የሰፊ ባለሙያ |
| 16. | አቶ ጥጋቡ ምርቴ | ደሃና | ወ | 70 | 20/09/10 | አርሶ አደር |
| 17. | አቶ ስሬ ታደግ | ደሃና | ወ | 65 | 26/09/10 | አርሶ አደር |
| 18. | ወ/ሮ አልማዝ አትክልፈቲ | ደሃና | ሴ | 41 | 26/09/10 | የቤት እመቤት |
| 19. | ወ/ሮ መለሱ ጌታሁን | ደሃና | ሴ | 50 | 20/09/10 | የቤት እመቤት፣በሠርግ ያገዙ |
| 20. | ወ/ሮ አለምነሽ በላይ | ሰቆጣ | ሴ | 75 | 22/10/10 | የባህሉ አዋቂ የቤት እመቤት |
| 21. | ወ/ሮ ተወዳጅ ገ/ኪዳን | ሰቆጣ | ሴ | 70 | 21/10/09 | ቤት እመቤት |
| 22. | ወ/ሮ መሰረት አጠና | ሰቆጣ | ሴ | 60 | 20/06/10 | የቤት እመቤትና አዋቂ |
| 23. | ወ/ሮ ሙሉ አበራ | ሰቆጣ | ሴ | 50 | 20/06/10 | የቤት እመቤት |
| 24. | አቶ ብርሃነ መስቀል ይርጋ | ሰቆጣ | ወ | 50 | 23/08/10 | አርሶ አደር |
| 25. | አቶ ተፈራ አስማረ | ጋዚገብለ | ወ | 68 | 20/10/10 | የመ/ሰራተኛ የትምህርት ባለሙያ |
| 26. | መ/ት ወርቃፈራሁ ቸኮል | ሰቆጣ(ስሬ | ሴ | 40 | 21/10/09 | የመ/ሠራተኛ መ/ር |
| 27. | አቶ አበባው ኃይሉ | ሰቆጣ አቅም | ወ | 42 | 09/10/09 | መ/ር/የመ/ሠራተኛ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 28. | አቶ መስፍን ሲሳይ | ሰቆጣ/ከተማ | ወ | 60 | 09/10/09 | ከተማ/ነዋሪ |
| 29. | አቶ ብርሃኑ አወቀ | ሰቆጣ/ከተማ | ወ | 85 | 03/06/11 | ውሃ የቆዳ |
| 30. | አቶ ቸኮል ካሳው | ሰቆጣ/ከተማ | ወ | 75 | 08/10/11 | ቀን ሰራተኛ |
| 31. | አቶ ኃዲሽ ሞገስ | ሰቆጣ ወረዳ | ወ | 50 | 08/10/11 | ርዕስ መ/ር ስራ |
| 32. | አቶ መለስ ታረቀ | ሰቆጣ ወረዳ | ወ | 45 | 10/10/10 | ርዕስ መ/ር ስራ |
| 33. | አቶ አስራት ታደሰ | ሰቆጣ | ወ | 62 | 12/10/09 | የመ/ሠራተኛ |
| 34. | አቶ መርሃ ፅድቅ | ሰቆጣ ወረዳ | ወ | 50 | 12/10/09 | የት/ቤቶች ሱፐርቫይዘር |
| 35. | አቶ አበበ ተስፋዬ | ሰቆጣ ወረዳ | ወ | 40 | 28/10/10 | የጤና መኮንን |
| 36. | መ/ር ወንድምሰን ጌታሁን | ሰቆጣ | ወ | 50 | 28/06/10 | የከፍ/ድ/ር/ወ/ር |
| 37. | ወ/ሮ ጌጤ ደሱ | ሰቆጣ | ሴ | 35 | 10/10/10 | የቤት እመቤት |
| 38. | አቶ በላይ መንገሻ | ዝቋላ | ወ | 60 | 20/10/10 | የመ/ሠራተኛ |
| 39. | ወ/ሮ ህዳጋ መስፍን | ዝቋላ | ሴ | 60 | 16/10/10 | የቤት እመቤት |
| 40. | ወ/ሮ ወርቂ ቸኮል | ዝቋላ | ሴ | 45 | 25/10/10 | የመ/ሠራተኛ መ/ር |
| 41. | አቶ አምዴ ተክሉ | ዝቋላ | ወ | 75 | 20/06/10 | አርሶ አደር |
| 42. | ቄስ ፈምሴ መኮንን | ዝቋላ | ወ | 72 | 28/06/10 | የቤ/አገልጋዩን |
| 43. | ሀብታም አስማረ | ዛረብላ | ሴ | 45 | 20/08/10 | ገበሬ |
| 44. | አቶ ተፈራ አስማረ | ዛረብላ | ወ | 40 | 20/08/10 | ወረዳ ስራ አስኪያጅ |
| 45. | አቶ በለጠ ሽፈራው | ዝቋላ | ወ | 65 | | የወረዳ ት/ባለሙያ |

## ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ወረዳው ስም | ዓይነት | ሴት | ወንድ | ጠቅላላ ብዛት | ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሰቆጣ ዙሪያ ወረዳ | ሴቶች ብቻ የባህል መድሃኒቶች የባህል ዘፈን መሪዎች ተረት የሚተርቱ፣ የእጅ ሙያ ባለሙያዎች ፀጉር ሰሪዎች | 7 | - | 7 | 08/10/10 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2. | ሰቆጣ ከተማ አስተዳደር | ወንድ አባላት ብቻ ያሉት ተዋቂ ግለሰቦች አባቶች፣ የእጅ ሙያተኞች የተሣተፉበት ባለውቃቢዎች | - | 7 | 7 | 08/10/10 |
| 3. | ደሃና ወረዳ | አገር ሽማግሌዎች ፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች/ሴቶችና የባህል መድሃኒት አዋቂዎች የወበራ ስራ አስተባባሪዎች የልዩ ልዩ ጌጣጌጥ ሠራተኞች የትካተቱበት | 2 | 5 | 7 | 26/09/10 |
| 4. | ዝቋላ | የባህል ሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋቾች ተረት የሚነግሩ/ነጋሪዎች በባህላዊ ሥርዓት ላይ ማ/ቡን የሚሰሩና የሚያስተባብሩ የታወቁ ሰዎች የተካተቱበት | 2 | 5 | 7 | 23/08/10 |
| 5. | አበርሌ | የአገር ሽማግሌዎች ፣ ባህላዊ ወጌሻዎች ፣ የግብርና ባሙያዎች መምህራን ፣ የልምድ አዋቂዎች | 2 | 5 | 7 | 10/08/10 |
| 6. | ጋዝጊብላ | እጅ ሙያተኞች ፣ አዛውንትና ወጣቶች ባህሉን የሚያውቁ የታወቁ ሰዎች | 2 | 5 | 7 | 29/10/10 |
| 7. | ስሃላ ሰዬምት | የግብርና ባሙያ እና የባህል መድሃኒት አዋቂ | 1 | 2 | 3 | 30/10/10 |
| 8. | | ድምር | 16 | 29 | 45 | |

## የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም | ፆታ | ዕድሜ | ሥራ/መተዳደሪያ | ቀበሌ | ወረዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ ታፈረ ስለፋ | ወ | 45 | ባህላዊ ማሲንቆ ተጫዋች/አዝ | ሰቆጣሚ/ኤል | ዝቋማ |
| 2. | አቶ እሸቱ አበራ በየነ | ወ | 70 | አርሶ አደር | አቅም/14 | ሰቆጣ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዙሪያው ን |
| 3. | መሪጌታ ሰለሞን ደስታ | ወ | 65 | መምህር | 02 | ሳቆጣ |
| 4. | አቶ ደሳለኝ ታደሰ | ወ | 50 | መድሃኒተኛ | ሰሬ | ሰቆጣ ዙሪያ |
| 5. | አቶ ሞገስ ገ/ኪዳን | ወ | 50 | አንጥረኛ/ብረት ሠራተኛ | ሰቆ.01 | ሰቆጣ አስ/ |
| 6. | ወ/ሮ ሙቀት ወንዴ | ሴ | 44 | ባህላዊ የልምድ አዋላጅ | አምደወርቅ | ዳሃና |
| 7. | ቄስ ደምሴ መኮንን | ወ | 72 | የቤተክርስቲያን አገልጋይ ገበሬ | ፅፅቅ | ዝቋላ |
| 8. | ወ/ሮ ታምር አሰፋ | ሴ | 65 | የቤት እመቤት፣ የስፌት ባሙያ | ሲልዳ | ዳሃና |
| 9. | አቶ ተፈራ አስማረ | ወ | 40 | የወረዳ ስራ አስኪያጅ | አስ ከተማ | ግዝጊብ ላ |
| 10. | ወ/ሮ በለጡ ገላው | ሴ | 55 | የቤት እመቤት | ማይግንዶ | ሰቆጣ ዙሪያ |
| 11. | ወ/ሮ ኤደን ወልዱ | ሴ | 36 | የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ | 014 | ሰቆጣ ከ/አስ |
| 12. | ወ/ሮ ማንጠግቦሽ ደሳለኝ | ሴ | 65 | የባህል መዳኒት አዋቂና ባለወቃቢ | ኒራቅ | አበርገሌ |
| 13. | አቶ ተቀባ አሸብር | ወ | 50 | የባህል አዋቂና ገበሬ | አምደወር | ደሃና |
| 14. | ወ/ሮ ህዳጋ መስፍን | ሴ | 60 | የቤት እመቤትነዛ ፀጉር ሰሪ | ፅፅቅ | ዝቋላ |
| 15. | አቶ ዝናው ጠምተው | ወ | 58 | የባህል አዋቂና አስታራቂ | አስ | ጋዝጊብ ላ |
| 16. | አቶ በለጠ ሽፈራው | ወ | 45 | አርሶ አደር | ፅፅቅ | ዝቋላ |
| 17. | አባ/ቄስ አሸብር አለሜ | ወ | 80 | የብራና መጽሐፍ አዘጋጅ | ሲልዳ | ዳሃና |
| 18. | ወ/ሮ ታንጉት ሽበሽ | ሴ | 35 | የቤት እመቤትና መዳኒተኛ | ሰቆፃ | ሰቆጣ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዙርያ |
| 19. | ወ/ሮ እመቤት ጌታወይ | ሴ | 36 | የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ | ሲሬል | ሰቆጣ ዙሪያ ወረዳ |
| 20. | መቶ አለቃ ወዳጄ አባሪ | ወ | 60 | የአካባቢ አስታራቂ ሽማግሌ | ሰቆፃ | ሰቆጣ አስ/ |
| 21. | ወ/ሮ ጠጇ አለሙ | ሴ | 58 | የቤት እመቤት መዳኒተኛ | ሲሬል | ሰቆጣ ዙሪያ |
| 22. | አቶ አበበ ያለው | ወ | 55 | የጌጣጌጥና የብረት ሰራተኛ | ዳግብጃ | ሰቆጣ ዙሪያ |
| 23. | ወ/ሮ መለሱ ጌታሁን | ሴ | 50 | የቤት እመቤት የሰረግ ፀጉር ሰሪ | ሲልዳ | ዳሃና |
| 24. | ወ/ሮ ማንጠግቦሽ አየለ | ሴ | 65 | የሸክላ ስራ ባለሙያ | ፅፅቅ | ዝቋላ |
| 25. | ወ/ሮ ባዩሽ መንግስቴ | ሴ | 55 | የቤት እመቤትና የባህል መዳኒት አዋቂ | 1.02 | ሰቆጣ ከ/አስ |
| 26. | ቄስ ካሴ አስረስ | ወ | 60 | አርሶ አደርና የቤ/ክ/አገልጋይ | አባሊባስ | ሰቆጣ ዙሪያ |
| 27. | አቶ ሲሳይ ይሄይስ | ወ | 55 | አርሶ አደር | ዘንዚራ/4 | ሰቆጣ ሩዚያ |
| 28. | አቶ ደሳለኝ አማረ | ወ | 52 | የመንግስት ሰራተኛ | ቋራአቦ | ሰቆጣ ዙሪያ |
| 29. | አቶ ተበጀ በላይ | ወ | 50 | የመንግስት ሰራተኛ | ቋራአቦ | ሰቆጣ ዙደሪያ |
| 30. | ወ/ሮ መለሱ ጌታሁን | ሴ | 54 | የቤት እመቤትና የልምድ አዋላጅ | ማይግንዶ | ሰቆጣ ዙሪያ |
| 31. | ወ/ሮ አደነቁሽ ግዛት | ሴ | 30 | የመንግስት ሰራተኛ | ማይግንዶ | ሰቆጣ ከ/አስ |
| 32. | ወ/ሮ ሙሉወርቅ | ሴ | 48 | የመንግስት ሰራተኛ | ሴሬል | ሰ/ዙሪያ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አወጣ | | | | | |
| 33. | አቶ አምባው አለማየሁ | ወ | 56 | አርሶ አደር | ፅፅቅ | ዝቋላ |
| 34. | ወ/ሮ ደስታ አሰፋ | ሴ | 58 | የባህል ዘፈን አቀንቃኝና ባለውቃቢ | ቃለአምባ | ሰቆጣ አ/አስ |
| 35. | ቄስ አለሙ ወረታ | ወ | 60 | አስታራቂ አባትና አርሶ አደር | ሴሬል ሊባስ | ሰቆጣ ዙሪያ |
| 36. | አቶ ካሤ ሹምየ | ወ | 65 | አርሶ አደር | ኣስ | ጋዝጊብ ላ |
| 37. | አቶ አምደ ተክሉ | ወ | 65 | አርሶ አደር አስታራቂ | ሰቆጣ ሚ/ኬ | ዝቋላ |
| 38. | አቶ ግርማይ አግዴ | ወ | 50 | የቆዳ ባለሙያ | አቅም | ሰቆ ከ/አስ |
| 39. | አቶ ጥጋቡ ምረቴ | ወ | 56 | አገር ሽማግሌና የባህል አዋቂ | አምደወርቅ | ዳሃና |
| 40. | አቶ ወ/ማርያም እሸቱ | ወ | 75 | ግብርና/ገበሬ/ ባለሙያ | አስ | ጋዝጊብ ላ |
| 41. | አቶ አዳነ ግርማይ | ወ | 65 | የቅል ስራ/ጌጣጌጥ ባለሙያ | ኒራቅ | አበርገሌ |
| 42. | አቶ አበባው ኃይሉ | ወ | 43 | የመ/ሠራተኛ | 01 | ሰቆጣ ከ/አስ |